# ሀዲስ አለማየሁ

## ትዝታ



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ትዝታ

ከ

ሀዲስ አለማየሁ

፲፱፻፴፰ ዓ.ም

# ማውጫ


መቅድም .......... 5
የወልወል ግጭት .......... 7
ቅድመ - ዝግጅት .......... 17
ዝግጅት .......... 26
ምዕራፍ .......... 41
የዘመቻው ጉዞ .......... 41
ደባት .......... 46
ደባጉና .......... 55
ተከዜ .......... 67
ከደባጉና እስከ እንዳስላሴ .......... 74
የሰለከላካ ጦርነት .......... 81
ሽሽት .......... 90
ሌላ ዘመቻ .......... 108
ከደባርቅ እስከ ሱዳን .......... 112
ሱዳን የቆዬንበት ጊዜ .......... 129
ከካርቱም እስከ ጎሬ .......... 147
ጎሬ .......... 156
ከጎሬ እስከ (ጎይ?) .......... 167
ከጉይ እስከ ጉማ .......... 178
ጌራ .......... 188
ጎጅብ .......... 198
ቦንጋ .......... 212
አዲስ አበባ .......... 219
ካዲስ አበባ እስከ ፓንዛ .......... 229

ፓንዛ ........................................ 242
ሊፓሪ ........................................ 250
ሎንጎቡኮ ........................................ 258
ነፃነት ........................................ 275

# ሰው ቢሞት ፍቅር አይሞትም!!

ይህ ትንሽ መፅሐፍ ፋሽስት ኢጣልያ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት በተነሳችብን ጊዜ ለመከላከል ስንወጣ አብረውኝ ወጥተው አብረውኝ ሳይመለሱ በጦርነቱ፥ ወድቀው ለቀሩት ወንድሞቼ ለዘሪሁን ወጋየሁና ገላው ተገኝ መታሰቢያና እነሱ በሞት፥ ቢለዩኝም እኔ በህይወት እስካለሁ ድረስ ፍቅራቸው አብሮኝ የሚኖር መሆኑን የምገልፅበት ነው።

**ደራሲው።**

# መቅድም

በዚህ ትዝታ ብዬ በሰየምኩት ትንሽ መፅሀፍ የተፃፈው ሁሉ እውነተኛ ታሪክ ነው። መፅሀፉን «ታሪክ » በማለት ፈንታ ትዝታ ብዬ የሰየምሁት «ታሪክ » ለመባል የሚጎድሉት ነገሮች ስላሉ ነው። እኒያን «ይጎድላሉ » የተባሉትን ነገሮችና የጎደሉበትን ምክንያት በሚከተሉት መስመሮች እገልፃለሁ።

በ1928 የፋሽስት ኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን መውረሩ እንደ ታወቀ በሙሉ ኢትዮጵያጵያ የጦርነት አዋጅ ሲታወጅ በዚያ ጊዜ የጎጃም እንደራሲ የነበሩት (ሁዋላ ልኡል) ራስ እምሩም የጎጃምንጦር አስከትተው በዚያ ላይ በደጃዝማች አያሌው ብሩ ይመራ የነበረውን የሰሜንን ጦር ጨምረው ትግራይ ውስጥ «የሽሬ ግምባር » በመባል ወደ ታወቀው የጦር ግንባር ዘመቱ። ከዚያ እዚያው ሽሬ በመባል ወደ ታወቀው የጦር ግንባር ዘመቱ። ከዚያ፥ እዚያው ሽሬ ውስጥ «ሰለክለካ » በተባለው ቦታ ላይ ከጠላት ጋር ዋናውን ጦርነት ገጥመው ድል ከሆኑ በሁዋላ ተመልሰው በምእራብ ኢትዮጵያ በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው፥ በጅማና በከፋ ውስጥ ጎጀብ በሚባለው ወንዝ ላይ ተያዙ። ታዲያ እኔ፥ ሽሬ ግንባር ጦርነትም በምእራቡ ያርበኝነት ትግልም አብሬያቸው ስለ ነበርሁ በየቀኑ የተደረገውንና የሆነውን ሁሉ እየተከታተልሁ ዝርዝር ማስታወሻ እይዝ ነበር። ነገር ግን እኛ ከጎጃም ሽሬ እስክደርስ የያዝሁት ዝርዝር ማስታወሻ እዚያው ሽሬ ውስጥ ደባጐና ከተባለው ኢጣልያኖች መሽገው ተቀምጠውበት ከነበረው ቦታ አጠገብ ጠላት ሰፈራችንን ባይሮፕላን በደበደበበት ጊዜ ድንኩዋኔና በውስጡ የነበረው ሁሉ በቦምብ ሲቃጠል አብሮ ተቃጠለ። 2ኛ - ያ የመጀመሪያው ማስታወሻዬ ከተቃጠለ በሁዋላ እንደ ገና የፃፍሁት ማስታወሻ ደግሞ፥ በምእራብ ኢትዮጵያ ካርበኝነቱ ትግል በሁዋላ እኔ ከራስ ጋር ተይዤ ወደ ጣሊያን አገር እስር ቤት ስወሰድ ለዘመዶቼ እንዲያደርስልኝ የሰጠሁት ሰው ሳያደርስልኝ እንደያዘው ወደ አርበኝነቱ ተመልሶ እዚያ ሲሞት አብሮት ጠፋ። እንግዲህ ከዚያ ሁሉ የተረፈኝ ከራሴው ውስጥ ሳይጠፉ ቆይቶ ከብዙ በጥቂቱ የማስታውሰው ወይም ትዝ የሚለኝ ብቻ ነው። ቢሆንም ያው የማስታውሰው በጊዜ በቦታና በሰው ስም እንዲሁም

ባንዳንድ ዝርዝር ነገር በኩል የተሙዋላ ስላልሆነ «ራሱን የቻለ ሙሉ ታሪክ » ባይባልም «የጦርነቱን ሙሉ ታሪክ የሚፅፉ ሰዎች አንዳንድ የሚፈልጉዋቸውን ነገሮች ያገኙበት ይሆናል » ብዬ ተስፋ በማድረግ እኔ ሳልፍ ያውም ጥቂቱ ጠፍቶ እንዳይቀር ትዝታ የሚል ስም ሰጥቼ ሳሳትመው አሰብሁ።

ከመጽሀፉ የመጀመሪያው ምዕራፍ ለጦርነቱ መነሳት ምክንያት ስለ ሆነው ስለ ወልወል ግጭት ባጭሩ የሚልፅ በማስረጃ የተደገፈ ታሪክ ነው። ከታሪክነቱም ሌላ፤ ኢጣሊያ ወሰን አልፋ ኢትዮጵያ ውስጥ ወልወል ላይ ጦርነት አድርጋ ብዙ ኢትዮጵያውያንን በመፍጀትዋ የኢትጵያ መንግስት ለአለም መንግሥታት ማህበር አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ ማህበሩ ከህግና ከፖለቲካ ማናቸውን እንደሚመርጥ መወሰን አቅትቶ አስር ወራት ሙሉ ሲያመንታ ከኖረ በኋላ የተረፈው ላይቀር - ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር እንዳይተባበር የሚያሳይ ነው። ኢትዮጵያን መስዋዕት አድርጎ ማቅረቡን የሚያሳይ ነው። ባጠቃላይ «የአለም መንግሥታት ማህበር » የሚባለው ሀያላን መንግስታት ወደዬግባቸው ለመድረስ የፖለቲካ ጨዋታቸውን የሚጫወቱበት ሜዳ መሆኑንና «አለም አቀፋዊ ህግ » የሚባለውም እንደ ብሄራዊ ህግ ስልጣን ላላቸው ሀይለኞች የፖለቲካ መሳሪያ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በዚህ ትንሽ መፅሐፍ ስለ ጦርነቱ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በሁዋላ እስከ 1936 ሰባት አመታት ያህል ጣሊያን አገር በግዞት ስለቆየንበትም ትዝ የሚለኝን ፅፌያለሁ። በጣም የማዝነው ቀደም ብዬ እንደገለፅሁት የፃፍሁት ማስታወሻ በመጥፋቱና መፅሀፉን የፃፍሁት የጦርነቱም የግዞቱም ጊዜ ካርባ አመታት በላይ ካለፈ በሁዋላ በመሆኑ የብዙ ጀግኖችን ስምና ስራቸን በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ቦታ ሰጥቺኤ ከተከታታይ ትውልዶች ጋር ለማስተዋወቅ ሳልችል ስለ ቀረሁ ነው።

## ምዕራፍ አንድ

# የወልወል ግጭት

ኢጣሊያ በ1888 አድዋ ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገችው ጦነት ድል ከተመታች በሁዋላ እንደገና ኢትዮጵያን ወግታ ድል ለመቀዳጀትና ያድዋን ቂም ለመበቀል፣ ከዚያም ወደ አይነተኛ ግብዋ ለመድረስ ማለትም ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛትዋ ለማድረግ ፅኑ ፍላጎት የነበራት መሆኑ ለፖለቲካ ተመልካች ሁሉ ስውር አልነበረም። ይህ ፅኑ ፍላጎትዋ ፋሽስቶች መንግስቱን ስልጣን ከመያዛቸው በፊት የነበረና እነሱም ስልጣን ከያዙ በሁዋላ የቀጠለ ነበር። ቀደም ብላ፥ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች ካሠራጨቻቸው ሚሲዮኖችዋ ሌላ፥ የንግድ፣ የባህል፥ ወይም ኢትዮጵያንና ኢጣልያን የሚያገናኙ ጉዳዮች ቅንስላዎችዋን አቁዋቁማ በነሱ አማካይነት መኳንንቱም የቤተ ክርስቲያንን አለቆችም በገንዘብና በመሳሪያ ስጦታ እንዲሁም በሹመት ተስፋ እያባባለች ለረዥም ጊዜ አላማዋ እንዲረድዋት አጥብቃ ስትሰራ የኖረች ለመሆንዋ ጦርነቱ በተነሳ ጊዜ ያባበለቻቸው ሁሉ ባይሆኑም ከነሱ መሀከል ብዙ አገራቸውን እየከዱ ለስዋ ይገቡ መኖራቸው ምስክር ነው።

ይልቁንም፥ በኢትዮጵያ ሰሜንና ደቡብ (በኤርትራና በሱማሌ) በንግድ ኩባንዮችዋ አማካይነት ትንንሽ ቦታዎች ከያዘችበት ጊዜ ጀምራ እስከ ወልወል ግጭት ድረስ ስታደርገው የኖረችው ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛትዋ ማድረግ የረዥም ጊዜ አላማዋ የነበረ ለመሆኑ ሌላው አይነተኛ ምስክር ነው።

በሰሜን «ሩባቲኖ » በተባለው ኩባንያዋ ስም ከያዘችው ከአሰብ ተነስታ አንዳንድ መንግስቶች በተለይ የእንግሊዝ መንግስት ረድተዋት ምፅዋን ከያዘች በሁዋላ በ«ዶጋሊና በሰሀጢ » እንዳደረገችው በጦርነት ሳይሳካላት ሲቀር በማባበልና በማታለል ቀስ እያለች፥ ኤርትራን በሙሉ ያዘች። በደቡብም እንዲሁ ከዛንዚባር ሱልጣንና ከእግሊዝ መንግስት ጋር ተስማምታ የ«በናዲር ኩባንያ » በተባለ ኩባንያዋ ስም በህንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ለጠረፍ «በናዲር » የሚባለውን የሱማሌ ክፍል ያዘች። ከዚያ ለከብቶቻቸውም

ለግመሎቻቸውም ሳርና ውሀ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ አጋዴን የሚዘምቱትን የሱማሌ ዘላኖች አስቀድማ ሁዋል ሁዋላ እየተከተለች የበናዲርን ወሰን አልፋ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እነ «ሉ - ፋርንዲን » እና ባካባቢው ያሉትን ሌሎች ቦታዎች መያዝዋ ታወቀ። ስለዚህ አፄ ምኒልክ ምንም እንኳ ለአውሮፓ መንግስታት መላልሰው ከፃፉት እንደሚታየው የኢትዮጵያ ወሰን ባህር መሆኑን ቢያምኑም ያን የማያቋርጥ ግፊትዋን ለመግታት የወሰን ስምምነት ለማድረግ በመገደዳቸው ካድዋ ጦርነት በሁዋላ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1897 በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መንግስቶች መሀከል አንድ የወሰን ስምምነት ተደረገ። ያ ወሰን በደቡብ ምእራብ ከጁባ ወንዝ «ባርደራ » ከሚባል ስፍራ አጠገብ ተነስቶ ቀጥታ መስመር እየተከተለ ሄዶ ሰሜን ምስራቅ ሲደርስ የእንግሊዝንና የጣሊያንን ሱማሌዎች ከሚለየው ወሰን ጋር የሚገናኝ ነበር።

«የ1897 ስምምነት » የሚባለው እንደ ሌሎች ስምምነቶች በዝርዝር ተፅፎ የተፈረመ አልነበረም። አንድ የጀርመን ሰው በሰራው «የሀበኒከት ካርታ » በመባል በታወቀ የጂዎግራፊ ካርታ ላይ አፄ ምኒልክ ከጁባ ወንዝ የእንግሊዝና የጣሊያን ሱማሌዎች እስከሚገኙበት ወሰን ድረስ በቀይ ቀለም አስምረው ማህተማቸውን አትመው የ«ሻለቃ ኔራስኒ » ለተባለ የጣሊያን መንግስት እንደራሴ የሰጡት ቀጥ ያለ መስመርና ያን የወሰን መስመር የጣሊያን መንግስት የተቀበለው መሆኑን ያስታወቀበት ቴሌግራም ባንድነት ተጣምረው ነው።

ከ11 ዓመት በሁዋላ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1908 በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መንግሥቶች መሀከል አዲስ የወሰን ስምምነት ተፈረመ። አዲሱ ስምምነት በደቡብ ምእራብ በኩል በ1897 ስምምነት የጣሊያን ሱማሌ የሰሜን ወሰን የሆነውን «ባርደራን » ወደ ደቡብ ትቶ ወደ ሰሜን እስከ «ዶሎ » ይደርስና ከዚያ ወደ ምስራቅ ሄዶ ዋቢሸበሌ ላይ ከ1897 መስመር ጋር ይገናኛል። ይህ የ1908 ስምምነት በጁባና በዋቢሸበሌ መሀከል ያለውን ሰፊና ለም አገር ሁሉ «ባይዳዋ » የሚባለውን የርሻ አገር ጭምር ለኢጣሊያን አገር ሱማሌ የሚሰጥ ነበር። ያንጊዜ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩት

ሲኞር ትቶኒ «ባዲሱ ስምምነት ኢጣሊያ ያገኘችው አገር 50.000 ኪሎ ሜትር ወይም ከሲሲሊ ከሁለት ጊዜ የሚበልጥ ነው » ብለው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የካቲት 13 1908 ለፓርላሜንት መናገራቸው ስምምነቱ ለጊዜው ጣሊያኖችን ደስ አሰኝቶዋቸው የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ያሰኛቸው ወደ አይነተኛ ግባቸው ለመድረስ አንድ ትልቅ እርምጃ በመሆኑ ወንጂ የሱማሌ ግዛታቸው የሚያሰፋ በመሆኑ ብቻ አልነበረም። አይነተኛ ግባቸው ኢትዮጵያን በጦርነት ድል መትቶ ቅኝ ግዛት ማድረግ አለ ነበረ በስምምነት ያገኙትን እጅ ካደረጉ በሁዋላ ከዚያ ተነስተው ወደ ፊት መግፋታቸውን ቀጠሉ። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1987 የኢትዮጵያ መንግስት ከኢጣሊያ መንግስት ጋር እንዳደረገው ከእንግሊዝ መንግስት ጋርም በኢትዮጵያ ኦጋዴንና በእንግሊዝ ሱማሌ መሀከል ስላለው ወሰን ስምምነት አድርጎ ነበር። በዚያ ስምምነት መሰረት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በህዳር ወር 1934 የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መንግስቶች የወሰኑን መስመር እየተከተለ በመሬት ላይ ምልክቶችን የሚያደርግ የጋራ የወሰን ኮሚሽን ሾሙ። የኮሚሽኑ አባላት መሪዎች በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ደጃዝማች ተሰማ ባንቴ፣ በእንግሊዝ መንግስት በኩል ኮሎኔል ክሊፎርድ ነበሩ።

ኮሚሽኑ የወሰን ምልክቶችን ካደረገ በሁዋላ እንደ ስምምነቱ የእንግሊዝ ሱማሌ ጎሳዎች በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ ኦጋዴን እየገቡ ግጦሽ የሚያግጡባቸውንና ውሀ የሚያጠጡባቸውን ቦታዎች እየዞሩ ሲያዩ ወልወልን ባንድ «ሻምበል ሮቤርቶ ችመሩታ » የተበለ መኮንን የሚመራ የባንዳ ጦር ተይዞ አገኙት። የባንዳው ጦር ምሽግ መሽጎ፥ ከምሽጉ አጠገብ በከፍተኛ ቦታ ላይ የኢጣሊያ ሰንደቅ አላማ ተሰቅሎ ነበር። ለወሰኑ ኮሚሽን ጠባቂ የነበሩት የጅጅጋው አገረ ገዥ ፊታውራሪ ሽፈራው ባልቻና ምክትላቸው ግራዝማች አፈወርቅ ከጦራቸው ጋር ቀድመው ወልወል ደርሰው ከጣሊኢያን የባንዳ ጦር ጋር እንደ ተፋጠጡ ኮሚሽኑ ደረሰ።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ህሩይ በጊዜው ለነአብረው የአለም መንግስታት ማህበር እንዳስታወቁት ወልወል በ1987 እና በ1908 ከተፈረሙት የወሰን ክልል ስምምነቶች 60 ኪሎ ሜትር ኢትዮጵያ

ኦጋዴን ውስጥ ገብቶ የሚገኝ ቦታ ነው ያውም አፄ ምኒልክ በ«ሀበኒክት » ካርታ ላይ በቀይ አስምረው ማህተማቸውን አትመው ለጣሊያን መንግስት የላኩትና የጣሊያን መንግስትም የተቀበለው መሆኑን በቴሌግራም ያስታወቀው የወሰን መስመር በዚያን ጊዜ ብላቴን ጌታ ህሩይ ጠፍቶባቸው ይሆናል እንጂ ወልወል ስምምነት ከተደረገበት ወሰን 60 ኪሎ ሜትር ብቻ ሳይሆን 130 ኪሎ ሜትር ያህል ኢትዮጵያ ኦጋዴን ውስጥ ገብቶ የሚገኝ ቦታ ነው። እንዲህ መሆኑን ለማረጋገጥ ከስምምነቱ በሁዋላ የኢጣሊያ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ያወጣውን «ኦፊሻል » ካርታ ‹ካሮሴሊ› የተበለ ኢጣሊያዊ ፀሀፊ ባሳተሙት «FERROE FUOCO In SOMALIA (ሰይፍና እሳት በሶማሌ) ከተባለ መፅሀፍ ማየት ይቻላል።

የፊታውራሪ ሽፈራው ጦር ከኢጣሊያ የባንዳ ጦር ተፋጦ እንዳለና ኮሚሽኑ ባጠገቡ እንደ ሰፈረ የባንዳው መሪ ሻምበል ችመሩታ የኮሚሽኑንና የጠባቂውን ጦር ወልወል መድረስ ሞካዲሾ ለሱማሌ አገረ ገዥ ‹ለማውሪስዮ ራቫ› (MAURIZIORAVA) አስታውቆ አገረ ገዡ አይሮፕላኖች ስለ ላከበት እኒያ አይሮፕላኖች የኮሚሽኑ አባሎችና ጠባቂያቸው ጦር የሰፈሩበትን ቦታ እየዞሩ ያስፈራሩ ጀመር።

የኮሚሽኑ መሪዎች ደጃዝማች ተሰማና ኮሎኔል ክሊፎርድ ወልወል ከደረሱ ጀምሮ ያዩት ሁሉ ከማሳዘን አልፎ ስላስገረማቸው፥ የኢጣሊያን መንግስ ጦር በኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ መመሸጉና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ለስራ የተላኩትን የኢትዮጵያና የእንግሊዝ የወሰን ኮሚሽን አባሎች በአይሮፕላን ማስፈራራቱ ህገ ወጥና የእብሪት ስራ መሆኑን ለሻምበል ችመሩታ ፃፉለት። ነገር ግን የሻምበሉ መልስ ካይሮፕላኖች ሌላ ተጨማሪ ጦር ከታንኮችና መድፎች ጋር ማመጣት ሆነ። ከዚያ በሁዋላ የጣሊያን ባንዳ አለቃም ሆነ ያገረ ገዡ አድርጎት ሁሉ ጠብ ለመጫር የተነሱ መሆናቸውን የሚያመለክት ስለ ነበረ የኮሚሽኑ መሪዎች የማይቀረው የሚቀር መሎዋቸው - ነገሩ አደገኛ ሁኔታ ላይ ሳይደርስ በመንግስት ደረጃ ንግግር ተደርጎበት እንዲወሰን ለማመልከት ከወልወል ተነስተው «አዶ » ወደ ሚባለው ቦታ ለመሄድ ወሰኑ።

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ የጋራ ኮሚሽን አባሎች ከጠባቂው ጦር ጥቂት አስከትለው የቀረውን እዚያው እንዲጠብቅ ትተው ወደ አዶ መሄዳቸውን ሻምበል ችመሩታ እንዳወቀ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 5 1934 በ9:30 ላይ ያይሮፕላን የታንክ የመድፍና የሌላም የልዩ ልዩ መሳሪያውን ሀይል አስተአብብሮ እዚያ በቀረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ ስለ ጣለ መራራ ጦርነት ተደረገ። የኢትጵያ ጦር የጋራ ኮሚሽኑን ለመጠበቅ እንጂ እንዲያ ላለ ከባድ ጦርነት የተሰናዳ ባይሆንም ብዙዎች አገር የሚያኮራ የጅግንነት ስራ ሰርተው እዚያው ወደቁ።

የወልወል ግጭጥ አዲስ አበባ እንደ ታወቀ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴ በጊዜው የጣሊያን ጉዳይ ፈፃሚ የነበሩትን «ስኞር ሞምቤሊን » ጠርተው የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ብቶ ያላንዳች ምክንያት የወሰን ኮሚሽንን እንዲጠብቅ በታዘዘው የኢትዮጵያ ዘብ ላይ ጦርነት አንስቶ ብዙ ሰው በመፍጀት የመንግስታቸውን ፅኑ ሀዘን በቃል ካስታወቁ በሁዋላ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1928 በሁለቱ መንግስታት መሀከል በተፈረመው የወዳጅነትና የሽምግልና ስምምነት መሰረት ግዳዩ፥ በሽምግልና (Arbitration) እንዲታይ የፃፉትን ለመንግስታቸው እንዲያስተላልፉ ሰጡዋቸው። ሮም በነበሩ የኢትዮጵያ መንግስት እንደራሲ በኩልም ተመሳሳይ ጥያቄ ለጣሊያን መንግስት ቀረበ። ነገር ግን ለጣሊያን መንግስት የወልወል ግጭት ኢትዮጵያን ወግቶ ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ላቀደው የረዥም ጊዜ እቅዱ በር ከፋች ወይም የመጀመሪያ እርምጃ እንጂ ድንገተኛ አደጋ አለመሆኑን በስኞር ሞምቤሊ በኩል የተሰጠው መልስ ደህና አድርጎ ያሳያል።

መልሱ ባጭሩ፡-

«1ኛ፡- በሀረሩ ገዥ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ወልወል ምሽግ ድረስ ሄደው በኢትዮጵያ መንግስት ስም የጣሊያንን ጦር አዛዥ ይቅርታ እንዲለምኑ፥

«2ኛ፡- በጦርነቱ ምክንያት ከጣሊያን የባንዳ ጦር ውስጥ ለሞቱትም ለቆሰሉትም ካሳና ለፈረሰው ምሽግ ዋጋ፥ የኢትዮጵያ መንግስት 200.000

ጠገራ ብር አዲስ አበባ ባለው የጣሊያን ለጋሲዮን በኩል ለጣሊያን መንግስት እንዲከፍል፥

«3ኛ፡- ለደረሰው አደጋ ሀላፊዎች የሆኑት የኢትዮጵያ የጦር መኩዋንንት ከወታደሮቻቸው ጋር ለጣሊያን ሰንደቅ አላማ የክብር ሰላምታ ከሰጡ በሁዋላ በፍጥነት ተይዘው ማእረጋቸውን እንዲገፈፉና እንዳገሩ ልማድ ተቀጥተው እንዲታሰሩ » የሚል ነበር።

እንዲያ ያለ እብሪትና ንቀት ደራርቦ የተሸከመ ጥያቄ ሊውጡት የማይቻል መራራ ከመሆኑ ሌላ «በድሎ ካሱኝ ሾህ ይዞ እጄን ዳስሱኝ ለነገር ነው » እንደሚሉት የጣሊያን መንግስት ለነገር የታጠቀ መሆኑን በመረዳት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 14 1934 የኢትዮጵያ መንግስት በሱና በኢጣሊያ መንግስት መሀከል የተፈጠረውን አስጊ ሁኔታ በዝርዝር ገልፆ ለአለም መንግስታት ማህበር ዋና ፀሀፊ አስታወቀ። ከዚያ እንደ ገና በዚያው ወር 24 1934 ኢጣሊኢያ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወልወልን ከያዘች በሁዋላ ደግሞ «አፍደብን » «አዶን » እና «ጌርሎጐቢን » መያዝዋን ለዋናው ፀሀፊ አስታወቀ። ኢጣሊያም ወልወልም ሆነ ሌሎች የተቆጠሩት ቦታዎች በግዛትዋ ውስጥ መሆናቸውንና ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ አለመግባትዋን ገልፃ መልስ ሰጠች።

እንደ አውሮፓ አቆጣጥገር ትር 3 1935 የኢትዮጵያ መንግስት የአለም መንግስታት ማህበር (League of Nations) በተቋቋመበት ቃል ኪዳን (Covenant) መሰረት በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከ የተፈጠረውን አስጊ ሁኔታ ማህበሩ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄ አቀረበ። ከዚያው ወር 17 1935 ማህበሩ በጉዳዩ ለመነጋገር ወስኖ አጀንዳው ፃፈው። ነገር ግን የኢጣሊያ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ሊያደርገው ላሰበው ጠቅላላ ጦርነት በቂ ዝግጅት ለማድረግ ጊዜ እንዲያገኝ አንድ ጊዜ «ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በቀጥታ የተጀመረው ንግግር ስላላለቀ ወደ ሽምግልና የመተላለፉ ጊዜ አልደረሰም » ሲል፥ ሌላ ጊዜ «ኢጣሊያና ኢትዮጵያ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1928 የፈረሙት የወዳጅነትና የሽምግልና ስምምነት መሰረት ልዩነታቸውን

ራሳቸው ተስማምተው ለሚያቋቁሙት የሽምግልና ፍርድ ቤት (Arbiitration) አቅርበው ማስወሰን እንጂ ለማህበሩ ማቅረብ የሚያስፈልግ አደለም » እያለ ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየሰጠ ነገሩ (League Council) የኢትዮጵያ መንግስት ባቀረበው አቤቱታ ላይ ንግግር አላደረገም። ምክንያቱ በጉዳዩ የማህበሩ ምክር ቤት ተነጋግሮ ውሳኔ እንዳይሰጥበት የኢጣሊያ መንግስት ተንኮሉን ለመሸፈን ከሚፈጥረው ዘዴ ሌላ፥ ጀርመን አውሮፓ ውስጥ ጦርነት ለማድረግ መሰናዳቱ መታወቅ ጀምሮ ስለ ነበር፥ «ማህበሩ ሙሶሊኒን የሚያስቀይም ነገር ያደረገ እንደሆነ ከጀርመኑ መሪ ከሂትለር ጋር እንዳይተባበር ተፈርቶ » ነው ይባላል።

በግንቦት 25 1935 የማህበሩ ምክር ቤት (Council) በጉዳዩ ተነጋግሮ ፈራ ተባ እያለ «የኢትዮጵያና የጣሊያን ልዩነት በማህበሩ ውስጥ ሁለቱ ተስማምተው በሚያቋቁሙት የሽምግልና ፍርድ ቤት (Arbitratiion) እንዲወሰን 2ኛ ጉዳዩ በሽምግልናው ፍርድ ቤት በተያዘበት ጊዜ፥ የጦርነት መሰናዶ እንዳታደርግ » የሚል ውሳኔ  (Resolution) አሳለፈ።

በማህበሩ ውሳኔ መሰረት የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግስቶች የሽምግልና ዳኞቻቸውን መርጠው ፍርድ ቤቱ (Arbitration Tribunal) ተቋዋቋዋመ። የኢጣሊያን መንግስት ለዳኝነት የመረጠው «ሉይጂ አልድሮቫንዲ » እና «ራፋየሌ ሞንታኛ » (Luigi Aldrovandi e Raffoele Montagna) የተባሉትን ሁለት ጣሊያኖች ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት ፕሮፌሰ ጂዎፍር ደላ ፕራደል » (Professor Geouffre de la Pradelle) የተባሉትን ፈረንሳዊና «ፕሮፌሰር ፔትማን ፖተር » (Professor Pittman Potter) የተባሉትን አሜሪካዊ መረጠ። በሽምግልናው ፍርድ ቤት የኢጣሊያ መንግስት ወኪልና ነገረ ፈጅ «ፕሮፌሰር ሴሶና » የኢትዮጵያ መንግስት ወኪሎችና ነገረ ፈጆች ፕሮፌሰር ጋስቶን ዥዝ የተባሉት ፈረንሳዊና በፓሪስ የኢትዮጵያ ሚኒስትር በዥሮንድ ተክለ ሀዋርያት ነበሩ። የፍርድ ቤቱን ፅህፈት ቤት እንዲመሩ የተሾሙ ሶስት ጣሊያኖችና

በኢትዮጵያ በኩል አንድ ፈረስንሳዊ (ሬሞ ደላ ፕራደል፥ የዳኛው የጂዎፍር ደላ ፕራደል ልጅ) ነበሩ።

ፍርድ ቤቱ በዚህ አሆሁዋን ተቋቁሞ ከተደራጀ በሁዋላ የኢትዮጵያ ነገረ ፈጆች «ለግጭቱ ምክንያት ሆኖ ክርክሩን ያስከተለው ወልወል በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ለመሆኑ ማስረጃ እናቅርብ » አሉ። ነገር ግን የኢጣሊያ መንግስት ነገረ ፈጅ «ወልወል በማን ግዛት ውስጥ መሆኑ ጨርሶ መነሳት የለበትም » ብለው ስለ ተቃወሙ፥ የኢጣሊያን መንግስት የመረጣቸው (ኢጣሊያን) ዳኞችየጣሊያንን ነገረ ፈጅ አቋዋም፣ የኢትዮጵያ መንግስት የመረጣቸው ዳኞች የኢትዮጵያን ነገረ ፈጆች አቋዋም ደገፉ። ስለዚህ ነገሩ መውጫ የሌለው ዝግ መንገድ ሆነና ወደ ማህበሩ ምክር ቤት ቀርቦ መመሪያ እንዲሰጥበት ተደረገ። ምክር ቤቱ ጉዳዩ ቀርቦለት ከተነጋገረበት በሁዋላ ሀምሌ 31 1935 ወሳኝ ድምፅ (Castiing Vote) የሚኖረው አምስተኛ ዳኛ እንዲመረጥ መመሪያ ሰጥቶ በፓሪስ የግሪክ ሚኒስቴር የነበሩት «ሙሴ ፖሊቲስ » ተመረጡ። ከዚያ አምስቱ የሽምግልና ዳኞች (Arbitration Tribunal) ተሰብስበው የሁለቱን ወገኖች የማይቀራረቡ አቋዋሞች ለማቀራረብ ወይም ህግንና ያመፅ ስራን ማስማማት አስቸግሮዋቸው ዘለግ ያለ ጊዜ ጉዳዩን ይዘው ከቆዩ በሁዋላ በመጨረሻ መስከረም 3 1935 የሚያሳዝንና የሚያስገርም ውሳኔያቸውን ሰጥተው ተነሱ። ውሳኔው ባችሩ እንደሚከተለው ነበር።

«1ኛ. የኢትዮጵያ መንግስትም የኢጣሊያን መንግስትም ወልወል በየራሳቸው ግዛት ውስጥ መሆኑን ያምኑ ስለ ነበረ እዚያ ላይ ለተነሳው ግጭት ሁለቱም በደለኞች ሊባሉ አይችሉም።

«2ኛ. በወልወል ግጭት ምክንያት በቦምብና በሌላ በልዩ ልዩ መሳሪያ የተደረገው ጦርነትም እንዲያ ባሉ ቦታዎችና እንዲያ ባሉ ሁኔታዎች ዘወትር የሚደርስ ተራ ነገር ስለ ሆነ ‹ለአለም ሰላም ያሰጋሉ› ተብለው ከሚያሳስቡት ጉዳዮች ተራ የሚገባ አይደለም »

የሽምግልናው ፍርድ ቤት፥ የኢጣሊያን መንግስት ከጉልህ ያመፅ ስራው አጥቦ ከማጥራቱ ሌላ ኢትዮጵያን ወርሮ ለመያዝ የሚያስችለውን የጦር

ሰራዊትና ዘመናዊ መሳሪያ ካገሩ አጉዞ፥ በኤርትራና በሱማሌ ውስጥ ለማከማቸት ተጨማሪ ጊዜ ሰጠው። በዚያ ረዥም ጊዜ ውስጥ፥ የኢጣሊያ መንግስት ወታደሩንና መሳሪያውን በኤርትራና በሱማሌ ወሰን ድረስ፥ ያከማቸውን የጦር ስራቶችና መሳሪያ ለማጉዋጉዋዝ መንገድ፥ በሌለባቸው ክፍሎች መንገድ ለመስራትና የኢትዮጵያን ወሰን ሰብሮ ለመግባት ባቀደባቸው ቦታዎች ሁሉ ምሽጎቹን ለመመሸግ ቻለ።

የጣሊያን መንግስት የጦርነት መሰናዶውን በገሀድ ሲያሰናዳ ረዥም ጊዜ ቆይቶ ኢትዮጵያን በሰሜንና በደቡብ መውረር ሲጀምር የአለም መንግስታት ማህበር «ምንም አላደረገም » እንዳይባል ለኢጣሊያም ለኢትዮጵያም (ላጥቂዋና ለተጠቂዋ) የጦር መሳሪዒያ እንዳይሸጥላቸው ወይም እንዳይሰጣቸው የሚያግድ ውሳኔ አሳለፈ። ውሳኔው የተሰሩትን የጦር መሳሪያዎች እንጂ፥ ለጦር መሳሪያ የሚሆኑትን ጥሬ እቃዎች ጭምር ስለማያግድ፥ «እገዳው የተደረገ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ነው » ማለት ይቻላል። ኢጣሊያ ጥሬ እቃ እስካልተከለች ድረስ ለጦርነቱ የሚያስፈልጋትን መሳሪያ ሁሉ የምትሰራበት ፋብሪካ ስለነበራት እገዳው እስዋን የሚነካ አልነበረም።

የኢትዮጵያ መንግስት ለዘመናዊ የፖለቲካ ውስብስብ እንግዳ ስለ ነበረ ኢትዮጵያ የአለም መንግስታት ማህበር አባል መሆንዋን ብቻ ወሰንዋ እንዳይደፈርና ነፃነትዋ እንዲከበር የታመነ ዋስ መሆኑን ከልብ ያምን እንደ ነበረ የጊዜው ባለስልጣኖች ከሚናገሩትም፥ በጋዜጣም ከሚፃፈውም ይታወቅ ነበር። እንዲያውም ኢትዮጵያ ለአለም መንግስታት ማህበር አባል የሆነችበት ዋና ምክንያት ማህበሩ የተመሰረተበት «ቃል ኪዳን » (Convenant) አይነተኛ አላማው ያባሎቹን ደህንነትና የአለም ሰላም ለመጠበቅ በመሆኑ «አፍሪካን ተከፋፍለው ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ከሚሽቀዳደሙት የአውሮፓ ታላላቅ መንግስታት ይጠብቀኛል » ብላ በማመን ነበር ይባላል።

የኢትዮጵያ መንግስት አለም አቀፋዊ ህግ እንደ ብሄራዊ ህግ ስልጣንና ሀይል ላላቸው መንግስታት የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን አያውቅም ነበር። ስለዚህ በዚያ ረዥም ጊዜ ውስጥ የጣሊያን መንግስት ወታደሩንና መሳሪያውን ካገሩ እያጉዋዘ በኤርትራና በሱማሌ አከማችቶ ከዚያ ጦርነት ለመክፈት

ባቀደባቸው ግንባሮች ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ወሰን መንገዶችና ድልድዮች ሲሰራ፥ በኢትዮጵያ ወሰን ላይ ምሽጎችንና ሌሎችንም ለጦርነቱ የሚያስፈልጉትን መሰናዶዎች ሁሉ ሲያሰናዳ የኢትዮጵያ መንግስት በመጀመሪያ ደረጃ እምነቱን በአለም መንግስታት ማህበር ላይ በመጣል 2ኛ የነበረውን መጠነኛ የመሳሪያ ሀይል እንኳ በሚያስፈልገው ጊዜና በሚያስፈልግበት ቦታ የማደራጀት ችሎታ ስለልነበረውና የሚያደርገው ስለ ተደናገረው አንዳች መሰናዶ ሳያደርግ እጅ እግሩን ሰብስቦ አገሩ በይፋ እኪወረር ድረስ ይጠብቅ ነበር።

የኢጣሊያ የጦር ሰራዊት - በሱማሌ ግንባር መቸም ቀደም ብሎ ነው ኦጋዴን ውስጥ ብዙ ቦታዎች የያዘ - በሰሜን ግንባር፥ መረብን ተሻግሮ ትግራይ ውስጥ ብዙ ቦታዎችን ከያዘ በሁዋላ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥቅምት ወር 1928 የኢትዮጵያ መንግስት ለጦርነት «የክተት አዋጅ » አወጀ። የአለም መንግስታት ማህበር በገባው ቃል ኪዳን መሰረት የጣሊያን መንግስት ኢትዮጵያን እንዳይወር ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ጦርነቱ ባዋጅ ከተጀመረ በሁዋላ እንኳ በማህበሩ ፊት በደለኛ ወይም አጥቂ ሆኖ ላለመገኘት ትእዛዙን ባይኔ አላየሁም እንጂ፥ «ጠላት ሲያጠቃ ከመከላከል በቀር የኢትዮጵያ ጦር ለማጥቃት እንዳይሞክር በየግንባሩ ጦሩን ለሚመሩት የኢትዮጵያ የጦር አለቆች የመንግስቱ ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቶዋል » እየተባለ በሰፊው ይነገር ነበር። እንዲያ ያለ ትእዛዝ መስጥቱ እውነት መሆኑን ትእዛዙን ከተቀበሉት የጦር አለቆች አንዱ በጭፍሮቻቸው ፊት ሲናገሩ (ጭፍሮቻቸውን በፈንታቸው ሲያስጠነቅቁ) ሰምቻለሁ። ግን ጦርነት ለመዋጋት ተሰልፎ «ካልተጠቃችሁ እንዳተጠቁ » የሚል ትእዛዝ እንዴት ያለ የሚያስገርም የየዋሆች ትእዛዝ ነው! ታዲያ፥ የኢትዮጵያ መንግስት ፍፁም የዋህነት ከአለም መንግስታት ማህበር በለውጡ አንድ ብጣሽ ነገር ሳያገኝ ኢትዮጵያን ውድ ዋጋ፥ በጣም ውድ ዋጋ ነፃነቷን ጭምር አስከፈላት።

# ምዕራፍ ሁለት

# ቅድመ - ዝግጅት

የወልወል ግጭት ሲደረግ እኔ ጎጃም አገው ምድር ውስጥ ዳንግላ በምትባ ትንሽ ከተማ ያንድ ትንሽ ትምህርት ቤት አስተማሪና ስራ አስሂያጅ ነበርሁ። በዳንግላና በአዲስ አበባ መሀከል ካንድ ፖስታ ቤት በቀር የስልክ ይሁን ወይም የመኪና መንገድ መገናኛ ስላልነበረ፥ ዳንግላ እንኖር የነበር ሰዎች እንኩዋንስ ስለ «ወልወል ግጭት » ስለ አዲስ አበባም የምንሰማው ወሬ እጅግ ጥቂት ነበር። ያውም ጥቂት አዲስ አበባ ደርሰው እስኪመለሱ ከሶስት ወራት ያላነሰ ጊዜ ከሚወስድባቸው ሲራራ ነጋዴዎችና እጅግ ፈጠነ ሲባል በወር አንድ ጊዜ ከሚደርሰው እግረኛ ፖስታ አመላላሽ የሚገኝ ነበር። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ተጨምሮበት አንዳንድ ጊዜም ተቀንሶለት፥ በዚያም ሆነ በዚህ መልኩ ተለውጦ ካልሆነ እውነተኛው ወሬ ደርሶን አያውቅም። የሆነ ሆኖ፥ በነበርሁበት አገርና ባካባቢው የሚኖረው ህዝብ ስለ ወልወል ግጭትም ሆነ ስለ ሌላው ኢትዮጵያ ከውጭ መንግስታት ጋር ስላላት ግንኙነት የሚከታተልና በጠቅላላው የፖለቲካ ጉዳይ የሚያሳስበው ስላልነበረ ለኔም እዚያ በቆየሁበት ጊዜ፥ ግጭቱ የሁዋላውን ያህል ከብዶ አልተሰማኝም ነበር። እርግጥ የፖስታ ቤቱ ሹም፣ አቶ ይትባረክ ተገኝ በወር አንድ ጊዜ ስለ ነበረና ከሳቸው ጋር ግንኙነት ስለ ነበረኝ ጊዜ ያለፈ ጋዜጣ በማንበብም ከደብዳቤዎች ያገኙትን ያረጀ ወሬ እየነገሩኝም፥ ከሌሎች የተሻለ አውቅ ነበር። ግን ካቶ ይትባረክ አገኘው የነበረው ወሬ የግጭቱን አስጊነት የሚያሳይ አልነበረም።

የወልወል ግጭት በህዳር ወር መጨረሻ 1927 ከተደረገ በሁዋላ በዚያው አመት በመጋቢት ወር ላይ ከዳንግላ ወደ ደብረ ማርቆስ ትምህርት ቤት ተዛወርሁ። ደብረ ማርቆስ የትምህርት ቤቱ ሹማምንትና መምህራንም ለየመስሪያ ቤቱ አላፊዎችና ሰራተኞች ሆነው ካዲስ አበባ የተላኩት ሰዎችም ስለ ፖለቲካ ጉዳይ የመወያየት ልማድ የነበራቸው ስለ ነበሩ፥ የወልወል ግጭት ከዳንግላ የበለጠ ውይይት ሲደረግበት አልፎ አልፎ ይሰማ ነበር። ይሁን እንንጂ እዚያም ቢሆን፥ ባዲስ አበባና በደብረ ማርቆስ መሀከል የመኪና መንገድ ስላልነበረ፥ የለት ቀርቶ የማግስት ወሬ ለጠቅላላው ህዝብ የሚያደርስ ሌላ መገናኛ ስለልነበረ ካዲስ አበባ ትክክለኛ ወሬ የሚያገኙ የስልክና የራዲዮ

ሰራተኞችና በነሱ አማካይነት መልእክቱ የሚተላለፍላቸው የበላይ ሹሞች ብቻ ነበሩ። እነሱም በምስጢርና በተራ ወሬ መሀከል ያለውን ልዩነት ባለማወቅ ይሁን ወይም በሌላ በማይታወቅ ምክንያት፥ ከበላይ የሚላከውን ነገር ሁሉ ምስጢር አድርገው ስለሚይዙት፥ ስለ ወልወል ግጭት ትክክለኛውን ሁኔታ ከነሱ በቀር የሚያውቅ አልነበረም። የቀረው ሰው ጫፍና ጭምጭምታ ወሬ እየያዘ በዚያ ላይ የየራሱን ግምት እየጨመረ ነበር ሲያወራና ሲተች የሚሰማው። ብቻ በጠቅላላው «በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀከል ጦርነት ይደርጋል » ብሎ የሚገምት አልነበረም።

ነገር ግን ወደ ሁዋላ ኢጣሊያ ወሰን አልፋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ጦርነት ማድረግዋንና ብዙ ህዝብ ፈጅታ አንዳንድ የኢትዮጵያን አገሮች መያዝዋን የኢትዮጵያ መንግስት ለአለም መንግስታት ማህበር አስታውቆ፥ ማህበሩ በጉዳዩ በመነጋገር ላይ መሆኑ ይሰማ ጀመር። እሱንም የሚያወሩት አልፎ አልፎ ከሚደርሰው ጋዜጣ ያነበቡና «የአለምን ፖለቲካ እንከታተላለን » የሚሉ ሰዎች ነበሩ። ታዲያ እኒያ ሰዎች ግምታቸውንና ምኞታቸውን ከጋዜጣ ያነበቡት ወይም ካዋቂዎች የሰሙት አስመስለው እያጋነኑ ሲናገሩ ኢጣሊያ፥ የምትቀጣ መሆንዋን እንደማያከራክር የተረጋገጠ ነገር ቆጥረውት ክርክሩም ሆነ ትችቱ ስለ ቅጣቱ አይነትና ስለ ካሳው መጠን ነበር።

የአለም መንግስታት ማህበር አሰራር እንኩዋንስ ደብረ ማርቆስ ከነበሩት ሹማምንትና ሰራተኞች አዲስ አበባ የመንስቱ አባላት ከሆኑት ሰዎች መሀከልም ጠንቅቀው የሚያውቁ አልነበሩም። የአለም መንግስታት ማህበር ከማህበሩ፥ አባላት ሀይለኞች የሆኑት ታላላቅ መንግስታት ታናናሾችን በእርዳታ ተስፋ እያባበሉም እያስፈራሩም እንዲተባበሩዋቸው አድርገው መፈፀም የሚፈልጉትን መልካም ይሁን ክፉ ህጋዊ መልክ እንዲኖረው ለማድረግ የሚጫወቱበት መድረክ መሆኑን ያን ጊዜ በኢትዮጵያውያን መሀከል የሚያውቅ አልነበረም። ከዚህ ሁሉ ሌላ «የማህበሩ ውሳኔ ከህግና ከህግና ከህሊና ፍርድ የራቀ ይሆናል፤ ወይም አንድ አባል የቀሩትን መንግስታት ሁሉ ፈቃድ ጥሶ ያመፅ ስራውን ለመፈፀመ ድፍረትም አቅምም ሊኖረው ይችል ይሆናል » ብሎ የሚጠረጥር ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ስለዚህ፥ የማህበሩ

ምክር ቤት (League Council) የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጉዳይ፥ በማህበሩ ስር በሽምግልና ፍርድ ቤት (Arbitration) ታይቶ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲቀርብለት ውሳኔ (Resolution) ማሳለፉ ከታወቀ በሁዋላ የኢትዮጵያ መንግስትም ከሹማምንቱና ከሰራተኞች ወገን ጉዳዩን የሚከታለው ክፍልም ፍፃሜውን በታላቅ ተስፋና በጉጉት ይጠባበቅ ነበር። ለጥንታውያኑ መኩዋንንትና ለጠቅላላው ህዝብ ግን፥ ጉዳዩ እንኩዋንስ ለውይይት ለአሳብም ሩቅ ስለ ነበር በነሱ መሀከል ሲነሳ እምብዛም አይሰማ ነበር።

የአለም መንግስታት ማህበር ውሳኔ ቅን ፍርድን የተከተለ እንደሚሆን በማመን፥ የኢትዮጵያ መንግስትና የፖለቲካ ጉዳይ የምንከታተለው ሁሉ ውሳኔውን በናፍቆት በመጠባበቅ ሰፊው፥ ህዝብ በግዴለሽነት ላይ እንዳለን፥ ትምህርት ቤት የሚዘጋበት ጊዜ ደረሰ። ስለዚህ እኛ በትምህርት ቤት ስራ የተሰማራነው ሁሉ አስተማሪዎች፥ ፈተና ለማሰናዳትና ለማረም ሌሎች ሰራተኞች የመዝጊያው በአል የሚከበርበትን ስነ ስራት ለማደራጀት በነበረው ውጥረትና ጥድፍያ ምክንያት አሳባችንም ጊዜያችንም በሙሉ በዚያ ስራ ተውጦ፥ የወልወል ግጭት ያስከልተለውን መዘዝም ሆነ ሌላውንም ነገር ሁሉ ለጊዜው ወደ መርሳት ደርሰን ነበር። የፈተናው ውጤት፥ በዚያ ጊዜ ይሰጡ በነበሩት ትምርቶች ሁሉ፥ በጣም ጥሩ ስለ ነበረ፥ አስተማሪዎች ትጋትና ብርታት እንዲህም ላስተማሪዎች የትምህርት አሰጣጥ ችሎታ እንደ ምስክር ሆኖ ታይቶ በረከቱ ካልደረሳቸው ጥቂት አስተማሪዎችና ከቤተሰቦቻቸው በቀር ባጠቃላይ ሁሉንም ደስ አሰኝቶ ነበር።

የትምርት ቤታችነን የመዝጊያ በአል ካከበርን በሁውላ ወደ ደብረ ማርቆስ ትምህርት ቤት ከተዛወርሁበት ጊዜ ጀምሬ ሳስበበት የቆየሁት ጉዳይ ላለቃዬ፥ ለጎጃም የትምህርት ክፍል አላፊ፥ ላቶ (ሁዋላ ፊታውራሪ) ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ ገልጨ፥ ትምህርት ቤታችን በተዘጋበት በረፍቱ ጊዜ ያሰብሁትን ለመፈፀም ፈቃድ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁዋቸው። አሳቤ የተወለድሁበት አገር እንዶዳም ኪዳነ ምህረት ከደብረ ማርቆስ ቅርብ ስለ ሆነ እዚያ በሬዎች ገዝቼ ሁለት ጥማዶች ባስጠምድ በህል በጥራ ጥሬና በሌሎች ለኑሮ አስፈላጊዎች በሆኑ ነገሮች በኩል የሚኖርብኝን ችግር የሚያቀልልኝ ከመሆኑ ሌላ ድሀ ዘመድ ለመርዳትም የሚያስችለኝ ስለ መሰለኝ ይህን ለማድረግ ነበር።

አቶ ወልደ ጊዮርጊስ፥ በመሰረቱ አሳቤን ደግፈውና አበረታተው፥ በተከታዩ አመት አዳዲስ ትምህርት ቤቶች በሚከፈቱባቸው አንዳንድ አውራጃዎች ለጊዜው ስለሚያስፈልጉት አስተማሪዎችና ሌሎች አስቸኳዋይ መሰናዶዎች ተመካከረን መወሰን ስላለብን፥ እስከ ነሀሴ አጋማሽ ድረስ ቆይቼ እንድሄድና ትምህርት ቤት እስከሚከፈትበት ጊዜ ድረስ ያሰብሁትን ፈፅሜ እንድመለስ ፈቀዱልኝ። እንዲያውም ያልጠይቅሁዋቸውን ገንዘብ የሚያጥረኝ እንደሆነ በየወሩ ከደመወዜ እየተቀነሰ የሚከፈል ብድር ሊፈቅዱልኝ የሚችሉ መሆናቸውን ገለፁልኝ። ስለዚህ ለመመካከር በትምርት ቤት ውስጥ ከምሰበሰብበት ስንነሳ፥ ወይም ስብሰባ በሌለን ጊዜ፥ እንዶዳም ሄጄ ስሰነብት የሚያስፈልጉኝን ሳዘጋጅ ሰነበትሁ።

አንድ ቀን የስብሰባ ጊዜ ስላልደረሰ ወንበር አውጥቼ እደጄ እንደ ተቀመጥሁ እስከ ዛሬ ሲያስገርመኝ የሚኖር «አንባቢዎችንም ሳያስገርማቸው አይቀርም » ብዬ የምገምተው ነገር ደረሰ።

ሀምሌ 28 1927 ጤናው መንገሻ የሚባል ወዳጄ ካገው ምድር እኔን ፈልጎ እቤቱ ድረስ መጣ። ጤናውን ዳንግላ ሳለሁ መጀመሪያ ያወቅሁት በሽፍታነቱ ነበር። በጀግናነቱ የሚያውቁት ሁሉ ተባብረው የሚያደንቁት ነበር። ምንም እንኩዋ ትንሽ ከመንገዳችን የወጣን ቢመስል፥ ጤናውና እኔ የተወቅንበት ሁኔታ አንባቢዎች ቢያውቁት የሚከፋ ስላልመሰለኝ ባጭሩ፥ እንደሚከተለው መግለፅ እወዳለሁ።

ዳንግላ የመጨረሻው የእንግሊዝ ቆንስል የነበሩት ሜጀር ችዝማን ከዚያ ለቅቀው ሲነሱና በሳቸው እግር ሌላ ቆንስል እንደማይተካ ሲታወቅ ቆንስላው ትምህርት ቤት ሆኖ፥ እኔ ወደዚያ ተዛውሬ ትምህርት ቤቱን እናቁዋቁም እስኪደረግ ድረስ በጉምሩክ፥ ውስጥ የተቆጣጣሪነት ስራ ነበር የምሰራው። በተቆጣጠሪነቴ በየወሩ መጨረሻ ሂሳብ በሚወራረድበት ጊዜ ካሆነ ብዙ ስራ አልነበረኝም። ስለዚህ አለቃዬ ያገው ምድርና ያቸገር የጉምሩክ ስራ አላፊ የነበሩት፥ ብላታ፥ ህለተወርቅ እሸቴ፥ ከጉምሩክ ሹምነታቸው ሌላ «የባሪያ ነፃ » ሹም ክልፍም እንድረዳ ጠይቀውኝ «በወዶገባነት » ሊተባበሩኝ ከፈቀዱ ጉዋደኞቼና እሳቸው ለዚያ ስራ ከመደቡዋቸው ወታደሮች ጋር ባንድነት ሆነነ

እንሰራ ጀመር። ምንም እንኳዋ በባሪያ ሲነግዱ የተያዙ ሰዎች በስቅላት እንደሚቀጡ ቀደም ብሎ የታወጀ አዋጅ ቢኖርም በዚያ ጊዜ፥ ብርቱ የባሪያ ንግድ በምስጢር ይሀሂድ ስለ ነበር ስራችን «ባሪያ ፈንጋዮችንና » በጠቅላላው ባሪያ ነጋዴዎችን እያደኑ የያዙዋቸውን ባሮች ነፃ ማድረግ ስለ ነበረ ብዙ ባሮች ነፃ አደረግን። ከጤናው መንገሻ ጋር የተዋወቅንም ያን ጊዜ ነበር። ጀግንነቱን ብዙ ሰዎች ሲያደንቁለት እሱማ ስለ ነበረ፥ «እሱ ከኛ ጋር የሆነ እንደሆነ ከባሪያ ፈንጋዮችና ነጋዴዎች ጋር በነበረን ጦርነት ሀያልችን ይበረታል » ብዬ በማመን እኔ ነበርሁ ፈልጌ የተዋወቅሁት። ብቻ በመነጋገር ላይ እንዳለን እኔ ከጉምሩክ ወደ ትምህርት ቤት በመዛወሬ ንግግራችን ፍፃሜ ሳያገኝ በጅምር ቀረ። ይሁን እንጂ ወዳጅነታችን አልተቋረጠም፤ ዳንግላ ትምህርት ቤት በቆየሁበት ጊዜ ሁሉ ቶልቶሎ እየመጣ ይጠይቀኝ ነበር።

«ጤናው ዛሬ ምን እግር ጣለህ? » አልሁት፥ እደጅ እንደ ተቀመጥሁ ወደኔ ሲመጣ ሳየው ገና ተገናኝተን ከመሳሳማችን በፊት።

«አንተን ልጠይቅ ነው የመጣሁ » አለ ከተሳሳምን በሁዋላ።

«እኔን ለመጠየቅ ብቻ ካገው ምድር እዚህ ድረስ? »

«ወዳጅነታችን ካገው ምድር እዚህ ድረስ አያስመታም ማለትህ ነው? »

«እንዲያ ማለቴ እንኳዋ አይደለም፤ ሌላ የደረሰብህ ችግር እንዳለ ለማወቅ ነው እንጂ። »

«የደረሰብኝ ችግር የለም፤ አንተን ለመጠየቅና ወዲያውም የፍልሰታን ፆም እዚህ ለመያዝ ብዬ ነው የመጣሁ። »

ይዤው እቤት ገብቼ ቁርስ እንዲያደርግ ብለምነው «አድርጌ አለሁ » ብሎ «እንቢ » ስላለኝ አንድ ብርጭቆ ጠጅ ከጠጣ በሁዋላ፥ ስብሰባ እንዳለብኝ ነግሬው ለምሳ እንዲመጣ ተቃጠርንና፥ እኔ ወደ ስብሰባ፥ እሱ ወደሚሄድበት ሄድን። ከስብሰባ ስመለስ ቀድሞኝ እደጅ ቁጭ ብሎ አገኘሁት።

«ለምን እቤት ገብተህ አልተቀመጥህ? » አልሁት።

«ልጆች እንኩዋ እንድገባ ለምነውኝ ነበር፤ ነገር ግን ብቻዬን እቤት ከመቀመጡ፥ እዚህ ተቀምጬ እንዲህ አካባቢውን ስመለከት መቆየቱን ስለ መረጥሁ ነው አልገባም ያልሁዋቸው። »

ከዚያ ገብተን ስለ አገው ምድርም ስለ ደብረ ማርቆስም፥ እያወራንም ምሳ በለን። ከቀትር በሁዋላ ስብሰባ ስላልነበረኝ ስንጫወት እንድንውልና እዚያው እኔ ቤት እንዲያድር ለመንሁት።

«የለም የሚያስቸኩል ጉዳይ ስላለብኝ እሄዳለሁ » አለኝ።

«ምን? »

«ማታ ከሌሎች ሰዎች ጋራ እራት እንድንበላ አስቀድሜ ስለ ተቀጣተጠርሁ፥ እዚያው ነው የማድር፥ አሁን ከዚህ ሄጄ ሽንብራና የንፍሮ መቀቀያ፥ አንዳንድ የሚያስፈልገኝን እቃዎችም ስገዛዛ አመሻለሁ፤ ነገ ደህና መቃብር ቤት ባገኝ ፈልጌ አስንዳዳለሁ፤ ስለዚህ ጊዜ የለኝም » አለ፤ እንደሚያፌዝ ጥርሶቹን በከፊል ገለጥ አድርጎ።

«ትቀልድብኛለህ መሰለኝ! » አልሁት፥ የተናገረው እውነቱን ይሁን ቀልዱን ማወቅ ስላልቻልሁ።

«ቀልድ አይደለም፤ ውነቴን ነው። ከመጣሁለት አንዱ ዋና ጉዳይ፥ በፍልሰታ ፆም እዚህ ሱባኤ ለመግባት ነው። »

«ስንት ነፍሰ ገዳይ ስንት ንብረት የዘረፍህ ሀጢያተኛ እንኩዋንስ አስራ አምስት ቀን፥ አስራ አምስት አመት ሽንብራ እየበላህ ሱባኤ ብትገባ ምህረት አገኛለሁ በለህ ተስፋ ታደርጋለህ? » አልሁት። ለምቀለድ ያህል ነው እንጂ፥ ከጅግናነቱና ሌሎች ሽፍቶች ሳይቀሩ ይፈሩት የነበረ ከመሆኑ ሌላ፥ እንኩዋንስ ብዙ አንድ ነፍስ ያጠፋ መሆኑን ሰምቼ አላውቅም።

«ሀጢያተኛ መሆኔን ስላወቅሁና ፈጣሪዬን ምህረት እንዲያደርግልኝ ብለምነው እንደሚምረኝ ስላመንሁ ነውኮ ምህረት ልመና ሱባኤ የምገባው። ጌታችን፥ ‹ሀጥአንን እንጂ ፃድቃንን ልፈልግ አልመጣሁም› አላለምን? »

ብሎኝ ተነሳ። ጤናው ዜማም፥ ቅኔም አዋቂ ነበር። ልሸኘው ወጥተን እደጅ ስንደርስ።

«ያቺ ዳዊትህ አለች እንደሆነ እባክህ ስጠኝ » አለኝ።

«የትዋ ዳዊቴ? »

« ‹በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ› የሚል የተጻፈበት የኪስ ዳዊትህ፤ ለሰው ሰጠሀት? »

«ለሰው እንኳን አልሰጠሁዋትም፤ ብቻ የት እንዳስቀመጥሁዋት አላውቅም » ብዬ ገብቼ የነበሩኝን ጥቂት መፃህፍት ወደ ደረደርሁበት ክፍት ሳጥን ብሄድ በቅርብ ስላገኘሁዋት አምጥቼ ሰጥቼው ፆሙ ሲፈሰክ፥ ነሀሴ አስራ ስድስት ቀን ምሳ እኔ ቤት አብረን ልንበላ ተቃጠረን ተሰነባበትን።

ነሀሴ አስራ ስድስት ከምሳ ሰአት ትንሽ ቀደም ብሎ መጣ። ትንሽ ቀጠን ከማለቱ በቀር፣ መልኩ ምንም ያክል ስላልተለወጠ አስራ አምስት ቀም ሙሉ ሽንብራ - ያውም በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እየበላ - ሲፆም የሰነበተ አይመስልም ነበር።

«ትንሽ የቀጠንህ ትመስላለህ እንጂ፥ ሌላ የመጎዳት መልክ አይታይብህም፤ ፊትህማ እንዲያውም ካስራ አምስት ቀን በፊት የመጣህ እለት ሳይህ ከነበረውም ቁልጭ ብሎ ደምህ ጠርቶ አምሮብሀል » አልሁት፤ ምሳ እየበለና ስናወራ።

«አቀበት መወጣት፥ ቁልቁለት መውረድ የለ፤ ሽምብራ ቦቀልት ቀቅሎ አንድ ጊዜ በዘጠኝ ሰአት በልቶ ጥሩ ውሀ ጠጥቶ መተኛት ብቻ ነው። ታዲያ ምን ጎደለብኝና የጉዳት መልክ ይታይብኝ? እንዲያውም ሲሳማማ ብታይ፤ እንዲህ እንዳይመስልህ! » አለኝ። የማፌዝበት መስሎት እንዳይሰማው ከዚያ አልፌ ስለ ሱባኤው አላነሳሁበትም፤ እሱም አላነሳም፤ ሌላ ወሬ እያወራን ምሳ በልተን ስንጨርስ ደክሞት እንደ ተኘቶ ትንሽ እንዲያርፍ ጠየቅሁት።

«ምንም አልደከመኝም፤ ይልቅ ተነስ ውትርን እንውረድ » አለኝ እጁን ታጥቦ ተነሳና፡ ውትርን ከትምህርት ቤታችን በታች ያለ ወንዝ ነው። በቀኙና በግራው ሰፊ ሜዳ ስላለ፤ ደስ ያሰኛል። እዚያ ወርደን ዙሪያውን ደህና አድርጎ በሚያሳይ ጉብታ ላይ ተቀምጠን ስንጫወት እንደቆየን የሰጠሁንት ዳዊት ከኪሱ አውጥቶ፣ እዚያ ውስጥ ያስቀመጠውን የተፃፈበትን ወረቀት ገልፆ ይመለከት ጀመር። ከዚያ፥ ዳዊትዋን አጥፎ እፊቱ አስቀመጠና ቅር ያለው ፊቱን ቀና አድርጎ ከወንዙ ወዲያ ማዶ ‹አረደኸዣን› የሚባለውን ተራራ እየተመለከተ ዝም አለ።

«ምንድነው? » አልሁት፤ ወረቀቱን ካነበበ በሁዋላ ፊቱን ቅር ሲለው ስላየሁ፥ የመርዶ ወረቀት የያዘ መስሎኝ ልቢኤ እየፈራ።

«ፈርንጁ በቅርቡ ጦርነት ሊያደርግብን ነው። እና የሚቀናን አይመስለኝም፤ ድል አድርጎ አገራችንን የሚይዝ ይመስለኛል። ብቻ ይዞ ብዙ አይቆይም፤ ይወጣል፤ አንተም የምትዘምት ይመስለኛል » አለ፤ በቅርታ የከበደ ፊቱን ካረደኸዣን ተራራ ወደኔ መልሶ።

የዘመድ ሞት ሊያረዳኝ ብዬ ስፈራ ከወረቀቱ ሲያነብ የቆየው ሱባኤ ገብቶ ያየውን ህልም መሆኑን ከሰማሁ በሁዋላ ልቢኤን ተጭኖት የነበረው ፍራት ገለል ሲልልኝ ተሰማኝና ደስ ብሎኝ ሳይታወቀኝ እንድ እመሳቅ አልሁ። ከዚያ የደስታ ስሜቴ ከፊቴ እንዳይታይ፥ ነገሩ ያሳሰበኝ ለመምሰል አንገቴን ደፍቼ ቆይቼ፥

«እሲት ሁሉም ይሁን፤ የኔ መዝመትስ ምን ይባላል? ወታደር አደለሁ! »

«በምን ምክንያት እንደምትዘምት እኔ አላውቅም። »

ህልም የሚባለውን ነገር ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገብቼ ከቆየሁበት ጊዜ ጀምሬ ማመኑን ስለ ተውሁ ያንለት ጤናው የነገርኘንም አላመንሁ። ነገር ግን እጅግ ብርቱ ምስጢር አድርጎ እቤት እንዳይነግረኝ ቤቱን እንኩዋ ስለ ጠረጠረ እጠራ ሜዳ ላይ ወስዶ የነገረኝን ያለመንሁት አስመስሎ የሚያሳይ ነገር እንዳልናገርና እንዳላስቀይመው በነገርኝ ህልም ላይ መተቸት

አልፈለግሁም። እሱ ግን አለማመኔ እንደ ገባው ከፊቱና ከጠቅላላው ሁኔታው ይታይ ነበር።

ወደ ቤት ተመልሰን ወደ ህልሙ የሚመራ ነገር እንዳንናገር እኔም እሱም እየተጠነቀቅን ሌላ ወሬ ስናወራ ከቆየን በሁዋላ፥

«መቸም ዛሬ ስንጫወት አምሽተን እራትም አብረን በልተን እዚህ ነው የምታድረው » አልሁት።

«የለም እዚህ አላድርም። ወደ አገው ምድር ከሚሄዱ ሰዎች ጋር አብረን አድረን፥ ነገ ከጥዋቱ ቀደም ብለን ለመነሳት ስለ ተቃጠርንና የምፈፅመው ብርቱ ጉዳይ ስላለኝ ልሂድ፤ እንዲያውም ጊዜ ሳልፈያለሁ » ብሎኝ ተነሳ። አጥብቄ ብለምነውም ያካፈለኝን ብርቱ ምስጢር ደስ ብሎኝ ባለመቀበሌ አዝኖ ይሁን፥ ወይም እንዳለው ለማግስቱ የጥዋት ጉዞው እንዲመቸውና ያንለት የሚፈፅመው ጉዳይ ኖሮት በዚያ ምክንያት ይሁን «እንቢ » አለኝ። ስለዚህ አብሬው ወጥቼ ስንሰነባበት፥

«ታዲያ ነገ ጥዋት የምትሄድ ከሆነ መቼ ነው የምንገናኝ? እንግዲህ አንገናኝም ማለት ነው? » አልሁት።

«በቅርቡ እንገናኛለን፤ ወደ ዘመቻ ከመሄድህ በፊት መጥቼ አይሀለሁ » አለ፤ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ። «የነገርሁህን አሁን ባታምን፥ በቅርቡ ሲደርስ ታያለህ! » ማለቱ ነው። እኔም ያሽሙሩ ትርጉዋሜ ገባኝና ሳቅሁ።

ከተለያየን በሁዋላ እደጅ፤ እንደ ቆምሁ ካይኔ እስኪጠፋ ስመለከተው ቆይቼ፥ የነገረኝን ህልም እያሰላሰልሁ እቤት ገብቼ ቁጭ ስል፥ ዳንግላ ሳለሁ ጣሊያኖች «ይሰራሉ » እየተባለ ይወራ ስለ ነበረ አንድ የተንኮል ስራ የሰማሁት ትዝ አለኝ።

ጣሊያኖች እንደ ባህታውያንም እንደ ባለዛሮችም ለብሰው ጠጉራቸውን አሳድገው ወደየምኩዋንንቱና በዝህብ ዘንድ ተሰሚዎች ወደ ሆኑ ሰዎች እየሄዱ፥ «በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀከል ጦርነት ተደርጎ ኢጣሊያ እንድታሸንፍና ኢትዮጵያ ላጭር ጊዜ ይዛ ቆይታ እንድትለቅ እግዚአብሔር

አዝዞዋል » እያሉ የሚሰብኩ ሰባኪዎች ገዝተው በዚያ ክፍል ያሰራጩ መሆናቸው ይወራ ነበር። ባህታዊዎች የነገሩዋቸው ሰዎች ራሳቸው «ነገሩን » እያሉ የሚያወሩም ነበሩ። ስለዚህ ጤናው «ህልም አየሁ » ብሎ የነገረኝ የጣሊያን ሰባኪዎች «በምስጢር ይሰበካሉ » እየተባለ ይወራ ከነበረው ስብከት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ታየኝና ለጊዜው ደነገጥሁ። ነገር ግን ትንሽ ሳስብ ከቆየሁ በሁዋላ «ጤናው እንዲያ ያለ ነገር ያደርጋል » ብሎ ማመኑን ልቤ አልቀበለው ስላለ አሳቡን ቶሎ ከራሴ ውስጥ አባረርሁት። ያን ድንገት ትዝ ብሎ ያደነገጠኝን ነገር ብቻ ሳይሆን ለጊዜው ጤናውንም ህልሙንም ረስቼ እንዶዳም ሄጄ ስቆይ ስለሚያስፈልጉኝ ነገሮች ወደ ማሰቡና ወደ ማሰናዳቱ ገባሁ። ብቻ ጤናውንና ህልሙን ይረሳሁዋቸው ለጊዜው ነው። ጤናው «በህልም መልክ ታየኝ » ብሎ የነገረኝን የሚያስገርም ትንቢት ወዲያው ሲፈፀም ስላየሁት እሱም ህልሙም ተመልሰው መጥተው እንደማይጠፉ ሆነው ባእምሮዬ ተቀርፀው ይኖራሉ።

በጦርነቱ ጊዜ ሲደረገ ካየሁትና፥ እኔ ራሴ እንኩዋ ካደረግሁት ብዙ ተረስቶኛል። ሀምሌ 28 1927 ከጤናው መንገሻ ጋር የተነጋገርነውን ግን፥ ከዚያ ከሚያስገርም ትንቢት ጋር የተያያዘ ስለ ሆነ፥ አንዱን አልረሳውም። እንኩዋንስ የተነጋገርነው ጤናው ሲናገር በጁ፥ በከንፈሮቹ ባይኖቹ ያደርገው የነበረውን እያንዳንዱ ትንንሽ እንቅስቃሴ እስከ ዛሬ ይታየኛል።

ከጤናው ከተለያየንበት ቀን ማግስት ይሁን ሳልስት፥ ትምህርት ቤት ከመከፈቱ በፊት በሬዎችን ለመግዛት አለቃዬን ተሰናብቼ ወደ እንዶዳም ኪዳነ ምህረት ወረድሁ።

## ምዕራፍ ሶስት

# ዝግጅት

እንዶዳም፥ የናቴ አባት፥ አያቴ እናቴና ሁለት እህቶቼ ባንድ ላይ የሚኖሩበት ከመሆኑ ሌላ ብዙ የቅርብና የሩቅ ዘመዶቼ የሚኖሩበት አገር ነው። ስለ ሄድሁበት ጉዳይ ዘመዶቼን ሳማክራቸው፥ በመሰረቱ አሳቤን ደግፈው፥ ወራቱ ያዝመራ ወራት በመሆኑ መሬቱ ሁሉ የተዘመረ ስለሆነና አዝመራው እስኪሰብሰብ ማረስ ስለማይቻል፥ በዚያ ጊዜ ከብቶችን የመግዛት ትርፉ፥ እነሱን ሲጠብቁ መቆየት ብቻ መሆኑን አስረድተው፥ አዝመራ እስኪሰበሰብ ቢያንስ እስከ ጥቅምት መጨረሻ ቆይቼ እንድገዛ ስለ መከሩኝ ምክራቸውን ተቀበልሁ። ከዚያ በኋላ፣ የረፍት ጊዜዬን እዚያው ከዘመዶቼ ጋር ለማሳለፍ ወስኜ ጥቂት ቀናት እንደ ቆየሁ አንድ ቀን ያለቃዬ ያቶ ወልደ ጊዮርጊስ መላከተኛ መጥቶ፥ «ቶሎ ድረስ በልውሀል » አለኝ። ምክንያቱን ያውቅ እንደሆነ ብጠይቀው፥

« ‹ዛሬ ባይችል ነገ እንዳይቀር ንገረው› አሉኝ እንጂ ምክንያቱን አልነገሩኝም » አለኝ።

በማግስቱ ጥዋት ከንዶዳም ተነስቼ ደብረ ማርቆስ እንደ ደረስሁ በችኮላ የተጠራሁበትን ምክንያት ለመጠየቅ ወደ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ፅህፈት ቤት ሄድሁ። አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ለምን እንደ ጠሩኝ እኔ እስክጠይቃቸው አልቆዩም፤ ሰላምታ ሰጥተው ካስቀመጡኝ በሁዋላ፤ ወዲያው የሄድሁለትን ሳልፈፅም እንድመለስ ለማድረግ የተገደዱበትን ምክንያት ሊገልፁልኝ ጀመሩ።

«ጣሊያኖች ጦርነት ሊያደርጉብን ታጥቀው መነሳታቸው ተረጋግጦዋል። ጦራቸውን በሰሜን በኩል መረብ ወንዝ ላይ አሰልፈዋል፤ እንዲያውም ባንዳንድ ቦታ «ወንዙን ተሻግረዋል » ይባላል። በደቡብም ቀደም ብለው ኢትዮጵያ ውስጥ የያዙዋቸውን ቦታዎች አልፈው፥ ወደ ፊት ገፍተዋል ይባላል። ይህ እርግጥ ነው፤ ራስ እምሩ ናቸው አስጠርተው የነገሩኝ። ብቻ እስካሁን ከሳቸውና ካቶ ገብረ መስቀል ሀብተ ማርያም በቀር እዚህ አገር ያወቀ የለም። ለኔም የነገሩኝ ህዝቡን ካሁን ጀምረህ ስለምቀሰቅስበት ዘዴ ሊያማክሩኝ ነው። ስለዚህ ከላይ በይፋ እስኪገለፅ ድረስ ምስጢር ነውና፥ ለማንም ቢሆን ካፍህ እንዳይወጣ አደራህ። አሁን እንዳልሁህ ከራስና ካቶ ገብረ መስቀል እዚህ ትምህርት ቤት ከኔና ካንተ በቀር የሚያውቀው የለም።

ካስተማሪዎች እንኳዋ አንድ የሚያውቅ የለም » አሉ። አቶ ገብረ መስቀል እዚህ ትምርት ቤት ከኔና ካንተ በቀር የሚያውቀው የለም። ካስተማሪዎች እንኳዋ አንድ የሚያውቅ የለም » አሉ። አቶ ገብረ መስቀል ሀብተ ማርያም (ሁዋላ ደጃዝማች) የደብረ ማርቆስ ራዲያ ጣቢያ ሹም ነበሩ።

«ታዲያ ጣሊያኖች ጦራቸውን አሰልፈው አገራችን ውስጥ ቦታ ከያዙ እስከ መቼ ድረስ ነው ነገሩ ምስጢር ሆኖ የሚቆይ? ለምን ቶሎ የዘመቻ አዋጅ አይታወጅ? » አልሁዋቸው።

«የዘመቻ አዋጅ መቸ እንደሚታወጅ አላውቅም፤ መንግስት አዋጁን ያቆየበት ምክንያት ይኖረዋል። »

«ለመሆኑ ያለም መንግስታት ማህበር ፈቅዶላቸው ነው? ወይስ ፈቃዱን ጥሰው ጣሊያኖች በኛ ላይ ጦርነት የሚያደርጉ? » አልሁዋቸው፤ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ልታደርግ መነሳትዋ እርግጥ መሆኑን ሲነግሩኝ ስለ አለም መንግስታት ማህበር ስሰማው ከኖርሁት ጋር አልጣጣምልኝ ስላለ ግራ ገብቶኝ።

«መፍቀድማ እንዴት አድርጎ ይፈቅድላቸዋል? ፈቃድን ጥሰው ይሆናል እንጂ። ብቻ ‹ማህበርተኞች ከሆኑት መንግስታት መሀከል እንግሊዝና ፈረንሳይ ማስተረቂያ አሳብ አቅርበው አሳቡ የኢትዮጵያን አገር ከፍሎ ለኢጣሊያ የሚሰጥ ስለ ሆነ፥ የኛ መንግስት አልተቀበለውም› ይባላል። ይህ በኔ ግምት ማህበተኞች መከፋፈላቸውን በማህበርተኞች መሀከል እኛን የማይደግፉ መኖራቸውን የሚያሳይ ይመስለኛል » አሉና ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው፥

«ልክ ባርባ አመታቸው ተመልሰው መጡብን! አይገርምህም? ያድዋ ጦረንት ልክ አርባ አመቱ ነውኮ! » አሉኝ።

«አዎ፤ አርባ አመት ነው። ነገር ግን አሁን ያንጊዜ የደረሰው ውርደት እንዳይደርስባቸው ደህና ሆነው ተሰናድተው ስያመጡ አይቀሩም። »

«እውነትህን ነው፤ ደህና ሆነው ስለ ተሰናዱ አቅማቸው ከዚያን ጊዜው የበረታ መሆኑን ቢተማመኑ ነው ተመልሰው የመጡብን። እኛ ግን እንኩዋንስ ከዚያን ጊዜው ልንበረታ እንዲያውም ደከምናል! » አሉ።

«እንዴት? »

«ያድዋን ድል ባስገኙት የድሮ መሪዎችና በጦር ሰራዊታችወ መሀከል የነበረው የተቀራረበ ግንኙነት በዛሬዎቹ መሀከል የለም። የድሮ መሪዎች ተወልደው ባደጉበት አገር፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የገዥነት ወይም የመሪነት ስልጣናቸውን ከዘር የወረሱ በመሆናቸው ከመኩዋንንታቸውና ከጦር አለቆቻቸው ጋር እርስ በእርሳቸው ብቻ ሳይሆን አባት ላባት አያት ላያትና ታሪክ ለታሪክ ጭምር የሚተዋወቁ ስለ ነበሩ፥ ግንኙነታቸው የጠበቀ ነበር። ዛሬ ግን እኒያ በያገራቸው ከመኩዋንንቱ ከጦር አለቆችና በጠቅላላው ከጦር ሰራዊቱ ጋር በቅርብ ይተዋወቁ የነበሩት መሪዎች እየተነሱ፥ አዳዲስ መሪዎች ካዲስ አበባ ተልከው ስለ ተተኩ፥ በያገሩ ያለው የጦር ሰራዊት ‹ያውራዎቻችን ልጆች አውራዎቻችን› በሚላቸው መሪዎች ፈንታ የማያውቃቸውና የማያውቁት እንግዶች መሪዎቹ እንዲሆኑ በመደረጉ ቅር ያለው መሆኑ ይሰማል።

«እንደምታውቀው ከኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ውስጥ በጣም የሚበዛው ከውጭ ጠላት ጋር በጀግንነት ሲዋጋ የኖረው ከላይ እስከ ታች በየደረጃው ስጋ አብልቶ ጠጅ ለሚያጠጣው ለሚሾመውና ለሚሸልመው ጌታው ሲል ነው እንጂ ላገሩ ወይም ለባንዲራው ብሎ የሚዋጋ ቢኖር በጣም ጥቂት ይሆናል። በጥንቱ ልማድ የኢትዮጵያ ወታደር ታማኝነቱ ለጌታው እንጂ፤ ላገሩ አይደለም! ልብ አድርግ ይህን ክፉ ልማድ መደገፌ እንዳይመስልህ! ክፉ ልማድ መለወጥ የሚገባው መሆኑ መቸም የታወቀ ነው! ነገር ግን ክፉም ቢሆን ልማድ ሆኖ ስራት ሆኖ አጋእራንን እስከ ዛሬ በነፃነት ያቆያት ስለሆነ ታማኝነቱ ላገሩና ለባንዲራው የሆነ ዘመናዊ የጦር ሰራዊት አሰልጥኖ ሳይተኩ የነበረውን ማድከም ወይም ማፍረስ ባዶ እጅ የሚያስቀር ስለሆነ ይህን ነው የጠላሁት። ዛሬ ያለንበት ሁኔታ፥ ከጥቂት ሽህ የክብር ዘበኞች በቀር ዘመናዊ የጦር ሰራዊት

ተሰናድቶ ሳይተካ የጥንቱ የደከመበት ነው። ለዚህ ነው፤ ‹እንኩዋንስ ከጥንቱ ልንበረታ እንዲያውም ደከምናል› ያልሁህ » አሉ።

«ብቻኮ ዘመናዊ የጦር ሰራዊት ለማሰልተን አሁን እንዳሉት በክብር ዘበኞች ተጀምሮ ነበር። ሆለታም የጦር መኮንኖች በብዛት ይሰለጥናሉ ይባላል። ደግሞ ኢትዮጵያ የአለም መንግስታት ማህበር አባል እስከ ሆነች ድረስ ጠላት ሊያጠቃት እንዳማይችል ፅኑ እምነት ስለ ነበረ ይመስለኛል፤ የጦር ሰራዊቱን በሙሉ ከጥንታዊው ወደ ዘመናዊው ለመለወጥ መንግስት ያልቸኮለበት » አልሁዋቸው።

«የቸልተኛነት ይሁን ወይም ያቅም ማነስ ወይም ሌላ ምክንያቱን ስላማላውቀው ልነግርህ አልችልም። ብቻ መተኪያውን ሳናሰናዳ፥ የጥንቱን ስራት እያፈረስን በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ መሆናችንን ነው ልነግርህ የፈለግሁ። የሆነ ሆኖ አሁን እሱን እንተውና የሄድህለትን ስራ ትተህ እንድትመጣ ለማድረግ የተገደድሁበትን ምክንያት ልንገርህ » ብለው ወደ ተጠራሁበት ጉዳይ ተመለስን።

«ቅድም እንዳልሁህ፥ ራስ አስጠርተውኝ ካሁን ጀምሮ ህዝቡን መስቀስቀስ አስፈላጊ መሆኑን ከተስማማን በሁዋላ የሳቸው አሳብ እኛ እዚህ ትምርት ቤት ትያትር አዘጋጅተን እሳቸው፥ መኩውንንቱንና የጦር አለቆችን፥ እንዲሁም ከከተማው ነዋሪዎች የታወቁትን ሰዎች ጠርተው እግቢ እንዲታ ይሁለተኛ የሚያነቃቃ ንግግር እየተዘጋጀ፥ ህዝብ በሚሰበስባቸው ቦታዎች እንዲነገር ነው። ስለዚህ የጠራሁህ፥ ከመሀከላችን ካሁን ቀደም ካዲስ አበባ ትያትር ሰርተህ ያሳየህ አንተ ስለ ሆንህ ራስ የጣሉብኝን ከባድ አደራ ባንተ ላይ ለመጣል ነው » አሉ። እውነትም፣ እንኩዋንስ ስራው ወሬው ከባድ ስለ ነበረ ከብዶኝ አንገቴን ደፍቼ ቆይቼ አልሁና፥

«ለመሆኑ ትያትር አዘጋጅተን አስጠንተን ለማሳየት የሚበቃ ጊዜ ይኖረናል? »

«ጊዜውስ አጭር ነው፤ ከሚመጣው ወር (መስከረም) መጨረሻ በፊት መታየት ይኖርበታል፤ ብቻ በኔ አሳብ አዲስ አበባ ማጀስቲክ ሆቴል የታየውን

ትያትር አሁን ለተፈጠረው ሁኔታ እንዲስማማ አድርጎ ማሻሻል የተቻለ እንደሆነ ባለን አጭር ጊዜ ውስጥ ለማሳየት የሚደርስ ይመስለኛል፤ እንዲህ ማድረግ አይቻልም? »

«አዲስ አበባ የታየው ትያትር ፅሁፍ በጄ ስላለ፥ እስቲ አሁን ለተፈጠረው ሁኔታ እንዲስማማ አድርጌ ማሻሻል እችል እንደሆነ ዛሬ አይቸው ነገር ልንገርዎና ከዚያ በሁዋላ ስለምናደርገው እንነጋገር » ብያቸው ተሰነባበትን።

እውነትም አቶ ወልደ ጊዮርጊስ እንዳሉት አዲስ አበባ ማጀስቲክ ሆቴል የታየው «ያበሻና የወደሁውላ ጋብቻ » የተባለ ትያትር የመጨረሻው ክፍል ያጥራል እንጂ በጊዜው ለተፈጠረው ሁኔታ የሚስማማ ሆኖ አገኘሁት።

ከዚያ ረዥም ትያትር የሚበዛ፥ «አበሻና ወደ ሁዋላ » ተዋደው ፍቅራቸውን በግጥምና በልዩ ልዩ የፍቅር መግለጫዎች ሲገላለፁ ከዚያ እንዲጋቡ ወስነው ከጋብቻ በፊት የሚደረገው ስነ ስራት ተፈፅሞ፥ በዘፈን በደስታና በሆታ ሲጋቡ ከዚያ በጋብቻ ኑሮዋቸው ወደ ሁዋላ ያበሻን ሀብትና ንብረት እየሸጠ መስከሪያና መደሰቻ አድርጎ ጨርሶ እሷ ደህይታ፥ አይነ በሽተኛ ሆና ስታለቅስ የሚታይበት ነበር። በመጨረሻው ክፍል አበሻን፥ ከጥንት ጀምሮ የሚያውቃት አቶ ‹አእምሮ› የተባለ አስተዋይ ሽማግሌ ልጆችዋን ሰብስቦ እናታቸው እድኒያ ስትንገላታ ዝም ብለው በመመልከታቸው ወቅሶ ከወደሁዋላ እንዲያለያይዋት የመከራቸውና ያበሻ ልጆች ባንድነት ሆነው ወደ ሁዋላ እናታቸውን በሰላም አልፈታም ስላለ እሱን ገድለው እናታቸውን ነፃ ሲያወጡ ደስታ ችፈራ ቀረርቶና ፉከራ ይሆናል። ይህ የመጨረሻው ክፍል ከማጠሩ በቀር፥ «በወደሁዋላ » ፈንታ «ፋሽስት ኢጣሊያን » ተክተን እንዲስማማ የማሻሻያ ለውጦች ተደርገውለት ለታሰበው ስራ ሊሆን እንደሚችል ላቶ ወልደ ጊዮርጊስ ነገርሁዋቸው። ወዲያው ከማሻሻያው ጋር ተባዝቶ የሚሰሩት ልጆች እንዲያጠኑት ተሰጣና ልጆቹ ያን ሲያጠኑ፥ እኔ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለዚኢያ ተጭማሪ የሚሆን አጠር ያለ ትያትር አዘጋጅቼ አደረስሁ። መቸም ቀስቅሶ ለማሽለልና ለማስፎከር ያክል የሚበቃ ከመሆን አልፎ በኪኢነት መልኩ ሲታይ ‹ከትያትር ተራ ገብቶ የሚቆጠር ነበር›

ለማለት አያስደፍርም። ያዲሱ ትያትር የታሪክ ንድፍ ባጭሩ እንደሚከተለው ነበር።

አንድ የፈረንጅ አገር ንጉስ፥ ባገሩና በኢትዮጵያ መሀከል የወዳጅነት ግንኙነት እንዲመሰረት የሚሻ መሆኑን ገልፆ ለኢትዮጵያ፥ ንጉስ ይፅፋል። የኢትዮጵያ ንጉስም አሳቡን በደስታ የተቀበለ መሆኑን አስታውቆ፣ መልስ ይሰጣል። ከዚያ የፈረንጁ ንጉስ ግብዣ ቢደረግለት ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚወድ መሆኑን መሆኑን ለኢትዮጵያ ንጉስ ይፅፍና ተጋብዞ መጥቶ፣ ለንጉስ የሚገባ አቀባበል ተደርጎለት ኢትዮጵያን እየዞረ ሲያይ ሰንብቶ፥ ደስ ብሎት ይመለሳል። አገሩ ከደረሰ በሁዋላ ስለ ተደረገለት የወዳጅነት አቀባበልና መስተንግዶ አመስግኖ በጉብኝቱ ጊዜ እንደ ተመለከተው፥ ኢትዮጵያ መሬትዋ ሰፊ፥ ህዝብዋ ጥቂት ሲሆን፥ የሱ አገር መሬቱ ትንሽ ህዝቡ ብዙ ሆኖ ብርቱ ችግር ስለ ገጠመው የኢትዮጵያ ንጉስ መልካም ፈቃድ ሆኖ ከሰፊ ሀገሩ አንድ ክፍል ከፍሎ ቢሰጠው መሬት የጠበበው ህዝቡን እዚያ አስፍሮ ወዲኢያው ኢትዮጵያንም በዘመናዊ ስልጣኔ ኢትዮጵያን በሙሉ በጦር ሀይል ለመያዝ የሚገደድ መሆኑ አስታውቆ ይፅፋል። የኢትዮጵያ ንጉስ፥ የፈረንጁ ንጉስ እንደ ወዳጅ ተጋብዞ መጥቶ ያገሩን መግቢያና መውጫ ካጠና በሁዋላ እንዲያ ያለ የክህደትና እብሪት መልእክት ስለ ላከበት ተገርሞ መኩዋንንቱንም የጦር አለቆችንም ሰብስቦ ስለ ደረሰው የፍልሚያ ጥሪ ሲነግራቸው ሁሉም ይቆጡና ለጦርነት የተዘጋጁ መሆናቸውን ለተፋላሚው ሳይውል ሳያድር እንዲጻፍለት ይነግሩታል። ከዚያ፥ የኢትዮጵያ ንጉስ «አንተ በዘመናዊ መሳሪያና በሰለጠነ ወታደርህ ብትመካ፥ እኔ እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባህር አሸዋ በበዛው የሰራዊቴ ጀግንነትና በእግዚአብሔር ሀይል ተማምኘ እጠብቃለሁ፤ ና » ብሎ ለፈርንጁ ንጉስ ይመልስለታል። ከዚያ ጦርነት ይሆንና ኢትዮጵያውያን ድል አድርገው፣ከ፣ እያቅራሩና እዬፈከሩ የማረኩትን፥ የጠላት ወታደርና መሳሪያ ከንጉሳቸው ፊት ሲያቀርቡ ይታያሉ።

ሁለት ትያትሮች እንዲሰሩ የተመረጡት ተማሪዎች በብርቱ ትጋት አጥንተውና በትምህርት ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ሲያለዝቡ ሰንብተው ከተገመተው ጊዜ በፊት እግዝቢ፥ በ«ሰንተራ ሜዳ » ስም በተሰየመው ሰፊና፥ ረዥም አዳራሽ ውስጥ አሳዩ።

ራስ እምሩ ከመኰዋንንቱና ከጦር አለቆች ሌላ፥ በከተማው የታወቁ ሰዎች፥ በንግድ፥ በሚሲዮንና በተለያዩ ስራዎች እዚያ ይኖሩ የነበሩት ጥቂት የውጭ ዜጎች እንዲሁም አዳራሹ እስከ ቻለ ድረስ ወታደሩ ተጠርቶ እንዲያይ አድርገው ስለ ነበረ፥ የተቀመጠው ተቀምጦ፥ የቆመው በግንቡ ዙሪያ ተደራርቦ ቆሞ አዳራሹን እስኪጨንቀው ሞልቶት ነበር። ትያትሮች ሲጀምሩ አዲስ አበባን ማጀስቲክ ሆቴል «ያበሻና የወደሁዋላ ጋብቻ » የተባለው ትያትር በታየ ጊዜ ለሱ መክፈቻ እንዲሆን አሰናድቼ ያስዘመርሁት መዝሙር ተዘመረ። ያ «ተነሱ ታጠቁ » የተባለው መዝሙር ከዚህ የሚከተለው ነበር።

«ተነሱ ታጠቁ፤ ኢትዮጵያን፥
እንጀምር ስራ በስመ አብ ብለን፥
ርቀው ሄደዋል፥ ጉዋደኞቻችን፥
እንድረስባቸው በጣም ተፋጥነን፥
አሁን በብርሃኑ ጨለማ ሳይሆን
ወደ ሁዋላ ቀርተን አውሬ እንዳይበላን፤
ኢትዮጵያ አገራችን ስለ ነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን »

«ምስጋና ይድረሰው ለሰማዩ ጌታ፥
ጠብቆ ላቆየን በሰላም በደስታ፥
ውድ ሀገራችንን ከብዙ ወስላታ፥
እንግዲህ እንጠንክር በጣም እንበርታ
እንዳናወላውል እንዳናመነታ
ህይወታችን ይለፍ ባንዲራችን ፈንታ፤
ኢትዮጵያ አገራችን ስለ ነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን »

«እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ ውዲቱ፥

በሶስቱ ቀለሞች የተሸለምሽቱ፥

ነፃነት የሚደፍር ቢመጣብሽ ብርቱ፥

ደማችን ይፈሳል አይቀርም በከንቱ፥

ላንቺ የማይረዳ ሳለ በህይወቱ፥

በረከትሽን ይንሳው እስከ እለተ ሞቱ፤

ኢትዮጵያ አገራችን ስለ ነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን። »

ሁለቱንም ትያትሮች ተመልካችሁ ሁሉ በጣም ነበር የወደዳቸው። ይልቁንም መጀመሪያ ያበሻ ልጆች ወደ ሁዋላ ገድለው ሲያቅራሩና ሲፎክሩ፥ በሁዋላ ከፈረንጁ ጠላት ጋር በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያውያን ድል አድርገው እያቅራሩና እየፎከሩ ምርኮዋቸውን በንጉሳቸው ፊት ሲያቀርቡ በተጫዋቾች ላይ ይታይ የነበረው ግለት በተመልካቾች ተጋብቶ ወኔያቸውን የቀሰቀሰ መሆኑ በግልፅ ይታይ ነበር። ከትያትር ተጫዋቾች አንድ ድምፃዊ ‹የነሲብ› ልጅ ምርኮኛውን እንደ ያዘ በሚሸጥ ድምፅ አቅራርቶ አቅራቶ መፎከር ሲጀምር ወዲያ ታች ያዳራሹን ጥግ ይዘው ከቆሙት ወታደሮች አንዱ የተቃጠለ ስሚዔቱን አፍኖ መያዝ አቅቶት፥

«አ - ሀ! ቡር -! አካኪ ዘራፍ! » ብሎ ጎራዴውን መዝዞ እያወናጨፈ ወደ ፊት ሲሮጥ ሁሉም ፊቱን ከትያትር ሰራተኞች ወደ ሱ አዞረ። ያ ወታደር የሚያብረቀርቅ ጎራዴውን እያወናጨፈ፥ ሮጦ ራስ በግንባር ከተቀመጡበት ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው እዚያ በግንባር ከተቀመጡት የውጭ ዜጎች አንዳንዶቹ - ነገሩ እንግዳ ስለ ሆነባቸው እንደ ሆነ አይታወቅም - ከተቀመጡበት ተፈንጥረው እየተነሱ ለመሸሽ ቃጥተው ነበር። ወዲያው ራስ ለጊዜው ተቆጥተው ወታደሩ ተይዞ እንዲቆይ ስላደረጉ ሰላም ሆነና ጭዋታው ቀጠለ። ነገር ግን ጭዋታውም ወደ መጨረሻው ደርሶ ስለ ነበረ እንዳለቀ ተይዞ የቆየው ወታደር እንዲለቀቅና እፊታቸው ቀርቦ እንዲፎክር ፈቅደውለት ፉከራውን ያንደቀድቀው ጀመር። እዬተን በረከከ እየተነሳ፥ ዙሪያ እየዞረ እየዘለለ፥ ቆሞ እንደ ባላውሌ እየተንዘረዘረ ሲፎክር በፊቱ ይወርድ የነበረው ላክ ከውስጡ

እየፈላ በራሱ ገንፍሎ ፊቱን የሚያጥለቀልቅ ውሀ እንጂ ላብ አይመስልም ነበር! ከዚያ ምን እንደሚፈልግ ሲጠየቅ፥ የሚጠይቀው ጠፍትቶ ዝም ብሎ ቆይቶ፥

«ገድዬ እፊትዎ የምሞትበት አንድ አዲስ ጠመንጃ ብቻ ነው የምፈልገው ራስ ሆይ፤ ለጌታዬ ሌላ የምፈልገው ነገር የለም! » አለ። ወዲያው አንድ ጠመንጃ ከሚያስፈልገው ጥይት ጋርና ሀያ ብር እንዲሸለም ታዝዞለት ደስ ብሎት ወደ ቦታው ተመለሰ። ከዚያ የውጭ ዜጎች እንዲሰናበቱ አደርጎ እነሱ ከወጡ በሁዋላ ለኢትዮጵያውያን ብቻ የሚነቃቃ ንግግር እኔ እንዳደርግ ታዝዤ ስለ ነበረ፥ ያሰናዳሁትን ንግግር አደረግሁ።

ያንለት በረዥሙ ያደረግሁትን ንግግር አሁን መለስ ብዬ ሳስታውሰው ይገርመኛል! ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ስለ ዘመናዊ መሳሪያ ሲነገር የሰማሁት እውነቱም ስህተቱም ባንድነት፥ የተደባለቀበት ወሬ በሙኡሉ እውነት መስሎኝ ያን እያስፋፋሁና እያጋነንሁ በድፍረት መናገር «የማያውቁ አፍረ አይጨነቁ » እንደሚሉት ስላላወቅሁ እንኩዋንስ እፍረት ሊሰማኝ የምናገረው ሁሉ እውነት ለመሆኑ ትንሽ የጥርጥር ምልክት አይታይብኝም ነበር! አዳራሹን የሞሉት ሰሚዎቹም የምናገረው እውነት መሆን አለመሆኑን ከመመርመር ይልቅ፥ - በንግግሩ ማማር ተማርከው ይሁን ወይም ከኔ የተሻለ የማያውቁ ስላልነበሩባቸው እንደ ሆነ አይታወቅም - ሁሉም የደስታና ያድናቆት ምልክት ነበር የሚታይባቸው።

በሙሉ አፍሪካ ከሚኖሩት አገሮች ሁሉ፥ ኢትዮጵያ ብቻ ወሰንዋ ታፍሮ፥ ነፃነትዋ ተከብሮ የኖረች በልጆችዋ ጀግንነት እንጂ በመሳሪያ ጥራት አለመሆኑ ኢትዮጵያውያ በመሳሪያችው ትራት እየተመኩ በየጊዜው የመጡባቸውን ጠላቶች ሁሉ በጦርና በጎራዴ ድል እየመቱ፥ መሳሪያቸውን ማርከው ውርደት እያከናነቡ ሲኢመልሱ የኖሩ መሆናቸውን ኢጣሊያ ራስዋ ከዚያ በፊት ከታንክና ካይሮፕላን በቀር በጊዜው በነበረው ዘመናዊ መሳሪያዋ እንደ ሌሎቹ ተመከታ ሰሀጢ ዶጋሊ መቀሌና አድዋ ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገቻቸው ጦርነቶች ድል ተመትታ፥ መሳሪያዋንና ሰዎችዋን አስማርካ የተመለሰች መሆንዋን ያን ሁሉ ካስረዳሁ በሁዋላ ታንክና አይሮፕላን ወሬያቸው

የሚያስፈራውን ያክል አለመሆናቸውን ለመግለፅ እያጋነንሁ ከተናገርሁት ትዝ የሚለኝ ከሞላ ጎደል እንደ ሚከተለው ነበር።

«ታንክ እንደ ኢትዮጵያ ተራራማ በሆነ፥ አገር ለሚደረግ ጦርነት የተሰራ መሳሪያ አይደለም። ታንክ ተራራ ወጥቶ፥ ገደል ወርዶ ሊዋጋ የማይችል እንደ ወይዘሮ ባልተደለደለ ጉርብጥብጥ መሬት ላይ የማይንቀሳቀስ ዘበናይ መሳሪያ ነው። አይሮፕላንም የጦርነት ግጥሚያ ሲሆን ለማስፈራራት እላይ ሆኖ ከማጉራራት በቀር፥ ወገኑን ጭምር እንዳይመታ፥ በምብ ለመጣል አይፈቀድለትም፤ በጥብቅ የተከለከለ ነው። ሁለተኛ የጠላቱን የጦር ሰራዊት ከወገኑ ሩቅ በሆነ ቦታ እሜዳ ላይ ሰፍሮ ካላገኘ ሊያጠቃ አይችልም። ሶስተኛ በጠመንጃ ይቅርና በሽጉጥ እንኩዋ ከተመታ ወይም ዝቅ ብሎ ሲበር ክንፉን የዛፍ ቅርንጫፍ ከነካው ሰለሊት እንደ በላው ሽክላ ተንኮታኩቶ የሚወድቅ ግብዝ ነገር ነው። ስለዚህ ዞሮ፥ ዞሮ፥ ጦርነቱን የሚወስነው ጀግነነት ስለ ሆነና ጀግንነትም ማንም የማይከፈላቸው የኢትዮጵያውያን የተፈጥሮ ሀበት ስለ ሆነ አሁንም እንደ ሁልጊዜው ድሉ የኢትዮጵያውያን እንደሚሆን አይጠረጠርም! » እያልሁ እንደዚያ እንደ ፎከረው ወታደር ፊቴ በላብ ባይታጠብም፥ ላብ ላብ እያለኝ ደረቴን ነፍቼ ስናገር ያይሮፕላንና የታንክን መልክ ብቻ ሳይህን ውስጠ ምስጢራቸውን ሁሉ አንድ ባንድ የማውቅ እመስል ነበር! የተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት ተማሪ በነበርሁ ጊዜ፥ የመጀመሪያው ይሁን ሁለተኛው አይሮፕላን መጥቶ ጃንሜዳ ሲያርፍ ብዙ ተማሪዎች እየሮጥን ሄደን እሜዳው ውስጥ እንዳንገባ ስለ ተከለከልን፥ በውጭ ቆመን አይሮፕላኑን ከሩቅ አይተን ተመልሰናል። እንግዲህ ያይሮፕላን እውቀቴ ያን ያክል ነው። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በሁዋላ እስከ ዘመቻው ድረስ ጎጃም በቆየሁበት ጊዜ አይሮፕላን የሚባል አይቼ አላውቅም። እንዲያውም የታንክንማ ከስሙ በቀር መልኩን እንኩዋን አንድ ቀንም አይቼ አላውቅ! ይሁን እንጂ ያደረግሁት ንግግር አላማውን ግሩም አድርጎ መታ! መኩዋንንቱም የጦር አለቆችና ወታደሩም ጠላታቸውን ድል እንደሚመቱ ሙሉ እምነት አድሮባቸው ያኔውኑ ሲቃ እንደ ያዛቸው ከሁኔታቸው ሁሉ ይታይ ነበር። ከዚያ በሁዋላ መስከረም 22 1928 አዲስ አበባ ወዲያው ተከታትሎ ደብረ ማርቆስ የጦርነት አዋጅ ታወጀ።

የከተት አዋጁ ከተነገረ በሁዋላ ደብረ ማርቆስ በግቢ፥ በገብያ ወይም በሌላ ሰው በርከት ብሎ በምገኝበት ቦታ ሁሉ ሲወራ የሚሰውማው ስለ ዘመቻው ሲደረግ የሚታየው ለዘመቻ የሚያስፈልገው ነገር ሆነ። ትምርት ቤት እንኩዋ ምንም ለስሙ ቢከፈት በዚያ ጊዜ ካስተማሪዎችም ከተማሪዎችም ስለ ትምርት የሚነጋገሩ አልነበሩም፤ ሁሉም የሚነጋገሩና የሚከራከሩ ስለ ጦርነቱ ነበር። ከመሸ በሁዋላ መጠጥ ቤቶች ወዳሉበት ወደ መልሀ ከተማ የተሄደ እንደ ሆነ እዚያ የሚሰማው በዘፈን ፈንታ «ሰንጎ መንጋ » «እረ ቸ በለው » ወይም እነሱን የመሰለ ወኔ የሚቀሰቅስ ጭዋታ ነበር። እንዲሁም ማታ ማታ በትምርት ቤታችን አቅራቢያ ከነበሩት የመኩዋንንት ሰፈሮች ባንዳንዶቹ ከዚያ በፊት ተሰምቶ የማያውቅ ቀረርቶና ፉከራ ይሰማ ስለ ነበረ፥ ብዙዎቻችን እደጅ ቁጭ እያልን ያን ቀረርቶና ፉከራ ስንሰማ ማምሸት እንወድ ነበር።

የከተማው ብቻ ሳይሆን የባላገሩ ዘማች፥ ለጠመንጃው ጥይት ለሌለው ጥይት ሊገዛ ድንኩዋን የሌለው ለድንኩዋኑ አቡጀዲድ ሊገዛ፥ ለስንቁና ለድንኩዋኑ መጫኛ የሌለው በቅሎ ወይም፥ አህያ ሊገዛ በያካባቢው ወደ ደብረ ማርቆስ መጥቶ፥ በየሱቁና በየገብያው ሲጣደፍ የሚታየው ሁሉ ወደ ሞት ሳይሆን ደስ ወደሚያሰኝ የጭዋታ ቦታ ለመሄድ የሚሽቀዳደም ይመስል ነበር።

ታዲያ በወጣሁ ቁጥር ያን፥ ጠቅላላ የህዝብ እንቅስቃሴ አይቼ ተመልሼ ወይም ማታ ከቤቴ ደጅ ተቀምጬ ባካባቢዬ ከመኩዋንንቱ ሰፈር የሚሰማማውን ቀረርቶና ፉከራ ስሰማ ቆይቼ ገብቼ ስተኛ ያ፥ ለዘመቻ የሚያስፈልጉትን ነገሩች ለመግዛት ሲሽቀዳደም ያየሁት ሁሉ ያ፥ ሲያቅራራና ሲፎክር የሰማሁት ሁሉ፥ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ወደ ጦርነቱ ሲጉዋዝ እዚያ ከጠላት ጋር ገጥሞ ሲዋጋ ሲኢገድል ሲሞት፥ ቅስሎ፥ ሲጨነቅ፥ ስእሉ ይታየኝና መንፈሴ እረፍት አጥቶ እየተወራጨሁ ስነሳ፥ ተመልሼ ስተኛ ቆይቼ «ልዝመት ወይስ ልቅር? » እላለሁ። ለዚህ ጥያቄ በቀላሉ መልስ ለማግኘት አልቻልሁም። ካንድ ወገን ጭፍራ የሌለኝ ነጠላ ሰው ብቻዬን ዘምቼ በጦርነቱ ሜዳ ላይ ላደርገው ከምችለው ይልቅ ያስተማሪነት ስራዬን ስሰራ ብቆይ ላገር የበለጠ የሚጠቅም መሆኑ ይሰማኛል። ከሌላ ወገን፥ ያ ሁሉ እንዲሁ በተለምዶ ወይም «ሀይማኖር የሚያስለውጥ ርስት የሚነቅልና ነፃነት አሳጥቶ እንደ ባሪያ የሚገዛ ጠላት መጣብህ » ተብሎ የተነገረውን እንዲሁ በጭፍኑ አምኖ

ለመዋጋት ሲዘምት እኔ የነፃነትን፥ ትርጉም ከብዙዎቹ የተሻለ የማውቀው ወደ ሁዋላ መቅረት የማይገባ መስሎ ይሰማኛል። ይልቁንም ትያትር ያሳየን እለት ወኔ በሚቀሰቅስ ንግግር የሌሎችን ለጦርነት ታጥቀው እንዴንሱ አደፋፍሬ እነሱ ታጥቀው ሊዋጉ የኔን ወደ ሁዋላ መቅረት ሳስብ በልጅነቴ ጎበዛዝት በርከት ብለው በሚገኙባቸው የድግስ ቤቶች ስለ ፈሪ፥ «እሽረረ » ግጥም እየገጠሙ ሲጫወቱ እስማቸው ከነበሩት ግጥሞች አንዳንዶቹ ትዝ ሲሉኝ ያን ጊዜ በኔ ላይ እንደ ገጠሙዋቸው ሁሉ እረፍት ይሰማኛል። ከኒያ የ«እሽረረ » ግጥሞች ትዝ ያሉኝ የሚከተሉት ናቸው።

«የማይመጣ መስሎት እያለ ሲያቅራራ ‹ጎራው ና፥ ጎራው ና›

ይመስለን ነበረ ልቡ ሙሉ ጅግና፤

ሆድ ቁርጠት አመመው፥ የጎራውን መምጣት ከመስማቱ ገና፥

ለካስ አሞት የለሽ ፈሪ ኖሮዋልና! »

«አብረን ልንሰለፍ እሱ ምሎ ነበር፤ እኛንም አምሉ፥

ማየቱን ፈራና መሬት ጢሳ ስትነድ፥ በጥይት ቃጠሎ፥

እንደ ባቄላ አሹቅ፥ ቀረ ሹልክ ብሎ! »

«ባምስት ፈጅ እንካቦ ጠላውን ከልብሶ፥

ተነስቶ ሲፎክር ግንባሩን ከስክሶ አይኑን ደም አጉርሶ

ጀግና መስሎን ነበር ጠላት አሽባሪ ምሽጉን ጣጥሶ፤

‹ጦር መጣብህ!› ቢሉት አእምሮው ተቃውሶ

ሆዱኡ እየተንጉዋጉዋ እንደ ጠጣ ኮሶ

ተሸሽገ እማጀት የናቱን ነት ለብሶ! »

«ምን ያለው ፈሪ ነው ምን ያለው ወራዳ፥

እኛን ገፍቶ ሰዶ ወደ ጦሩ ሜዳ

እሱ ተሸሽገ ገብቶ እናቱ ጉዋዳ! »

ያን ሁሉ ባሳቤ እያወጣሁ እያወረድሁ መወሰን አቅቶኝ ሁለት ቀናት ያህል ስቸገር ቆይቼ፥ በመጨረሻ ለመዝመት ቆረጥሁና እሳቸው ፈቅደው ራስ እምሩን እንዲያስፈቅዱልኝ አለቃየን፥ አቶ ወልደ ጊዮርጊስን ለመንሁዋቸው። መጀመሪያ እሳቸውም ራስም አሳቤን አልተቀበሉም ነበር። ሁዋላ ግን ብቀርም የመንፈስ እረፍት ስለሌለኝ ስራዬን በሙሉ ልብ ልሰራ የማልችል መሆኑን ላስረዳቸው ፈቅደውልኝ፤ ስንቅ ለማሰናዳት ከደብረ ማርቆስ ዳንግላ የሚሻል ስለ ነበርና ወዲያውም የዘመቻው መንገድ በዚያ ስለ ነበረ እዚያ ልቆያቸው ከራስ ተሰናብቼ ወደዚያ ለመሄድ አሰብሁ።

ከደብረ ማርቆስ ከመነሳቴ አንድ ቀን ቀድሞ ጤናው መንገሻ መጣ። እሱን እንደ ገና እስካየው ድረስ፥ የነገረኝን ህልም መጀመሪያ ከቁም ነገር ስላልፃፍሁት፥ ሁዋላም በሰነበትሁበት ግርግር ምክንያት ረስቸው ነበር። እሱን ሳይ ትዝ አለኝና ደነገጥሁ፤ እንዲያውም ጤናውን ፈራሁት።

«ከየት መጣህ? » አልሁት።

«ዛሬ ከዚሁ ከከተማ ነው፤ ካገውምድር ትናንት መጥቼ እዚህ እዘመድ ቤት አደርሁ። »

«ካገው ምድር ለምን ጉዳይ መጣህ? »

«ለዘመቻ ከመነሳትህ በፊት መጥቼ አይሀለሁ! ብዬህ አልነበረም? ለዚያ ነው የመጣሁ » አለ፤ ለመሄድ በመሰናዳት ላይ መሆኔን ሰምቶ ኖሮ፤ ያሸሙር ፈገግታ በፊቱ እየታየ።

ምሳ አብረን ከበላን በሁዋላ ትንሽ ስንጫወት እንደ ቆየን ከኔ ጋር ለመዝመት መወሰኑን ነገረኝ። መጀመሪያ እውነት አልመሰለኝም፤ የሚቀልድ መሰሎኝ ነበር። ሁዋላ እውነቱን መሆኑን ስረዳ ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየፈጠርሁ አሳቡን ለማስለወጥ ያደረግሁት መከራ፥ ከኔ ጋር መሄዱን ያልፈቀድሁ አስመስሎ አሳይቶት ቅር አለውና ከኔ ጋር ባይሆን ከሌሎች ጋር መሄዱ የማይቀር መሆኑን ነገረኝ። እኔም ቅር ያለው መሆኑን ሳይ፥ እንዲቀር

ለማሳመን ነበር እንጂ ማስረጃ ምክንያቶችን ያቀረብሁለት የማይቀር ከሆነ ከኔ ጋር ቢሄድ እንዲያውም ብርቱ ድጋፍ ስለሚሆነኝ ደስታውን የማልችለው መሆኔን አረጋግጨለት አብረን ልንዘምት ተስማማን። እንዲሁም ከዚያ በፊት አዋጁ ተነግሮ የኔ መዝመት እንደ ታወቀ ያከስቴ የወይዘሮ ይታከቱ ቦጋለ ልጅ፥ ‹ገላው ተገኘ› የሚባለው ካስራ ስድስት አመት የማይበልጠው ልጅዋ ካልዘመትሁ ብሎ አስቸግሮዋት ኖሮ፥ ጠፍቶ ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር እንዳይሄድባት ሰግታ ከኔ ጋር እንዲዘምት አጥብቃ ስለ ለመነችኝ ደስ ሳይለኝ ተቀበልሁ። ሶስተኛ ከተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ከወጣሁ ጀምሮ አራት አመት ሙሉ አብሮኝ የኖረው ‹ዘሪሁን ወጋየሁ‹ መቸም ከኔ የማይለይ አብሮኝ ዘማች መሆኑን አስቀድሜ አውቅ ነበር። ስለዚህ ከኔ ጋር አራት ዘማቾች ሆነን፥ ራስ እምሩ ከደብረ ማርቆስ ከመነሳታቸው ቀደም ብለን ወደ ዳንግላ ሄድን። ዳንግላ ከደረስን በኋላ ደግሞ አንድ ሌላ ዘሪሁን የተባለ ረዥም ወጣት (ያባቱን ስም ረስቸዋለሁ) መጥቶ የጌታ አደረልኝ። ያን ሁዋላ የመጣውን ዘሪሁን ፊት ከነበረው ዘሪሁን ለመለየት «ረዥም ዘሪሁን፥ አጭር ዘሪሁን » እንዲባሉ እነሱም እኛም ተስማማን። በመጨረሻ አቶ ‹ዘውዴ ወልደ ተክሌ› መጥቶ ከኛ ጋር ተጨመረ። አቶ ዘውዴ ባቶ ህለተወርቅ እሸቴ ውስጥ ባቸፈር ክፍል ግብግቢት (ደንገል - በር) ለሚባለው ኬላ የጉምሩክ ሹም ነበር። እኔ ልጁን ክርስትና አንስቼ አበ ልጁ ነኝ። ከዘመቻ የማይቀርበትን ልዩ ምክንያት ላቶ ህለተ ወርቅ ገልፆላቸው ምንም እንኩዋ እሳቸው ዘማች ቢሆኑ ከኔ፥ ጋር እንዲዘምት ስለ ፈቀዱለት ነበር ወደኔ የመጣ። ስለዚህ ዳንግላ ስንደርስ፥ ዘማቾች ከኔ ጋር ስድስት ሆንን ማለት ነው።

አቶ ዘውዴ ጤናውና እኔ፥ የየራሳችን ጠመንጃና ጥይት ነበረን። ለረዥም ዘሪሁንና ላጭር ዘሪሁን ሁለት ጠመንጃዎች ከሚያስፈልጋቸው ጥይት ጋር እኔ እዚያው ዳንግላ ገዛሁ። እንዲሁም አንድ መጠነኛ ሽራ ድንኩዋን ለራሴ፥ አንድ መጠነኛ አቡጀዲድ ድንኩዋን ላቶ ዘውዴና ለጤናው ሌላ አቡጀዲድ ድንኩዋን ለሁለቱ ዘሪሁኖችና ለገላው ገዛሁ። የኮርቻ በቅሎ ፊቱንም ስለ ነበረኝ፥ ለድንኩዋኖቻችንና ለስንቅ መጫኛዎች የሚሆኑ አንድ የበቅሎ አጋሰስና አንድ ስናር አህያ ገዛሁ። በዚያ ጊዜ ማናቸውም ነገር ርካሽ ስለ ነበር እኒያን የገዛሁዋቸውን ነገሮች ሁሉ ለመግዛትና ስንቅ ለማሰናዳት ብዙ ገንዘብ

አላወጣሁም። ለምሳሌ ለቁዋንጣ የምትሆን አንድ መሲና ላም የገዛ ቆዳ ምላሽ ባምስት ብር ነበር።

## ምዕራፍ አራት

# የዘመቻው ጉዞ

በ1928 ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት እስካደረገችበት ጊዜ ድረስ የጎጃም የጦር ሰራዊት ከሞላ ጎደል በሁለት ምድብ የተመደበ ነበር ማለት ይቻላል። አንደኛው ዋናው ምድብ ከላይ ከሻለቃው ወይም ከጠቅላይ ግዛት ሰጥቶ፥ ግዛት ላልሰጠው ወይም ግዛት መስጠት የማይችል ሲሆን እቤቱ ግብር እያበላ ልብሱንም መሳሪያውንም ችሎ የሚያኖረው ወታደር ነበር። በዚያ ምድብ ውስጥ ግዛት ከነበራቸው በቀር ለግብረ በላ ወታደሮች በዘመቻ ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ስንቅና ትጥቅ የሚችሉ ጌቶቻቸው ነበሩ።

በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኙት መደበኛ ስራቸው እርሻ፥ ወይም ሌላ ስራ ሆኖ ለገዢዎች ኩዳድ ከመኮደድ ቤት ከመስራት አጥር ከማጠር ወይም ከሌላ የጉልበት ስራ ነፃ ለመሆን በሻለቃው ወይም ከሻለቃው በታች ባሉት ታላላቅ አገረ ገዥዎች መዝገብ ገብተው የደንብ ብረት የሚይዙት ነበሩ። እኒያ የደንብ ብረት ያዦች ብረታቸውን እቤታቸው አስቀምጠ፥ ባመት አንድ ጊዜ የዘብ ተራቸውን እየተወጡ ዘመቻ ካልመጣ መደበኛ ስራቸውን (እርሻ፥ ወይም ሌላ ስራ) እየሰሩ የሚኖሩ ዘመቻ ሲመጣ ብቻ የሚዘምቱ «የዘመቻ ባለዳዎች » ነበሩ። ስንቃቸውን መሰነቁም ሆነ የስንቃቸውን መጫኛ እንደየአቅማቸው - በቅሎ ወይም አህያ - መግዛቱ የራሳቸው ጉዳይ ነው። ከነዚህ የጦር ሰራዊቱ ከተመደበባቸው ሁለት ምድቦች ሌላ፥ ሻለቃው ወይም ከበታቹ ያሉት ታላላቅ አገረ - ገዢዎች ለስንቅ ለድንኳን ወይም ለዘመቻ አስፈላጊዎች ለሆ፥ ለሌሎች ነገሮች መጫኛ፥ አጋሰሶችና ጫኞች የማይበቁዋቸው ሲሆኑ ባንድ ነጋድራስ የሚተዳደሩ ነጋዴዎች በገዛ አጋሰሶቻቸው ጭነው እንዲዘምቱ ይታዘዙ ነበር። ለስሙ ‹ዋጋ ይከፈላችኋል› ይባላሉ ግን መክፈሉ የማያጠራጥር ነው።

በ1928 በራስ እምሩ አዝማችነት ወደ ሽሬ ግንባር የዘመተው የጎጃም የጦር ሰራዊትም እንደዚያው እንደ ጥንቱ ከሻለቃው ጀምሮ እንደ የደረጃው የመኩዋንንቱ አሽከር የዘመቻ ባለዳ የሆነው ባላገርና ስንቅ ጫኙ ነጋዴ ነበር። ከዚያ ላይ የተጨመረው አዲስ ዘማች ‹ልጅ ግዛው ቡኔ› በተባሉ መኮንን የሚታዘዝ ከ800 -1000 አባሎች የነበሩበት የክብር ዘበኛ ጦር ነበር። በግምት ሰላሳ አምስት ሺህ ያክል ይሆናል ይባል ነበር። የያዘው መሳሪያም፥ ከክብር ዘበኛው በቀር እንዲዒሁ ከያይነቱ የተደበላለቀ ከመሆኑ ሌላ አብዛኛው፥ የማያስተማምን አሮጌ፥ ነበር። ባላገሩና ከተራው ወታደር የሚበዛው የያዘው ጠመንጃ ናስ ማሰር ውጅግራ፥ ወጨፎ ስናዲር መስኮብና እነሱን የመሳሰለ ጊዜው ያለፈበት መሳሪያ ነበር። ለዚያውም በቂ ጥይት የነበራቸው ጥቂት ይሆናሉ። መኩዋንንቱና ባለሙዋሎቻቸው ብቻ እንደ - መውዜር ዲሞትገር (ለሚትፊር) ለበን ያለ ጠመጃና በቂ ጥይት ነበራቸ። በመሳሪያ በኩል ከሁሉም የክብር ዘበኞች በጣም ይሻሉ ነበር። ያን ጊዜ አባሎች ከነበሩት መሀከል አንዱ አሁን እንደ ነገሩኝ፥ ጠመንጃቸው መውዜርና ለበን ነበር፤ በዚያ ላይ ስድስት መትረየሶችና አንድ ያይሮፕላን ማውረጃ ነበራቸው።

ከጎጃም የጦር ሰራዊት ሌላ፥ በደጃዝማች ‹አያሌው ብሩ› ይታዘዝ የነበረውም የሰሜን የጦር ሰራዊት በክቡር ራስ እምሩ ውስጥ እንዲዘምት ተደርጎ ስለ ነበረና የደጃዝማቹ ጦር አስር ሽህ ክል እንደሚሆን ይገመት ስለ ነበረ የሁለቱ መሪዎች የጦር ሰራዊት ባንድነት አርባ አምስት ሽህ ይሆን ነበር ማለት ነው። የጣሊያን የሰሜኑ ግንባር የጦር ሰራዊት አዛዥ የነበረው ማርሻል ፔትሮ በዶሊዮ ግን፥ «የኢትዮጵያ ጦርነት » (La Guerra di Ethiopia) በተባለው መፅሀፉ «የራስ እምሩና የደጃች አያሌው የጦር ሰራዊት ባንድ ላይ አምሳ ሽህ ይሆን ነበር » ብሎ ፅፏል።

በዚያን አንፃር ማርሻል ባዶሊዮ በተጠቀሰው መፅሀፉ እንደ ገለፀው በሽሬ ግንባር የተሰለፈው የጣሊያን የጦር ሰራዊት ካይሮፕላን ከታንክ ሌላ፥ አምስት ዲቪዥን (ክፍላተ - ጦር) እና አንድ ብርጌድ ነበር። ያ ሰራዊት 173 መሀከለኛና ቀላል መድፎች እንደ ነበሩ ማርሻሉ በዚያው መፅሀፉ ፅፏል። መቸም እያንዳንዱ አገር በዲቪዥኑ እና በብርጌዱ ውስጥ የሚደለድለው የሰው

ቁጥር የተለያዩ ስለሆነ በሽሬ ግንባር የተሰለፈው የጣሊያን አምስት ዲቪዥን እና አንድ ብርጌድ ሰራዊት በቁጥር ስንት ሰው እንደ ነበረ እርግጠኛ ማወቅ ያስቸግራል። ነገር ግን፥ ባጠቃላይ እንደ «ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ » (ENCYCLOPEDIAN BRITANICA) የጦር ሰራዊት አመዳደብ፥ ባንድ ዲቪዥን ውስጥ 17,000 – 20,000 ሰው፥ ባንድ ብርጌድ ውስጥ 6,000 – 7,000 ሰው ስለሚመደብ ዝቅተኛው ምድብ የሚያዝ ቢሆን እንኳዋ ማርሻ ባዶሊዮ የጦር ሰራዊት በድምሩ ከ90,000 (ከዘጠና ሺህ) ወታደር በላይ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ በሽሬ ግንባር የጣሊያን የጦር ሰራዊት በመሳሪያ ዓይነት፥ ጥራትና ብዛት ብቻ ሳይሆን በወታደር ብዛትም ከኢትዮያ ሰራዊት ብልጫ ነበረው ለማለት ያስደፍራል። ከዚያም ሌላ የሚያሳዝነውም የሚያስገርመውም ራስ እምሩ ገና ከጎጃም ከመነሳታቸው በፊት፥ የጣሊያን የጦር ሰራዊት ወሰኑን፥ መረብን አልፎ ትግራይ ውስጥ ምቹ ቦታዎች እየመረጠ ምሽጉን አጠንክሮ ሰርቶ ይጠብቅ ስለ ነበረ፥ ጦርነቱ የተደረገው በኒያ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንክረው በተሰሩት የጣሊያን ምሽጎች ላይ መሆኑ ነው። ያ ሁኔታ፥ ጣሊያኖችን ከመሳሪያቸውና ከሰዋቸው ብዛት ያላነሰ ወይም የበለጠ የጠቀማቸውን ያክል ኢትዮጵያውያንን የጎዳ መሆኑ የማይጠረጠር ነው። እንዲያ ያለው ሁኔታ፥ በሽሬ ግንባር ብቻ ሳይሆን በሌሎች የጦር ግንባሮችም የደረሰ ስለ መሆኑ ማርሻ ባዶሊዮ በተጠቀሰው መፅሀፉ እንዲህ ይላል።

«የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ተሰብስቦ እስኪንቀሳቀስ ረዥም ጊዜ በመውሰዱ ተጠቅመን በሙሶሊኒ ትእዛዝ መረብን ጥቅምት 3, 35 አድዋ ጥቅምት 6, 35 መቀሌን ህዳር 8, 35 አንድ ጥይት ሳይጮህብን ያዝን። ባጠቃላይም ያለብዙ ችግር ከትግራይ ብዙዎችን ክፍሎች (Nuona Parte de Tigrai) በቁጥጥራችን ውስጥ አደረግን »።

አሁን ከመስመሬ ወጥቼ ወደ ጠቅላላው የጦርነት ታሪክ በሚያመራው መንገድ በመግባቴ ይቅርታ ይደረግልኝና ወደ ጀመርሁት፥ ወደ ሽሬ ግንባር ልመለስ።

ክቡር ራስ እምሩ፥ ያን በምኑም በምኑ ካቅማቸው ጋር የማይመጣጠን የጠላት ሀይል ለመግጠም በጥቅምት ወር 1928 የመጀመሪያ ሳምንት ከደብረ ማርቆስ ተነስተው በዚያው ወር አጋማሽ አካባቢ (ቀኑን ረስቸዋለሁ) ዳንግላ ሲደርሱ ብላታ ህለተወርቅ እሸቴ፥ የጉምሩክ ጭፍሮቻቸውንና የከተማውን ህዝብ አሰልፈው ተቀበሉዋቸው። እኔና ከኔ ጋር የሚዘምቱ ጉዋደኞኖቼም ከሳቸው ጭፍሮች ጋር ተሰልፈን ነበር።

ራስ እድንኩዋናቸው ገብተ ትንሽ እንዳረፉ፥ የዳንግላንና ያካባቢውን ዘማች ሰልፍ እንዲመለከቱ ሲጠየቁ እኔን አስጠርተው ደብረ ማርቆስ ትያትር ያሳየን ዕለት ያደረግሁትን ንግግር ይዤው እንደ ሆነ፥ እዚያም ከሰልፉ በሁዋላ እንድደግመው ስለ ነገሩኝ ያረፍሁበት ቤት ከሰፈሩ አጠገብ በመሆኑ ሮጨ አመጣሁት። ከዚያ ሰራዊቱ ተሰልፎ በያለቃው እየተመራ በፊታቸው አልፎ ሲጨርስ ያ ያንለት መጥቶ ሰልፍ ያሳየውና አብሮዋቸው የመጣው ሰራዊት ባንድነት ተሰበሰበበት ከቁመቴ ባይበልጥ የማያንስ ረዥም ለበኔ አንግቼ ደብረ ማርቆስ ያደረግሁትን ወኔ የሚቀሰቅስ ንግግር አንድ ቃል ሳልጨምርበት ወይ ሳልቀንስበት እንዲሁ እንዳለ ደገምሁት። ልዩነት ቢኖር ደብረ ማርቆስ ስናገር የነበረኝ ድንፋታ፥ የነበረኝ ግለትና ላብ ላብ ማለቱ ያንለት አለመኖሩ ነው። ሆኖም ያ ንግግር ለኔ ፊት የሰጠኝን የጋለ ስሜት አይሰጠኝም እንጂ ሌሎችን አስፎከራቸው። እንዲያው ደብረ ማርቆስ የፎከረው አንድ ወታደር ሲሆን ዳንግላ ያንለት ስለፍ ካሳዩትም ከራስ ጋር ከመጡትም መሀከል ብዙ፥ ወታደሮችና መኩዋንንት የጀግንነት ስሜታቸውን ልብ በሚነኩ ቃላት እየገለፁ ሲፎክሩ ማየቱ እንዴት ልብ የሚሞላ ነበር! ድልን በጅ ያስጨበጠ ይመስል ነበር! ከፈከሩት መኩዋንንት አንዱ ድልን በጅ ያስጨበጠ ይመስል ነበር! ከፈከሩት መኩዋንንት አንዱ፥ «ያገሬ መሬት የጠላት መቃብር እንጂ፥ የጠላት ግዛት እንደማትሆን በራሴና ባሽከሮች ስም ቃል ለምድር ለሰማይ! » ብለው የሚሉትንና ሲፎክሩ በፊታቸው ላይ ሲነድ ይታይ የነበረውን የወኔ ስሜት ልረሳው አልችልም።

የራስ እምሩ ሰራዊት ከዳንግላ ባቸፈር በዱርቤቴና በደንገል በር አልፎ፥ ቤገምር ግዛት እስኪገባ ድረስ በየሰፈሩበት ቦታ አካባቢ የሚኖረው ዘማኦች

እየመጣ ሰልፍ ባሳየ ቁጥር፥ ረዥም ለበኔም እያነገትሁ ያን ረዥም ንግግሬን ስደግም አፌ፥ እንደ «አቡነ ዘበሰማያት » ለምዶት አይኔን ንግግሩ ወደ ተፃፈበት ወረቀት መመለሱን እንኩዋ ትቼ ነበር።

የቤገምድር እንደራሴ የነበሩት ደጃዝማች ወንድወሰን ካሳ ቀደም ብለው ያገሩን የጦር ሰራዊት ይዘው አባታቸው፥ ልኡል ራስ ካሳ ወደ ዘመቱበት የትግራይ ግንባር ሄደው ስለ ነበረ ክቡር ራስ እምሩ ጎንደር ሲደርሱ የተቀበሉዋቸው የቤገምድርና የሰሜን ጳጳስ አቡነ አብርሃምና አገር ለመጠበቅ ከዘመቻ የቀሩት መኩዋንንት ከነጭፍሮቻቸው ነበሩ።

ራስና ዘማች ሰራዊታቸው፥ ከጎንደር ተነስተው ጉዞዋቸውን ሲቀጥሉ አቡነ አብርሃምም ያንድ ይሁን የሁለት ቀን ጉዞ አብረው ተጉዘው ነበር። እንዲያውም «አብረው ለመዝመት ራስን ቢለምኑዋቸው ራስ ከሚዘምቱ ይልቅ ጎንደር ቆይተው ለዘማቹ ሰራዊት እንዲቀናው ፀሎት ቢያደርጉና ጦርነቱ መርዘሙ ስለማይቀር ስንቅ እየተሰናዳ ነጋዴ በኪራይ ወደ ጦሩ ግንባር እንዲያደርስ ቢያደርጉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን አሰረድተው ለስንቅ ማሰናጃ የሚሆን ገንዘብ ሰጥተው እንዲመለሱ አደረጉዋቸው » ብለው ራስና ጳጳሱ ሲነጋገሩ እዚኢያው የነበሩ ሰዎች ነገሩኝ። ጳጳሱ ገንዘብ ተቀብለው መመለሳቸው እርግጥ መሆኑ ወደ ፊት በሌላ ምዕራፍ ይታያል።

የሰሜንን ግዛት ከገባን በሁዋላ ተከዜን ‹በትክል ድንጋይ› በኩል ለመሻገር አፋፉን ወረድ ብለን እወገቡ ላይ ደረስን « ‹ትእዛዝ እስኪደርስዎ ባሉበት ይቆዩ› የሚል የራዲዮ መልእክት ለራስ ደረሳቸው » ተብሎ እዚያ ሰፍረን ሰነበትን። ታዲያ ከመስፈሪያው ጥበትና ከሰራዊቱ ብዛት የተነሳ ከመጠን ያለፈ መተፋፈግ ስለ ነበረ፥ የተቅማት ወረርሽኝ (በሽታ) በሰፈሩ ገብቶ ሰራዊቱን ክፉኛ ጎዳው። ደብረ ማርቆስ የነበሩትና በዘመቻው ግዚኤ ከሰራዊቱ ጋር የዘመቱት ግሪካዊ ሀኪም ቀን ብቻ ሳይሆን እስከ ማታ እየሰሩ፥ ጉዳቱን ለማቅለል ብርቱ ጥረት አድርገዋል። ነገር ግን በረዳቶችና በመድሀኒት እጥረት ምክንያት ርዳታቸው ለበሽተኛው ሁሉ ሊደርስ አልቻለም። ከዚያ ክፉ በሽታ ካመለጡት ጥቂት ሰዎች መሀከል እኔና ሰዎቼ ነበርን። ከዳንግላ ስንነሳ፥ አንድ የእንግሊዝ ቆንሲል ዘበኛ የነበሩ ሰው፥ ቆንስሉ ወደ ሀገራቸው ሲሄዱ

የሰጡዋቸውን አራት ጠርሙስ መራራ አረቄ (ፈርኔት) ሰጥተውኝ ስለ ነበረ ከዚያ አንዳንድ መለኪያ ከምግብ በሁዋላ እየጠጣን እሱ ረድቶን ይሁን ወይም በእድላችን እኛ ሰፈር በሽታው አልገባም። እንዲያ ባለ ችግር ከሰነበትን በሁዋላ፥ ፊት እንደ ታሰበው ተከዜን ‹በትክል ድንጋይ› በኩል መሻገራችን ቀርቶ፥ ላዩን ‹በለማለሞ› በኩል እንድንሻገር ስለ ተደረገ ወደዚያ ለመሄድ እንደ ገና ተመልሰን አፋፉን ወጥተን ወደ ደባት አመራን።

## ምዕራፍ አምስት

# ደባት

ሰራዊቱ ከሰነበቱበት ወጥቶ የደባትን ከተማ ወደ ግራ እየተወ አልፎ ተከዜ አፋፍ አቅራቢያ እስኪደርስ ተከዜ አፋፍ አቅራቢያ እስኪደርስ የተጉዋዘበት አገር በጠቅላላው ዱር የሚባል ነገር የማይታይበት ለጥ ያለ ሜዳ ነው።

በዚያ ሜዳ ላይ የራስ አጀብ ጥንታዊውን ያጀብ ስነ - ስራት ተከትሎ መጉዋዝ ሲጀምር ልዩ መስሎ ታየ፤ እንደ ያንለት አምሮ ታይቶ አያውቅም። ሜዳው ይሁን አጀቡን ያሳምረው ወይስ አጀቡ ሜዳውን አይታወቅም፤ ብቻ ግሩም ነበር!

እንደ ልማዱ ፊታውራሪ ጦር፥ ራስ ከሚሰፍሩበት ቀደም ብሎ ወደ ፊት መስፈር ስላለበት ጥዋቱን ቀድሞ ሄዶአል። ከፊታውራሪው ጦር በሁዋላ ራስ ሰፈር ድንኩዋን አስተክለው ግብር አሰናድተው የሚቆዩት ሹማምንት ከመሶበኞቻቸውና ከገንቦኞቻቸው ጋር ቀድመው ሄደዋል። ደጀኑ ጦርም ራስ ከሚሰፍሩበት ራቅ ብሎ ወደ ሁዋላ መስፈር ስላለበት ገና አልደረሰም፤ ወደ ሁዋላ ነበር። ስለዚህ ያ ወደ ፊትም ወደ ሁዋላም አይን ሊደርስ እስከሚችልበት ድረስ ሜዳውን አሳምሮት የሚታየው የራስ አጃቢ ሰራዊት ብቻ ነበር!

የፊት አጃቢው ባለብረት ሰራዊት ግንባሩን ይዞ ይጉዋዝ ነበር። ከሱ በሁዋላ ማለፊያ ፈረሶችና ማለፊያ ፈረሶችና ማለፊያ በቅሎዎች እንደ ተጫኑ መሬት በሚጠርግ ባለ ልዩ ልዩ ቀለም ቀሚስ አሸብርቀው ይሳቡ ነበር። ከነሱ በሁዋላ አንጋቾች ባለሙዋሎችና የልፍኝ አሽከሮች ምርጥ ምርጥ መሳሪያዎችን እያነገቱ ራስን ከብበው ያጅቡ ነበር። ከዚያ ራስ ጥልፍ ዕቃ በተጫነች ረዥም በቅሎዋቸው ላይ ተቀምጠው ከመኩዋንንቱም ከባለሙዋሎቻቸውም አንዳንዶቹን በተራ እያስጠሩ፥ - ፊታቸውን ተመልክቶ መገመት የሚቻለውን ያክል - ካንዱ ጋር ቁም ነገር እየተነጋገሩ ከሌላው ጋር ተራ ጨዋታ እየተጫወቱና እየተሳሳቁ ይሄዱ ነበር። ከራስ በሁዋላ ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ማለፊያ መሳሪያዎቻቸውን ባለ ልዩ ልዩ ቀለም ቀሚስ እያለበሱ ይዘው ይከተሉ ነበር። ከጋሻ ጃግሬዎች በሁዋላ፥ መኩዋንንቱ በየበቅሎዋቸው እየተቀመጡ እንደ የማእረጋቸው የቅደም ተከተል ተራቸውን ይዘው ይጉዋዙ ነበር። ከመኩዋንንቱ በሁዋላ፥ ባጀብ ውስጥ የተመደበ ቦታ የሌለው ወታደር ባለ ብረቱ ጀሌው የጫነው፥ ያልጫነው ሁሉም ባንድ ላይ ይጥመለመል ነበር።

ያን ሁሉ ሰራዊት ታጃቢውንም አጃቢውንም ባንድነት ጥሩንበኞች እንቢልተኞች፥ መልከተኞችና ነጋሪት መቺዎች መሳሪያቸውን አስተባብረው በጉዞ ሙዚቃ እያጫወቱና እያስደሰቱ ጉዞው በመቀጠል ላይ እንዳለ ከሩቅ የሚሰማ የብቸኛ ንብ «ህሞታ » የመሰለ ድምፅ ይሰማ ጀመር። ያን ጊዜ የሁሉም ጆሮ ከሙዚቃውና ከጭዋታው ወዳዲሱ ድምፅ ተመለሰ። ያ ድምፅ እየቆየ እየጎላ እየጎላ ሲሄድ ያይሮፕላን ድምፅ መሆኑ ታወቀ። ወዲያው አይሮፕላንዋ ስትመታ መልከዋም ታየ። ወደ ላይ ከመራቅዋ የተነሳ ትንሽ አሞራ መስላ ነበር የምትታይ! ያቺ አይሮፕላን የራስ እምሩን ሰራዊት ለመፈለግ ሰፍሮ በሰነበተበት ቦታ ደርሳ ከዚያ ወጥቶ የሄደበትን መንገድ ስታገኝ ተከትላ መምጣትዋ ነበር።

ከዚያ «ተበታተኑ በል! ተበታተኑና ተኩሱባት በል! » የሚል ትእዛዝ ከራስ አጠገብ እንደ ተሰማ ያን ትእዛዝ ፊት ያሉት ለፋፊዎች ወደ ፊት፥ ሁዋላ ያሉት ወደ ሁዋላ እየተቀባበሉ አስተላለፉ። ያን ጊዜ፥ ያ ስነ - ስራቱን ተከትሎ ይጉዋዝ የነበረው ሰራዊት ብትንትን ብሎ ሁሉም ከያለበት መተኮስ ጀምሮ

እስኪቆም ድረስ እዚያ ሜዳ ላይ የጦርነት ግጥሚያ የተደረገ መስሎ ቆየ። የክብር ዘበኞች ያይሮፕላን ማውረጃ መድፍ ተኩዋሽም ተኩሱን ከጀመሩት ሰዎች መሀከል ነበር። መድፉን ተኩዋሽም ተኩሱን ከጀመሩት ሰዎች መሀከል ነበር። መድፉን ተኩዋሹ መደገኛውን ከመሬት ተክሎ፥ በዚያ ላይ መድፉን ጠመደና ሽቅብ አነጣጥሮ መጀመሪያ ሁለት «አመልካች ጥይቶች » (Tracer Bullets) አከታትሎ ተኮሰ። እኒያ አመልካች ጥይቶች በሰማይ ላይ የሚምዘገዘግ ጅራታም ኮከብ ረዥም ነጭ አመልማሎ የመሰለ ነገር በሁዋላቸው እየተጎተተ፥ አንዱ ባይሮፕላንዋ ሁዋላ ሁለተኛው በፊትዋ ጠፈሩን ሰንጥቀው ወጥተው እንደ ገና ወደ መሬት ተመልሰው እስኪወድቁ ሲታይ በጣም ያምሩ ነበር። ብቻ ሁለቱም ካይሮፕላንዋ ሩቅ ነበሩ፤ ኢላማቸውን ሳቱ ማለት ነው። ከዚያ መድፈኛው «ባገኝ ባጣውን » ጥቂት መምቻ ጥይቶች ከተኮሰ በሁዋላ መድፉን ተሰናከለበትና አንደኛውን አቆመ።

አይሮፕላንዋ ወደ ላይ በጣም ርቃ ትበር ስለ ነበረ፥ በሌላው ጠመንጃ የተተኮሰው ጥይት ሁሉ የደረሰባት አይመስልም። የሚበዛው ጠመንጃ አሮጌ የነበረ በመሆኑ በዚያ አሮጌ ጠመንጃ የተተኮሰው ጥይትማ ግማሽ መንገድ መድረሱም የማያጠራጥር ነበር! ስለዚህ ያቺ አይሮፕላን የያዘችውን ቀጥታ መስመር ትንሽ ሳታቃውስ ቀጥ ብላ የሰራዊቱ ፊታውራሪ ጦር እስከ ደረሰበት ቦታ ሄደች። ከዚያ ከሄደችበት መንገድ ተመልሳ እንደ ገና ወደ ደጀኑ ጦር ሄደች። እንዲያ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ እየተመላለሰች ዙሪያ እየዞረች የጦር ሰራዊታችንን ልክ ካጠናች በሁዋላ የትግራይን አቅጣጫ ይዛ ሄዳ እዚያው ቀረች።

ሰራዊቱ በተበታተነበት እንዳለ፥ ስለ አይሮፕላንዋ በየጉዋዱ ልዩ ልዩ ትችት ሲተች ዘለግ ያለ ሳትመለስ ስለ ቆየች ሁሉም ያጀብ ቦታ ቦታውን እንዲይዝና ጉዞውን እንዲቀጥል ተለፈፈ።

‹ይቺ አይሮፕላንዋ ቦምብ የምትተኩስ ናት› ይባል የለ? ታዲያ ዛሬ ያልተኮሰች ለምን ይሆን? » ባጠገቤ ከነበሩት ሰዎች አንዱ እኔን እያየ። ራሴ ፊት ሰልፍ በታየ ቁጥር ስለ አይሮፕላን ስናገር ውስጠ - ምስጢርዋን ሁሉ

የማውቅ እመስል ስለ ነበረ፥ ያነለት ቦምብ ያልጣለችበትን ምክንያትም የማውቅ መስሎት ነበር ይመስለኛል።

«ወቴ በሄደችበት በጥይት ሲያዋክባት መቸ ፋታ አገኘች! ለመተኮስ ትንሽ ቆም ብሎ ማነጣጠር ያስፈልጋል! » አለ ጉዋደኛው፤ እኔ ፍርጥም ብዬ ዝም ስላልሁ።

«ለመሆኑ ተመትታ ይሆን በሄደችበት የቀረች? » አለ ሶስተኛው።

«ብትመታማ እዚህ ነበር የምትወድቅ፤ ባትመታ ነው እንጂ! » አለ ለፊተኛው ጥያቄ መልስ የሰጠው ሰው።

«ምናልባት ሰልላ እንድትመለስ የተላከች ሰላይ ትሆናለች » ብዬ ትቻቸው ሄድሁ።

ከዚያ ጥዋት ቀድመው የሄዱት ሹማምት ሰፈር መርጠው የራስን ድንኳዋን አስተክለው በሚጠብቁበት ቦታ ለመድረስ ብዙ ጊዜ አልፈጀም። ሰፈሩ ወደ ትግራይ ለመሄድ ከዳባት ከተማ በስተቀኝ አለፍ ብሎ ፍንትው ባለ ሜዳ ላይ ነበር። በዚያ ሜዳ ላይ አንዱ ከሌላው በጣም እየተራራቁ በቅለው ከማታዩ ብቸኛና አጫጭር ግራሮች በቀር ሌላ የንጨት ምልክት የለም።

ሰራዊቱ እዚያ እንደ ደረሰ፥ የራስን ድንኩዋን እያየ፥ ያስፋፈሩን ስነ - ስራት ተከትሎ ወደ ፊት የሚሰፍረው ወደ ፊት በቀኝና በግራ የሚሰፍረው በቀኝና በግራ ወደ ሁዋላ የሚሰፍረው ወደ ሁዋላ ቦታ ቦታውን እየያዘ ሰፈረ።

የሰሜኑ አገረ ገዥ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ለዘመቻው ቀደም ብለው ወደ ተከዜ አፋፍ በመሄዳቸው ዳባት ስላልነበሩ፥ ወደ ሰፈር መጥተው ራስን የተቀበሉ አገር ጠባቂ ሆነው የቀሩት የደጃዝማች ታናሹ ልጃቸው «ፊታውራሪ መርሶ » ነበሩ። ፊታውራሪ መርሶ፥ የጦርነቱ ጊዜ የሚረዝም የሆነ እንደ ሆነ በየጊዜው ስንቅ እየተሰናዳ ለሰራዊቱ እንዲላክ ከራስ ጋር ሲነጋገሩ ቆይተው ለዚያ የሚሆን እንደ አቡነ አብርሃም ገንዘብ ተቀብለው መሄዳቸውን ሁዋላ ሰማሁ።

በማግስቱ ጥዋት ገና ፀሀይ ሳትወጣ ሰራዊቱ ቅሩስ ቀምሶ ጉዞውን ለመቀጠል ከሜዳው ኩበት ለቃቅሞ በየምድጃው እሳት ማንደድ እንደ ጀመረ ያይሮፕላን ድምፅ ተሰማ። ከዚያ፥

«እሳታችሁን እያጠፋችሁ፣ ተበታትናችሁ ያይሮፕላንዋ ላይ ተኩሱ! » የሚል ትእዛዝ ይለፈፍ ጀመር። ወዲያው እንደ ትናንቱ አንድ ብቻ ሳትሆን፥ ብዙ አይሮፕላኖች በሁለትም በሶስትም ቡድን እየሆኑ በግንባር - ቀደሙ (በፊታውራሪ) ጦር ሰፈር ላይ መጥተው በመሀከሉ (ራስ ባሉበት) ጦር ሰፈር አልፈው ምንም ሳያደርጉ እስከ ደጀኑ ጦር ሰፈር የመጨረሻ ዳርቻ ደረሱ። ድምፃቸው ባንድነት «የሰማይ ቁጣ » ይመስል ስለ ነበረ አይሮፕላን መሆናቸውን ባይነግርባቸው ወደ ላይ ከመራቃቸው የተነሳ፥ ትናንሽ አሞሮች እንጂ አይሮፕላኖች አይመስሉም ነበር። ሲመለሱ ከደጀኑ ጦር ሰፈር ጀምረው የቦምብ ነጎድጉዋድ እያወረዱ በመሀከሉ ጦር ሰፈር አልፈው እስከ ፊታውራሪ ጦር ሰፈር ደረሱ። እንደ ገና ከፊታውራሪው ጦር እስከ ደጀኑ ጦር! እንዲያ ከሁዋላ ወደ ፊት፥ ከፊት ወደ ሁዋላ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ እየተመላለሱ ያን ያላንዳች መጠለያ፥ በጠራ ሜዳ ላይ የተሰጣ ሰራዊት ሲደበድቡ አረፈዱ። መቸም የተኩሱ ነገር «ይህን ይመስል ነበር » ለማለት ምሳሌ ማግኘት አይቻልም። እንዲያው ባጭሩ «ከሰራዊቱ ጠመንጃ የያዘው ሁሉ ሳይተኩስ የቀረ አይመስልም » ቢባል ያ፥ ተኩስ ምን ይመስል እንደ ነበረ ለመገመት አሳብ ይሰጥ ይሞናል! ያን ያክል ከተተኮሰው ጥይት ጥቂቱ እንኩዋ፥ አይሮፕላኖች በሚበሩበት የሚደርስ ቢሆን ኖሮ አንዳቸው ባልተመለሱ፤ ሁሉም ባለቁ ነበር! ነገር ግን እንኩዋንስ በሚበዛው አሮጌ ለሱ፤ ሁሉም ባለቁ ነበር! ነገር ግን እንኩዋንስ በሚበዛ አሮጌ ጠምንጃ የተተኮሰው ጥይት በጥሩ ጠመንጃ የተተኮሰው ጥይትም ሊደርስ ከማይችልበት ሩቅ ከፍታ ስለ ነበረ ቦምብ የሚጥሉት፥ አንዳቸውንም ጉዳት ሳያገኛቸው እደረቅ ርፋድ ላይ ድምፃቸውን ባንድነት አስተባብተው እያንጎረጎሩና እየፎከሩ የትግራይን አቅጣጫ ይዘው በመጡበት መንገድ ተመልሰው ሄዱ።

ቦምብ ሲጥሉ ከመፍጠናቸውም ሌላ ተበታትነው ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ፥ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ይዋነቡ ስለ ነበረ፥ ትክክለኛ ቁጥራቸውን ለማወቅ

አስቸጋሪ ነበር። እኔ፥ «አስራ ሁለት » መስለውኝ ነበር። ሌሎች ያነጋገርሁዋቸው ሰዎች ግን ተስማምተው «አስራ ስምንት ናቸው » አሉኝ። ለኔ እንደ መሰለኝ «አስራ ሁለት » ቢሆኑም ጥቂት አደሉ፤ ብዙ ናቸው! ነገር ግን እንደ ብዛታቸው ሰፈሩን ሲደበድቡ እንደ ቆዩበት ረዥም ጊዜና እንዳወረዱት የቦምብ መአት ሰው ተርፎ የሚቀር አይመስልም ነበር። ነገር ግን ቦምብ ይጥሉ የነበረ ወደ ላይ በጣም ከፍ ብለው ከሩቅ ከመሆኑና ከመፍጠናቸው ሌላ ሰራዊቱም በዚያ ሰፊ ሜዳ ላይ ተበታትኖ ስለ ነበረ ያደረሱት ጉዳት የተፈራውን ያክል አልነበረም፤ መጠነኛ ነበረ። የሞቱት ጉዳት የተፈራውን ያክል አልነበረም፤ መጠነኛ ነበረ። የሞቱትን «አስራ አራት » ሰዎችና «አርባ » አጋሰሶች ነበሩ። የቆሰሉትን ሰዎች ቁጥር ረስቸዋለሁ። ብቻ ከሞቱት ሰዎች ቁጥር ቢበዛም ብዛቱ እጅግ የሚባል እንዳልነበረ ትዝ ይለኛል።

የባሰባቸው ቁስለኞች ወደ ግሪኩ ሀኪም ድንኩዋን እየተወሰዱ የህክምና ርዳታ ከተደረገላቸው በሁዋላ ሰራዊቱ ወዲያው ከሰፈረበት ቦታ ተነስቶ ጉዞውን ቀጥሎ የፎገራን፥ ሜዳ ሲጨርስ አስር ሰአት ግድም ቁጥቁዋጦና አንዳንድ ከፍ ያሉ ዛፎች የበቀሉበት ቦታ ስለ ተገኘ እዚያ ሰፈረ። ያነለት በሚበዛው ሰው ፊት ይታይ የነበረው የሀዘን የብስጭትና የቀቢፀ - ተስፋ ምልክት ነበር። እውነትም ጦርነት ገጥሞ ከጠላት በኩል አንድ እንኩዋ የተገደለና የቆስለ ሳያዩ ከወገን ብቻ የተገደለና የቆሰለ ማየት የሚያሳዝንም የሚያበሳጭም ነው! እኔንማ እንደ ሌሎች ሀዘንና ብስጭት ብቻ ሳይሆን ብርቱ እፍረት ጭምር ነበር የተሰማኝ! አይሮፕላንን ያን ያክል ዋጋ እያሳጣሁ ስሰብክ ኖሬ፥ ያንለት እኒያ አይሮፕላኖች እኔ ዋጋ እንዳሳጣሁዋቸው አለመሆናቸውን በሰሩት ስራ ሲያመሰክሩ አላዋቂነቴን ገለፀብኝና ቀና ብዬ የሰው ፊት ማየቱን እንኩዋ አፈርሁ።

ድንኩዋናችንን ተክለን እቃችንን ቦታ ቦታውን ካስያዝን በሁዋላ፥ እኔንና አጭሩ ዘሪሁንን እድንኩዋን ትተው ሌሎች ጉዋደኞቻችን ከብቶችን ይዘው ውሀ ወዳለበት ሄዱ። እኔ እድንኩዋኔ ውስጥ ዘሪሁን እውጭ እንዳለን ‹ፊታውራሪ ዳምጠው ተሰማ› መጡ። ፊታውራሪ ዳምጠው ከታላቁ አባታቸው ከፊታውራሪ ‹ተሰማ ጎሹ› ጀምረው በጎጃም ቤተ መንግስት

የታወቁና የተከበሩ ነበሩ። ክቡር አስ እምሩ የጎጃም አገረ ገዥ ጀምሮም ፊታውራሪ ዳምጠው ያንድ ትልቅ ወረዳ አገረ ገዥ በመሆናቸው ላይ ‹የወረገኑ ሹም› ጭምር ነበሩ። ስለዚህ፥ ከግል ወታደሮቻቸው ሌላ ለወረዳውና ለወረገኑ የደንብ ብረት ያዡችም አዝማች ስለ ነበሩ ከታላላቅ የጭፍራ አለቆች አንዱ ነበሩ። ከማውቃቸው የጎጃም መኰዋንንት ሁሉ ፊታውራሪ ዳምጠው ዘመናዊውን አስተሳሰብና አሰራር ይከተሉ ስለ ነበረ ከደብረ ማርቆስ ትምርት ቤት መምህራን ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ነበራቸው። እኔንም ወደ ደብረ ማርቆስ ከተዛወርሁበት ጊዜ ጀምሮ በጣም ያቀርቡኝ ነበር። ብዙ ጊዜ ወደ ቤታቸው እያስጠሩኝ አንዳንድ ጊዜም እኔ ቤት እየመጡ ስንጫወት ማምሸቱን ልማድ አድርገነው ነበር። በዘመቻው ጉዞ ላይ ግን የሳቸውን ድንኳዋን የሚከብበው - ሎሌውም ጭፍራውም - ስለሚበዛ ከኔ ጋር መነጋገር ሲፈልጉ ጋሻ ጃግሬያቸውን ብቻ አከትለው ወደኔ ድንኩዋን ነበር የሚመጡ። ያንለትም ጠመንጃቸውንና በነጭ እራፊ ቁዋንጣ የያዘ ጋሻ ጃግሬያቸው ተከትሎዋቸው መጥተው እድንኩዋን ያን ቁዋንጣ እየበላን ስንጫወት በርከት ያሉ ሰዎች እየተነጋገሩ ወደ ድንኩዋናችን ሲቀርቡ ተሰማን። እደጅ ያሉት የፊታውራሪ ጋሻ ጃግሬና ዘሪሁን ብቻ ናቸው፤ ድምፁ ግን ከሁለት ሰዎች ድምፅ የበዛ ነው። ፊታውራሪና እኔ ጭዋታችንን አቁመን ስናዳምጥ፥

«አንተ ያ ተማሪ የት ነው? » አለ አዲስ ከመጡት ሰዎች አንዱ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

«የቱ ተማሪ? » አለ ዘሪሁን።

«ያ ያንተ ጌታ »

ዘሪሁን አልመለሰም።

«የት አለ ነውኮ እምልህ! » አለ ሰውየው በቁጣ።

«እድንኩዋን ውስጥ ናቸው » አለ ዘሪሁን።

«ጥራው! »

ዘሪሁን አልተንቀሳቀሰም፤ ዝም ብሎ ተቀመጠ።

«አትጠራውም? » አለ ሰውየው፤ አሁንም ተቆጥቶ። ዘሪሁን ንቅንቅ አላለም።

«እስቲ ልውጣና ማን መሆኑን ልይ » ስነሳ፥

«አፈረህ ተቀመጥ፤ የሰከረ ሰው ይመስላል! » አሉ ፊታውራሪ።

«ወደሱ አልሄድም፤ እበር ቆሜ ለማየት ነው » ብያቸው ሽጉጤን እመንገድ አልጋየ ላይ ካኖርሁበት አንስቼ ታጥቄ፥ ድንኩዋኑን ገለጥ አደረግሁና ወጣሁ። እንዲያ አጥብቆ የሚፈልገኝ ልጅ ‹ዳኛቸው ተሰማ› ነበር።

ልጅ ዳኛቸው ተሰማ የፊት ‹ምን ያምር› የሚሉት አይነት አይሁን እንጂ ቁመቱ ዘለግ ያለ ውሀ ጠይም ጠጉረ ላዛ፥ ሽንጥና ወገቡ ሎጋ፥ በጠቅላላው ደስ የሚል የወንድ ቅርፅ ያለው፥ ወጣት መኮንን ነው። ትውውቃችን ተቀራርበን ለመጫወት ያክል ባይሆንም እንዲሁ በሩቁ እንተዋወቃለን። ጠመንጃውን የያዘ ጋሻ ጃግሬውና አራት ወይም አምስት የሚሆኑ ባለ ብረት ወታደሮች ተከትለውታል። እሱ ጥይት የሞላ ዝናሩን እላይ ረዥም ጎራዴውን ከታች አድርጎ ታጥቆ ያን ትጥቁንና ሎጋ ወገቡን ለማሳየት እንደሚፈልግ ሁሉ፥ ቀጭን ኩታውን ከታች ወደ ቀኝና ግራ ትከሻዎቹ መለስ አድርጎ ረዥም ዘንጉን በግራ እጁ ይዞ፥ እነዘሪሁን ከተቀመጡበት ራቅ ብሎ ቆሞዋል።

«እኔን ነው መሰለኝ የምትፈልግ ልጅ ዳኛቸው፤ ለምን ፈለግከኝ? » አልሁ ከድንኩዋኔ በር ቆሜ።

«ዛሬ ልፋረድህ ነው የመጣሁ! » አለ፤ በቀኝ እጁ የጎራዴውን ውላጋ ጨብጦ።

«ለምኑ? » አልሁ።

«ደሞ ለምኑ ይለኛልኮ! ‹አይሮፕላን እንኩዋንስ በጠመንጃ በሽጉጥ ይወድቃል› እያልህ ሰውን ሁሉ አታልለህ ማስፈጀትህ ጠፍቶህ ነው አሁን ለምኑ የምትለኝ? አንተ አታላይ ቀጣፊ! » አለ ጎራዴውን ነቅነቅ እያደረገ።

«አዎ፤ ‹እንኩዋንስ በጠመንጃ በሽጉጥም ከተመታ ይወድቃል› ብያለሁ፤ ግን አልተመታምኮ ልጅ ዳኛቸው! » አልሁት። እንዲያ ስል ለካስ ሳይታወቀኝ ፈገግ ብዬ ኖሮዋል።

«ጥርስህን ያርግፈውና ደሞ ‹ጥርስ አለኝ› ብለህ መሳቅህ ነው? በል አሁን ና ወዲህ! » አለ ጎራዴውን እየነቀነቀ።

«ለምን ነው የምመጣ? አልመጣም! አልሁት » ፈገግ እንዳልሁ። ፊታውራሪ ዳምተው እውስጥ ሆነው ሲስቁ እሰማቸዋለሁ።

«ካንተ ወይ ከኔ፥ ማን ወንድ እንደ ሆነ ዛሬ ይለይልናል! በል ና! » አለ አሁንም ጎራዴውን እየነቀነቀ።

«ታዲያ ወንድነታችንን ለማሳየት አንተና እኔ እዚህ ከመጋደል ያን ወንድነት እፊታችን ተሰልፎ በሚጠብቀን ጠላት ላይ ብናሳይ አይሻልም? አንተና እኔኮ ወንድማሞች ነን » አልሁት።

«ወንድማሞች! ደሞ አንተ ነህ የኔ ወንድም? እንዳንተ ያለ ወንድም የለኝም! » አለ የኔን ወንድምነት እየተፀየፈ ሁሉ ከፈንሩን አበላልጦ።

«የኔን ወንድምነት ካልፈለግህ፥ እኔም ያንተን ወንድምነት አልፈልግም ያንተን ወንድምነት እፀየፈዋለሁ! አሁን ሂድ ወግድ ከዚህ! ወግድ ብየሀለሁ! » አልሁ ለጀመሪያ ጊዜ ግልፍ አድርጎኝ፥ እጅጄን በሽጉጤ ላይ አደረግሁና። የድምፄን መለዋወጥ ሲሰሙ ፊታውራሪ ወጥተው መጡና እኔን ወደ ሁላቸው ገፍተው፥

«አንተ ዳኛቸው ዛሬ ደህና አይደለህም? በል አሁን ሂድ ከዚህ » አሉ።

«እኔ ጉዳየ ከሱ ጋር ነው፤ እርስዎን የሚያገባዎ አይደለምና አርፈው ይቀመጡ። እሱን ግን አሳየዋለሁ! » አለ የጎራዴውን ወሊጋ እንደ ጩበጠ እግሮቹን አፈራጦ ቆሞ።

«አዎ ታሳየዋለህ፤ ሞልፉጣ! እሱን ጎራዴህን መዝዘህ እዚህ እስክትደርስ ሶስት ጊዜ ይገድልሀል! » አሉት።

«የሱ ጥይት እንከዋንስ ሊገድለኝ አይነካኝም! » አለ። ያን ጊዜ ፊታውራሪ ነጥቀው የዘሪሁንን ሽመል ከጁ ነጠቁና፥

«ሂድ ወግድ ከዚህ በዚህ ዱላ ሳላበራይህ፥ አንተ ሰካራም! » አሉ የሚያበራዩበትን ዱላ እያሳዩ።

ልኡል ራስ ኃይሉ የጎጃም አገረ ገዥ በነበሩት ጊዜ ፊታውራሪ ዳምጠው ከታወቁት ታላላቅ መኩዋንንት አንዱ ሲሆኑ ልጅ ዳኛቸው የራስ የእልፍኝ አሽከር ሆነው አብረው የኖሩ ነበሩ። በክቡር (ሁዋላ ልኡል) ራስ እምሩ ጊዜም፥ ፊታውራሪ ያንድ ትልቅ ወረዳ አገረ ገዥ ከመሆናቸው በላይ ‹የወረገኑ› ሹም በመሆናቸው ለራስ የቅርብ ረዳትና ስለ ጎጃም ምክር ከሚሰጡት ታላላቅ መኩዋንንት አንዱ ነበሩ። ስለዚህ ልክ ዳኛቸው መቆጣታቸውን ሲያይ፥ ፈርቶዋቸው ይሁን ወይም አክብሮዋቸው በረድ ብሎ እጁን ከጎራዴው ውላጋ ላይ አወረደ። ወዲያው አብረውት ከነበሩት ሰዎች ፀና ፀና ያሉት እንደ መገላገልም እንደ ማባበልም እያደረጉ ይዘውት ሄዱ።

በማግስቱ ጥዋት፥ ደጃዝማች ‹ገሰሰ በለው› ሌሊቱን ጠፍተው ወደ አገራቸው ወደ ጎጃም መመለሳቸው ታወቀ። ልጅ ዳኛቸው ተሰማም ከሳቸው ጋር መመለሱን ሰማን።

## ምዕራፍ ስድስት

# ደባጉና

ለቁስለኞች ህክምና እንዲደረግላቸው አጋሰሶች የሞቱባቸው ሰዎች በካባቢው ካለው ባላገር ፈልገው እንዲገዙና ወዲያውም ደጃዝማች አያሌው

ብሩ የሚገኙበትን ለማጠያየቅ ቢያንስ ያንድ ቀን ውሎ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለ ተገኘ ውሎው እዚያው ሰራዊቱ ሰፍሮ ባደረበት ቁጥቋጦና አንዳንድ ዛፎች ባሉበት ቦታ እንዲደረግ ተወሰነ።

ደጃዝማች አያሌው ስለሚገኙበት ቦታ፥ የተጠየቁት ባላገሮች ከጥቂት ቀናት በፊት እዚያ አቅራቢያ ሰፍረው የነበር መሆናቸውንና ከዚያ ተነስተው ተከዜ አፋፍ መስፈራቸውን ከመስማታቸው በቀር የተከዜ አፋፍ ወንዙን በቁሙ ተከትሎ የሚሄድ ስለሆነ የት ቦታ እንደ ሰፈሩ የማያውቁ መሆናቸውን ተናገሩ።

ስለዚህ ራስ እኔን አስጠርተው ለደጃዝማች የፃፉላቸውን ወረቀት ሰጥተው ያሉበትን ፈልጌ ያን ወረቀት እንዳደርስላቸውና የሚሰጡኝን መልስ ይዤ ቶሎ እንድመለስ አዘዙኝ። ለደጃዝማች እንዲደስር በሰጡኝ ወረቀት የፃፉላቸው ሁለቱ የሚገናኙበትን ቦታ ቀን እንዲያስታውቁዋቸው መሆኑንም በቃል ገለፁልኝ።

ረፋድ ላይ ጤናውና ረዥሙ ዘርይሁን እኔና ገላው ከሰፈራችን ተነስተን የለማለሞን መንገድ ይዘን ስንገሰግስ፥ ከቀትር በሁዋላ ሰባት ሰአት ግድም ተከዜ አፋፍ ደረስን። እዚያ አንድ ትንሽ መንደር አጠገብ ጥቂት ሰዎች ተሰብስበው ስላየን ወደነሱ ሄደን ደጃዝማች አያሌው የሰፈሩበትን ቦታ እንዲያመለክቱን ብንጠይቃቸው መጀመሪያ በጥርጣሬ መልክ እስ - በሳቸው ከተያዩ በሁዋላ፥

«እኛ ደጃዝማች አያሌው የሰፈሩበትን የት እናውቃለን ጌቶች አሉ ከመሀከላቸው አንድ ሽምገል ያሉ ሰው።

«ለክፉ ነገር አይደለምኮ የደጃዝማችን ሰፈር የምንፈልገው ጌቶች፥ ይህን ከክቡር ራስ እምሩ የተፃፈላቸውን ወረቀት ልናደርስላቸው ነው » አልሁ ማህተም ከላይ የታተመበትን አንቨሎፕ ከኪሴ አውጥቼ እያሳየሁ። ከዚያ እስ - በሳቸው በሹክሹክታ ሲነጋናገሩ ትንሽ ቆዩና፥

«ያቺን መንገድ ሳትለቁ አፋፍ - ለአፋፍ ስትሄዱ ዘበኞቻቸውን ታገኛላችሁና እነሱ ይመሩዋችሁዋል » አሉ ሽማግሌው ሰው፥ መንገድዋን

በሽመላቸው እያሳዩ። «ብቻ - እኛ መንገዱን እንዳመለከትናችሁ እንዳትናገሩ አደራችሁ! » አሉ ሽማግሌው ቀጠሉና።

«ግዴለም አትስጉ፤ አንናገርም ብያቸው አመስግነን ዘወር ስንል «ያ ሮቢላው የራስ እምሩን ሰው ከፉኛ ጎዳው የሚባለው እውነት ነው?› አሉ። «የተፈራውን ያኽል አይደለም እንጂ መጉዳትስ ጐድቶዋል ነገር ግን ከሰው የበለጠ የጎዳ ከብቱን ነው » አልሁዋቸው።

«ይገርማል! የእድል ነገር ሆኖ ነው እንጂ የእኛን ጌታ ደጃዝማችን ዳባት ከከተማቸው ሲኖሩም ከዚያ ሰራዊታቸውን ይዘው ወጥተው እዚህ አካባቢ ሰፍረው ሲሰነብቱም እያለፈ ከመሄድ በቀር አንድ ቀን አስደንግጦአቸው አያውቅም » አሉ ሽማግሌው።

ከዚያ የለማለሞን መንገድ ወደ ቀኝ ትተን ወደ ግራ ባላገሮች ያሳዩንን ቀጭን መንገድ ይዘን አፋፍ ላፋፍ በግምት ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ሄድን፥

«ቁሙ! » የሚል ከፍተኛ የትእዛዝ ድምፅ ሰማን። ያዘዘንን ሰው ግን፥ ሁላችንም ዙሪያውን ባይናችን ፈልገን ልናየው አልቻልንም። ስለዚህ ምንም እንኩዋ እዚያ አካባቢ ዘበኞች መኖራቸውን ባላገሮች ቢነግሩን ያን ትእዛዝ ዘበኞች ይስጡን፥ ወይም ሌሎች ማወቅ ስላልቻልን ሰግተን እኔ ከበቅሎዬ ወርጄ የጐረሰ ጠምንጃዬን ከገላው ተቀብዬ ጤናውና ዘሪሁንም እንደ ኔ የጐረሰ ጠመንጃ ጠመንጃቸውን እንደ ያዙ ፈንጠር ፈንጠር ብለን ቀጥሎ የሚመጣውን ተጠንቅቀን እንጠብቅ ጀመር። ካዛዣችን ተጨማሪ ድምፅ ሳይመጣ፥ እኛም እንዲያ በስጋት ላይ እንዳለን ዘለግ ያለ ጊዜ ካለፈ በሁዋላ፥

«ሂድና ጠይቃቸው! » አለ እንደ ፊተኛው ጐርነን ያለ ድምፅ።

«ሰውየው ያውና እዚያ ዛፍ ውስጥ! » አለ ጤናው፤ ሁለተኛው ትእዛዝ ከመስጠቱ አንገቱን ዝቅ አይኑን ጭንቁር አድርጎ ወዳንድ ዛፍ ባገጩ እያመለከተ። ያ ሰው ከመንገዱ ጐን ትንሽ ራቅ ብላ በበቀለች ቅጠላም ዛፍ ላይ እንዳይታይና ቅጠሉን ለብሶ ጠመንጃውን ወደ መንገዱ ደግኖ ተቀምጦዋል።

ወዲያው እንዲጠይቀን የታዘዘው ሰው እመንገዱ ዳር ከነበረ ቁዋጥኝ ድንጋይ ጀርባ ከተሸሸገበት ወጥጦ ጠመንጃውን በፊቱ አስቀድሞ ወደኛ መንገድ ሲጀምር፥

«ትተኩሱና ከፉ ነገር ይደርስባችሁዋል፤ እኛ የክብር ጌታችን የደጃዝማች አያሌው ዘብ ጠባቂዎች ነን! » አለ እዛፉ ላይ የነበረው ሰው።

«እኛም ከክቡር ራስ እምሩ ይህን መልእክት ለክቡር ደጃዝማች አያሌው ብሩ እንድናደርስ የተላክን መላክተኞች ነን » አልሁ፤ መልእክት የያዘውን አንቨሎፕ ከኪሴ አውጥቼ ከሩቅ እንዲያዩት እያወለበለብሁ። ያልሁትን ሲሰሙና አንቬሎፑን ሲያዩ ጠመንጃውን በፊቱ አስቀድሞ ወደኛ መንገድ የጀመረው ሰው ወደ ትከሻው መልሶ አንግቶ እዛፍ ላይ ተቀመጠ ትእዛዝ ሲሰጥ የነበረው ሰውና ከሌላ ወገን በሌላ ዛፍ ላይ ቅጠል ለብሶ ተቀምጦ ሳናየው የቆየ ሌላ ሰውም እንዲህ ጠመንጃቸውን እያነገቱ ወርደው መጡ። ከዚያ ሰላምታ ተሰጣተን፥ ዳባት እሰፈራችን ላይ ስለ ደረሰው የቦምብ አደጋ ትንሽ ከተነጋገርን በሁዋላ ከሶስቱ አንዱ እየመራ ወስዶ ሁለተኛውን በር ከሚጠብቁት ዘበኞች ጋር አገናኘን፤ ከዚያም አንድ ሌላ ዘበኛ ወደ ደጃዝማች ሰፈር ወሰደን።

ደጃዝማች አያሌው የሰፈሩበት ቦታ ተከዜ አፋፍ ላይ እንደ መሆኑ ቁጥቁዋጦና በርከት ያሉ ዛፎች ያሉበት ነው። ስለዚህ ከሳቸው ሰፈር ራቅ ባለ ቁጥቁዋጦ ውስጥ እኛ ያላየነው የወታደር ሰፈር ኖሮ እንደሆነ እንጂ እኛ እንዳየነው፥ እዚያ እሳቸው በሰፈሩበት ላይ የነበሩት የመኩዋንንትና የወታደር ድንኩዋኖች ይህን ያህል ብዙ የሚባሉ አልነበሩም።

አጋፋሪው ደጃዝማች አያሌው ወደ ተቀመጡበት ድንኩዋን አስገብቶኝ እጅ ስነሳ እሳቸውና ደጃዝማች ‹ገብረ መድህን› የሚባሉ ከትግራይ የመጡ የልኡል ራስ ስዩም ታላቅ መኮንን ጐን ለጐን በተነጠፉ ድልዳሎች ላይ ተቀምጠው ነበር። በሁለቱም ፊት፥ ባንድ ጠረጴዛ ላይ ጠጅ የያዙ ብርሌዎች ተቀምጠዋል። ከራስ የተላከላቸውን በአንቬሎፕ የተደፈነ መልእክት ለደጃዝማች አያሌው ሰጥቻቸው አንብበው በጎናቸው እድልዳሉ ላይ ካስቀመጡት በሁዋላ፥

«ጠጅ አምጣለት » አሉት፥ ያስገባኝን አጋፋሪ።

«ጌታዬ ይቅርብኝ » አልሁ፥ እጅ ነስቼ።

«ለምን? »

«ጠጅ አልጠጣም »

«ብርዝም አትጠጣም? »

«ብርዝ እጠጣለሁ »

«ብርዝ አምጣለት » አሉና አጋፋሪው ሲመጣ፥

«ተቀመጥ » አሉኝ።

ድንኩዋኑ ከዳር እስከ ዳር ስጋጃ ምንጣፍ ግጥም ብሎ የተነጠፈበት ነበር። ይሁን እንጂ ጥይት ሙሉ ዝናሬንና ሽጉጤን እንደ ታጠቅሁ እግሬን አጣጥፌ እመሬት ላይ መቀመጥ አስቸጋሪ ስለ ነበረ፥ ቆሜ ብቆይ በወደድሁ ነበር። ነገር ግን ትእዛዛቸውን አለማክበር መስሎ ይታይብኝ ይሆናል ብዬ ፈርቼ በግድ እግሮቼን አጣጥፌ እምንጣፉ ላይ ተቀመጥሁ።

ለኔ የታዘዘው ብርዝ እስኪመጣ ድረስ እዚያ ድንኩዋን ውስጥ ትንፋሽ አይሰማም ነበር። ደጃዝማች አያሌው ሽቅብ አንጋጠው የድንኩዋኑን ጣራ እየተመለከቱ ደጃዝማች ገብረ መድህን አንዳንድ ጊዜ ደጃዝማች አያሌውን አንዳንድ ጊዜ እኔን አንዳንድ ጊዜ መሬቱን እያለዋወጡ እያዩ፥ እኔም አንዳንድ ጊዜ ብቻ ስርቅ እያደረግሁ ሁለቱን ደጃዝማቾች ከማየቴ በቀር አንገቴን ደፍቼ የተቀመጥሁበትን መሬት እየተመለከትሁ ከባድ ዝምታ ሰፍኖ ቆየ። ብርዝ እንዲያመታልኝ የታዘዘው ሰው አምጥቶ እፊቴ አስቀምጦልኝ ከወጣ በሁዋላ፥

«ይገርማል መቆየት ብዙ ያሳያል ብዙ ያሰማል! መቆየታችን እኛ የምንጠረጥር እኛ የማንታመን መሆናችንን አሳየን፤ አሰማን! » አሉ ደጃዝማች አያሌው አይናቸውን ከድንኩዋኑ ጣራ መልሰው እኔን ፍጥጥ አድርገው እያዩ። «ለመሆኑ » አሉ ቀጠሉና «ለመሆኑ የምኒሊክ አልጋ የጣይቱ አልጋ የሀይለ ስላሴ አልጋ፥ የኔ አልጋ ሳይሆን ቀርቶ ነው እኔ አያሌው በገዛ ላልጋዬ፥ ‹ደባ

ይሰራል› ተብዬ የምጠረጠረው? ግዴለም እንዲያ ያለውን ወሬ ካስወሩብኝ ጠላቶች ጋር፥ ልብና ኩላሊት መርምሮ የሚያውቀው አምልካ ያፈራርደኛል። እኔም እውነት እንዲያ ያለውን ደባ የምሰራ ከሆንሁ እሱ ደሜን እንዲህ ያፍስሰው! » አሉና ጠጅ የያዘ ብርሌያቸውን አንስተው በጠረጴዛው ላይ ሲከሰክሱት ጠጁ ከሳቸው አልፎ ተርፎ፥ በደጃዝማች ገብረ መድህን ላይ ተረጨ! ያን ጊዜ እኔ በጣም ደነገጥሁ። ይልቁንም ያን የተናገሩትን ሁሉ ሲናገሩ እኔነ ፍጥጥ አድርገው ያዩ ስለ ነበረ ‹ምናልባት እሳቸውን ለመሰለ የተላከሁ መስያቸው ይሆን?› ብዬ አሳብ ገባኝ።

«ማነው ደግሞ እርስዎን የሚጠረጥር? ይህ እንዲያው ከንቱ የማይረባ ነገር ነው! ‹ይጠረጠራሉ› ብሎ የነገረዎ ሰው ካለ ይልቅ እሱ ነው ጠላትዎ እንጂ እስዎን የሚጠረጥር ይኖራል ብለው አያስቡ » አሉ ደጃዝማች ገብረ መድህን።

«እርስዎ የሚዶለትብኝን ሁሉ አያውቁምና ዝም ይበሉ ደጃዝማች፤ እኔ ነኝ የማውቀው እኔ ሁሉንም ተከታትዬ ደርሼበታለሁ » ብለው በቁጣ ሲያጨበጭቡ አጋፋሪው ገባ።

«ገሰስን ጥራው! » አሉ ደጃዝማች አያሌው፤ እንደ ተቆጣ አንበሳ የሚያፈራ ፊት። ከዚያ ግራዝማች ይሁን ወይም ቀኛዝማች «ገሰሰ » የሚባሉት ጠና ያሉ መኮንን ኩታቸውን በካኪ ኮታቸው ላይ አደግድገው የጠመንጃቸውን አፈሙዝ ዘቅዘቀው ሲገቡ፥

«ገሰሰ » አሉ ደጃዝማች በተቀመጡበት እንዳሉ እየተንቆራጠጡ። «ገሰሰ እኔ አያሌው በታዘዝሁበት የጦር ሜዳ ሁሉ የመንግስቴን ጠላት እያስጨነቅሁ መሬት እያስጋጥሁ ሳሳምን የመንግስቴን ክብር ሳስጠብቅ የኖርሁ አይደለሁም? ‹በመንግስቱ ላይ ደባ ይሰራል› ተብዬ የምጠረጥር ነኝ? በታዘዝሁበት የጦር ሜዳ ሁሉ ተለይተውኝ ከማያውቁት አሽከሮቼ አንዱ አንተ ነህ፤ እስቲ መስክር! »

«እንዴት! ደግሞ ማነዋ ጌታየን ‹በመንግስቱ ላይ ደባ ይሰራል› የሚል! በመንግስት ላይ ደባ የሰሩትን ‹ካይዳኖች› እያሳደደ ሲቀጣ የኖረ ማን ሆኖ ነዋ ጌታዬ ‹በመንግስት ላይ ደባ ይሰራል› የተባለ! ያንተን ታማኝነትና ጀግንነት እኛ አሽከሮችህ ብቻ ነን የምንመሰክር? ያንተን ታማኝነታ ጀግንነት አለም ሁሉ ያወቀው አለም ሁሉ ተናግሮ ያበቃው አደለም? ጌታዬን ‹በመንግስት ላይ ደባ ይሰራል› የሚሉት ራሳቸው ደባ የሚሰሩ ካይዳኖች ናቸው! አንድ ትንሽ ምልክት ብቻ አሳየንና እኒያን ስምህን በሀሰት የሚያካፉትን ጠላቶችህን እኒያን ካይዳኖች አስጨንቀን ያንተን ታማኝነትና የነሱን ካይዳንነት በገዛ አፋቸው እንዲመሰክሩ እንዲናዘዙ እናድርጋቸው! አንድ ምልክት ብቻ አሳየን! ዘራፍ ያንተ አሽከር! ዘራፍ ገሰሰ….! » እያሉ የጠመንጃቸውን አፈሙዝ ዘቅዝቀው ይዘው የፉከራ ግጥማቸውን እየደረደሩ በድንኩዋኑ ውስጥ ሲንጎራደዱ ለሳቸው ቦታ ለመልቀቅ ያሰብሁ መስዬ ከዚያ በይሉኝታ ተገድጄ እግሮቼን አጣጥፌ ከተቀመጥሁበት መሬት ብርዜን ይዤ ተነሳሁና ድንኩዋኑን ተጠግቼ ቆሜ አይ ጀመር።

ግራዝማች (ወይም ቀኛዝማች) ገሰሰ እንዲያ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ፉከራቸውን ጨርሰው እጅ ነስተው ከወጡ በሁዋላ ትንሽ ቆይቶ አጋፋሪው ገብቶ «ከፊታውራሪ ሽፈራው ወረቀት የያዘ መላክተኛ መጥቶዋል » አለ።

«ከየት ከግንባር » ጥራው! » አሉ ደጃዝማች የስጋት ምልክት በፊታቸው እየታየ። ፊታውራሪ ሽፈራው ጌታሁን ተከዜ አጠገብ፥ ደባጉና የተባለውን ጣሊያኖች መሽገው የተቀመጡበትን ቦታ ከብበው እንዲጠብቁ ከተላኩት ሶስት የጦር አለቆች አንዱ፤ ተከዜን በለማለም በኩል ተሻግረው የምስራቁን ግንባር እንዲይዙ የታዘዙት ነበሩ። ‹በአዲያቦ› በኩል የምእራቡን ግንባር ይዘው ለመጠበቅ የሄዱት የጦር አለቃ የደጃዝማች አያሌው ትልቁ ልጃቸው (ስማቸውን ረስቻለሁ) የነበሩ መሆናቸውን ያንለት ደጃዝማች ራሳቸው ሲናገሩ ሰምቻለሁ። የመሀከሉን ግንባር ይዘው ሊጠብቁ ታዝዘው የሄዱት ሌላ ትልቅ የጦር አለቃ ነበሩ።

የፊታውራሪ ሽፈራው መላከተኛ ገብሮ እጅ ከነሳ በሁዋላ የያዘውን ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ለደጃዝማች አያሌው ሰጥቶ እንደ ቆመ፥ ደጃዝማች ስሜታቸው መታወኩ በፊታቸው እየታየ ወረቀቱን አንብበው በጎናቸው እድልዳሉ ላይ ጣሉና፥

«እንዴት! መላልሼ ነግሬው ያን ያክል አደራ ብዬው እንዲህ ያደርገኛል? » አሉ በብርቱ ቁታ አይናቸውን በመላከተኛው ላይ አፍጥጠው። «ጠላት አስቀድሞ ካላጠቃ አንተ የምታዘው ጦር በምንም ምክንያት ቀድሞ እንዳያጠቃ » ብዬ በጥብቅ አስጠንቅቄው፥ አደራ ብዬው፥ ይህ እብድ «ትእዛዝ ተላልፈሀል ብለው ጃንሆይ እንዲጣሉኝ እንዲህ ያደርገኛል? »

«ማጥቃት ጀመርን› ነው የሚለው ፊታውራሪ? » አሉ ደጃዝማች ገብረ መድህን። ደጃዝማች አያሌው ለተጠየቁት መልስ ፊታውራሪ ሽፈራው ጌታውሁን የፃፉላቸውን ወረቀት ከጣሉበት አንስተው ለሁላችንም እንዲሰማ አድርገው አነበቡት። ወረቀቱ የሚለው - ከሞላ ጎደል - እንደሚከተለው ነበር።

«ሌሊቱን ተከዜን ተሻግረን አፋፉን ከወጣን በሁዋላ ተሸሽገን የምንቆይበት ጫካ ፍለጋ ወደ ፊት ስንሄድ፥ ደባጉና አጠገብ እንደ ደረስን ስለ ነጋብን፥ ትንሽ ቁትቁዋጦ አግኝተው እዚያ መስፈር ግድ ሆነብን። ይህ የሰፈርንበት ቦታ ትንሽ ቁጥቁዋጦ እንጂ፥ ጫካ የሌለበት በመሆኑ ዛሬ ሳንታይ ብንውል ነገ ሳንታይ ልንውል አንችልም። ስለዚህ ጦራችን ጠላት ባለበት እንኩዋ ሳይደርስ ባይሮፕላን ተደብድቦ እንዳያልቅ ነገ እንጋት ላይ ደባጉናን እንመታለንና ረዳት ጦር ቶሎ እንዲደስልን »

«ፊታውራሪ ሽፈራው ያለው እውነት ነውኮ ጌታዬ፥ የትግራይን ምድር ጣሊያን በቦምብ አቃጥሎት ዛሬ እንኩዋንስ ሰው ወፍ የሚሸሽግ ጫካና ቁጥቁዋጦ አይገኝም። ስለዚህ ጦሩ አንድ ስራ ሳይሰራ በሰፈረበት ባይሮፕላን ተደብድቦ ሳያልቅ ቀድሞ ባደጉናን ለመምታት ማሰቡ ማለፊያ አሳብ ነው » አሉ ደጃዝማች ገብረ መድህን።

«ያልሁትን አልሰሙኝም መሰለኝ! » አሉ ደጃዝማች አያሌው ቆጣ ብለው። «ያልሁትኮ ‹እኔ የታዘዝሁት እሱንም ያዘሁት ጠላት ቀድሞ ካላጠቃ

በምንም ምክንያት እሱ የሚያዝዘው ጦር ቀድሞ እንዳያጠቃ› ነው! ይህን ነበር በጥብቅ ያስጠነቀቅሁት፤ አሁን ጉድ አደረገኝ! ከንግዴህማ እንዲያውስ ምን ላድርግ እችላለሁ! አሁን መላክተኛ ቢላክ ከንጋት በፊት እዚያ ደርሶ ወደ ሁዋላ እንዲመለስ ማድረግ ይቻላል! »

«ዋይ! እንዲህ ያለው ነገር እዚህም አለ? እንዲህ ያለው ነገር እርስዎም ዘንድ መኖሩን ባውቅ መች እመጣ ነበራ! » አሉ ደጃዝማች ገብረ መድህን እሳቸውም ተቆጥተው። «ጌታየ ልኡል ራስ ስዩም ወደ ሄዱበት መሄዱን ትቼ ወደርስዎ የመጣሁ እንዲህ ያለው ነገር አበሳጭቶኝ መሆኑን ነግሬዎታለሁ። ‹መረብን ጠላት እንዳይሻገር ተከላከል› ተብየ ከተላክሁ በሁዋላ ‹ጠላት ካልተኮሰብህ እንዳትተኩስ› ስለ ተባልሁ እጄን አጣጥፌ እንደ ተቀመጥሁ፥ ጠላት በኔ ሳይተኩስ እኔነ አልፎ አድዋን ባይሮፕላን ሲደበደብ ራስ ለቅቀው ወደነራስ ካሳ ስለ ሄዱለት አንድ ጥይት ስናጮህበት መረብን ከኛ ትንሽ ራቅ ብሎ ተሻግሮ አድዋን ያዘ። ለምን? ‹ካልተኮሰባችሁ እንዳትተኩሱበት› ስለ ተባለን! ለመሆኑ ለጦርነት ተሰልፎ ‹ጠላት ካልተኮሰባችሁ እንዳትተኩሱ› ማለት ምን ፈሊጥ ነው? ፍራት ነው? ወይስ ምን? »

«እንኔ አያሌው ነኝ የምፈራ? አያውቁኝም ማለት ነዋ፤ ደጃዝማች! »

«ጀግንነትዎን ደህና አድርጌ አውቃለሁ እንጂ! ጀግናነትዎን ደህና አድርጌ ስለማውቅ ነበርኮ ከርስዎ ጋር ሆኜ መረብ የተሳሳትሁትን ስህተት ለማረም ወደርስዎ የመጣሁ! ነገር ግን አሁን ሲናገሩ የሰማሁትን ከስዎ ሰምቸው የማላውቅ፥ እንግዳ ነገር ሆነብኝና ግራ ገባኝ! »

« ‹ጠላት ሲያጠቃ ከመከላከል በቀር እናንተ ቀድማችሁ እንዳታጠቁ› የሚል ነው ትእዛዛችን፤ እንዲህ ያለው ትእዛዝ የተሰጠበትን ምክንያት የሚያውቁት ከኛ በላይ ያሉት ናቸው፤ እኛ አይደለምን! »

«ጠላታችን ወሰን ጥሶ ሲገባ ካልተኮስንበት እንዲሁ ሰተት እያለ አገራችንን አንድ ባንድ ይዞ ይጨርሳል እንጂ፤ ለምን ብሎ ይተኩሳል? ለምን ጥይቱን ያባክናል! »

«ስማ ወዳጄ! » አሉ ደጃዝማች አያሌው ለደጃዝማች ገብረ መድህን መመለሳቸውን ትተው፥ ወደ ኔ ባገጫቸው አመለከቱና። «ደባጉናን ከብበው እንዲጠብቁ ከላክሁዋቸው የጦር አለቆች አንዱ፥ ‹ነገ እንጋት ላይ ጦርነት እንገጥማለሁና ረዳት ጦር ይላክልኝ› ብሎ የፃፈልኝን አሁን ሳነብ ሰምተሀል። ነገር ግን ያለኝን ጦር ሁሉ በሶስት ከፍየ ለዚያው ለከበባው ስለ ላክሁ፥ እኔን ለመጠበቅ ከቀሩት ጥቂት ዘበኞች በቀር በተጨማሪ የምልክለት ጦር የለኝም። ‹አዲያቦንና› መሀከለኛውን ግንባሮች ይዘው እንዲተብቁ የሄዱትም ለርዳታ እንዳይደርሱለት ያሉበት የተራራቀ ነው። ስለዚህ ከራስ ሌሊቱን ብርቱ ረዳት ጦር ተልኮ ለነገ እንዲደርስለት በጥብቅ አደራ ማለቱን እንድትነግርልኝ! ስለዚህም ስለምንገናኝበትም ወረቀት እሰጥሀለሁ »

ከዚያ ብርዜን ጠጥቼ እጅ ነስቼ ወረቀቱን ተፅፎ እስኪሰጠኝ ከሰዎቼ ጋር እውጭ ቆየሁና አስር ሰአት ግድም ተነስተን ስንገሰግስ፣ ሲጨልም ሰፈራችን ደረስን።

ጤናው ረዥሙ ዘሪሁንና ገላው ወደ ድንኩዋናችን ሲሄዱ፥ እኔ በቀትታ ወደ ራስ ድንኩዋን ሄድሁ። እዚያ ‹ሊጋባው› ፊታውራሪ ሀይሉ እምሩ ተቀብለው ወዲያው ከራስ ጋር አገናኙተውኝ ደጃዝማች አያሌው ያልኩትን ወረቀት ከሰጠሁዋቸውና በቃል ‹አደራ› ያሉኝን ከነገርሁዋቸው በሁዋላ እደጃዝማች ድንኩውና ገብቼ እስከወጣ ድረስ ያየሁትን ትያትር የሚመስል ነገር እንዲሁም በሁለቱ ደጃዝማቾች መሀከል ተነስቶ የነበረውን ክርክር በዝርዝር ተረክሁላቸው።

«በወረቀት የፃፍሁላቸው ላንተ በቃል ከነገርሁህ የተለየ አደለም። ስለዚህ እሳቸው የሚያውቁት እኛ የማናውቀው ነገር ይኖር እንደሆን እንጂ፥ እኔ በፃፍሁላቸው ‹ተጠርጠርሁ› አሰኝቶ የሚያስቆጣ ነገር የለበትም » አሉ ራስ፤ እንደ ማገረም ብለው።

እኔ ተሰናብቼ ወደ ድንኩዋኔ ከሄድሁ በሁዋላ ምክር ተደርጎ ፊታውራሪ ‹ከፍኔ ማንያህልህል› ሌሊቱን በግስጋሴ ተከዜን ተሻግረው ለፊታውራሪ ሽፈራው ርዳታ እንዲደርሱ ታዝዘው በነጋው አፍላ ጦርነት ላይ የደረሱላቸ

መሆኑን ሰማሁ። ፊታውራሪ ከንፈ ማንያህልሀል ለጎጃም ፊታውራሪ ጦር አዛዥ ነበሩ።

የደባጉና ጦርነት ታህሳስ 6 1928 ነበር የተደረገው። በሰው ቁጥር ደባጉና መሽጎ ከተዋጋው የጣሊያን ጦር የፊታውራሪ ሽፈራውና የፊታውራሪ ከንፈ ጦር ባንድነት ይበዛ እንደ ነበረ፥ በጦርነቱ ተካፋዮች የነበሩ ሰዎች ይናገራሉ። በመሳሪያ በኩል ግን በሁለቱ ወገኖች መሀከል የነበረው ልዩነት የሰማይና የምድርን ያክል የተራራቀ ነበር! የኢትዮጵያውያን መሳሪያ አብዛኛው ያው አሮጌ ጠመንጃ ነበር። በዚያ አንፃር የጣሊያኖች ጦር ምሽጉን አጠንክሮ ሰርቶ ይዋጋ የነበረ ከመሆኑ ሌላ መድፎች ብዙ ከባድና ቀላል መትረየሶች እንዲሁ የጅ ቦምብ በብዛትና ታንኮች ነበሩት። ያም ሆኖ በመጨረሻ ድሉ ለኢትዮጵያውያን ሆነ።

በጦር ሜዳ፥ እንኳዋንስ የጠላትን ሙታንና ቁስለኞች የራሳችንንም ቁጥሮ የመያዝ ልምድ ስለሊዔለን በደባጉና ጦርነት ከኛም ከጠላትም ምን ያክል ሞተው ምን ያክል እንደ ቆሰሉ በኛ በኩል እርግጡን የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም መቸም እኔ አላውቅም። ማርሻል በዶሊዮ ግን ቀደም ብየ በጠቀስሁት መፅሀፉ ከጣሊያን ጦር ወገን የሞቱና የቆሰሉ 392 ወታደሮችና 9 መኮንኖች በምድር 401 መሆናቸውን ፅፎዋል። ታዲያ ደባጉና ጦር ሜዳ ላይ ከሞቱት ተርፈው የእንዳ ስላሴን መንገድ ይዘው ሲሸሹ እስከ ብዙ ኪሎ ሜትር ድረስ ወድቀው ይታዩ የነበሩት የጣሊያንና የመለዮ ለባሽ «አሽከሬ » ሬሳዎች ቁጥር ተይዞ ሲገመት ማርሻ ባዶሊዮ የሰጠውን የሙታንና የቁስለኞች ቁጥር የሚያስተባብል ሆኖ ይገኛል፤ ከጣሊያንም ከኢትዮጵያም ወገን የሞቱትና የቆሰሉት ትክክለኛ ቁጥራቸው ባይታወቅም ብዙ ነበሩ። ከጣሊያኖች የተማረከው መሳሪያም እጅግ ብዙ ነበር። ከባዱና ቀላሉ መትረየስ ጠመንጃው የመተረየሱና የጠመንጃው ጥይት በሳጥን በሳጥን እንዳለ ሁሉም ብዙ ነበር። ሊሬው ከወታደሩ ተርፎ በባላገሩ እጅ በብዛት ይገኝ ስለ ነበረ እኛ ስንደርስ፥ ባንድ ብር እስከ ሺህ ሊሬ ይለወጥ ነበር። የተሰባበሩም ያልተሰባበሩም ታንኮችና ብረት ለበስ ካሚዎኖች በጦሩ ሜዳ በእንዳ ስላሴ መንገድ ቆመውም ተገልብጠውም በብዛት ይታዩ ነበር።

ማርሻል ባዶሊዮ ስለ ጦርነቱ በመፅሀፉ ሲተች «የደባጉና ጦርነት ከጠቅላላው ጦርነት አንፃር ሲታይ ከቁም ነገር የሚቆጠር አይደለም » ብሎዋል። እርግጥ ከጠቅላላው ጦርነት አንፃር ሲታይ የደባጉና ጦርነት ትንሽ ነው። ነገር ግን ብቻውን ሲታይ፥ - ብቻውን መታየትም ይገባዋል - ታሪካዊ ነው። የደባጉና ጦርነት የተደረገበት ቦታ የተደረገበት ቀን በጦርንቱ ድል ያደረጉት ኢትዮጵያውያንና ድል የሆኑት ጣሊያኖች የራሳቸው የሆኑ መልክና ጠባይ ያሉዋቸው ናቸው። ስለዚህ፥ ኢጣሊያ በመጨረሻ በጠቅላላው ጦርነት ድል አድራጊ ሆኖ ኢትዮጵያን መያዝዋ የደባጉናን መልክና ጠባይ አይለውጠውም። ኢጣሊያ በመጨረሻ ኢትዮጵያን ድል አድርጋ መያዝዋ ደባጉና ያለቁንት ሽማምንትዋንና ወታደሮችዋን ከሞቱበት በግዘሪ - ሥጋ አያስነሳቸውም፤ አካላተ ጎደሎዎች የሆኑትን በለሙሉ አካላት አያደርጋቸውም። ይህ የተደረገ ጎደሎዎች ስለ ሆነ፥ የተደረገው እንድ እገና እንዳልተደረገ ሊሆን አይችልም! እርግጥ በሌሎች ቦታዎችና በሌሎች ቀኖች ኢጣሊያ ድል አድርጋ ኢትዮጵያን ይዛለች። ነገር ግን ያ ሁሉ ጀግናው ፊታውራሪ ሽፈራውና ጀግኖች ተከታዮቻቸው ምሽግ አፍርሰው የመድፍና የመትረየስ አጥር ጥሰው ታንክ ሰባብረው የሚበዙትን ጣሊያኖች ገድለው የተረፉትን መሳሪያቸውን እያስጣሉ አባርረው የደባጉናን ድል የተቀዳጁ መሆናቸውን በምንም መንገድ ሊለውጠው አይችልም! ኢጣሊኢያ ኢትዮጵያን ድል አድርጋ መያዝዋ የሽፍራውን ጀግናነት ሊቀማው አይችልም! ሽፈራው ድል ባደረገበት ቦታ፥ ደባጉና ላይ ቢወድቅም ምድርን ከነታሪከዋ የሚያጠፋ መአት እስካልመጣ ድረስ ጀግናነቱና ስሙ ከደባጉና ተራራ ጋር ለሁልጊዜ ይኖራሉ።

# ምዕራፍ ሰባት

# ተከዜ

የጎጃም ጦር ዳባት ሜዳ አጠገብ ቁጥቋጦ ባለበት ቦታ ሰፍሮ ከቆየበት ተነስቶ በሁለተኛው ይሁን በሶስተኛው (እርግጡን እረሳሁት) ቀን፥ ከቀትር በሁዋላ በደህና ጊዜ ተከዜ ሸለቆ ውስጥ ሰፈረ። የተከዜን አፋፍ ወጥቶ ትግራይ ውስጥ ሽሬ ለመስፈር የሚበቃ ጊዜ እያለ ሰፈር እሸለቆ ውስጥ እንዲሆን የተመረጠበትን ምክንያት አላውቅም። ምናልባት ከዚያ በፊት ሰፈር በተደረገባቸው አንዳንድ ቦታዎች ለሰውና ለከብቱ የሚበቃ ውሀ ሳይገኝ እየቀረ ችግር ይፈጠር ስለ ነበረ፥ እንዲያ ካለ ችግር ለመዳንና ወዲያውም ድንገት አይሮፕላን ቢመጣ ለመጠለያ ጫካውም ዋሻውም እዚያ የሚመች በመሆኑ ሊኆን ይችላል።

የጎጃሙ ፊታውራሪ ጦር አዛዥ ፊታውራሪ ክንፌ ማንያህልህል፥ ለደባጉናው ጦርነት ይዘውት የሄዱት ጦር ቢቀነስለትም የቀረው ብዙ ስለ ነበረ፥ የተከዜን ወንዝ በቀኝና በግራ ተከትሎ ሸለቆውን በወርዱም በቁሙም እስከ ሩቅ ድረስ ሞልቶ ሰፈረ። የራስ ሰፈር ወንዙን ተሻግሮ ወደ ግትራይ ግንባር ነበር። የኛ ሰፈርም ከሳቸው ሰፈር በጣም ሩቅ አልነበረም። ድንኳዋኖቻችንን ተክለን እቃችንን ቦታ ቦታውን አስይዘን ካሰነዳዳን በሁዋላ ለማረፍ እንደተቀመጥን እኔ «ራስ ይፈልጉሀል » ብሎ መላክተኛ መጥቶ ስለ ነገረኝ ለመሄድ ተነሳሁ። ገላውም እንደ ልማዱ ሊከተለኝ ጠመንጃየን ይዞ ሲወጣ አይቼ፤ የራስ ሰፈር ቅርብ ስለ ነበረ፤ «ተመለስ » ብዬው ብቻዬን ሄድሁ።

ራስ አነጋግረውኝ ስወጣ፤ እዚያ ውጭ በቡድን በቡድን እየሆኑ ቆመው የሚያወሩ ብዙ ሰዎች ስለ ነበሩ እኔም ከወሬው ለመጋራት ወዳንዱ ቡድን ጠጋ ከማለቴ ያይሮፕላን ድምፅ ተሰማ። ወዲያው «ተበታትናችሁ ወደ አይሮፕላኖች ተኩሱ » ለማለት ምልክት የሆነው የክብር ዘበኞች ጥሩንባ ይነፋ ጀመር። ከዚያ «ተበታትናችሁ ወደ አይሮፕላኖች ተኩሱ » ለማለት ምልክት የሆነው የክብር ዘበኞች ጥሩንባ ይነፋ ጀመር። ከዚያ ራስ ባቅራቢያው ወደ ተሰናዳላቸው መጠለያ ሲሄዱ እኛም ወደ ዛፉ ስር እየሄድን እንደ ተጠጋን፤ ድምፃቸውን ከሩቅ ያሰሙን አይሮፕላኖች ታዩ። እኔና አብረውኝ የነበሩት

ሰዎች የተጠጋንበት ዛፍ ትልቅ ስለ ነበረ እዚያ ስር ሆኖ አይሮፕላኖችን ለመቁጠር ያስቸግር ነበር። ቢሆንም እኔ ለመቁጠር እስከቻልሁት ድረስ አመት መለውኝ ነበር። ሌሎች ግን እንደኔ አምስት ናቸው ያሉም ሰባት ናቸው ያሉም ነበሩ። ያም ሆነ ይህ ደባት ሜኢዳ የደበደቡንን ሲደበድቡን አልቆዩም። የተጫኑትን ቶሎ ቶሎ አራግፈውብን ቶሎ ተመለሱ መቸም በጦሩ ሰፈር ላይ የጣሉትን ጥለው እስኪመለሱ ድረስ የነበረው ተኩስ ከመብዛቱ የተነሳ ጠመንጃ ያለው ሁሉ የሚተኩስ ይመስል ነበር። ያንለት የተጣለው ቦምብ ደባት ሜዳ ከተጣለው የተለየ በጣም ትልልቅ ነበር። ስለዚህ ካይሮፕላኖች አካላት አንዳንድ ክፍል እየተሰበረ የወደቀ መስሎት ብዙ ሰው ወደዚያ «ያይሮፕላን ስባሪ » ወደ ተባለው ነገር እየሮጠ እየሄደ ከብቦ ሲመለከት ቆየ።

በኒያ የአይሮፕላን ስባሪ መስለውት ሰው ተሰብስቦ በሚመለከታቸው ነገሮች አካባቢ አየሩ እንደ ሰናፍጭ በሚከነክን ትናኝ ተበክሎ እዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ሁሉ አይናቸውን እየለበለበ ወዲያው ያስላቸውና ያስነጥሳቸው ጀመር። የዛፎች ቅርንጫፍ ቅጠሉና ሳሩም ሁሉ የዘይት ጠባይ ያለው ፈሳሽ አቁሮ ስለ ነበረ ያ ስረሳሽ እየተንጠባጠበ ራቁት አካላታቸውን የነካቸው ሁሉ የተነካው አካላታቸው እሳት እንደ ፈጀው መጉረብረብና ማበጥ ጀመረ። ከዚያ ግሪኩ ሀኪም አይተው ያንለት የተጣለው «ማስታርድ ጋዝ » የተባለው የመርዝ ጋዝ ስለ ሆነ ሰውም ከብትም ካጠገቡ እንዲርቅ ካስታወቁ በሁዋላ ይህ በየሰፈሩ ተለፈፈ።

የሀኪሙ ማስታወቂያ ከመለፋፉ በፊት አይሮፕላኖች እንዲሄዱ የሰዎቼን ደህንነት ለማወቅ ቸኩዬ ተጠግቼ ከቆየሁበት ዛፍ ስር ወጥቼ ወደ ሰፈሬ እየሮጥሁ ብሄድ ከገላው በቀር ሁሉንም ተቀምጠው ስለ ደረሰው አደጋ ሲያወሩ አገኘሁዋቸው።

«ገላውስ? » አልሁ፥ እሱን ብቻ ሳጣው ስጋት ተሰምቶኝ።

«አይሮፕላን ተስብሮ ወደቀ » እያሉ ሰዎች ሊያዩ ሮጠው ሲሄዱ አይቶ፥ እሱም እንደ ሄደ አልተመለሰም » አለኝ ከመሀከላቸው አንዱ፤

«ለምን ለቀቃችሁት? » ብዬ «ስባሪው ወደቀ » ወደ ተባለበት ቦታ ስሄድ አቶ ዘውዴ ተከትሎኝ መጣ። እዚያ ስንደርስ አይናቸውን እየፈጃቸው እያነጠሳቸውና እያሳላቸው እንዲሁም ዘይታማው ፈሳሽ በራቁት አካላታቸው ላይ የፈሰሰባቸው እያቃጠላቸው በዬዛፉና በየደንጋዩ ስር ተቀምጠው የሚጨነቁት ሰዎች ብዙ ነበሩ። ገላውን አንድ ቁዋጥኝ ደንጋይ ተጠግቶ ተቀምጦ አይኖቹን በሁለት እጅጅጆቹ ይዞ ያለማቁዋረጥ ሲያስለውና ሲያስነጥሰው ሱሪው ቁምጣ ስለ ነበረ ከጭኖቹ በታች ዘይታማው ፈሳሽ የነካቸው እግሮቹ እሳት የለበለባቸው መስለው አገኘነው። አይሮፕላኖች መርዝ ጥለው ከሄዱ በሁዋላ የሰናፍጭ ሽታ በሸለቆው ውስጥ ሁሉ ቢሰማም በተለይ የመርዙ ጋዝ በወደቀበት አቅራቢያ ሁሉ በጣም ከብዶ ይሰማ ነበር። ስለዚህ ምንም እንኩዋ የመርዝን ጋር ከስሙ በቀር ሽታውንም ሌላ ጠባዩንም ባላውቅ ያንለት አይሮፕላኖች የጣሉብን ያስከተለውን ልዩ ልዩ ጠንቅ ሳይ የመርዝ ጋር መሆኑን ጠረጠርሁ። ገላውን ከጠቀመጠበት አንስተን በቀኝና በግራ ደግፈን ወደ ሰፈራችን ስንሄድ በመንገድ ላይ እንዳለን የሀኪሙ ማስታወቂያ ሲለፈፍ ስለ ሰማን ወደ ድንኩዋናችን መሄዱን ትተን ወደ ሀኪሙ ድንኩዋን ሄድን። እዚያ ሀኪም ለሳሉና ለማስነጠሱ መድሀኒት ከሰጡት በሁዋላ አይኑንም እግሮቹንም በሸንት እንድናጥበውና በማግስቱ ወደሳቸው መልሰን እንድንወስደው ነግረውን ሄደን እንዳሉን ንበሸንት አጠብነው። ማምሻውን ማሳሉንም ማስነጠሱንም ባይተወውም ትንሽ ፋታ ሰጠው ያይኖቹና የግሮቹ ስቃይም ትንሽ መለስ አለለት፣ ነገር ግን እግሮቹ በጣም አብተው ሊቆምባቸው አይችልም አይኖቹንም መከፈት አይችልም ነበር።

ያንለት ማታ ጦሩ ከሌሉቱ ቀደም ብሎ የተከዜን ሸለቆ እንዲለቅና እንጋት ላይ ፋፉን ወጥቶ ቁጥቁዋጦ ባለበት ቦታ እንዲዒሰፍር ሲለፈፍ አመሸ። ነገር ግን ሰፈር ሲሆን፥ ሌሊትም ቢሆን የሚያስፈልገውን ከያለበት እየፈለጉ መፍታቱና ማቅረቡ ሰፈር ሲለቀቅ ተፈትቶ የተበታተነውን አጠረቃቅሞ ማሰሩና መቻኑ ካሰቡት የበለጠ ጊዜ የሚወስድ ነው። ስለዚህ እንጋት ላይ ሁሉም የተከዜን አፋፍ ወጥቶ በየቁጥቁዋጦው ውስጥ ሰፈሩን እንዲይዝ ከታዘዘው ሰራዊት እስከ ርፋድ ድረስ ገና አፋፉን እየወጡ ሲመጡ የሚታዩ

በጣም ብዙ ነበሩ። እንዲያውም እስኪመሽ ድረስ ከሸለቆው ያልወጡም ነበሩ ይባላል።

ራስ ምን ጊዜ የተከዜን ሸለቆ ለቀው እንደ ወጡ ትዝ አይለኝም እኛ ግን ከሌሊቱ አስር ሰዓት ግድም ተነስተን ገላውን በኔ በቅሎ አስቀምጠን ቀስ ብለን እያዘገምን ሲነጋጋ አፋፉን ወጣን። ከዚያ ትንሽ ስንሄድ እንደቆየን ለመንገዱ ቀረብ ባለ ቦታ ቁጥቁዋጦ በስሱ የከበበው ትልቅ የግራር ዛፍ ስላየን ያ ቦታ ለሰፈር የሚስማማ መሆኑንና ወዲያውም ያልተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ አቶ ዘውዴ ሮጦ ሄዶ ሲመለስ ተስማሚ መሆኑንም አለመያዙንም ነገረን። ስለዚህ፥ ወደዚያ ሂደን ቶል ቶሎ ጭነታችንን አራግፈን ጀንበር ሳትወጣ ድንኩዋኖቻችንን ተክለን እቃችንን አሰነዳድተን ጨረስን። እውነትም ያ ቦታ ከትልቅ ግራር ሌላ ባጠገቡ ከሩቅ ያልታዩን ትንንሽ ግራሮችም ያሉበት ስለ ነበረ፤ ምንም እንኩዋ የሁሉንም ቅጠል የቦምብ እሳት ቢያቃጥለው ቅርንጫፋቸው ባንድነት ችፍግ ያለ በመሆኑ ስፍራችንን ከላይ አይሮፕላን ያየዋል ተብሎ የሚያሰጋ አልነበረም።

በጠቅላላው ጦሩ የሰፈረበት ደባጉናን ወደ ፊት አድርጎ ጦርነት በተደረገበት ቦታ ሳይደርስ በቁጥቁዋጦዋማው ቦታ ላይ ነበር። ያ ቦታ ፊታውራሪ ሽፈራው ጦርነት ከመግጠማቸው በፊት ሰፍረውበት የነበረው መሆኑን ሰዎች ነገሩን። በዚያ ቦታና በደባጉና ምሽግ መሀከል ያለው አንድ ሚኤዳ ብቻ ስለሆነ፥ እውነትም ፊታውራሪ ሽፈራው እንዳሉት «እዚያ ሰፍረው አንድ ቀን ሳይታዩ ቢውሉ በሁለተኛው ሳይታዩ እንደማይቀሩ » የታወቀ ነበር!

እቃችንን በየቦታው አድርገን አሰነዳድተን ቁርስ ስናደርግ ገላውም ትናንቱን ምሳ ከበላ በሁዋላ ምንም ሳይቀምስ አድሮ ስለ ነበረ የማር ተልባ በወፍራሙ በጥብጠን ሰጥተነው ጠጣ፤ ማስነጠሱንም ተወው። ሳሉ የሌሉትን ያክል ባይሆንም ያስለው ነበር። ነገር ግን፥ ምንም እንኩዋ አይኖቹንና እግሮቹን ሀኪሙ መክረውን እንደ ተመለስንም ጥዋት ጉዞ ከመጀመራችን በፊትም በሸንት ብናጥበው የማቃጠሉን ስቃይ አስታገሰለት እንጂ አይኖቹን መግለጥ

አልቻለም፤ ይልቁንም እግሮቹ ይብሱን አብተውና ተጉረብርበው እንኩዋንስ ሊቆምባቸው ከተደጋገቡበት ማንቀሳቀሱም በጭንቅ ነበር።

ከቁርስ በሁዋላ ገላውን ወደ ሀኪም ከመውሰዳችን የራስን ሰፈር አይቼ ምናልባት እኔን የሚፈልጉበት ጉዳይ ቢኖርም ታይቼ ቶሎ እመለስለሁ ብዬ ሄድሁ። እዚያ እንዳለሁ አይሮፕላኖች መጥተው ቦምብ ሲጥሉ ቆይተው ሄዱ። ያን ጊዜ ከራስ ጋር እመጠለያቸው ውስጥ ስለ ነበርሁ ቁጥራቸው ስንት እንደ ነበረ አላየሁም፤ ያዩትን ሰዎችም ቀጥሎ በሚገለፀው ምክንያት ለመጠየቅ ጊዜ አልነበረኝም። ከራስ ጋር ቆይቼ ስወጣ ፊታውራሪ ሀይሉ እምሩ ወደ ጎን ሳብ አድርገው፤

«ከሰፈርህ ሰው ተልኮ መጥቶ ሰዎችህ እንድትሄድላቸው መፈለጋቸውን ነግሮን ሄደ። እስቲ - የተቸገሩበት ነገር ቢኖር ይሆናልና ሂድላቸው። ብቻ - ቀላል ነገር ሳይሆን አይቀርም አይዞህ አትደንግጥ » አሉ ወዲያው ቀጥለው መደንገጤን ከፊቴ ሲያዩ።

ክፉ ነገር እንደ ደረሰ ወዲያው ገባ። ከዚያ በፊት በሌለሁበት ክፉም ሆነ በጎ ቢደርስ ከሄድሁበት ስመለስ ይነግሩኛል እንጂ ሰዎቼ አንድም ቀን ካለሁበት ድረስልን ብለው ጠርተውኝ አያውቁም። ስለዚህ ከክፉም ክፉ ቢደርስ ነው እያልሁ አሳቤን ለራሴ እየነገርሁ ከራስ ሰፈር የሮጥሁ እሰፈሬ አጠገብ ስደርስ ከግራሮቹ ስር ድንኩዋኖች በነበሩበት ቦታ ያመድ ክምርና ባመዱ ክምር ዙሪያ የሚጤስ ጢስ ብቻ ይታያል! ሌላ ነገር ምንም የለ። የኔ ሰዎችና በሰፈራችን አቅራቢያ ካሉት አንዳንድ ሰዎች መጥተው ሁሉም አንገታቸውን እየደፉ ቆመዋል። ያን መአት ሳይ ራሴን በከባድ ነገር የተመታሁ መስሎ ተሰማኝና በቆምሁበት እንዳለሁ ደንዝዤ ቀረሁ። በዚያ ጊዜ እዚያ የቆሙት ሰዎች ሁሉ የሰዎች ጥላ እንጂ ሰዎች መስለው አይታዩኝም ነበር! አቶ ዘውዴ ወደኔ ሲመጣ፥ የሚንቀሳቀስ የሰው ጥላ መስሎ ነበር የሚታየኝ እጄን ይዞ ሊያነጋግረኝ ሲጀምር ብቻ መልኩ ጥርት ብሎ ይታየኝ ጀመር።

«ተው እንጂ ጦርነት ነውኮ ለዚህ መመጣታችንን ረሳህው? » አለ ትልልቅ የደረፈሱ አይኖቹ እንባ ምልተው ሳግ እየተናነቀው አላለቀስሁ፤ ክርር ብዬ ከመቆም በቀር አንድ ቃል እንኩዋ አልተነፈስሁ፤ ፊቴና ጠቅላላ ሁኔታዬ

ምን መስሎ ታይቶት እንዲያ እንዳለ አላውቅም። ሰዎችን አጥርቼ ማየት ስጀምር ሁሉንም አንገታቸውን እየደፉ ቆመው አየሁ። ገላውን ብቻ አይኔ ዙሪያውን ቢፈልግ አጣው።

«ገላው የት አለ? ሞ - ተ? » አልሁ አፌ እየፈራ። አቶ ዘውዴ አልመሰለኝም፤ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ።

«ሬሳውም የለ? ተቃጠለ? » አልሁ ገላው ሲቃጠል ታየኝና አድርነው ይመስል ሳይታወቀኝ እጆቼን ዘርግቼ ወደ አመዱ እየሮጥሁ። ያን ጊዜ ሁኔታዬን ሲያዩ የኔ ሰዎችም እዚያ የነበሩት ሌሎች ሰዎችም ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እየጮሁ ያለቅሱ ጀመር። ሲቃጠል እናቶ ዘውዴ ከሰውነቱ ሊያተርፉ የቻሉትን ትንሽ ቁርጥራጭ ሰብስበው በትንሽ ጨርቅ አስረው አንድ ዛፍ ስር አስቀምጠውት ነበር ፈትቼ ለማየት አልቻልሁም፤ ድፍረት አነሰኝ።

የደረሰብንን አደጋ የሰሙት ወዳጆቻችን ሁሉ ከቅርብም ከሩቅም ሰፈር ተሰብስበው ስናለቅስ የቆየን በሁዋላ የኛ እቃ ሁሉ ተቃጥሎ ምንም የተረፈን ነገር ስላልነበረ ሰዎቹ ስንቅ የተጋባላት ትንሽ ሳጥን በግዢ ይሁን በልመና ፈልገው አግኝተው ያን በትንሽ ጨርቅ የታሰረ የገላው የሰውነት ፍርፋሪ በዚያ ከትተን ቤተ ክርስቲያን በቅርብ ባለመገኘቱ እዚያው እሰፈራችን ከትልቁ ግራር ስር ቀበርበነው።

ገላውና አንዳንድ እንደሱ መተኪያ የሌላቸው አልተተኩም እንጂ ሌላውን የተቃጠለ እቃና ስንቅ ሁሉ፥ ራስ፣፤ ብዙ መኩዋንንት ወዳጆቼም የመጡት እያስያዙ መጥተው ያልመጡት እየላኩ ያንለት እስከ ማታ ድረስ ተኩልኝ። እንዲያውም የምንጭንባቸው ከብቶች የማይችሉልን በመሆናቸው እያመሰገንሁ ባልመልሰው ኖሮ ወዳጅ ያመጣልን ልዩ ልዩ ስንቅ፥ ከኛ ተርፎ ለብዙ በበቃ ነበር።

«እዚያ ግራር ስር ድንኩዋን የተተከለ መሆኑን አይሮፕላን እንዴት አውቆ ሰፈራችንን ቦምብ መታው? » ብዬ ሁዋላ ሰዎቹን ብጠይቅ አይሮፕላኑ እዚያ ግራር ስር ሰፈር መኖሩን አውቆ ሳይሆን እሸለቆው ውስጥ አርፍደው እየወጡ ይመጡ የነበሩ ብዙ ሰዎች አይሮፕላን ድንገት ሲመጣ ስላዩት መጠለያ ፍለጋ

እኛ ወደ ሰፈርንበት ቁጥቋጦና ዛፍ ሲሸሹ በነሱ ላይ አከታትሎ የጣለው ቦምብ ከነሱ አንዳቸውንም ሳይነካ፥ የኛን ሰፈር ያቃጠለ መሆኑን ነገሩኝ።

ገላው አስቀድሞ በመርዝ ጋር አይኖቹ ባይደፈኑና እግሮቹ ባይስነከሉ ኖሮ አይሮፕላኑ የመጣበትን አቅጣቻ ሲያይ፥ እንደ ሌሎቹ ሸሽቶ ያመልጥ ነበር እንጂ እድንኩዋን ውስጥ እንደ ተኛ በቦምብ አይቃጠልም ነበር። ስለዚህ የገላው መቃጠል ጠንቁ አስቀድሞ በመርዝ ጋዝ ለመንቀሳቀስ እንደማችይል ሆኖ መጎዳቱ ነው እላለሁ። ምናልባት ከቦምቡ ቃጠሎ ቢተርፍም በመርዝ ጋዝ ክፉኛ ስለተጎዱ እንደ ሞቱ ሰዎች፥ ይሞት ኖሮ ይሆናል። በመርዝ ጋዝ የሞቱትን ሰዎች ቁጥር አላውቅም እንጂ ብዙ መሞታቸውን ሰምቻለሁ። ክፉኛ የቆሰሉትንና በታምር ካልሆነ ‹ሊተርፉ ይችላሉ› የማይበሉትን ግን፥ ብዙ ባይኔ አይቻለሁ። መርዙ በበዛት የፈሰሰባቸው ሰዎች የቆሰለ አካላታቸው ልብስ እንኳ አላስነካ ብሎ ራቁታቸውን ተጋድመው ጉማሬዎች እንጂ ሰዎች ስለማይመስሉ፤ ከሩቅ ማየቱም ያሰቅቅ ነበር። እኒያ ሰዎች የጣእራቸውን እድሜ ከማስረዘም በቀር መቸም እንዲያ ከፈራረሱ በሁዋላ የመትረፍ እድል እንደማይኖራቸው የታወቀ ነው።

በውነት እንዲያ ያለውን መሳሪያ ምንም ጠላት ቢሆን በሰው ላይ ለማዋል የሚጨክን ሰው፥ በልብ ሰባዊ ስሜት የሌለው፥ አለት ድንጋይ የተፈጠረበት መሆን አለበት፤ እንዲያ ያለውን መሳሪያ በሰው ላይ ማዋል ሰባዊ ህሊና ሊሸከመው የማይችል እጅል ከባድ መሆኑን አለም ሁሉ ያወቀውና ያወገዘው በመሆኑ የኢጣሊያ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ከማድረጉ በቀር ‹ሌላ መንግስት በሌላ አገር ላይ አደረገ› ሲባል ተሰምቶ የሚያውቅ አይመስለኝም። ታዲያ መንግስታት በጦርነት ጊዜ በመርዝ ጋዝ እንዳይዋጉ የሚከላከለውን፥ እንደ አውሮፓ አቆጥጣጠር 17 1925 ጀኔቭ ላይ የተፈረመውን «ፕሮቶኮል » (ስምምነት) ፈርመው ካፀደቁ መሀከል አንዱ፤ የጣሊያን መንግስት ነው! የጣሊያን መንግስት ሰውን እንደ ክፉ ተባይ በመርዝ መፍጀት የሰው ባህሪ ያለው ይልቁንም እንደ ጣሊያን በስልጣኔው የሚኮራ ህዝብ ሊያደርገው የማይገባ መሆኑን አይክድም። እስከ ዛሬም ድረስ የሚክደው ማድረጉን ነው። ግን ምን ይሆናል! ሙታንን አስነስቶ የሚያስመሰክር ምድራዊ ዳኛ የለ!

ቢኖርማ ገላውንና እንደሱ በጣሊያን መርዝ ያለቁትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ አስነስቶ ባስመሰከረ ነበር!

## ምዕራፍ ስምንት

# ከደባጉና እስከ እንዳስላሴ

የጐጃም ጦር፥ ከደብረ ማርቆስ ተነስቶ ትግራይ ውስጥ «ሰለክለካ » አጠገብ «እንዳስላሴ » እስኪደስ ከጥቅምት እስከ የካቲት 1928 አምስት ወራት ያክል ፈጀበት። ከዚያ ጊዜ ውስጥ ከሁለት ወራት በላይ ያሳለፈው ሽሬ አውራጃ ውስጥ ከደባጉና እንዳስላሴ እስኪደርስ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በሰፈረባቸው ቦታዎች እንዲሰነብት የሚያስገድዱት ምክንያቶች ይገጥሙት እንደ ነበረ ባይካድም ያን ያክል ጊዜ ይልቁንም ትግራይ ባንድ አውራጃ (በሽሬ) ውስጥ፥ ከሁለት ወራት በላይ ማሰለፍ በምንም ምክንያት ባልተገባ ነበር። የጉዞው ጊዜ ያን ያክል መርዘሙ ጠላትን የጠቀመውን ያክል በኛ ሰራዊት ላይ ችግር ማድረሱ በሰራዊቱ መሀከል ሲናገር ይሰማ ነበር።

ለጠላት መንገድ ባልነበረባቸው ክፍሎች መንገድ እየሰራ ሰራዊቱንም ለሰራዊቱ የሚያስፈልገውን መሳሪያና ስንቅም ለማጉዋዝ ጠቅሞታል። እንዲሁም ትግራይ ውስጥ በቁልፍ ቦታዎች ምሽጎቹን አጠንክሮ ለመስራትና የያዘውን አገር ህዝብ በገንዘብም በስብከትም ለማባባል ያመቻው መሆኑ ግልፅ ነበር። ባንፃሩ የኛ ሰራዊት የሻለቃውና የታላላቁ መኩዋንንት ግብረ - በላዎች እየኖኑ ከዘመቱት በቀር፥ የገዛ ስንቁን እያሰናዳ ባህያ ጭኖ የዘመተው ሰራዊት ሁሉ፥ ጉዞው በረዘመ መጠን ከጦሩ ግንባር ሳይደርስ ስንቁ እያለቀ በመሄዱ መቸገር ጀምሮ ነበር።

በድሮው ልማድ ዘማች ሰራዊት ዘመቻ ሲሄድ ስንቁን ቆጥቦ፥ በሚያልፍባቸው አገሮች ወይም በሚሰፍርባቸው ቦታዎች ከሚኖረው ባላገር ቤት ገብቶ በውድም በግድም እየበላ እየጠጣ፥ ተጨማሪ ስንቅም እየያዘ ስለሚሄድ በሚዋጋበት ቦታ ደርሶ እስኪመለስ ድረስ በስንቅ በኩል እምብዛም አይቸገር ነበር። ዘማች በሚያልፍባቸው አገሮች የሚኖር ባላገርም ዘማች ሰራዊት ባገሩ የሚያልፍ መሆኑን ገና ከሩቅ ሲሰማ ከብቱንና ገንዘቡን እንዲሁም ሊይዘው የሚችለውን ሁሉ እየያዘ ሊይዘው የማይችለውን እየሸሸገ ራቅ ወዳለ ቦታ ሸሽቶ ይቆያል። ብቻ ያን ማድረጉ ከሚያስከትለው ችግር ይልቅ በየቤታቸው ቆይተው ወታደሩን አብልቶ አጠጥቶ የሚይጠይቀውን ስንቅ ሰጥቶ መሸኘቱ የሚመርጡ ስለሚኖሩ የስንቅ ችግር ከብዶ አይከብድም ነበር።

ራስ እምሩ ግን ዘመናዊውን አስተሳሰብ በመከተል ባለፉባቸው አገሮችና በሰሩባቸው ቦታዎች ሁሉ እባላገር ቤት ገብቶ የሚዘርፍ ወይም በምንም አይነት የሚያስቸግር ወታደር ብርቱ ቅጣት የሚቀጣ መሆኑንና ባላገርም ለስንቅ የሚሆን እህልም ከብትም ገብያ አውጥቶ ለወታደር በዋጋ እንዲሸጥ አዋጅ ያስነግሩ ስለ ነበረ፥ ወታደር እባላገር ቤት ገብቶ ያስቸግራል ሲባል ወሬ አይሰማም ነበር። ይሁን እንጂ ሰፈር በሚደረግባቸው ቦታዎች ከሚኖረው ባላገር አዋጁን በሙሉ ልብ ባለማመን የሚበዛው ቤቱን እየዘጋ ከብቱን ነድቶ ሸሽቶ በመንደርም ሆነ በገብያ የሚታየው ሰው ጥቂት ነበር። ገብያ የሚወጣው እህልና ከብትም በዚያው መጠን ጥቂት ነበር። ያንኑም መግዛት የሚችሉት ገንዘብ ያላቸው እንጂ የሌላቸው ስላልሆኑ ዞሮ ዞሮ የጉዞው መርዘም በተለይ መጠነኛ ስንቅ እየያዙ በተነሱት ዘማቾች ላይ የስንቅ ችግር ማድረሱ አልቀረም።

አንድ ቀን ሽሬ ውስጥ ሰፍረን በሰነበትንበት ቦታ፣ የባላገር ዘማቾች «ጠላት ባለበት ቦታ ደርሰን ጦርነቱን ሳንጀምር በመንገድ ስንቃችን አልቆ ራብ ሳይገድለን አይቀርም » እያሉ ሲያማርሩ የሰማሁትን ለፊታውራሪ ሀይሉ እምሩ ነግሬ ሳያስፈልግ ባንዳንድ ቦታ ሰፈር እየተደረገ ያን ያክል የሚሰነበትበን ምክንያት ጠየቅሁዋቸው።

«ሳያስፈልግ እንኩዋ አይደለም » አሉኝ ፊታውራሪ።

«ምንድነው አስፈላጊ ያደረገው? »

«በሰፈርንባቸው ቦታዎች ጥቂት ጥቂት እየቆየን ቀስ ብለን ብንሄድ ይሻላል ከተባለባቸው ምክንያቶች አንዱ እንዲያውም ስንቅ ያለቀባቸው ወይም ያነሳቸው ዘማቾች ገብያ ሊያገኙ ያልቻሉትን አገር ላገር ዞረው ለመግዛት ጊዜ እንዲያገኙ ታስቦ ነው። ሁለተኛው አይነተኛው ምክንያት ግን አሁን ጦርነት ወደ ምንገጥምበት ቦታ እየተቃረብን በመሄዳችን ከመግጠማችን በፊዒት የተቻለውን ያክል ስለ ጠላት ድርጅት አሰላለፍ መረጃ ለማግኘት ነው »

«ጠላት ሰለክለካን አጠንክሮ መሸጎ መሰለፉ ገና ድሮ ታውቆዋል፤ ሌላ ምን መረጃ ነው ማግኘት የሚያስፈልገው? »

«መቸም የሰለክላካን ተራራ ሁሌ መመሸግ አይቻል፤ ዞረን ማጥቃትን የምንችልባቸው ክፍት ቦታዎች ይኖራሉ። እንዲሁም በግንባር መሸጎ ላለፈው ወታደር ጥይትና ስንቅ የሚያቀብልባቸውን መንገዶችና በጀርባ የመሳሪያም የስንቅም ማከማቻዎች ያሉበትን ትክክለኛ ቦታ ማወቁ፥ እነሱን ለማጥፋት ያስችለናል። ያን ማድረግ ከተቻለ ደግሞ ጣሊያኖችን የሚጎዳውን ያክል እኛን እንደሚጠቅም አይጠረጠርም። ታዲያ እንዲያ እንዲያ ያለውን መረጃ ካገሩ ሰው በቀር ማንም ሊያውቅ ስለማይችል የሚያውቁ ሰዎች እየተፈለጉ በቡድን በቡድን ሆነው በያቅጣጫው ተልከው የነሱ መልስ እስኪደርስ መጠበቁ ነው ጉዞዋችንን የሚጎትተው » አሉ ፊታውራሪ።

«በዘመናዊ የጦር ትምህርት ከሰለጠነውና በዘመናዊው የጦር መሳሪያ ሁሉ ከታጠቀው የጣሊያን ጦር ሰራዊት ጋር ግንባር ለግንባር ከመግጠም ይልቅ ከጀርባው መንገዶችን እያፈረሱ፥ የመሳሪያና የስንቅ ማከማቻዎችን እያቃጠሉ የድብቅ ጦርነት መዋጋቱ ኢጣሊያን የበለጠ እንደሚጎዳና ኢትዮጵያን የበለጠ እንደሚጠቅም የውጭ አገር የጦርነት ስልት አማካሪዎች ለኢትዮጵያ መንግስት ምክር ሰጥተዋል » እየተባለ ሲነገር እሰማ ነበር፤ ራስ እምሩ በዚያ ጊዜ ያን ዘዴ በስራ ለማዋል በመሞከር ላይ መሆናቸውን ግን ያንለት ፊታውራሪ ሀይሉ መማቴ ነበር።

እውነትም ሁዋላ የጣሊያን ዋና ጦር መምሪያ ጦርነቱን ይመራበት የነበረውን መንገድ እንደ ተመለከትሁት - ቀደም ብሎ ታስቦበት - የኢትዮጵያ

ጦር የጣሊያንን ጦር በግንባር መግጠሙ ሳይቀር ወዲያው ከዚያ ጋር ተጣምሮ በጦር ግንባሮች አካባቢ ከሚኖሩት ባላገሮችና ከወታደሩ ክፍል ተውጣጥተው በቡድን በቡድን እየተደራጁ በጀርባው ተሰማርተው መንገዶቹን የሚያፈርሱና የነዳጅ የመሳሪያና የስንቅ ማከማቻዎችን የሚያቃጥሉ ድርጅቶች ቢኖሩ ኖሮ የጦርነት ጠባይም ሆነ የመጨረሻ ውጤቱ የተለየ ይሆን እንደ ነበረ የሚያምኑ ሰዎች ቢኖሩ ከነሱ አንዱ እኔ ነበርሁ። ነገር ግን በድሜየም የጭፍራ አለቃ ባለመሆኔም ምክንያት ስለ ጦርነቱ ጉዳይ ምክር ሲደረግ ተካፋይ ሆኘ ስላማላውቅ፥ አሳቤን በግል ላንዳንድ መኩዋንንት ወዳጆችና አጋጣሚ ሳገኝ ለራስ ከመግለፅ በቀር በስብሰባ ለመግለፅ እድል አልነበረኝም። በዚያ ዘዴ መዋጋት ጣሊያንን የሚጎዳ መሆኑን በጭዋታ ላይ ከገለፅሁላቸው መኩዋንንት አንዱ «ጠላቱን በድብቅ የሚያጠቃ ሌባ፥ ወይም አጋሚዶ ነው እንጂ፥ እንኩዋንስ የመንግስት ጦር አንድ ጀግና ጎበዝ ተሸሽቶ ጠላቱን አያጠቃም » ብለው ያፌዙብኝ ትዝ ይለኛል።

የጣሊያን ጦር ሰራዊት በሚዋጋበት የጦር ግንባር ይዞት የሚሰለፈው መሳሪያ ጥይት ነዳጅ ስንቅና ሌላውም ለውጊያ አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ ለጥቂት ቀናት ያክል ነው እንጂ እንደ ኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ጥይቱን ሁሉ በወገቡ ዝናር ታጥቆ ስንቁን ባጠገቡ አድርጎ አይሰለፍም። በግንባር የሚዋጋውን የጣሊያን ጦር ሰራዊት በማናቸውም ነገር (በመሳሪያ በነዳጅና በስንቅ) የሚመግበው ድርጅቱ (ሎጅስቲክስ) አደጋ እንዳይደርስበት በግንባር ከሚዋጋው ሰራዊት ርቆ ወደ ሁዋላ መሆን አለበት። የጣሊያን 4ኛ ጦር ሰራዊት (አርሚ ኮር) «ሰለክለካ » ግንባር ሲሰለፍ ባክስምና ባድዋ አጠገብ ከነበረው መጋቢ ድርጅት ይዞት የሄደው ለ3 ቀን የሚሆን የወታደር ስንቅና ያጋሰስ ገፈራ ለ2 ቀን የጠመንጃና የመትረየስ ጥይት ለ1 ቀን የሚሆን የመድፍ ጥይት መሆኑን «ማርሻል ባዶሊዮ » ቀደም ብዬ በጠቀስሁት መፅሀፋቸው ይናገራሉ። እንዲሁም «የልኡል » ራስ ካሳ «ጦር በከፊል መገናኛ ቆርጦ » የመጀመሪያውን የተንቤን ትልቅ ጦርነት «ድል ባደረገ ጊዜ » ማርሻል ባዶሊዮ እንዲህ ይላሉ፡-

«በመጀመሪያው የተንቤን ጦርነት የጠላት ሀየል በማየሉ፥ የኛ አዛዥ ለጊዜው የጦሩን ሜዳ መልቀቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲለቅ ከመቀሌ 70.000 ወታደር 14.000 የጭነት አጋሰስና 300 መድፍ ወደ ሁዋላ ለመመለስ ጥናት ስናደርግ ከዚያ ጋር እዚያ ተይዞ የነበረውን ከሁለት እስከ ሶስት ቀን የሚበቃ ጥይት፥ ለስድስት ቀን የሚሆን የወታደር ስንቅና ያጋሰስ ገፈራ ለዚያ ያክል ቀን የሚሆን የነዳጅና ልዩ ልዩ መሳሪያ ለማጉዋዝ መንገዱ በከፊል ደህና ስላልነበረ ተቸግረን ነበረ። ደግነቱ የራስ ካሳ ጦር እዚያው በመቆሙ ሁኔታው ቀስ በቀስ እየተረጋጋ ሄዶ አስግቶን የነበረው ችግር ሳይደርስብን ቀረ። »

ይህ ማርሻሉ ያለው ስንቅ ጥይት፥ ነዳጅና እነሱን የመሰለውን ለጦርነት የሚሆነውን አላቂና ላለቀ ነገር መተኪያ ሁሉ ለጥቂት ቀናት ከሚያስፈልገው በቀር የቀረው አይነተኛው በግንባር ከሚዋጋው ጦር ሰራዊት ተለይቶ በመጋቢ ድርጅቶች (በሎጅስቲኮች) ውስጥ የሚቆይ መሆኑን ስለሚያስረዳ መጋቢ ድርጅቶች (ሎጅስቲኮች) ከተቃጠሉ ወይም አቀባባይ መንገዶች ከፈረሱ ተዋጊው ሠራዊት ለውጊያ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ይቋዋረጥበትና ጦርነቱን መቀጠል አይችልም ማለት ነው።

ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት በግንባር የሚዋጋ ጦር ሰራዊት እንዳደራጀ እንዲሁም ከጠላት ሁዋላ በመጋቢ ድርጅቶችና (ሎጅስቲክስ) በመንገዶች ላይ የድብቅ ጦርነት ለማድረግ የሰለጠኑ ብርቱ ሀይሎች ቢያደራጅና በሁለት ግንባር (በፊትና በሁዋላ) ቢዋጋ ኖሮ ኢጣሊያ ቶሎ ድል ባትሆን ግንባር ምናልባት ጦርነቱ ሁለተኛው ያለም ጦርነት እስከ ተጀመረበት ጊዜ ተራዝሞ በኢትዮጵያ ላይ ያዘመተችውን የጦር ሰራዊት ወደ አውሮፓ ለመመለስ ትገደድና ኢትዮጵያም ላጭር ጊዜም ጊዜም ቢሆን የነፃነት ክብርዋን ሳትገፈፍ ትቀር ነበር እላለሁ። ይህ መቸም የኔ አስተያየት ነው። ስለዚህ እዚህ ላይ ላቁመውና አሁን ፊታውራሪ ሀይሉ «ከጠላት ጦር ጀርባ ስለ ነበሩት መጋቢ ድርጅቶችና መንገዶች መረጃ ለማምጣት በያቅጣቸው ተልከዋል » ወዳሉዋቸው ሰዎች ልመለስ።

ከኒያ «በያቅጣጫው ተልከዋል » ከተባሉት የመረጃ ቡድኖች አንዱ የሰለክለካን ተራራ መሽጎ ከተሰለፈው የጣሊኢያን ጦር ጀርባ በጣም ራቅ ብሎ በሰፊው በሽቦ የታጠረና በወታደር በጥብቅ የሚጠበቅ - ባልሳሳት - «ራማ » የተባለ ጦርና የመሀንዲስ መሳሪያ የነዳጅና የስንቅ መጋቢ ማከማቻ ለማቃጠል ይወስንና አቶ ‹ዮሀንስ አብዱ› (ሁዋላ ሻለቃ) የሁለት ግራዝማቾች ጦር አስተባብሮ ሄዶ እንዲያቃጥለው ይታዘዛል። ከሁለቱ ጋራዝማቾች አንዱ ግራዝማች ባያብል ደስታ ያዬ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ «የደስታ መሸሻ » ልጅ ነበሩ። ግራዝማች «ግራዝማች ደሴ » (ያባታቸውን ስም ረስቻለሁ) ዳሞት ውስጥ አንድ የጭፍራ አለቃ ነበሩ።

ያባቶ ዮሀንስ የተመራው የሁለት ግራዝማቾች ጦር ቀን በዋሻ ውስጥ ተሸሽጎ እየዋለ ሌሊት እየተጉዋዘ ራማ ደርሶ ለጥበቃ የተመደበው የጣሊያን ጦር ላይ ድንገት አደጋ ይጥልና ከብርቱ ጦርነት በሁዋላ ድል አድርጎ መጋቢ ድርጅቱን አጥፍቶ ይመለሳል። በዚኢያ ጦርነት ከኢትዮጵያውያን የሞቱና የቆሰሉ ስንት እንደ ነበሩ ላውቅ አልቻልሁም። እዚያ ከጣሊያን ሹማምንትና ወታደሮች የሞቱና የቆሰሉ 141 (አንድ መቶ አርባ አንድ) መሆናቸውን ፅፎዋል። ታዲያ ማርሻሉ «በዚያ ጦርነት ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን ድል አድርገው አባርረው እንሰኡ ከ2ኛው ጦር ሰራዊት (አርሚ ኮር) ጋር ተጨመሩ » ይላል። 2ኛው ጦር ሰራዊት «ሰለክለካ » መሽገው ከተሰለፉት የጣሊያን ጦር ሥራዊቶች አንዱ ነበር። ነገር ግን ጣሊያኖች ማሸነፋቸው እውነት አይደለም። እውነቱ ጥንቱንም ኢትዮጵያውያን መጋቢ ድርጅቱን ለማጥፋት እንጂ ለመያዝ ስላልሄዱ የሄዱለትን ፈፅመው ብዙ ጣሊያኖችን ገድለውና አቁስለው ጥቂት ጣሊያኖችንም (5 ይሁን 6 ረስቻለሁ) ማርከው በሄዱበት አሆሁዋን ሌሊት ሌሊት ተጉዘው ወደ ሰፈራቸው መመለሳቸው ነው። ማርሻል ባዶሊዮ እንደሚለው ጣሊያኖች «ራማ » ወይም አፍጋጋ ላይ ድል ቢያደርጉ ኖሮ፥ ከነሱ ከሞት የተረፉት ቦታቸውን ትተው ወደ 2ኛው የጣሊያንጦር ሰራዊት ባልሸሹ ነበር። ኢትዮጵያውያንም የማረኩዋቸውን ጣሊያኖች ይዘው ወደ ሰፈራቸው ባልተመለሱ ነበር።

ባቶ ዮሀንስ አስተባባሪነት ራማን ለማጥፋት የታዘዘው የግራማች ባያብልና የግራዝማች ደሴ ጥምር ጦር ቀንቶት መመለሱንና ራስ ሰፈር የሚደርስበትን ጊዜ ገና በመንገድ ሳለ አስቀድሞ አስታውቆ ስለ ነበረ ራስ መኩዋንንቱና ሰፈር ከቀረው ሰራዊት ብዙው ወጥተው ተቀበሉት። ድል አድራጊው ጦር የማረካቸውን ጣሊያኖች እመሀል አድርጎ በሰልፍ «አድራጊው ጦር የማረካቸውንጣሊኢያኖች እመሀል አድርጎ በሰልፍ «አሞልማልጉሚ » እያለ እያረበረበ በራስና በተቀባዩ ሰራዊት ፊት ሲያልፍ ጣሊያኖችም ያሞልማልጉሚን ቅኝት በግድ ተምረው ከማራኪዎቻቸው ጋር ተሰልፈው ሲያረበርቡ ምንም እንኩዋ ያይን የተያዙበትን ወጥመድ ያጠመዱት ራሳቸው ቢኢሆኑ ያሳዝኑ ነበር። ከመሀከላቸው አንዱ ክንዱን ሊቆረጥ ትንሽ እስኪቀረው በጎራዴ ተመትቶ ያን ሊቆረጥ ትንሽ የቀረው ክንዱን በግድ አያይዘው አስረው ወደ ላይ ባንገቱ አጥልቀውለታል። ታዲያ ያን ተሸክሞ እሱም ከማራኪዎቹ ጋር ሲያረበርብ ማየቱ ከማሳዘን አልፎ የሚያስቆጣ ስለ ነበረ ራስ ተቆጥተው ጣሊያኖች ከሰልፉ እንዲወጡና ቁስለኛው ቀደ ግሪኩ ሀኪም ተወስዶ ህክምና እንዲደረግለት አዘዙ።

ከዚያ እኒያ የተማረኩ ጣሊያኖች ባዲስ አበባና በዳባት መሀከል አልፎ አልፎ በሚመላለሰው የኢትዮጵያ አይሮፕላን ወዳዲስ አበባ እንዲሄዱ በማግስቱ ይሁን በሳልስቱ ወደ ዳባት ተላኩ። ሁዋላ ከዘመቻው መልስ አቶ ዮሀንስ አብዱና እኔ ዳባት ተላኩ። ከዘመቻው መልስ አቶ ዮሀንስ አብዱና እኔ ዳባት ሁለት ቀናት በቆየንበት ጊዜ ስለ ጣሊያን ምርኮኞች ብንጠይቅ «አይሮፕላኑ ካዲስ አበባ እስኪደርስ ባንድ ቤት ውስጥ ሲጠበቁ እንዲቆዩ ተደርጎ የቁስለኛው ሽታ ጉዋደኞቹን በማስቸገሩ ለብቻው ድንኩዋን ተተክሎለት በተቀመጠበት አንድ ቀን የጣሊያን አይሮፕላን መጥቶ በዳባት አንድ ሌላ ነገር ሳይነካ እሱን ብቻ በቦምብ ገድሎ ሄደ ሌሎች ወደ አዲስ አበባ ተላኩ » አሉን።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

# የሰለክላካ ጦርነት

ሰለክላካ በአክሱምና በእንዳስላሴ መሀከል፥ ከምስራቅ እስከ ምእራብ በበዙ ኪሎ ሜትር ርዝመት ተዘርግቶ የሚታይ፥ ትልቅ ተራራ ነው። ማርሻል ባዶሊዮ ደጋግሜ በጠቀስሁት መፅሀፍ እንደ ገለፀው የጣሊያን 2ኛው ሰራዊቶች (አርሚ ኮርስ) ያን ተራራ፥ ከአክሱም ወገን እስከ አናቱ ድረስ መሽገው ተሰልፈውበት ነእብር። 2ኛውና 4ኛው ሰራዊቶች በመሀከላቸው አምስት ክፍላተ ጦር (ዲቪዥንስ) እና አንድ «ብርጌድ » ነበራቸው ለሁለቱ ሰራዊቶች አስተባባሪ ራሱ መሆኑን ማርሻል ባዶሊዮ ሲገልፅ እንዲህ ይላል። «ሁለቱን ሰራዊት አስተባብሮ ለመሥራት እንዲመቸኝ የመምሪያ ቦታየን ከጀርባ ቀረብ እንዲል አድርጌ ነበር። »

የራስ እምሩ ጦር፥ እየዘገመ ሲጉዋዝ ብዙ ወራት ካሳለፈ በሁዋላ የካቲት 19 ወይም 20 1928 (ትክክለኛው ቀን ረስቻለሁ) እንዳስላሴ ደረሰ። ሰለክለካ አናት ላይ የመሸገው የጣሊያን ጦር፥ ጠላት ወደ ተራራው እንዳይጠጋ ለመከላከል ቀንና ሌሊት ሳያቋዋርጥ መድፉን ከሩቅ ሲስሙት የሰማይ ነጎድጉዋድ እንጂ እውነት የመድፍ ተኩስ አይመስልም ነበረ። የባውዛው መብራትም ሌሊቱን ሙሉ እንዲሁ ሳያቋዋርጥ ከሰለክለካ ተራራ ወደ እንደስላሴ ወገን ያለውን አገር ሁሉ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ እንደገና ወደ ምስራቅ እየተሽከረከረ እንዳበራ ያድር ነበር።

የራስ እምሩ ጦር እንደስላሴ በደረሰበት እለት ማታውን ፊታውራሪ ጦርና የተቆጠሩ ያውራጃ ገዥዎች የግልና የየግዛታቸውን እይደንብ ጦር ይዘው መሽጎ የሚጠብቀውን የጣሊያን ጦር ለመግጠም ታዝዘው የሄዱት ድጋፍ እንዲሰጡ ስለ ታዘዙ፥ እየተከታተሉ ይሄዱ ጀመር። በመጨረሻ የካቲት 22፥ 1928 ማታ ይመስለኛል ራስ ባጠገብ ሆነው ጦርነቱን ለመምራት ከሳቸው ጋር የቆየውን ጦር ይዘው ወደ ግንባር ሄዱ። ከመነሳታቸው በፊት ሁሉም ጉዋዙንና ጉዋዝ ጠባቂውን እዚያው እንዳስላሴ ትቶ ከመሳሪያው ጋር የእለት ስንቁን ብቻ

እየያዘ ወደ ጦርነቱ ግንባር እንዲሄድ በየሰፈሩ ስለ ተለፈፈ በቅሎ ያለው የለት ስንቁን በከረጢት አድርጎ በኮርቻ ድህራው እያነገበ እግረኛው የስንቅ ቀረጢቱን ባንገቱ አግብቶ በብብቱ ስር እያንጠለጠለ ደረቅ ጦር ሆኖ ወደ ግንባር ገሰገሰ። እኛም አጭሩ ዘሪሁንን ለጉዋዝ ጥበቃ እንደስላሴ ትተን አቶ ዘውዴና ጤናው እኔና ረዥሙ ዘሪሁን እንደ ትእዛዙ የለት ስንቃችንን ይዘን ተከተልን።

የራስ መምሪያ፥ ከንዳስላሴ ወገን አንድ ትንሽ ወንዝ ከግርጌው አድርጎ፥ ከሰለክለካ ተራራ ጥግ ነበር። ያ ቦታ ለዚያ ጦርነት ሲባል ካይሮፕላን ቦምብና ከመድፍ ጥይት እንዲጠብቅ ቀደም ብሎ ታስቦ በጥናት የተሰራ እንጂ ባጋጣሚ የተገኘ አይመስልም። እዚያ ስንደርስ እጦሩ ግንባር የመድፉ የመትረየሱና የጠመንጃው ተኩስ አንድ አፍታ እንኩዋ ጋብ ሳይል መደዳውን ይንጎደጎድ ስለ ነበረ፥ ሰው ተርፎ የሚያድር አይመስልም ነበረ። ነገር ግን፥ ያ ሁሉ ተኩስ ጣሊያኖች የኛ ጦር ምሽጋቸውን ሰብሮ እንዳይገባባቸው የኛ ጦር በበኩሉ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው የተሰለፈበትን ቦታ እንዳይዙበት ለመከላከል እንጂ ሁለቱ ወገን ጠላቶች እስበሳቸው እየተያዩ፥ ወይም አንዳቸው ባንዳቸው ላይ እያነጣጠሩ የሚተኰሱት ስላልነበረ ከሁለቱም ወገን ጉዳት ቢኖር ከስንት አንድ ነበረ። በማግስቱ ግን የካቲት 23 1928 ከንጋት ጀምሮ የመከላከሉ ተኩስ እያበቃ በሱ ፈንታ የመገዳደሉ ተኩስ ሲተካ ሁኔታው ተለውጦ የካቲት 23 ከንጋት ጀምሮ የዋለው ጦርነት እንደ ቋያ እሳት በፊት የተማገደውን ብቻ ሳይሆን አልፎ ባካባቢው ያለውንጭምር የሚፈጅ ነበር። ደግነቱ ጦርነቱ በጣሊያን ምሽግ ላይና ባካባቢው ስለ ነበረ እዚያ፥ ኢትዮጵያውያንን ለይቶ መምታት አስቸጋሪ በመሆኑ ያይሮፕላን ቦምብና የከባድ መድፍ ጥይት አልነበረም። አይሮፕላኖችና ከባድ መድፎች የሚደበድቡ ሰፈራችነንና ከሰፈር ወደ ጦሩ ግንባር የሚሄዱትን ነበር። በምሽጉና ባካባቢው የጦርነቱ ግጥሚያ በጣልያኖች በኩል በቀላል መድፍ በከባድና በቀላል መትረየስ እንዲሁም በጅ ቦምብና በጠመንጃ ሲሆን በኢትዮጵያውያን በኩል በጠመንጃና በጎራዴ ነበር።

ራስ እመምሪያቸው ውስጥ እንዳሉ፥ በግንባር ከሚያዋጉት ኢትዮጵያውያን አዛዦች ልዩ ልዩ መልእክቶች ይደርሱዋቸው ነበር። ታዲያ እኒያ መልእክተኞች በተሰሙ ቁጥር እዚያ በነበረው ሰው ሁሉ ፊት አንዳንድ

ጊዜ ፈገግታ አንዳንድ ጊዜ ቅሬታ ይታይ ነበር። አንዱ ጠላትን ከምሽጉ ወደ ሁዋላ እንዲያፈገፍግ ማድረጉንና እሱ ምሽጉን መያዙን አስታውቆ ጠላት ሀይሉን አጠንክሮ የተመለሰ እንደሆነ ለመመከት የሚያስችለው ጦር እንዲጨመርለት ይጠይቃል። ቆየት ብሎ ሌላው ጠላት በሰውና በመሳሪያ ብዛት ያየለት በመሆኑ ትንሽ ለማፈግፈግ ስለተገደደ ተጨማሪ ጦር እንዲላክለት ይጠይቃል። ደግሞ ሌላው በወታደሩ ላይ ከባድ የሞትና የመቁሰል ጉዳት ስለ ደረሰ ረዳት ጦር እንዲላክለት ይጠይቃል። አሁንም ሌላው ከሰዎቹ የሚበዙት ስላለቁ ከተረፉት ጋር እንዳይከበብ ቶሎ ከመከበብ የሚያድነው ርዳታ እንዲደርስለት ይማጠናል። ከዚያ ሌላው ከምሽግ ውጭ በጎን የጠላት ብርቱ ጦር ድንገት ስላለ፤ ቶሎ የሚመልሰው፥ ወይም ባለበት የሚያግደው ከሱ የበረታ ሀይል ካልተላከለት እሱ ያሰለፈውን ጦር ከመክበብ አልፎ ዋናውን መምሪያ የሚያሰጋ መሆኑን ያስጠነቅቃል። ራስም እንዲያ ላለው ሁኔታ መጠባበቂያ ተቆትቦ ከቆየው ጦር ወደየተጠቀበት ግንባር በያለቃው እንዲሄድ ተቆጥቦ ከቆየው ጦር ወደየተጠየቀበት ግንባር በያለቃው እንዲሄድ ትእዛዝ ይሰጣሉ። እንዲያ ሲሆን ቀኑ ወደ ቀትር ግድም ሆነ። እስከዚያ ድረስ፥ ሶስቱ ጉዋደኞችና እኔ የጭፍራ አለቆችም ያለእቃ ጭፍሮችም ስላልነበረርን ወደ ግንባር ከታዘዙት ጋር እንድንሄድ ባለመታዘዛችን እዚያው እራስ መምሪያ ሆነን ከግንባር የመጡት የሚያወሩትን ስንሰማና ወደ ግንባር ታዘው የሚሄዱትን ስናይ ዋልን።

ያንለት፥ ደጃዝማች አያሌው ብሩም ራስ መምሪያ ውስጥ አብረዋቸው ነበሩ። ደጃዝማች ተከዜ አፋር የራስን መልዕክት ላደርስላቸው ሄጄ ካየሁዋቸው በሁዋላ ከያለለት በቀር አይቻቸው አላውቅም ነበር። እንዲያውም ከራስ ጋር ተቀምጠው ከግንባር አዛዦች የተላኩ መልእክተኞች እየመጡ «ጠላት አየለብን ሰው አለቀብን ልንከበብ ነው ከምሽግ ውጭ የሚያየው ብርቱ የጠላት ጦር ዋናውን ምሽግ እንዳይከብ ያሰጋል። » እያሉ መልእክታቸውን በተናገሩ ቁጥር አሽከሮቻቸውን አንድ ባንድ እያስጠሩ ተከዜ አፋፍ እኔን የተቀበሉ እለት እንዳፈረጉት ያስፈክሩ ነበር።

እዚህ ላይ እንዳመለከትሁት ወደ ቀትር አካባቢ አቶ ዘውዴ ጤናውና እኔ ባንታዘዝም የመጣንለት ተግባራችን ስለሆነ ወደ ጦርነቱ ግንባር እንድንሄድ

ተመካከረንና ዘሪሁን ረዥሙ በቅሎዋን ይዞ እዚያው ራእስ መምሪያ እንዲቆዬን ትተነው ከታዘዙት ወታደሮች ጋር ወደ ግንባር ለመሄድ ከመምሪዊያው ወጣን። የተጉዋደንናቸው ወታደሮች በከርት ማለታቸውን አይተን ተከተልናቸው እንጂ በምን ደንብ ውስጥ እንደሆኑና ማንኛውን የግንባር አዛዥ ሊረዱ እንደሚሄዱ አላወቅንም ለመጠየቅም ጊዜ አልነበረንም። ከመምሪያው ዋሻ እንደ ወጣን ባካባቢው ያለውን ቁጥቁዋጦና ቅጠሉ የተቃጠለ ዛፍ ብቻ የሚታይበትን ክፍል አልፈን ወደ ጦርነቱ ቦታ የተቃረንብ ስንሄድ አንድ ቦታ ላይ እሩምታ የተተኮሰ የከባድ የቀላል መሳሪያ ጥይት ከላይ እንደ ናዳ ወረደንብ። ያን ጊዜ ሁላችንም በያለንበት ወደቅን። ያ ቦታ ካካባቢው ሁሉ ገለጥ ያለ በመሆኑ ልንቆይ የምንችልበት አልነበረም። ፊቱንም እንድያ ብዙ ሆነን ተበታትነን መሄድ ሲገባን እንደ ሰርገኛ ባንድነት እጅብ ብለን ስንሄድ እዚያ ገላጣ ቦታ ላይ የጠላት ቃፊር ከሩቅ አይቶን ይሆናል መሳሪያውን አስተባብሮ የተኮሰብን። ትንፋሼን አስተጋብቼ መተንፈስ እንደቻልሁ የተሻለ ቦታ ለፊቴ አንድ ትልቅ ቁዋጥኝ ድንጋይ ስላየሁ በጉንብሴ እየሮጥሁ ሄጄ እሱን ተጠጋሁ። ወዲያው ጉዋደኞቼ አብረውኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በቀኝም በግራም ባይ ጤናው ብቻ ተከትሎኛል፤ አቶ ዘውዴ የለም።

«አቶ ዘውዴስ ተመትቶ ይሆን የቀረ? » አልሁት ጤናውን በጣም ደንግጬ።

«ኧረ እንጃ! አንተን ወደ ፊት ስትሮጥ ሳይህ ጊዜ ተከትዬህ ሮጥሁ እንጂ ወደሱ ዘወር ብዬ አላየሁም። ግን የተመታ አይመስለኝም እንዲያውም ሰው ያለ አይመስለኝም » አለ ጤናው።

«የተመታ ሰው አለመኖሩ እንዴት ይታወቃል? »

«የቆሰለ ሰው ቢኖር እዚያው እንዳለን የስቃይ ድምፅ እንሰማ ነበር??

«እስቲ ለማናቸውም ወድቀንበት ወደ ነበረው ቦታ ተመልሰን እንፈልገው፤ ተመትቶ እዚያው ካልቀረ ከሌሎች ጋር በሌላ አቅጣጫ ወደ ግንባር ቢሄድ ነው » አልሁ።

«እዚህ ቆይ እኔ ደርሼ ልምጣ » አለ ጤናው። ግን ቦታውን ራሴ ካለየሁት የልብ ርጋታ የማገኝ ስላልመሰለኝ ከጤናው ጋር አብሬ ሄጄ ወድቀንበት የነበረውን ቦታ ብቻ ሳይሆን ባካባቢው ሁሉ ፈልገን አቶ ዘውዴን አላገኘነውም፣ ጤናው እንዳለው ሌላ ቁስለኛም በቦታው አልነበረም። ከዚያ በሌላ አቅጣጫ ሄዶ እጦርነቱ ውስጥ መግባቱን አምነን እኛም ወደዚያው ሄድን። ጠላት የሚተኩሰው የልዩ ልዩ መሳሪያ ጥይት በፊት የተሰለፉትን አልፎ ከጀርባ ያለውን ዛፍና ቁጥቋጦ ይጨፈጭፍ ስለ ነበረ እግንባር ደርሶ ቦታ መያዙ ቀላል አልነበረም። ሆኖም እንደ ምንም ብለን በግንባር ቦታ ያዝን። ብቻ ያ ቦታም፤ ከሱ በሁዋላ ሁለት ጊዜ ያክል ለውጠን የያዝናቸው ቦታዎችም አንዳንዶቹ ከጠላት ጥይት ሊተግኑን የማይችሉ መስለው እየታዩን አንዳንድ ደግሞ አላማችንን ለመምታት የማይመቹ እየሆኑብን ቢያንስ ከሶስት ጊዜ ያላነሰ ቦታ ለውጠናል። ግንባሩን ስንለቅ ወደ ምእራብ ሰሜን የተሻለ ቦታ ያየን ሲመስለን ተኩሱ ትንሽ ፋታ እስኪሰጥ እንጠብቅና አጎንብሰን እየሮጥን፥ ወይም በሆዳችን እየተሳንን ከቆየንበት ቦታ ወዳዲሱ እንዛወራለን። የጦርነቱ ግንባር ከምእራብ ሰሜን እስከ ደቡብ ምስራቅ ሲሆን እኛ ወደ ምእራብ ሰሜን መጠጋቱን የመረጥንበት ምክንያት በተለይ፥ እኔን ቶልቶሎ ውሀ ይጠማኝ ስለነበረና ከራስ መምሪያ ግርጌ የተሻገርናት ወንዝ የምትወርድ ከዚያው ከምእራብ ሰሜን አቅጣጫ ስለሆነ ከዚያች ወንዝ ላለመራቅ ከዚያው ከምእራብ ሰሜን አቅጣጫ ስለሆነ፥ ከዚያች ወንዝ ላለመራቅ ነበር። ውሀ ጥሙ ሲጠናብኝ ጤኢናው ኮዳ ይዞ ስለ ነበረ በሆዱ እየተሳበ ሁለት ጊዜ ወድ ወንዝ እየሄደ የራሱን እዚያው ጠጥቶ ለኔ ኮዳውን እየሞላ ሲያመጣልኝ ቆየ። ነገር ግን ሶስተኛ ሲሄድ ጣሊያኖች ከላይ ቆርጠውብን ይሁን ወይም ውህው አልቆ «አፍህን ታረጥብበት እንደሆን » ብሎ ጭቃ ይዞልኝ መጣ።

መቸም ሰው አስቦና አቅዶ ከሞት የሚድንበትን መንገድ እንጂ ወደ ሞት የሚወስደውን መንገድ እንደማይከተል የታወቀ ነው። ነገር ግን ይልቁንም ብዙ ህዝብ ባለበት ቦታ የቁጣ የሲቃ ወይም የፍርሀት ስሜት የሚያስነሳ ሁኔታ ተፈጥሮ አእምሮን እንዳያስብና እንዳያመዛዝን ሲሸፍን የሚከተሉት መንገድ ወደ ሞት ወይስ ወደ ደህንነት የሚወስድ መሆኑን ለይቶ ማየት አይቻልም። ያን ጊዜ እንደ በግ መንጋ በስሜት ብቻ ተነድቶ ፊት የቀደመውን ተከትሎ ወደ

ጥፋት ቢሆን እየተንጋጉ መሄድ ነው። ይህ እውነት መሆኑን ያንለት በምእራብ ሰሜን ያየሁት ትርእይት የሚያሳምን ነበር፤ እስከ ዛሬም። ያ ትርእይት ለብዙ ጊዜ በህልሜ ይመጣብኝ ነበር፤ እስከ ዛሬም ስለ ጦርነቱ ሳስብ ባይነ - ህሊናዬ ፊት በጉልህ እየተደነቁ ከሚታዩኝ ስእሎች አንዱ እሱ ነው።

ቀደም ብዬ እየደጋገምሁ እንዳመለከትሁት ጣሊያኖች፥ ምቹ ቦታ እየመረጡ አለፍ አለፍ አድርገው በሰሩዋቸው ምሽጎቹ ላይና ባካባቢያቸው ነበር ጦርነቱ የሚደረገው። የኢትዮጵያውያን ምሽጎች ግን እግዚአብሔር ከፍም ዝቅም አድርጎ ሰርቶ እዚያ ያስቀመጠላቸው ደንጋዮችና አለፍ አለፍ አድርጎ ያበቀለላቸው ቅጠላቸውን የቦምብ እሳት ያቃጠላቸው ግንዶች እንዲሁም ውሀ ሸርሽሮ ያጎደጎዳቸው ጉድባዎች ብቻ ነበሩ፤ በጥንቃቄ የተሰሩ ምሽጎች አልነበሩዋቸውም። ታዲያ እኒያ ደንጋዮች፤ ግንዶችና ጉድባዎች ጠላት ከከፍተኛ ምሽጉ በከባድና በቀላል መሳሪያ ከሚወርድባቸው ጥይትና የጅ ቦምብ በቂ መንድ ሊሆኑ ስለማይችሉ እዚያ እንዳሉ የሚገድሉና የሚቆስሉ ብዙ ነበሩ። ባንፃሩ። ጠላት አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ጉዳት በዝቶባቸው ወደሁዋላ ለማፈግፈግ ሲገድዱ እንዳይመለሱ ቦታ ሊይዝ ከመውጣቱ በቀር የሚበዛውን ጊዜ በጥንቃቄ በተሰራ ምሽግ ውስጥ ተጠብቆ ስለሚዋጋ ያን ያክል ጉዳት አያገኘውም አግኝቶትም እንደሆን አይታይም። ይህ ኢትዮጵያውያንን ሳያናድድና ሳያስቆጣ እንዳልቀረ የታወቀ ነው። ጠላት የሚተኩሰው ጥይት ሳያስቆታ እንዳልቀረ የታወቀ ነው። ጠላት የሚተኩሰው ጥይት ሳያስቆጣ እንዳልቀረ የታወቀ ነው። ጠላት የሚተኩስ ጥይት ጠላትን ሲገድልና ሲያቆስል አለማየታቸው እነሱ የሚተኩሱት ጥይት ካገራቸው ደንጋይ ጋር ሊዋጋ የዘመቱ ይመስል በጠላት ፈንታ የምሽግ ደንጋይ ሲደበድብ ማየታቸው ይህ ሁሉ የያንዳንዳቸውን ልብ አስቆጥቶና ሁሉንም ተስፋ አስቆርጦ ተስፋ የቆረጡ ሁሉ የሚያደርጉትን እንዲያደርጉ የስሜት መገናኛ አስተባብሮ አስነሳቸው።

ከሁለቱም ወገን ተኩስ እንደ ተፋፋመ ሳለ፥ ምንም ትእዛዝ ሳይሰማ፥ ፊትም ሁዋላም ከተሰለፉት ኢትዮጵያውያን ብዙዎች አለቃና ጭፍራ እንደ ተማከሩ ሁሉ ባንድነት «ሆነ! » ብለው አውክተው በመንገድ ተመትተው የወደቁት ወድቀው የቀሩት ኢጣሊያኖች ምሽግ ውስጥ ገብተው የጨበጣ ጦርነት ገጠሙዋቸው እዚያ ከኢትዮጵያውያን ሽጉጥ ያለው በሽጉጥ ሌላው

በጎራዴና በጩቤ ያ የሌለው በጠመንጃው አፈሙዝ ጣሊያኖች በሳንጃ በጅ ቦምብና ባላቸው መሳሪያ ሲጨፈጭፉ ሲተራረዱ ከቆዩ በሁዋላ፥ ጣሊያኖች ያን የግንባር ምሽጋቸውን ለቀው ከሁዋላ ለማፈግፈጊያ ወደ ተሰራ ምሽጋቸው ሸሹ። ብቻ የግንባር ምሽጋቸውን ለጊዜው ቢለቁም በሁዋለኛው ምሽግ ውስጥ የግንባር ምሽጋቸውን ለጊዜው ቢለቁም በሁዋለኛው ምሽግ ውስጥ ከነበሩት ጋር ሀይላቸውን አስተባብረው ኢትዮጵያውያንን እንደ ገና ወደ ነበሩበት ባንዳንድ ቦታም ከዚያ አሳልፈው ወደ ሁዋላ መለሱዋቸው። እዚያ ምሽግ ውስጥ ስንት ኢትዮጵያውያንና ስንት ጣሊያኖች እንደሞቱ ስንት እንደቆሰሉ ጣሊያኖች ቦታውን ይዘው ስለ ቀሩ መቸም ያውቃሉ እኛ፤ ግን አላወቅንም። እኔና ጤናው ለጨበጣው ጦርነት ተካፋዮች ሳይሆኑ አወደ ሁዋላ ከቆዩት መሀከል ነበር። ጤናው «ሆ! » ብሎ የተነሳው ወታደር ሲቃ ተጋብቶበት ተነስቶ ሩጫ ጀምሮ ነበር። ነገር ግን ተከትዬ ይዤው ብዙ ከታገልን በሁዋላ አሸንፌ አስቀረሁት።

ጤናውና እኔ እቀትር ላይ ወደ ግንባር ከሄድን ጀምሮ ጦርነቱ የይባህር ማእበል ይመስል እንዲያው ወደ ፊት ሲሄድና ወደ ሁዋላ ሲመለስ ግንባሩ ምንም ያክል ሳይለወጥ በነበረበት እንዳለ ቀኑ እየመሸ ሄደ። ጨለምለም ሲል ከኛ ወገን ተኩስ እየተቀነሰ ይሄድ ጀመር። ባቅራቢያችን በየድንጋዩና በየግንዱ ስር አድፍጠው ይተኩሱ ከነበሩት ሰዎችም አንዳንዶቹ በቦታቸው አይታዩም ነበር። የጣሊያኖች ተኩስ ግን ምናልባት የኛው መቀነሱን ጎልቶ እንዲሰማ አድርጎት እንደሆን እንጂ እንዲያውም የጨመረ ይመስል ነበር።

«ወደ መምሪያው ሄደን እዚያ ምን እንደሚደረግ ብናይ ምን ይመስልሀል? አሁን ስለጨለመ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ወደ ፊት ለመግፋት የሚደፍሩ አይመስለኝም » አለኝ ጤናው።

«ደህና አስበሀል እንሂድ » አልሁት። ወደ መምሪያው የመሄድ አሳብ ስለ ተነሳ እንደሆን አላወቅም፤ ራብ ተሰማኝ። ከነጋ እህል አልቀመስንም ነበር። ከዚያ የጠላት ጥይት እንዳያገኝ ቀስ ብለን ካንድ ተገን ወደ ሌላ እየተላለፍን እወንዝዋ ስንገባ አንደኛ ከየአቅጣጫው እየመጣ ወንዝዋን ተከትሎ ወደ መምሪያው አኩዋያ የሚወርደው ወታደር ብዙ ሆኖ አገኘነው። ትንሽ እንደ

ሄድን አቶ ዘውዴንም ከኛ ዝቅ ብሎ ከነበረ ግንባር ከሚመለሰው ወታደር ጋር ሲመጣ አገኘነውና ጤናውም እኔም ከደስታችን ብዛት የተነሳ እስኪጨንቀው እያቀፍን ሳምነው። ሽሽት የተጀመረ መሆኑን የነገረን አቶ ዘውዴ ነበር።

«አይደረግም! መች ድል ሆነና ነው የምንሸሸው? ወታደሩ ግንባሩን ይዞ እየተዋጋ! » አልሁ በጣም ደንግጬ።

«ጠላት በብዙ ግንባር ከማየሉም ሌላ በጎን ብርቱ ሀይል አውጥቶ ዋናውን መምሪያ ለመክበብ በማስጋቱ ነው ወደ ሁዋላ ማፈግፈግ ግዴታ የሆነው ይባላል። ስለዚህ ጠላት መሸሻችንን አውቆ እንዳይከተል አንዳንድ የጭፍራ አለቆች ሰዎቻቸውን ይዘው እስከ እኩለ ሌሊት ግንባር ሳይለቁ ሲተኩሱ እንደቆዩ ተደርጎ የቀረው ጦር ቀስ እያለ እንዲመለስ በመነገሩ ገና በጊዜ ነው ሰው መመለስ የጀመረ፥ እኛ ከፊተኞችም ከመጨረሻዎችም አደለንም፤ ከመሀከለኞች ነን » አለ አቶ ዘውዴ።

«እኛ በነበርንበት ግንባር አሁን ያልኸው ትእዛዝ መነገሩን አልሰማንም ወታደሩም ግንባሩን ሳይለቅ በመዋጋት ላይ እንዳለ ነው ትተነው የመጣን፤ ታዲያ እንዴት ነው ባንዳንድ ግንባር ለሚዋጋው ወታደር እንዲመለስ ሲነገረው በሌላው ግንባር ላለው የማይነገረው? » አልሁ ግራ ገብቶኝ።

«እንጃ፤ ምናልባት የናንተ ግንባር ወታደሮች እስከ እኩለ ሌሊት ሲተኩሱ ቆይተው ሁዋላ እንዲከተሉ ከተመደቡት ክፍሎች ሊሆኑ ወይም ተረስቶ ትእዛዝ ሳይደርሳቸው ቀርቶ ሊሆን ይችላል » አለ አቶ ዘውዴ።

«ወዲያውምኮ እኛ ከሄድን ጀምረን ግንባራችንን ይዘን ስንተኩስ ዋልን እንጂ ከሰዎች ጋር ተቀራርበን ለመነጋገር ጊዜ ስላልነበረን የደረሰ ትእዛዝ ቢኖርም ካልተለፈፈ ልናውቅ አንችልም » አለ ጤናው።

የራስ መምሪያ ወደ ነበረው ዋሻ ስንደርስ እዚያ ማንም አልነበረም እውነትም ሽሽት ሆኖዋል! ትናንት ሌሊቱን ሙሉና ያንለት እስከ ስድስት ሰአት ግድም ጢስ እንዳጤሰበት የቀፎ ንብ ያን ዋሸሻና አካባቢውን ሞልቶ ሲዋነብ ሲተራመስ ከነበረው ሰራዊት ሁሉ ያን ጊዜ አንድ አልነበረም። ሁሉም

ሲተራመስ ከነበረው ሰራዊት ሁሉ ያን ጊዜ አንድ አልነበረም። ሁሉም ሸሽተዋል። ከዚያ ዝም ብዬ ወደ ዋሻው በራፍ ስሄድ አቶ ዘውዴና ጤናው ተከተሉኝ። ለምን እንደ ሄድሁ አላውቅም። ብቻ እዚያ በራፍ ቆሜ ወደ ውስት ሳይ ማስፈራራቱ! የዋሻው ውስጥ በሌሊቱ ጨለማ ላይ የሲኦልን ግርማ እንደ ደረበ ሁሉ በጣም ያስፈራ ነበር።

«አሁን እዚህ ዋሻ ውስጥ ምን የሚኖር መስሎህ ነው ልታይ የመጣህ? እባክህ ና እንሂድ » አለኝ አቶ ዘውዴ እጄን ይዞ። ከዚያ ስንመለስ ከዋሻው በራፍ ትንሽ ፈንጠር ብሎ አንድ ትልቅ ደንጋይ አየሁና ወደሱ ኄጄ እስሩ ስቀመጥ አቶ ዘውዴ እፊቴ ቆሞ ለተናገረው መልስ ስላልሰጠሁት እሱም ጤናውም ዝም ብለው ባጠገቤ ተቀመጡ። ያቶ ዘውዴ ድምፅ እንጂ የተናገረው ምን እንደ ሆነ አልተሰማኝም ነበር። ያን ጊዜ የማደምጠው አሳቤ መልስ ሳያገኝ እያከታተለ የሚጠይቀውን ጥያቄ ነበር። «እንግዲህ ድል ሆነ ማለት ነው? ድል መሆን እንዲህ ነው? በደባጉናና በራማ ጠላትን ድል መትቶ መሳሪያውን ገንዘቡን ሰውንም የማረከ የኛ ጦር ነበር። እኔ ባየሁት መጠን እስከ ዛሬም ድረስ ቀኙ የኛ ነበር። እስከ ዛሬ ድረስ አሸናፊው የኛ ጦር ነበር። ዛሬም ቢሆን የሌላውን ግንባር አላውቅም እንጂ፥ በኛ ግንባር የተሰለፈው ወታደር ከተሰለፈበት ግንባር ስንዝር ሳይለቅ በመዋጋት ላይ እንዳለ ነው። ታዲያ ድል መሆን እንዲህ ነው? የጠላት ጦር ዋናውን መምሪያ ለመክበብ ስላሰጋ ወደ ሁዋላ መሸሽ ግዴታ ሆነ የተባለውስ ለመክበብ ያሰጋው የጠላት ጦር የት አለ? ጠላት ያሰራቸው የውሸት ወሬ ታምኖ የጠላት የወሬ ጦርነት አስፈርቶ ይሆን ሽሽት የሆነ? እና ኢጣሊያን በመሳሪያ ብዛት ባይሆንለት በወሬ ጦርነት ድል አድርጋ ኢትዮጵያን ልትይዝ ነው? እና እንግዲህ የኢትዮጵያ የነፃነት ታሪክ መጨረሻ ሊሆን ነው? » እንዲህ እንዲህ ያለውን ጥያቄ ዝም ብዬ ብዝነ ህሊናየ ሳዳምጥ ቆየሁና «እንዴት! » አልሁ ሳይታወቀኝ ድምፄን አሰምቼ

«ምኑ ነው እንዴት? » አለኝ አቶ ዘውዴ።

«ጦርነቱ አልቀ ማለት ነው? ዛሬ የጦርነቱ መጨረሻ ሆነ ማለት ነው? » አልሁ።

«አ - ይ የጦርነቱ መጨረሻ አደለም። ጠላትን ለመቋቋቋም የሚያስችል የተሻለ ቦታ ይዞ ለመዋጋት ወደ ሁዋላ ማፈግፈግ ነው ሲባል እንጂ የመጨረሻ ሽሽት ነው ሲባል አልሰማሁም » አለ አቶ ዘውዴ። ታዲያ እኔን ለማፅናናት የተናገረው ነገር እንጂ እውነቱ አልነበረም ያ እለት የጦርነቱ መጨረሻ ነበር።

የሰለክለካ ጦርነት በሶስት ቀን ብቻ ያለቀ ይመስለኛል። ማርሻል ባዶሊዮ ግን በፈርንጆች አቆጣጠር የካቲት 29 ተጀምሮ መጋቢት 3 1935 ማለት ባራት ቀን ማለቁን ፅፎዋል። ከዚያ ጦርነት ከሁለቱ ወገኖች የሞቱትና የቆሰሉት ስንት እንደሆኑ በኛ በኩል አይታወቅም። ማርሻል ባዶሊዮ «የሞቱትና የቆሰሉት ከኢትዮጵያ ወገን 4.000 ከኢጣሊያ ወገን 63 መኮንኖችና 906 ወታደሮች ድምር 969 ነበሩ » ይላል። መቸም ጣሊያኖች በምሽግ ውስጥ ሆነው ከመዋጋታቸው ሌላ የመሳሪያ ብልጫቸው - ባይነትም ሆነ በብዛት - ኢትዮጵያውያን ከነበራቸው ጋር የማይቀራረብ እጅግ የላቀ ስለ ነበረ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰው ጉዳት የሚበልጥ መሆኑን አይቻልም። ይሁን እንጂ በጣሊያኖች ላይ ስለ ደረሰው ጉዳት ማርሻሉ የሰጠው ቁጥር ትክክለኛ መሆኑ ያጠራጥራል፤ ያሳነሰው ይመስላል።

## ምዕራፍ አስር

# ሽሽት

«እንሂድ እንጂ፥ እስከ መቼ እዚህ እንቀመጣለን? » አለ አቶ ዘውዴ።

«ወዴት? » አልሁት።

«ሰው ሁሉ ወደሚሄድበት። »

«ሰፈራችን ደርሰን ዘሪሁን ምን እንደ ሆነ ሳናውቅ? »

«ረዥሙ ዘሪሁንም በቅሎውን ይዞ ወዴት እንደ ሄደ አላወቅንምኮ። የሚሸሸውን ሰው ተከትሎ አልሄደ እንደሆነ ምናልባት፥ ወደ ሰፈር ሄዶ ይሆናል። ስለዚህ ለማናቸውም ሰፈር መድረሱ የሚያስፈልግ ይመስለኛል » አለ ጤናውም።

ከዚያ ተነስተን ወደ እንዳስላሴ ስንሄድ ከኛ በቀር ወደዚያ የሚሄድ ሰው አላየንም፤ ሁሉም ላዩን ወደ ደቡብ - ምስራቅ የሚወስደውን መንገድ ይዞ ነበር የሚጎርፍ። የንዳስላሴን መንገድ እንዳጋመስን ከሰፈራችን የሚመጡ ወታደሮች አግኝተን ብንጠይቃቸው ሰፈሩ በሙሉ መቃጠሉንና እዚያም አንድ ሰው አለመኖሩን ሁሉም መሸሹን ነገሩን። ቢሆንም እሰፈር ደርሰን የተባለው እውነት መሆኑ እንድናረጋግጥ ተስማማንና ሄድን። እውነትም ሰፈር በነእብረበት ቦታና ባካባቢው የድንኳዋንም፤ የሰውም ምልክት አልነበር ባዶ ነበር። «ሰፈሩ በሙሉ በቦምብ ተቃጥሎዋል » የተባለው ግን ወታደሮች አጋንነው ያወሩልንን ያክል ሆኖ አላገኘነውም። ምንም እንኳን ጊዜው ማታ ቢሆንና እኛም ሰፈሩን ሁሉ ዞሮ ለማየት ጊዜም ፍላጎትም ባይኖረን ያው በጨረቃ ብርሃን ማየት የቻልነውን ክፍል ያክል ብዙ የቃጠሎ ምልክት አይታይበትም፤ መጠነኛ ነበር። ቢሆንም የኛ ድንኳዋኖች ተተክለውበት ወደ ነበረው ቦታ ስንደርስ እስክናይ ድረስ ደባጉና የደረሰብን ጉዳት ገና ባሳባችን ውስጥ እንዳለ ስለ ነበረ እየፈራን ነበር የሄድን። ግን እዚያም የቃጠሎ ምልክት አልነበረም፤ ድንኳዋኖች ተነቅለው እቃው ሁሉ ተጠቅልሎ ተነስቶዋል። ስለዚህ አጭሩ ዘሪሁን ጉዋዙን ይዞ ሰው ሁሉ የሄደበት መንገድ ተከትሎ የሄደ መሆኑን አምነን እኛም ወደዚያው ተመለስን።

ሰው በሚሸሽበት መንገድ ስንደርስ ከግንባር እየተመለሰ ያን መንገድ ይዞ የሚሄደው በጣም ብዙ ነበር። አቶ ዘውዴ እንደ ነገረን እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ግንባሩን ሳይለቁ ሲተኩሱ እንዲቆዩ የታዘዙ ካሉ እንዲያውም ከግንባር የሚመለሰው ገና እስከ እኩለ - ሌሊትና ከዚያም በሁዋላ ይቀጥላል ማለት ነው።

ለካስ ሽሽቱ የተጀመረ ገና በቀን ኖሮ አይሮፕላን እየተከታተለ በቦምብ ሲደበደብ ከሞተው ሌላ ከመንገዱ ቀኝና ግራ በየዛፉም በየቁዋጥኙም ስር

ወድቆ «እግዚኦ » የሚለውን የሚማጠነውን ቁስለኛ መገመት ያስቸግራል፤ እጅግ ብዙ ነበር። አንዱ «እባካችሁ አይኔ እያየ አውሬ አይብላኝ፤ አንስታችሁ ሰፈር አድርሱኝ » ይላል። አንዱ «እባካችሁ ከወደቅሁበት ቀና አድርጋችሁ ዛፉን ወይም ደንጋዩን አስደግፉኝ » ይላል። ሌላው ‹ስለ በላኤ - ሰብ እምበኤት በጠብታ ውሀ አፌን አርጥቡልኝ » ይላል። ደግሞ ሌላው «በወንድ ልጅ አምላክ አንድ ጥይት አትንፈጉኝ፤ ገድላችሁኝ ሂዱ » ይላል። እኒህን ለምሳሌ ያክል ጠቀስሁዋቸው እንጂ የልመናው አይነት ብዙ ነበር። ታዲያ ምንም እንኩዋ ያን ከመንገዱ ቀኝና ግራም ከየዛፉና ከየቁዋጥኙ ስርም የሚሰማውን የተለያየ ልመና ያን የስቃይና የጣር ልመና ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰሙት ልብን በጣም የሚያስጨንቅና የሚያሰቅቅ ቢሆን እንዲያ ማስጨነቁም ሆነ ማሰቀቁ ለጊዜው ብቻ ጆሮ እስኪለምደው ብቻ ነው! እግዚኦታውና ምጥነታው እየተደጋገመ ከዚያም እየበዛ በሄደ መጠን ጆሮ ይለምደውና ድምፁን እንጂ፥ ቃሉን እስከ መስማቱም ይተወዋል! ስለዚህ ከዚያ መንገዱን ሞልቶ ተርፎ በቀኝና በግራ ቁጥቁዋጦውን እየጣሰ ይሄድ ከነበረው ሰራዊት መሀከል ከያቅጣጫው የተለያየ ርዳታ የሚለምኑትን ቁስለኞች መርዳቱ ቀርቶ ለመጠየቅ እንኩዋ መለስ ወይም ጎንበስ የሚሉ ቢኢንሩ ከስንት አንድ ነበሩ፤ እነሱም የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ ጠፍቶባቸው የሚፈልጉ ሳይሆኑ አይቀሩ! የቀረው የሚበዛው መንገዱን ሞልቶ እስበሱ እየተገፋፋ ከመንገዱ ቀኝና ግራ ቁጥቁዋጦውን እየጣሰ ዝም ብሎ ወደ ፊት መሄድ ብቻ ነው። በፊቱ ምን እንደሚቆየው ያውቅ ይመስል አይሮፕላን በፊቱ እንደማይቆየው እርግጠኛ የሆነ ይመስል ካይሮፕላን ለመሸሽ እስበሱ እየተገፋፋ ዝም ብሎ እውር ድንበሩን ወደ ፊት መሄድ ብቻ ነው!

መቸም አንድ ሰራዊት ድል ሆኖ እምሸሽ ሲጀመር እያንዳንዱ ሰው ነፍሱን ለማዳን ብቻ በደመነፍስ እየተነዳ ተያይዞ እንደ በግ መንጋ መንጋጋት ነው እንጂ በዚያ ጊዜ «ላደርገው የሚገባኝን አላደረግሁም » ብሎ የህሊና ወቀሳ ወይም «የምን ይሉኝ » ስሜት የሚሰማው አለመኖሩ የታወቀ ነው። ለመሆኑ ህሊናው ወቅሶት ለመርዳት የሚፈልግ ቢኖርስ ስንቱን ሊረዳ ይችላል? ወይስ ማነኛውን ረድቶ ማነኛውን ይተዋል? መፍረዱ የሚያስቸግር ነው። እንዲያ

ባለ ጊዜ እንዲያ ያለ ሁኔታ ሲፈጠር የሌሎች ጦር ሰራዊቶች ለውጊያው ተካፋዮች የማይሆኑና ድል አድርጊው ጦር ጉዳት እንዳያደርስባቸው ባለም - አቀፍ ህግ እየተጠበቁ ቁስለኞችን የሚረዱ እንደ «ቀይ መስቀል » ያሉ ድርጅቶች ይኖሩዋቸዋል። የኛ ጦር ሰራዊት ግን እንዲያ ያሉ ድርጅቶች ስላልነበሩት ቁስለኞቻችን የማዳን ወይም የመግደል ርዳታ ለማግኘት የሚጠብቁት ከጠላቶቻቸው ነበር! ስለዚህ ጠላቶቻቸው የሚያደርጉዋቸውን እንዲያደርጉዋቸው በየወደቁበት እንዳሉ ሲጮሁ እየሰማን ትተናቸው እንሄድ ነበር!

ከመንገድ ቀኛን ግራ ወድቀን ከሚጮሁት ቁስለኞች መሀከል ያንዳንዶቹ ድምፅ ልክ ያጭሩ ዘሪሁንን ይመስል ነበር። ዘሪሁን ከትምህርት ቤት ከወጣሁበት ቀን ጀምሮ ያልተለየኝ አብሮኝ የኖረ ስለ ነበረ መልኩን ሳላይ ከሩቅ በድምፅ የማውቀው ነበር። ታዲያ ያን ሌሊት «እባካችሁ ርዱን » እያሉ ከሚጮሁት መሀከል የሱን ድምጽ የሰማሁት ሲመስለኝ ቆም ብዬ፤ «በዚያ በኩል ‹ላውሬ ትታችሁኝ አትሂዱ የሚለው ዘሪሁን ነው » እላለሁ። ከዚያ እኔ ቀድሜ አቶ ዘውዴና ጤናው ተከትለውኝ ድምፅ ወደ ሰማሁበት እንሮጥና ቁስለኛው ዘሪሁን አለመሆኑን ስናይ አንስተን ልንወስደው አለመቻላችንን ነገርነው፤ ከወደቀበት ቀና ወይም ጋደም እንድናደርገው ፈልጎ እንደ ሆነ ጋደም አድርገን ወይም ቀና አድርገን አንድ ድንጋይ ወይም ዛፍ አስደግፈን እዚያው ትተነው እንሄዳለን። አሁንም ትንሽ እንደ ሄድን የዘሪሁንን የመሰለ ድምፅ ስሰማ ቆም እልና «ያ ‹ውሀ› እያለ የሚጮኸው ሌላ ሊሆን አይችልም ዘሪሁን ነው » እላለሁ። ወዲያው ‹ውሀ› ወደ ሚለው ቁስለኛ ሮጠን እንሂድና፤ በግንባሩ ተደፍቶ እንደሆነ ግለበጥ አድርገን አይተነው ዘሪሁን አለመሆኑን ስናውቅ በጀርባው አስተኝተን ትተነው እንሄዳለን! ደግሞ ስንሄድ ቆይተን የዘሪሁንን ድምፅ የሰማሁ ሲመስለኝ «በዚያ በኩል ‹ገድላችሁኝ ሂዱ› እያለ የሚማጠነው ያለ ጥርጥር ዘሪሁን ነው » እላለሁ። አሁንም ሶስታችን እየሮጥን ሄደን ቁስለኛው በጀርባው ወድቆ በደም እየዋኘ ሲሰቃይ ጎንበስ ብለን በጨረቃ ብርሃን በላብ የጠለቀ ፊቱን አይተን ዘሪሁን አለመሆኑ ስናረጋግጥ ከፈራችንን እየመጠጥን ብቻ ትተነው እንሄዳለን! እንዲያ የዘሪሁንን ድምፅ

የሰማሁ በመሰለኝ ቁጥር ከሁለቱ ጉዋደኞቼ ጋር መንገዳችንን እያሳበርን ያን ድምፅ ወደ ሰማሁበት ቦታ እየሮጥን እየሄድን ቁስለኞችን ስናገላብጥ ስናቃናና፤ ስናስተኛ ዘሪሁንን ሳናገኘው ሌሊቱ ነጋ! ያን ሌሊት ሁለቱ ጉዋደኞቼና እኔ ዘሪሁንን ፍለጋ ወድቀው እንደሆነ ቀና ድርገን ደንጋይ ወይም ዛፍ አስደግፈን አስቀምጠን የተውናቸው ደንጋይ ወይም፥ ዛፍ ተደግፈን ተቀምጠን እንደሆነ ዝቅ አድርገን አስተኝተን የተውናቸው ካንድ ጎናቸው ወደ ሌላው መገላበጥ ፈልገው እንደሆነ አገላብጠን የተውናቸው ቁስለኞች ስንት እንደሆነ እግዜር ይወቅ እንጂ እኔ እንኩዋንስ አሁን ያን ጊዜ ባፍላውም ላውቅ አልችል ነበር!

የቢጋ ንጋት ከሰአቱ ብርሃን ስለሚቀድም ሰአቱ ገና ሳለ፥ ብርሃኑ ቀደም ብሎ አገሩን በሙሉ ቀን አደረገው። ወዲያው ያይሮፕላን መልክ ሳናይና ድምፅ ሳንሰማ ከሁዋላችን በሩቁ፥ ቦምብ እየተከታተለ ሲፈነዳ ተሰማን። መጀመሪያ እንዲያ ሲንጎደጎድ ከሩቅ የሰማነው የመድፍ እሩምታ ተኩስ መስሎን ነበር። ነገር ግን ካጭር ጊዜ በሁዋላ አይሮፕላኖች በሁለትም በሶስትም ቡድን ሆነው መንገዱን ሞልቶ እየተተራመሰ በሚሸሸው ሰራዊታችን ላይ ከባድ ቦምባቸውን እያወረዱበት ሲመጡ ታዩ። ያንለትና በተከተሉት ቀናት ይጥሉዋቸው የነበሩት ቦምቦች ባለ ስንት ኪሎ ግራሞች መሆናቸውን አላውቅም እንጂ፤ ከዚያ በፊት ይጥሉዋቸው ከነበሩት በጣም ከፍተኞች ነበሩ። አንዱ ቦምብ ተጥሎ በፈነዳ ጊዜ መሬቱን በላዩ እስከ በቀለው ዛፍና ቁጥቁዋጦ ጎርዶ ብዙ ሜትር ወደ ሰማይ ሲያጉነው፤ እስሩ ተቆፍሮ የሚቀረው ጉድጉዋድ ጎርዶ ብዙ ሜትር ወደ ስማይ መጠነኛ የቤት ክፍል ባይበልጥ የማያንስ በጣም ሰፊ ነበር። ጥልቀቱም በዚያው መጠን ነበር። ታዲያ እኒያ አይሮፕላኖች ሰራዊታችንን ከደጀኑ እስከ ፊታውራሪው ጦር ድረስ እንዲያ በቡድን በቡድን ሆነው እየተከታተሉ በቦምብ ሲደበድቡ ተስፋ መቁረጡ አፍዝዞን እንደሆነ አላውቅም፤ ከመሀከላችን ወደነሱ የሚተኩስ አልነበረም። የሚበዛው ሰው እንኩዋንስ መተኮሱን አይሮፕላኖች አልፈው እስኪሄዱ ድረስ እንደ ፊቱ ተበታትኖ በየዛፉና በየቁዋጥኙ ስር ተተግኖ መቆየቱን ረስቶ ከላዩ ቦምብ እየወረደ ዝም ብሎ ወደ ፊት ብቻ ይሄድ ነበር። ደግነቱ፥ አይሮፕላኖች ቦምብ የሚጥሉ ከፍ ካለ ርቀት በባዶው ቦታ ላይ ነበር የሚወድቅ። ስለዚህ ምንም እንኩዋ ራሱን መርሳትና

ይወርድ ከነበረው የቦምብ ብዛት አንፃር ሲመለከቱት «በሰውም ሆነ በከብት ላይ የደረሰው ጉዳት ሊደርስ ይችል ከነበረው ያነሰ ነበር » ማለት ይቻላል።

ያንለትና ከዚያ በፊት በነበረው ሌሊት፥ ከዚህ በላይ ባጭሩ እንደ ተረከሁት መንገድ ይታይ የነበረውን የመከራና የስቃይ ትርኢት ሳስታውስ ከሁሉም ጎልቶ ባይነ ህሊናየ ፊት የሚታየኝ ባንድ ሴት ላይ ሲደርስ ያየሁት ነው። አንድ ያይሮፕላን ቡድን ደብድቦን ካለፈ በሁዋላ ዛፍና ቁዋጥኝ ወይም ሌላ ተገን ወዳለበት መሸሹን ያልረሳን ሰዎች ከየተሸሸግንበት ወጥተን ስንሄድ እንደቆየን አይሮፕላኖች ከሁዋላችን እንደ ገና ቦምብ እየጣሉ ሲመጡ ሰማን። ያንጊዜ የደረስንበት ቦታ የዘንባባ ዛፎችና ሌሎች ዛፎች አለፍ አለፍ ብለው የበቀሉበት ስለ ነበረ ወዳሉበት እየሸሸን ተጠጋን። በበቅሎ ተቀምጣ ጥቂጣችን ዛፎች ወዳሉበት እየሸሸን ተጠጋን። በበቅሎ ተቀምጣ ከሰራዊቱ ጋር የምትሄድ አንድ ሴት ነበረች። ይች ሴት ባለማህደር ዳዊት ባንገትዋ አግብታ ካንድ ብብትዋ ስር አንጠልጥላ አንድ አጭር ዲሞትፈር ጠመንጃ እንዲሁ ባንገትዋ ስር አንጠልጥላ አንድ አጭር ዲሞትፈር ጠመንጃ እንዲሁ ባንገትዋ አግብታ በጀርባዋ አዝላ ባንድ እጅዋ የተቀመጠችበትን በቅሎ ዛብ በሌላ እጅዋ የተጫነች አጋሰስ በረዥም ለኮ ይዛ ከሁዋላዋ እየሳበች ትሄድ ነበረ። በክፉ አጋጣሚ አይሮፕላኖች እዚያ ቦታ ሊደርሱ ሲቃረቡ፥ አጋሰስዋ ገረገረችባት፥ (ቆማ ወደ ሁዋላ ሳበቻት።) ዘውር ብትል ያጋሰስዋ ጭነት ባንድ ወገን አጋድሎ ከጀርባዋ ወደ ሆድዋ ወርዶዋል። ከዚያ ሴትዬዋ ከበቅሎዋ ወርዳ ያጋደለውን ጭነት ወዳጋሰስዋ ጀርባ ለመጫን ትታገል ጀመር። ያን ጊዜ ሁላችንም ያይሮፕላኖችን መድረስ አይተን «ሴትዮ አይሮፕላኖች መጡብሽ በቅሎዎችን ተያን ነይ! እባክሽ ተያቸውና ወዲህ ነይ! » እያለን ከያለንበት ጮህን። እሷ የኛን ጩኸትም ሆነ ቦምብ እየጣሉ የመጡትን አይሮፕላኖች አይታም አትሰማም ነበር። አይንዋም ጆሮዋም አሳብዋም ሁሉ ተሰብስቦ ያተኮረው ያን ያጋደለ ጭነት መልሳ ለመጫን በጀመረችው ትግል ላይ ብቻ ነበር። ከየዛፉና ከየቁዋጥኙ ስር ስንጮህ ከነበርነው መሀከ አንድ ሰው ሴትዮዋን ለማዳን ወደስዋ ሮጦ ነበር። ነገር ግን አይሮፕላኖች ስለ ቀደሙት ከመሀል መንገድ ወደ መሸሸጊያው ተመለሰ። ያች ሴት እንዲያ ካጋሰስዋ ጭነት ጋር በመታገል ላይ እንዳለች አይሮፕላኖች ከጣሉትዋቸው ቦምቦች አንዱ እስዋና በቅሎዎችዋ

በቆሙበት መሀል ወደቀ። ወያው ያ፥ የቆሙበትና በዙሪያው የነበረው መሬት ሁሉ ተጎርዶ ብዙ ሜትር ወደ ሰማይ ሲነሳ የስዋና የበቅሎዎችዋ የመሬቱ፥ የደንጋዩ የሳሩና የቁጥቋዋጦው ብጥስጣሽ ባንድነት ተደባልቶ ባየር ውስጥ ከጉዋነ በሁዋላ ተምለሶ ቦምቡ መሬቱን ጎርዶ ሲያነሳው እስር ተቆፍሮ በቀረው ሰፊ ጉድጉዋድ ዙሪያ ተበተነ። ታዲያ የሚያስገርመው አይሮፕላኖች እዚያ ባጠገባችን በጣሉት ብዙ ቦምብ ከዚያች ሴትና ከበቅሎዎችዋ በከዚያ ሁሉ ሰራዊት ሞቶ ወይም ቆስሎ ሲወድ ያየነው አልነበረም።

አይሮፕላኖች ከሄዱልን በሁዋላ ከየዛፉ ስር ወጥተን መንገዳችንን ስንቀጥል ሴትየውና ለማዳን ሩጫ ጀምሮ የነበረው ሰው እንደ ነገረን፥ ያቺ ሴት ያንድ መኮንን በጣም የሚወዱዋት የጭን ገረድ ኖራለች። ከሁለት ቀን በፊት የመኮንኑ አሽከሮች እጦርነቱ ውስጥ አልቀው እሳቸውም ክፉኛ ሲቆስሉ፥ ከሞትም ከመቁሰልም የዳኑ እስዋና አንድ ወንድ አሽከራቸው ብቻ ኖረዋል። ጌትየው በፅኑ ቆስለው በጣእር ውስጥ እንዳሉ እስዋ ባጠገባቸው ሆና ስታስታምማቸው እንደማይተርፉ ተረድተው ኖሮ «አንቺና ተስፋው (ወንዱ አሽከራቸው) ከሞት ተፋችሁ አገራችሁ ለመግባት የበቃችሁ እንደሆነ፤ መሳሪያየንና አባቴ ሲሞቱ ለመታሰቢያቸው የሰጡኝን ዳዊቴን ለልጄ ለንጋቱ እንድታደርሱልኝ አደራ። እሱ እስኪያድግ የናቱ ወንድም ብላታ በየነ ባላደራ ሆነው ይጠብቁለት » ብለው ተናዘው ሞተዋል። እንዲኢህ ያቺ ሰው ሁሉ ነፍስዋን እንድታድን ያን ያክል ሲማጠናት አይንዋ እያየ በቦምብ ተቃጥላ የሞተች የወዳጅዋን ያደራ ኑዛዜ ለመፈፀም ኖሮዋል! ምን አይነት እስከ ሞት የሚያደርስ ታማኝነት ምን አይነት ሀይል ፍቅር ቢሆን ነው!

«ለሀይማኖትዋ ብላ ለማተብዋ ብላ እንዲያ ተቃጥላ ሞተች! » አለ ሰውየው የሴትየዋን ታሪክ ከተረከልን በሁዋላ እየተከዘ።

«እንዴት ለሀይማኖትዋ ብላ? ያይሮፕላን ቦምብ ስንቱን አቃጥሎ ሲጨርስ እያየች ካጋሰስ ጭነት ጋር ስትታገል መሞትዋ ‹ሀይማኖተኛ› የሚያሰኛት መስሎዋት ነው? እንዲህ ያለው ሞኝነት ወይም እብደት ነው እንጂ

ሀይማኖተኝማነት አደለም! » አለ ጤናው ከማዘኑ የተነሳ ቆጣ ብሎ፤ ግን ሀያል ፍቅር ሞኝም እብድም ሀይማኖትም ሁሉንም ያደርጋልኮ!

ከዚያ ራስና ከሰራዊቱ አብሮዋቸው የሚጉዋዘው ክፍል በሰፈሩበት ዋሻ አጠገብ ደረስንና ከኛ ጋር ከነበሩት የሚበዙት ሰራዊቱ የሚሄድበትን ዋና መንገድ እንደ ያዙ ሲቀጥሉ ሁለቱ ጉዋደኞቼና እኔ አንዳንድ ሰዎች ጭምር ወደ ራስ ሰፈር አመራን። እህል ከቀመስን ሁለት ሌሊትና አንድ ቀን አልፈው ሁለተኛው ቀን መጀመሩ ስለነበረ ዝለን እግራችንን እየጎተትን ነበር የምሄድ። ስለዚህ እሰፈር እንደ ደረስን ራስን ከማየታችን በፊት ትንሽ ለማረፍ አንድ ዛፍ ስር ገደም ባልንበት ድካምና እንቅልፍ ተደራርበው ተጨንውን እኩለ ቀን ሲሆን ነቃን። ከዚያ ወደ ራስ ሄደን እጅ ነስተን ተመልሰን ትንሽ እንድ እቆየን ሁለት አሳላፊዎች አንዱ እንጀራ በጥራር፥ ሁለተኛው አገልግል ሙሉ ፍትፍት ይዘው መጡ። ያንጊዜ ለኔ ያ አሳላፊዎች ይዘው የመጡት እንጀራና ወጥ ዘወትር የምንበላው አንዳንድ ጊዜም ተርፎን የምንጠው መስሎ አልታየኝም ነበር። በመልኩም ገና ሳልቀምሰው በጣሙም ከማውቀው እንጀራ ወጥ ሁሉ የተለየ ተበልቶ የማይጠገብ መልሶ ነበር የታይኝ። ወዲያው ባጠገባችን በርከት ያሉ ሰዎች ስለ ነበሩ በኛና በነሱ መሀከል ሲከፋፈል ለያንዳንዳችን የሚደርሰን ያለ ጥርጥር ትንንሽ መሆኑን አሰብሁና፥ እኒያ ሰዎች ላይ አንድ አይነት የጥላቻ ስሜት ተሰማኝ። ከዚያ ለኒያ ሰዎችና ለኛ፥ ባለጥራሩ እንጀራ እየቆረሰ በጅ በጃችን ሲያሲዘን ባላገልግሉ እጁ እስኪሞላ ፍትፍቱን እያፈሰ በያዝነው እንጀራ ላይ አድርገውልን ሄዱ። ያን ከቀማመስን በሁዋላ እዚያ ባጠገባችን ልትነጥፍ ምንም ያክል ያልቀራት ትንሽ ወንዝ ስለ ነበረች ጤናው ሄዶ የራሱን እዚያው ጠጥቶ ላቶ ዘውዴና ለኔ እንደ ምንም አጠራቅሞ ግማሽ ኮዳ ውሀ አምጥቶልን መጣንና እንደ ገና ተኝተን ከመሸ በሁዋላ ነቃን። «እክል ያፀንአ ለሰብ » አደል? ያ አንዳንድ እፍኝ ጉርሻም ከምግብ ተቆጥሮ ነፍስ ዘራብንና በርታ በለን ተነሳን። ምግቡን የተካፈሉን ሰዎች ግን ስንነሳ አልነበሩም ሄደዋል። የነሱን መሄድ ሳይ ወዲያው አሳላፊዎች እንጀራና ፍትፍት ይዘው መጡ እዚያ በመኖራቸው የተሰማኝ ጊዜያዊ የጥላቻ ስሜት ትዝ አለኝና ሰውነቴን ታዝቤው ሳይታወቀኝ ራሴን እየወዛወዝሁ ፈገግ አልሁ።

«ምን ታስቦህ ነው ራስህን እየወዘወዝህ የምትስቅ? » አለኝ ጤናው ያየኝ ሳይመስለኝ አይቶኝ ኖሮ።

«ምንም አደል እንዲያው፥ ነው » አልሁት፥ ድንገት ስለ ጠየቀኝ የምሰጠ መልስ አጥቸ እውነቱንም እንዳልናገር አፍሬ።

ሌሊቱን ከራስ ጋር ከዚያ ሰፈር ተነስተን ሲነጋጋ ለተከታዩ ቀን ሰፈር እንዲሆን መሪዎች በመረጡት ቦታ ደረስን። ያ ቦታ ካንድ ትልቅ ተራራ ስር - ለስር የተራራው ርዝመት ተከትሎ እስከ መጨረሻው የሚደርስ ዋሻ ነበር። እዚያ ዋሻ ውስጥ ራስን የተከተለው ሰራዊት ሁሉ ጥቅልል ብሎ ገብቶ ሰውም ሆነ ከብት አይታይ ነበረ። ጠቋዋሚ ካላመለከተው በቀር፤ «ጠላት እዚያ ቦታ ሰው መኖሩን ጠርጥሮ ቦምብ ይጥል ይሆናል » ተብሎ የሚያሰጋ አልነበረም።

ቀኑን አርፈን የምንውልበት ቦታ ለመምረጥ ስንዘዋወር ከልጅ (ሁዋላ ቀኛዝማች) አለማየሁ ቦጋለ ጋር ተገናኝተን እሱ ከያዘው ቦታ አጠገብ ሰው ያልያዘው ባዶ ቦታ አግኝተን እዚያ አረፍን። ልጅ አለማየሁ ከጉዋዙና ከጉዋዝ ጠባቂዎቹ ጋር አንደኛ እንዳስላሴ ቢለያዩም፤ በቅሎና ስንቅ ከያዘለት አሽከሩ ጋር አልተጠፋፋም ኖሮዋል። ስለዚህ እጭዋታ ላይ የጦርነቱን ግንባር ከለቀቅን ጀምሮ በቅሎየንና ስንቃችንን ከያዘው ሰው ጋር መጠፋፋታችንን ስነግረው በጣም አዝኖ የተረፈውን ትንሽ ስንቅ አብረነው እንድንከፋፈል አጥብቆ ለመነን።

«የተረፈህን ስንቅ ትንሽ ከሆነ ያኑ ትንሹን አሁን አራግፈህ ለኛ አካፍለህ ሁዋላ አንተም እንደኛ ከመራብ በቀር የምትቀምሰው የት ታገኛለህ? እኛስ እንደዚያ እንደ ምቀኛው ነጋዴ ካልሆነ በቀር ከንቱ ላንጠግብ አንተንም እንደኛ ስትራብ ማየቱ ምን ይጠቅመናል? » አልሁት «ምቀኛው ነጋዴ ተናገረ » የተባለው ትዝ ስላለኝ እንደ መሳቅ ብዬ።

«የምን ምቀኛ ነጋዴ ነው? » አለ ልጅ አለማየሁ።

«ያ ወረቁን ወንበዴዎች ዘርፈውት ሰዎች ተሰብስበው ሲያስተዛዝኑት ‹ከመዘረፌ የባሰ የሚያስቆጨኝ አብረውኝ የነበሩት ነጋዴዎች ሁሉ አንድ ነገር ሳይወሰድባቸው እኔ ብቻ መዘረፌ ነው› ያለው አልሁት።

«ላህኑ የማይበቃ መሆኑ ነው እንጂ የሚያሳዝን ለሁዋላውስ ግዴለም እግዜር ያውቅልናል » አለ በተረቱ ሲስቅ ቆይቶ። «ለሁዋላውስ..... » አለ ቀጥሎ። «ለሁዋላውስ ከዚህ ተነስተን ከተከዜ ወዲያ ማዶ እጋራው ጥግ ስንሰፍር እንዳስላሴ የተውነው ጉዋዛችንም ሰዎቻችንም ከቦምብ ቃጠሎ ተርፈው እንደሆነ እዚያ እንገናኝ ይሆናል። »

«እስካኍን ያልተገናኘን እዚያ እንደምንገናኝ እንዴት ይታወቃል? »

«ሰራዊቱ ለየብቻ ተበታትኖ ጋራውን እንዳይወጣና የደጋውን አገር ህዝብ እንዳይበድል ግንባር ቀደሞ ጦር እንዲያግደው ትእዛዝ ተሰጥቶዋል። ስለዚህ መንገድ ለመንገድ ከደረሰው የቦምብ አደጋ የተረፈው ሁሉ እዚያ ሳይገናኝ አይቀርም » አለ። ልጅ አለማየሁ፤ ራስ ከሹማምንቱ ጋር ምክር ሲያደርጉ ተካፋይ በመሆኑ እኛ የማናውቀውን ያው ነበር።

ከዚያ የነበረውን ትንሽ በሶና ዳቦ ቆሎ አሸከሩ አምጥቶ እፊታችን አራግፎ አቅርቦን ከሄደ በሁዋላ፤ «ለሱስ ምን ቀረው ልንጨርስበት ነውኮ! » አልሁ።

«ድንገት በመንገድ የተጠፋፋን እንደሆነ እንዳንቸገር ሁላችንም ድርሻችንን ተከፋፍለን ይዘናል፤ ስለዚህ እሱም ሌሎችም ትንንሽ ይኖራቸዋል ይህ የኔ ድርሻ ነው » ሲለኝ የሱን ጥንቃቄ በልቤ አድንቄ እኔም እንደሱ ባለማድረጌ ራሴን ነቀፍሁ።

የልጅ አለማየሁን ስንቅ ሁለቱ ጉዋደኞቼና እኔ ከሱ ጋር ተከፋፍለን በልተን የሌሊቱን ፋንታ በየቦታችን ልንተኛ ስንሰናዳ መንገዱን ይዞ በሚጉዋዘው ላይ ቦምብ እየጣሉ ወደ ተከዜ የሚያልፉትን አይሮፕላኖች ድምፅ ከመስመታችን ሶስት ወይም አራት ጊዜ ያክል ተደጋግሞ ሲተኮስ ሰማን። ተኩሱ ደከም ያለ ስለ ነበረ ከኛ ራቅ ብሎ ባይሮፕላኖች ላይ የተተኮሰ መስሎን ነበር። ግን ባይሮፕላኖች ላይ የተተኮሰ አልነበረም «ባለቃ አምሳሉ የተመኙ »

ላይ የደረሰ ድንገተኛ አደጋ ነበር። አለቃ አምሳሉንና «ድማህገነት (ሁዋላ መላከ ፀሀይ) ታዬን፤ አለቃና ሊቀ ጠበብት ሆነው ደብረ ኤልያስንና ያካባቢውን ገጠሮች ሲገዙ በልጅነቴ አውቃቸዋለሁ። ያለቃ አምሳሉን ጉብዝናም በቅርብ የሚያውቃቸው ሰዎች ሲያደንቁ ሰምቻለሁ። በድሮው የጌቶች ባህል ሲያበሉና ሲያጠጡ አይናቸው የማይሳሳባቸው ለጋስ መሆናቸውን እኔም አይቻለሁ። የልኡል ራስ ሀይሉ ፀሀፌ ትእዛዝ በነበሩ ጊዜ ሎሌዎቻቸውንና ዘመድ ወዳጃቸውን ብቻ ሳይሆን ወደ ራስ ሀይሉ ላቤቱታና ለደጅ ጥናት ከሚሄደው ሰው ለሚበዛው ባልደረባ (ጉዳይ አስፈጻሚ) እሳቸው ስለ ነበሩ ያን ሁሉ ሰው ጉዳዩን ጨርሶ እስኪመለስ በዬለቱ ግብር እያገቡ ሲያበሉና ሲያጠጡ የሚኖሩ ለጋስ መሆናቸው በሰፊው የታወቀላቸው በመሆኑ «አባ ባህር » ይባሉ ነበር

ያነለት አለቃ አምሳሉና ድማህገነት ታዬ ከጦርነቱ ሚዒኤዳ ሲመለሱ፥ ራስ እዚያ ተራራ ስር መሆናቸውን ሰምተው ወደሳቸው ለመሄድ ከዬበቅሎዋቸው ወርደው አፋፍ ላፋፍ እየሄዱ ተራራውን የሚወርዱበት መንገድ ሲፈልጉ አይሮፕላን ይመጣባቸዋል። አለቃ አምሳሉ አይናቸውን ታመው በቅጥ ማየት አይችሉ ኖሮ፥ ድማህገነት ፊት ፊታቸውን ሲሄዱ እሳቸው እዬተከተሉ ይሄዱ ኖሮዋል። ድህማገነት ባቅራቢያቸው አንድ ዛፍ ያዩና እዚያ ተጠግተው አይሮፕላኖችን ለማሰስለፍ «ና ወንድሜ ብለው ሲሄዱ አለቃ በሳቸው ለመድረስ ቸኩለው የሚቆሙበትን ሳያዩ ባንድ ድንጋይ ላይ ይቆሙና ድንጋዩ ተገልብጦ ይጥላቸዋል። ከዚያ ድማህገነትም የተከተሉዋቸው አሽከሮችም ሊያነሱዋቸው ሲሮጡ ቁልቁለት ስለ ነበረ አምልጠዋቸው እየተንከባለሉ ከገደሉ አፋፍ ይደርሳሉ። ከዚያ ገደሉ ብዙ እርከኖች ስለ ነበሩት፤ ካፋፍ ተወርውረው በመጀመሪያው እርከን ላይ ሲወድቁ ያ አንጥሮ ወደ ታችኛው እርከን ይወርውራቸዋል። እንዲያ ከላይኛው እርከን ወደ ታችኛው እየተወረወሩ በወደቁ ቁጥር የታጠቁት ሽጉጥ እየተተኮሰ ራስ በሰፈሩበት ከገደሉ ስር ወርደው ይወድቃሉ። ለካስ ያ ቀደም ብሎ በአይሮፕላኖች ላይ እየተደጋገመ የተተኮሰ መስሎን የነበረው ደከም ያለ ተኩስ ካለቃ አምሳሉ ሽጉጥ የተተኮሰው ኖሮዋል! እኛ ወሬውን የሰማን ትንሽ ቆይተን ነበር።

ልጅ አለማየሁና እኔ ከጉዋደኞቻችን ጋር አለቃ አምሳሉ ከገደሉ ስር በወደቁበት ቦታ ስንደርስ አሽከሮቻቸው ቀደም ብለው ደርሰውላቸው ቅጠል ጎዝጉዘው በላይ ምንጣፍ አንጥፈው በጀርባቸው አስተኝተዋቸው ነበር። እንዲያ ተኝጠው ሲንቀሳቀሱ፥ ወይም ሲተነፍሱ ስለማይታዩ የህይወት ምልክት የማይታይባቸው የሞቱ ይመስሉ ነበር። ጎንበስ ብዬ ስዳስሳቸው ግን ሰውነታቸው ይሞቃል፤ ወደ አፍንጫቸው ጠጋ ብዬ ሳዳምጥ በጣም ደካማ ትንፋሽ እየቆየ ይሰማል። ብቻ እንኩዋንስ ቀኑን ውለው ሊያድሩ ከጥቂት ሰአቶች በላይ የሚቆዩ አይመስሉም ነበር። ከዚያ ሰዎቻቸውን አያፅናናን አብረናቸው ቆይተን ያን ቀን የከፋ ነገር የደረሰ እንደ ሆነ ቢያስታውቁን የምንረዳቸው መሆናችንን ነገረናቸው ልንተኛ ሄድን። ግን የደረሰ ክፉ ነገር አልነበረም። በማግስቱ ከተከዜ ማዶ ሰፈር በተደረገበት ያለቃ አምሳሉ ሰዎች አልጋ ሰርተው በዚያ ላይ አለቃን አንገታቸውን ቀና አድርገው አስተኝተው ሲያመጡዋቸው አይቸ፥ ሄጄ ብጠይቃቸው ፈገግ ብለው በጎ መሆናቸውን ሲነግሩኝ ገረመኝ። ከብዙ አመታት በሁውላም አዲስ አበባ ተገናኘን። እምቸም ከዚያ ገደል ወድቆ ወዲያውኑ መሞት ቢቀር የእድሜ ልክ አካለ - ስንኩል ሳይሆን መቅረት፥ ወይ በታምር ያለዚያም ከብረት የተሰራ አካልና በምንም ሁኔታ የማይሸነፍ ፅኑ መንፈስ ያለው ሰው መሆን ያስፈልጋል!

ሌሊት በዋሻው ከዳር እስከ ዳር ጫጫታ ሆነ። ራስና አጃቢ ሰራዊታቸው ጉዞ ለመጀመር መነሳታቸው ነበር። ልጅ አለማየሁና ሰዎቹም ቀስቅሰውን ወደ ራስ ሄዱ። እኛ ግን ከተኛንበት መነሳት አቅቶን እዚያው ብዙ ቆይተን ሰው ሁሉ ሄዱ። እኛ ግን ከተኛንበት መነሳት አቅቶን እዚያው ብዙ ቆይተን ሰው ሁሉ ሄዶ ሰፈሩ ባዶ ከሆነ በሁዋላ ነበር የተነሳን። ከዚያ ተራራውን በወረድንበት መንገድ እያዘገምን ወጥተን ከሰራዊቱ ጋር ተጨምረን ጉዞዋችነን ጀመርን። ወደ ተከዜ አፋፍ እዬተቃረብን በሄድን መጠን መሬቱ ደልዳላ መሆኑ እዬቀረ ከመንገዱ ባንድ ወገን አቀበት በሌላው ወገን ቁልቁለት እየሆነ በመሄዱ፥ ይልቁንም ሌሊት ከመንገድ ወጥቶ በቀኝ ወይ በግራ የሚሄድ አልነበረም ሁሉም እመንገዱ ውስጥ ታጉሮ፥ እስበሱ እየተገፋፋ ነበር የሚሄድ። እዚያ ውስጥ መሄድ ከመንገዱ ይልቅ መጋፋቱ ያደክማል! እዚያ ውስጥ ከቀኝ ከግራ ከፊት ከሁዋላ ጆሮ የሚሰማው «ሂዱ ሂድ ሂድ እንጂ! አትሄድም? »

ብቻ ነበር። እዚያ ግፊያ ውስጥ አንድ ሰው ደክሞት ወይም አነቅፎት ቢወድቅ በላዩ ቆሞ መሄድ ነው እንጂ ለመርዳት የሚሞክር አልነበረም። እንዲዒያ እየተጋፋን ስንሄድ ከሌሊቱ በዘጠኝና ባስር ሰዓት መሀከል ግድም አንድ ደረቅ ወንዝ ደረስን። ወንዝዋን ተሻግሮ ከትግራይ ወገን የተከዜን አቀበት ነው። ያን አቀበት አሻግሬ ሳይ የተረፈኝ አቅም ሁሉ ተሙዋጦ ያለቀ መስሎ ተሰማኝና፤ «እዚህ ትንሽ ካላረፍን አቀበቱን መውጣት አልችልም » አልሁ፤ ለጉዋደኞቼ። ከዚያ መንገዱን ለቀን፤ ወደ ላይ ወገን ትንሽ እንደ ሄድን ጠርቦ ያለሰለሱት የመሰለ ሰፊ አለት ደንጋይ አገኘንና ሶስታችንም እዚያ ተጋደምን።

ትንሽ አርፈን ጉዞዋችነን ለመቀጠል በተጋደምንበት በዚያው እንቅልፍ ተጫጭኖን ጤንው ቀድሞ ነቅቶ ሲቀሰቅሰን ጀንበርዋ የምትወጣበትን አድማስ የወርርቅ ቀለም የተቀባ አስመስላ አሳምራ አገሩ ሁሉ ወገግ ብሎዋል ቀን ሆኖዋል። በዚያ የንጋት ወጋገን ከከደረቅዋ ወንዝ ባሻገር ሳር ቅጠሉ የተቃጠለው የተከዜ ዳገት ከቁዋጥኞቹ ጋር ከግር እስከ ራሱ ራቁቱን ይታያል። ሰማዩ በሙሉ የደመና ምልክት የማይታይበት እነእ ወለወሉት መስታዋት የጠራ ነበር። በመንገድ የሚሄደው ሰራዊት የሌሊቱን ያክል አይሁን እንጂ ያንጊዜም እስበሱ እየተገፋፋ የሚሄድ፥ ብዙ ነበር። ጤናው ተኝቶበት ከነበር አለት ወርዶ ከግርጌያችን ቆሞ የሚጉዋዘውን ሰራዊት ይመልከት ነበር።

«አሁን አይሮፕላኖች የሚመጡበት ጊዜ ነው፤ እንዲያውም ዛሬ ቆይተዋል እንጂ መሰንበቻቸውን ከዚህ ቀድመው ነበር የሚመጡት። ስለዚህ ከሰራዊቱ መሀል ገብተን እዬተገፋፋን ስንሄድ የመጡብን እንደሆነ በግራና በቀኝ መጠለያ የሚሆን ነገር ስለማይታይ፥ እዚያ ማዶ ከሚታዩት ትልልቅ ቁዋጥኞች ወዳንዱ እንድሂድና እስሩ ተቀምጠን እስከ ቀትር እንቆይ። ከዛሬ ቀድመ እንደ ተመለከትነው ከቀትር እስከ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ አይሮፕላኖች መጥተው ቦምብ አይጥሉም » አለ አቶ ዘውዴ።

«እውነትህን ነው እኔም ከቀትር በሁዋላ አመሻሽ ላይ ካልሆነ መጥተው ቦምብ የጣሉበት ቀን ትዝ አይለኝም። ያን ጊዜ እነሱም ነጂዎቻቸውም ሆዳቸን ሞልተው የሚያርፉበት ይሆናል። ወዲያውም ትናንት ልጅ አለማየሁ እንደ

ነገረን ሰፈሩ ከተከዜ ማዶ አፋፉ ጥግ ከሆነ ቆይተን መንገዱን ሰው ለቀቅ ሲያደርግልን ብንሄድ እንደርሳለን » አልሁ። ጤናውም ተስማማ።

እኛ ስንነጋገር ሰማዩ የደመና ምልክት የማይታይበት ጥሩ ነበር። ነገር ግን በቅፅበት «ከዚህ መጣ » ሳይባል ከባድ ጉም የተከዜን ሸለቆ ከላይ እስከ ታች አዳፈነው። ከዚያ በዚያ አራራ በጋና የዝናብ ቀርቶ የደመና ምልክት በሰማይ ሳይታይ እንዲያ ያለ ከባድ ጉም በመውረዱ እየተገረምን ሰራዊቱ የሚሄድበትን መንገድ አቁዋርጠን እንደ ተማርከርነው እስከ ቀትር ወደምንቆይበት መሄድ ስንጀምር፥

«አያ ጤናው አያ ጤናው » አንድ ሰው ከሰራዊቱ መሀል። ሶስታችንም ዘወር ስንል ረኸርሙ ዘሪሁንን በቅሎውን እየሳበ ከሰራዊቱ ተለይቶ ወደኛ ሲመጣ አዬነው። ያንጊዜ ዘሪሁን ከሞተበት ተነስቶ የመጣ እንጂ ጠፍቶን ሰንብቶ የተገኘ አልመሰለንም። እሱ ወደኛ ሲመጣ እኛም ወደሱ ሄደን ሶስታችንም በተራ እያቀፍን አስጨንቀን ከሳምነው በሁዋላ ሳልጭሩ ዘሪሁን ከፉ ወሬ እንዳይነግረኝ እየፈራሁ የሚያውቀው ነገር እንዳለ ብጠይቀው ምንም የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን ነገረኝ። ከጦርነቱ ሰፈር ቀድሞን ተነስቶ ያነለት ከሁዋላችን የመጣበት ምክንያት አደጋ አግኝቶት ኖሮ እንደሆነ ጠይቄው መልስ በቅጡ ሳይሰጠኝ አይሮፕላኖች ሲመጡ ድምፃቸውን ስለ ሰማን ቶሎ እደረቅዋ ወንዝ ገብተን ቅጠል በሌላቸው ዛፎች ስር ተጠጋን። ግን የሚበርሩት ከጉሙ በላይ ስለ ነበረ እንኩዋንስ እኛን መንገዱን ሞልቶ እንደ ውሀ ሙላት ይጥመለመል የነበረውን ሰራዊት ሳያዩ ወደ ፊት እዬተከታተሉ አልፈው ሩቅ ቦታ ቦምብ ሲጥሉ እንሰማ ነበር። እኛም በላያችን ሲያልፉ ድምፃቸውን ከመስማት በቀር በጉም ምክንያት መልካቸውን አላዬን። ከዚያ ወጥተን ከተከዜ አፋፍ ጥግ አንድ ትልቅ ቁዋጥኝ አገኘንና ባጠገባችን ቦምብ የፈነዳ እንደሆነ ፍንጣሪው እንዳያገኘን እዚያ ከመላው ድንጋይ ቶልቶሎ ሰብስበን በግንባር ጥሬ ካብ ክበን በቅሎው የዘሪሁንን ወይባ የነተነከረ ኩታ እንደ ተከናነበ እፊታችን ካንድ ዛፍ ግንድ ጋር አስረን እምሽጋችን ውስጥ ገብተን ተቀመጥን። ዘሪሁን የስንቅ መያዣውን የሸራ ከረጢት ሲያመጣልን ለዚያ ጊዜ በቅቶ የሚተርፍ በሶ ጭኮና ዳቦና ቆሎ አገኘን። ብቻ ውሀ ስላልያዝንና ባጠገባችንም ስላልነበረ በሶ ልንበላ አልቻልምንም። ከጭኮውና ከዳቦ ቆሎውም ቢሆን

የራበንን ያክል አልበላንም ከቀትር በፊት ቢያንስ ደከመንና ተኛን። እዚያ እንዳለን አይሮፕላኖች ከቀጥር በፊት ቢያንስ ሶስት ጊዜ ያክል መጥተው ቦምብ እዬጣሉ ሄደዋል። ግን የሚጥሉትን ቦምብ እንዲሁ «ባገኝ ባጣውን » ባቀበቱ ሁሉ ላይ ዘርተውት ይሄዳሉ እንጂ፥ መንገዱን ይዞ እንደ ጉንዳን ሰራዊት እየተደራረበ የሚርመሰመሰውን ሰው ሊያዩት ስላልቻሉ ያነለት እዚያ ዳገት ላይና ከዚያም አልፎ እስከ ተከዜ ወንዝ ድረስ በሰውም ሆነ በከብት ላይ ያደረሱት ጉዳት ከስንት አንድ ነበር። ያነለት የጣሉትን ቦምብ ሁሉ በሚጓዘው ሰራዊት ላይ አነጣጥረው ቢጥሉት ኖሮ ሰው ባልተረፈ።

ርፋድ ላይ ካምስት በሁዋላ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ ያ ከባድ ጉም እዬሳሳ ሄዶ በመጨረሻ በንኖ ጠፋና ሸለቆው በሙሉ ግልጥ ሆነ። ያይሮፕላን ድምፅ ከሰማንም ዘለግ ያለ ጊዜ አለፈ። በዚያ ጊዜ መንገዱን ሞልቶት የነበረው ሰው በመጠኑ ቀለል ብሎዋል። ስለዚህ ከቆየንበት አቀበት ወርደን እዋናው መንገድ ስንደርስ የበላነው ጭኮና ዳቦ ቆሎ ፅኑ ውሀ ጥም ለቆብን ስለ ነበረ እኔ በበቅሎየ ተቀምጬ ተከዜ ወንዝ እስክንደርስና ውሀ እስክንጠጣ ቸኩለን ስንሄድ፥ ልጅ ሀብቴ አሻግሬን ከመንገድ ወጣ ብሎ አንድ ዛፍ ስር ተቀምጦ አዬነው። ባጠገቡ አንድ ሰው ቆሞ ነበር። ልጅ ሀብቴ በቅርብ የማውቀው ክቡር ራስ እምሩ ሰው ነበር። ከበቅሎዬ ወርጄ ምን እንደሆነ ብጠይቀው መታመሙን ስለ ነገረኝ በቅሎዬን ለሱ ሰጥቼ እኔ እንደ መሰንበቻዬ በግሬ እየሄድሁ ተከዜ ወንዝ ደረስን። እዚያ ያየነው ደግሞ ስለ ሽሬ ግንባር ጦርነት ሳስብ ባይነ - ህሊናዬ ፊት ጎልተው ከሚታዩኝ ከፉ ትርኢቶች አንዱ ነው።

የተከዜ ውሀ እመሻገሪያው ላይ ሰፊና ፀጥ ያለ ነው። ታዲያ ያ ሰፊ ውሀ፤ ገና ከሩቅ ሲያዩት ቀይ ቀለም በከባዱ የተበጠበጠ ይመልሳል። «ምን ነገር ነው ምን ጉድ ነው? » እየተባባልን ቀረብ ስንል መሻገሪያው በቁሙም በወርዱም ከዳር እስከ ዳር ሬሳ ሞልቶበት የዚያ ሬሳ ደምና ፈርስ ነው! የሰው ሬሳ የፈረስና የበቅሎ ሬሳ ያህያ ሬሳ ያውሬ ሬሳ ሬሳ፥ ሬሳ ብቻ! እግር ከራስ ራስ ከግር እዬተመሰቃቀለ እየተደራረበ ሞልቶበት፥ የዚያ ሁሉ ሬሳ ደምና ፈርስ ነው። ያን ሳይ ውሀ ጥሜ ተቆረጠ። ከዚያ በሁዋላ የመጠጣቱ አሳብ ቀረና አሳሳቢ የሆነው እዚያ ገብቶ መሻገሩ የሚዘገንን ነበር። ግን፤ መሻገር የማይቀር ግዴታ

ስለ ነበረ የሬሳው ብዛት ቀለል ያለ በሚመስልበት በስተ ላይ በኩል ጥርሳችንን ነክሰን ገብተን ተሻገርን። ያ የሬሳ ክምር መቸም ያንድ ቀን ሊሆን አይችል፤ ከጦርነቱ ግንባር ሽሽት ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ መሰንበቻውን ሰውና ከብቱ ሊሻገር ሲገባው አውሬው ውሀ ሊጠጣ ወይም ሬሳ ሊበላ ሲመጣ ሁሉም ባንድ ላይ እዚያ በቦምብ ሲያልቅ የሰነበተበት መሆን አለበት!

ከዚያ እዬሄድንም ተቀምጠን እያረፍንም አስር ሰአት አቅራቢያ የወንዙን ዳገት ልንወጣ ትንሽ ሲቀረን አይሮፕላኖች መጡብን ግን ብዙ አልቆዩም፤ ጥቂት ቦምቦች ጥለው ሲሄዱ ተሸሽገን ከቆዬንበት ወጥተን ቀስ እያልን ጉዞዋችንን ስንቀጥል ሰፈር ከተደረገበት አጠገብ አንድ ትንሽ ወንዝ አገኘን። እዚያ ውሀ ጠጥተን የተከዜን ውሀ ስንሻገር የተበላሸ ያካላት ክፍላችነን ከነሱሪያችን አጥበን ከወንዝዋ ዳር አርፈን ለመቆዬት ጋደም ባልንበት አጭሩ ዘሪሁንን ሲመጣ ከሩቅ አዬነው። «ደስታ ቀሊል » የሚሉት አሰት አደለም። ዘሪሁንን በህይወት ባገኘው ደስታውን የምችለው አልመሰለኝም ነበር። ግን ደስታው ያሰብሁትን ስሜት አልሰጠኝም። ዘሪሁንን ፊት ክስል ብሎ ጠቅላላ ሰውነቱ ተጎሳቅሎ ሳየው፥ እንዳሰብሁት በሚያስቅና በሚያስፈነድቅ ደስታ ፈንታ፥ ደስታ አይሉት አዘን፥ የውስጥ ህዋሳቴን ሁሉ የሚያውክ ልዩ ስሜት ተሰማኝና ሳላስበው አይኖቼ እምባ ሞሉ፤ ከዚያ እሱ እኛ ዘንድ እስኪደርስ ሳልጠብቅ፥ ተነስቼ ወደሱ ስሄድ፥ ሌሎች ጉዋደኞቻችንም ተከተሉኝ።

«አዋዋ አለህ? ደህና ነህ? » አለኝ ዘሪሁን ገና ሳንገናኝ ተጣርቶ። ዘሪሁን «አዋዋ » ነበር የሚለኝ። መልስ መስጠት ስላቃተኝ አልመለስሁለትም፤ ዝም ብዬ ሄጄ አንገቱን አቅሬ ከሳምሁትት በሁዋላ እንዲያ እንደ ያዝሁት አሳቤ ፀጥ እስኪል ቆይቼ፤

«አደጋ ደርሶብህ ኖሮዋል? ለምን እንዲህ ሆንህ? » አልሁት።

«አህያየን እንደ ተጫነ ቦምብ አቃጠለብኝ እንጂ እኔስ ደህና ነኝ ምንም አልሆንሁ » አለ። ቦምብ ያቃጠለው የኔን አህያ ነበር። ግን ዘሪሁን እኔን እንደ ራሱ ቆጥሮ የኔ የሆነ ማናቸውም ነገር ሁሉ የሱ መሆኑን በፍፁም ልብ

የሚያምን ስለ ነበረ የኔን አህያ «ያህያየ » የኔን በቅሎ «በቅሎየ » የኔን ቤት «ቤቴ » እያለ መናገሩ የተለመደ ነበር።

«እንኳዋን አንተ ደህና ሆንህ » ብዬ አንገቱን ስለቅላቸው ዝም ብለው ይመለከቱን የነበሩት ጉዋደኞቻችን ሁሉ በተራ «እንኳዋን እግዚአብሔር አተረፈህ! » እያሉ ከሳሙት በሁዋላ ከወንዝዋ ዳር አርፈንበት ወደ ነበረው ቦታ ተመልሰን ተቀምጠን ረዥሙ ዘሪሁን በሶ አዘጋጅቶ አቅርቦለት ይበላ ጀመር።

«አህያውን ቦምብ ያቃጠለው እመንገድ ላይ ነው? » አለው አቶ ዘውዴ።

«አዎ ትናንት እመንገድ ላይ ነው » አለ ዘሪሁን።

«ታዲያ አንተና አጋሰስዋ እንዴት ተረፋችሁ? »

«በቅሎዬን እዬሳብሁ አህያየን ፊት ፊት እዬነዳሁ ስንሄድ የበቅሎዋ ጭነት ሲያጋድልብኝ ጊዜ ጭነቱን አስተካክዬ ለማጥበቅ እስዋን ከመንገዱ ወደ ዳር አድርጌ እስክጭን ድረስ አህያው ከሚጉዋዘው ብዙ ሰውና ከብት ጋር ከኔ ትንሽ ራቅ ብሎ ነበርና ያን ጊዜ አይሮፕላኖች መጥተው እዚያ እሱ በነበረበት የጣሉት ቦምብ ብዙ ሰውና ከብት ሲጨርስ ነው እሱም አብሮ የተቃጠለ። እንግዲያ እኔ በነበርሁበትና ባጠገቤማ ከሰውም ከከብትም የቦምብ ፍንጣሪ እንኩዋ የደረሰበት አንድ አልነበረም። እሱንም ጭነቴን እስካስተካክል ባጠገቢኤ ባቆዬው ኖሮ አይሞትም ነበር » አለ ዘሪሁን መብላቱን ትቶ እዬተከዘ።

«ብቻህን ምን ማድረግ ትችል ኖሮዋል አጋሰስዋን ትጭን ወይስ አህያውን ትይዝ አንተ ምንም ማድረግ አትችልም ነበርና አሁን ማዘኑን ትተህ ብላ። እንኳዋን አንተ ደህና ሆነህ እንጂ እሱን በማጣታችን ማዘንና ማማረር አይገባንም » አልሁት። እውነቴን ነው መንገድ ለመንገድ በቦምብ እንደ ቅጠል ሲረግፍ እዬረገጥነው የመጣ ነውን የሬሳና የቁስለኛ ብዛት ሳስብ ከዚያ ሁሉ

መሀከል ዘሪሁን ሳይሞት ሳይቆስል በደህና ከኛ ጋር መገናኘቱ እንኩዋንስ ያህያውን ብቻ የበቅሎዋን ጭምር መጥፋት ኢምንት አድርጎ የሚያሳይ ነው።

የራስ እምሩ ሰራዊት ከሰለክለካ የጦር ግንባር ሸሽቶ የተከዜን ወንዝ እስኪሻገር ያይሮፕላን ቦምብ እዬገደለና እያቆሰለ መንገድ ለመንገድ የጣለውን የሬሳውን የሬሳና የቁስለኛ ብዛት፥ እንኩዋንስ ያንጊዜ ሲያዩት ካለፈ በሁዋላም ቢያስቡት ልብ የሚያስጨንቅና የሚያሰቅቅ ነው! የጣሊያን ሰራዊት በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ በጦር ግንባር ካደረሰው ጉዳት ገና ከጦርነቱ ግንባር ሳይደርስና ከግንባር ሳይሸሽ ያደረሰበት ጉዳት «የከፋ ነው » እላለሁ። በጦርነቱ ላይ የኢትዮጵያ ሰራዊት የሞትና የመቁሰል ጉዳት ይድረስበት እንጂ በመጠኑም ቢሆን ጠላቱን ገድሎና አቁስሎ ሲጥል ማየቱ ትንሽ የመበቀል ርካታ ይሰጠዋል። የጣሊያን አይሮፕላን ከጦር ግንባር ውጪ በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ ያደርገው የነበረው ጦርነት ግን ሲገድልና ሲያቆስል እንጂ ሲሞትና ሲቆስል የማይታይበት በመሆኑ አካል ብቻ ሳይሆን መንፈስ ጭምር የሚገልድ ነበር። እሸሽት ላይ ከሰለክለካ የተከዜን ወንዝ እስክንሻገር በሞትና በመቁሰል የደረሰብንን ጉዳት እዚያ ወድቆ የቀረውን ህዝብ ብዛት የያንዳንዱ ቤት ይወቀው እንጂ እኛ መቸም አናውቀ! ማርሻል ባዶሊዮ 3000 መሆኑን ፅፈዋል።

በተቀመጥንበት እንዳለን ዘሪሁን እስኪያርፍ እንዳስላሴ ከተለያዬንበት ጊዜ ጀምሮ ጉዋዝ ጠባቂው ሰራዊት ስለ ሰንተተበትና ሁዋላም ከዚያ ሲነሳ ስለ ነበረው ሁኔታ በጠቅላላው እንዲያወራን እየጠየቅነው ሲነግረን ቆይቶ ከዚያ ተነስተን ከወንዝዋ ሩቅ ያልሆነ ቦታ ፈልገን ሰፈርን።

ሰፈሩ የተከዜን ወንዝ ዳገት ወጥቶ ከጠቅላላው የተከዜን ሸለቆ ዳገት ግርጌ በሁለቱ ዳገቶች መሀከል ከላይ እስከታች ገደም ብሎ የሚወርድ ቁጥቁዋጦም አንዳንድ ቅጠላቸው ያልተቃጠለ ዛፎችም የነበሩበት ቦታ ነው። የሸለቆው ዳገት በስተምስራቅ በኩል አናቱ «ራስ ዳሽን » ተራራ ነው። ስለዚህ የሱ ቅዝቃዜ ስለሚሰማው ሰፈሩ በጣም ብርዳም ነበር። እዚያ በቂ አዬር (ኦክሲጂን) ባለመኖሩ እንጨት ማንደድ አይቻልም። አንድ እንደ ሸንበቆ ውስጡ ክፍት ሆኖ ጥቃቅን ቅጠሎች ያሉት የንጨት አይነት በብዛት ስላለ

እሱን ብቻ እዬነቀሉ ማንደድ ይቻላል። ግን ያ አይነት እንጨት አንድ ጊዜ «ግልብልብ » ብሎ ተቃጥሎ ፍም ወይም ከሰል ሳይተው አመድ ብቻ ሆኖ የሚያልቅ ነው። ስለዚህ ከብርዱ ለመከላከል እሱን በላይ በላዩ እዬደራረቡ እያቃጠሉ ለመሞቅ ካልሆነ ውሀ ለማሞቅ ወይም ምግብ ለማብሰል አይሆንም። የዚያ ቦታ ብርድ መቸስ ለብቻው ነው። አንድ ቀለኛ በክፉ አጋጣሚ እንዲያ ባለ ቦታ ተገኝቶ «እጅ ቢገኝ የንፍጥ ማለቂያው አሁን ነበር! » እንዳለው አውራ ጣትን ባጠገቡ ካሉት ሌሎች ጣቶች ጋር አቀራርቦ አፍንጫን መያዝ አይቻልም እንጂ፥ ቢቻል ኖሮ እውነትም ከንፍጥ ለሁልጊዜ መገላገል የሚፈልጉ ሁሉ መሄጃው ያ ቦታ በሆነ!

## ምዕራፍ አስራ አንድ

# ሌላ ዘመቻ

ከሰለክለካ የጦር ግንባር ተመልሰን ከተከዜ ማዶ በሰፈርን ማግስት፣ እጥዋቱ ላይ የራስ መላከተኛ መጥቶ እንደሚፈልጉኝ ነግሮኝ ሄደ።

እኔ እራስ ድንኳዋን ስደርስ አቶ ዮሀንስ አብዱ (ሁዋላ ሻለቃ) ከሳቸው ጋር ቆይቶ ይወጣ ነበር።

«እኔና አንተ አብረን እንድንሰራ የታዘዝነው ስራ አለ፤ ለሱ ነው የተጠራህ » አለኝ እጁን ለሰላምታ ወደኔ ዘርግቶ።

«ምን ስራ ነው? » አልሁት እጁን ጨብጨ።

«ስትገባ ራስ ቢነግሩህ ይሻላል » አለ፤ እንደ መሳቅ ብሎ። ወዲያው አጋፋሪው ራስ ወዳሉበት አስገብቶኝ እጅ ስነሳ የቃል ሰላምታ ሰጡኝና፤

«እጦርነቱ ላይ ወይም ከዚያ እመልስ ላይ የተጎዳብህ ሰው አለ? » አሉኝ።

«የለም፤ ሁላችንም ደህና ነን » አልሁ።

«ትልቅ እድል ነው! »

«መቸም - በጦርነቱ ግንባር ላይ ከተጎዳብን ሰው ይልቅ እሸሽቱ ላይ ባይሮፕላን ቦምብ የተጎዳው ሳይበልጥ የሚቀር አይመስለኝም! » አልሁ፤ ልጠይቃቸው ላሰብሁት አይነተኛ ነገር መንገድ ለመከፈት ብዬ።

«ይመስልሀል? »

«አዎ፤ ለኔ ይመስለኛል። ምክንያቱም የሌላውን ግንባር አላውቅም እንጂ እኔ ከቀትር ጀምሬ እስኪጨልም ድረስ በዋልሁበት በምእራቡ ግንባር እዬሞቱና እዬቆሰሉ የወደቁት ብዙ ቢሆኑም ብዛታቸው ከጠላት የመሳሪያ አይነትና ብዛት አንፃር ሲታይ ይህን ያክል ‹ከመጠን ያለፈ ነው› የሚባል አይደለም መጠነኛ ነው። ደግሞ በዚያ ሁሉ ጊዜ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው የኢትዮጵያ ወታደሮች ከያዙት አንድ ትንሽ ቦታ እንንኳዋ አስለቅቀው መያዝ አልቻሉም። እንዲያው አንድ ጊዜማ የኢትዮጵያ ወታደሮች «ሆ! » ብለው ኢጣሊያኖች ምሽግ ውስጥ ገብተው በጨበጣ ጦርነት አሸንፈው ከምሽጋቸው አባረዋቸው ነበር! ብቻ ከሁዋላ ተጨማሪ ሀይል ስላገኙ በሱ ርዳታ እንደገና ወደ ምሽጋቸው ለመመለስ ቻሉ። ያም ሆኖ ከጨለመ በሁዋላ እኔ ጉዋደኞቼ ስለ ጠቅላላው የጦርነት ሁኔታ ለመረዳት ወደ ዋናው መምሪያ እስክንመለስ ድረስ እንኩዋንስ የኛን ሰራዊት ድል አድርገው ወደ ፊት ሊገፉ ከምሽጋቸው አልወጡም። ሰራዊታችንም እቀትር ላይ እኛ ስንሄድ የነበረበትን ቦታ ሳይለቅ በመዋጋት ላይ እንዳለ ነው ትተነው የመጣን። ታዲያ ይህ ሁሉ ሲታይ ‹በግንባር የተሰለፈው ሰራዊታችን የደረሰበት ጉዳት ከመጠን ያለፈ ነው› የማይባል ከመሆኑ ሌላ ተዋግቶ ጠላቱን ድል የማድረግ ፍላጎቱና ሲቃው ያልተቀነሰ የመሸነፍና ተስፋ የመቁረጥ ምልክት የማይታይበት ነው የሚመስል ከግንባር ተመልሰን መንገድ ለመንገድ ባይሮፕላን ቦምብ ተገድሎና ቆስሎ የወደቀውንና የሚሸሸውን ሰራዊት

ስንመለከት ግን በግንባር ከሚታዬው በፍፁም የተለዬ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው። »

«አዎ፤ በሌላው ግንባርም ቢሆን ጣሊያኖች የኛን ሰራዊት ድል አድርገው ወደ ፊት የገፉበት ቦታ እምብዛም የለም » አሉ ራስ እንደ መተከዝ ብለው።

«እንግዲያ - ለምን ሸሽን? » አልሁ ሸሸት የሚባለውን ቃል የራስ አፍ እንደ ተፀየፈው ስለ ተሰማኝ ጥያቄየ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አዬተጠራጠርሁ። ይሁን እንጂ ወታደሩ መስመሩን ሳይለቅ በመዋጋት ላይ እንዳለ የሸሸበትን ምክንያት ከመጀመሪያ ጀምሮ ስላልገባኝና ከንክኖኝ ስለ ነበረ፥ መጠዬቅ ነበረብኝ።

«ሰራዊታችን በግንባር ድል ስለሆነ አልነበረም ወደ ሁዋል ለማፈግፈግ የፈለግን። ጠላት ከሁዋላ መንገዳችንን ቆርጦ ለመክበብ ብርቱ ሀይል አሰናድቶ በጎን መሆኑን ስለ ተረዳን እወጥመዱ ውስጥ እንዳንገባ ወደ ሁዋላ ምቹ ቦታ ይዘን ለምሳሌ ተከዜን በግንባራችን አድርገን ለመዋጋት ነበር አሳባችን። አሁን ግን ከሰራዊቱ የሚበዛው ተስፋ የቆረጠና ለመዋጋት ፍላጎት የሌለው ሆኖ ስላገኘነው የፊተኛውን አሳባችንን ትተን ሌላ አዲስ አሳብ አስበናል። አንተንም የተራህን ስላዲሱ አሳባችን ልናነጋግርህ ነው። አሳቡ አዲስ ቢሆንም ያው ጦርነቱን ለመቀጠል ነው። ስለዚህ ወዶ - ዘማች ነህና አሁንም በዚኢያው በወዶ - ዘማችነትህ ለመቀጠል ትፈቅድ እንደሆን ሌላ ዘመቻ ልናዝህ አስበናል ትፈቅዳለህ? » አሉ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብለው።

«መቸም ጦርነቱ የሚቀጥል ከሆነ የምችለውን ሁሉ እያደረግሁ እስካለሁ ድረስ ከመቀጠል በቀር ሌላ አሳብ የለኝም » አልሁ።

«እኛም ጦርነቱን ለመቀጠል ነው አሳባችን፤ ግን ፊት እንዳሰብነው እዚህ አካባቢ ሳይሆን፤ ያገራችንን ምእራብና ደቡብ - ምእራብ ይዘን መዋጋት ለኛ ምቹ የሚሆነውን ያክል ለጠላት የማይመች በመሆኑ ወደዚያ ለመሄድ ወስነናል። ያ ክፍል ደን የሞላበት ስለ ሆነ ጠላት እንደ ልብ ባይሮፕላንና በታንክ ሊዋጋበት የማይችል ከመሆኑ ሌላ እኛ የመክበብ ስጋት እንዳይኖርብን እንግሊዞች የሚገዙውቸውን አገሮች ሱዳንና ኬንያ በጀርባችን አድርገን

እግዚአብሔር ፊቱን እስኪመልስልን ድረስ ስንታገል ብዙ ጊዜ ልንቆይ እንችላለን። ስለዚህ አሁን አንተን ወደ ፈለግንበት ጉዳይ እንመለስና «በትግራይ ምድር የምንዋጋው ጦርነት ረዢም ጊዜ የሚወስድ መስሎን በስንቅ በኩል እንዳንቸገር በዬጊዜው እዬተሰናዳ እንዲላክልን የሚያደርጉበት ገንዘብ ዳባት አገር ጠባቂ ሆኖ ለቀረው ለደጃዝማች አያሌው ልጅ ‹ለፊታውራሪ መርሶ› እና ጎንደር ለጳጳሱ ‹ላቡነ አብርሃም› ሰጥተን ነበር። አሁን ይኸው እንዳየህው ጦርነቱ በጥቂት ቀናት ስላለቀ ያን ገንዘብ ላንተና ላቶ ዮህንስ አብዱ እንዲያስረክቡዋችሁ ለሁለቱም እንፅፋለንና ሲያስረክቡዋችሁ ይዛችሁት ወደ ሱዳን እንፅፋለንና ሲያስረክቡዋችሁ ይዛችሁት ወደ ሱዳን እንድትሄዱ ነው ያሰብነው። አቶ ዮህንስ ከንግሊዝኛ ሌላ አረብኛ ቁዋንቁዋም ሰዎችም ሰልሚያውቅ ከሚረዱህ ሰዎች ጋር አገናኝቶህ ተመልሶ በመንገድ ሳለን እንዲደርስብን ነው የሚሄድ። አንተ ግን እኛ ባገራችን ምእራብ ‹ጦርነቱን ለመቀጠል ይመቻል› ብለን የምንመርጠውን ዋና ሰፈር እስክናስታውቅህ ድረስ ገንዘቡን ይዘህ እዚያው ትቆያለህ። ዋና ሰፈራችንን ስናስታውቅህ ከሱ ጋር ለወታደራችን ልብስና ድንኩዋን የሚሆን ካኪ ለስንቅ የሚሆን ደረቃ ደረቅ ነገርና መድህኒት እንዲሁም በዚያ ጊዜ ሁኔታውን አይተን አስፈላጊ ሆኖ የምናገኘውን ሁሉ በዝርዝር ፅፈን እንልክልሀለን ገንዘብ እስከ በቃ ድረስ ገዝተህ ገንዘቡ እንዳይጠፋብህ በኛ ስም ባንክ ለማግባትም ለምትገዛው ነገር ሁሉ ለማውጣትም የሚያስችል የስልጣን ወረቀት ያልገባህ ነገር እንዳለ ወይም ለራስህ የምትጠይቀው ነገር እንዳለ አሁን ጠይቅ » አሉ።

«የነገሩኝ ሁሉ ግልፅ ነው፤ ገብቶኛል። ለራሴ የምጠይቀውም የለ። ነገር ግን ከዚህ ሄደው ጦርነቱን ለመምራት የሚመርጡት ሰፈር እኔ ከምቆይበት ከሱዳን ጋር መገናኛ መንገድ የሌለው እንደሆነ የኔ መመለሻ ችግር እንዳይሆን አስቀድሞ ቢታሰብበት ደህና ይመስለኛል። እንዲያውም የሚቻል ቢሆንማ፤ እኔም ባውቀው ደስ ይለኝ ነበር » አልሁ። በጦርነት ጊዜ ‹የሚሄዱበትን አስቀድመው ይንገሩኝ› ማለት የማይገባ መሆኑ ትዝ ያለኝ ከተናገርሁት በሁዋላ ነበር።

«መቸም - ከኢሉባቦርና ከከፋ አንዱ ሳይሆን አይቀር፤ ታዲያ ሁለቱም ከሱዳን ጋር እንደሚገናኙ ታውቃለህ » አሉኝ ትንሽ ፈገግ ብለው።

«አዎ፤ ይገናኛሉ »

«ደመወዝህን እስከ መቼ ተቀብለሀል? » አሉኝ፤ ሁለታችንም ላጭር ጊዜ ዝም ብለን ከቆዬን በሁዋላ።

«እስከ ጥቅምት ወር ድረስ ደብረ ማርቆስ ተቀብያለሁ »

«የወሩ ስንት ነው? »

«አምሳ አምስት ብር ነው »

«ፃፍና ከህዳር እስከ ሚያዝያ አሁን እዚህ እንዲከፈልህ ይደረጋል » አሉኝ » በመጋቢት ወር መጀመሪያ ግድም ስለ ነበርን የሁለት ወር ቅድሚያ ተከፈለኝ ማለት ነው።

ያነለት ከቀትር በሁዋላ አቶ፥ ዮሀንስ አቡዱና እኔ ከጉዋደኞቼ ጋር፥ ወረቀቶቹ ሁሉ ተጠናቅቀው ተሰጥተውን አብረውን እንዲሄዱ የታዘዙት «ያምሳ አለቃ አበበ ወልደ ማርያም » ከክብር ዘበኞች ጭፍሮቻቸው ጋር ጭምር ራስን ተሰናብተን፥ ከዚያ ብርዳም ሰፈር ወጥተውን አደርን።

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

# ከደባርቅ እስከ ሱዳን

ራስ ከሰፈሩበት ተነስተን የተከዜን ሸለቆ ዳገት ወጥተን ያደርንበት ቦታ፥ ከደባርቅ ግንባር እዳገቱ አንድ ትንሽ ወንዝ አጠገብ ነበር። ወንዝዋ እንዳቅምዋ ሸለቆ ስለ ነበራት ሰፈራችን ትናንቱን ባደርንበት ሰፈር አይን ሲታይ ሞቃት

ነበር። ስለዚህ ያለፈው ሌሊት የንቅልፍ ውዝፍ ባለቱ እንቅልፍ ላይ ተደርቦ ሁላችንንም ከብዶን በማግስቱ ጀንበር እስክትወጣ ድረስ ከመሀከላችን የነቃ አልነበረም። ጥዋት ስንነሳ፥ የኔን ሁለት በቅሎች ያገሩ ሌቦች ሌሊት ሰርቀዋቸው አገኘን።

ከሁለት በቅሎዎቼ የኮረቻ በቅሎየ «የግራጭ » መጥፋት ነበር በጣም ያሳዘነኝ። በዘመቻው ካዩሁዋቸው በቅሎዎች ሁሉ አፌን ሞልቼ «የግራጭን የመሰለ አልነበረም » ማለት እችላለሁ። በትልቅነቱ ከሩቅ ለሚያየው ፈረስ እንጂ በቅሎ አይመስልም። እድሜው እዬገፋ በመሄዱ ጠጉሩ ጨርሶ በመንጣቱ ከግራጭነቱ ወደ ዳለቻነት ቢለወጥም በድሮ መልኩና ስሙ «ግራጭ » እንለው ነበር። ግራጭ በሙያውም ሆነ ባመሉ ልዩ ነበር። ገና ተጭኖ ወደሚቀመጥበት ሰው ሲቀርብ አንገቱን ሰበር ጆሮዎቹን እንደ ተደገነ ጣምራ ቀስት ወደ ፊት ቅስር ጭራውን ነሰነስ አድርጎ ሰልፉን አሳምሮ ይቆይና ከተቀመጡበት በሁዋላ ሲሰግር፥ ቆሞ ስግሪያውን እዬተመለከተ ሳይደነቅ የሚሄድ አላፊ መንገደኛ አልነበረም።

አንድ ቀን ተቀምጨበት እያሰገርሁት ስሄድ አንድ እግሩ ሳር ለብሶ በማይታይ ጉድጉዋድ ላይ ቆሞ እስከ ጉልበቱ ጠለቀና ወደ ፊት ደፋ ሲል እኔ ከላዩ ተወርውሬ በፊት ወደቅሁ። እንዲያ እንደወደቅሁ ዘወር ብዬ ከሁዋላየ ሲፈራገጥ አይቼ በላየ እንዳይወድቅብኝ ፈርቼ ነበር። ነገር ግን እሱ እንደ ምንም እዬተፍገመገመ እግሩን ከገባበት ጉድጉዋድ አውጥቶ እኔን አሳልፎ ከሄደ በሁዋላ የተጎዳ ጉልበቴን እያሻሽሁ በወደቅሁበት እንደ ተቀመጥሁ ስለ ነበርሁ ከሄደበት ተመልሶ ወጥቶ ሲያሸተኝ ቆዬና ባጠገቤ ቆመ። ዘሪሁንም አንድ ቀን ወሀ ለማጠጣት ወደ ወንዝ እዬጋለበው ሲሄድ ወድቆ ልክ እኔ የወደቅሁ እለት እንዳደረገው፥ ርቆ ከሄደበት ተመልሶ እሱን እያሸተተ ባጠገቡ መቆሙን ነግሮኛል። እንዲህ የሚያደርጉ በቅሎዎች አይቼ አላውቅም አይተናል ከሚኢሉ ሰዎችም ሰምቼ አላውቅ! በቅሎዎች ከላያቸው የጣሉዋቸውን ሰዎች ባይረግጡዋቸው እንደኔ ጥለዋቸው ይጋልባሉ እንጂ ከሄዱበት ተመልሰው ቁስለኞቻቸውን አያስታሙም፤ ይህ በተለይ ለግራጭ የተሰጠ ባህሪ ነበር።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግራጭ እንደ አንዳንድ ቀን የጣላቸው ባለማእረጎች ቀን ጥሎት፥ በኔ በድህው እጅ እስኪወድቅና መጨረሻ የሰረቀው ሌላ ያንጋሬ ወይም የሌላ መናኛ ነገር መጫኛ አጋሰስ እስኪያደርገው ድረስ፥ ጥንት ከንግስተ - ነገስታት ዘውዲቱ ምኒልክ ማለፊያ የኮርቻ በቅሎዎች አንዱ የሆነ በወርቅ ድግድግ መረሻት የሚያጌጥ ባለማእረግ በቅሎ ነበር።

ጎጃም የንጉስ ተክለ ሀይማኖት ልጅ፥ ወይዘሮ ንግስት ተክለ ሀይማኖት አዲስ አበባ ብዙ ቆይተው ወደ አገራቸው ሲመለሱ፥ ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ከሸለሙዋቸው የክብር ሽልማት መሀከል አንዱ የጭን በቅሎዋቸው ግራጭ ነበር። ሁዋላ፥ ወዘሮ ንግስት ተክለ ሀይማኖት ግራጭን የዳንግላ ተወላጅ ለሆኑት ሹማቸው ለ«ቀኛዝማች ሙሉነህ ቦጋለ » ሸለሙዋቸው። ቀኛዝማች ሙሉነህ ዳንግላ በነበርሁበት ጊዜ ለኔ ሸጡልኝ። ግራጭን ከኔ የሰረቀው ሌባ፥ ወይም እሱ የሚሸጥለት ሰው፥ የምን መጫኛ አጋሰስ እንደሚያደርገው መቸም የሚያውቅ የለ!

ባቶ ዮሀንስ አብዱ በቅሎዎች ላይ በተደራቢ ሊጫን ከተቻለው የተፈውን እቃየን የኔ ሰዎችም ወታደሮችም እንዲይዙት ካደርግን በሁዋላ ሁሉም ወደ ደባርቅ ጉዞ ሲጀምሩ አቶ ዘውዴ ወልደ ተክሌና እኔ፥ በቅሎዎቹን ለመፈለግ፥ ወንዝዋን ተከትለን ወደ ታች ብዙ ከወረድንና ከዚያም ሰፍረን ካደርንበት ማዶ ወደ ነበረች መንደር ተመልሰን ጠያይቀን ምንም ፍንጭ ካጣን በሁዋላ እኛም አወራውን መንገድ ይዘን ወደ ደባርቅ ጉዞ ጀመርን።

ትንሽ እንደ ሄድን በወርዱም በቁሙም እንደ ኩዳድ እርሻ በጣም ትልቅ የሆነ ዙሪያውን በቁጥቋጦ የተከበበ እርሻ አገኘን። አወራው ጎዳና ያን እርሻ እኩል ሰንጥቆ ነበር የሚያልፍ። እርሻው መሀከል እንደ ደረስን ዙሪያውን፥ ከከበበው ቁጥቋጦ የጥይት እሩምታ ወደኛ ተተኮሰብን። ከያቅጣጫው የሚተኮብንን የተኩስ ብዛት ስናት በብዙ ሰው መከበባችነን አወቅን። መጀመሪያ ሲተኮስብን በወደቅንበት እንዳለን ትንሽ ቆይተን ከኛ ራቅ ብሎ አንድ ትልቅ የግራር ዛፍ ስለ ነበረ ሄደን እሱን እንድንጠጋ ተመካከርንና፥ በጉንብሳችን እዬሮጥን ሄደን፥ ግራሩን በመሀከላችን አድርገን ሁለታችንም ጀርባችንን ወደ ግራሩ ፊታችን ወደ ጠላቶቻችን አድርገን ተኝተን እንታኮስ

ጀመር። ካቶ ዘውዴም ከኔም ፊት ለፊትና ከግራ ቀኛችን የሚተኮሰው ጥይት ስለ እኛ ባለንበት ሳይደርስ ካጠገባችን ራቅ ብሎ እርሻቸውን ሲፈልስ ስላዬን ጠላቶቻችን ሁሉ የሚተኩሱት ባሮጌ ጠመንጃ መሆኑን ተረዳን። ባንፃሩ የኔ ጠመንጃ ረዥም ለበን ያቶ ዘውዴ ረዥም ምኒሽር ስለ ነበሩ፥ እኛ የምንተኩሰው ጥይት ጠላቶቻችነን አልፎ ይሄዳል። ስለዚህ ልባችን እንደ መርጋት አለና ጥይት እየቆጠብን እንድንተኩስ ተመካከርን።

ከዚያ በሁዋላ እንደ ተመካከርነው «የጠላቶቻችነን ተኩስ በተኩስ እንመልስ » እነሱ ሲተኩሱ አድፍጠን እንቆይና ከቁጥቁዋጦው ብቅ ያለ ሰው ስናይ እንተኩስበታለን፤ እንደ ገና ወደ ቁጥቁዋጦው ተመልሶ ጉዋደኞቹ ጭምር ሲተኩሱብን አድፍጠን እንቆያለን። እንዲህ ወደ እርሻው ብቅ ሲሉ ተኩሰን እዬመለስናቸው እቁጥቁዋጦው ውስጥ ሆነው ሲተኩሱ አድፍጠው እዬቆዬን፥ ስንተኩስ ረዥም ጊዜ ካለፈ በሁዋላ እግዚአብሄር ከገባንበት ወጥመድ ሊያወጣን ሲፈልግ በክፍል በክፍል እዬሆነ ከሚጉዋዘው ዘማች ሰራዊት አንድ ክፍል አውራውን ጎዳና ይዞ ከሁዋላ ብቅ አለ። እሱን ስናይ አስፈርቶን ከነበረው አደጋ ለመዳናችን እርግጠኞች ሆንና በጣም ደስ አለን። ሰራዊቱ ሳይደርስ በነበርንበት ሁኔታ እንዳለን ቀኑን ሙሉ ብንውል ኖሮ፥ ምንም እንኩዋ እዬቆጠብን ብንተኩስ ጥይታችን ማለቁ ስለማይቀር እኒያ የከበቡን ሰዎች እኛን ገድለው ወይም ከነነስፋችን መሳሪኢያችነን መግፈፋቸው አይቀርም ነበር። መቸም የነሱ አላማ እንዲህ በተናጠል የሚያገኙዋቸውን ዘማቾች ገድለውም ይሁን ከነነስፋቸው መሳሪያቸውን መግፈፍ ነው።

ዘማቹ ሰራዊት በብዛት መምጣቱን ሲያዩ ከብበው ይተኩሱብን የነበሩ ሰዎችም ደብዛቸው ስለ ጠፋ፥ ከሰራዊቱ ጋር ተጨምረው ወደ ደባርቅ ተጉዋዝን። ደባርቅ አጠገብ በሰፈርንበት የጡት፥ አባቴን «ቀኛዝማች አለማየሁ ሀይለ ማርያምን » አግኝቼ የበቅሎዎቻችን መሰረቅ ስለ ነገርሁዋቸው ከነጋዴዎች ይሁን ከዘማቾች ሁለት በቅሎዎች አስገዙልኝና ሰራዊቱ «የባህር ዳርን » መንገድ ይዞ ጉዞውን ሲቀጥል አቶ ዮሀንስና እኔ ከሰዎቻችን ጋር ወደ ዳባት አመራን።

ዳባት አገር ጠባቂ ሆነው ለቆዩት፥ ለደጃዝማች አያሌው ልጅ (ለፊታውራሪ መርሶ) ከራስ እምሩ የተፃፈላቸውን ወረቀት ሰጥተን ሁለት፥ ይሁን ሶስት ቀን ያክል እዚያው ቆዬን። ዳባት በቆየንበት ጊዜ ባቶ ዮሀንስ አብዱ መሪነት «ራማ » የተባለው የጣሊያኖች የመሳሪያና የስንቅ ማከማቻ ሲመታ ተማርከው ወደዚያ (ወደ ዳባት) ስለ ተላኩት ጣሊያኖች ጠይቀን ክንዱን በጎራዴ ተመትቶ የነበረው ቁስለኛ ጣሊያን በቁስሉ ሽታ ምክንያት ከጉዋደኞቹ ጋር ባንድ ቤት ሊቀመጥ ባለ መቻሉ ለብቻው ድንኩዋን ተተክሎለት በተቀመጠበት የጣሊያን አይሮፕላን መጥቶ በቦምብ ገድሎት መሄዱንና ሌሎች በኢትዮጵያ አይሮፕላን ወዳዲስ አበባ መላካቸውን ሰማን። እንዲሁም እዚያው ዳባት እንዳለን አንድ የኢትዮጵያ አይሮፕላን መጥታ አረፈች። ነጂዋ «ደምሴ ኃይሌ » የተባለ የትምህርት ቤት ጉዋደኛየ ነበር። ያችን አይሮፕላን ከማረፊያው ወደ ዳር አወጥቶ አቁሞ ከጣሊያን ቦምብ ለመሰወር፥ ያካባቢውን ቁጥቁዋጦ እንድትመስል ቅጠልና ቁጥቁዋጦ እያስቆረጠ አልብሶ ተዋት። ደምሴ ያን ሁሉ ካደረገ በሁዋላ ከተማ ገብቶ ከማረፉ፥ አንድ የጣሊያን አይሮፕላን መጣና «ቀኝ ወይ ግራ » ሳይል ያለችበትን አስቀድሞ እንዳወቀ ሁሉ (አውቆም ሊሆን ይችላል) በቀጥታ ወደስዋ ሄዶ አመድ አድርጎዋት ሌላ ነገር ምንም ሳይነካ ወደ መጣበት ተመለሰ።

የደጃዝማች አያሌው ልጅ፥ ስንቅ እየተሰንዳ እንዲላክበት ከራስ የተቀበሉትን ሰላሳ ሺህ (30.000) ጠገራ ብር ስለ ሰጡት ያን ጭነን ወደ ጎንደር ተጉዋዝን። ጎንደር ለቤገምድርና ለሰሜን የትምህር ሚኒስቴር ሹም የነበሩት አቶ (ሁዋላ ፊታውራሪ) «ዳባ ወሌ » ተቀብለው፥ አቶ ዮሀንስንና እኔን እንዲዒኢያውም እቤታቸው በምቾት አስቀምጠው ደህና አድርገው ሲያስተናግዱን ሰነበቱ። ጎንደር በገባን ማግስት አቶ ዮሀንስና እኔ ወደ ጳጳሱ ወደ፥ ወደ አቡነ አብርሃም ሄደን ከራስ እምሩ የተፃፈላቸውን መልእክት ሰጥተውናቸው ከተመለከቱት በሁዋላ «ነገ እቤተክርስቲያን ስለምውል እስቲ - ለሁሉም ነገ ወደ ማታ ተመለሱ » አሉ የቅርታና የማመንታት መልክ እዬታየባቸው። ጊዜው «አቢይ ፆም » ስለ ነበረ እቤተክርስቲያን መዋላቸው

እውነት ሊሆን ይችላል። በማግስቱ ወደ ማታ እንደ ተቀጠርነው ወደ አባታችን ቤት ሄደን አገኘናቸው።

«ይህን ጉዳይ - ትናንት እናንተ ከሄዳችሁ ጀምሬ፥ አውጥቼ አውርጄ፥ አገላብጬ፥ ባየው አስቸጋሪ ሆኖ አገኘሁት » አሉ ካስቀመጡን በሁዋላ። «እንዴት ነው አስቸጋሪ የሆነብዎ አባታችን? » አላቸው ዮሀንስ። «እያችሁ ልጆቼ ይህ የመንግስት ገንዘብ በኔ እጅ መሆኑን ብዙ ሰው ያውቃል። ስንቅ ተሰናድቶ ወደ ጦርነቱ ግንባር የሚላክበት ጊዜ ሲደርስ ሲደርስ ለማሰናዳቱም ለማስጫኑም «ይረዱኛል » ብዬ ላሰብሁዋቸው ነጋዴዎችና አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች እንዲያውም እኔ ራሴ ነኝ የነገርሁዋቸው። እና መቸም አሁን - ራስ እምሩ በጦርነቱ ድል ሆነው መመለሳቸውን ከማንም የበለጠ እናንተ ታውቃላችሁ። በተንቤን ግንባርም፥ እነራስ ካሳ በርግጥ ድል መሆናእችው እዚህ ከታወቀ ቆይተዋል። ጃንሆይም ድል ሆነው መመለሳቸው በሰፊው ይነገራል። ታዲያ፤ እግዚአብሔር አያድርገው እንጂ ጣሊያኖች ድል አድርገው የመንግስቱን ስልጣን ከያዙ ‹አንተ ዘንድ የተቀመጠውን የመንግስት ገንዘብ አምጣ› ቢሉኝ ምን እመልሳለሁ? ብርቱ ችግር ይደርስብኛልኮ! መቸም እኔ እችግር ውስጥ ብገባ እንደማትወዱ አውቃለሁ። ራስ እምሩም ቢሆኑ እኔ እንድቸገር የሚፈልጉ አይመስለኝም! » አሉ ጳጳሱ።

«የሌላውን ግንባር ሁኔታ አላውቅም እንጂ ራስ እምሩኮ አሁን አባታችን እንዳሉት ድል ሆነው ጦርነቱ አልቆ መመለሳቸው አደለም። እስከ ዛሬ የተደረገው ጦርነት ጠላት ምሽጉን አጠናክሮ መሽጎ እስከ ምሽጉ ድረስ የወታደር የመሳሪያና የስንቅ ማመላለሻ መንገዶች ሰርቶ ባሰናዳቸው ለሱ ምቹ በሆኑ ቦታዎች ላይ በመሆኑ ሰው ስለ ተጎዳባቸው ለሰራዊታቸው ምቹ በሆነ ቦታ ይዘው እዚያ ላይ መሽገው ጠላትን ከመሽገው ምሽግና ከሰራው የመንገድ ሩቅ በሆነ ለሱ በማይመች ቦታ ለመዋጋት ወደ ሁዋላ ማፈግፈጋቸው ነው። የኛም መልእክት የሚቀጥለው ጦርነት በዚህ ገንዘብ ለወታደር ትጥቅና ስንቅ መድሀኒት ገዝተን ለማቅረብ ነው » አልሁ ራስ የነገሩኝን ከሞላ ጎደል ደግሞ። «እኛም የምንመኘው እኛም ቀን ከሌት አምላካችነን በፆምና በፀሎት የምንማጠነው መጨረሻ ድሉ የኛ እንዲሆን ነው። እኛ እግዚአሄር

የሚያደርገው አይታወቅምና የፈራነው የማንወደው ክፉ ነገር የደረሰ እንደ ሆነ እኔ ምን እሆናለሁ? ነው የምላችሁ። »

«መቸም ገንዘቡን ላባታችን የሰጡ ራስ እምሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። አሁን ያን ገንዘብ ለኛ እንዲያስረክቡን ማህተማቸው የታተመበትና ፊርማቸው የተፈረመበት ፅሁፋቸው ደርሶዎታል። ራስ እንደፃፉልዎ ለኛ ለሚያስረክብንም አስፈርመው ነው። ስለዚህ በኛ አስተያየት ባደራ ያስቀመጡትን ገንዘብ ለባለገንዘቡ መመለስ ምንም ችግር የሚያመጣብዎ አይመስለንም » አለ አቶ ዮሀንስ።

«ነገሩ ሁሉ እንዲህ አንተ እንዳልኸው ቀልላ ቢሆንማ እንዴት መልካም ነበር! ግን ላንተ መሰለህ ቀላል አደለም። እስቲ አስቡበት፤ እኔም አስበበታለሁ። አሁን የቀጠርሁዋቸው እንግዶች የሚመጡበት ጊዜ ስለ ደረሰ ሂዱ » ብለው አሰናበቱን።

የጃንሆይን ድል መመለስ ጎንደር እስክንደርስ ድረስ አላወቅንም ነበር። ከሰማን በሁዋላ ግን የጳጳሱን አነጋገርና ጠቅላላ ሁኔታቸውን ስናይ ገንዘቡን እንደማይሰጡን ሁለታችንም ገመትን። ይሁን እንጂ «አስብበታለሁ » ብለው ስለ ነበረ፥ ከቤተክርስቲያ የሚመለሱ ከቅዳሴው በሁዋላ በዘጠኝ ሰአት አካባቢ መሆኑን አረጋግጠን ቁርጡን ለማወቅ በማስቱ ቀደም ብለን ሄደን፥ ከግቢያቸው አጥር ውጭ ቆመን ስንጠብቃቸው በበቅሎ ተቀምጠው በርከት ያሉ ሰዎች አጅበዋቸው መጡ። አጥሩን ገብተው ከበቅሎ እንደ ወረዱ፥

«ትናንት ተነጋግረን ጨርሰን አልነበረም? ዛሬ ልታደርጉ መጣችሁ? ሌላ የምታነጋግሩኝ ጉዳይ አላችሁ? » አሉ፥ አጅበዋቸው ከመጡት ሰዎች መሀከል እደጅ በቆምንበት።

«ለዚያው ለተላከንበት ጉዳይ ነው እንጂ ሌላ ጉዳይስ የለንም። ትናንት አባታችን ‹ላስብበት› ብለው አሰናብተውን ስለ ነበረ አስበው የወሰኑትን እንዲነግሩን ነው ዛሬ የመጣን » አላቸው ዮሀንስ።

«አስቤ የወሰንሁትን ትናንት ነግሬያቸዋለሁ፥ ሌላ አስቤ የምወስነው ነገር የለም። እና - እባካችሁ እዚህ እዬተመላለሳችሁ አታስቸግሩኝ » አሉና ዘበኛቸውን ጠርተው «እነዚህን ሁለት ሰዎች እዚህ እንዳታደርሳቸው! ዳግመኛ የመጡ እንደሆነ ወዲያ ማለት ነው! እንዴት ያሉ - አስቸጋሪዎች ናቸው! » ብለው እያጉረመረሙ ወደ ቤታቸው ሲገቡ ዘበኛው ብቻ ሳይሆን እዚያ ከነበሩት ሰዎች «ሂዱ፤ ወግዱ፤ ሂዱ እንጂ ምን ታደርጋላችሁ? የተባላችሁትን አልሰማችሁም? » የሚሉን ስለበዙ እዬተጉረምን ወደ ማረፊያችን ተመለስን። ጳጳሱ እዚያ ባደባባይ ያን ያክል የማያስፈልግ ነገር ከመናገር፥ ሁለታችንን ይዘው ገብተው ውሳኔያቸውን ነግረው በጭዋነት ሊያሰናብቱን ሲችሉ እንዲያ ያለ «እዩልኝ ስሙልኝ! » አድራጎት ያደረጉበትን ምክንያት ለጊዜው አቶ ዮሀንስም እኔም ልናስተውለው አልቻልንም ነበር። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ከያዙ በሁዋላ እኒያ ጳጳስ፥ የኢትዮጵያ «ፓትርያርክ » ሆነው ተሾሙ።

ራስ እምሩ ለደጃዝማች አያሌው ልጅም ለጳጳሱም የፃፉላቸው ወረቀቶች በተደፈርኑ አንቬሎፖች ሆነው ስለ ተሰጡንና በቃልም ስላልነገሩን በሁለቱ ሰዎች እጅ የነበረው ገንዘብ ምን ምን ያክል እንደ ነበረ አናውቅም ነበር። የደጃዝማች አያሌው ልጅ ገንዘቡን ሲሰጡን የተከቡበትን ሰነድ ስላሳዩን 30.000 ብር መሆኑን ተረዳን። ነገር ግን፥ በጳጳሱ እጅ የቀረው ገንዘብ ምን ያክል እንደ ሆነ አላውቅነውም።

ጃንሆይ ድል ሆነው መመለሳቸውና ጣሊያኖች ያላንዳች ተቃውሞ አዲስ አበባ ለመግባት ከያቅጣጫው በመጉዋዝ ላይ መሆናቸውን ጎንደር እዬተጋነነ ስለ ተወራ እዚያ ከነበሩት ሹማምት አንዳንዶቹ ወደ ሱዳን ለመሸሽ መሰናዳታቸውን ሰማን። መጀመሪያ ከሄዱት መሀከል አሁን የማስታውሳቸው የጎንደር ከንቲባ የነበሩት፥ ከንቲባ ደስታ ምትኬ እና የጎንደር ባንክ ሹም የነበሩት አቶ ተክሌ ሮሮ ነበሩ። ከነሱ ጋር በሽሬ ግንባር የኢትዮጵያን የጦር ሰራዊት ለመርዳት ተልኮ ጦርነቱ ቶሎ ስላለቀ ከጎንደር ወዳገሩ የሚመለስ አንድ የሱዳን «የቀይ መስቀል » ቡድን ነበር። ለቡድኑ ያስተዳደር አላፊና ወዲያውም እንደ አነጋጋሪ ሆኖ የሚረዳ ሱዳን ተምሮ እዚያው ብዙ ጊዜ የቆየ፥

አቶ ሀብቴ ደስታ የሚባል ኢትዮጵያዊ ወጣት ነበር። ሀብቴ ደስታ ሱዳን በተለይ ካርቱም በቆዩሁበት ጊዜ፥ እዚያ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ጋር ያስተዋወቀኝና ችግር በገጠመኝ ቁጥር ስጠራው ይደርስልኝ የነበረ ወዳጄ ነበር።

ጎንደር አንድ ሳምንት ያልሞላ ጊዜ ካሳለፍን በሁዋላ አቶ ዳባ ወሌን አመስግንና ተሰናብተን እኔ አጭሩ ዘሪሁንን ሱዳን አብሮኝ እንዲቆይ አቶ ዘውዴ ወልደ ተክሌን እዚያ ድረስ ሸኝቶኝ ከናቶ ዮሀንስ ጋር እንዲመለስ ይገፍ፥ ከሌሎች ጉዋደኞቼ ጋር እዚያው ጎንደር ተሰነባብተን ከሚሸሹት ሹማምትና ከቀይ መስቀል ሰዎች ጋር በጭልጋ በኩል ተጉዘን ኢትዮጵያና ሱዳን ወሰን ደረስን። ወሰኑ በኢትዮጵያ በኩል «መተማ » በሱዳን በኩል «ገላባት » ናቸው። መተማና ገላባት በበጋ ወራት በሚደርቅ ወንዝ የተለያዩ ከመሆናቸው በቀር እንደ አንድ ከተማ የሚቆጠሩ ናቸው።

እወሰኑ እንደ ደረስን የሱዳን ቀይ መስቀል ሰዎች ተሻግረው ገላባት ገላባት ሲሰፍሩ እኛ ኢትዮጵያውያን መተማ፥ ከከተማው አጠገብ አርፈን፥ ወደ ሱዳን ክፍል ለመሻገር ገላባት የነበሩትን እንግሊዛዊ የወረዳ ገዢ ፈቃድ ጠዬቅን። ወዲያው መሳሪያ የያዙት በኢትዮጵያ ክፍል (መተማ) ቆይተው፥ እኛም የያዝነውን መሳሪያ እዚያ ትተን መሻገር የምንችል መሆናችን ስለተነገረን፥ ያምሳ አለቃ አበበ ወልደ ማርያምን ከጭፍሮቻቸው ጋር መተማ ትተን ዮሀንስ ከአንድ ልጅ ጋርና እኔ ከዘሪሁን ጋር ጀሌያችነን፥ ተሻግረን ገላባት ሰፈርን። ያምሳ አለቃ አበበ፥ አቶ ዘውዴና ሌሎችም ቢሆኑ መሳሪያ ይዘው መሻገር ተከለከሉ እንጂ ጀሌያቸውን ማሻገር ስላልተከለከሉ ወደ «ገዳሪፍ » እስከንሄድ ድረስ አልተለዩንም፤ አብረን ነበርን።

እንግሊዛዊው አገረ ገዢ ማታ ለራት ጋብዘውን ነበር። የመሄጃው ጊዜ ከመድረሱ በፊት፥ አቶ ዮሀንስ ወደ ድንኩዋን ጠርቶኝ ስሄድ ከግራጫ ብርድ ልብሱ በቀጭኑ የቆረጠውን እዬጠቀለለ ይሰፋል።

«የምን ጥብጣብ ነው የምትሰፋው? » አልሁት።

«ና ተቀመጥ » አለና፥ ያን ቀጠን አድርጎ በረዢሙ የሰራውን ጥብጣብ የሚመስል ነገር ባጭር ባጭር ቆርጦ፥

«በል ከሌላው ወገን እንዲህ እያደረግህ ስፋ! » ብሎ ቁራጮቹን ባንድ ወገን በኮቱ ትከሻ ላይ እያጋደመ በተራ አስቀምጦ ይሰፋ ጀመር። እኔም የሰጠኝን ቁራጮች የሱን እያዬሁ በሁለተኛው የኮቱ ትከሻ ላይ ሰፋሁ። በደረቱ ኪስ ላይም አንድ ነገር ሰፋ፥ ከዚያ ያን የብርድ ልብስ ቁራጮች በትከሻዎቹና በደረቱ ኪሱ ክዳን ላይ የተሰፋበት ኮት ሲለብስ የወታደር ሹም ሆነ።

«የምን ምልክት ነው ይሄ? » አልሁት።

«ይህ የምን ምልክት መሆኑን አታውቅም? »

«አላውቅም » አልሁት። እውነቴን ነበር፤ እንኩዋንስ ያን ጊዜ፥ ዛሬም የወታደርን ሹማምንት «የመቶ አለቃ ሻምበል ሻለቃ፥ ወ.ዘ.ተ » እያሉ ሲጠሩዋቸው ካልሆነ መለያ ምልክቶቻቸውን ሆነ ብዬ ስላላጠናሁዋቸው አላውቃቸውም።

«ይህ የሻለቃ ምልክት ነው » አለኝ።

«እና አሁን አንተ ራስህን የሻለቃ አድርገህ መሾምህ ነው? »

«ታዲያስ! የሻለቃነት ይበዛብኛል? »

« ‹ያልሆንኸውን› ማለቴ ነው እንጂ፥ እሱስ ባያንስህ አይበዛህም! »

እንዲያ እየተቀላለድን ስንሳሳቅ ቆይተን ወጥቼ ከድንኩዋኔ በራፍ እንደ ተቀመጥሁ፥ «‹ጊንጥ » የሚሉዋት መርዘኛ ነገር ነድፋ ከተቀመጥሁበት አዘልላ አስነሳችኝ። ጩኸቴን ሲሰሙ ዮሀንስም፥ እዚያ የነበሩት ሌሎች ሰዎችም እዬሮጡ መጥተው «መርዝዋ በሰውነትህ ሁሉ እንዳይሰራጭ የነደፈችው ገላህ ዙሪያውን መበጣት አለበት » ብለው በጥተውኝ ሄዱ። በዚያ ምክንያት እንኩዋንስ አገረ ገዢው ግብዣ ልሂድ ሌሊቱን እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር «እግዚኦ » እንዳልሁ አድሬ በማግስቱ ነበር የተሻለኝ። ዮሀንስ ግን፥ የሻለቃ ልብሱን ለብሶ ሄዶ በክርብር ራቱንም፥ ውስኪውንም ሲጋበዝ ካመሸ በሁዋላ

የሄድንለትን ጉዳይ ላገረ ገዢው ነግሮ፥ ገዳሪፍ ድረስ የሚያደርሰን ካሚዮን አሳዝዞ፥ በደስታ እዬፈነጠዘ ተመለሰ። በማግስቱ ይሁን በሳልስቱ ሁለቱን በቅሎዎቼን እዚያው ገላባት በውድ ዋጋ፥ ያውም በሱዳን ብር ሸጥናቸው። ከዚያ ዘሪሁንና እኔ፥ ካቶ ዘውዴ ወልደ ተክሌ ካምሳ አለቃ አበበ ወልደ ማርያምና ከጭፍሮቻቸውም ተሰናባብተን ካቶ ዮሀንስና ከተከተለው ልጅ ጋር በታዘዘልን ካሚዮን ገንዘባችንን ጭነን ወደ ገዳሪፍ ሄድን። የቀይ መስቀል ሰዎችም በራሳቸው መጉዋጉዋዣ እስከ ገዳሪፍ አብረውን ሄደው ወደ ካርቱም በባቡር ጉዞዋቸውን እስኪቀጥሉ እዚያው ገዳሪፍ ሆቴል ይዘው አረፉና አቶ ሀብቴ ደስታ፥ እኛን ወስዶ «አቶ ዘውዴ » (ያባታቸውን ስም ረሳሁ) ከሚባሉ ኢትዮጵያዊ ጋር አገናኘን።

አቶ ዘውዴ ገዳሪፍ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ጉዳይ እንዲፈፅሙ በእንግሊዝ ባለስልጣኖች ተሹመው በዚያ ስራ ረዢም ጊዜ የቆዩ ነበሩ። በዚያ ጊዜ፥ ገዳሪፍ ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን፥ ከፍተኛ ስራ የነበራቸው በመጠኑ ቢሆኑም በጉልበት ስራ የሚተዳደሩ ሴቶችና ወንዶች በጣም ብዙ ነበሩ። ከወንዶችም ይልቅ ሴቶች! ታዲያ አቶ ዘውዴ የሁሉንም ገመና እንደያመሉ ሸሽገው የሚኖሩ ወገኖቻቸውን ወዳጅ በመሆናቸው እዚያ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚወዱዋቸውና የሚያከብሩዋቸው ነበሩ።

አቶ ዘውዴ እግቢያቸው ውስጥ አንድ የተለዩ ቤት ሰጥተውን እዚያ አረፍን። በማግስቱ አቶ ዮሀንስና እኔ ወደ ሱዳን ስለ ተላክንበት ጉዳይ ለመነጋገር ወደ አገረ ገዢው ከመሄዳችን በፊት የተጎሳቆለ ሰውነታችነን እና ልብሳችነን ስናፀዳዳ እንድንውል እንዲሁም የጎደለንን ልብስ እንድንገዛ ተመካከርን እሱ «ቀደም ብዬ የምደርስበት ሰው አለ » ስላለ ተለያይተን እኔ ወደ ገበያ ሄድሁ። ከዚያ ሀብቴ ደስታ የምፈልገው ነገር በሚገኝበት እያዞረ የምገዛውን ከገዛሁና ጠጉሬን ካስተካከልሁ በሁዋላ ምሳየን እሱ ባረፈበት ሆቴል ጋብዞኝ በልቼ፥ አመሻሽ ላይ አቶ ዘውዴ ግቢ አጠገብ አድርሶኝ ተመለሰ።

«ምሳህን በላህ? » አልሁት ዘሪሁንን እንደ ገባሁ የያዝሁትን እቃ ሲቀበለኝ።

«እኔስ ስጠብቅህ ቆይቼ ስትቀር ጊዜ በላሁ፤ አንተ ጦምህን ዋልህ እንጂ! ለመሆኑ በጤንነት ነው ይህን ያክል የዋልህ? » አለኝ።

«ደህና ነኝ ምሳየን ካቶ ከብቴ ጋር በልቼ እዚያው ስንጫወት ቆዬን፤ ዮሀንስ አልተመለሰም? » አልሁት።

«አቶ ዮሀንስማ ጥዋት ከወጣችሁ በሁዋላ ትንሽ ቆይተው በመቶቢል ተመልሰው ገንዘቡን ወዴት እንደ ወሰዱት አላውቅም ይዘው ሄደው እንደ ገና መጡና እዚህ ከባለቤቱ ጋር ሲነጋገሩ ቆይተው ወደ ገላባት መሄዴንና ነገ የምመለስ መሆኔን ለሀዲስ ንገረ በለውኝ ሄዱ » አለኝ።

ምን እንደ ደረሰ ማወቅ ስላልቻልሁ፥ ግራ ገብቶኝ ዝም ብዬ ከቆየሁ በሁዋላ ወደ አቶ ዘውዴ ሄጄ ዮሀንስ ምን ነግሮዋቸው እንደ ሄደ ጠዬቅሁዋቸው።

«አገረ ገዥ (ዲስትሪክት ኮሚሽነር) መስርያ ቤት ሄዶ፥ ጣሊያኖች መተማን ለመያዝ በግስጋስ ላይ መሆናቸውን ስለ ነገሩት እዚያ እዲቆዩ የተዋቸው ወታደሮች ከነመስሪያቸው በጣሊያኖች እንዳይማረኩ፤ ሰዋራ ቦታ አስይዞዋቸው ነገ የሚመለስ መሆኑን ነግሮኝ ሄደ » አሉኝ።

«ለስራ ያመጣነውን ገንዘብ በኦቶሞቢል ጭኖ መውሰዱን ከኔ ጋር ያለው ልጅ ነገረኝ፤ ወዴት ወስዶ እንዳስቀመጠው የነገረዎ ነገር አለ? » ብላቸው፤

«ስለ ገንዘቡ የነገረኝ ነገር የለም፤ ወደ ገላባት የሚወስደው ካሚዮን እውጪ ቆሞ ይጠብቀው ስለ ነበረ በታም ቸኩሎ ነበር። እኔን ያነጋገረኝ ከግዛቱ መስሪያ ቤት በቀጥታ እንደ መጣ ነበር። ስለዚህ ምናልባት ገንዘቡን እዚያ አስቀምጦት እንደሆን? » አሉኝ አቶ ዘውዴ።

አቶ ዮሀንስ በማግስቱም በሳልስቱም አልተመለሰ። ባራተኛው ቀን አቶ ዘውዴን ወደ ግዛቱ መስሪያ ቤት እንዲወስዱኝ ለመንሁዋቸውና ወስደው ከዋናው ፀሀፊ ካቶ «ሚካኤል በኪት » ጋር አገናኙ። አቶ ሚካኤል በኪት፥ ከኢትዮጵያውያን ወላጆች ሱዳን ውስጥ ተወልደው እዚያው እዬተማሩ አድገው ከዚያ ከፍተኛ ደረጃ ከሚናገሩ ደግ ሰው ነበሩ። አማርኛ መናገር ብቻ

ሳይሆን እንዲያውም ከሚናገሩት የበለጠ ማንበብ መፃፍ የሚያውቁ ነበሩ። አቶ ዘውዴ ማን መሆኔንና ለምን ስራ ወደ ሱዳን እንደ ተላክሁ፥ እኔ ያስጠናሁዋቸውን ገልፀው ካስተዋወቁኝ በሁዋላ አቶ ዮሀንስ ከሶስት ቀን በፊት ገንዘብ እነሱ ዘንድ አስቀምጠ ሄዶ እንደሆነ ሲጠይቁዋቸው ማስቀመጡን አረጋገጡልን።

ገንዘቡ የራስ እምሩ መሆኑንና ያን ገንዘብ በስማቸው ባንክ ለማግባትም እያወጣሁ ያዘዙኝን ስራ ለመስራትም ለኔ ሙሉ ስልጣን የሰጡበትን ፅሁፍ አሳይቼ «አቶ ዮሀንስ ከወታደሮች ጋር እኔን ሱዳን አድርሶ ከመመለስ በቀር ገንዘቡን ለማስቀመጥም ለማውጣትም ስላልታዘዘ እሱ የዘገዬ ወይም ጭራሽ ያልተመለሰ እንደ ሆነ፥ ገንዘቡን ለኔ ማስረከብ አይቻልም ወይ? » አልሁዋቸው።

«አቶ ዮሀንስ ገንዘቡን ያስቀመጡትም ደረሰኝ የተቀበሉትም በስማቸው ስለሆነ ሳያስቸግር አይቀርም። ግን ለሁሉም አገረ - ገዢውን እናነጋግራቸው » አሉና ፅሁፉን እዚያው ራሳቸው ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመው በመኪና አስመትተው ወረቀቱንም እኔንም ይዘውን ወደ አገረ - ገዢው ገቡና ከፅሁፉም ከኔም እንደ ተረዱት ደህና አድርገው ገለፁላቸው።

«አቶ ዮሀንስ በሄዱበት ቀን ማግስት እንደሚመለሱ ነበርኮ የነገሩን፤ አልተመለሱም? » አሉ አገረ - ገዡ።

«ከሄደ አራተኛ ቀን ነው፤ ግን አልተመለሰም » አልሁዋቸው።

«የተገናኘን እለት ስንነጋገር ጣሊያኖች መተማን ለመያዝ መቅረባቸውን ስለነገሩኛቸው መሳሪያ የያዙ ወታደሮች መተማ ትቼ መጥቻለሁና ጣሊያኖች እንዳይማርኩዋቸው ቢቻል ወደ ገላባት እንዲሻገሩልኝ ያለዚያም ሰዋራ ቦታ ይዘው እንዲቆዩኝ አድርጌ ቶሎ እመለሳለሁ ብለው ነበር የሄዱ። ታዲያ ጣሊያኖች መተማን ይዘዋል። ምናልባት ወታደሮቶችንም እሳቸውንም ይዘዋቸው እንደሆነ እስቲ ገላባት በስልክ ልጠይቅ » ብለው አገረ - ገዡ ከገላባት አገረ - ገዢ ጋር ሳይያዙ የሸሹ መሆናቸውንና በተለይ ስለ ዮሀንስ ግን የሰሙት ነገር አለመኖሩን እንዳስታወቁዋቸው ነገሩን።

«እኔ ወደዚህ የተላክሁት አዛዣችን ራስ እምሩ ጦርነቱን ለመቀጠል ስለ ወሰኑ፥ ለወታደሮቻቸው ልብስ መድሀኒትና አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ለመግዛት ነው። ታዲያ ይህን ለማድረግ እንድችል ዮሀንስ ቶሎ ያልተመለሰ እንደ ሆነ ገንዘቡን ለኔ ለማስረከብ ምን የሚያስቸግር ነገር አለ? » አልሁዋቸው። ከዚያ ዮሀንስ ገንዘቡን መስሪያ ቤቱ እንዲያቀምጥለት የጠዬቀበትን ፅሁፍና ከመስሪያ ቤቱ የተቀበለውን የደረሰኝ ግልባጭ አስመጥተው ከተመለከቱ በሁዋላ፥

«አቶ ዮሀንስ ይህን ገንዘብ እዚህ ያስቀመጠው በስሙ ነው፤ መስሪያ ቤታችንም የሰጠው ደረሰኝ የሱን ገንዘብ ባደራ ያስቀመጠ መሆኑን የሚገልፅ ነው፤ በሁለቱም ውስጥ ገንዘቡ የራስ እምሩ መሆኑን የሚያመለክት አንድ ቃል የለም። ስለዚህ ወይ እሱ ካልመጣ ያለዚያም ካለበት ቦታ በመስሪያ ቤታችሁ ያስቀመጥሁትን ገንዘብ ለሀዲስ አስረክቡልኝ ብሎ ካልፃፈልን ላንተ ማስረከብ አንችልም » ብለው ቁርጡን ነገሩኝ።

«ከራስ እምሩ ወረቀት እንደሚያዩት፥ ለዚህ ገንዘብ ባላደራ ያደረጉኝ እኔን ብቻ ነውኮ! በወረቀቱ ውስጥ ያቶ ዮሀንስ ስም እንዲያውም አልተነሳም! » አልሁዋቸው።

«እውነት ነው፤ በዚህ ወረቀት ውስጥ ያቶ ዮሀንስ ስም የለም፤ ግን እሱ እዚህ መስሪያ ቤት ባደራ ያስቀመጠው ገንዘብ በራስ እምሩ ወረቀት ውስጥ የተመለከተው ለመሆኑ ሌላ፥ የራሱን ገንዘብ ላለመሆኑ ምን ማስረጃ አለ? » አሉ እንግሊዛዊው ባለስልጣን እንደ መሳቅ ብለው። «ይልቅስ » አሉ ከተል አድርገው «በጣሊያኖች እጅ ካልወደቀ የሱዳንና የኢትዮጵያ ወሰን በጣም ረዢም ስለሆነና ለጊዜው ጣሊያኖች የያዙት መተማን ብቻ ስለሆነ ካልተያዙት በሮች ባንዱ በኩል አልፎ እዚህ ይደርስ ይሆናልና ተስፋ ሳንቆርጥ እስቲ እሱን እንጠንቀው » ብለው አሰናበቱኝ።

መቸም ዮሀንስ ጣሊያኖች መተማን ለመያዝ መቃረባቸውን ሲሰማ ባይደነግጥና እዚያ የተውናቸውን ወታደሮች ከምርኮ ለማዳን ባይቸኩል ኖሮ፥ በኔ ላይ እንዲያ ያለ ችግር የሚፈጥር ነገር እንደማያደርግ እርግጠኛ ነኝ። ግን

በድንጋጤ ውስጥ በነበረበት ጊዜ በወታደሮች ላይ ያንዣበበውን አደጋ ብቻ ሲመለከት ድንገት ሳይመለስ ቢቀር ገንዘቡን ካስቀመጠበት መስሪያ ቤት እኔም ልሁን ሌላ ሰው ማውጣት የማንችል መሆናችን እንዴት ሳይታዬው ቀረ?

ካገረ - ገዡ ከተሰናበትሁ በሁዋላ፥ እሳቸው ፊት አልቀርብም እንጂ በቀን አንድ ጊዜ መስሪያ ቤታቸውን ሳልረግጥና ካቶ ሚካኤል በኪት ጋር ተገናኝቼ ሳልናገር ውዬ አላአውቅም። ነገር ግን በሄድሁ ቁጥር፥ እዚያ የማገኘው በዮሀንስ ውሬ ፋንታ ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ይዞታቸውን እያስፋፉ መሄዳቸውን ስለ ነበረ፥ ሁል ጊዜ እያዘንሁና እዬተከዝሁ ነበር የምመለሰ። ዘሪሁንም ያዘነና የተከዘ ፊቴን ሲያይ፥ ስለ አቶ ዮሀንስ ከሰማሁት ደስ የሚያሰኝ ወሬ አለመያዜን ገምቶ ምን ወሬ ሰምቼ እንደ መጣሁ መጠዬቁን ተወ።

ካስራ አምስት ቀናት ያክል በሁዋላ እኔ ከግዛቱ መስሪያ ቤት ተመልሼ ዘሪሁን ምሳ፥ የማሰናዳት ስራውን ጨርሶ እደጅ ተቀምጠን ስናወራ፥

«አዋዋ፥ አቶ ዮሀንስ መጡ! » አለ ዘሪሁን፤ ወሬያችነን አቋዋርጦ ወደ አውራው ጎዳና ቀና ብሎ አዬና። ያቶ ዘውዴ ግቢ ካውራው ጎዳና አጠገብ ስለ ሆነ፥ እደጅ ተቀምጦ አላፊ አግዳሚውን መመልከት አንዱ የጊዜ ማሳለፊያችን ነበር።

«የት አለ? » አልሁ፤ የሱን አይን ተከትዬ አውራውን ጎዳና እዬተከተለሁ፤ ዮሀንስን ብፈልግ ማየት ስላልቻልሁ።

«ያቺ ተጭና ሰውዬው የሚስባት የምትሄድ ጥቁር በቅሎ ያቶ ዮሀንስ «ምስንጅር » የሚሉዋት በቅሎ ናትኮ፤ የሚስባት ሰውዬም ያቶ ዮሀንስ አሽከር ነው » አለ ዘሪሁን፤ አቶ ዮሀንስን ከጠፋበት እሱስ አግኝቶ እንዳመጣው ሁሉ ፊቱ በደስታ በርቶ። እውነትም በቅሎዋም ጭኖ እዬሳባት የሚሄደው ሰውም ያቶ ዮሀንስ ነበሩ። ያቺ «ምስንጅር » የሚሉዋት ግመል የምታክል በቅሎ ጣሊያኖች በ «ደባ ጉና » ጦርነት ድል ሆነው ሰፈራቸው ሲዘረፍ ባላገር ዘርፎ ለዮሀንስ የሸጠለት የማታሳስት ነበረች።

«እስቲ ሩጥና ዮሀንስ የት እንዳለ ጠይቀው » አልሁት ዘሪኹንን። ዘሪሁን ሮጦ ባቶ ዮሀንስ አሽከር ደርሰበትና ቆመው ትንሽ ሲነጋገሩ ቆይተው አብረው ወደኔ መጡ።

«ዮሀንስ የት ነው? » አልሁት የዮሀንስ አሽከር ከተሳሳምን በሁዋላ።

«ጌቶችማ - እንጃ! ወዳገራቸው የሄዱ ይመስለኛል! » አለ።

«እንዴት? መቼ? »

«ጣሊያኖች መተማን የያዙ እለት »

«ታዲያ አንተ እንዴት ተለይተህ ቀረህ »

«እኔና ሁለት ወታደሮች ከተማ በገባንበት ጣሊያኖች ከተማውን ስለ ከበቡት በግርግሩ ሾልከን ወጥተን ወደ ሰፈራችን ብንመለስ ሁሉም ሄደው ቆዩን። ከዚያ መሳሪያ ስላልነበረን ወደ ገላባት ተሻግረን ሰንብተን ወታደሮች እዚያው ቀሩ፤ እኔ ግን እናንተን ፍለጋ ወዲህ መጣሁ » አለ።

«እኛን ፍለጋ ከሆነ የመጣህ በቅሎውና አራግፍና አርፈህ ሁሉንም ታጫውተናለህ፤ አሁን የነገርኸን እኔን ጭራሽ አልገባኝም » አልሁት። ከዚያ በቅሎዋ ከተራገፈች በሁዋላ ዘሪሁን ምሳችነን አቅርቦልን ሶስታችንም ተቀምጠን እዩበላን ታሪኩን እንደሚከተለው ዘርዝሮ ተረከልን።

«ጌቶች (አቶ ዮሀንስ) ከዚህ ወደ ገላባት የሄዱ እለት ካገረ ገዡ ጋር ለመነጋገር እንደሆነ አላውቅም፤ እዚያው ገላባት አድረው በማግስቱ ከረፈደ በሁዋላ ነው ወደኛ የመጡ። ወዲያው እንደ ደረሱ ወታደሮቹንም እኛንም ሰብስበው ‹ጣሊያኖች መተማን ለመያዝ በመንገድ ላይ ናቸውና ቁርስ ያልበላችሁ ቶሎ ከተማ ገብታችሁ በልታችሁ ከዚህ እንድንነሳ› አሉን። ከሁለት ወታደሮች በቀር ወታደሮች ሁሉ ቀደም ብለው በተራ እየሄዱ በልተው ተመልሰው ስለ ነበረ ሁለቱ፥ ወታደሮችና እኔ ከተማ ገብተን ቁርስ በመብላት ላይ እንዳለን፥ እውጭ ጫጫጣ፤ ሆነ። ከዚያ ‹ምንድነው› ብንል ‹ከተማውን ወታደር ከበበው› አሉን። እኛ የጣሊያን ጦር መቅረቡን ቀደም ብለው ጌቶች

ነግረውን ስለ ነበረ ከባቢው እሱ መሆኑን አውቀን በግርግሩ ሾከን ወደ ሰፈራችን ብንሄድ ከድንኩዋንና ከቃ በቀር አንድ ሰው የለም፤ ሁሉም አንድ እቃ ሳያንጠለጥሉ መሳሪያቸውን ብቻ እዬያዙ ሸሽተዋል! ከዚያ ድንኩዋኖችን ትሎ ነቃቅለን እቃውን ሰብስበን ይዘን መሳሪያ ባለመያዛችን ስላልተከለከልን ወደ ገላባት ተሻግረን ሰነበትን። ሁለቱ ወታደሮች እዚያው ቀሩ። እኔ ግን ለዘመቻ ከተነሳንበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ደመወዜን ጌቶች እንዲያስቀምጡልኝ አድርጌ ስለ ነበረና አሁን ስለ ተለያዬን ‹ይቺን በቅሎ ብሸጥ የደመወዜን ያክል አላጣባትም ይሆናል› ብዬ ‹በቅሎ በቅሎ ከገላባት ይልቅ ገዳሪፍ ይወደዳል› ሲሉኝ ጊዜ እስዋን እዚህ ለመሸጥና ወዲያውምም ‹እስዋን ባገኝ ስራ ፈልገው ያስይዙኛል ብዬ› ወደዚህ መጣሁ። ገላባት ለመሰንበቻም ወዲህ ለመምጫም ምንም ገንዘብ ስላልነበረኝ እያለቀስሁ እንደ ሙት ንብረት የጌቶችን የመንገድ አልጋና ምንጣፍ የልስብ ሳጥን እንዲሁም አንዳንድ ነገር መሸጥ ግድ ሆነብኝ። የጅ ሻንታቸውንም ሰዎች ‹እንግዛ› ቢሉኝ ምናልባት የመንግስት ጉዳይ የተፃፈበት ወረቀት ይኖርበት እንደሆነ እስዎን ባገኝ ሳያዩት አልሸጥም ብዬ እሱን አልሸጥሁትም » አለ።

ምሳ በልተን ከጨረስን በሁዋላ የጅ ሻንጣው መክፈቻ ከዮሀንስ ጋር በመሆኑ ዘሪሁንና የዮሀንስ ልጅ ሻንጣውን ገብያ ወስደው እስከ ፍትወት እንደ መጡ በውስጡ የነበሩትን ወረቀቶች እያወጣሁ ሳይ፥ ገዳሪፍ ግዛት ፅህፈት ቤት የተቀመጠውን የሰላሳ ሽህ ብር ደረሰኝ እዚያ ስላገኘሁት የደረሰኙ ሳይሆን ገንዘቡ ያኔውኑ በጄ የገባ ያክል ነበር ደስ ያለኝ!

«ግሩም ነው! ይህን ሻንጣ አለመሸጥ እግዚአብሔር መክሮህ እግዚአብሔር ልትልከው የሚገባህን ትክክለኛ መንገድ አመልክቶህ ነው። ግምትህ ትክክል ነው። ይህ ወረቀት ለጊዜው በዮሀንስ እጅ የነበረ ግን እኔ እዚህ አገር ስቆይ የሚያገለግለኝ ብርቱ የመንግስት ትእዛዝ ያለበት ነው። ታዲያ ዮሀንስ እኔ በሌለሁበት ጣሊያኖች መተማን ሊይዙ መቃረባቸውን ድንገት ሲሰማ ቸኩሎ እንደ ያዘው ሄዶ ነበር። እና ቢጠፋ ኖሮ እኔን ብርቱ ችግር ይገጥመኝ ስለ ነበረ እንዲያ ካለ ችግር በማዳንህ በጣም ነው የማመሰግህንህ! » ብዬ ስስመው እሱም ደስ አለው።

በማግስቱ ያን ደረሰኝ ይዤ ወደ ግዛቱ መስሪያ ቤት ሄጄ ላቶ ሚካኤል በኪት ሳሳያቸውና ታሪኩን በዝርዝር ስተርክላቸው እንደ ታምር ቆጥረውት ተገረሙ። ወዲያው ወደ አገረ - ገዡ ይዘውኝ ገብተው የሆነውን ሁሉ እኔ እንደ ተረክሁላቸው አድርገው ከነገሩዋቸው በሁዋላ የደረሰኙን ሲያሳዩዋቸው አገረ - ገዡም ደስ አላቸው። ድሮውንም አገረ - ገዡ የራስ እምሩን ወረቀት እንዳዩ የገንዘቡ ባላደራ እኔ መሆኔን አምነው ነበር። ነገር ግን ዮሀንስ በስሙ አስቀምጦ በስሙ የደረሰኝ የተቀበለበትን ገንዘብ ለኔ ማስተላለፍ ህጋዊ የደረሰኝ ከተመለሰ በሁዋላ እሱ ተቀድዶ የራስ እምሩ ገንዘብ በኔ ባላደራነት በግዛቱ መስሪያ ቤት ባደራ መቀመጡን የሚገልፅ የደረሰኝ እንዲሰጠኝ አዝዘውልኝ ወዲያውኑ ተሰጠኝ።

## ምዕራፍ አስራ ሶስት

# ሱዳን የቆዩንበት ጊዜ

ዘሪሁንና እኔ ሱዳን የቆዬንበት ጊዜ፥ ከግንቦት 1928 መጀመሪያ እስከ ነሐሴ 1928 መጨረሻ ግድም አራት ወራት ያክል ነበር። ካራቱ ወራት ሁለቱን ወራት ያክል የቀረውን ካርቱም ነበር የቆዬን። ገዳሪፍ አቶ ዘውዴ በሰጡን ካስራ አምስት እስከ ሃያ ቀናት ያክል ከቆዬን በኋላ፥ ምንም እንኩዋ እሳቸው አፋቸውን አውጥተው ባይናገሩ፥ እኛ ከያዝነው ሌላ እንግዳ የሚቀበሉበት ቤት ያልበራቸው መሆኑን በማየት እዚያው ባጠገባቸው አንድ ትንሽ ቤት ተከራይተን ወጣን። ግን ከግቢያቸው ብንወጣም ገዳሪፍን እስከ ለቀቅንበት ቀን ድረስ ያቶ ዘዴ ርዳታ አልተለየንም። እንኩዋንስ ጠይቀናቸው ሳንጠይቃቸው እሳቸው አውቀው የሚያደርጉልን ርዳታ ብዙ ነበር።

ካቶ ዘውዴ ሌላ፥ ገዳሪፍ በነበርንበት ጊዜ አይነተኛ ረዳታችን አቶ ሚካኤል በኪት ነበሩ። በተለይ እኔ ሬዲዮ ስላልነበረኝ ስለ ኢትዮጵያ የውስጥና

የውጭ ሁኔታም ሆነ በጠቅላላው ስለ አለም ሁኔታ የማውቀው ካቶ ሚካኤል በኪት ጋር በመነጋገር ነበር። መቸም ፅህፈት ቤታቸውን በቀን አንድ ጊዜ ሳልረግጠው ውዬ አላውቅም! ታዲያ፥ በሄድሁ ቁጥር በደስታ ተቀብለው ቡና እየጋበዙን በየጊዜው ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ውስጥ የያዙዋቸውን ክፍሎች እንዲሁም ለአለም ማህበር አባል ከሆኑት መንግስታት እነማን ኢትዮጵያን ደግፈው በኢጣሊያ ላይ ቅጣት እንዲጣልባት አሳብ እንዳቀረቡና እነማን ቅጣቱን እንደተቃወሙ ነግረውኝ ተስፋ እንዳልቆርጥ አበረታተውኝ እሄዳለሁ። ጃንሆይ ቤተሰባቸውንና ብዙ መኩዋንንታቸውን ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳቸውን፥ ከዚያም ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄዱ መሆናቸውን መጀመሪያ የሰማሁ ካቶ ሚካኤል ነበር።

አቶ ሚካኤል በኪት፥ ምንም እንኩዋ ሱዳን ተወልደው አድገው እዚያ በክብር የኖሩ ቢሆኑ የኢትዮጵያ ነፃነት መጥፋት በጉያዋ አቅፋ የናትነት ፍቅርዋን እየመገበት እንዳሳደገቻቸው ኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ሁሉ ነበር ያሳመማቸው። ሙሶሎኒ የጦር ሰራዊቱ አዲስ አበባ የገባበትን ቀን አስታውቆ፥ ከዚያ ቀን ጀምራ ኢትዮጵያ ነፃ አገር መሆንዋ ቀርቶ የጣሊያን ቅኝ ግዛት እንደ ሆነች ማስታወቁን ሰምተው የነገሩኝ እለት ከኔ ጋር ያለቀሱትን መሪር ልቅሶ አልረሳውም አብሮኝ ይኖራል።

ኢትዮጵያ የጣሊያን ቅኝ ግዛት መሆንዋን ሙሶሊኒ ባዋጅ ካስታወቀ በሁዋላ የኢትዮጵያ የክብርዋና የነፃነትዋ ምልክቶች የሆኑት ነገሮች ሁሉ ተዋረዱ ወደቁ። በገዳሪፍ ግዛት መስሪያ ቤት ያስቀመጥሁት የኢትዮጵያ ብርም ከነፃነትዋ ምልክቶች አንዱ ስለ ነበረ ከኢትዮጵያ ነፃነት ጋር አብሮ ወደቀ፤ ዋጋ አጣ! ሳስቀምጠው ከሱዳን ብር ጋር አንድ ላንድ የነበረው ባንድ ጊዜ በግማሽ ወረደ። እዚያ ላይም አልቆመ፤ በዬቀኑ እየወረደ እየወረደ ሄዶ በመጨረሻ ፈላጊ አጣ። የሚፈልጉት አንዳንድ ነጋዴዎች ቢኖሩ ለመገበያያ ገንዘብነቱ ሳይሆን፥ ተነጥሮ ጥሩውን ብር ለጌጣጌጥ መስሪያነቱ ብቻ ሆነ። ያን ጊዜ ወደ ሱዳን የተላክሁበት አላማ ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ታዬኝና አዘኔ ከኔ አልፎ አቶ ሚካኤልንና አቶ ዘውዴን አስጨንቆዋቸው እኔን ለመርዳት ያላሰቡትና ያልሞከሩት ነገር አልነበረም።

አንድ ቀን አቶ ዘውዴን ጭምር አቶ ሚካኤል በኪት ጠርተውን እፅህፈት ቤታቸው ገብተን እንደ ተቀመጥን፤ «የሱን የወንድማችንን ችግር የሚያቃልል መስሎ የታኘዬን አሳብ እንድልገልፅልዎና እንድንመክርበት ነው፥ ዛሬ እርስዎ ጭምር እንዲመጡ ያስቸገርሁዎ » አሉዋቸው «የሱን የወንድማችንን » ሲሉ ወደኔ እያመለከቱ።

«ምንጊዜም ቢሆን ወደስዎ መምጣት በስራዎ ጣልቃ ገብቸ እንዳላስቸግርዎ እሰጋለሁ እንጂ ለኔስ ደስታ ነው። ይልቁንም የሱ ችግር የሚቃለልበት መንገድ ከተገኘ እንኩዋንስ እርስዎ ዘንድ ሩቅ አገር ብሄድ አይከብደኝም » አሉ አቶ ዘውዴ።

«እንደሚያውቁት እዚህ እኛ ዘንድ ያስቀመጠው ገንዘብ ዋላ ስላጣ፣ እንደታሰበው ኢትዮጵያ ውስጥ ከጠላት ጋር ለሚዋጉት ወታደሮች ልብስና መድሀኒት ገዝቶ ሊወስድላቸው ላይችል ነው ማለት ነው። ታዲያ እዚያ (ኢትዮጵያ) ያሉት ኢትዮጵያውያን ለጋራ አገራችን ነፃነት ህይወታቸውን ሲሰጡ እኛ እዚህ ያለነው ኢትዮጵያውያን ለመድሀኒትና ለልብስ የሚሆናቸው ገንዘብ እንደያቅማቸው አዋጥተው መስጠት ይበዛብናል? ለኔ እንደሚመስለኝ ገዳሪፍ የምንኖረው ኢትዮጵያውያን ብዙ ስለሆን ሴት ወንዱ ልጅ አዋቂው እንደያቅሙ ቢያዋጣ ይህን ዋጋ ያጣ ገንዘብ ይህን እንደ ጠፋ የሚቆጠር ሰላሳ ሺህ ብር ሰብስቦ መተካት ይቻላል። ስለዚህ ይህን አሳብ መሰንበቻውን ብቻየን ሳሰላስል ከሰነበትሁ በሁዋላ ነው፤ ከሰዎቹ ጋር ከኔ የተሻለ ግንኙነት ያለዎ ከመሆንዎ፤ ከርስዎ ጋር እንድንመካከርበት ፈለግሁ።

«ማለፊያ አሳብ አስበዋል ፈቃደኞች ስንት እንደሚሆኑ አናውቅም እንጂ ሁሉም ፈቃደኞች ከሆኑማ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ ይቻላል። አቅም የሚያንሳቸው ስለሚኖሩ እነሱን ብንተዋቸው እንኩዋ ከሚችሉት ሰላሳ ሺህ የሱዳን ብር መሰብሰብ ባይቻልም የኢትዮጵያን ብር ለጌጣጌጥ ስራ ገዝተው ለሚነግዱ አትራፊ ነጋዴዎች ባወጣው ዋጋ ሸጦ የሚጐድለውን የሚያሙዋላ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚቻል ይመስለኛል። ለማናቸውም የሁለታችሁም ፈቃድ ቢሆን ስለ ብሩ ሽያጭ ካንዳንድ ነጋዴዎች ስለመዋጮው ካንዳንድ

ተደማጭነት ካላቸው ያገራችን ሰዎች ጋር ተነጋግሬ አሳባቸውን ካወቅሁ በሁዋላ እንደ ገና እንነጋገርበት » አሉ አቶ ዘውዴ።

«ማለፊያ ነው። ብቻ ስለ ብሩ ሽያጭ ካንድ ብቻ ሳይሆን በርከት ካሉ ነጋዴዎች ጋር ቀስ ብለው ውስጥ ለውስጥ ተነጋግረው እያንዳንዳቸው ያቀረቡትን ዋጋ ካወቁ በሁዋላ የስምምነት ቃልዎን ከመስጠትዎ በፊት እዚህ እንደገና ብንነጋገርበት ይሻላል። ይህን ያልሁበት ምክንያት እኔም የማውቃቸው አንዳንድ ነጋዴዎች ስላሉ መጠየቁ አይቀርምና ለሁለታችን የቀረቡትን ዋጋዎች አመዛዝነን መምረጥ እንድንችል ነው » ብለው አቶ ሚካኤል አሰናበቱን። ያነለታ ጠፍቶ የነበረው የመልእክቴ አላማ እንደፊቱ ጠርቶ ጎልቶ ባይሆንም ደብዘዝ ብሎ በሩቅ ይታየኝና ደስ እያለኝ ወደ ቤቴ ተመለስሁ።

አቶ ዘውዴ ላቶ ሚካኤልና ለኔ እንደ ነገሩን ከብር ነጋዴዎችና ስለ መዋጮው ከኢትዮጵያውያን ጋር በመነጋገር ላይ እንዳሉ አንድ ቀን፥ አቶ ሚካኤል ፅህፈት ቤት ስደርስ አዲስ ወሬ ቆዩኝ።

«ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛታቸው መሆንዋን ካስታወቁ በሁዋላ መገበያያ ገንዘብ በኢትዮጵያ፥ ብር ፋንታ የጣሊያን ሊሬ እንዲሆን አውጀው፥ አሁን ብሩን ከኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በወሰንዋ ባሉት አገሮች የሚገኘውንም በውድ ዋጋ እዬገዙ መሰብሰብ ስለ ጀመሩ ለጊዜው የኢትዮጵያ ብር ዋጋ ከፍ እያለ መሄዱን ሰማሁ። ስለዚህ ከሱዳን ብር ጋር አንድ ላንድ በሚለወጥበት ደረጃ ከደረሰ፤ ‹ይዋል ይደር› ሳትል ቶሎ ብትሸጠው ይሻላል። ይህን የምልበት ምክንያት ጣሊያኖች መሰብሰቡን ሲያቆሙ የብር ዋጋ ተመልሶ መውደቁ የማይቀር መሆኑን ስለማወቅ ነው » አሉኝ አቶ ሚካኤል። እኔም ሳላመነታ በሳቸው ተስማማሁ።

እውነትም በጥቂት ቀናት ውስጥ አቶ ሚካኤል እንደነገሩኝ መተማን የያዙት ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ብር እየፈለጉ በውድ ዋጋ መግዛታቸው ገዳሪፍ በሰፊው ስለተወራ፥ ቀደም ብለው አቶ ዘውዴ ያነጋገሩዋቸው የብር ነጋዴዎች አንዱን የኢትዮጵያ ብር አንድ የሱዳን ብር ካንድ መሀለቅ (ፒያስትር) ሂሳብ ገዙት። አስር መሀለቅ (ፒያስትር) አንድ የሱዳን ብር ስለሆነ ሰላሳው ሺህ

የኢትዮጵያ ብር ሰላሳ ሶስት ሺህ የሱዳን ብር ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ ያን ሰላሳ ሶስት ሺህ ብር የሱዳን ብር ባንክ አግብቼ «ኧሁ! » አልሁ፤ አረፍሁ!

አቶ ዘውዴ ስለ መዋጮው ከኢትዮጵያውያን ጋር ባደረጉት ንግግር ደስ የሚያሰኝና የተረጋገጠ ተስፋ ማግኘታቸውን ላቶ ሚካኤልና ለኔ ነግረውን ነበር። ገዳሪፍ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሁሉቃ፤ ገብተው ነበር። በተለይ ሴቶች ወርቃቸውንና ሌላ ጌጣቸውን እዬሸጡ ለማዋጣት ያስታውቁት ገንዘብ ወርቃቸውንና ሌላ ጌጣቸውን እዬሸጡ ለማዋጣት ያስታውቁት ገንዘብ ሲታይ መዋጮው ከአሰበው በላይ የሚገመት ነበር። ነገር ግን ያልታሰበ አጋጣሚ ደርሶ፥ የኢትዮጵያ ብር ከቀድሞ ዋጋው እንኩዋ ከፍ ብሎ ስለ ተሸጠ አቶ ዘውዴ ለሁሉም ምስጋናችንን ገልፀው መዋጮው የሚያስፈልግ መሆኑን እንዲያስታውቁልን አደረግን።

ራስ እምሩ ጎሬ መድረሳቸውን አቶ ሚካኤል በኪት እዚያ በነበረው የቆንስላቸው መስሪያ ቤት በኩል አውቀው ነግረውኝ ነበር። ነገር ግን ምንም እንኩዋ አቶ ዮሀንስ ደርሰባቸው ከተገናኙ እኔ ገዳሪፍ መሆኔን ሳይነግራቸው እንደማይቀር የታወቀ ሲሆን እስከዚያ ድረስ ከራስ የደረሰኝ መልእክት እንደማይቀር የታወቀ ሲሆን እስከዚያ ድረስ ከራስ የደረሰኝ መልእክት አልነበረም። በመሀከሉ የግል ገንዘቤ እያለቀ ስለሄደ ዘሪሁንና እኔ እንዴት አድርገን መኖር እንደምንችል በታም ያሳስበኝ ጀመር። ወደ ሱዳን እንድንሄድ ስንታዘዝ፥ የስድስት ወር ደመወዜን ከሶስት መቶ ብር በላይ ተቀብዬ ነበር ከራስ የተሰናበትሁ። እንዲሁም ሁለቱን በቅሎዎችን ገላባት ሸጨ ከሞላ ጎደል ያኑ ያክል የሱዳን ብር አግኝቻለሁ። ያን ያክል ገንዘብ በኢትዮጵያ ለሁለት ሰዎች ለብዙ ጊዜ በበቃ ነበር። ነገር ግን ሱዳን የኑሮ ዋጋ ከኢትዮጵያ ይወደድ ስለ ነበር፥ ሁለት ወራት ሳያቆዬን ወደ ማለቁ ተቃረበ።

አንድ ቀን ጥዋት ዘሪሁን ለምግባችን የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሊገዛ ወደ ገበያ መሄድ ፈልጎ፥ ገንዘብ ሲጠይቀኝ የነበረን ገንዘብ ትንሽ መሆኑን አይቼ «ዘሪሁን ከምትገዛው ነገር አንዳንዱን ብትተው ይሻላል። እዚህ አገር ምን ያክል ጊዜ እንደምንቆይ አናውቅም፤ ያለን ገንዘብ ግን ብዙ ጊዜ የሚያቆዬን

አይደለም » አልሁት። ዘሪሁን ማዘኔን ከፊቴ ሲያይ እሱም እንደ ማዘን ብሎ ትንሽ አንገቱን ደፍቶ ሲያስብ ቆዬና፤

«የቀረን ገንዘብ አንድ አህያ ለመግዛት አይበቃም? » አለ፤ አዝኖ የነበረ ፊቱ ከመቅፅበት በርቶ።

«አህያ? አህያ ለምን እንገዛለን ዘሪሁን? » አልሁት።

«አዬህ አዋዋ! አንድ ደህና አህያ ከነውሀ መጫኛ ሸራው ለመግዛት የሚበቃ ገንዘብ ካለን፥ ስድስት ወይም ሰባት ዘበኞች (ደንበኞች) አብጅቼ ለነሱ በዬቀኑ የሚያስፈልጋቸውን ውሀ እዬቀዳሁ ባቀብል፥ እንኳዋንስ ላንተና ለኔ ለሌላም የሚተርፍ ገንዘብ ማግኘት እንችላለን። ስለዚህ በገንዘብ የምንቸገር መስሎህ አይዞህ አትስጋ! እዚህ ውሀ ቀድተው ለዘቡኞቻቸው እያደሉ ልጆቻቸውን አስተምረው አባት እናቶቻቸውን ረድተው ምንም ችግር ሳያገኛቸው የሚኖሩትን ብዙ ሰዎች አይታይም? ስለዚህ እግዚአብሔር ጤና ከሰጠን፥ ብዙ ፈገግ ባለ የሚያበረታታ ፊት እንደ ፈራ ህፃን እዬመላለሰ «አይዞህ! አይዞህ! » እያለ። ዘሪሁን እኔን ለመርዳት ምን ያክል እንደሚያስብ ካነጋገሩና ከሁኔታው ሁሉ ስንመለከት ልቤ ተነክቶ፣ አይኖቼ እንባ ሲያዝሉ ስላዬ፤

«ምነ አዋዋ? የሚያሳዝንህ ነገር ተናገርሁ? » አለ እንደ መደንገጥ ብሎ።

«ኧረ የለም! በጣም ደስ የሚያሰኝ ግሩም አሳብ ነው ያሰብኸው ዘሪሁን! ምናልባት ራስ ይፅፉልን እንደ ሆነ ትንሽ እንጠብቅና ካልፃፉልን የኛ ገንዘብ ባይበቃም ተበድረን ሞልተን አሁን እንዳልኸው አህያውን እስከ መሳሪያው እንገዛና ኋዋላ አንተ ሰርተህ ከምናገኘው ገንዘብ እዬቆጠብን ብድራችንን እንከፍላለን። ስታነጋግረኝ እንባ የመጣብህ ይህ ሁሉ ችግር ባገራችን ላይ የደረሰው መከራ ያስከተለው መሆኑ ድንገት ስለታሰበኝ ነው » ብዬ ውሸቴን ነገርሁትና ገንዘብ ሰጥቸው እሱ ወደ ገብያው ሲሄድ እኔ ወዳቶ ሚካኤል ፅህፈት ቤት ሄድሁ።

ከዘሪሁን ጋር ስለ ገንዘብ ችግር ከተነጋገርን በኋላ፥ በሶስተኛው ይሁን ወይም ባራተኛው ቀን እንደ ልማዴ ወሬ ለመጠየቅ አቶ ሚካኤል ፅህፈት ቤት ስደርስ ፈቃደ፥ ስላሴ ህሩይ እና ሲራክ ህሩይ የሚባሉ ሁለት ሰዎች ከኢትዮጵያ ወደ እንግሊዝ አገር ሲሄዱ ካርቱም አርፈው ለኔ መልእክት ስለያዙ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ካርቱም ‹ሴንት ጀምስ ሆቴል› እንደሚጠብቁኝ ስልክ ማድረጋቸውን ነገሩኝ።

ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይና ልጅ (ሁዋላ ብላታ) ሲራክ ህሩይ ለብዙ ጊዜ፥ በጦርነቱ ጊዜ ጭምር የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የብላቴን ጌታ ህሩይ ልጆች ነበሩ። ሁለቱንም በስም ካልሆነ አይቻቸው አላውቅም። ልጅ ሲራክ ህሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ፀሀፊ መሆኑ እስማ ነበር። ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይ የክቡር ራስ እምሩ ልጅ የወይዘሮ የምስራች እምሩ ባለቤት ስለ ነበሩ በጎሬ በኩል አልፈው እንደሆነ የያዙልኝ መልእክት ከራስ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትሁ። ከዚያ ግምቴ ልክ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ፤

«እነህ ሁለት ሰዎች ከኢትዮጵያ በየት በኩል ሱዳን ገብተው ይሆን ካርቱም የደረሱ? » አልሁዋቸው አቶ ሚካኤልን።

በሳልስቱ ዘሪሁንና እኔ ቤት ነው ሱዳን የገቡ » ሲሉኝ መልእክቱ እርግጥ ከራስ መሆኑን ስላመንሁ እጅግ ደስ አለኝ!

በሳልስቱ ዘሪሁንና እኔ ቤት ላከራዩን ሰው የኪራዩን ውዝፍ ከፍለን አቶ ሚካኤል በኪትንና አቶ ዘውዴን ገዳሪፍ በቆዬንበት ጊዜ ስላደረጉልን የማይረሳ ርዳታ አመስነንና ተሰናብተን በባቡር ወደ ካርቱም ተጉዋዝን። እዚያ፥ አቶ ሀብቴ ደስታ አድራሻውን ሰጥቶኝ ስለ ነበር፤ የራሳችንን ቤት በሱ ርዳታ እስከናገኝ በቀጥታ እሱ ቤት ሄደን አረፍን። ወዲያው «ሴንት ጀምስ » ሆቴል ወስዶ ከልጅ ሲራክ ጋር አገናኘኝ። ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይን አላገኘሁዋቸውም፤ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው ቆዩኝ። ልጅ ሲራክ ህሩይም እኔን ለመጠበቅ ብቻ ነበር የቆዬው።

ልጅ ሲራክ ገዝቼ ወደ ጎሬ እንድወስድላቸው ራስ ከሰጡት የዕቃ ዝርዝር ጋር፥ ከግንቦት 1928 እስከ ጥቅምት 1929 የስድት ወር ደመወዜን ጭምር

በሱዳን ብር ስለሰጠኝ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ተጭኖኝ የነበረው ከባድ ያሳብ ጭንቀት ከትከሻየ ወርዶ የወደቀ መስሎ ተሰማኝና ቀለል አለኝ። ከዚያ በሁዋላ ሁለት ቀን እዬተገናኘን እሱ ጣሊያኖች ከገቡ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ነበረው ሁኔታ እዬነገረኝ እኔ ስለ ሽሬ ገጠሙን አንዳንድ ችግሮችም እያወራሁት ስንወያይ ቆይተን ወደ እንግሊዝ አገር ሄደ።

ከልጅ ሲራክ ጋር ተገናኝቼ መነጋገሬ በጣም ነበር የረዳኝ። ጣሊያኖች ሰራዊታቸው አዲስ አበባ መግባቱንና ኢትዮጵያ የነሱ ቅኝ ግዛት እንደሆነች ማስታወቃቸውን ስሰማ የክቡር ራስ እምሩ ወሬም ሲጠፋኝ «ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን በሙሉ ይዘው ያለተቃውሞ ተደላድለው ተቀምጠው ይሆን? » የማለት ስጋት አድሮብኝ ተስፋየ መመንመን ጀምሮ ነበር። ነገር ግን ጣሊያኖች አዲስ አበባ የገቡ እለት ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢትዮጵያ የነሱ ቅኝ ግዛት መሆንዋን ማስታወቃቸው እውነት ቢሆንም በሲዳሞና በባሌ በገሙጎፋና በኢሉባቦርና በወለጋ በጠቅላላው ከደቡብ ምዕራብ እስከ ምዕራብ የኢትዮጵያ አገረ - ገዥዎች ሁሉም የጦር ሰራዊታቸውን እንደያዙ በየቦታቸው እንዳሉ ከመሆናቸው ሌላ ጃንሆይ የኢትዮጵያ መንግስት መቀመጫ ጎሬ ሆኖ እሳቸው እስኪመለሱ ቢትወደድ ወልደ ፃድቅን ጠባቂ አድርገው ሾመው ከአለም ማህበር እርዳታ ሊጠይቁ የሄዱ መሆናቸውን ልጅ ሲራክ ሲነግረኝ ቀዝቅዞ ከሞት አፋፍ ደርሶ የነበረው ጦርነቱን ቀጥሎ ድል የመቀዳጀት ተስፋየ እንደገና ሙቀትና ህይወት አገኘ። ልጅ ሲራክ እንደነገረኝ ጣሊያኖች «ይዘናቸዋል » በሚሉዋቸው አገሮች በትግራይ በቤገምድርና በሰሜን በጎጃምና በሸዋ እንኩዋ ከከተሞች በቀር መሀል አገሩ በኢትዮጵያውያን አርበኞች እጅ ነበር። ይህ ሁሉ ትግሉ ለረዥም ጊዜ ሊቀጥል የሚችል መሆኑንና «በመጨረሻ ድሉ ለኢትዮጵያ ይሆን ይሆናል! » የማለትን ተስፋ የሚፈጥር ነበር።

ልጅ ሲራክ ወደ እንግሊዝ አገር እንደ ሄደ አቶ ሀብቴ ደስታ፥ እኔንና ዘሪሁንን ካርቱም ይኖሩ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ካንዳንዶቹ አስተዋወቀን እሱ ባስተዋወቀን ሰዎች አማካይነትም ከብዙ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተዋወቅን።

ገዳሪፍ በቆየንበት ጊዜ ምንም እንኳዋ እዚያ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ብዙ ቢኢሆኑ ካቶ ሚካኤል በኪትና ካቶ ዘውዴ በቀር ከሌሎች ጋር ይህን ያክል የተቀራረበ ግንኙነት አልነበረንም። ምናልባት ገዳሪፍ ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች በጣም የሚበዙት የጉልበት ሥራ እዬሰሩ በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ ስለ ነበሩ እኛን ለመንከባከብና ለመርዳት ጊዜያቸውም ሁኔታቸውም ባይፈቅዱላቸው ይሆናል። ካርቱም የነበሩት ኢትዮጵያውያን ግን በመግንስት የሰላም የጦር አስተዳደር ውስጥ በሹመት ላይ ኖረው በጡረታ የተገለሉም ባገልግሎት ላይ የነበሩትም ነበሩ። እንዲሁም የንግድና ልዩ ልዩ የግል ስራቸው እየሰሩ ደህና ኑሮ የሚኖሩት ብዙ ነበሩ። ታዲያ እኒያ ሰዎች የሚበዙት ዘሪሁንንና እኔን የጋራ ጠላት ከሆነው የፋሽስት ጦር ጋር ሲዋጉ ቆይተው ወደ ሱዳን ከገቡት ኢትዮጵያውያን የመጀመሪያዎቹ እኛ በመሆናችን እንደሆነ አይታወቅም ‹እንደ ከፉ ቀን እህል› እየተሻሙ በዬቤታቸው ይጋበዙን ስለ ነበረ ከቁስ በቀር ምሳን ራት እቤታቸው በዬቤታቸው ይጋበዙን ስለ ነበረ ከቁርስ በቀር ምሳና ራት እቤታችን የምንበላበት ጊዜ አልፎ አልፎ ሆነ። ይልቁንም የሚጋበዙን ሁሉ ዘሪሁንንና እኔን ብቻ ሳይሆን ለኛ ክብር ትልቅ ድግስ እዬደገሱ ብዙ ሴቶችንና ወንዶችን ኢትዮጵያውያን ጭምር ጋብዘው እዚያ ከሙብሉና ከመጠጡ ጋር በሸክላ የተቀረፀ ያገራችን ዘፈን እንጉርጉሮ ቀረርቶ ፉከራ፥.......ወዘተ በሙዚቃ ሲሰማ ባንድ ላይ ሆነን ደስ የሚያሰኘው ደስ እያሰኘን የሚያሳዝነን የሚሸንጠው እዬነሸጠን አናሳልፍ የነበርንበትን ጊዜ ምንም ቢሆን አልረሳውም፤ ትዝታው አብሮኝ ይኖራል።

አቶ ሀብቴ ደስታ ካርቱም መጀመሪያ ካስተዋወቁኝ ኢትዮጵያውያን መሀከል ወዳገሬ እስኪመለስ ድረስ በምክርና በስራም ዋና ረዳቴ የነበሩ አቶ «መንግስቱና ናይዝጊ » ነበሩ። አቶ መንግስቱ የኤሌክትሪክ ስራ አዋቂ ስለ ነብሩ ከመንግስትም ከግል ድርጅቶችና ሰዎችም ጋር የተዋዋሉ እዬሰሩ ደህና ንብረትና በርከት ያሉ ልጆች የነበሩዋቸው ጭዋ ሰው ነበሩ። አቶ ሳሊም እና አቶ ኡመር የተባሉ ከሀረር ሄደው በሱዳን ጦር ሰራዊት ውስጥ በመኮንንነት ማእረግ ሲያገለግሉ ኖረው ጡረታ የወጡ ሁለት ሰዎችም ያቶ መንግስቱን ያክል አይሁን እንጂ ደህና ረዳቶቼ ነበሩ።

አቶ ሳሊም በጡረታቸው ላይ ማለፊያ የልዩ ልዩ ሸቀጦች ሱቅ ስለ ነበራቸው ሀብት ካላቸው ኢትዮጵያውያን መሀከል አንዱ ናቸው ሲባል እስማ ነበር። ግብዣ ከሌለኝ ብዙ ጊዜ እሳቸው ሱቅ እዬሄድሁ ነበር የማመሽ። ከሀይማኖት ጋር ተያይዞ በቆዬ ልምድ ይሁን ወይም በህግ የሚያስከር መጠጥ መግዛት ለሱዳኖች ክልክል ስለ ነበረና ለኢትዮጵያውያን ግን ይፈቀድ ስለ ነበረ አንድ አቶ ሳሊም በጡረታ የተገለሉ የስላም የጦር መኩዋንንት ጉዋደኞቻቸው ገንዘባቸውን አዋጥተው ውስኪው፥ ቢራውና ሌላው ልዩ ልዩ መጠጥ ባቶ ሳሊም ስም በገፍ ተገዝቶ እሳቸው ሱቅ እየተጠጣ ጭዋታውና ውካታው በጣም ደስ ያሰኝ ስለ ነበረ እዚያ ማምሸት እወድ ነበር። እኒያ ከልጅነታቸው ጀምረው አብረው አድገው፥ አብረው የሸመገሉ ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲጠራጠሩም ሲነጋገሩም ሲሰዳደቡም ልክ እንደልጅነታቸው ‹ስማ አንተ ልጅ! ምን ማለትህ ነው? አንተ ልጅ! ምናባቱ ይኸ ልጅ!› ነበር የሚባባሉ። በጭዋታቸው መሀከል እስበሳቸው አባት እናቶቻቸውን የሚሰዳደቡባቸው ቃላት በኛ ልምድ ከረኞች ልጆች ካልሆነ፥ ካዋቆች አፍ የማይወጡ ‹ነውር› ወይም ‹ፀያፍ› የምንላቸው ነበሩ። ታዲያ እኔ አረብኛ መናገር ባልችልም በመጠኑ መስማት ችዬ ስለ ነበረ እኒያ ሽማግሎች የሚሳደቡባቸውን ቃላት ስሰማ ሳቄን መግታት ያቅተኝና ትንፋሽ እስኪያጥረኝ ከልቤ ስስቅ እነሱ ደግሞ እኔን እንደ ቂል ቆጥረውኝ «ኢነአላቡክ! » ብለው ትከሻየን እዬመቱ ይስቁብኛል።

ለኛ ክብር ትልቅ ድግስ እዬደገሱ በካርቱም ነዋሪዎች የነበሩትን ብዙ ኢትዮጵያውያን ከጋበዙት ወይዛዝር መካከል በተለይ እመይቴ ወይዘሮ ደጊቱ ፈለቀና እመይቴ ወዘርሮ ላቀች (ያባታቸውን ስም ረቻለሁ) ዘሪሁንንና እኔን ልክ እንደ ቤተሰቦቻቸው ነበር የሚያዩን። ካርቱም እስክንለቅ ድረስ፥ እኒያ ሁለት ወይዛዝር ልክ እንደ ቤተሰቦቻቸው፥ ቀጠሮ ሳንጠይቅና ጊዜ ሳንጠብቅ ባሻን ጊዜ እቤታቸው እዬገባን በልተን ጠጥተን ተጫውተን የምንወጣባቸው ነበሩ።

በጠቅላላው ዘሪሁንና እኔ ካርቱም የነበርንበት ጊዜ አገራችን በጠላት እጅ የወደቀችበት ከመሆኑ ሌላ እኛ ወደ ፊት ምን እንደሚገጥመን የማናውቅ

በመሆናችን በብርቱ ጭንቀት ውስጥ የነበርንበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን እዚያ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በየበኩላቸው እኛን ለማስደሰት ያደርጉልን የነበረው እንክብካቤ ርዳታቸው ፍቅራቸውና ጭዋታቸው የነበረብን ጭንቀት በሙሉ ከብደት እንዳይሰማን የሚያደርግና ብዙ ጊዜ እንዲያውም ጭንቀታችንን አስረስቶ ያዝናናን ስለ ነበረ አሁን እንኳዋ ሳስታውሰው ልቤን ይነካዋል!

ካርቱም በቆዬንበት ጊዜ የጃንሆይ ዋና የልፍኝ እስከልካይ የነበሩት ‹ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ› ጃንሆይ ኢትዮጵያን ለቀው ሲወጡ መጀመሪያ እስከ ኢዬሩሳሌም ከዚያ፥ እስከ እንግሊዝ አገር ሸኝተዋቸው ተመልሰው እኛ ከመድረሳችን ጥቂት ቀናት ቀደም ብለው በካርቱም በኩል ወደ ጎሬ ማለፋቸውን ሰማን። በልሁ ደገፉ ጃንሆይን እንግሊዝ አገር አድርሰው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ለጠላት ለመግባት ሳይሆን፥ ጠላትን ለመውጋት ነበር። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን መያዛቸውን ካስታወቁ በሁዋላ አገራቸውን እየለቀቁ ከወጡት ኢትዮጵያውያን መሀከል፥ በባእድ አገር ስደተኞች ሆኖ ከመኖር ቢከፋም የኢትዮጵያ ድል መመታት ያስከተለውን ጠላት ሁለተኛ ደረጃ ዜግነት እንደ ህዝቡ ሁሉ ተቀብሎ አገር ውስጥ መኖርን መርጠው እንደገና እዬተመለሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ብዙ መሆናቸውን ሰምቻለሁ። ነገር ግን በባእድ አገር ተሰዶ መኖርንም ባገር ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ሆኖ መኖርንም ተፀይፈው «ለነፃነቴ ወይ ለሞቴ! » ብለው ጠላትን እስከ መጨረሻው ለመዋጋት አብረዋቸው ከወጡት ተለይተው በዚያ ብቻ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ፥ እኔ እስከማውቀው ድረስ በልሁ ደገፉ ብቻ ነበሩ!

ከቀኛዝማች በሁል በሁዋላ ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይም እንደ ቀኛዝማች በልሁ ከእንግሊዝ አገር ተመልሰው ለጦርነት ወደ ጎሬ መጥተው ከራስ እምሩ ጦር ሰራዊት ጋር ተጨምረዋል።

ከቡር ራስ እምሩ ገዝቼ እንድወስድላቸው የፈለጉትን የእቃ ዝርዝር ከልጅ ሲራክ ከተቀበልሁ በሁዋላ ከነበረን ገንዘብ ጋር እያነፃፀርሁ ስመለከተው ምንም እንኳዋ ያገሩን ዋጋ ባላውቅ እቃው ስለበዛ ገንዘቡ የማይበቃ መስሎ ታዬኝ። ራስ እንድገዛ የፈለጉት ለወታደር ድንኳዋን የሚሆን ብዙ ጣቃ ካኪ፥

ለቁስልና ለሌሎች ተራ ለሆኑ በሽታዎች የሚሆን ልዩ ልዩ መድሀኒት ለስንቅ የሚሆን ደረቃ ደረቅና በቆርቆሮ የታሸገ ልዩ ልዩ ምግብ እንዲሁም ብዙ ጥቃቅን ነገሮች ነበሩ። የእቃውን ዝርዝርና በባንክ የነበረን ገንዘብ 33.000 የሱዳን ብር መሆኑን ላቶ መንግስቱ ናይዝጊ አስታውቄ አሳባቸውን ብጠይቃቸው እሳቸውም እንደ እኔ ተጠራጠሩና የተፈለጉት እቃዎች ከሚገኙባቸው እሳቸውም እንደ እኔ ተጠራጠሩና የተፈለጉት እቃዎች ከሚገኙባቸው መደብሮች ጠይቀን ጠቅላላ ግምት ብናገኝ የሚሻል መሆኑን ስለ ነገሩኝ ዞረን ጠይቀን ውድ ሆነብን። ከዚያ ወደ አቶ መንግስቱ ቤት ተመልሰን ምን ማድረግ እንደ ሚሻለን ስንወያይ «እንዲህ እንዲህ ያሉትን እቃዎች ለመንግስት ወታደሮችና ድርጅቶች የሚሸጡ ኩባንያዎች እንድንገዛ ፈቃድ የምናገኝ ቢሆን ኖሮ በቀላል ዋጋ ለመግዛት እንችል ነበር » አሉኝ።

«ማን ይፈቅድልናል? » አልሁዋቸው።

«እሱ ነው ችግሩ ዋናው አገረ - ገዥ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደዋል። በምትካቸው የሳቸውን ስራ የሚሰሩ ዋናው ፀሀፊ (ሲቪል ሴክሬታሪ) ናቸው። ታዲያ ዋናው ፀሀፊ ‹ለመንግስት አገልግሎት የማይውል እቃ ለመንግስት በተተመነ ዋጋ ለናንተ እንዲሸጡ ኩባንዮችን ማዘዝ አልችልም፥ ከስልጣኔ በላይ ነው› ሳይሉን የሚቀሩ አይመስለኝም« አሉ አቶ መንግስቱ።

«ዛሬ እኛ በምንገናኝበት ሁኔታ ለሚገኙ ሁሉ ልዩ አስተያየት ተደርጎ ፈቃድ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች ይኖሩ ይሆናልኮ። ታዲያ እንዲህ ያሉ ምክንያቶች ይኖሩ እንደ ሆነ ሊነግሩን ከሚችሉ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እርስዎ የሚያውቁዋቸው የሉም? ቢኖሩኮ ፈቃድ ማግኘት የሚቻል መሆን አለመሆኑንና የሚቻል እንደሆነም የሚኢያስችሉትን ምክንያቶች ቢገልፁልን ይጠቅመን ነበር » አልሁዋቸው።

«እንጃ! እንዲህ እንዲህ ያለውን የውስጥ ምስጢር ከሚያውቁት ሰዎች እንኩዋ የማውቀው ያለ አይመስለኝም፤ ግን ዋናው ፀሀፊ ተቀብለው እንዲያነጋግሩ ሊያደርጉ ከሚችሉ ሰዎች ጋር የሚተዋወቁ ወዳጆች አላጣም። ስለዚህ ለነሱ ልንገራቸውና ዋናው ፀሀፊ ተቀብለው የሚያነጋግሩህ ከሆነ

ችግርህን ነግረህ የምትፈልጋቸውን እቃዎች ለመንግስት በተተመነ ዋጋ ከሚሸጡ ኩባንያዎች ለመግዛት ፈቃድ እንዲሰጡህ ጠይቃቸው። ቢፈቅዱልህ እሰዬ ነው! ባይፈቅድልህ መቸም ገንዘብህ ሊገዛ የሚችለውን ያክል ገዝተህ እንዳትሄ የሚከለክልህ የለ! ምን ይቀርብሀል? ስለዚህ እስቲ እንድትገናኝ ለማድረግ እንሞክር » አሉ አቶ መንግስቱ። ከዚያ እኔም ባሳባቸው ተስማምቼ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቀጠሮ ተደርጐልኛል ከ ‹ሲቪል ሴክሬታሪው› ጋር ተገናኘሁ።

ሲቪል ሴክሬታሪው ደስ በሚያሰኝ ፈገግታ ሰላምታ ሰጥተው ካስቀመጡኝ በሁዋላ በኢትዮጵያ ላይ ፋሺስቶች ባደረጉት የግፍ ወረራ እሳቸውም መንግስታቸውም እጅግ ያዘኑ መሆናቸውን ገልፀው፥ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውጋት ገና የጦር ሰራዊትና መሳሪያ ወደ ኤርትራና ወደ ሱማሊያ በማጋዝ ላይ እንዳሉም ጦርነቱን ከጀመሩ በሁዋላም የእንግሊዝ መንግስት ካንዳንድ መንግስቶች ጋር የግልግል አሳብ አቅርበው ጦርነቱ እንዲቀርና ነገሩ በእርቅ እንዲያልቅ ብርቱ ጥረት አድርገው ሙሶሊኒ «አሻፈረኝ! » በማለቱ የቀረ መሆኑን ነገሩኝ።

«ኢትዮጵያ የአለም ማህበር አባል በመሆንዋ ነፃነትዋ እንደሚጠበቅላትና ከአባሎቹ አንዱ ቢያጠቃት ማህበሩ አጥቂውን እንደሚቀጣላት ሙሉ እምነት ነበራት። ስለዚህ፥ እምነትዋን በማህበሩ ላይ ጥሳ ሳትጠነቀቅ በተቀመጠችበት ሙሶሊኒ የጦር ሰራዊቱንና መሳሪያውን በገፍ ወደ ኤርትሪያና ወደ ሱማሊያ ማጋዝ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በያቅጣጫው እስከ ወሰናችን መገናኛ መንገዶች ሰርቶና በወሰናችን ዳር ለዳር ምሽጎችን አጠንክሮ መሽጎ ስለ ወጋን የሰሜን የመሀልና የምስራቅ ኢትዮጵያ ከተሞች መያዝ ችሎዋል። ነገር ግን የነዚህ ክፍሎች መሀል አገር አሁንም በኢትዮጵያ አርበኞች እጅ ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ በምእራብና በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ አገረ ገዥዎች ከነጦር ሰራዊታቸው በያገራቸው እንዳሉ ጦርነትቱን ለመቀጠል በመሰናዳት ላይ ናቸው። ስለዚህ ጣሊያኖች የሰሜን የመሀልና የምስራቅ ኢትዮጵያ ከተሞች በመያዛቸው ጦርነቱ አያልቅም ገና ይቀጥላል። የምእራብ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ጣሊያኖች ባይሮፕላን መዋጋት የማይችሉበት ጫካ ብቻ ስለሆነ

በመጨረሻ አድራጊዎች እኛ እንደምንሆን አንጠራጠርም! » አልሁዋቸው አላዋቂነቴን በሚገልፅ የምነትና የድፍረት አነጋገር።

«የኢትዮጵያውያን ጦረኝነትና ጀግንነት በአለም ሁሉ የታወቀላቸው ነው። ለዚህ በአፍሪቃ ካሉት አገሮች ሁሉ እነሱ ብቻ ነፃነታቸውን ለብዙ ሺህ ዘመን አስከብረው መኖራቸው አንድ አይነተኛ ምስክር ነው። ግን በታሪክ እንደሚታየው ኢትዮጵያውያን ከውጭ ጠላት ጋር ጦርነት ባደረጉበት ቦታና ቤት ሁሉ የልዩ ልዩ አገረ ገዥዎችን ጦር ሰራዊት ባንድነት እያስተባበሩ መርተው በድል አድራጊነት የሚወጡ ነገስታት ነበሩ። ነገስታቱ ከሌሉ አገረ ገዥዎች እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ እንጂ ተባብረው የጋራ ጠላታቸውን አይወጉም ሲባል እንሰማለን። እንዲሁም ንጉሱ አስተባብረው የሚመሩት የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ንጉሱ እጦርነት ውስጥ ቢወድቁ ይበታተናል፤ እንጂ ተባብሮ ጠላት መመከት አያውቅም ሲባል እንሰማለን። ለምሳሌ፥ እዚህ አገር ባፄ ዮሀንስ እየተመራ በመጣው የኢትዮጵያ ሰራዊትና በ «መሀዲስቶች » የመራ በነበረው የሱዳን ሰራዊት መሀከል በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያውያን አይለው ሱዳኖች የተሰለፉበትን መስመር እዬለቀቁ መሸሽ ከጀመሩ በሁዋላ ድንገት መሪው ዐፄ ዮሀንስ ተመተው በመውደቃቸው የኢትዮጵያ ጦር ፈርሶ መጨረሻ ድሉ ማህዲስቶች እንደሆነ አንዳንድ የዚህ አገር ሽማግሌዎች ጭምር ይተርካሉ። ታዲያ አሁን የሁሉም አስተባባሪ የነበሩት ንጉሱ አገራቸውን ለቀው በወጡበት ከአገረ ገዥዎች ያላስተባባሪ ተባብረው በዘመናዊ የጦር ትምህርት ከሰለጠነ የጦር ሰራዊትና ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ካለው ሀይለኛ ጠላት ጋር ጦርነቱን መቀጠል እንዴት ይችላሉ? በኔ አስተያየት ከንግዲህ ወዲያ ጦርነቱን መቀጠል የሚፈልግ ሰው ከንቱ ከመንገላታትና ምናልባትም ከመሞት በቀር ድል የማድረግ ተስፋ ያለው አይመስለኝም። ከንግዲህ ወዲያስ አርፎ የተመቸ ጊዜ መጠበቅ ነው የሚሻለው » አሉኝ።

«ጃንሆይ ከአለም ማህበር ርዳታ ለመጠየቅ እንጂ አንድያቸውን አገራቸውን ለቀው አለመሄዳቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴራችን ዋና ፀሀፊ ሲራክ ህሩይ ወደ እንግሊዝ አገር ሲሄድ በቀደም እዚህ ተገናኝተን ነግሮኛል። ግን አንድያቸውን ቢሄዱ እንኩዋ ያገራችንን ሸለቆና ጫካ ይዘው ስላልሄዱ

ያገራአችን ሽለቆና ጫካ ብዙ አመታት በውስጣቸው አቅፈው ሸሽተው ከጠላታችን ተዋግተን ለመጨረሻ ድል እንድንበቃ ያደርጉናል! » አልሁዋቸው ከሞቅታ ጋር ‹ድል የማድረግ ተስፋ የላችሁም› ሲሉም ድንገት ስሜቴ ስለታወከ ፊቴ ግሎና አይኖቼ እንባ ሞልተው።

ሲቪል ሴክሬታሪው በየዋህነቴ አዝነውልኝ ይሁ ወይም፥ ታዝበውኝ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ዝም ብለው ሲመለከቱኝ ቆይተው፤ «እሺ እንግዲህ፤ እግዚአብሔር ይርዳችሁ! ታዲያ አሁን እኔ ምን እንድረዳህ ነው ልታየኝ የፈለግህ? » አሉኝ።

«በሽሬ ግንባር የተዋጋው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት አዛዥ፥ ራስ እምሩ ጦርነቱን ለመቀጠል ወስነው ሰራዊታቸውን እንደ ያዙ ወደ ምእራብ ኢትዮጵያ ሲሄዱ፥ እኔ ወታደር ልብስ፥ ስንቅና መድሀኒት ከዚህ ገዝቼ እንድወስድላቸው ነበር ታዝዤ የመጣሁ። አሁን ተገዝቶ እንዲሄድላቸው የሚፈልጉትን የእቃ ዝርዝር ሲራክ ህሩይ አምጥቶ ሰጥቶኝ ከተመለከትሁ በሁዋላ የገበያውን ዋጋ ዞሬ ብጠይቅ፤ ከሰጡኝ ገንዘብ በላይ ሆኖ አገኘሁት። ስለዚህ እርስዎን ልለምን የመጣሁ፥ ገንዘብ በላይ ሆኖ አገኘሁት። ስለዚህ እርሶን ልለምን የመጣሁ፥ ለመንግስት የጦርና የሰላም ድርጅቶች የሚያስፈልጉትን እቃዎች የሚሸጡ ኩባንያዎች ለመንግስት በተተመነው ዋጋ ለመግዛት ፈቃድ እንዲሰጠኝ ነው ጌታዬ » አልሁ።

«ንጉሳችሁኮ ራስ እምሩ ከቤተሰባቸውና ከቅርብ ረዳቶቻቸው ጋር፥ በኢትዮጵያ አቅራቢያ የእንግሊዝ መንግስት ከሚያስተዳድራቸው አገሮች ወዳንዱ ገብተው ለመኖር እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው፥ «ዩጋንዳ » ገብተው እንዲኖሩ ስለታሰበ፥ የዩጋንዳ አገረ - ገዥ ተጠይቀው፥ የሳቸው መልስ ነው የሚጠበቀው። ታዲያ ራስ እምሩ ወደ ዩጋንዳ የሚሄዱ ከሆነ እቃውን መግዛት ለምን ያስፈልጋል? » አሉኝ።

«ጃንሆይ መቸ ነው ለራስ እምሩ የእንግሊዝ መንግስት ከሚያስተዳድራቸው አገሮች ወዳንዱ ገብተው እንዲኖሩ ፈቃድ የጠዩቀላቸው? »

«ቆይተዋል። የዩጋንዳ አገረ - ገዥ ከተጠየቁ እንኳዋ ካንድ ወር በላይ ሳይሆን የጻፉልኝ ወረቀትትና የእቃዎችን ዝርዝር ሲራክ ህሩይ አምጥቶ የሰጠኝ በዚህ ሳምንት ውስጥ ነውኮ! ስለዚህ ለኔ እንደሚመስለኝ፥ ጃንሆይ ለራስ እምሩ መኖሪያ የእንግሊዝን መንግስት ፈቃድ የጠዬቁ የሳችውን ውሳኔና ፈቃድ ሳያውቁ በራሳቸው ፈቃድ ሳይሆን አይቀርም። ይህን የምልበት ምክንያት ራስ ጎሬ ከደረሱ ጀምሮ ከምእራብና ከደብቡ ምእራብ ኢትዮጵያ አገረ - ገዥዎች ጋር ተላልከው ጦርነቱን ከህብረት ለመቀጠል የተስማሙ መሆናቸውን አሁን የእቃዎችን ዝርዝርና ለኔ የተፃፈውን ትእዛዝ ከሳቸው ያመጣልኝ፥ ሲራክ ህሩይ ስለ ነገረኝ ነው » አልሁዋቸው።

«እንዳልኸው ሊሆን ይችላል » አሉና ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው፤

«መግዛት የምትፈልጋቸውን እቃዎች ዝርዝር አሁን ይዘሀል? » አሉኝ።

«አዎን ጌታየ » ብዬ በእንግሊዝኛ የተፃፈውን የእቃዎች ዝርዝር ከኪሴ አውጥቼ ሰጥቻቸው ከተመለከቱት በሁዋላ አጥፈው እፊታቸው በጠረጴዛው ላይ አስቀመጡና፤ «ስለዚህ ፈቃድ መስጠቱ እንኩዋ አያስቸግርም፥ ቀላል ነው። ለዚህ ፈቃድ መስጠቱን በሌላ ባይሆን ለህሊና ከባድ የሚያደርገው በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሰለጠነና ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ ሰራዊት ካለው ሀይለኛ ጠላት ጋር ባዶ እጃችሁን ያለ መሪ ጦርነቱን ቀጥላችሁ እንድታልቁ እንደ መገፋፋትና እንደ መደፋፈር የሚቆጠር መሆኑ ነው! የፋሽስቶችን ሀይል እናንተ አታውቁትም። ፋሽስቶች ወጣቶቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምረው በዳቦ ፋንታ የጦር ትምህርት መግቢው እያሳደጉ፥ ጠቅላላ ህዝባቸውን በሀብት ፋንታ የጦር መሳሪያ እስኪከብደው አሸክመው እያኖሩ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ‹አለምን እንደ ሮማውያን አባቶቻችን እንገዛለን› ብለው የተነሱ እብሪተኞችና ሀይለኞች ናቸው። ስለዚህ በኔ አስተያየት የኢትዮጵያ ጀግኖች በተለይ እንደናንተ ያላችሁ በኔ አስተያየት የኢትዮጵያ ጀግኖች በተላይ እንደናንተ ያላችሁ ወጣቶች እንዲህ ባለው ጎደለ ጊዜ፥ ያላቀማችሁ ከሀይኛ ጠላት ጋር ጦርነቱን ቀጥላችሁ ከምታልቁ የተመቸ ጊዜ ሲያጋጥም አገራችሁ የሰው ድሀ ሆና የሚያገለግሉዋት ልጆች እንዳታጣ፥

የምትችሉት ሁሉ ይህን ጎደሎ ጊዜ ዘወር እያላችሁ ብታሳልፉት የሚሻል ይመስለኛል። ለምሳሌ አንተ እንግሊዝኛ እንደምትናገረው የምትፅፍ ከሆንህ፥ እዚህምን ቢሆን ስራ እዬሰራህ ልትቆይ ትችላለህ » አሉኝ።

ሲቪል ሴክሬታሪው እንዲያ ያለ ተስፋ የሚያስቆርጥና የሚያደክም ነገር ሲነግሩኝ፥ ምናልባት እኒህ ሰው ፈረንጅ በመሆናቸው ወገኖቻቸውን ጣሊያኖችን ለመርዳት ይሆን? ወይስ የጣሊያኖች ሀይል የማይበገር፥ እጅግ ብርቱ ስለሆነ እነሱን ለመቋዋቋዋም መምከር ከማለቅ በቀር ምንም ትርፍ የሌለው መሆኑን ላገኙዋቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲሰብኩ ተገዝተው ይሆን? የማለት ጥርጣሬ አድሮብኝ ነበር። ነገር ግን በረዥሙ ከተነጋገርን በሁዋላ ያላንዳች ማመንታት የጠዬቅሁት ፈቃድ እንዲሰጠኝ ሲያደርጉ ለምክር ብለው የተናገሩትን በክፉ ተርጉሜ ስለ ጠረጠርሁዋቸው ህሊናየ ወቀሰኝ።

«እኔ በሽሬ ግንባር ለተደረገው ጦርነት ተካፋይ ስለ ነበርሁ፥ የፋሽቶች ሀይል ምን እንደ ሆነ አውቀዋለሁ ጌታየ። የኢትዮጵያ መንግስት ለአለም ማህበር አባል በመሆኑ በማህበሩ ተማምኖ በሚገባ ስላልተሰናዳ ፋሽስቶች በዚያ ተጠቅመው ከያቅጣጫው መንገዶቻቸውን እስከ ወሰናችን ሰርተው በወሰናችን ዳር ለዳር ምቹ ቦታዎች እያዩ ምሽጎቻቸውን አጠንክረው መሽገው ጦርነቱ የተደረገው ወታደርና መሳሪያ ሲያልቅባቸው ከሁዋላ ቶሎ በሚተኩባቸው ምሽጎቻቸው ላይ ነበር። እንዲያም ሆኖ ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ምሽግ ሰብረው ወይም አልፈው እኒያን ‹ከልጅነታቸው ጀምረው በዘመናዊ የጦር ትምርት የሰለጠኑ ፋሽስቶች› የጨበጣ ጦርነት ሲጋጠሙዋቸው ሬሳቸውን ቁስለኞቻቸውንና መሳሪያቸውን ጥለው ይሸሹ ነበር! ሁዋላ ብቻ አይሮፕላኖቻቸውን አምጥተው ኢትዮጵያውያን የተሰለፉበትን ቦታን ከሁዋላ ሲደበድቡ ኢትዮጵያውያን የያዙዋቸውን ምሽጎች ትተው ይሸሹና ፋሽስቶች ከተጨማሪ ሀይል ጋር ለቀዋቸው ወደ ነበሩት ምሽጎቻቸው ይመለሳሉ። በዚህ አሆሁዋን ነው እስካሁን የሰሜን፥ የመሀልና የምስራቅ የኢትዮጵያን ከተሞች ለመያዝ የቻሉ። ወደ ፊት ጦርነቱን ለመቀጠል የታሰበበት ኢትዮጵያ ምእራብና ደቡብ ምእራብ ግን ፋሽስቶች መንገድና ምሽግ ያልስሩበት አይሮፕላኖቻቸው አላማቸውን ተመልክተው ሊመቱ

የማይችሉበት ጫካ ነው። ስለዚህ እዚያ ምሽግና አይሮፕላን በሌሉበት የፋሽስትና የኢትዮጵያ ወታደሮች ብቻ ለብቻ በሚገጥሙበት ጦርነት እኔ ባዩሁት መጠን ድሉ የኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም! » አልሁዋቸው፤ ከሞላ ጎደል ፉከራ በመለስ አነጋገር።

«እሺ እንግዲህ ቅድም እንዳልሁህ የጠዬቅሽውን ፈቃድ መሰጠቱ አያስቸግርም » ብለው የገንዘብ ክፍሉን ሹም (ፋይናሻልክ ሴክሬታሪ) በስልክ ጠርተዋቸው መጥተው ከተነጋገሩ በሁዋልካ ፈቃዱ አሁን ይሰጥሀል አሉኝ። ከዚያ ፋይናንሻል ሴክሬታሪው » ሊሄዱ ሲነሱ፥

«ይህ ወጣት ያለኝን ልንገርዎ! » አሉዋቸው ሲቪል ሴክሬታሪው።

«ምን አለ? »

«ንጉሳችሁ አገር ለቀው ወጥተዋል። ያለ መሪ ከሀይለኛ ጠላት ጋር ጦርነት መቀጠል እንዴት ይሆንላቸዋል? » ብለው «ንጉሱ ያገራችንን ሽለቆዎችና ጫካዎች ይዘው አልሄዱም፤ ሽለቆዎቻችንና ጫካዎቻችን ለጠላት አጋልጠው አይሰጡንም በጉያቸው አቅፈው ለመጨረሻ ድል ያበቁናል » አለኝ አሉዋቸው አኔ ባልሁት ላይም ጨማምረው።

«እውነቱ ነው አገር ካቀፈ በዘመናዊ መሳሪያ የሚዋጋን ጠላት ባርበኝነት ከመከላከል የተሻለ መንገድ የለም » አሉና ፋይናንሻል ሴክሬታሪው «ፈቃዱን አሁን ታገኛለህ እማረፊያ ቤት ቆይ » ብለውኝ ወጡ። እኔም ሲቪል ሴክሬታሪውን አመስግኘ አቶ መንግስቱ ማረፊያ ቤት ተቀምጠው ይጠብቁኝ ስለ ነበረ ወደሳቸው ሄጄ ፈቃዱን ማግኘቴንም ከሲቪል ሴክሬታሪው ጋር የተነጋገርነውንም ባጭሩ ስነገራቸው ደስ አላቸው። ከዚያ ምንም ያክል ሳንጠብቅ ፈቃድ ወጥቶ ስለ ተላከልን ወዳቶ መንግስቱ ቤት ተመለስን።

## ምዕራፍ አስራ አራት

# ከካርቱም እስከ ጎሬ

የሲቪል ሴክሬተሪውን ፈቃድ ካገኘን በሁዋላ የፈለግናቸውን እቃዎች ለመግዛት እንኩዋንስ ገንዘብ ሊያጥረን እንዲያውም መጠነኛ ገንዘብ ተረፈን። እቃዎችን እንዲሸጡ ከተፈቀደላቸው መደብሮች የመግዛቱንም ከተገዙ በሁዋላ አሳስሮ በመርከብ የማስጫኑንም ስራ እኛ ምንም ሳንቸገር እንዲከናወን ካደረጉልን ሰዎች ዋናዎቹ አቶ መንግስቱ ናይዝጊ አቶ ሀብቴ ደስታና አቶ ዮሀንስ አንዶም ያቶ መለስ አንዶም፥ ወይዘሮ ጽዮን አንዶምና የጄነራል አማን አንዶም ወንድም ነበሩ። ሌሎችም «ምን እንርዳ? » የሚሉ ብዙ ነበሩ።

መቸም ያንድ አገር ሰዎች ባገራቸው ሙሉ ስምምነት ያልነበራቸው ቢሆኑ እንኩዋ በባእድ አገር ሲገናኙ በመሀከላቸው የነበረውን አለመስማማት ረስተው ለመቀራረብና ለመረዳዳት እንደሚፈልጉ የታወቀ ነው። ስለዚህ ሱዳን ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን፥ ዘሪሁንና እኔ የነሱም የኛም፤ የጋራ ጠላት ከሆነው የፋሽስት ጦር ሠራዊት ጋር ስንዋጋ ቆይተን ወደ ሱዳን ስንሄድ ያደርጉልን እንክባካቤና እኛን ደስ ለማሰኘት ያደርጉት የነበረው ርብራቦ ሁሉ አያስገርም ይሆናል። የሚያስገርመው የሱዳኖች ነው። ሱዳኖች አቶ ሳሊም ሱቅ ሲጫወቱ ከሚያመሹት ጀምሮ በሌላ ቦታም ዘሪሁንንና እኔን ከሚያገኙን መሀከል የሚበዙት ከጦርነት መመለሳችንን ሲሰሙ ልክ እንደ ዘመዶቻቸው «እንኩዋን ደህና መጣችሁ! » እያሉ እስኪጨንቀን እያቀፉ ይስሙን ነበር። ዘሪሁንና እኔ፥ ሱዳን በነበርንበት ጊዜ አገሩ የእንግሊዝና የግብፅ «የጋራ ግዛት » (ኮንዶሚኒየም) ነበር። ብቻ ለስሙ «የጋራ ግዛት » ይባል እንጂ እኛ ባዩነው መጠን የሰላሙንም የጦሩንም አስተዳደር የሚመሩት ሹማምንት እንግሊዞች ብቻ ነበሩ። ስለዚህ ሱዳኖች በገዛ አገር በባእድ መገዛት ምን ያክል የውርደት ውርድት ምን ያክል ስለደረሰብን ስለሚያውቁ ያ! የሚያውቁት ውርደትና ስቃይ በኛም ስለደረሰብን የውርደትና የስቃይ ጉዋደኞቻቸው የውርደትና የስቃይ ወገኖቻቸው በመሆናችን ይሆናል እንደ ዘመዶቻቸው ይመለከቱን የነበር። እኛም እንዲያ ሲያዝኑልንና ያገራችን ነፃነት በመጥፋቱ ሲቆረቆሩ ስናይ ጠላቶቻችነን ፋሽስቶችንም ከኛ ጋር ሲረግሙ ስንሰማ እንደ ወገኖቻችን እንጂ እንደ ባእዶች አናያቸውም ነበር። ስለዚህ ዘሪሁንና እኔ

ሱዳንን ለቀን ወዳገራችን ለመመለስ ከካርቱም ስንነካ አገራቸውን ትተው ከወገኖቻቸው ተለይተው እንደሚሄዱ ሰዎች ነበር ቅርታ የተሰማን።

መስከረም 1929 እንደ ገባ፥ ዘሪሁንና እኔ በመርከብ ተሳፍረን ወዳ ወዳገራችን ለመመለስ ተነሳን። ጥቂት ወዳጆቻችን አጅበውን እመሳፈሪያው ቦታ ስንደርስ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያን ዞረን የተሰናበትናቸው ወይዛዝርና ሽማግሎች እንኩዋ ሳይቀሩ ቀድመው እዚያ ሲጠብቁን አገኘናቸው። በዚያ አጭር ጊዜ ያፈራናቸው አንዳንድ የሱዳን ወዳጆቻችንም ነበሩ። ከዚያ እቃችን ቀደም ብሎ ተሳፍሮ ስለ ነበረ እኒያን ካርቱም በቆዬንበት ጊዜ እንዲያ ግሩም አድርገው ያስተናገዱንንና የረዱነን ወገኖቻችነን ሁሉ አመስግነንና ተሰነባብተን፤ «በነጭ አባይ » ላይ የመርከብ ጉዞዋችነን ጀመርን።

መርከብዋ ትልቅ ካለ መሆንዋም ሌላ ቁልቁል የሚወርደውን ውሃ እዬተጋፋች ሽቅብ ትሄድ ስለ ነበረ ፍጥነት አልነበራትም ቀስ ብላ ነበር የምትጉዋዝ። ከካርቱም ተነስተን «ማላካል » አጠገብ የ «ባሮ » ወንዝ ከነጭ አባይ ጋር በሚገናኙበት እስክንደርስ ስንት ቀን እንደ ተጉዋዝን አላስታውሰውም ረስቸዋለሁ። ነገር ግን ከካርቱም እስከ ጋምቤላ የተጉዋዝነው በጠቅላላ፤ አስራ ሶስት ቀንና አስራ ሶስት ሌሊት እንደ ሆነ ትዝ ይለኛል። ግን ከዚህ፥ የባሮ መርከብ ደርሳ፥ እቃሽን ከነጭ አባይ መርከብ ወደ ስዋ እስኪዛወር ማላካል ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት ስለ ቆዬን ያ ሲቀነስ፥ በጠቅላላው በመርከብ የተጉዋዝነው አስራ አንድ ቀንና አስራ አንድ ሌሊት ነበር ማለት ነው።

ማላካል ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት ስንቆይ አንድ የሱዳን ሴት አግብቶ በሚኖር አቶ «በየነ አስፋው » በተባለ ኢትዮጵያ ቤት ነበር ያረፍን። አቶ በየነ በመርከብ የሚሳፈሩትንና ከመርከብ የሚወርዱትን ሁሉ የሚያስተናብር የመንግስት ሰራተኛ ስለ ነበረ እቃችነን ከነጭ አባይ መርከብ ወደ ባሮ መርከብ ለማዛወር አንዳች ችግር አልገጠመንም ዘሪሁንና እኔ እየተቆጣጠርን የማዛወሩን ስራ እሱ ነበር ያሰራልን። እኒያ ደጋግ ባልና ምሽት እቤታቸው በቆዬንበት ጊዜ መጠነኛ ኑሮዋቸው በፈቀደላቸው መጠን እኛን ደስ ለማሰኘት ያደርጉት የነበረው መጣጣርና መቸጋገር ልረሳው የማልችል፤ ሁልጊዜ ትዝ

ሲለኝ የሚኖር ነው። የባልና ምሽቱ ቤት አንድ የነሱ ምኝታ ክፍልና አንድ እንደ እንግዳ መቀበያም እንደ መብል ቤትም ሆኖ የሚያገለግል በድምሩ ሁለት ክፍሎች ብቻ የነበሩት ነበር። የመብልና የመጠጥ ችግር ያልነበረ ከመሆኑ በላይ ሁለቱም ከማባበላቸውና ከማቆላመጣቸው ብዛት የተነሳ ዘሪሁንና እኔ «በይሉኝታ » ከጥጋብ በላይ እዬበላንና እዬጠጣን እንቸገር ነበር። በመኝታ ጊዜ ባልና ምሽት የምኝታ ክፍላቸውን ለኔ ለቀው እነሱ ከዘሪሁን ጋር «እንግዳ መቀመያው ክፍል እንተኛለን » ስላሉ ዘሪሁንና እኔ እንግዳውም ያ ካልሆነ ግን እውጭ እምኝታ ክፍላቸው እንድንተኛ ብለምናቸውም ያ ካልሆነ ግን እውጭ እተኛ እንደሆን እንጂ እነሱን አስለቅቄ እምኝታ ቤታቸው እንደማልተኛ ባስፈራራቸውም «ጭራሽ አናደረገውም! » አሉኝ።

«ላንተ ብቻ ሳይሆን የተከበረ እንግዳ ስንቀበል ሁልጊዜ የምናደርገው ነው » አለ አቶ በየነ። ታዲያ በርከት ያለ እቃ በመርከብ አስጭነን መጉዋዝችን ልንከበር የሚገባን ሀብታሞች አስመስሎ አሳይቶን እንደሆነ እንጂ ዘሪሁንና እኔ በድሜያችንም ሆነ በሌላ ሁኔታችን አንዳች የሚያስከብር ምልክት የሚታይብን አልነበርንም። የሆነ ሆኖ አቶ በየነንና ባልተቤቱን ለምኘም አስፈራርቼም ውሳኔያቸውን ማስለወጥ ስላልቻልሁ እየከበደኝ መስተንግዶዋቸውን ተቀብዬ፤ ማላካልን እስክንለቅ ድረስ እምኝታ ቤታቸው ስተኛ እንድቆይ ተገደድሁ።

የባሮ መርከብ ከነጭ አባይ መርከብ እንኩዋ በጣም ያነሰች ነበረች። የባሮ ወንዝም ከነጭ አባይ ወንዝ በጣም ያንሳል። ሰዎች እንደ ነገሩኝ በዋናው በጋ የባሮ ውሀ ሲጎድል ያችን ትንሽ መርከብ እንኩዋ ማስሄድ ስለማይችል መርከብዋ አገልግሎትዋን አቁዋርጣ የምትቆይበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ቦታ ወንዙ ከመጥበቡ የተነሳ መርከብዋ የግራና ቀኝ ግንዶችን ለመንካት ምንም ያክል አይቀራት። ስለዚህ ጠባቡን ቦታ እስኪታልፍ ቀስ ብላ እየተጠነቀቀች ነበር የምትጉዋዝ።

መርከብዋ የባሮን ወንዝ ተከትለው አልፎ አልፎ ከሚገኙት መንደሮች አጠገብ ስትደርስ የሚወርዱ መንገደኞች ቢኖሩ ለማውረድና የሚሳፈሩ ቢኖሩ ለማሳፈር ስትቆም፤ የመንደሩ ነዋሪዎች ሴቶች የሚበዙት፤ የሚወርዱትንና የሚሳፈሩትን መንገደኞች ለማየት ብቻ ሳይሆን ገብያ ለመገብየት ጭምር

የሚመጡ ናቸው። ከመስከረም ጀምሮ ወራቱ የሸት ስለሆነ የተጠበሰም የተቀቀለም በቀሎ አምጥተው ለመንገደኞች ይሰጡና በለውጡ ስንቁ ያለቀለት ቆርቆሮ ጠርሙስ ወይም ሌላ እቃ ይቀበላሉ።

የባሮን ወንዝ ተከትለው እስከ ጋምቤላ በሚገኙት መንደሮች የሚኖሩት ነዋሪዎች ያንጊዜ እንዳየሁዋቸው ልብስ አልለበሱም፤ ራቁታችውን ነበሩ። ሴቶች ብቻ ከወገባቸው እስከ ጭናቸው አጋማሽ ድረስ ትንሽ ጨርቅ ያገለድማሉ። ወንዶች ግን እንዲሁ፥ እግዜር እንድ እፈጠራቸው ርቃናቸውን ናቸው። እንዲያውም «ተመልካችን ይግረመው! » ብለው በሌሎች ባህሎች ሁሉ እንዳይታይ መሸሸግ ያለበትን የወንድነት አካል እነሱ የሰው አይን እንዲስብ ዙሪያውን ላጭተው አካባቢውንና ራስ ዋናውን በልዩ ልዩ ቀለም ሸልመው አስጊጠው ያሳዩታል ከዚህ ሌላ እኒያን በባሮ ወንዝ ዙሪያ የሚኖሩትን ጥቁሮች ሁሉ ከሌሎች የጥቁር ዘሮች ልዩ የሚያደርጋቸው የሚበዙት በቁመታቸው ሎጋዎች በፊት - መልካቸው ሸጋዎች መሆናቸው ነው።

ከካርቱም ተነስተው የመርከብ ጉዞዋችነን ከጨረስን በሁዋላ፥ ባስራ አራተኛው ቀን ይመስለኛል እጥዋቱ ላይ ጋምቤላ ደረስን። የጋምቤላ ከተማ በሁለት ተከፍላ የምስራቁ ክፍል በኢትዮጵያ ባለስልጣኖች የምእራቡ ክፍል በእንግሊዝ ባለስልጣኖች ነበር የሚተዳደሩ የመርከብዋ መቆሚያ እንግሊዞች በሚያስተዳድሩት ክፍል ስለ ነበረ አቶ «ተክለ ማርያም » የተባሉ የኢትዮጵያ ጉምሩክ አስተዳደር ሹም ከጭፍሮቻቸው ጋርና ለእንግሊዞች ክፍል አስተዳዳሪ የነበሩት እንግሊዛዊ ባለስልጣን ካንድ የንግሊዝ ሻለቃ ጋር እዚያ ድረስ መጥተው ተቀበሉን። ሻለቃው በጋምቤላ የንግሊዝን ጥቅም እንዲጠብቁና እዚያ ፀጥታ እንዲያስከብሩ ለተመደቡት ወታደሮች አዛዥ ነበሩ።

ካቶ ተክለ ማርያምና ከሰዎቻቸው ጋር ከተዋወቅን በሁዋላ እሳቸው ከእንግሊዝ ባለስልጣኖች ጋር አስተዋውቀውን እንግሊዞች ደስ በሚያሰኝ ፈገግታ «እንኩዋን ደህና መጣህ » እያሉ ሰላምታ ሰጥተውኝና በውዳጅነት መንፈስ ሲያነጋግሩኝ ቆይተው ተሰነባብተን ሲሄዱ እኔና ዘሪሁን እቃችን ወዳቶ ተክለ ማርያም መስሪያ ቤት ተግዞ እንዳለቀ ከናቶ ተክለ ማርያም ጋር ወደ

መስሪያ ቤታቸው ለመሄድ መንገድ ስንጀምር ራቅ ብሎ ቆሞ ሲጠባበቅ የቆዬ ሱዳናዊ ያስር አለቃ፤ ሶስት ወታደሮች አከትሎ መጥቶ፥

«ወደ ኢትዮጵያ ክፍል ከመሸገርህ በፊት ወደኛ መስሪያ ቤት ሄደህ ከእንግሊዛዊው አስተዳዳሪ ጋር መነጋገር አለብህ » አለኝ ለማስተዋል ያክል በሚበቃ እንግሊዝኛ።

«ካስተዳዳሪው ጋር አሁን እዚህ ስንነጋገር ቆይተን አሰናብተው ናልኮ » አልሁት።

«የለም ከመስሪያ ቤታችን ድረስ ሄደን ማነጋገር አለብህ! » አለኝ ወታደሮቹን ሲያዝ እንደሚያደርገው ፊቱን ኮስተር አድርጎ።

«ስራቱ እንዲህ ነው? » አልሁ፥ ወዳቶ ተክለ ማርያም ዘወር ብዬ።

«እስከ ዛሬስ እንዲህ ያለ ስራት አልነበረም፥ ግን አዲስ ስራት አውጥተው እንደ ሆነ ምን ይታወቃል? አስተዳዳሪው በቅርብ የመጥ፥ አዲስ ነው » አሉኝ አቶ ተክለ ማርያም።

«እስከ ዛሬ ተደርጎ የማያውቅ ነገር ዛሬ በኔ የሚጀመርበት ምክንያት ምንድነው? አልሄድም! » አልሁት ያስር አለቃውን እገፋበት ይመስል አይኔን አፍጥጬ።

«እንዲያው ወደ ኢትዮጵያ ክፍልም አትሂድ! ሁላችሁም አትሄዱ! » አለ ያስር አለቃ ከወታደሮቹ ጋር ቀድሞ መንገዳችነን ዘግቶ።

«እስቲ ግዴለም ለማናቸውም ነገር አብረን እንሂድ » አሉ አቶ ተክለ ማርያም።

«መሄድ ካልቀረስ፥ እኔ ልሂድና ችግር የተፈጠረ እንደሆነ እልከብዎታለሁ » ብያቸው ከዘሪሁን ጋር በወታደሮች ታጅበን ወደ እንግሊዞች መስሪያ ቤት ሄድን። እዚያ ስንደርስ ያስር አለቃው አጥሩን አስገብቶ ትቶን ወደ አስተዳዳሪው ገብቶ ምን እንደ ነገራቸው አላውቅም እንግሊዛዊ አስተዳዳሪ ካጭር ጊዜ በፊት ካየሁዋቸው ፍፁም ጭነን እንጋት

ላይ የሴሪቴን አቀበት ወጣን። አቀበቱን ስንወጣ፥ ሶስት ጥምድ «ባቱዎች » (ተሸካሚዎች) በተነጠፉ አልጋዎቻቸው ላይ መከዳዎቻቸውን አድርገው ሶስት፥ ፈረንጆችን ተሸክመው ሲወርዱ ተገናኘን። እኒያ ባልጋ ላይ ተኝተውም፤ ተቀምጠውም የሚጉዋዙ ፈረንጆች በሽተኞች እንደሆኑ ነጋዴዎችን ብንጠይቅ ሌሊት፥ በበቅሎ ወደ ጋምቤላ መውረድ ወይም ከጋምቤላ ቆላውን መውጣት የማይፈልጉ ፈረንጆችና አንዳንድ የተመቻቸው ኢትዮጵያውያን ቀን በባቱ መጉዋዛቸው የተለመደ መሆኑን ነገሩኝ።

ሴሪቴን ወጥተን «ቡሬ » ከምትባል ትንሽ ከተማ አጠገብ ስንደርስ ጎጃም አስተማሪ ሳለሁ አለቃየ ከነበሩት ካቶ (ሁዋላ ፊታውራሪ) ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ፥ ደብረ ማርቆስ የራዲዮ ጣቢያው ሹም ከነበሩት፥ ካቶ (ሁዋላ ደጃዝማች) ገብረ መስቀል ሀብተ ማርያም ከልጅ ሩት ካቶ (ሁዋላ ደጃዝማች) ገብረ መስቀል ሀብተ ማርያም ከልጅ (ሁዋላ ደጃዝማች) አሰጋኸኝ አራያና ካቶ ጉርሙ (ያባታቸውን ስም ረስቻለሁ) ጋር ተገናኘን። አቶ ጉርሙ ፈንሳይ አገር ስራ ይዘው ትዳር መስርተው ከሚኖሩበት ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ጥርነት ስታደርግ አገራቸውን ለማገልገል መጥተው ጦርነቱ በማለቁ ወደ ፈረንሳይ አገር መመለሳቸው ነበር። ሌሎች ተሰደው ወደ ሱዳን መሄዳቸው ነበር። ከናቶ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር እንደ ተገናኘን ነጋዴዎች ወደ ጎሬ ጉዞዋቸውን እንዲቀጥሉ አድርገን ዘሪሁንና እኔ ከስደተኞች ወገኖቻችን ጋር ትንሽ አርፈን ለመነጋገር ቡሬ ከተማ ገባን። እዚያ እናቶ ወልደ ጊዮርጊስ ጠጅ ገዝተው እየጠጣን እነሱ ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ እኔ ስለ ሸሬ ጦርነትና ከዚያ ከተመለስን በሁዋላ በሱዳን መንገዳችንም ሱዳን በቆየንበት ጊዜም ስላጋጠሙን መልካምና ክፉ አጋጣሚዎች ስናወራ ካሰንበው በላይ ቆዬን።

ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ ስደተኞች ወዳጆቼ ያወሩኝ ካርቱም ልጅ ሲራክ ህሩይ ካወራኝ ብሩህ ተስፋ የሚያሳይና የሚያበረታታ ወሬ ፍፁም የተለዩ ነበር። እነሱ እንደ ነገሩኝ ወለጋን ጅማን ከፋን ባሌን ሲዳሞንና ጎምጎፋን ጣሊያኖች ገና ያልያዙዋቸው መሆኑና ራስ እምሩ ከነዚህ አገሮች ገዥዎች ካንዳንዶቹ ጋር መላላካቸው እውነት ቢሆንም «ተባብሮ ጠላትን ለመቃወም በመሀከላቸው ስምምነት ተደርጎ » የተባለው እውነት አልነበረም። ያን ጊዜ

የተነጋገርንባቸው ቃላት (ካንዳንድ የረሳሁዋቸው በቀር) በሙሉ ትክክል ሊሆን ባይችሉም በጠቅላላው የንግግራችን መስመር እንደሚከተለው ነበር።

«እንኩዋንስ ከጠላት ተዋግቶ ነፃነታችንን የሚያስመልስ ባልተያዙት አገሮች ያለውን የጦር ሰራዊት ባንድ ላይ አስተባብሮ ለመምራት ስልጣኑን ሁሉም አምነው የሚቀበሉትና ጦርነቱን ዘለግ ላለ ጊዜ ለመቀጠል የሚችል መሪ የለም። እንዲያ ያለ መሪ ቢኖርማ እኛስ አገራችንን ትተን የምሰደድ ይመስልሀል? እስካሁን ባልተያዙት አገሮች ያሉት አገረ - ገዥዎች ተባብረው ጠላትን ለመቃወም ሲሉ አንዱ የሌላውን መሪነት ከመቀበል ይልቅ ጠላት ደርሶ ለየብቻቸው ተዋግተው ወይም ሳይዋጉ ስልጣናቸውን እስኪወስድባቸው ድረስ የበላይ ሳይኖርባቸው መቆየቱን የሚመርጡ ናቸው። እንዲያውም እንደ ሰማነው ወሬና እኛም በዚህ አካባቢ እንደ ተመለከትነው ያልተያዙት የምእራብና የደቡብ ምእራብ አገሮች ህዝብ ፊቱንም ጥላቻ ቢኖረው ይሁን ወይም «ለማያዘልቅ ነገር አገራችንን የጦር ሜዳ ያደርጉብናል » ብሎ በመፍራት ይሁን፥ ከጠላት ለመዋጋት የተሰለፉትን የኢትዮጵያ መንግስት ወገኖች ሁሉ እንኩዋንስ ሊረዳ ተቃዋሚነቱን ለጠላት ለማሳዬት የሚፈልግ ነው። ለዚህ እንደማስረጃ አድርጌ የምነግርህ የሆለታ መኮንኖችና ወታደሮች አብረዋቸው የነበሩት ሰላማውያን ጭምር ሸሽተው ነቀምት ከከረሙ በሁዋላ እዚያ የወረደውን የጣሊያን አይሮፕላን አቃጥለው ነጅውንና አብረውት የነበሩትን ታላላቅ መኮንኖች ስለገደሉ፥ ያገሩ ህዝብ ከዚያ እንዲባረሩ ማድረጉን ነው። ስለዚህ እንዲህ እንዲህ ያለውን ተቃውሞ እስኪያጋጥም ገለል ብለን መቆየቱ ይሻል ይሆናል› ብለን ነው እያዘን አገራችንን ትተን መሰደድን የመረጥን » አሉ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ። ሌሎችም በዋናዎቹ የጦር ግንባሮች የኢትዮጵያ ሰራዊት ድል ከተመታ በሁዋላ ከዬነበሩበት ቦታ የተመለከቱትን እዬገለፁ ተባብሮ ጠላትን ለመቃወም የነበረው ተስፋ የመነመነ መሆኑን ነገሩኝ።

«ያገራችን ሰዎች ሲተርቱ፥ ‹ውሾች ቀን ባጥንት ይጣላሉ፤ ሌት ጅብ ሲመጣባቸው እሱን ለመቃወም ይተባበራሉ!› ይላሉ። ታዲያ ከውሾች የሚሻሉት ሰዎች የጋራ ጠላታቸው ሁሉንም እያጠቃቸው ሲመጣ እያዩ

ተባብረው ያን የጋራ ጠላታቸውን በመቃወም ፈንታ እንዴት እስበሳቸው ለመፋጀት ይነሳሉ? » አልሁ።

«አዬህ ሀዲስ! የሚበዛው የኢትዮጵያ ህዝብ ስላልተማረ መንግስትን ከሱ የተለዩ እሱን እንዲገዛ እግዚአብሔር በላዩ የጫነበት ባለስልጣን አድርጎ ነው የሚያየው። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት ቢገዛው የጣሊያን መንግስት ቢገዛው ልዩነት ያለው መስሎ አይታዬውም። ስለ ጣሊያን ድል ማድረግ ሰዎች ሲነጋገሩ የሰማሁትን ልንገርህ። ‹እኛ እንገዛ ይመስል እግዚአብሔር ከሰጠው ያበሻ ንጉስ ቢገዛ የፈርንጅ ንጉስ ቢገዛ ምን አገባን? ‹እናቴን ያገባ ሁሉ የእንጀራ አባቴ ነው› እንደ ተባለው አደል› ሲል አንዱ ‹ልክ ነው ልክ ነው አሉ ሌሎች። እየውልህ የሚበዛው የኢትዮጵያ ህዝብ ጦርነቱ የሁለት ንጉሶች ወይም የሁለት ገዥዎች ጦርነት መሆኑንና የሱ ተግባር እግዚአብሔር ረድቶት ድል ላደረገው መገዛት ብቻ መሆኑን የሚያምን ነው! » አሉ አቶ ገብረ መስቀል ሀብተ ማርያም።

«መቸም ጦርነት የሚደረገው ለስሙ በመንግስቶች ወይም በገዥዎች መሀከል ይሁን እንጂ፤ ተዋጊው ሰራዊታቸው ወይም ህዝባቸው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብም በረዥም ታሪኩ ከውጭ ጠላቶቹ ጋር ብዙ ጦርነቶች ሲያደርግ ነገስታቱ ብቻቸውን ሄደው የተዋጉበት ጦርነት የለም ሁልጊዜም ሰራዊቱ ወይም ህዝቡ በጀግንነት ተዋግቶ ጠላቱን ድል እያደረገ ነው ያገሩን ነፃነት አስከብሮ የኖረ። ስለዚህ እንዴት የኢትዮጵያ ህዝብ የጠላት መንግስት ባገሩ ላይ የሚያደርገውን ጦርነት በንጉሱ ላይ እንደሚያደርገው እንጂ በሱ ላይ እንደሚያደርግበት ስለማይቆጥረው በግዴለሽነት ይመለከተዋል ይሉኛል? የውጭ መንግስቶች አገሩን የሚመለከት ከሆነ ለምን በብዙ ጦር ሜዳዎች ደሙን እያፈሰሰ ያገሩን ነፃነት ሲያከብር ኖረ? » አልሁዋቸው።

«ይህ ያስተያየት ጉዳይ ያለበት ስለሆነ የሚያከራክር ነው። አዬህ? መቸም የኢትዮጵያ ወታደር ወይም በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተፈጥሮው ጀግና መሆኑንና ባለስልጣን አክባሪ እንደ መሆኑ እንዲዋጋ ሲታዘዝ በጀግንነት ተዋግቶ ጠላቶቹን ድል እያደረገ ያገሩን ነፃነት አስከብሮ የኖረ መሆኑ በአለም ሁሉ የታወቀለት ነው። ነገር ግን እንዲያ በጀግንነት እየተዋጋና ደሙን እያፈሰሰ

ያገሩን ነፃነት አክብሮ የኖረ እንዲዋጋ ስለታዘዘ ነው? ወይስ ባይታዘዝም ላገሩ ነፃነት ሲል ተባብሮ እዬተነሳ የመጣበትን ጠላት ይዋጋ ኖሮዋል? ሁለተኛ ኢትዮጵያውያን በጦርነት ላይ የሚያሳዩት ጀግንነት ጦርነቱ፥ የሚቀሰቅሰው የተፈጥሮ ወኔ ነው? ወይስ ነፃነትን ለማስከበር ካላቸው ፅኑ ፍላጎት የተነሳ ያገር ፍቅር የሚቀሰቅሰው ነው? ወይስ ደግሞ «ፈሪ » ተብሎ ላልመሰደብ «ጀግና » ተብሎ ለመከበር ነው? ከነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ «ትክክለኛው ይህ ነው » የምልህ የለኝም። እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ በራሴ ውስጥ ተነስተው መጉላላት የጀመሩ የቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። ድሮ «በአፍሪቃ ምድር ካሉት አገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ ብቻ ነፃነትዋን አስከብራ የኖረች ጀግኖች ልጆችዋ በዬጊዜው ሊያጠቁዋት የመጡበትን ብርቱ ጠላቶች ሁሉ ተባብረው ለመቃወም በመቻላቸው ነው » እዬተባለ የሚተረከውን ታሪክ በሙሉ ልብ እምኘ እኖርላቸው ነው » እዬተባለ የሚተረከውን ታሪክ በሙሉ ልብ አምኘ እኖር ነበር። ነገር ግን አሁን ከጎጃም ተነስቼ እዚህ እስክደርስ ከመኰዋንንቱ አንስቶ እስከ ተራው ህዝብ ሁሉም የሚያደርገውን ሳይና የሚናገረውን ስሰማ የነበረኝ እምነት ተናጋብኝ። ይቅርታ አድርግልኝ ሀዲስ ወደ ጦርነት ለሚሄድ ሰው እንዲህ ያለ የሚያደክም ነገር ማናገር አይገባኝም ነበር። ግን ነገር ነገርን እየሳበ፥ ስላስበው ብዙ መናገር የማይገኝን ተናገርሁ » አሉ አቶ ገብረ መስቀል።

አቶ ወልደ ጊዮርጊስና አቶ ገብረ መስቀል በድሜም ሆነ በውቀትና በአእምሮ ብስለት ለኔ አስተማሪዎች የሚሆኑ አዋቂዎች ነበሩ። ሁለቱም ፅኑ ያገር ፍቅር የነበራቸው መሆናቸውን ከማወቄም ሌላ፥ የነገሩኝ ሁሉ ከቅን ልቡናና የህዝባችነን ሁኔታ ጠልቆ ከማስተዋል የመነጨ መሆኑን የሚያስጠረጥር አንዳች ምክንያት አልነበረኝም። ይሁን እንጂ «ያ ብዙ ሽህ ዘመን ከልዩ ልዩ ሀይለኞች ጠላቶች ጋር እየተዋጋ ነፃነቱን አስከብሮ የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ የሁሉንም ጠላቱን ሊያጠፋ የመጣ ጠላአቱ በፊቱ ተሰልፎ እያዬው ተባብሮ የጋራ ጠላቱን በመቃወም ፈንታ እስበሱ ተዋግቶ እንዳይተላለቅ በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ ነው » ያሉትን አስተያየት መቀበሉ አስቸገረኝ። ግን «የጠላት አይሮፕላንና ታንክ በሙሉ ሀይላቸው ተካፋዮች

በማይሆኑበት ረዥም የጫካ ጦርነት ተባብረን ሀይላቸው ተካፋዮች በማይሆኑበት ረዥም የጫካ ጦርነት ተባብረን ጠላታችንን አድክመን መጨረሻ ድል የኛ እንደሚሆን » የነበረኝ እምነት እነሱ የተናገሩትን ከሰማሁ በሁዋላ መድከሙ አልቀረም።

የሆነ ሆኖ ከስደተኞች ወዳጆች ጋር እንዲያ ያለፈውንም የወደፊቱንም ችግራችነን ሰፋ አድርገን ከተወያየን በሁዋላ እየተላቀስን በንባ ተሰነባብተን እነሱን እዚኢያው ትተናቸው ዘሪሁንና እኔ ወደ ጎሬ ጉዞዋችነን ቀጠልን።

## ምዕራፍ አስራ አምስት

# ጎሬ

ጎሬ እንደ ደረስን እቃውን እንዲረከቡ ክብር ራስ እምሩ ለመደቡዋቸው ሰዎች አስረክበን እኔም ሂሳቤን አስወርጄ ተገላገልሁ ነፃ ሆንሁ። አቡነ አብርሃም፥ ላቶ ዮሀንስ አብዱና ለኔ እንዲያስረክቡን ተፅፎላቸው የነበረውን ገንዘብ ስለከለከሉን እቃው የተገዛው ከደጃዝማች አያሌው ልጅ ከፊታውራሪ መርሶ በተከብነው ገንዘብ ብቻ መሆኑን ለራስ ስነገራቸው አቶ ዮሀንስ ሳይነግራቸው ቀርቶ እንደሆነ ወይም ነግሮዋቸው ረስተውት እንደሆን አላውቅም እንግዳ ሆኖባቸው ተገረሙ! አቶ ዮሀንስን ግን ጎሬ አላገኘሁትም ጎሬ እንደ ደረሰ ወዲያው ወደ ሱዳን መሰደዱን ሰማሁ።

ትንሽዋ የጎሬ ከተማ በቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ተጠባባዊነት ለተቋዋቋዋመው የኢትዮጵያ ጊዜያዊ መንግስት መንበር በመሆንዋ ጦርነቱን ለመቀጠል የወሰኑትም ገና ያልወሰኑትም ሁሉ ተሰብስበው የሚገኙባት ስለ ነበረች መቆያ ለማግኘት ቀላል አልነበረም። እኔና ዘሪሁን ግን ራስ በነእብሩበት ሰፊ ግቢ ውስጥ ሁለት ክፍሎች እንድናገኝ ስለ ታዘዘልን ጎሬን እስክንለቅ ድረስ አልተቸርንም። ያ፥ ራስ የነበሩበት ሰፊ ግቢ በውስጡ ከነበሩት ማለፊያ ቤቶች

ጋር «ልጅ ተድላ ሀይለ ጊዮርጊስ » የተባሉ የመንግስት ትልቅ ሹም ንብረቶች ኖረዋል። ታዲያ ልጅ ተድላ ጦርነቱ ሲጀመር ከጣሊያኖች ጋር ሲሻረኩ ስለ ተገኙ እሳቸው በስቅላት ተቀጥተው ንብረታቸው ሁሉ የተወረሰ መሆኑ ያን ጊዜ በግሀድ ይነገር ነበር።

ዘሪሁንና እኔ ያመጣነውን እቃ አስረክበን የታዘዘልንን ማረፊያ ካገኘን በሁዋላ እኔ ከመንግስቱ ተጠባቂ ከቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ጋር ለመገናኘት ወደ ጊዜያዊው ቤተ መንግስት ሄድሁ። ቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ለኔና ለጥቂት ጉዋደኞቼ፥ ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት በነበርንበት ጊዜ የማይረሳ ርዳታ ያደረጉልን ባለውለታችን ስለ ነበሩ ማየት ነበረብኝ።

‹የቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ውለታ› ያልሁት ምንም እንኩዋ ከመንገድ የወጣ ቢመስል በዚህ መፅሀፍ ምዕራፍ ሶስት ከተመለከተው «ያበሻና የወደሁዋላ ጋብቻ » ከተባለው ትያትር ጋር የተዛመደ ከመሆኑ ሌላ የልጅነት አሰባችንን አሁን መለስ ብዬ ሳስታውሰው፥ እኔን እያጫወተ እንደሚያስቀኝ «አንባቢዎችንም ለማጫወትና ለማሳቅ ያክል ያገለግል ይሆናል » በማለት ከዚህ ቀጥየ እፅፈዋለሁ።

የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጊዜው ይሰጥ የነበረው ትምህርት አጥጋቢ ካለ መሆኑም ሌላ፥ አንዳንድ አስተማሪዎች ችሎታ ያልነበራቸው በመሆናቸው እንዲለወጡ ችሎታ ካላቸው መሀከልም አንዳንዶቹ የስካር አመል ስለ ነበራቸ በትምርት ጊዜ ሰክረው እቤታቸው የሚውሉ በመሆናቸው አቤቱታቸውን ደጋግመው አሰምተው ምንም ስላልተደረገላቸው በፈትና ጊዜ አድማ አድርገው «አንፈተንም » አሉ። ወዲያው ባለስልጣኖች «እንዲያ ላለው አድማ ጠንሳሾችም መሪዎችም ባዳሪነት የሚማሩት ትልልቅ ተማሪዎች ሳይሆኑ ስለማይቀሩ ከወለጋ ልጆች በቀር እድሜያቸው ተማሪዎች ሳይሆኑ ስለማይቀሩ ከወለጋ ልጆች በቀር እሜያቸው አስራ ስምንት አመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ተማሪዎች ሁሉ ካዳሪነት ወጥተው በተመላላሽነት እንዲማሩ » የሚል ደንብ አወጡ። ወለጎችን ከዚያ ጨካኝ ደንብ ነፃ እንዲወጡ ያደረጋቸው «የወለጋ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ለያንዳንዳቸው ከመክፈላቸው

ሌላ ትምህርት ቤቱን ጠቅም ባለ ገንዘብ ይረዱ ስለ ነበረ ነው » ይባል ነበር። የሆነው ሆኖ ያ ደንብ ከወጣ በሁዋላ፥ በተመላላሽነት ትምህርታቸውን መቀጠል የሚችሉ አዲስ አበባ ዘመዶች የነበሩዋቸው ካልሆኑ ከየክፍላተ ሀገሩ ተሰብስበው ባዳሪነት ይማሩ የነበሩት አስራ ስምንት አመትና ከዚያ በላይ እድሜ የነበራቸው ሁሉ ትምህርታቸውን አቋርጠው «የትሜና » እንዲሄዱ ተፈረደባቸው ማለት ነው! ስለዚህ እድሜያችን አስራ ስምንት አመትና ከዚያ በላይ የሆነ ትልልቅ ልጆች ተሰብስን ትምርታችንን ለመቀጠል ማድረግ የምንችለው ነገር ባይኖርም ሳንበታተን ባንድ ላይ ሆነን እስከዚያ ድረስ ተምረን ባገኘነው እውቀት ያስተማረችንን አገራችንን የምንረዳበት መንገድ ፈልገን ማግኘት እንዳለብን ተስማማን። ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ያክል በድብቅ እየተሰበሰብን ከተመካከርን በሁዋላ ማህበር እንድናቁዋቁም ወስነን፥ እኔ ሰብሳቢ ገብረ አብ ቢያድግልኝ ፀሀፊ ተወልደ ብርሃን ገንዘብ ያዥ ሆነን ተመረጥን።

የማህበሩ አላማ ከትምርት ቤት ወጥተው ስራ የያዙ አባሎች ሁሉ በደመወዛቸው መጠን የተወሰነ መዋጮ አዋጥተው ስራ ካልያዙት መሀከል ትያትር መድረስ የሚችሉት እዬደረሱና የማይደርሱትን «በተዋናያንነት » እያሰሩ ገንዘብ ሰብስበው በኒህ በሁለት መንገዶች በሚገኘው ገንዘብ መጠን የህል ወፍጮዎች ማቁዋቁዋም ከዚያ በሁዋላ ከደመወዝ መዋጮ ከትያትርና ከወፍጮዎች የሚገኘው ገንዘብ እየበረከተ ሲሄድ ከህል ወፍጮ ተራምዶ በኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ በየተራ የኤሌክትሪክ ሀይልና መብራት ማቁዋቁዋም ከዚያ ተራምዶ የጨርቃ ጨርቅ የጫማና የብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች ማቁዋቁዋም ከዚያ በሁዋላ እንዲያ ካንዱ ተነስቶ፤ በዚያ ርዳታ ወደ ሌላው እየተሸጋገሩ ልዩ ልዩ ከባባድ ፋብሪካዎችን በማቁዋቁዋም ኢትዮጵያን የሰለጠኑት አገሮች በደረሱበት እንድትደርስ ማድረግ ነበር! አቤ - ት እንዴት ቀላል ነው! «ልጆች ሰማይን እንደሚያዩት ቅርብ መስሎዋቸው ሊመቱት ደንጋይ ሽቅብ ይወረውሩበታል! » እንደሚባለው አደል? ታዲያ በዚያ አላማ በልጆች ሸንጐ ተሰብስበን ባንድ ድምፅ ተስማማን። ስላፈፃፀሙ በመጀመሪያ ደረጃ እኔ «ያበሻና የወደሁዋላ ጋብቻ » የተባለ ትያርት ደርሼ ትምርት ቤት

ሲዘጋ እንዲታይልኝ ያንጊዜ የትምርት ሚኒስትር የነበሩትን «ብላቴ ጌታ ህ ሳህሌ ፀዳሉን » ጠይቄያቸው ከተመለከቱት በሁዋላ «ትምርት ቤት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ የውጭ አገር አገር ዲፕሎማቶችና ሊሌሎች ፈረንጆች ስለሚገኙ በማያውቁት ቁዋንቁዋ እንዲያ ያለ ረዥም ትያትር ማሳየት አይገባም! » በማለታቸው ሳይታይ ቀርቶ ስለ ነበረ ቲኬት አሳትመን ሸጠን እሱን ሆቴል ለማሳየት ወሰን። ከዚያ በሁዋላ አስቸጋሪው ነገር የትምህርት ሚኒስትሩ እንዳይታይ የከለከሉትን ትያትር በተለይ ጃንሆይ ካልፈቀዱ ማሳየት የማይቻል ስለሆነ የብላቴ ጌታ ሳህሌ ፀዳሉን ጥል ሳይፈራ በትምርት ሚኒስቴር ስራ ገብቶ ጃንሆይን ለማስፈቀዱ የሚደፍር ባለስልጣን የማግኘቱ ጉዳይ ነው።

በዚያ ጊዜ ያገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ቢትወደድ ወልደ ፃድቅ «ቅንና ለሚያምኑበት ነገር ከማንም ጋር ቢሆን ከመጋፈጥ ወደ ሁዋላ የማይሉ ናቸው! » እየተባለ ሲነገር እንሰማ ስለ ነበረ ወደሳቸው ሄደን እንድንለምናቸው ተስማማን። ስለዚህ ገብረ አብ ቢያድግልኝና እኔ ሄደን ስንለምናቸው ምንም ሳያመነቱ ትያትሩን አሳይተናቸው የሚጠቅም መሆኑ ከተረዱት እንደሚያስፈቅዱልን ተስፋ ሰጥተውን በማግስቱ ወስደን ልናሳያቸው ቀጠሮ አድርገውልን ተመለስን። በቀጠሮዋችን እሳቸው ከስራ ከመመለሳቸው ቀድመን እግቢያቸው በቀጠሮዋችን እሳቸው ከስራ ከመመለስቸው ቀድመን እግቢያቸው ገብተን ስንጠብቅ መጥተው ከአተመቢል እንደ ወረዱ ሲያዩን ይዘውን ገቡ። ክረምት ስለ ነበረ ይወይራ ፍልጥ «ግወ » ብለው ነዶ ቤቱን አሙቆት ነበር። ቢትወደድ ገብተው በተነጠፈ ድልዳላቸው ላይ ከቀኝና ከግራ መከዳዎቻቸው መሀከል ከተቀመጡ በሁዋላ ሁለታንች ባጠገባቸው ቆመን እኔ ትያትሩን ከመጀመሪያው ጀምሬ ማንበብ ጀመርሁ። አንዳንድ ነጥቦች እንዲብራራላቸው ሲጠይቁም፤ ለማብራራትና ሌሎች ጥያቄዎች ሰፋ ወዳለ ክርክር ይመሩ ስለ ነበረ፥ ስንከራከር ባንድ ማታ ስናጨርስ ቀርተን፥ በተከታዩ ማታ እንደ ገና ሄደን ጨረስን።

«ማለፊያ ትያትር አዘጋጅታችሁዋል፤ እግዚአብሔር ይባካችሁ ልጆቼ። መማራችሁ እንዲህ እንዲህ ያለ ስራ እየሰራችሁ ያልተማረውን

እንድታስተምሩ ነውና በርቱ። አሁን የት ሆቴል ነው ለማሳየት ያሰባችሁ? » አሉ ቢትወደድ ደስ ብሎዋቸው።

«ማጀስቲክ ሆቴል በሚባለው ነው »

«እንግዲህ ሊያዩት የሚገባ ማለፊያ ትያትር መሆኑን አስረድቼ ቢመቻለው ጃንሆይ ራሳቸው ሄደው እንዲያዩላቸው ባይመቻቸው ለማሳየት እንዲፈቀድላችሁ እነገራቸዋለሁ » ብለው መልሱን ከሶስት ቀን በሁዋላ እንድንጠይቃቸው ቀጠሮ ሰጥተውን ተመለስን። በቀጠሮዋችን ስንሄድ ጃንሆይ ሆቴል ሄደ ትያትር ለማየት የማይመቻቸው በመሆኑ ካልጋ ወራሽ ጀምሮ፥ ራሶች፥ ደጃዝማቾችና ሌሎች ታላላቅ ሰዎች ትያትሩ ሆቴል በሚታይበት ቀን ሄደው እንዲያዩ ባገር ግዛት ሚኒስትር ቀላጢነት እንዲታዘዝ የተረፈውን ቦታ ቲኬት ገዝቶ ማየት ለሚፈልግ ሁሉ እንድንሸጥ የተፈቀደልን መሆኑን ነገሩን። አቤ - ት ያን ጊዜ የተሰማን ደስታ! ያን ጊዜ የተሰማንን ደስታ ሊገልፁት የሚችሉ ቃላት አይገኙም! ያን ጊዜ የሩቅ አላማችንን የመታን መስሎ ተሰምቶን የምስራቹን፥ ለማህበርተኞችን ለመንገር በደስታ እየፈነደቅን ሄድን።

በተከተሉት ሁለት ሳምንቶች ከትምርት ቤቱ ዘበኞች ጋር ተሻርከን ሌሊት ሌሊት ሰው ሁሉ ሲተኛ የትያትር ማሳይውን አዳራሽ መስኮቶች እየዘጋን እዚኢያ ተዋንያኑ ልምምዳቸውን ሲያደርጉ ሰነበቱ። ልምምዱ ደህና ሆኖ ከተጠናቀቀ በሁዋላ ትያትሩ ሶስት ሰአት ያክል እንደሚፈጅ ስለ ታወቀ፥ የሆቴሉን የትያትር ማሳያ አዳራሽ ለሶስት ሰዓት በሰማንያ ብር ተከራይተን እዚያ እንዲታይ አደረግን። ለትያትሩ መክፈቻ እንዲሆን «ተነሱ ታጠቁ » የተባለውን ያገር ፍቅር መቀስቀሻ መዝሙር የደረስሁት ልምምዱን እናደርግ በነበርንበት ጊዜ ነው። በቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ቀላጢነት ለተጠሩት መሳፍንት መኩዋንንትና ብዙ ታላላቅ ሰዎች እንዲሁም ቲኬት ለገዙት ሁሉ ያ ሰፊ አዳራሽ «አልበቃ » ብሎ በየመኮቱ ጠርዝ ተቀምጠውና ግንቡን እዬተደገፉ ዙሪያውን ቆመው የሚያዩ ብዙ ነበሩ። በቢትወደድ ቀላጢነት ከተጠሩት መኩዋንንት መሀከል «አሞኛል » ብለው ሳይመጡ የቀሩ ብላቴን ጌታ ሳህሌ ፀዳሉ ብቻ ነበሩ።

ሀበሻ ወደ ሁዋላን አግብታ ከመደህየትዋና ከመንገላታትዋ የተነሳ በልቅሶ ብዛት አይነ በሽተኛ ስትሆን ዝም ብለው በመመልከታቸው ልጆቹዋን እየወቀሰች በፊታቸው ተቀምጣ በዜማ ስታለቅስ ከተጠሩት መኩዋንንትም ቲኬት ገዝቶ የሚያየው ህዝብም መሀከል፤ አብረዋት የሚያለቅሱ ብዙ ነበሩ። ትያትሩን ያዩት ሁሉ ከመውደዳቸ የተነሳ በጃንሆይ ትእዛዝ ከተጠሩት መሀከል ጥቂቱ የገንዘብ ስጦታ አደረጉልን። ራስ ብዙ አንድ መቶ ብር ሌሎች ካምሳ ብር ጀምሮ ወደ ታች ሰጡ። ያን ትያትር ያዩት አይተው በመውደዳቸው ያላዩት ካዩት ሰምተው ሊያዩት በመፈለጋቸው ተደግሞ እንዲታይ በጋዜጣ የፃፉት ስለ ብዙ፥ ባጭር ጊዜ ውስጥ ቲኬት አሳትመን ሽጠን ሁለተኛ አሳዩነው። ሁለተኛ ሲታይ ማጀስቲክ ሆቴልም ከመውደዱ የተነሳ ኪራይ ሳያስከፍል በነፃ እንድናሳይ ፈቀደልን። ስለዚህ ላንድ ጊዜ የሆቴል ኪራይ ለቲኬት ማሳተሚያና ላንዳንድ ጥቃቅን ወጪ ያደረግነው ተቀንሶለት ሁለት ጊዜ ካሳዩነው ቲያትር ከሰባት ሽህ ጠገራ ብር በላይ ትርፍ አግኝተን ተወልደ ብርሃን (ገንዘብ ያዣችን) ባንክ እንዲያገባው አደረግን። ከዚያ ወዲያስ? ከዚያ ወዲያማ ምንም ያክል ጊዜ አዲስ አበባ ሳንቆይ በስራ ወደ የጠቅላይ ግዛቱ እንድንበታተን ተደረገ! ላገራችን እድገት የታሰበው ብርም፤ ባንክ እንደ ተቀመጠ፥ ነፃነትዋን ሊያጠፉ ለመጡት ፋሽስቶች ሆነ!

አሳባችን የልጆች አሳብ እንደ መሆኑ በህልም ተራ እንደ ሆነ እንጂ በድገት እቅድ ተራ ገብቶ የሚታይ አለመሆኑ መቸም የቅድንና ያፈፃፀሙን ስራ ለሚያውቁ ሁሉ ግልፅ ነው! ግን ቢትወደድ ወልደ ፃድቅን ጎሬ ከማግኘቴ ጋር ከብላቴን ጌታ ሳህሌ ፀዳሉ ጋር በነበረን ፍልሚያ የዋሉልን ውለታ ትዝታዎቻቸው እስከ ዛሬ ከሚያጫውቱኝ የልጅነት አሳቦቻችንና ትግሎቻችን አንዱ ስለ ሆነ፤ «አንባቢንም ያጫውት ይሆናል » በማለት ነውና እዚህ ላይ ያለ ቦታው ጣልቃ ያገባሁት፤ ይቅርታ እንደሚደረግልን ተስፋ አደርጋለሁ።

ቢትወደድ አልረሱልኝ ኖሮ ገና ሲያዩኝ ረዥም ጊዜ ተለይቶዋቸው እንደ ኖረ ዘመዳቸው አቅፈው ሳሙኝ። ከዚያ ስለ ራሴም ስለሚያውቁዋቸው ጉዋደኞቼም ጤንነትና የኑሮ ሁኔታ እየጠየቁኝ ስንነጋገር ከቆየን በሁዋላ ቤት አላገኘሁ እንደሆነ ከቤተ መንግስቱ ግቢ ውስጥ ላገኝ እንደምችል ስለ ነገሩኝ

አመስግኘ ክቡር ራስ እምሩ ደህና ቦታ ሰጥተውኝ እዚያ መሆኔን ነግሬያቸው ልሂድ ስነሳ በየጊዜው እየሄድሁ ባነጋግራቸው ደስ የሚላቸው መሆኑን ገልፀውልኝ ተሰናበትሁ። ከዚያ በሁዋላ በየጊዜው እየሄድሁ ሳነጋግራቸው ተስፋፋቸውን ያሳረፉት በጃንሆይና በአለም መንግስታት ማህበር ላይ እንጂ ሌላ «ጣሊያንን ድል አድርጎ ከኢትዮጵያ የሚያስወጣ ሀይል ይኖራል » ብለው የማያምኑ መሆናቸውን ከንግግራቸው ተረዳሁ።

«አየህ ልጄ ጃንሆይ ለአለም መንግስታት ማህበር አቤቱታቸውን አቅርበው ማህበሩ በቃል ኪዳን መሰረት ጣሊያንን አስገድዶ ካገራችን ካላስወጣልን አስተባብሮ የሚመራው መሪ በሌለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነቱን ቀጥሎ ነፃነቱን ያስመልሳል ብሎ ማሰብ ከንቱ ነው። ሁላችንም ተስፋ የምናደርገው የአለም መንግስታት ማህበር ለጣሊያን ብሎ ቃል ኪዳኑን ማላውን አያፈርስም ብለን ነው » አሉኝ ቢትወደድ ስለ ጦርነቱ መቀጠል ያለውን ተስፋ መጀመሪያ የጠየቅሁዋቸው እለት።

«ድሮውንም ኢጣሊያ ደፍራ አገራችንን የወረረች የአለም መንግስታት ማህበር ሊያግዳት እንደማይችል ስላወቀች ነውኮ ጌታየ። የጣሊያን ጦር ሰራዊት አዲስ አበባ እንደ ገባ ኢትዮጵያ የጣሊያን ቅኝ አገር መሆንዋን ሙሶሊኒ ባዋጅ ካስታወቀ ይኸው አምስት ወር ማለፉ ነው። ግን እስካሁን የአለም መንግስታት ማህበር የጣሊያንን መንግስት እንኩዋንስ ጦሩን ከኢትዮጵያ እንዲያስወጣ ሊያስገድደው፤ ቃል ኪዳኑን በማፍረሱ ከማህበሩ እንዲወጣም የቀረበ አሳብ የለ። እንዲያውም ከማህበርተኞቹ መሀከል ኢትዮጵያ ነፃ አገር መሆንዋ ቀርቶ፥ የጣሊያን ቅኝ ግዛት መሆንዋን አውቀው የተቀበሉ አሉ ይባላል። ስለዚህ ከአለም መንግስታት ማህበር ርዳታ እናገኛለን ብሎ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ነው » አልሁዋቸው።

«እንግዲያውስ ሌላ ምን ተስፋ አለን? ጃንሆይ ሙሉ ተስፋ አድርገው፥ ለኛም ሙሉ ተስፋ ሰጥተውን የሄዱ ከአለም መንግስታት ማህበር ርዳታ አግኝተው እንደሚመለሱ ነበር። ግን አሁን አንተ እንዳልኸው ከሆነ አገራችን የጣሊያን ግዛት፥ ህዝብዋ የጣሊያን ባሮች ሆነን መቅረታችን ነዋ! ምነው ይህን ሳላይ ሳልሰማ በሞትሁ! ይህን ሳያዩ ሳይሰሙ የሞቱ ምንኛ እድለኞች ናቸው!

» አሉ ቢትወደድ ብስጭት በተቀላቀለበት አዘን ፊታቸው ካጭር ጊዜ በፊት ከነበረው ተለውጦ።

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት አባሎች ከነበሩት መኩዋንንት የሚበዙት ለአለም ውትብትብ ፖለቲካ እንግዶች የነበሩ ከመሆናቸው ሌላ ቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ስለ አለም ፖለቲካ ተባራሪ ወሬ እንኩዋ ከሚገኙበት ካዲስ አበባ ርቀው ጎሬ በመቆየታቸው ከኔ ጋር እስከ ተገናኙበት ጊዜ ድረስ ጃንሆይ ኢትዮጵያን ለቀው ሲሄዱ ከአለም መንግስታት ማህበር ርዳታ አግኝተው እንደሚመለሱ የነገሩዋቸው አምነው፤ ርዳታው እስኪደርስላቸው በተረጋገጠ ተስፋ የሚጠብቁ ነበሩ።

«ጌታየ ‹ከአለም መንግስታት ማህበር ርዳታ የማናገኝ ከሆነ ሌላ ምን ተስፋ አለን› ላሉት የአለም መንግስታት ማህበር ባልነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ተባብሮ የውጭ ጠላቶቹን ሁሉ ድል እየመታ ያገሩን ነፃነት አስከብሮ እንደ ኖረ መቸም የታወቀ ነው። ስለዚህ ወደፊትም እንደ ድሮው ተባብሮ ጦርነቱን ከቀጠለ በመጨረሻ ጠላቱን ድል አድርጎ ካገሩ ሊያስወጣ የሚችል መሆኑ የሚያጠራጥር ስለሆነ በአለም መንግስታት ማህበር ርዳታ ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በህዝባችን ጀግንነት ተስፋ ማድረግ ነው የሚገባ » አልሁዋቸው።

«ንጉሡ ነገሥቱ ከሙሉ ሠራዊታቸው ጋር ተዋግተው ያልቻሉትን ሀይለኛ ጠላት አስተባብሮ የሚመራው ንጉስ ሳይኖረው ህዝቡ እንዴት አድርጎ ካገሩ ሊያስወጣው ይችላል ልጄ? »

«ከዚህ በፊት በትግራይና በኦጋዴን ግንባሮች የተደረገው ጦርነት ሁለቱም አገሮች የጫካ ምልክት የሌለባቸው ገላጣዎች በመሆናቸው የጣሊያንን ጦር ለድል አብቅቶ አዲስ አበባ እንዲገባ ያደረገው የኢትዮጵያ ሰራዊት የሚከለክልበት ጫካ ስላልነበረው አይሮፕላኖች ከሰማይ ያወርዱበት የነበረው ቦምብና የመርዝ ጋዝ ነው እንጂ የወታደሩ ጀግነንት ወይም የሌላም መሳሪያ ብዛትና ጥራት አልነበረም። ወደ ፊት ግን ጦርነቱ የሚደረግ እስካሁን ባልተያዙት ጫካ የሞላባቸው አገሮች ስለሆነና እዚያ አይሮፕላኖች እንደ ልብ ለጦርነቱ ተካፋዮች ስለማይሆኑ ጦርነቱን የሚወስነው፥ የኢትዮጵያና የጣሊያን

ወታደሮች ጀግንነት ነው የሚሆነው። የኢትዮጵያና የጣሊያን ወታደር ጀግንነት ደግሞ አይሮፕላን ባልነበረበት ባድዋ ጦርነት ታይቶዋል። ለዚህ ነው፥ በወታደሮቻችንና በጠቅላላው ህዝባችን ጀግንነት ተስፋ ማድረግ ይገባናል ያልሁ። »

«ስማ ልጄ » አሉ ቢትወደድ ባላዋቂነቴ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብለው። «አንተ ሌላ ሌላውን ነው እንጂ ገና ልጅ ስለሆንህ ያገራችንን ልማድ አታውቀውም። የኢትዮጵያ ወታደር መሰል የሌለው ጀግና መሆኑ እውነት ነው። ግን አስተባብሮ የሚመራው መሪ ያስፈልገዋል። በልማዱ አገራችንን የሚወር የውጭ ጠላት ሲመጣ ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉንም የሚሾም የሚሽር የበላይ ባለስልጣን በመሆኑ በያገሩ ያሉትን ንጉሦችና ራሶች ወይም ባለሌላ ማእርግ አገረ - ገዥዎች ጦራቸውን አስከትተው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ከተወሰነ ቦታ እንዲገኙ ያዝዛቸውና ሁሉም ትእዛዙን አክብረው ጦራቸውን እየያዙ በተነገራቸው ቦታ ሲገኙ ንጉሠ ነገሥቱ አስተባባሪና መሪ በመሆኑ ቦታ ቦታቸውን አስይዞ እያዋጋ ያው እንዳልኸው ጠላቶቹን ድል እየመታ ይመስል ነበር። ዛሬ ግን በውድም በግድም አዝዘው የሚመሩት ንጉሡ የሉም፥ መሳፍንትና መኩዋንንትም ‹ማን በማን ታዝዞ ይዋጋል!› ባዮች ናቸው። ስለዚህ ነገሩ ላንተ እንደ መሰለህ ቀላል አይደለም አስቸጋሪ ነው። ‹መሪ የሌለው ሰራዊትና እረኛ የሌለው ከብት አንድ ነው!› እንደሚባለው ነው። እረኛ የሌለው ከብት አውሬ ቢመጣበት ሁሉም ከመበላት ለመዳን በየፊናው ይፈርጥጣል እንጂ፤ እንኩዋንስ ተባብሮ አውሬውን ሊቃወም፤ ባንድ ተሰብስቦ እበረቱ መግባት አያውቅም። አስተባብሮ የሚመራው የሌለው ሰራዊትም እንደዚያ ነው » አሉ ቢትወደድ።

«የጋራ ጠላት ሲመጣ ተባብሮ በመከላከል ፈንታ፤ ‹ማን በማን ይታዘዛል› መባባል ካለማ፤ ምንም ማድረግ እንደማይቻል የታወቀ ነው። ግን ከብላቴን ጌታ ህሩይ ልጅ፤ ከሲራክ ህሩይ ጋር ሱዳን ተገናኝተን ‹ጦርነቱን ባንድነት ተባብረው እንዲቀጥሉ፤ ከቡር ራስ እምሩ ከወለጋ ከጅማው፤ ከከፋው፤ ከገሞጎፋው ከባሌውና፤ ከሲዳሞው አገረ - ገዥዎች ጋር ተላልከው ተስማምተው፤ ክረምቱ እስኪወጣ ነው የሚጠብቁ› ብሎኝ ነበር። ታዲያ

በራስና በኒያ ባልተያዙት አገሮች ገዥዎች መሀከል ጦርነቱን ለመቀጠል ስምምነት አልተደረገም ማለት ነው? »

«ራስ ለሁሉም የላኩባቸው መሆኑን ለኔም ነግረውኛል። ግን ራስ ደስታ ደጃዝማች ገብረ ማርያምና ደጃዝማች በየነ መርዕድ ያሉባቸው አገሮች ሲዳሞ ባሌና ገምጎፋ ከዚህ ሩቅ በመሆናቸው በክረምት የተላኩ መላክተኞች ደርሰው እስኪመለሱ ብዙ ጊዜ ስለሚወስድ መልስ እንኳዋ የተገኘ አይመስለኝም። ቀረብ ያሉት የወለጋው መልስ እንኳዋ የተገኘ አይመስለኝም። ቀረብ ያሉት የወለጋው ደጃዝማች ሀብተ ማርያም የጅማው ከንቲባ ጋሻው ጠናና የከፋው ደጃዝማች ታየ ናቸው ከነሱም የተጨበጠ ነገር አለመኖሩን አልሰማሁ። ስለዚህ፥ ‹ራስ እምሩና ባልተያዙት አገሮች ያሉ አገረ ገዥዎች ተባብረው ጦርነቱን ለመቀጠል ተስማምተዋል› ለማለት የሚቻል አይመስለኝም » አሉኝ።

ጦርነቱን ለመቀጠል ስለ ታሰበው አሳብና ስለ ታቀደው እቅድ ክቡር ራስ እምሩን በጠየቅሁዋቸው ቁጥር ሁልጊዜ ይሰጡኝ የነበረው መልስ ክረምቱ ሲወጣ ጠላትን ለመውጋት እሳቸው ከጎሬ ወደ ውስጥ እንደሚገቡና በዚያ ጊዜ ባልተያዙት አገሮች የነበሩት አገረ - ገዥዎችም ጦራቸውን አዘጋጅተው ለጦርነት እንዲነሱ በሁሉም የላኩባቸው መሆኑን ብቻ ነበር። ስለዚህ ራስ እምሩንም ቢትወደድ ወልደ ፃድቅንም በየጊዜው ካነጋገርሁዋቸው በሁዋላ እንደ ተረዳሁት እንኩዋንስ ከጠላት ጋር ለመዋጋት በህብረት የተሰናዳ የጦርነት እቅድ ሊኖር፥ ልጅ ሲራክ እንደ ነገረኝ ጦርነቱን ባንድነት ለመቀጠል በራስ እምሩና ቀደም ብሎ ስማቸው በተነገረው አገረ - ገዥዎች መሀከል የተደረገ ጠቅላላ ስምምነትም አልነበረ! እንዲያውም ባልተያዙት አገሮች ከነበሩት ገዥዎች እነማን ጠላትን ለመቃወም እነማን ጠላትን ለመቀበል ተሰልፈው እንደሚጠብቁ እንኩዋ አይታወቅም ነበር! ከነዚህ ሌላ ደግሞ በኒያ ባልተያዙት አገሮች የሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ ጦርነቱን ለመቀጠል የሚፈልጉን የኢትዮጵያ መንግስት ወገኖች መርዳት የሚፈልግ ወይስ ጦርነቱን መቀጠል እንደማያዛል ወገኖች መርዳት የሚፈልግ ወይስ ጦርነቱን መቀጠል እንደማያዛልቅ በመረዳት የጣሊያንን ገዥነት ተቀብሎ በሰላም መኖርን የሚፈልግ ስለ መሆኑ አስቀድሞ

መረጃ ለማግኘት የተደረገ ምኩራ አልነበረም። ስለዚህ ልጅ ሲራክ ሱዳን በነገረኝ መሰረት ጦርነቱን በማስረዘም ጠላታችንን አድክመን ካገራችን ለማስወጣትና ነፃነታችንን ለማስመለስ የነበረኝ ፅኑ ተስፋ ጎሬ ከደረስሁ በሁዋላ ሁኔታውን ሁሉ ስመለከት ከተስፋ ደረጃ ወርዶ ከንቱ ምኞት መሆኑን ተገነዘብሁ።

ከመስከረም 1929 መጨረሻ ግድም ቀደም ብሎ በክረምቱ ውስጥ፥ የሆለታ መኰንኖችና ወታደሮች፤ ከወለጋ ተገደው ሲወጡ አብረዋቸው ከነበሩት መሀከል አቶ ይልማ ደሬሳ ዶክተር አመለወርቅ በየነና የሙቶ አለቃ በኩረ የተባለ ወጣት መኮንን ጎሬ መጥተው ከራስ ጋር ተገናኝተው መመለሳቸውን ሰማሁ። እኔ አግኝቼ አላነገርሁዋቸውም። ነገር ግን አግኝተው ካነጋገሩኝ ሰዎች እንደ ሰማሁት ወለጋን ለቀው ወደ ኢሉባቦር ግዛት ከተሻገሩ በሁዋላ ስለ ደጃዝማች ሀብተ ማርያምና ስለ ጠቅላላው የወለጋ ህዝብ አቋዋም የሚያውቁት የተረጋገጠ ነገር አልነበረም። እናቶ ይልማ ተመልሰው ከሄዱ በሁዋላ የትምርት ቤት ጉዋደኛየ፤ በትረ ፅድቅ ካሳና በስም ብቻ የማውቀው ተመስገን ገብሬ ካዲስ አበባ ሸሽተው ከሆለታ ሰዎች ጋር የማውቀው ወደኛ መጡ። እነሱም የሆለታ መኮንኖች የጣሊያንን አይሮፕላን አቃጥለው ነጂውንና አብረውት የነበሩትን ሹማምንት በመግደላቸው «ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ከመኩዋንንታቸው ጋር መክረው ካገራቸው እንዲወጡ ማድረጋቸው ከጣሊያኖች ጋር ለመቀራረብ ቢፈልጉ ይሆናል » ብለው ከመጠርጠር በቀር በዚያ ጊዜ የደጃዝማችና የህዝባቸው አቋዋም ምን እንደ ነበረ እርግጠኛውን የማያውቁ መሆናቸውን ነገሩኝ። ታዲያ የደጃዝማች ሀብተ ማርያም አቋዋም መሆናቸውን ጠራጥር ሁኔታ እንዳለ «ራስ እምሩ ከሳቸው ጋር ተባብረው በጠላት ላይ ጦርነቱን ለመቀጠል ወደ ወለጋ ሊሂዱ ነው » ተብሎ የተፋጠነ ዝግጅት ሲደረግ ይታይ ነበር።

ያንጊዜ ከነበረው የክቡር ራስ እምሩ ጦር ሠራዊት የሚበዙት ከረዥም ጊዜ ጀምሮ አብረዋቸው የኖሩ መኩዋንንታቸውና ወታደሮቻቸው ነበሩ። ከነሱም አንዳንዶቹ እየጠበቁ ሌሎች በድሜና በልዩ ልዩ ምክንያት ራስ እያሰናበቱዋቸው ወዳዲስ አበባም ወደ ያገራቸውም የገቡት ተቀንሰውለታል። ከራስ ነዋሪ ሰዎች ሌላ ጎጃም ከነበረው አንድ ሻለቃ የክብር ዘበኛ ጦር ባዛዡ፥

በልጅ ግዛው ቡኔ ስር ጥቂት የክብር ዘበኞች ነበሩ። እንዲሁም ጎጃም በግዛት ላይ ከነበሩት መኰዋንንት ትዝ እንደሚሉኝ የጎጃም ተወላጅ ፊታውራሪ ዳምጠው ተሰማ እና ወለየው ፊታውራር ከብደ ያዘው ብቻ ከጥቂትት ከጥቂት ሰዎቻቸው ጋር ነበሩ። ከነዚያ ሌላ በጉምሩክና ባንዳንድ የመንግስት መስሪያ ይሰሩ የነበሩ ሹማምንትም ሰራተኞችም ሊኤሎች ግለሰቦችም ነበሩ። ቀኛዝማች በልሁ ደገፉና ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይ ለጦርነት ከእንግሊዝ አገር ከጃንሆይ እየተሰናበቱ መመለሳቸውን ቀደም ብዬ ስላመለከትሁ እነሱም ከጥቂት ሰዎቻቸው ጋር ነበር። ስለዚህ ክቡር ራስ እምሩ ጦርነቱን ለመቀጠል ከጎሬ ሲነሱ የነበራቸው ጦር ሰራዊት በድምሩ ከሶስት መቶ «ከፍ ቢል » ካራት መቶ ሰው የሚበልጥ አይመስለኝም።

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

# ከጎሬ እስከ (ጎይ?)

የጣሊያን ጦር ሰራዊኢት አዲስ አባባን እንደ ያዘ ሙሶሊኒ ኢትዮጵያ የጣሊያን ቅኝ ግዛት መሆንዋን ባዋጅ ካስታወቀ በሁዋላ በየክፍሉ ይደረግ የነበረውን ጦርነት እኛና ጣሊያኖች በተለያየ ስም እንጠራው ነበር። በኛ በኩል «የኢትዮጵያ መንግስት መንበሩን ካዲስ አበባ ወደ ጎሬ አዛወረ እንጂ ስላልጠፋ በየክፍሉ የሚደረገው ጦርነት መንግስቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚዋጋው ጦርነት ተከታታይ ወይም ክፍል በመሆኑ ‹ጦርነቱን መቀጠል› ሊባል ይገባዋል » እንል ነበር። ጣሊያኖች በበኩላቸው «የጣሊያን መንግስት ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛቱ መሆንዋን ባዋጅ አስታውቆ የመንግስቱን ስልጣን ከያዘ በሁዋላ በየክፍሉ የሚደረገው ጦርነት የሽፍተንት ጦርነት ነው » ባዮች ነበሩ። የሆነ ሆኖ እኛ በሰጠነው ስምም ይሁን ወይም ጣሊያኖች በሰጡት ስም ጠላትን ለመውጋት ክቡር ራስ እምሩ ያን በትጥቅና በስንቅ ወይም በህዝብ ድጋፍ አዝላቂ

መተማመኛ የሌለው ጥቂት የጦር ሰራዊታቸውን ይዘው በጥቅም 1929 መጀመሪያ ግድም፥ ወደ ወለጋው ገዥ ወደ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ለመሄድ ከጎሬ ተነሱ።

ዘሪሁንና እኔ ራስ ከጎሬ ከመነሳታችን ጥቂት ቀናት ቀደም ብለን «ቡኖ ዋቤኮ » ወደ ሚባል አገር ሄድን። ዋቤኮ አቦ አባቴ ካገራቸው ከጎጃም ሄደው ረዥም ጊዜ ይኖሩበት የነበረ ከወለጋ መንገድ ምንም ያክል የማይርቅ አገር ነው። ስለዚህ አባቴን አይቼ ወዲያውም በቅሎዎችና በቂ ስንቅ ስላልነበሩኝ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ሊገኝ የተቻለውን ያክል ይዘን፤ ራስ በዚያ ሲያልፉ እንደምናገኝ አውቀን ነበር የሄድን።

አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ራስ እኛ ወደ ነበርንበት አገር መቅረባቸውን ስለ ሰማን አባቴ የሰጡኝን ሁለት በቅሎዎችና ስንቅ ይዘን እሳቸው ጭምር «ሱጴ » እስከምትባል አገር ድረስ አብረን ሄድን ከራስ ጋር ተገናኘን።

«ልጅዎ ያለ ስራው ከወታደር ጋር ዘማች ሆኖ እንደሚያዩት ካገር አገር ይዞራል። አሁን በደህና ከርሶ ጋር አገናኝተነዋልና ከንግዲህ መክረው ከርስዎ ጋር እንዲቀር ያደርጉት » አሉዋቸው ራስ አባቴን ተቀብለው ሲያነጋግሩዋቸው። ከልባቸው ይሁን ወይም የሚሉትን ለመስማት እንደሆን አላውቅም።

«እንኩዋንስ እሱን ከኔ ጋር እንዲቀር ልመክረው ባልሸመግል ኖሮ እኔም አብሬው ብሄድ በወደድሁ ነበር! » አሉ አባቴ። ካባቴ ጋር ስሰነብት የጦርነቱ ነገር በተነሳ ቁጥር «የኢትዮጵያ አምላክ እግዚአብሔር ይርዳችሁ! » ከማለት በቀር አንድም ቀን ከጦርነቱ ቀርቼ ከሳቸው ጋር እንድቆይ እንኩዋንስ በቀጥታ ሊጠይቁኝ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተያይተውኝ አያውቁም። ስለዚህ ያንለት «ለይስሙላ » ሳይሆንን ንከልባቸው ነበር የተገናገሩት። ራስም ያ ጊዜ አልፎ ነፃነታችን ከተመለሰ በሁዋላ እንኩዋ ተገናኝተን ስላባቴ ጤንነት ሲጠይቁኝ፤ ያንለት ያሉዋቸውን እንዳልደረሱት ይነግሩኝ ነበር፡

የሆለታ መኮንኖችና ወታደሮች እንዲሁም ካዲስ አበባና ከልዩ ልዩ ቦታዎች እየሸኙ አብረዋቸው የቆዩት የጦርም፥ የሰላምም ሰዎች ባንድነት ተሰልፈው ከራስ ጋር የተገናኙ ባልሳሳት እዚያ ‹ሱጺ› ላይ ይመስለኛል። አዛዡ ኮሎኔል በላይ ሀይለ አብ የተባለ አጠር ያለ ቆፍጣና ወጣት መኮንን ነበር። የሰልፈኛውን መዝሙር እየመራ የሚያይዘመር «ይልማ መንገሻ » የተባለ ዘለግ ያለ ጠይም ጠጉረ ላዛ ነበር። ይልማ መንገሻ አምቦ የርሻ ትምህርት ቤት ዲሬክተር የነበረ መሆኑን ሰማሁ። ይልማ መንገሻ ካኪ ሱሪና ሸሚዝ ብቻ ለብሶ የተመዘዘ ጩቤውን በቀኝ እጁ ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ይዞ «እረደው! » ሲኢል ጩቤውን ገደም አድርጎ የማረድ ምልክት እያሳየ «በለው! » ሲል ጩቤውን ዘቅዝቆ የመውጋት ምልክት እያሳየ።

«እረደው እረደው አታርደውም ወይ

ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ! »

«በለው በለው አትለው ወይ፥

ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ!

«ኧረ በለው ኧረ በለው አትለውም፥ አይ

ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ! »

እያለ፥ ላቡ በፊቱ ሲወርድ ከሩቅ እየታየ፤ የመዝሙሩን ቅኝት የተከተሉ በዚያ ረዥም ቁመቱ ሲደረግ፤ የተቀባዩን ሰልፈኛ ብቻ ሳይሆን የተመልካቹን ስሜት ጭምር ማርኮ አብሮት ያስገረገርው ነበር! ያ ትርኢት በውነት እንዴት ግሩም ነበር! እንዴት ልብን በወኔ የሚያሞቅና፤ ሞትን የሚያስንቅ ነበር! እኔ ብረሳው ይሆናል እንጂ መዝሙሩ ይህ፤ እዚይ የተጠቀሰው ብቻ አይመስለኝም፤ ይህ «አዝማቹ » ሳይሆን አይቀርም።

ከሰልፉና ከመዝሙሩ ትርኢይት በሁዋላ የሆለታ መኮንኖች ወደ ራስ ቀርበው በየስማቸውና በየማእረጋቸው ተዋወቁ። ከዚያ ድርጅታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የራስን ትእዛዝ ለነሱ እነሱ የሚፈልጉት ጉዳይ ቢኖር ለራስ

እያስተላለፉ የሚያስፈፅሙ አማካይ መኮንን (ለየዞን) ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ መሆናቸውን ሰማሁ። የሆለቶች ጦር ከራስ ጦር ጋር ከተጨመረ በሁዋላ በጠቅላላ ሰራዊቱ በብዛት ብቻ ሳይሆን በጥራት ጭምር የተሻለ እንደ ሆነ አይጠረጠርም። ግን ብዛቱ እጅግም አልነበር ግፋ ቢል አንድ ሽህ ያክል ቢሆን ነው። ያን ያክል መሆኑም የሚያጠራጥር ነው እጉዞ ላይ በትእዛዝ ይሁን ወይም እነሱ ፈልገው እንደሆነ አላውቅም ሁልጊዜ የጦር ሰራዊቱኡን ግንባር ይዘው ሲዋጉ የማይ ሆለቶችን ነበር። አንድ ቀን ሆለቶች ቀድመው ሌላው ሰራዊት ተከትሎ ከደዲሳ ሸለቆ አፋፍ ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን አንድ መጠነኛ ዳገት አጠገብ እንደ ደረስን እስሩ ከነበረው ጫካ ውስጥ ተዝናንቶ በሚጉዋዘው ሰራዊት ላይ ተኩስ ተከፈተ። ተኩሱን የከፈቱት የወለጋ አገረ ገዥ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም የክቡር ራስ እምሩን ሰራዊት እንዲወጋ ከላኩት ጦር ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ወዲያው በበቅሎ የነበረው እየወረደ ከግረኛው ጋር ባንድነት ሆኖ ተኩስ ወደ ተከፈተበት ቦታ ሩጫ ሆነ። ግን እኒያ የተኮሱት ጥቂት ሰዎች በተሸሸጉበት ጫካ ውስጥ ምንም ያክል ሳይቆዩ እየዞሩ እየተኮሱ ዳገቱን ወጥተው ሲሄዱ ይታዩ ነበር።

ሆለቶችና ከራስ ሰዎችም ቀደም ያልነው ተኩስ የከፈቱን ሰዎች እየተከተልን ሮጠን ከዳገቱ አናት ላይ ስንደርስ ከዳገቱ ጀርባ ቁልቁለቱን ወርደው ከስሩ ያለውን ዛፍና ቁጥቋጦ የለበሰ ወንዝ ተሻግረው ከማዶ አቀበት ላይ «ጉይ? » ከሚባለው ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ባለው ጫካ እየሮጡ ሲገቡ አየናቸው።

መቾም ጠላቶቻችን ያቀዱት የጦርነት እቅድ ግሩም የሆነ እቅድ ነበር! እዚያ ከቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ባለው ጫካ ውስጥ ብዙ ከባድና ቀላል መሳሪያ ጠምደዋል! ከስሩ ባለው ወንዝ ውስጥ ብዙ ባለ መትረየስና ለባለ ልዩ ልዩ መሳሪዒኢያ ጦር አስተኝተዋል! ዋናዎቹ ወጥመዶች እኒህ ከቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያና በወንዙ ውስጥ የተጠመዱት ናቸው። ታዲያ ወጥመዶቻቸውን እንዲህ አድርገው ካስናዱ በሁዋላ እወጥመዶቹ ውስጥ እኛን ስቦ የሚያገባላቸው አንድ ቡድን ወደ ፊት ልከው በኛ ላይ እየተኮሰ እንዲሸሽ አድርገዋል። የተላከብን ጦር የደጃዝማች ሀብተ ማርያም ይሁን እንጂ ያን እቅድ ያቀዱት ጣሊያኖች መራሳቸው ወይም እነሱ የጦርነት እቅድ ያስተማሩዋቸው ሰዎች መሆን

አለባቸው! እቅዱ አስቀድሞ ያልተጠነቀቀን ጠላት ሲስት የማይችል እወጥመዱ ውስጥ እንዲያገባ ሆኖ የታቀደ ስለ ነበረ አሳባቸው ተሳካላቸው እወጥመዳቸው ውስጥ ገባንላቸው! ቀድመን እዳገቱ አናት የደረሰውም እኛን ተከትለው የደረሱትም ሮጠው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የገቡትን ሰዎች ብቻ እያየን እነሱን ለመከተል ከዳገቱ አናት ወርደን እደረቱ ላይ ሆነን ደረታችንን እንደ ሰጠን ከማዶ ቤተ ክርስቲያን በከባድና በቀላል መሳሪያ የተተኮሰ ጥይት እንደ መዓት ይወርድብን ጀመር። ያን ጊዜ የሞተው ሞቶ የቆሰለው ቆስሎ ደህነኛው በየዛፉና በየቁጥቋዋጦው ስር ተገን ፈልጎ ያልወደቀ አልነበረም። እንዳጋጣሚ ባጠገቡ ስለ ነበርሁ ቆሞ ያየሁት ኮሎኔል በላይ ሀይለ አብን ብቻ ነበር። ከማዶ የሚተኮሰው የልዩ ልዩ መሳሪያ ጥይት ከፊት ከሁዋላ ከቀኝ ከግራው እንዲያ እንደ መአት እየወረደ በዙሪያው የነበረውን የዛፍ ቅርንጫፍ ሁሉ እንዲያ እየገነጣጠለ ቁጥቁዋጦውን ሁሉ እንዲያ እያብጠለጠለ ሲጥል ከዚያ መሀል ኮሎኔል በላይ የተመዘዘ፤ ያዛዥ ሰይፉን በቀኝ እጁ ከትከሻው ዝቅ አድርጎ ዘርግቶ፤ ትንሽ እንኳ ስቅጥጥ ሳይል ዝም ብሎ ፊት ለፊት ያይ ነበር! ተኩሱ ፀጥ እስኪል ተገን ይዞ እንዲቆይ ከተኛሁበት ዛፍ ስር ጠርቼ ለመንገር ካሰብሁ በሁዋላ በቅጡ ያልተለማመድን ከመሆናችንም ሌላ «ምናልባት ስልታቸው ቢሆን ይሆናል » ብዬ ልናገር ያሰብሁትን መልሼ ዋጥሁት። ትንሽ ቆይቶ ተኩሱ ጋብ ያለ ሲመስል በላይ ያዛዥ ሰይፉን ከትከሻው ዝቅ አድርጎ ከያዘበት ሁሉም እንዲያ ሽቅብ ከራሱ በላይ አውጥቶ እንደገና ወደ ፊት ወነጨፈና «አናቫ! » (ወደፊት) አለ በጣ ጮሆ። ወዲያው አጭር ቁመናው በፈቀደለት መጠን እርምጃውን አስረዝሞ ወደ ፊት ስሄድ በየዛፉም በየቁጥቁዋጦውም ስር ተገን ይዞ የነበረው ሁሉ ከያለበት እየወጣ ወደ ፊት ሩጫውን ያዘ። ያን ጊዜ እንደገመትሁት ኮሎኔል በላይ ያን ትእዛዝ የሰጠ እዳገቱ ደረት ላይ የነበርንበት ቦታ ከማዶ ለሚተኩስብን ጠላቶቻችን ምቹ አድርገን ስለ ነበረ፥ ከዚያ ወርደን ወንዙን የያዝን እንደ ሆነ እሱን ተገን አድርገን ብርቱ ጉዳት ሳይደርሰን ጠላቶቻችንን ከስር ለማጥቃት እንደምንችል በማመን ሳይሆን አይቀርም። አሳቡ ትክክል ይመስላል። ጠላቶቻችንም እንዲሁ እንደሚታሰብ ስላወቁ ነው፥ እቅዳቸውን ሲያቅዱ እዳገቱ ደረቱ ላይ የሚገኝ ሁሉ ከማዶ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ከሚተሶስበት ተገን ፍለጋ ሸሽቶ ወደ ወንዙ መሄዱ የማይቀር በመሆኑ

ተቀብሎ የሚፈጅ ጦር እዚያ ወንዝ ውስጥ መሸሸጋቸው። እኔም ወደ ወንዙ ሩጫ ከጀመሩት ጋር ስሮጥ ከማልፍበት ቁጥቋጦ ውስጥ ጣእር የሚያስጨንቀው ድምፅ «ሀዲስ » ሲል ስለሰማሁ ድምፁን ወደ ሰማሁበት ቁጥቋጦ ዘወር ብል ጣሰው አይችሉህም እዚያ ወድቆዋል።

ጣሰው፥ የመኮንንነት ትምህርት ለመከታተል ወደ ሆለታ ከመሄዱ በፊት ምኒልክ ትምህርት ቤት፥ እኔም ተፈሪ መኮንን ትምርት ቤት በነበርንበት ጊዜ ተዋውቀን የሩቅ ጉዋደኝነት ነበረን። ቀረብ ብየ ሳየው አንድ ታፋው ተገንጥሎ ቆዳው እንደ ያዘው በጐኑ ወደ ወገቡ አፈንግጦዋል! ራሱ ተዘቅዝቆ እንደ ወደቀ ላቡ እንደ ውሀ ፊቱን ያጥበዋል ካፉና ካፍንጫውም ደም ይወርዳል! ያን ጊዜ ወንዙን ለመያዝ የሚሮጠው የኛ ጦር እስኪጠጋቸው ድረስ እዚያ ውስጥ አንጥፈው የሚጠብቁት የጠላት ሰዎች ገና ተኩስ አልከፈቱም ነበር። ስለዚህ ጣሰው ቆስሎ የወደቀው ቀደም ብሎ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ካለው ጫካ ውስጥ በተተኮሰ የከባድ መሣሪያ ጥይት መሆን አለበት። ወዲያውም የጠመንጃ ወይም የመትረየስ ጥይት እንዲያ አድርጎ ሊገነጥል የሚችል አይመስልም። ታዲያ እኒዔ ቁስለኛ የመርዳት ልምድ የሌለኝ አይመስልም። ታዲያ እኔ ቁስለኛ የመርዳት ልምድ የሌለኝ ስለ ነበርሁ የማደርገው ቅጡ ጠፍቶኝ ስርበተበት፥

«እባክህ ትንሽ ቀና አድርገኝ » አለ በደከመ ድምፅ።

ከወደቀበት ቦታ አንድ ሜትር ያክል ራቅ ብሎ አንድ ትልቅ ዛፍ ስለ ነበረና ጣሰው ከኔ የሚበልጥ በመሆኑ ተሸክሞ ወደዚያ መውሰዱ ስላቃተኝ ከላይ ሁለት ብብቶቹን ገብቼ ይገፎ እየሳብሁ ወስድሁና ቀና አድርጌ የዛፉን ስር ሳስደግፈው ጭንቀቱ ትንሽ ቀለል ያለለት መሰለ። ታፋውም እንደ ተለያዬ ይሁን እንጂ፣ ትንሽ ወደ ወገቡ ወጥቶ፤ ወጥሮት የነበረው ወደ ታች ወረድ ስላለ ከሁኔታው ስመለከት ውጥረቱ ያስከተለው ስቃይ የተቀነሰለት መስሎ ተሰማኝ። እኔ ጣሰውን ስረዳ ከግርጊያችን እወንዙ ውስጥ የተነሳው ተኩስ የቁዋያ እሳት የተቃጠለ ይመስል ነበር! ብቻ እንዲያ እንደሆነ ብዙ አልቆዬ፤ ትንሽ በትንሽ ከወንዙ እየራቀ ሄደ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የተፋፋመ ተኩስ ሲሰማ ቆየና ከዚያም ጠፋ። ጣሰውን ቀና አድርጌ የዛፉን ስር አንተርሸ አስተኝቼ፤ ካፉና ካፍንጫው የወጣውን የረጋ ደም በገዛ መሀረሙ

ከጠራረግሁለት በሁዋላ፤ ከዚያ አልፌ ምንም ሊያደርግለት የማይችል ስለ መሰለኝ፤ ሆለቶች ጉዋደኞቹ የተሻለ ርዳታ ሊያደርጉለ ቢችሉ ሄጄ ለነሱ ለመንገር ጠመንጃየን ካኖርሁበት ሳነሳ አይቶ፤

«ውሀ አጠጣኝ » አለ በዚያ በደካማ ድምፁ።

የዛፉን ስር ለማንተራስ ስስበው ኮዳውን ከያዘበት ወስጄ ባጠገቡ አኑሬለት ስለ ነበረ፥ አንስቼ ባየው ባዶ ነው። ጣሰው በወደቀበት ቁጥቋጦና በወንዙ መሀል አንድ ትንሽ ሜዳ አለች። እወንዙ ውስጥ ተኩሱ አቁሞ ስለ ነበረ፥ ከዚያ ላመጣለት ጠመጃየን እንዳነገትሁ ኮዳውን ይዤ ሮጥ ሮጥ እያልሁ ከቁጥቋጦው ወደ ሜዳው ብቅ ስል ከወንዙ ውስጥ ብዙ ጥይት እሩምታ ስለ ተተኮሰብኝ ወደቅሁ። ግን የተተኮሰብኝ ጥይት እንዳያገኘኝ ነው እንጂ አልተመታሁም። በወደቅሁበት እንዳለሁ ቆይቼ ተኩሱ ሲቆምልኝ በጉብሴ ወደ ጣሰው ተመለስሁ። ተቁዋርጦ እወንዙ ውስጥ የቀሩ የጠላት ወታደሮች እየተኮሱ አላስቀርበኝ ስላሉ ውሀ ለማምጣት አለመቻሌን ለጣሰው ነገሁት። ወዲያው ዶክተር አለመ ወርቅ መጣና ጣሰውን እዚያ ተኝቶ፥ እኔን ከፊቱ ቆሜ ሲያይ፤

«ጣሰው ቆስሎ ነው? » አለ፥ ደንግጦ። ዶክተር አለመ ወርቅ የከብት ሀኪም መሆኑን ቀደም ብየ ሰምቻለሁ።

«አዎ፥ ከፉኛ ቆስሎዋል » አልሁት። ወዲያው ጐንበስ ብሎ ታፋውን ካየና የልቡን ትርታ ሲያዳምጥ ትንሽ ከቆየ በሁዋላ ፊቱ በሀዘን ከብዶ ራሱን እየወዘወዘ ቀና ሲል፥

«አለመ ወርቅ፤ ውሀ አጠጣኝ፤ ተቃ - ጠልሁ » አለ ጣሰው፤ ደካማ ድምፁን ጣእር እየጎተተው።

«ኮዳው ውሀ አለበት? » አለኝ ዶክተር።

«የለበትም፤ ከወንዙ ላመጣ ብሞክር፤ እዚያ ተቁዋርጠው የቀሩ የጠላት ወታደሮች እየተኮሱ አላስቀርበኝ ስላሉ፤ ሳልደርስ ተመልሼ መጣሁ። »

«ጠመንጃህን ይዘህ ኖሮዋል የሄድህ? »

«አዎ! »

«እስቲ ስጠኝ እኔ ልሞክር » አለና ዶክተር አለመ ወርቅ ጠመንጃውን አኑሮ፥ ኮዳውን ከኔ ተቀብሎ ቁጥቋጦውን ወጣ አለ። ወዲያው ሰላማዊነቱን ለማሳየት ኮዳ የያዘ እጁንም ባዶ እጁንም ከራሱ በላይ ዘርግቶ እያሳየ ሜዳውን ሊገባ ሲል ልክ በንደኔ እንደ ተደረገው እሩምታ ተተኮሰበት። ወደ ቁጥቋጦው መለስ ብሎ ቆይቶ እንደገና ወደ ሜዳው ብቅ ሲል፥ አሁንም ተተኮሰበት። ከዚያ በሁዋላ እሱም ተስፋ ቆርጦ ባዶውን ተመለሰ። ዶክተር ከመመለሱ ከያነለት በፊት እቃ በኩታዋ እያዘለች ከሆለቶች ጋር ስትጉዋዝ አያት የነበረች ሴት መጣችና፤

«ጋሼ ጌታየ ለኔ ባደረገው! እኔ አፈር በበላሁ! » እያለች ከጣሰው ፊት ተንበርክካ ስጥጮህ፤

«እባክሽ ውሀ አጠጭኝ » አላት ለኔም ለዶክተር አለመ ወርቅም እንዳለው። ወዲያው ያቺ ሴት ኮዳውን ከዶክተር አለመ ወርቅ እጅ ነጥቃ ወንዙ ስትሮጥ፤

«ወንዙን የጠላት ወታደሮች ይዘው እየተኮሱ ስላላስቀረቡን ነውና የተመለስን አትሂጂ ይገድሉሻል » አላት ዶክተሩ። ሴትየዋ ግን እንኩዋንስ ልትመለስ የተናገረውን መስማትዋንም እንጃ! ዝም ብላ እየሮጠች ከቁጥቁዋጦው ወጥታ ወደ ሜዳው ዝቅ ስትል በኛ እንደ ተተኮሰብን እሩምታ ተተኮሰባት። እስዋ ግን እንደኛ በመመለስ ፋንታ ኮዳዋን አንጠልጥላ ወደ ሚተኩሱባት ሰዎች ሩጫዋን ቀጠለች። እኒያ ሰዎችም ሴት ስለ ሆነች እንደሆነ፥ ወይም በሌላ እስካሁን ላውቀው ባልቻልሁ ምክንያት ተኩሳቸውን አቁመውላት ውሀውን ቀድታ ተመለሰች። ዶክተር አለመ ወርቅና እኔ የዚያችን ሴት ጀግንነትና የኒያን ሰዎች መንፈሰ - ለጋስነት አይተን፤ በጣም ተደነቅን! ሴትየዋ ከጣሰው አፍ ደሙን ጠራርጋ ካመጣችለት ውሀ ትንሽ ካጠጣችው በሁዋላ፤ በረዥሙ ተንፍሶ፤ ሲወራጭ ቆየና አይኑን ገበብ አድርጎ ፀጥ አለ። አይቺ ጀግና ሴት፤ ለጣሰው ምኑ እንደነበረችና ስምዋ ማን እንደሚባል ያን ጊዜ ዶክተር አለመ ወርቅን ሳልጠይቀው መቅረቴ ሲያስፀፅተኝ ይኖራል።

«እስቲ እንዲህ ርዳታ ሊያገኝ ወደ ሚችልበት የሚያደርሱ ሰዎች ፈልጊሌ እስኪልክልሽ ድረስ አብረሽው ቆይ » ብሎዋት ዶክተር አለመ ወርቅ እኒኢያ ተቁዋርጠው የቀሩት የጠላት ወታደሮች ከነበሩበት ከፍ ብለን ወደ ወንዙ ሄድን። እዚያ ወንዝ ውስጥና ዳርዳሩን፥ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ሞተውም ቆስለውም ወድቀው የሚታዩት የኛና የጠላት ሰዎች ብዙ ነበሩ። በዚያ የጨበጣ ጦርነት ከራስ መኩዋንንትና ከወታደሮች የሞቱትንም የቆሰሉትንም ቁጥራቸውን አላስታወሰውም እንጂ በርከት ያሉ ነበሩ። ከሆለቶች ውስጥም፥ የሞቱና የቆሰሉ - ወታደሮች ሳይቆጥሩ - መኮንኖች ብቻ ስምንት መሆናቸውን ሁዋላ ሰዎች ነገሩኝ። ከሞቱት መሀከል ጣሰው አይችሉህም ዶክተር አለመ ወርቅና እኔ እንደ ተለየነው ወዲያው ህይወቱ ስላለፈ፥ እኔ ያየሁዋቸው እሱንና «አሰፋ ወልደ ሰማያት » የተባለውን ወጣት መኮንን ነበር። የጣሰው አይችሉህምና ያሰፋ ወልደ ሰማያት ሞት ምንም ቢሆን አይረሳኝም። ምክንያቱም ጣሰውን ከያንለት በፊት አውቀው የነበረ ነው ሞት ጋር ፊት ለፊት ተፋጥጣ ውሀ ቀድታ ከተመለሰች ጀግና ሴት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። አሰፋ ሁዋላ ሰዎች እንደ ነገሩኝ ሆለቶች ነቀምት በነበሩ ጊዜ ቡናይ ላይ ያረፈውን የጣሊያን አይሮፕላን ከቃጠሉትና ነጂውን አብረው ከነበሩት ብዙ የጣሊያን መኮንንኖች ጋር ከፈጁት የሆለታ መኮንኖች አንዱ ከመሆኑ በላይ፥ ያንለት የሞተበት አሀሁዋን ሊረሳ የማይችል በመሆኑ ነው። አሰፋ ወልደ ሰማያትና አንድ ቀይ ሽበቶ መኮንን የጨበጣ ሲዋጉ አሰፋ ሽበቶውን መኮንን ደረታቸውን በሽጉጥ መትቶዋቸው እሳቸው በጎራዴ ግንባሩን ፈልጠውት፥ እንደ ተያዙ ባንድ ላይ ወድቀው ሲታዩ «ወንድማሞች ያንድ እናት ልጆች፤ ምን ሰይጣን በመሀከላችን ገብቶ እስበሳችን እንድንጋደል አደረገን! » እያሉ በመሀከላቸው ገብቶ ያጋደላቸውን ሰይጣን ባንድነት የሚረግሙና ይቅርታ የሚለማመኑ ይመስሉ ነበር! እኒያ ቀይ፤ ሽበቶ መኮነን የደጃዝማች ሀብተ ማርያም አጋፋሪ የነበሩ መሆናቸውን ‹እናውቃለን› የሚሉ ሰዎች ሁዋላ ነገሩኝ።

ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ዘመናዊና ሀገራቸውን የሚወስዱ ሰው የነበሩ መሆናቸውን ብዙ በቅርብ እናውቃቸዋለን የሚሉ ሰዎች ሲናገሩ እስማ ነበር። ዘመናዊ አስተሳሰባቸውን ባሰራር የሚተረጉሙ ለመሆናቸውም ባገራቸው ትምርት ቤት መክፈት የሚፈልጉትን ሚሲዮናውያን ከማበረታታቸው ሌላ

ገንዘብ እየከፈሉ ብዙ የወለጋ ልጆች ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሲያስተምሩና ትምህርት ቤቱን በገንዘብ ሲረዱ እንደ ነበረ እኔም ስለማውቅ ይህ ሁሉ ዘመናዊ ሰው የነበሩ መሆናቸው የሚያስረዳ። እንዲሁም ከሆለታ መኮንኖች ጋር ከተለማመድን በሁዋላ አንዳንዶቹ እንደ ነገሩኝ ለነሱና ከሱ ጋር ለሀገራቸው ነፃነት ለመታገል ከየቦታው ተጠራቅመው ወደ ነቀምት ለሄዱት ሁሉ፥ እዚያ በቆዩበት ጊዜ የወር ደመወዝ እየከፈሉና በምክርም በሌላ በሚያስፈልጋቸው ጉዳይ ሁሉ እየረዱና እያበረታቱ ማቆየታቸው ሀገራቸውን የሚኢወዱና ለነፃነትዋ የሚያስቡ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። ታዲያ እኒያ ዘመናዊ አስተሳሰብ የነበራቸው እንደ መሆናቸው መጠን የነፃነትና የባእድ ተገዥነትን ልዩነት የሚያውቁ ሰው እኒያ ሀገራቸውን ወዳጅና ለነፃነትዋ የሚያስቡ እንደ መሆናቸው መጠን ለሀገራቸው ነፃነት የሚታገሉት ሁሉ ‹ርዳታና ድጋፍ ያደርጉልናል› ብለው ተስፋቸውን ያሳረፉባቸው ሰው ለኢትዮጵያ ነፃነትና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ደህንነት የሚታአገለውን የክቡር ራስ እምሩን ሰራዊት የሚወጋ ጦር መላካቸው ስለሳቸው ሲነገርና ሲታመንም ከኖረው መልካም ነገር ሁሉ ጋር ይስማማ ነበር።

ነፃነታችን ከተመለሰ በሁዋላ ካንድ የወለጋ ትልቅ መኮንን ጋር ይህን ነገር አንስተን ስንነጋገር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም፥ ጦርነቱን እስከ መጨረሻ ለመቀጠል ቆርጠን እንደ ነበረና አሳባቸውን እንዲተው ያስገደዱዋቸው ያባታቸው ትልልቅ መኳዋንንት እንደ ነበሩ ነገሩኝ። «መኳዋንንቱ » አሉ የወለጋው መኮንን «መኳዋንንቱ ንጉሠ ነገሥቱ የመሩትን የኢትዮጵያ ሰራዊት በሙሉ ድል ካደረገው ሀይለኛ ጠላት ጋር ገጥሞ ጦርነቱን መቀጠል፥ አገርን ከማስጠፋትና ህዝብን ከማስበደል በቀር የኢትዮጵያን ነፃነት ሊያስመልስ አይችልም » ብለው ባንድ ቃል ስለ ተቃውሞዋቸውና ህዝቡም የነሱን አሳብ እንዲከተል ቀስቅሰውት ስለ ነበረ፥ ከጥቂት አሽከሮቻቸው ጋር ብቻ በመቅረታቸው የመጀመሪያ አሳባቸውን ለመተው ተገደዱ።

ይህ ሊሆን ይችላል። ያን ጊዜ ባልተያዙት አገሮች የነበሩት አገረ - ገዥዎች ሁሉ ሰራዊታቸውንና ህዝባቸውን ባንድነት አስተባብረው ካልተነሱ ለየብቻቸው ዘመናዊ መሳሪያ ከታጠቀ ሀይለኛ ጠላት ጋር ጦርነቱን ለመቀጠል ቢሞክሩ ሀገርህን ከማስጠፋትና ህዝብን ከማስበደል በቀር፤ የኢትዮጵያ ነፃነት

ማስመስለ የማይችሉ መሆናቸውም እውነት መሆኑ ታይቶዋል። ነገር ግን ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ከዚህ በላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ጦርነቱን ለመቀጠል የነበራቸውን አሳብ ለመተው ቢገደዱም፤ እኒህን ምክኒያቶች ለራስ ገልፀው ወደ ወለጋ እንዳይሄዱ፤ የወለጋ መንገዳቸውን ለውጠው ወደ ሌላ እንዲሄዱ ሊልኩባቸው አይችሉም ኖሮዋል? ጦር ሲልኩ ኢትዮጵያውያን ወንድማሞች እስ በሳቸው እንደሚጋደሏልታያቸውም ኖሮዋል? ያሳዝናል!

የሆነ ሆኖ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ከላኩት አር ተቋውርጠው ከቀሩት እወንዙ ውስጥ አንጥፎ የነበረውም ከቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ከባድና ቀላል መሳሪያውን ጠምዶ ባአገሪ ሲያጠቃን የነበረውም ባጭር ጊዜ የሞተው ሞቶ የተረፈው ተርፎ ባንድነት የደጄሳን ሸለቆ ወርዶ ሄደ። ከዚያ በሁዋላ የተኩስ ድምፅ አልተሰማም።

ራስ፥ ከሁዋላ ደርሰው ወንዙን ከላይ በኩል ሊሻገሩ ከታች በኩል ተቋዋርጦ የቀሩ ጥቂት የጠላት ወታደሮች መኖራቸውን ሲሰሙ «ባላምባራስ ልመንህ » ይባል የነበረውን የጭፍራ አለቃ መኮንናቸውን አስጠርተው እኒያን ሰዎች «እሺ » ቢሉ እጃቸውን እንዲሰጡ ደጋግሞ ጥሪ እንዲያደርጉላቸውና የሰላም ጥሪውን የማይቀበሉ ከሆነ ባሉበት እንዲጨርሳቸው ትእዛዝ ሰጥተውት አለፉ። ሁውላ ባላምባራስ ልመንህ እንደ ነገረኝ እጃቸውን እንዲሰጡ ከማስጠንቀቂያ ጋር ተደጋግሞ የተደረገላቸውን የሰላም ጥሪ ባለመቀበላቸው እወንዙ ውስጥ እንዳሉ ተከበው ያለቁት፥ ጊዜው ጠላቶቻችን ያደረጋቸው ወንድሞቻችን አሥራ ሁለት ነበሩ።

የሞቱትን ለመቅበርም ለቆሰሉት ህክምና ርዳታ ለመስጠትም እንዲመች ጦርነቱ ከተደረገበት አቅራቢያ ሰፈር ማድረግ አስፈላጊ ስለ ነበረ ከጉይ ቤተ ክርስቲያን ግርጌ ሰፈር ሆኖ ሙታኑ እንዲቀበሩና ቁስለኞች እንዲታከሙ ተደረገ። ከያነለት ጀምሮ ረዳቶች ተደርገውላቸው ለቁስለኞች የህክምና ርዳታ ሲሰጡ አይ የነበረ ወይዘሮ ስንዱ ገብሩንና ያቶ ይልማ መንገሻን እህት ወይዘሮ? (ወይዘሪት?) ጽጌ መንገሻን ነበር።

## ምዕራፍ አስራ ሰባት

# ከጉይ እስከ ጉማ

ጉይ ላይ በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያውያን ተባብረው የጋራ ጠላታቸውን በመውጋት ፈንታ፥ እስ በሳቸው ተዋግተው መጋደላቸው እጅግ የሚያሳዝንና እንዳይደርስ ለማድረግ የሚቻል ነበር። ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ከክቡር ራስ እምሩ ጋር ተባብረው ጠላትን ለመውጋት የማይችሉበት ምክንያት ያጋጠማቸው መሆኑን ገልፀው ራስ ወደ ሳቸው እንዳይሄዱ ቢልኩባቸው ኖሮ፥ ወይም ክቡር ራስ እምሩ ስለ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም አቋዋምና በጠቅላላው ስለ ወለጋም ሆነ ስለ አካባቢው ህዝብ አሳብ የሚያስተማምን መረጃ ሳይገኝ እንዲሁም ዝም ብለው ወደ ወለጋ ጉዞዋቸውን ባይጀምሩ ኖሮ ጉይ ላይ ጦርነት ተደርጎ ኢትዮጵያን እስ በሳቸው አይጋደሉም ነበር። የደጃዝማች ሀብተ ማርያምን አቋዋም አጣርቶ ለማወቅ ወደ ወለጋ ወሰን ቀረብ ብሎ ማዳመጥ አስፈላጊ መስሎ ቢታይ እንኩዋ በጦርነት ጊዜ እንደሚደረገውና ከጉይ ጦርነት በሁዋላ በኛም ዘንድ ማድረግ እንደ ተጀመረው ከሰራዊቱ ቀድመው መንገዱና አካባቢው ካደጋ ነፃ መሆናቸውን እያሰሱ የሚያረጋግጡ፥ ቃፊሮች ማድረግ በተገባ ነበር። ነገር ግን እንዲያ ያለ ጥንቃቄ ባለመደረጉ፥ ጠላታችን ከፊታችን ተሰልፎ እንደሚጠብቀን ሳናውቅ ባጠመደው ወጥመድ ገብተን ያ ልናመልጠው እንችል የነበረና ሊደርስብን የማይገባው ጉዳት ደረሰብን።

ሌላው በኛ፥ በኩል የነበረ ጉድለት በቂ ስንቅና ትጥቅ ሳይኖረን «ጠላታችንን በረዥም ጦርነት አድክመን ካገራችን እናስወጣለን » ብለን ስንነሳ ክቡር ራስ እምሩ ክረምቱን ሙሉ ጎሬ ሲከርሙ ለስንቅም ሆነ ለትጥቅ አይነተኛ አለኝታችን የሆነው የዚያ ክፍል ህዝብ እንዲተባበረን ምንም የተደረገ ቅስቀሳ አለመኖሩ ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብ በቅኝ አስተዳደር ውስጥ ኖሮ ስለማያውቅ፤ በነፃነትና በቅኝ አስተዳደር መሀከል ያለውን ልዩነት የሚያቁት ጥቂት ይሆናል። ስለዚህ የቅኝ አስተዳደር ህዝቡን ላገሩ፥ ለሀብቱ፥ ለጉልበቱ ለሙብቱ ባለቤት እንዳይሆን የሚያደርግና ባንፃሩ እኛ ይህ ሁሉ ፈጣሪ ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰጠው ፀጋ እንዳይወስድበት ለዚህ ሁሉ ባለቤት እንደሆነ እንዲኖር የምታገል በመሆናችን የዚያ ክፍል ህዝብ ለራሱ ሲል በሀብቱ በጉልበቱ፥ በህይወቱ እንኩዋ፥ እንዲተባበረን ቅስቀሳ ማድረግ ይገባን ነበር። ግን አላደረግንም። እንዲያውም እንዲተባበረን በመጣር ፈንታ አንዳንድ ጊዜ ከኛ የሚሸሽበትን መንገድ ስንከፍትለት እንታይ ነበር። ለምሳሌ፡- ከጉይ ጦርነት በሁዋላ፤ ሰፈር በተደረገበት ዙሪያ የሚኖረውን ህዝብ ከብቶች ወታደሮችን እንደ አውሬ በጥይት ገድለው መብላታቸውና እመንደርም ገብተው ነዋሪዎችን ማስቸገራቸው ሲታወቅ እንዲያ ባደረጉት ወታደሮች ላይ እኑዋንስ ቅጣት ተግሳጥ አልደረሰባቸውም። ምክንያቱን ከወታደሮች አለቃ አንዱን ብጠይቃቸው «ጠላቶቻችን ከቤተ ክርስቲያኑ ዙሪኢያ ምሽግ ሰርተውና ከባድ መሳሪያ ጠምደው ከወንድዙ ውስጥም የተደራጀ ጦር አስተኝተው እኛን የሚያጠፉበትን እቅድ ሁሉ ሲያቅዱ በሰፈሩ ዙሪያ ያለው ህዝብ እያዩ ሌላው ቢቀር እንድንጠነቀቅ ምልክት ሊሰጠን ይችል ነበር። ነገር ግን በጠላቶቻችን ወጥመድ እስክንገባ ዝም ብሎ ተመለከተን። እና እንዲያ ማድረጉ የነሱ ተባባሪ ቢሆን ነውና ከጠላቶቻችን ለይተን የምናይበት ምክንያት የለም » ግን የወታደሮች አለቃ እንዳሉት «ህዝቡ ሌላው ቢቀር እንድንጠነቀቅ ምልክት ይሰጠን » የነበረ፤ ለሱ ጥቅመ የቆምን መሆናችነን አስረድተን እንዲተባበረን፥ አስቀድመን ጥረት ብናደርግ ነበር እንጂ፥ ያን ባለማድረጋችን ስላልተባበረን «ህዝቡን እንቀበል » ማለት ጠላት ከማብዛት በቀር ሌላ ትርፍ እንደሌለው ጉይ ብቻ ሳይሆን ከጉይ በሁዋላ በሄድንበት ሁሉ እስከ መጨረሻው፥ ወሬ ነጋሪ እንኩዋ አጥተን በጉይ የደረሰብን ሲደጋገም አዬን።

የከቡር ራስ እምሩ ሰራዊት ከጉይ ጦርነት ከሁዋላ በሰፈረበት ቦታ ሁለት ቀናት ያክል ቆይተን ተመክረና ወደ ወለጋ ተጀምሮ የነበረው ጉዞ ሳይታሰብ ድንገት በተደረገው ጦርነት ምክንያት አቅጣጫውን ወደ ጅማ እንዲያዞር ስለ ተወሰነ፥ ወደ ጅማ ጉዞ ተጀመረ። ወዲያውም ሰራዊቱ በዬለቱ

ጉዞውን ከመጀመሩ ሶስት ሰዓት ያክል እዬቀደሙ እየሄዱ የሚያልፍበት መንገድ ከአደጋ ነፃ መሆኑን እያሰሱ እንዲረጋገጡ «ፊታውራሪ ከበደ ያዘው » እና «ቀኛዝማች (ሁዋላ ፊታውራሪ) ደጀኔ ርገጤ » መመደባቸውን ሰማሁ። ሁለቱ በጀግንነታቸው የታወቁ የጭፍራ አለቆች ለቃፊርነት መመደባቸው «ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ » እንደሚሉት፤ ጉዳት ከደረሰብን በሁዋላ ከመሆኑ በቀር መቸም ለወደፊቱ መልካም የጥንቃቄ ዜዴ መሆኑ የታወቀ ነው። ግን ለኔ ያን ጊዜ «ለወደፊቱ » የሚባለው ነገር ትንሽ የተስፋ ብልጭታ የማይታይበ ጨለማ ሆኖ ነበር የሚታዩኝ።

በጉይ ጦርነትና ከዚያ በሁዋላ አቅጣጫችነን ወደ ጅማ አዙረን መጉዋዝ ከጀመርንበት ቀን ጀምሮ መንገድ ለመንገድ የተመለከትሁት ሁሉ ጦርነቱን በማስረዘም ጠላታችነን አድክመን ካገራችን ማስወጣት እንደምንችል የነበረኝን ተስፋ ከተስፋ ደረጃ አውርዶ ከንቱ ምኞት አደረብኝና ተስፋ ቢስነት ባዶነት ተሰማኝ! ዙረታችን ድካማችን ሞታን ሁሉ አላማ የለሽ ሆኖ ታዬኝ!

እስከዚያ ጊዜ ድረስ ተፅፎ ያነበብሁትም ባፍ ሲነገር የሰማሁትም «ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ እስበሳቸው አዬተጣሉ የተዋጉ ቢሆንም የውጭ ጠላት ሲመጣባቸው የስበሳቸውን ጥል ወደ ጎን ትተው እዬተባበሩ ከውጭ የመጣ የጋራ ጠላታቸውን መቃወም በማወቃቸው ያገራቸውን ነፃነት አስከብረው ለመኖር ቻሉ » የሚል ስለ ነበረ ያን አምኘ እኖር ነበር። ነገር ግን ያን ጊዜ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሳትወር በጉይ ጦርነት ስለ ኢትዮጵያም የጋራ ጠላት ስለሆነቺው ፋሽስት ኢጣሊያም ሆነው የሞቱ ኢትዮጵያውያን ብቻ መሆናቸውን ላይ በምናልፍበት መንገድ አቅራቢያ ከሚኖረው ህዝብ፥ የሚበዛው ቤቱን እዬዘጋ ከኛ ሲሸሽ ያልሸሸው በወገንነት ሳይሆን በጠላትነት አይን ሲመለከተን ሳይ ጫካችን እኛን ከጠላት በመተገን ፈንታ፥ የሚወጉንን በውስጡ እዬሸሸገ ሲያስወጋን ላይ የሚበቃ ስንቅና ትጥቅ ባይኖረንም ህዝባችን መግቦ ጫካችን ተግኖ ለመጨረሻ ድል እንዲያበቁን የነበረኝ ተስፋ ጥሎኝ ጠፋ።

«ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ኢትዮጵያን ለመያዝ በዬጊዜው የመጡትን ባእዳን መንግስታት ጣሊያንን ጭምር ኢትዮጵያውያን ተባብረው ድል እየመቱ

ያገራቸውን ነፃነት አስከርበው ኖረዋል። ታዲያ ያ ያስተባብራቸው የነበረው ያገር ፍቅር አሁን የት ደረሰ? ወዴት ጠፋ? ያሁኑን ትውልድ ምን ነካው? » እላለሁ፥ የወደፊቱ ተስፋ ሲጨልምብኝ አሳቤ ወደ ሁዋላ ተመልሶ በትግራይ እነ ደጃዝማች ሀይለ ስላሴ ጉግሳ በጎጃም እነ ደጃዝማች ገሰሰ በለው በወለጋ እነ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር፥ እዚያ መንገድ ለመንገድ ህዝቡ፥ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት ከመጣው የጋራ ጠላት ጋር መተባበራቸውን አንድ ባንድ ይቆጠርና ከዚያ ኢትዮጵያ ትታየኛለች! ኢትዮጵያ ከስታ ተንገላታ ተጎሳቁላ እያለቀሰች ትመጣና «እዩኝ እንዲህ ሆንሁ! አምሮብኝ ተከብሬ ታፍሬ እኖር የነበርሁይቱ፥ አሁን በናንተ ጊዜ እንዲህ ሆንሁ! » ብላ ልጆችዋን ኢትዮጵያውያንን ስትወቅስ ስትማጠን፤ ስትረግም ትታየኛለች።

ያን ጊዜ ከጉይ ተነስተን ወደ ጅማ ስንሄድ መንገድ ለመንገድ፥ «የኢትዮጵያ ልቅሶ » በሚል ርእስ አንድ ግጥም ገጥሜ ልጅ ፈቃደ ስላሴ ህሩይ እንግሊዝ አገር ደርሰው ሲመለሱ ባመጡት የማባዣ መኪና እያበዛን በሰራዊቱ መከልም በሌላ ተቀባይ በተገኘበት ቦታም ሁሉ እንበትን ጀመር።

ያን ግጥም «ልጅ (ሁዋላ ጀኔራል) ነጋ ሀይለ ስላሴ » ሱዳን በስደት በነበረበት ጊዜ ለወይዘሮ አበባ ፈለቀ ሰጥቶዋቸው ኖሮ፥ የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በሁዋላ እኔም ከጣሊያን እስር ቤት በ1936 የዛሬ አርባ አራት ዓመት ግድም መሆኑ ነው እንደ ተመለስሁ ወይዘሮ አበባ ከሱዳን መጥተው አዲስ አበባ ነዋሪ መሆናቸውን ሰምቼ ልጣይቃቸው ስሄድ አሳዩኝ። ታዲያ ያን ጊዜ ሲያሳዩኝ በማባዣው መኪና በተባዛው ላይ ከስሩ ጄኔራል ነጋ፥ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አብረው ስለ ነበርን ስለኔ ሰፋ አድርጎ እስከ ዛሬ በጃቸው ይኖር እንደሆነ እንዲሰጡኝ ወይዘሮ አበባን ጠይቄያቸው ያን ጊዜ ያሳዩኝን ፈልገው ስላጡት በደብተር ገልብጠው ያስቀመጡትን ሰጡኝ።

ግጥሙ በማዘዣ ከተባዛው ወደ ደብተር ሲገለበጥ፥ አንዳንድ የተዘለሉ ቃላት መኖራቸው ከንባቡ የሚታወቅ ከመሆኑና አንዳንድ ቦታም የፊቱ ሁዋላ የሁዋላው ፊት እዩሆነ ከመገልበጡ በቀር፥ በጠቅላላው ያው የኔ ግጥም ነው። ስለዚህ ከደብተሩ ያገኘሁትን ሳነብ የጎደሉትን ቃላት ያስታወስሁዋቸውን

ያለዚያም መሰላቸውን ሞልቼ ቦታ የተለዋወጡትንም በዬቦታቸው አስጨምቸ ላንባቢዎች አቅርቤዋለሁ። እንዲሁም ጀኔራል ነጋ ሀይለ ስላሲኤ ስለኔ ካተተው፥ የውዳሴውን ክፍል ትርፍ ስለመሰለኝ ትቼ ከግጥሙ ጋር የተዛመደውን ክፍል ብቻ እንደ መቅድም እንዲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ፅፌዋለሁ።

«ሀዲስ አለማዬሁ፣.......... የኢትዮጵያ መንግስት በፈረሰ ጊዜ ከራስ እምሩ ጋር ሆኖ ስለ ነፃነቱ በሚጋደልበት ጊዜ ቆሞም ተቀምጦም፥ ተኝቶም የሚያቃጥለው ያገር ፍቅር ልቡን እዬቀቀለው እንፋሎት እየገነፈለ አይኑን እንባ እዬሞላ ስለቸገረው በናቱ ስም «የኢትዮጵያ ልቅሶ » ብሎ ሀዘኑን ለወንድሞቹ ለኢትዮጵያውያን ለማካፈል ሲል በንባው የፃፈልንን የሚከተሉትን ቃላት ለሀሳባችሁ መሰረትና መሪ ይሆኑዋችሁዋል ስንል ተካፋይነታችነን እያረጋገጥንላችሁ፤ ሀዘኑን በጎደለ ሞልተን ፅፈንላችሁዋል »።

## የኢትዮጵያ ልቅሶ

፩. «ልጆቼ በማመን፥ ባለመጠርጠር፤

የሚደፍረኝ የለም፤ ይመስለኝ ነበር።

«ግን አሁን ተደፈርሁ ላልቅስ፥ እርሜን ላውጣ፤

ጀግኖች ያለቁብኝ፤ ስለሆንኩ አይቶ አጣ።

«አድምጡኝ ልጆቼ ላስጠንቅቃችሁ፤

ሳምናችሁ ብትከዱኝ ስመካባችሁ፤

ዘላለም ውርደት ነው ደመወዛችሁ።

አየ ዋዬ ልጆቼ እየ ዋዬ ከዳችሁ ወዬ።

፪. «ጀግና አልተተካም ወይ፥ በቴዎድሮስ ስፍራ፤

ጎበዝ አልቆመም ወይ በዮሀንስ ስፍራ፤

ሰው የለበትም ወይ በምኒልክ ስፍራ፤

ጠላቴ ሲወርረኝ ከቀኝ ከግራ፤
የሚሰማኝ ያጣሁ ብታራ ብጣራ።
ወይ እኔ ኢትዮጵያ የጀግኖች እናት፤
ሁሉም አለቁና ትተው ባዶ ቤት፤
ደርሶብኝ የማያውቅ አገኘኝ ጥቃት።
አየ ዋዩ ልጆቼ አየ ዋዩ ከዳሁኝ ወዩ።

፫. «ገንዘብ እዩዘራ ሲመጣ ጠላት፤
ከማታለል ጋራ፥ ውሸት ስብከት፤
ባጠመደው ወጥመድ እንድትገቡለት፤
ተንኮሉን ሳታውቁ መስሎዋችሁ እውነት፤
በግ ካራጁ ሁዋላ እንደሚጎተት፤
ትጎተታላችሁ፥ እናንተም ለሞት።
አየ ዋዩ ልጆቼ አየ ዋዩ ከዳችሁኝ ወዩ።

፬. ገንዘብ ተበድሮ አሁን ሲሰጣችሁ፤
ሁጊዜም እንደዚያው የሚያደርግ መስሎዋችሁ፤
እንዳትታለሉ ሁዋላ ወዮላችሁ።
አሁን ገንዘብ ሰጥቶ እንዳትታገሉት ካረገ በሁዋላ፤
እንኩዋንስ የራሱን ገንዝቡን ሊያበላ፤
የናንተም ይሄዳል ይሰጣል ለሌላ።
አየ ዋዩ ልጆቼ አየ ዋዩ ከዳችሁ ወዩ።

፭. አሁን ቢሰጣችሁ ገንዘብ ተበድሮ፤

በጁ ስትገቡለት እንዲህ ጥሮ ግሮ፤
ከዚያ በሁዋላ ክንዱን አጠንክሮ፤
ያጠፋውን ገንዘብ አንድ ባንድ ቆጥሮ፤
ይቀበላችሁዋል ወለዱን ጨምሮ።
አየ ዋዬ ልጆቼ አየ ዋዬ ከዳችሁ ወይ።

፮. አይ ሞኞች ተላላዎች ሆይ፤
ደሙን የሚያፈስው በሰው አገር ላይ፤
እናንተን ለማክበር መሰላችሁ ወይ።
አሁን ስነግራችሁ ቢመስላችሁ ዋዛ፤
በሁዋላ መከራው ስቃዩ ሲበዛ፤
ሞትን ብትፈልጉት በወርቅ አይገዛ፤
አየ ዋዬ ልጆቼ አየ ዋዬ ከዳችሁኝ ወዬ።

፯. ፀፀቱ ይውጣልኝ እስቲ ልንገራችሁ፤
ምናልባት ብትሰሙኝ ትንሽ ቢቆጫችሁ፤
ጠመንጃው ጥይቱ እያለ በጃችሁ፤
ዱሩ ሸንተረሩ ሳለ በደጃችሁ፤
አሁን ጊዜ ሳያልፍ ካልተጋደላችሁ፤
ይህን ሁሉ በጁ ካረገ በሁዋላ አጥቂው ጠላታችሁ፤
ቢጭኑት አጋሰስ ቢያርዱት ሰንጋ ናችሁ።
አየ ዋዬ ልጆቼ አየ ዋዬ ከዳችሁኝ ወዬ።

፰. ከዚህ ወዲያ በቃኝ መከሬያችሁዋለሁ፤

ለኔም ለናንተም ሞት፥ እርሜን አውጥቻለሁ፤

መከሬያችሁዋለሁ ሳይጠነክር አቅሙ፤

የናትነት ምክሬን ቃሌን ብትፈፅሙ፤

እግዜር ይባርካችሁ አብቡ ለምልሙ፤

ግን ይህን ጩኸቴን ልቅሶየን ባትሰሙ፤

በመልእልተ መስቀል የፈረሰው ደሙ፤

ርጉም ያድርጋችሁ እስከ ዘላለሙ።

አየ ዋዬ ልጆቼ አየ ዋዬ ከዳችሁኝ ወዬ »

ኮሎኔል በላይ ሀይለ አብ ጭፍሮቹ ሁሉ እንዲሰበስቡለት ካደረገ በሁዋላ ያን ግጥም ይዞ አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ይቆምና ወይም ከፍተኛ ቦታ በሌለበት አንድ ዛፍ ላይ ይወጣና ግጥሞችን አንብቦ «አዝማቹ » ላይ በደረሰ ቁጥር ትግሬ እንደ መሆኑ «ዋይ ዋይ፥ ልጆቼ ዋይ ዋይ ከዳችሁኝ ወይ » ሲል በጋለ ስሜት እጆቹን አንስቶ እዬነቀነቀ ምንም እንኩዋ ነገሩ የሚያሳዝንም የሚያበሳጭም ቢሆን፥ «ጥርስ ባእድ ነው » እንደሚሉት እንዳንታይ አፋችነን በጃችን ከድነን፥ በዚያ ከግር እስከራሱ ወኔ ብቻ በሆነ ጎበዝ እንስቅበት ነበር።

ከጉይ ተንስተን የኢሉባቦርን ግዛት አልፈን ጅማ ውስጥ «ጉማ » ከሚባለው ክፍል እስክንደርስ ስንት ቀን እንደወሰደብን ረስቸዋለሁ ምናልባት አንድ ሳምንት ወይም ከዚያ የበለጠ ጊዜ ወስዶብን ይሆናል። የሆነ ሆኖ በተጉዋዝንበት መንገድ አቅራቢያ ይኖር የነበረው ህዝብ፥ የጠላት ስብከት እኛን አስጠልቶት ይሁን ወይም ጉይ ላይ ወታደሮቻችን የህዝብ ከብቶች ገድለው መብላታቸውና እመንደር ገብተው ማስቸገራቸው ተሰምቶ አስፈርቶት ይሁን አይታወቅም፤ ቤቱን እዬዘጋ ከኛ ይሸሽ ነበር። ያልሸሸውም ለኛ በጎ ፈቃድ ያለው ስላልነበረ በምንሄድበት አገር ምን እንደ ሚቆዬን ወሬ ነጋሪ ባለማግኘታችን ሳናውቅ እንዲሁ «እውር ድንበራችነን » ነበር የምንሄድ።

የጉዞዋችን አቅጣጫ ከወሊጋ ወደ ጅማ እንዲለወጥ የተወሰነበት አላማ፥ ከቡር ራስ እምሩ ከጅማው እንደራሴ ከከንቲባ ጋሻው ጠና ጋር ተመካክረው ጠላትን በህብረት ወግቶ ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የሚያስችል እቅድ ለማቀድ ነበር። ነገር ግን ጣሊያንን ከኢትዮጵያ ስለምናስወጣበት መንገድ ለመመካከር የምንሄድባቸውን ከንቲባ ጋሻው ጠናን፥ ጉማ ጫካ ውስጥ አግኝተናቸው የጅማ ከተማ በጣሊያኖች የተያዘ መሆኑንና እሳቸው ከተማውን ለቀው ጫካ ከገቡ በርከት ያሉ ቀናት ማለፋቸውን የሰማነው ከከንቲባ ከራሳቸውና አብረዋቸው ከነበሩት ነበር። ጅማ እስከንደርስ የጅማን መያዝ አናውቅም ነበር። እዚያ ጫካ ውስጥ ከከንቲባ ጋሻው ጠና ጋር፤ ከሰዎቻቸው ሌላ ያገኘናቸው መኳዋንንትና ህዝቡም በጣም ብዙ ነበሩ። ከመኳዋንንቱ መሀከል ትዝ የሚሉኝ (ሌሎችም ይሆናሉ) የክብር ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ወንድም (ወይም ቅርብ ዘመድ) ፊታውራሪ አጥናፍ ሰገድ ወልደ ጊዮርጊስ የክቡር ራስ አደፍርሰው ልጅ ቀኛዝማች መኮንን አደፍርሰውና ብላታ ታከለ ወልደ ሀዋርያት ነበሩ። ወዲያው በተገናኘንበት እለት ይሁን፥ ወይም በማግስቱ (ቀኑን ረስቻለሁ) ራስና ከንቲባ ከሌሎች ታላላቅ የጦርና የሰላም (ሲቪል) መኳዋንንት ጋር ዘለግ ያለ ስብሰባ አድርገው ቆይተው ተነሱ። መቸም እንዲያ ባለው የታላላቆች ስብሰባ ለምክድር የቀረቡት ጉዳዮች ምን እንደ ነበሩና ምን እንደተወሰነ እርግጠኛውን ማወቅ አይቻል። አንዳንድ «ጭምጭምታ ሰማን » ያሉ ሰዎች እንዳወሩትና ሁዋላ ሲሆን ከታዬው መገመት እንደሚቻለው ግን ምክር የተደረገባእው ጉዳዮች «የጅማን ከተማ የያዘውን የጣሊያን ጦር እንምታ? ወይስ እሱን ትተን ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ ወዳሉበት፤ ወዳልተያዘው አገር ወደ ከፋ እንሂድ? » የሚሉት ሲሆኑ የተወሰነው ጅማ ያለውን የጣሊያን ጦር ከመምታት ወደ ከፋ እንድንሄድ ነው። ከስብሰባው እንደተነሱ ብላታ ታከለ ወልደ ሀዋርያት ሰዎቻቸውን ይዘው ተለይተውን ሄዱ። ወዴት እንደሄዱ አላውቅም። ከዚያ በሁዋላ ጭራሹ አላዬሁዋቸውም። የተወራው ወሬ ግን «እስብሰባው ላይ በተወሰነው ውሳኔ ስላልተስማሙ በሌላ ክፍል ካሉ አርበኞች ከነ ሻለቃ (ሁዋላ ራስ) መስፍን ስለሽ ጋር ሆነው ትግሉን ለመቀጠል ሄዱ » የሚል ነበር።

ከነከንቲባ ጋሻው ጠና ዙሪያ ተሰብስቦ ጫካውን ሞልቶት ያገኘነውና እኛም ከደረስን በሁዋላ እዬመጣ በላይ በላዩ ይጨምር የነበረው ከያገሩ በየምክንያቱ እየሄደ እዚያ ክፍለ - ሀገር ይኖር የነበረ ከልዩ ልዩ ዘር የተጠራቀመ ህዝብ ሲሆን ከዚያ የሚበዛው አማራነት ያለው ነው። በጠቅላላው ከዚያ ስደተኛ ህዝብ መሀከል ደምኅ ሽማግሌው ባልቴቱና ህፃኑ ይበዛ ነበር። ታዲያ እጉዞ ላይ ራሳቸውን ካልቻሉ ህፃናት በቀር ያ ሁሉ ወንዱ ከቤቱ ጋር ያልተወውን ለስደቱ የሚያገለግለውን ቁሳቁስ ጠቅልሎ በራሱ ወይም በትከሻው ተሸክሞ ፍየሉን በጁ ስቦ ወይም ዶሮውን በቅፉ ታቅፎ ይሄዳል። ሴትዋ ልጅዋን ወይም ምጣድዋን በጀርባዋ አዝላ አገልግልዋን ወይም ሌላ እቃዋን በጅዋ አንጠጥላ ትሄዳለች። ታዲያ ለዚያ ሁሉ ህዝብ መንገዱ አልበቃው ብሎ እየተተራመሰ ጫካ እዬጣሰ፥ አሞዋቸው ሲላቀሱ ያን ረብሻ ጫጫታ ያን ሁኔታ በጊዜው በቦታው ላይ ተገኝቶ መመልከቱ ብቻ ሳይሆን፤ ካለፈም በሁዋላ ትዝታው፤ የሚያሳዝን የሚዘገንን ነው።

«ያን ሁሉ ህዝብ አንዳንዱ ካባት ከናቱ ጀምሮ አንዳንዱም ራሱ ሄዶ ስራ እዬሰራ ቤት ንብረት መስርቶ ዘመድ ወዳጅ አበጅቶ የኖርንበትን አገር አስለቅቆ እንዲያ ባለ ችግር ውስጥ የጣለው ምንድነው? ተብሎ ሲኢጠየቅ ያን ጊዜ ሲነገሩ የሰማሁዋቸው ምክንያቶች ሁለት ነበሩ። አንዱ ምክንያት «ያገሩ ህዝብ ከሌላ አገር እዬሄደ እዚያ የሚኖረውን በተለይ አማራውን እንዲለቅ ስላስገደደው ነው » የሚል ነበር። ሁለተኛው ምክንያት «አባ ጀቢር » የተባሉት ያገሩ ባላባት፤ ያገሩ ተወላጅ ያልሆነው ሁሉ ካገራቸው እንዲያስወጣላቸው በተለይ አማራውን ግን ራሱን እዬቆረጠ ለሚወስድላቸው ሽልማት ላንድ ያምራ ራስ ሰላሳ (30) ብር እንደሚሰጡ ላገሬው በይፋ ስላስታወቁና ያንዳንድ ሰዎች ራስም ስለተቆረጠ፥ አማራው ራሱ እንዳይቆረጥ ሌላው ‹ዛሬ ባማራው የደረሰው ነገ በኔ ይደርስ ይሆናል› ብሎ ፈርቶ መሸሹ ነው » የሚል ነበር። ከነዚህ ከሁለት ምክንያቶች የትኛው እውነት እንደሆነ ማረጋገጥ አልቻልሁም በግምት ግን ሁለተኛው ምክንያት እውነት ይመስላል።

አፄ ሀይለ ስላሴ እስከ ነገሱበት ጊዜ ድረስ የየክፍለ ሀገሩ አይተኛ ባላባቶች፤ ከቅድመ - ቅድመ - አያቶቻቸው ጀምሮ ተያይዞ የወረደውን የዘር

ሀገር ሳይልቁ በያገራቸው በግዛት ላይ የሚኖሩ ነበሩ። አፄ ሀይለ ስላሴ ከነገሱ በሁዋላ ከኒያ ባላባቶች ብዙዎች ከግዛታቸው እንዲነሱ ተደርጎ፥ በነሱ ቦታ ካዲስ አበባ እንደራሴዎች እየተሾሙ ስለ ተተኩ በተሻሩት ባላባቶች ብቻ ሳይሆን በያገራቸው ህዝብ መሀከል ጭምር ጠቅላላ የቅርታ ስሜት ተፈጥሮ እንደ ነበረ ህዝብ መሀከል ጭምር ጠቅላላ የቅርታ ስሜት ተፈጥሮ እንደ ነበረ በምዕራፍ፥ 3 ያ በያገሩ ባላባቶች እዬተሻገሩ አዳዲስ የተናገሩትን አንባቢዎች ያስታውሳሉ። ስለዚህ አባ ጆቢር የጅማ ባላባት እንደ መሆናቸው «ግዛቱ እንደ ቆየው ልማድ ከኔ ቤት መውጣት የለበትም ከኔ ቤት ወጥቶ ካዲስ አበባ ለተላከ ባእድ መስጠቱ በደል ነው » ብለው በመንግስት ላይ ቂም ቢይዙ፥ በጊዜው ግዛታቸው የተወሰደባቸው ባላባቶች ሁሉ ያዘኑበት ጉዳይ ስለነበረ ላይፈረድባቸው ይችል ይሆናል። ነገር ግን በመንግስት ላይ የያዙትን ቂም በተራው ህዝብ ላይ ባላባቶች ሲገዙ የነሱ ታዛዥ ይኖር በነበረው ተራ ህዝብ ላይ ጭምር መወጣት «የሚገባ ነው » ይባል እንደ ሆነ ፍርዱን ላንባቢ መተውን እመርጣለሁ።

## ምዕራፍ አስራ ስምንት

# ጌራ

የክብር ራስ እምሩ ሰራዊትና ከከንቲባ ጋሻው ጠና ጋር የነበረው እጅግ ብዙ ስደተኛ ህዝብ ጉማ ላይ ተገናኝቶ፤ ከዚያ ወደ ከፋ ለመሄድ በጀመረው ጉዞ ጌራ እስኪደረስ ያለፈበት መንገድ ከምንዜውም የከፋ አስመራሪ ነበር። መንገዱ የሚያልፈው አንድ ቦታም ሳይቋዋረጥ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ነበር። ጠላት ጠመንጃና ጥይት ሰጥቶ እኛን እንዲወጉ እዚያ ደን ውስጥ የሰገሰጋቸው ብዙ ምንደኞች የሆኑ ወገኖቻችን ከቀኝና ከግራ ሲተኩሱብን እንደሚተኮሰው የጥይት ብዛት የተረፈ ሰው የሚኖር አይመስልም ነበር። ነገር ግን እኔ እንዳየሁትና ከሌሎችም እንደ ሰማሁት እዚያ መንገድ ለመንገድ በተደረገብን

ተኩስ በሰዋችን የደረሰውን የሞትና የመቁሰል ጉዳት «ከባድ » የሚባል አልነበረም።

«ቀን ሲከፋ ቀን ሲከዳ፤

ዘመድ ይሆናል ባዳ።

«ቀን ሲከፋ ሲቸገር፤

አገር የሰው አገር »

ይላሉ በገና ደርዳሪዎች። ስለዚህ ቀን ከፋብንና ቀን ከዳንና «የጋራ ጠላታችንን ድል መትተን አገራችንን ነፃ ለማድረግ በምንዋጋው ጦርነት ይተባበሩናል » ብለው ሙሉ እምነታችንን ያሳረፍንባቸው ወገኖቻችን - ወደው ይሁን ተገድደው አላውቅም - የጠላት ረዳቶች ሆነው ወገኑ! ከጠላታችን ጋር በምናደርገው ረዥም ጦርነት «ሸሽጎ ተገን ሆኖ ለመጨረሻ ድል ያበቃናል » ብለን የተማመንበት ደናችንም፤ በየዋህነት የጠላት መሳሪያ ለሆኑት ምንደኞች መሸሸጊያ ሆኖ አስወጋን።

ከዚያ መንገድ፥ ለመንገድ ብርቱ ተኩስ ከተደረገብን ቀን በፊት በነበረው ሌሊት ጉዋደኛየ በትረ ፅድቅ ካሳ፥ ታምሞ አድሮ ስለ ነበረ፥ በተኩስ ቀን እሱን በበቅሎየ አስቀምጨ እኔ ጠመንጃየን አንግቼ፥ የኮርቻውን ድህራ ይዤ እየተነጋገርን እንሄድ ነበር። ራስ በባለበቅሎዎች መኩዋንንትና በግረኞች ታጅበው በበቅሎ ተቀምጨው ከኛ ትንሽ ራቅ ብለው ፊት ፊት ይሄዱ ነበር። ያ ብርቱ ተኩስ ይብስ እየበረታ መሄዱን በትረ ፅድቅ አየና፤

«አንተ ሀዲስ ራስ እምሩ ሰው እንደሚያከብራቸው ጥይትም የሚያከብራቸው መስሎዋቸው ነው ይህ ሁሉ ጥይት እየተተኮሰ በበቅሎ ተቀምጠው የሚሄዱ? ይልቅ ተኩሱ በረድ እስኪል ወርደው ቦታ ቢይዙና የሚተኩሱብንን ከጫካው ውስጥ እንዲያባርር ለወታደሩ ትእዛዝ ቢሰቱ አይሻልም? » አለኝ።

«እውነትህ ነው፤ ይሻል ነበር » አልሁት።

«ታዲያ ለምን ሄደህ ይህኑ ለፊታውራሪ ፈንታ አትነግራቸው? » አለኝ። ፊታውራሪ ፈንታ ራስ ከሚወዱዋቸውና ከሚያከብሩዋቸው መኰዋንንታቸው አንዱ ነበሩ። በትረ ፅድቅ ተኩሱ በረድ እስኪል ራስ ከበቅሎ ወርደው ቢቆዩ የሚሻል መሆኑን ለኔ መንገር ከጀመሩ ትንሽ ቀደም ብለው ከመኰዋንንቱ መሀከል ከበቅሎዋቸው ወርደው ጠመንጃቸውን አንግተው ሄደው የራስን የኮርቻ ደሀራ ይዘው እያነጋገሩዋቸው መሄድ ጀምረው ነበር። ሄጄ ከሁዋላቸው ነካ አድርጌ በትረ ፅድቅ የነገረኝን ስነግራቸው፤

«ስለሱ ነው የምነጋገረው » አሉኝ ፊታውራሪ። እኔ ዘወር ከማለቴና ራስም ከበቅሎ ወርደው እግራቸው ሁለተኛውን ርካብ ለቅቆ መሬት ከመንካሩ ተቀምጠውባት የነበረችዋ በቅሎ በምንደኞች ጥይት ተመትታ እፊታቸው ወደቀች። ያን ጊዜ በበቅሎ የነበረው ከበቅሎ እየወረደ እግረኛው መንገዱ እየተው ሁሉም ተገን ይዞ ለመቆየት ወደየዛፉ ስር ሄደ። እመንገዱ ላይ የቀሩ በትረ ፅድቅና የኔ በቅሎ ብቻ ነበሩ። በትረ ፅድቅ ከበቅሎዋ ወርዶ ፊቱን ወደስዋ አዙሮ ሊስባት ቢሞክር «ገረገረችና » እስዋም ወደ ሁዋላ ትስበው ጀመር። እንዲያ እሱ ወደ ፊት በቅሎዋ ወደ ሁዋላ እየተሳሰቡ በዚያ ተኩስ መሀል እዚያ ገላጣ መንገድ ላይ ስለ ቀሩ ሁላችንም ከያለንበት በቅሎዋን ለቅቆ ወዳንድ ዛፍ እንዲጠጋ ጮኸንበት ነበር። ነገር ግን በትረ ፅድቅ ከበቅሎዋ ጋር እልከ እንደ ተጋባ ሁሉ ከስዋ ጋር የገጠመውን ትግል እንጂ በዙሪያው የሚወርደውን የጥይት አመትም ሆነ የኛን ጩኸት ከቁም ነገር የጣፈው አይመስልም። ደግነቱ እዚያ ጫካ ውስጥ ተሰግስገው የሚተኩስብንን ምንደኞች፥ ወታደሩ ገብቶ እንዲመታ ታዝዞ ገብቶ ሲገጥማቸው እነሱ እየሸሹ ወታደሩ እየተከተለ ተኩሱ ከኛ እየራቀ ሄደና መንገዱ አማን ሆነ።

«እኔም ሌሎችም ያን ያክል እየጮህንብህ ለምን በቅሎዋን ለቅቀህ እንደ ሁላችን ተገን ፍለጋ አልሄድህ? » ብየ በትረ ፅድቅን ሁዋላ ብጠይቀው፤

«ስለ ታመምሁ አንተ በግርህ እየሄድህ የሰጠኸኝን በቅሎ ለቅቄያት ጥይት ቢገድላት ወይም ብትጠፋ ያንተንም የህሊናየንም ወቀሳ የማልችለው ስለ መሰለኝ ነው » አለኝ። በትረ ፅድቅ ካሳ የህሊናውንና የሰው ከሰውም ይልቅ የህሊናውን ወቀሳ የሚፈራውን ያክል ሞትን የማይፈራ ቆራጥ ሰው ነበር!

ወታደሩ እዚያ ጭካ ውስጥ ተሰግስገው ይተኩሱብን የነበሩትን የጠላት ምንደኞች ካስለቀቀልን በሁዋላ የጠመኛ ድምፅ ሳንሰማ፥ ጫካውን ጨርሰን እገላጣው ክፍል ደረስን። በዚያ ጫካ ውስጥ እንጉዋዝ በነበርንበት ጊዜ ሁሉ የጠላት አይሮፕላኖች አልተለዩንም በላያችን ይመላለሱ ነበር። ነገር ግን ከስራቸው እጫካው ውስጥ መሆናችንን ቢያውቁም ያለንበትን በትክክል ለይተው ሊያዩ ባለመቻላቸው ቦምብ አልጣሉብንም። ያ ጫካ ካንድ ወገን ወገን በጠላት ለተገዙ ምንደኞች መሸሸጊያ ሆኖ ሲያስወጋን ቢውልም ከሌላ ወገን ሰራዊታችንን ያን ከጉማ ጀምሮ የተደረገብንን እጅግ ብዙ ስደተኛ ህዝብ ከጠላት አይሮፕላኖች በመሸሸጉ ካሰን። ሰራዊቱና ያ ሁሉ ብዙ ህዝብ የሚጉዋዝበት መንገድ በጫካ ውስጥ ባይሆን ኖሮ፤ ግልጥ ቢሆን ኖሮ እኒያ በላያችን ያለ ማቋዋረጥ ሲመላለሱ የዋሉት አይሮፕላኖች ብርቱ ጉዳት ያደርሱብን እንደ ነበረ አይጠረጠርም።

ከጫካው እንደ ወጣን እንደ መጠነኛ ኮረብታ አልፈን፥ ከስሩ ያለውን ጫካ የለበሰ ወንዝ ተሻገርንና ሌላ ከላይ እስከ ታች በረዥሙ ጉብ ያለ ለሰፈርነት የሚስማማ ቦታ ስለ ተገኘ እዚያ ሰፈርን። ያ የሰፈርንበት ቦታ ሰውም ከብትም እስሩ ካለው ወንዝ ውሀ እንደ ልብ የሚያገኝበት ከመሆኑ ሌላ እንዳልፍነው ጫካ ጥቅጥቅ ያለ አይሁን እንጂ ብዙ ቅልልቅና ትንንሽ ዛፎች የሸፈኑት ስለ ሆነ፥ አይሮፕላኖች ከላይ ኢላማቸውን አነጣጥረው ለመምታት የሚመች አልነበረም። ከትንንሾቹ ዛፎች የሚወዳደር ደገላ ሳርም ሞልቶበት ነበር። ያ ቦታና አካባቢው ከጅማ ግዛት ውስጥ «ጌራ » የሚባለው ክፍል መሆኑን ሰዎች ነገሩኝ።

ሰራዊታችንና አብሮት የሚጉዋዘው ስደተኛ ሕዝብ ቀኑን ሙሉ ፋታ ሳያገኝ የዋለበትን የሚያስመርር ጉዞ ጨርሶ በሰፈረበት ቦታ፥ ደህና እረፍት አግኝቶ አደረ። በማግስቱ እንጋት ላይ ቃፊሮች ፊታውራሪ ከበደ ያዘውና ቀኛዝማች ደጀኔ ርገጤ ከሰዎቻቸው ጋር እንደ ተለመደው ሰራዊቱ የሚጉዋዝበትን መንገድ አማንነት ለማረጋገጥ ቀድመው ሄዱ። ቆየት ብሎ ስደተኛው ህዝብና ከሰራዊቱም «ጉዋዝ » የሚባለው ክፍል ተከትሎ መንገድ ያዘ። ራስ ከደረቅ ጦራቸው ጋር ቀድመው የሄደው ብዙ ህዝብና ጉዋዙ እስኪርቅና መንገዱ ነፃ እስኪሆንላቸው ወደ ሁዋላ ቆዩ። አብሮዋቸው ከቆዬው

ሰራዊት መሀከል ቁርሱን አድርጎ ጨርሶ፥ ለጉዞ የሚሰጠውን ምልክት የሚጠባበቀውም ገና ቁርሱን ያልጨረሰውም ነበረ። ሰራዊታችን በዚያ ሁኔታ እንዳለ ከወንዙ ወዲያ ማዶ ካለው ኮረብታ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ተሰማ። ወዲያው ተኩሱ ከተሰማበት አቅጣጫ፥ አንድ «ዥም - ዥም - ዥም » የሚል ነገር አየሩን እየሰነጠቀ መጥቶ እሰፈራችን ላይ ፈነዳ። ጠላት የተኮሰብን የመድፍ እርሳስ ነበር! ከዚያ ሁለተኛው ከዚያ ሶስተኛው ከዚያ - ስንት እንደ ሆነ እግዜር ይወቅ እየተከታተለ ከማዶው ከዚያ - ስንት እንደ ሆነ እግዜር ይወቅ እየተከታተለ ከማዶው ኮረብታ በተተኮሰ ቁጥር የመድፉ እርሳስ እንደ ፊተኛው እየተውዠመዠመ እየመጣ እሰፈራችን ላይ ሲፈነዳ እንደ መጋዝ ስለታም ስብርባሪው በዙሪያው ያገኘውን የዛፍ ቅርንጫፍ ሁሉ እየቀነጣጠሰ ይጥለው ጀመር። ያን ጊዜ አደጋው ያልተጠረጠረ ድንገተኛ ስለ ነበረ በሰራዊታችን መሀከል መደናገር የተፈጠፈ መስሎ ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ የመድፉ ተኩስ ባያቋርጥ፤ «ታጠቁ » ምልክት የሆነው ጥሩንባ ሲነፋ ያ ጊዜያዊ መደናገር አለፈና ሁሉም ቀዋሚ ስራቱን በመከተል ወደየቡድን አለቃው እየሄደ ተሰብስቦ የሚሰጠውን ትእዛዝ በመጠባበቅ ላይ እንድለ «የጠላት ወታደር! የጠላት ጦር! የጠላት እግረኛ ጦር! » የሚል ድምፅ ከያቅጣጫው ተሰማ።

እውነትም በጣም ብዙ የጠላት እግረኛ ጦር ከማዶው ኮረብታ እየወረደ ከስራችን ያለውን ወንዝ ለመያዝ ዘቅዝቆ ይሽቀዳደማል! ግንባር ቀደሙ እንዲያውም እወንዙ ለመድረስ ተቃርቦዋል! ያን ሲያዩ የሆለታ መኮንኖችና ወታደሮቻቸው ከራስ ሰዎችም በከፊል ከጠላት ቀድመው ወንዙን ለመያዝ እነሱም እሽቅድድም ገጠሙ።

ወዲያው የራስ ድንኩዋን ከነበረበት አጠገብ አንድ ወርካ ይሁን ወይም ወርካ የሚመስል ትልቅ ዛፍ ስለ ነበረ የመድፉ እርሳስና የቦምብ ፍንጣሪ እንዳይገባ፥ የዛፉ ስር በግንባርም በቀኝና በግራም ግንድ እየተጐራረደና ከረጢት አፈር እየተሞላ ሰፋ ብሎ ታጥሮ ራስ እዚያ ሆነው፥ ወደ ግንባር ለሚሄዱት እንዲሄዱ ተራቸው እስኪደርስ በደጅግንነት ተቆጥበው ለሚቆዩት እንዲቆዩ ትእዛዝ እየሰጡ ጦርነቱን ይመሩ ጀመር።

ወንዙን ለመያዝ በኛ በጦርና በጠላት ጦር መሀከል የነበረው ተኩስ ደረቅ ጫካ እንደሚያቃጥል የቁዋያ እሳት ሲነጋጋ ራቅ ብሎ ለሚያየውና ለሚሰማው ያስፈራ ነበር። በዚያ ፈታኝ ጦርነት አንዳንድ ጊዜ የኛ ጦር አይሎ ወንዙን እጁ ሲያደርግ አንዳንድ ጊዜ የጠላት ጦር አይሎ የኛን ጦር እያስለቀቀ ሲይዝ፥ ያ ወንዝ ብዙ ጊዜ የሁለቱ ተፋላሚ ጦሮች እጅ ከተለዋወጠበት በሁዋላ በመጨረሻ በኛ ሰራዊት እጅ እንደ ሆነ ቀረና፥ የጠላት ጦር ሸሽቶ ከማዶው ኮረብታ ጥግ ቦታ እንዲይዝ ስለ ተገደደ እዚያ ሆኖ ይዋጋ ጀመር። ታዲያ ያ ሸሽቶ፥ ከኮረብታው ደረት ላይ የያዘው ቦታ ወንዙን የያዘው የኛ ሰራዊት የመሳሪያ ሀይሉን አስተባብሮ ለሚያወርድበት የጥይት መአት አጋልጦ ይሰጠው ስለ ነበረ፥ የሚተገንበት አጥቶ የተጨነቀ መሆኑን ከመሀከሉ ብዙዎች ቦታ ለመለወጥ ላይና፥ ታች ቀኝና ግራ ሲሩዋሩዋጡ ከሩቅ መታየታቸው ያመለክት ነበር።

የጠላት ጦር እንዲያ ባለ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲዋጋ ከቆየ በሁዋላ በቀኝም በግራውም በኩል ተጨማሪ የጦር ሀይሎች አምጥቶ ጦርነቱ ከሚደረግበት ላይና ታች ወንዙን እንዲይዙ ለማድረግ ሞከረ። ምናልባት የጦርነቱን ግንባር ለማስፋትና ያን የሰፋውን የጦርነት ግንባር ተከትሎ የኛ ሰራዊት ወደ ቀኝም ወደ ግራም ዘርዘር ሲል መሀሉ መድከሙ ስለማይቀር ያን የደከመውን ክፍል አጥቅቶ ወደ ነበረበት ቦታ ወደ ወንዙ ለመመለስ የሚልች መስሎት ይሆናል። ወይም ወንዙን የያዘው ሰራዊታችን እዚያ ከቆየው የጠላት ጦር ጋር እንደ ተያያዘ አዲስ የመጡት የጦር ሀይሎች ከቀኝና ከግራ ወንዙን ተሻግረው ሰራዊታችንን ለመክበብ የሚችሉ መስሎት ይሆናል። ነገር ግን፥ የጠላት አሳብ ያም ይሁን ይህ አዲስ የጦር ሀይሎችን ማምጣቱ በጦርነቱ ግንባር ምንም ያክል ለውጥ አላስከተለም። በደጀንነት ተቆጥበው ከቆዩት የራስ የጭፍራ አለቆችና ከከንቲባ ጋሻው ጠና ሰዎችም ታዝዘው ሄደው በግንባር ሲዋጉ ከቆዩት ጋር በመተባበር ወንዙን ወደ ላይም ወደ ታችም ታዝዘው ሄደው በግንባር ሲዋጉ ከቆዩት ከቆዩት ጋር በመተባበር ወንዙን ወደ ላይም ወደ ታችም በርዝመት ስለ ያዙት አዲስ የመጡት የጠላት የጦር ሀይሎች ያን ወንዝ ለመያዝ፥ ወይም በላይና በታች ተሻግረው ሰራዊታችንን ለመክበብ ባደረጉት ሙከራ፥ ከብርቱ ትንቅንቅና ተጋድሎ በሁዋላ እንደ ፊተኞች ጉዋደኞቻቸው ወደ ኮረብታው ጥግ እንዲያፈገፍግ ተገደዱ።

ጠላት፥ በሞትና በመቁሰል ከጦርነቱ ውጭ በሆኑት ወታደሮች ምትክ ወይም በጠቅላላው የግንባር ጦሩን ለማበርታት አዳዲስ ተጨማሪ ሀይል ባመጣ ቁጥር እንደ ማየል ብሎ እስከ ወንዙ መድረስ ይችልና እዚያ ላይ ብርቱ ትንንቅ ብርቱ ተጋድሎ ከሆነ በሁዋላ የኛ ወገን የደረሰ ጉዳት ደርሶበት ጠላቱን አሸሽቶ ወንዙን እንደ ያዘ ይቀራል። እርግጥ የጠላት ወገን ብቻ ሳይሆን የኛ አዛዦችም በርከት ያሉ ወታደሮች በሞትና በመቁሰል ከጦርነቱ ውጭ በመሆናቸው ወይም ጠላት ከማየሉ፤ ብዙ ጊዜ ድጋፍ እየጠየቁ ራስ ልከውላቸዋል። ነገር ግን ጠላት ከኮረብታው ጥግ የያዘው ቦታ ከኛ ወገን ለሚተኮስበት ጥይት አጋልጦ የሚሰጠው ሲሆን የኛ ሰራዊት የሚዋጋው የወንዙን ግንጅና ጫካውን ተተግኖ ስለ ነበረ፥ ከኛ ወገን ይልቅ በጠላት ወገን የደርሰው ጉዳት ይበልጥ እንደ ነበረ ገማቾች ሁሉ ይስማማሉ። ጠላት እንደ ማየል ብሎ ወደ ወንዙ በሚቀርብበት ጊዜ የሚተኩሰው የመትረየስና የጠመንጃ ጥይት ከወንዙ ውስጥ በመሽገው ሰራዊታችን ላይ ከሚያደርሰው ይልቅ የሰፈርንበት ቦታ ኮረብታነት ስለ ነበረውና ጠላት ከያዘው ከፍተኛ ቦታ ኮረብታነት ስለ ነበረውና የመትረየስና የጠመንጃ ጥይት ወንዙን እያለፈ የኮረብታውን ደረት ወይም ስር መምታት ይቀናው ስለ ነበረ እዚያ በነበረው ሰዎችን ላይ ያደረሰው የሞትና የመቁሰል ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። እሰፈር የነበረው ሰዎችን ጠላት ከወንዙ አጠገብ በሚተኩሰው የመትረየስና የጠመንጃ ጥይት ብቻ አልነበረም የተጎዳው። ከዚያ የባሰ ከማዶው ኮረብታ ላይ ጠላት ያለ ማቋዋረጥ የሚተኩሰው የከባድ መሳሪያ እርሳስና አይሮፕላኖች ያወርዱበት የነበረው የ«እሳተ ገሞራ ቦምብ » ነበር በጣም የጎዳው።

ጥዋት ጦርነቱ ከተጀመረ በሁዋላ ትንሽ ቆይተው ስንት እንደ ነበሩ ረስቻለሁ - የጠላት አይሮፕላኖች መጥተው እሰፈራችን ላይ የእሳተ - ገሞራ ቦምብ (ናፓልም) ይጥሉ ጀመር። ያ የእሳተ - ገሞራ ቦምብ መጀመሪያ የገደለውን ሳር ያቃጥልና ከዚያ ቦምቡ በወደቀበትና ሳሩ በተቃጠለበት ዙሪያ ያለውን ዛፍ ከዚያ ዘልሎ ባጠገቡ ያገኘውን ሁሉ ሲያቃጥል እንዲያ ካንዱ ወደ ሌላው እየተዛመተ ጫካውን በሙሉ የቁዋያ እሳት ተነስቶ የሚያቃጥለው ይመስል ነበር። ሠፈር የነበረው ሰው ሁሉ ከየመጠለያው እየወጣ እሳቱን ባፈርና በቅጠል ለማጥፋት ሲሩዋሩዋጥ ከመሀከሉ በቦምብና በከባድ መሳሪያ

የርሳስ ፍንጣሪ ወይም በቀላል መሳሪያ ጥይት እየሞቱም እየቆሰሉም የወደቁ ብዙ ነበሩ። እሰፈር የነበረው ሰው፥ በሙሉ ባይሆን በከፊል እሳቱን ለማጥፋት ፋታ የሚያገኝ አይሮፕላኖች - ከጥዋት ጀምሮ ወደ ከፋ ጉዞ እይጀመረውን ስደተኛ ህዝብና ጉዋዙን ለመደብደብ ይሁን ወይም ቦምብ አልቆባቸው ለመተካት ይሁን አይታወቅም - ከሰፈራችን ላይ ላጭር ጊዜ ጠፍተው ቆይተው እስኪመለሱ ነበር። እኒያ አይሮፕላኖች እንዲያ እየተመላለሱ በግንባር ለሚዋጋው ሰራዊት በደጀንነት እሰፈር የቆየውንና ወደ ከፋ በመጉዋዝ ላይ የነበረውን ሰዋችንን ከጥዋት ጀምሮ ከእኩለ ቀን በሁዋላ እስከ ስምንት ወይም እስከ ዘጠኝ ሰአት ግድም ድረስ ሲደበድቡ ውለው ከሄዱ በሁዋላ አልተመለሱም።

ከጥዋት ጀምሮ እስከ ስምንት ወይም እስከ ዘጠኝ ሰአት ግድም ድረስ ሰራዊታችን በግንባር ከጠላት ሰራዊት በደጀን ከእሳት ጋር በሁለት ግንባሮች ሲዋጋ ነበር የዋለ። ከዚያ በሁዋላ አይሮፕላኖች መምጣታቸውን ሲያቆሙ ጦርነቱ ከወንዙ አካባቢ በሚደረገው ተወስኖ፥ ጠላት ተጨማሪ ሀይል ባገኘ ቁጥር ወንዙን ለመያዝ በሚያደርገው ጥረት ውጊያው ተፋፍሞ ሲቃጠል ጉዳት በዝቶበት ወደ ተራው ጥግ ባፈገፈገ ቁጥር ውጊያው በመጠኑ በረድ ሲል እንዲሁ የኛ ሰራዊት ከወንዙ አንድ እርምጃ ወደ ሁዋላ ሳይፈገፍግ ቀኑ ተገባደደ።

እኔ ያነለት ራስ ጦርነቱን ከሚመሩበት ከፍተኛ ቦታ አጠገብ ስለ ነበርሁ፥ ያ ቦታ የጠላት ጦር ወንዙን ለማስለቀቅ የኛ ጦር ላለመልቀቅ ያደርጉት የነበረውን ተጋድሎ ደህና አድርጌ ለመመልከት አስችሎኝ ነበር። ወደ አስርና አስራ አንድ ሰአት መሀከል ጠላት ለመጨረሻ ጊዜ በተጨማሪ ጦር ሀይሉን አጠናክሮ የኛን ሰራዊት ከወንዙ ለማስወጣት በጦርነቱ ግንባር ከላይ እስከ ታች፥ ብርቱ የማጥቃት ውጊያ አደረገ። ያን ጊዜ ከመድፉና ካዳፍኔው (ከሞርታሩ) እርሳስ ሌላ፥ የመትረየሱና የጠመንጃው ጥይት ወንዙን አልፎ እኛ በነበርንበት አካባቢ፥ በጢስ ተረብሾ እንደ ወጣ የንብ ሰራዊት «ጢዝ - ጢዝ - ጢዝ » እያለ አየሩን ሞልቶ ሲዋነብ፥ መድረሻ ይሳጣ ነበር! በዚያ መሀል ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ ትንሽ ጐንበት ወይም - ተገን ፍለጋ - ወደ ቀኝ ይሁን

ወደ ግራ ሰግደድ አይሉ እንዲሁ ቀጥ እንዳሉ ጠመንጃቸውን አንግተው ከጦርነቱ ግንባር እየተጎማለሉ መጥተው ራስን እጅ ነሱና አፈር የተሞላውን ከረጢት ምሽግ ከውጭ በሁለት እጃቸው ደገፍ ብለው ቆመው ይነጋገሩ ጀመር። እዚያ ቆመው ከራስ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ሁሉ ጥይት ዙሪያቸውን ይዋነብባቸዋል ነገር ግን እሳቸው በፍፁም ርጋታ በፍፁም ፀጥታ ንግግራቸውን ሲቀጥሉ ዝንቦች የሚዞሩባቸውን ያክል የተቸገሩ አይመሉም ነበር! አንዳንድ ጊዜ በንግግራቸው መሀከል ሲስቁ ይታያሉ። የተቀመጥሁበት ቦታ ትንሽ ራስ ያለ ስለ ነበረ ምን እንደሚነጋገሩ ላውቅ አልቻልሁም፥ የማጥቃት ውጊያ የሚያደረግበት ጊዜ ስለ ነበረ፥ በደጀንነት ተቆጥበው የቆዩ የጭፍራ አለቆች ቢኖሩ ለርድታ ወደ ግንባር እንዲላኩ ለመጠየቅ መጥተው ስለሱ ኖሮዋል የሚነጋገሩ። ብቻ አልቀናቸውም። ከጋሻጃግሬዎችና ራስን ለመጠበቅ ከተመደቡት ጥቂት ሰዎች በቀር ደጀን ሆነው የቆዩት የጭፍራ አለቆች ሁሉ፤ በዬተራ እየታዘዙ ወደ ግንባር ሄደው እዚያ በመዋጋት ላይ ነበሩ።

ከዚያ ቀኛዝማች በልሁ ራስን እንደ ገና እጅ ነስተው ጥይቱ እሳቸውን እንደ ፈራ ሁሉ እመሀል ትቶ፥ በቀኝና በግራቸው ያለውን የዛፍ ቅርንጫፍ ሁሉ ሲጨፈጭፍ በመጡበት አሆሁዋን ረጋ ብለው እየተጎማለሉ ወደ ጦርነቱ ግንባር ተመልሰው ሄዱ። በተቀመጥሁበት የዛፍ ስር እንዳለሁ ካይኔ እስኪጠፉ ዝም ብየ ስመለከታቸው ቆይቼ ያ ሁሉ የጥይት በረዶ በዙሪያቸው ሲወርድ ትንሽ ስቅጠጥ የማይሉ በመሆናቸው ልባቸው ከቀዝቃዛ ብረት ወይም ካለት ድንጋይ እንደ ተሰራ ሁሉ ትንሽ ንቅንቅ የማለት ምልክት የማይታይባቸው በመሆናቸው ከልቤ አደነቅሁዋቸው አከበርሁዋቸው!

ምንም እንኳዋ ጠላት በተጨማሪ ጦር ሀይሉን አጠናክሮ ከባድና ቀላል መሳሪያውን አስተባብሮ በጦርነቱ ግንባር ከላይ እስከታች ለመጨረሻ ጊዜ - ያደረገውን የማጥቃት ውጊያ ተቋዋቁሞ ለመመለስ ቀኛዝማች በልሁ የጠየቅሁትን ድጋፍ ሳያገኙ ቢመለሱ፤ ሰራዊታችን ያለ ተጨማሪ ሀይል ከያዘው ቦታ አንድ ስንዝር ሳይለቅ፤ ጦርነቱ እንዲያ ተፋፍሞ እንደ ተቃጠለ ቀኑ መሸ። ጨለማው ከበድ እያለ ሄዶ አይን መያዝ ሲጀምር፤ ጠላት ወንዙን ለመያዝ ባደረገው የማጥቃት ውጊያ ብርቱ የሞትና የመቁሰል ጉዳት ከደረሰበት በሁዋላ፥ ሙከራው ሳይሳካለት በመቅረቱ ወደ ኮረብታው ጥግ አፈግፍጎ ከዚያ

የሚተኩሰው የመትረየስና የጠመኛ ጥይት እሰፈራችን ሳይደርስ፥ ወንዙንና የሰፈርንበትን የኮረብታ ስር ብቻ በመምታት ተወሰነ። ስለዚህ ከራስ መምሪያ አጠገብ የነበርን ሁሉ አልፎ አልፎ ከሚተኮስብን የከባድ መሳሪያ አደጋ በቀር ከሌላ ስጋት ነፃ ሆነ። የከባድ መሳሪያው እርሳስም ቢሆን፤ ብዙ ጊዜ እኛን አልፎ እየወደቀ ሲፈነዳ ነበር የምንሰማው።

ቢበዛ፥ ከምሽቱ ወደ አንድ ሰአት ላይ ቀኛዝማች በልሁና ጥቂት ታላላቅ መኰዋንንት ከጦርነቱ ግንባር ከወንዙ ወደ ራስ መምሪያ መጡ። ወሩ ታህሳስ ስለ ነበረ፥ ቀደም ብሎ ጨልሞ ነበር። መኰዋንንቱ ላጭር ጊዜ ከራስ ጋር ሲነጋገሩ ቆይተው ሲመለሱ ፊታውራሪ ዳምተው ተስማ ለንግግሩ ስለ ነበሩ፤ ምስጢር እንዳልሆነ ምን ተነጋግረው እንደ ወሰኑ ጠየቅሁዋቸው።

«ካንተ የሚሸሸግ አይደለም እንጂ ምስጢርነቱስ ምስጢርን ነው። ራስ አሁን ተነስተው ወደ ከፋ ጉዞዋቸውን እንዲቀጥሉና ከኛ ወገን ተኩስ ሲቆም ጠላት ግንባሩን ለቅቀን መሄዳችንን አውቆ ወዲያውኑ እንዳይከተለን ፥ ቀኛዝማች በልሁ የሆለታን ሰዎች ይዘው ከራስ ሰዎችም አንዳንድ የጭፍራ አለቆች ተጨምረው እስከ አምስት ሰአት ግድም ድረስ እዚሁ ወንዙን እንደ ያዙ ሲተኩሱ ቆይተው ከዚያ በሁዋላ መንገዱ ነፃ ስለሚሆንና እነሱም ደረቅ ጦር ስለ ሆኑ በሩጫ እንዲከተሉ ነው የተወሰነ » አሉኝ። ራስ ወዲያው ተነሱ፥ እኔ ግን በትረ ፅድቅን ተሽሎት ስለ ነበረ እሱ ሰዎቻችንን ይዞ ጉዞውን እንዲቀጥል ከተስማማን በሁዋላ በቅሎየን ብቻ አስቀርቼ የግንባሩን ሁኔታ እስከ መጨረሻ ለማወቅ እዚያ እንዲቆዩ ከተመደቡት ከነቀኛዝማች በልሁ ጋር መቆየት ፈለግሁና እዚያው ቆየሁ።

ያ፥ ከንጋት እስከ ምሽት ድረስ ቀኑን ሙሉ እንደ ተቃጠለ የዋለው የጌራ ጦርነት በጣም ብርቱ ስለ ነበር። በዚያ ጦርነት በጠቅላላው ስንት ሰው እንዳለቀብን ለኔ አላውቅም፥ በመጨረሻ የጦርነቱን ግንባር እንደ ያዘ የቀረው ጠላት ያውቅ እንደ ሆነ እንጂ ከኛ ወገን የሚያውቅ ሰው ያለም አይመስለኝም። በባህላችን በጦርነት ሜዳ ሲዋጉ የወደቁትን ጀግኖች ቁጥር ለቅሞ ማወቅ የተለመደ አልነበረም። የያንዳንዱን ሰው ሞት የሚያውቅ የጦርነት ጉዋደኞቹ ከዚያ ከፍ ሲል የቅርብ አለቃው፥ ከዚያ በሁዋላ ቤተሰቡ ብቻ ናቸው። ኢትዮጵያ ድል ካደረገችባቸውም ሆነ ድል ከሆነችባቸው ብዙ ጦርነቶች

ባንዳቸው እንኩዋ የሞቱትን የቆሰሉት ጀግኖችዋ ቁጥር በታሪክ ተመልክቶ አይታይም።

በጌራ ጦርነት ምንም እንኩዋ የኛ ሰራዊት የወንዙን ግንድና ወንዙ የለበሰውን ጫካ ተገን (ምሽግ) አድርጎ ሲዋጋ የዋለ በመሆኑ የደረሰበት ጉዳት በጠላት ከደረሰው ጋር ሲመዛዘን ዝቅተኛ እንደሚሆን ቢገመት ባጠቃላይ ያ ጦርነት በሰውና በጥይት ደካማ የነበረ አቅማችንን ይብስ እንዳደከመው የማይጠርጠር መሆኑን ያነጋገርሁዋቸው መኩዋንንት ሁሉ ተስማምተው ያረጋግጡ ነበር። ከጌራ ጦርነት በሁዋላ ሰራዊታችን የሰውና የጥይት፥ ከሰውም የባሰ የጥይት ድህ ሆነ። በወታደሩ ወገብ የሚታየው ዝናር ሁሉ ከቁጥር የማይገቡ በጣም ጥቂት ጥይቶች ያሉበት ወይም ምንም የሌለበት ነበር!

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

# ጎጀብ

ራስ ጦርነቱን ሲመሩ የዋሉበትን ቦታ ለቀው ወደ ከፋ ጉዞዋቸውን ከቀጠሉ በሁዋላ ቀኛዝማች በልሁና የሆለታ መኮንኖች ጠላት ወንዙን እንዳይሻገር ሲጠብቅ እንዲቆይ ተመድቦ የቀረውን ሰራዊት በግንባሩ ከላይ እስከ ታች ዘርዘር ብሎ ተሰልፎ ተኩሱን እንዲቀጥል ስላደረጉ ተኩሱ ቀጠለ። ብቻ ያ ተኩስ ሁለቱም ወገኖች - የኛም የጠላትም - ከማዶ የሚንቀሳቀስ ነገር ያዩ በመሰላቸው ቁጥር ለጥንቃቄ ያክል፤ እንዲሁም በየቦታቸው መኖራቸውን ለማስታወቅ ያክል ካልሆነ መቸም በዚያ ጨለማ «ጠላትን አነጣጥሮ ለመምታት ይቻላል » ተብሎ የሚተኮስ አልነበር።

ከጠላት ወገን ያለማቋረጥ ከሚነጉደው የከባድ መሳሪያ ተኩስ በቀር ወንዙን ተከትሎ ከላይ እስከ ታች የሚተኮሰው የጠመንጃና የመትረየስ ተኩስ እንደ ቀኑ ፋታ የማይሰጥ ሳይሆን፥ በረድ ሲልም ሲፋፋምም ነበር። አንዳንድ

ጊዜ ፀጥ ብሎ ቆይቶ ያንዱ ወገን ከማዶ የሚንቀሳቀስ ነገር ያየ መሎት ተኩስ ሲከፍት የሌላው ወገን አጠፋውን ይመልስና በግንባሩ ላይ እስከ ታች የተፋፋመ ተኩስ ሲተኮስ ይቆያል። ታዲያ፥ ያ ከፀጥታው በሁዋላ ጠላት የሚተኩሰው ተኩስ በቦታው መኖሩን ለማስታወቅ እንጂ ከዚያ አልፎ የሚያስከትለው ጉዳት እንደሌለ ታውቆ ተለመደና እዚያ የነበሩት ሰዎቻችን የሞት ወይም የመቁሰል ጉዳት እንደማይደርስባቸው መስጋቱን ረስተው በዚያ ፈንታ ፅኑ ርሀብ ተሰምቶዋቸው ሁሉም ሲነጋገሩ የሚሰሙት የሚባላ ነገር ስለሚገኝበት ዘዴ ሆነ።

ወታደሮቹ የሚባላ ነገር አጥብቀው መፈለጋቸውን ቀኛዝማች በልሁ እንዳወቁ ሰፈሩን ለቅቆ ወደ ከፋ የሄደው ሰራዊታችን ጥሎት የሄደ ስንቅ ቢገኝ በየሰፈሩ ዞረው የሚፈልጉ ሰዎች ላኩ። ነገር ግን የተገኘው አንድ ስልቻ ማር ብቻ ነበር። ስለዚህ አንድ ሰው ከስልቻው ውስጥ በሁለት እፍኙ እየዛቀ እዚያ ከቀኛዝማች አጠገብ ለነበርን ሁሉ ሰጥቶን በላንና ለግዚኤው ረሀባችነን አስታገሰልን። ቆይቶ ግን ግንባሩን ለቅቀን በመንገድ ላይ እንዳለን እኔ ብርቱ፥ ውሀ ጥም ስለለቀብኝ «ምነው ያን ማር ባልበላሁት በቀረብኝ ኖሮ! » አልሁ።

በጦርነቱ ግንባር እንዲያ ተኩስና ፀጥታ ሲፈራረቅ እስከ አምስት ሰአት ግድም ቆይተን ለቅቀን በሰራዊታችን ለመድረስ የመነሻው ጊዜ ሲደርስ ቀኛዝማች በልሁ ግንባሩን ሲጠብቁ ላመሹት የቡድን አለቆች ሁሉ ሰዎቻቸውን ይዘው እንዲነሱ በየተሰለፉበት ቦታ መላክተኞች ላኩ። ከዚያ በቅሎዎች ከተኩሱ ራቅ ባለ ሰዋራ ቦታ ተይዘው ሲጠብቁ ከቆዩበት እንደ መጡልን ባለ በቅሎ በበቅሎው እግረኛ በግሩ ሰራዊታችን የሄደንበትን የከፋን መንገድ ይዘን ገሰገስን። ግን ቢበዛ ከአንድ ሰአት ተኩል እስከ ሁለት ሰአት ተኩል ያክል ቢሆን ነው። ከዚያ በሁዋላ ቀድሞን በሄደው ሰራዊታችን አንድ ሰፊ ረግረግ ላይ ታግዶ ቆይቶ የመጨረሻው ክፍል የታገደበትን ቦታ ገና ሳይለቅ ደረስንበት። እዚያ ከነበረው ብዙ ህዝብ ከረግረጉ ወዲያ ማዶ ተራግፈው የቆዩ አጋሰሶቻቸውን የሚጭኑም ከረግረጉ ቀኝና ግራ አልፎ አልፎ ባንዳንድ ላይ ተሰብስበው የሚንጫጩም ነበሩ። እንደ ደረስን ያን ብዙ ህዝብ ስናይ ጠላት ቀድሞ መንገድ ዘግቶበት የታገደ መስሎን ነበር። ነገር ግን፥ ጠላት ያስታጠቃቸው ምንደኞች ምቹ እዬያዙ ማስቸገራቸው ባይቀርም፥ ሰራዊቱን

እዚያ ቦታ ላይ አግዶ ያን ያክል ጊዜ ያቆዬው ብርቱ የጠላት ጦር ገጥሞት ሳይሆን በረግረጉ ምክንያት መሆኑን እዚያ የነበሩት ሰዎች ነገሩን።

የዚያን ሰፊ ረግረግ መሻገሪያ መልካዎች ለማግኘት ዳርዳሩን ወደ ላይ ወደ ታች መሄድ ያስፈልግ ነበር። ነገር ግን እዚያ የነበሩት ሰዎች እንደ ነገሩን መሪዎች ካለመኖራቸውም ሌላ ሌሊት በመሆኑ የተጫኑ ከብቶች ያሉዋቸውም የሌሉዋቸውም እዬቸኮሉ ቀጥታ መንገዱን ይዘው እንደ መጡ ረግረጉ ውስጥ ይገባሉ። እዚያ ከብቶች ከነጭነታቸው ሲወድቁ እነሱን ተረዳድቶ ለማንሳትና ጭነታቸውን አራግፎ በሸክም እያሻገሩ እንደ ገና ለመጫን እጅግ አስቸጋሪና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ስለ ነበረ ያን ችግር አልፎ እንደ ልብ ለመሄድ አልተቻለም። ደግሞ እኒያ ሰዎች እንደ ተረኩልን ችግሩን እጥፍ ድርብ አድርጎ የዘጋው ያን ሁኔታ ሲያዩ ዳርዳሩን ወደ ላይም ወደ ታችም ሄደው መልካዎችን እያገኙ በደህና የተሻገሩ ቢኖሩም፤ ብዙዎች ባለ አጋሰሶችም በበቅሎ የተቀመጡና እግረኞችም ቀድመዋቸው ረግረጉ ውስጥ የገቡት መውጫ አጥተው ሲጨነቁ እያዩ እንደ ደረሱ ቀጥታ፥ እዚያ ረግረግ ውስጥ እዬገቡ በላይ በላዩ መጨመራቸው ነው።

ያን የሚያሳዝን ታሪክ ሰዎች ሲተርኩን «ድል ሆኖ የሚሸሽ ሰራዊት እንደ በግ መንጋ በፊቱ የሚሄደውን እያየ መከተል እንጂ የሚሄድበትት ገደል ይሁን ሜዳ አይታየውም! » ሲባል የሰማሁት ትዝ አለኝ። ታዲያ ሌሊት መሆኑ በጀ እንጂ ቀን ቢሆን ኖሮ እዚያ ረግረግ ውስጥና ዙሪያውን የነበርው እጅግ ብዙ ህዝባችን እንዲያ እንዳለ የጠላት አይሮፕላኖች ቢደርሱበት ያገኘው የነበረው ጉዳት ምን ያክል ይሆን እንደ ነበረ እግዚአብሔር ይወቅ።

አጋሰሶቻቸውን ጭነው ያበቁትና ሌሎችም ጉዞዋቸውን ሲቀጥሉ ጭነው ያላበቁትና ሌሊቱን ደጀን አድርገው (ጠላት በሌሊት እንደማይከተላቸው አምነው) እዚያ ረግረግ ዳር ቆመው ተቀምጠውም በርጋታ እያወሩ ብዙ ነበሩ። እኛ እነሱን እዚያ ትተን ከሚሄዱት ጋር ተጨምረን ስንጉዋዝ አንድ ቦታ ላይ አንድ ሰው ከመንገዱ ዳር እንደ ተጋደመ ፃእር የሚያስጨንቀው ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲናገር ከሩቅ ይሰማ ነበር። ሶት ወይም አራት የሚሆኑ ሰዎች በዙሪያው ቆመዋል። ታዲያ እንዲያው ያለው ነገር የተለመደ ሆነና፥ ከዚያ መንገዱን

ሞልቶ ከሚሄደው ህዝብ መሀከል ቀረብ ብሎ አይቶት ከንፈሩን እዬመጠጠ ከሚሄደው ህዝብ መሀከል ቀረብ ብሎ አይይቶት ከፍነሩን እዬመጠጠ የሚሄድም ዘወር ብሎ ሳያየው እንኩዋ የሚሄድም ነበረ። እኔም እንደ ደረስሁ ቀረብ ብዬ ሳየው ባላውቀውም የለበሰው ልብስ የሆለታ መኮንኖች መለዮ ያለበት ስለ ነበረ፥ ከሆለታ መኮንኖች አንዱ መሆኑን ተረዳሁ። እጦርነቱ ግንባር ቆስሎ እስከዚያ ድረስ ሰዎች በሸክም ወስደውት ይሁን ወይስ የት እንደ ቆሰለ ጠይቄ መልስ አላገኘሁም። «ጎበዝ እባካችሁ ከነነፍሴ በጠላት እጅ አንዳልወድቅ እናንተም እንዳላስቸግር ገድላችሁኝ ሂዱ እባካችሁ! አንድ ትይት ይበቃኛል አንድ ጥይት አትንጉኝ! » ሲል ያስለቅስ ነበር። «እባካችሁ ተሸክመን እስከ ሰፈር ልናደርሰው አንችልም? » አልሁዋቸው በዙሪያው የነበሩትን ሰዎች።

«ቃሬዛ ቢኖር ነበራ! ቅስሉ ላንድ ሰው ሸክም በማይመች ቦታ ስለሆነ ያለ ቃሬዛ አይቻልም » አለኝ አንዱ። የሆለታ መኮንኖች ወይም ቀኛዝማች በልሁ ምናልባት ወደ ሁዋላ ሆነው ወይም ሳያዩት በሌላ መንገድ አልፈው እንደ ሆነ አላውቅም እንጂ፤ ቢያዩት ኖሮ፥ እንድያ ሲማጠን አልፈውት እንደማይሄዱ ርግጠኛ ነበርሁ። እዚያ ቆሜ ስመለከተው ቆይቼ ብቻየን ምንም ላደርግለት እንደማልችል ስለ ተረዳሁ እኔ አቁስዬ ጥዬው የሄድሁ ይመስል የወንጀለኛነት ስሜት ተስምቶኝ አፌን እዬመረረኝ ጉዞዬን ቀጠልሁ። ትንሽ ያፅናናኝ ሆለቶች የጦርነቱ ግንባር ሲጠብቅ ላመሸው የሰራዊታችን ክፍል ደጀን ሆነው ሁዋላ የሚከተሉ ሰምቼ ስለ ነበረ «እነሱ ይደርሱለት ይሆናል » የማለቱ ተስፋ ነበር። እውነትም የሆለታ ጉዋደኞቹ ሁዋላ ደርሰው እንዲገደል ማድረጋቸውን ሲወራ ሰማሁ። መገደሉ እውነት ቢሆንም ማን እንደ ገደለው ወይም ከተወሩት ሁለት ወሬዎች የትኛው እውነት እንደ ሆነ ላረጋግጥ አልቻልሁም።

አንደኛው ወሬ «ሆለቶች ከመሀከላቸው አንድ ቁስለኛ ለመዳን ተስፋ ያለው ከሆነ ምንም ብርቱ ችግር ቢገጥማቸው ትተውት እንዳይሄዱ ለመዳን ተስፋ የሌለው ከሆነ ግን ገድለውት እንዲሄዱ ቃል ኪዳን ስለ ነበራቸው ያ

መኮንን የማይተርፍ መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ አንድ መኮንን እንዲገድለው ተደረገ » የሚል ነበር።

ሁለተኛው ወሬ «ቁስለኛው እንደማይተርፍ ከተረጋገጠ በሁዋላ የጎረሰ መሳሪያ ተሰጥቶት ራሱን እንዲገድል ተደረገ » የሚል ነበር። ያ እንደማይተፍ ሆኖ በመቁሰሉ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት የተደለ መኮንን «ሻምበል ለማ አያባሬ » ይባል ነበር።

የጌራ ጦርነት የተደረገበትን ቦታ የተጉዋዝንበት ክፍል አልፎ አልፎ ጫካ ቢኖርበትም በጠቅላላው ከመንገዱ ቀኝና ግራ የሚታዬው አዝመራ ነበር። ያን ያለፈን ዘንባባዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ ዛፎች በርከት ብለው የሚታዩበት ካካባቢው ትንሽ ከፍ ያለ ቦታ ስንደርስ እዚያ ላይ ሰፈር ተደርጎ ቆየን። እኔ ረሀብና ድካም ተደራርበው አዝለውኝ ስለ ነበረ ሰዎቹ የሰፈሩበትን ቦታ መፈለጉ ያመት መንገድ መስሎ ታይቶኝ እንደማላገኘው አስቀድሜ ተስፋ ቆርጬ ቅርብ ሆኖ ወደ ታዬኝ ዛፍ ሄጄ በቅሎየን ከዛፉ ጋር በለኮው አሰርሁና የኮርቻውን ምቹ አንጥፌ ኮቴም ሱሪየም ቁምጣዎች ስለ ነበሩ ግላሱን ለብሼ ጠመንጃየን ተንተርሼ እዚያ ዛፍ ስር ገደም አልሁ። ወዲያው ከባድ እንቅልፍ ወስዶኝ ዝናሙ ዘንሞ እስኪያባራ አልነቃሁም ነበር። ስነቃ የለበስሁትን ግላስና ያነጠፍሁትን ምቹ ዝናም አበስብሶዋቸው ብርቱ ብርድ እንደ ወባ ሲያንቀጠቅጠኝ አገኘሁ። በቅሎየም ልጉዋሙን በታሰረበት ዛፍ ፈግፍጎ አውልቆ ከፊቴ ጥሎልኝ ለኮውን ቆርጦ ሄዶዋል። ከዚያ ተነስቼ ጠመንጃየንና የበቅሎውን ልጉዋም እንዲሁም ዝናም ያበሰበሳቸውን ምቹና ግላስ ይዤ የምሄድበትን ሳላውቅ አእምሮየ ሳይሆን እግሬ በመራኝ እየተንቀጠቀጥሁ ትንሽ እንደ ሄድሁ የልጅ ቢተውን (ያባቱን ስም ረስቻለሁ) ድንኩዋን አዬሁ። ልጅ ቢተው የክቡር ራስ እምሩ ልዩ ፀሐፊ ነበር። ባልተቤቱ ወይዘሮ ዋጋየ (የሳቸውንም ያባት ስም ረስቻለሁ) በሽሬ ዘመቻ መኖራቸውን አላስታውስም እንጂ ከጎሬ ጀምሮ በምእራብ በተደረገው ትግል ሁሉ ከባላቸው ሳይለዩ ተካፋይ የሆኑ ብርቱ ወይዘሮ ነበሩ።

«ልጅ ቢተው ልጅ ቢተው » ብዬ ተጣራሁ ወደ ድንኩዋኑ በር ቀረብ ብዬ።

«ማነው! » አለ ልጅ ቢተው ከውስጥ።

ማን መሆኔን ከተናገርሁ በሁዋላ ወይዘሮ ዋጋየ ቶሎ የፋና መብራት አብርተው አስገቡኝ። ጠመንጃየን ባንድ ትከሻየ ዝናም ያበሰበሳቸው የበቅሎ እቃዎቼን በሌላው ትከሻየ ተሸክሜ እዬተንቀጠቀጥሁ ስገባ ባልና ምሽት አይተው መጀመሪያ ሁለቱም ደንግጠው የሚያደርጉትን አጡ ከዚያ ዋጋየ ከድንጋጤያቸው ወጥተው የተሸከምሁትን ሁሉ ካላየ ወስደው ወዲያ አስቀመጡና «ወባ አለብህ? » አሉኝ።

«የለብኝም፤ ብርድ ነው » አልሁዋቸው። ወዲያው ከየት አምጥተው ምን ጊዜ አንዳነጠፉት ሳላይ፤

«በል እዚያ ተኛ » አሉኝ፣ ከነሱ ምኝታ ትንሽ ራቅ ብሎ የተነጠፈ ምንጣፍ አመልክተው። ግማሽ ራቁቴን ባሳዩኝ ምንጣፍ ላይ ስጋደም ቶሎ ጫማየን አውልቀው በወፍራም ጋቢ ከራሴ እስከ እግሬ ከጠቀለሉኝ በሁዋላ በሱ ላይ ከነሱ ብርድ ልብስ አንዱን ደግሞ በዚያ ላይ ምን እንደሆነ አላውቅም ሌላ ነገር ደራርበው እስኪከብደኝ አሸከሙኝ። ትንሽ ቆይቼ ሰውነቴ ፀጥ እያለ ሄደና እንቅልፍ ወሰደኝ። ብቻ ምንም ያክል ተንቀልፍቼ ሳይቆይ፤ ከውጭ ሰዎች ሲንጫጩ ነቅቼ፥ የተከናነቡትን ልብስ ገለጥ ባደርግ ነግቶ የድንኩዋን ውስጥ ሁሉ ብርሃን ሆኖዋል። ወዲያው የበቅሎየ መጥፋት ትዝ ስላለኝ ቶሎ ተነስቼኤ ጫማየን ሳጠልቅ ባልና ምሽት ነቅተው፥

«አሁን ተነስተህ ወዴት ልትሄድ ነው? ብርዱ ገና አልለቀቀምኮ » አለኝ ልጅ ቢተው።

«ጉዞ ሳይጀመር በቅሎየን ልፈልገው ጉዞ ከተጀመረ በሁዋላ አላገኘውም » ብዬ ተነሳሁ።

«እንግዲያውስ ጋቢውን እንደለበስህ ሂድ » አሉኝ እመይቴ።

ቁምጣ ኮቴንና ቁምጣ ሱሪየን ከውስጥ የገላየ ከላይ ተደራርቦ የተጫነኝ የልብስ ሙቀት አድርቀውኛል። ምቹውና ግላሱ ግን፥ እንደ ረጠቡ ነበሩ።

ጋቢየን ተከናንቤ ጠመንጃየንና ርጥቡ የበቅሎ እቃየን ተሸክሜ በጎ አድራጊዎቼን ከልብ አመስግኘ በቅሎየን ልፈልግ ወጣሁ።

እድል ሁለት መልክ የለውም። ወይ ቀና ወይ ጠማማ ነው። ታዲያ ያነለት ከንጋት አቅራቢያ ጀምሮ ቀና እድል ገጠመኝና ከዚያ እንደ ወባ በሽታ ከሚያንቀጠቅጥ ብርቱ ብርድ በነልጅ ቢተው የማይረሳ ርዳታ ተገላግዬ ከነሱ ድንኩዋን እንደ ወጣሁ ብዙ ሳልሄድ፥ በርከት ያሉ ከብቶች (በቅሎዎች አህዮችም) ባንድነት ሲግጡ በሩቁ አዬሁ። ቀረብ እያልሁ ስሄድ ከመሀከላቸው አንዱ በቅሎ ባዶ ኮርቻ የተጫነ መሆኑን ሳይ «የኔ በቅሎ ሳይሆን አይቀርም » ብዬ ገመትሁ። እውነትም የኔ በቅሎ ነበር። ከጠባቂዎቹ አንዱ የማውቀው የፊታውራሪ ዳምተው ተሰማ አሽከር ስለ ነበረ የተሸከምሁትን ኮተት ሲያይ እንደ መደንገጥ ብሎ እዬሮጠ መጥቶ ሸክሜን ተቀበለኝና፤

«ምን ጉድ ነው? እነዘሪሁን ምን ሆኑ? በቅሎውስ ይህን ሁሉ እቃ ላንተ ጥሎ ኮረቻ ብቻ ተጭኖ እንዴት ወዲህ መጣ? » አለኝ።

እኔም ከነዘሪሁን የተለየሁበትን ምክንያትና ከዚያ በሁዋላ የሆነውን ባጭሩ ነገርሁትና ምናልባት እነ ዘሪሁን የሰፈሩበትን ያውቅ እንደሆነ ብጠይቀው የማያውቅ መሆኑን ነገረኝ።

ከዚያ ያ ልጅ በቅሎየን ለጉሞ ርጥብ ምቹና ግላሱንም ብዬቦታቸው አድርጎ ሲሰጠኝ ርቦኝ ስለ ነበረ ወደ ልጅ ቢተው ድንኩዋን ተመልሼ ቁስ በማድረግና ስዎቼ የሰፈሩበትን በመንፈለግ መሀከል መቁረጡ አስቸግሮኝ ሳመንታ ቆየሁ። ሁዋላ ጉዋዝ ከመነሳቱ በፊት ሰዎቼን ፈልጌ ካላገኘሁ ለያነለት ጭራሹን ላገኛቸው የማልችል መስሎ ስለታዬኝ እነሱን መፈለጉን መረጥሁና መንገዴን ስጀምር፤

«እነ ዘሪሁንን ያገኘሀቸው እንደ ሆነ በከፋ መንገድ ከሰፈሩ መውጫ ላይ ተቀምጬ የምጠብቃቸው መሆኑን ንገርልኝ። አሁን ሰፈር - ለሰፈር ዞሬ እንዳልፈልጋቸው ስላገኛቸው ሰራዊቱ ጉዞ የጀመረ እንደሆነ እንዳያመልጡኝ ነው » ብዬ ለልጁ ነግሬ እንደ ምንም ተጎትቼ በበቅሎየ ላይ ተቀምጬ የከፋን መንገድ ይዤ እስከ ሰፈሩ ወሰን ሄድሁ። አንድ ትንሽ ወንዝ ተሻግሬ በመንገድ

የሚያልፈውን ማየት የምችልበት ከፍተኛ ቦታ አገኘሁና እዚያ ተቀምጬ ስጠብቅ ሰፈርተኛው መጉዋዝ ከጀመረ በሁዋላ ብዙ ቆተው ሰዎቼን ሲመጡ አዬሁዋቸው። አቶ በትረ ፅድቅ ገና ከሩቅ ሲአይየኝ እዬሮጠ መጥቶ ስሞኝ ሰፈር ሳልደርስ ያደርሁበትን ምክንያትና ወዴት እንዳደርሁ ሊጠይቀኝ ሲጀምር የዘሪሁን ፉከራ አቁዋረጠው።

ዘሪሁን ሁለት ጠምጃዎች የራሱን አንግቶ ሌላውን በጁ ይዞ አንድ ጉልበቱን እንበርክኮ ሲፈክር ሲፈክር ቆዬና፥

«እኔ ያንተ ወንድም እኔ ያንተ አሽከር እንዲህ ነኝ! » ብሎ በጁ የያዘውን ጠመንጃ ከፊቴ አስቀመጠው። ማታውን እጉዞ ላይ ጠላት ያስታጠቃቸው ምንደኞች በሚጉዋዘው ሰራዊታችን ላይ አደጋ ጥለው ሲታኮሱ፥ ከነሱ የማረከው ጠመንጃ ነበር።

«ጠመንጃውን መርቄልሀለሁ። በል እንግዲህ የምበላው ነገር ስጠኝ » አቶ በትረ ፅድቅ ያነለት፥ እንኩዋንስ ሊስቅብኝ በመራቤና በመንገላታቴ በጣም ነበር ያዘነ። ሁዋላ ግን የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በሁዋላ እንኩዋ በኔ ለማሳቅ ሲፈልግ ከሚያነሳቸው ማሳቂያዎች አንዱ የዚያነለት ሁኔታየ ነበር።

«ሀዲስ » ይላል በትረ ፅድቅ ሊያስቅብኝ ሲፈልግ። «ሀዲስ፥ ሁለት ቀን ጦሙን እዬዋለ አድሮ፥ በሶስተኛው ቀን ከእህል በቀር ሌላ ነገር አልታየው ባለበት አሽከሩ የሚያስገርም የጀብድ ስራ ሰርቶ በወጉ አሽከሮች በጌቶቻቸው ፊት እድነሚያደርጉት የማረከውንጠመጃ ከፊቱ ጥሎ ሲፈክር ‹እባክህ ይህን ፍከራህን ለሌላ ጊዜ አቆይና ይልቅስ አሁን የምበላው ነገር ስጠኝ!› አለው » ብሎ እየሳቀ ያስቅብኝ ነበር። ታዲያ እውነቱ፥ በትረ ፅድቅ ሊያስቅብኝ ፈልጎ ይለው የነበረው አደለም። ዘሪሁንን የምበላው እንዲሰጠኝ የጠየቅሁት እንደ ወጉ ፍከራውን አስጨርሼ እንደ ወጉ የጣለውን ምርኮ (ጠመንጃውን) ተቀብዬ ከመረቅሁለት በሁዋላ ነበር። የሆነ ሆኖ ዘሪሁን ቶሎ ከወንዝ ውሀ አምጥቶ፥ በሶ አሰናድቶልኝ ከበላሁ በሁዋላ ከዚያው ከበሶው በጥብጦ በትልቅ ዋንጫ ስጠኝና ያን ጠጥቼ እኔ እስካርፍ እዚያው ቆይተው ጉዞዋችነን ቀጠልን።

ያንጊዜ ጅማና ከፋ የተላያዩ ጠቅላይ ግዛቶች ስለ ነበሩ ያነለት ሰፈር የተደረገበት ቦታ የሁለቱ ግዛቶች ወሰን ከነበረው ከጎጀብ ወንዝ አጠገብ ነበር። የከፋው ገዥ ክቡር ራስ ጌታቸው አባተ ከጃንሆይ ጋር ወደ ሰሜን ግንባር ለዘመቻ ታዝዘው ሲሄዱ ክቡር ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ ከሚመራ አውራጃ ተነስተው የከፋ ጠቅላይ ግዛት ጥብቅ ገዢ እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር። አንባቢዎች እንደሚያስታውሱት ክቡር ራስ እምሩ ክረምቱን ጎሬ ሲከርሙ ተባብረው ጠላትን እንዲቃወሙ ከፃፉላቸውና እንደሚስማሙ እምነት ተጥሎባቸው ከነበሩት ታላላቅ መኳዋንንት አንዱ ደጃዝማች ታዬ ስለ ነበሩ እሳቸውና የከፋ ህዝብ ጠላትን የሚቃወሙና ለኢትዮጵያ ነፃነት የቆሙ ለመሆናቸው አንዳች ጥርጣሬ የነበረ አይመስልም። ስለዚህ ማታ ጥሩንባ እዬተነፋ ከሞላ ጎደል የሚከተለው ማስጠንቀቂያ ሲለፈፍ አመሸ።

«ከነገ ጀምሮ የምንጉዋዝበት አገር ህዝብ ጠላትን፥ የሚቃወምና እኛን የሚረዳ በመሆኑ በመንገድም ሆነ በሰፈር ባላገሩ በፈቃዱ ለሽያጭ የሚያቀርበውን በገንዘብ ከመግዛት በቀር ወታደር ወይም ከወታደር ጋር የሚጉዋዝ ማነኛውም ሰው ባላገሩን በምንም አይነት ሲያስቸግር ቢገኝ ወይም ማስቸገሩን ያይን ምስክር ቢነግርበት በብርቱ የሚቀጣ መሆኑን እንድታውቁት! »

በማግስቱ ጥዋት እንደ ተለመደው መንገዱ አማን መሆኑን እያሰሱ የሚያረጋግጡት ቃፊሮች ፊታውራሪዒ ከበደ ያዘውና ቀኛዝማች ደጀኔ ርገጤ ከሰዎቻቸው ጋር ቀደም ብለው ተነስተው ሄዱ። ቆይተው ስደተኛው ህዝብና ከጉዋዙ የሚበዛው ክፍል ተከተሉ። ከሁሉም በሁዋላ ራስ ከመኳዋንንቱና ከሆለታ መኮንኖች ጋር መንገዳቸውን ያዙ። ደብረ ማርቆስ የነበሩት የክብር ዘበኞች አለቃ ልጅ (ሁዋላ ቀኛዝማች) ግዛው ቡኔ መትረየሳቸውን አስጭነው እሳቸው በበቅሎ ተቀምጠው ከራስ ፊት ለፊት ይሄዱ ነበር። ከራስና ከመኳዋንንቱ በሁዋላ አቶ በትረ ፅድቅና እኔ ተዝናንተን እያወራን ስንሄድ ሁለት ወታደሮች አንድ የጣሊዒያን መለዮ ያለበት ቆብ በራሱ የደፋ ሰው ቀኝና ግራ ክንዶቹን ይዘው እየሮጡ ባጠገባችን አልፈው ወደ ራስ ቀረቡና ይነጋገሩ ጀመር። ራስም ሰውዬውን እዬጠዬቁት ሲመለስ ከሩቅ እናይ ነበር። ምን እንደጠዬቁትና ምን እንደ መለሰ አልተሰማንም። ሁዋላ እንደ ሰማነው ግን

«ጣሊያኖች ከፋን መያዛቸውንና ያን መለዮም ያገኘው ለጣሊያን ወታደርነት ከተቀጠሩ የከፋ ጉዋደኞቹ መሆኑን ተናገረ » አሉን። ሰውዬው በወታደሮቹ እንደተያዘ እንዲቆይ ወደ ሁዋላ ተመለሰ። ጉዞው ግን አላቋዋረጠም፥ ይቀጥል ነበር። የከፋን መያዝ ከሰውዬው የሰሙ ከሁለት ወታደሮች በቀር ራስና ባጠገባቸው የነበሩት ብቻ ስለ ነበሩ ሌላው «አገር አማን ነው » ብሎ በሰላም ጉዞውን ይቀጥል ነበር።

ወደ ጎጀብ እዬቀረብን ስንሄድ ቀኙና ግራው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ይሁን እንጂ ጥርጊያው መንገድ በጣም ሰፊ ስለ ነበረ ያን ጥርጊያ መንገድ በወርዱም በቁሙም ባለበቅሎ መኰዋንንትና እግረኛ ወታደር ሞልቶት ሁሉም ባንድነት እንደ ማእበል ሲጥመለመል ማየቱ እንዴት ደስ ያሰኝ ነበር!

ጎጀብ ወንዝ ዳር ስንደርስ ሶስት ይሁን አራት ረዣዥም ፈረንጆች ድንገት፥ ከዬተሸሸጉባቸው አጫጭር ቁጥቋዋጦዎች እዬወጡ ቀጥ ብለው ቆሙ። በኪሳቸው ምን እንደ ያዙ እነሱና እግዜር ይወቁት እንጂ በጃቸው የመሳሪያ ምልክት አይታይም ነበር! ወዲያው ያ በሰላም እያወራና እዬተዝናና ይጉዋዝ የነበረው ሰራዊት «ቁም! » እንደ ተባለ ሁሉ ሁሉም ባንድ ጊዜ ቀጥ አለ! ወሬውና መዝናናቱም እንዲሁ ዝም ፀጥ አለ! ፈረንጆች የጠላት መትረየሶች ተደግነውባቸው እያዩ እንዲያ ባዶ እጃቸውን ደረታቸውን ገልብጠው መቆማቸው እኛን? ወይስ ሞትን? ማናቸነን ቢንቁ እንደሆነም እንዲሁ ከነሱና ከግዜር በቀር የሚያውቅ የለ! ያም ሆነ ይህ እኔ እስከ ዛሬ ድረስ አደንቃቸዋለሁ። ደቂቃ ባልመላ ጊዜ ውስጥ ያን ፀጥታ አቁዋርጠው፥

«በለው! » ካሉ በሁዋላ ልጅ ግዛው ቡኔ፥ «እንበላቸው? » አሉ እንደገና ወደ ራስ ዘወር ብለው።

«ተው ቆይ እስቲ! ‹ምንድን ናቸው?› በሉዋቸው » አሉ ራስ በጃቸው የያዙትን አለንጋ ይሁን ወይም ሌላ ነገር ላይና ታች እያወዛወዙ። ወዲያው ከኛ ዘንድ ጠያቂ ሳይሄድ ከፈረንጆቹ ዘንድ አንድ የምናውቃቸው ሰው እየሮጡ መጥተው ራስን እጅ ነሱ። እኒያ ሰው ቀኛዝማች መጊድ ይባሉ ነበር። ቀኛዝማች መጊድ የሻለቃ ዮሀንስ አብዱ እና የአቶ ዳዊት አብዱ የእንጀራ አባት

መሆናቸውን ጎሬ በቆየሁበት ጊዜ ሰምቻለሁ። ከቀኛዝማችነት ማእረግ ጋር የጎሬ ከተማ ገዥ ሆነው መሾማቸውንም የዚያ ልንነሳ አቅራቢያ ሰምቸ ነበር።

«ምንድን ናቸው እነዚህ? » አሉዋቸው ራስ፥ ቀኛዝማች መጊድን።

«ኮሎኔል ሚኒቲ? ማሌቲ (ስሙን ረስቼዋለሁ) እና ረዳቶቻቸው ጣሊያኖች ናቸው ጌታየ። ኮሎኔሉ ክቡርነትዎን የከበበው የጣሊያን ጦር አዛዥ ናቸው። ከመጡበት መንገድ ቀኝና ግራ ያለውን ጫካ የጣሊያን ጦር ይዞታል። ከወንዙ ወዲያ ማዶም መድፎችና ልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎች ተጠምደዋል። ስለዚህ ‹ተከበዋል መውጫ የለዎትምና እጅዎን ቢሰጡ ይሻላል!› ነው የሚሉት » አሉ ቀኛዝማች መጊድ።

«እጃችነን ባንሰጥስ? » አሉ ራስ ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው።

«ይህኑ ልንገራቸውና መልሱን ላምጣ » ብለው ቆይተው።

«ይህኑ ልንገራቸውና መልሱን ላምጣ » ብለው ቀኛዝማች እየሮጡ እንደ መጡ እየሮጡ ወደ ጣሊያን ሹማምት ሄደው ዘለግ ያለ ጊዜ ሲነጋገሩ ከቆዩ በሁዋላ ተመልሰው፥ የኮሎኔሉን መልስ ለራስ አስታወቁ። መልሱ ከሞላ ጎደል እንዲህ ነበር።

«ተከበዋልና በከንቱ ሰው ከሚያልቅ በፈቃድዋ እጅዎን እንሰጡ እንጠይቅዎታለን። ፈቅደው እጅዎን የማይሰጡ ከሆነ ግን እስካሁን ባደረጉት ሁሉ ለርስዎ ከፍ ያለ አክብሮት ስላለን እንዲህ በድንገት አደጋ ጥለን አንይዝዎትም በጦርነት ህግ የተደነገገውን ስነ - ስራት በመከተል ተዋግተን ነው የምይዝዎ። ስለዚህ ምርጫውን ለርስዎ እንተዋለንና መክረው አስበው ውሳኔዎን ያስታውቁን። እስከዚያ ድረስ እኛ፥ ከወንዙ ወዲያ ማዶ ሄደን እንቆያለን። »

ወዲያው ጣሊያኖች ወንዙን ተሻግረው ሲሄዱ ራስ መኳዋንንታቸውንና የሆለታን መኮንኖች እንዲሁም ከጅማ መጥተው የተጨመሩትን መኳዋንንት ሰብስበው ከመንገዱ አጠገብ ወደ ጫካው ትንሽ ገባ ብለው ምክር ያዙ።

ያነለት የጣሊያን የጦር አለቆች ያሳዩትን ጭዋነትና ደመ - በራድነት በሽሬ፥ የጦር ግንባር - ለማስፈራራት ሲሉ ብቻ - ይሸሽ የነበረውን ሰራዊት በእሳተ - ገሞራ ቦምብ ከማቃጠላቸውና እንደ ተባይ በመርዝ ከመፍጀታቸው ጋር ሳነፃፅረው ጣሊያኖች ባንድ አካሉ ሁለት የተለያዩ መልኮች ያሉት ሰው መስለው ታዩኝ

ያነለት ጎጀብ ወንዝ ላይ የሆነው ሁሉ በእለቱ ብቻ ሳይሆን ካለፈ በሁዋላም መለስ ብሎ ስያስቡት የሚያስገርሙና የማይገቡ ነገሮች ያሉበት ነው! ከሁሉ አስቀድሞ መንገዱን እያሰሱ አማን መሆኑን እንዲያረጋግጡ ከሰዎቻቸው ጋር ቀደም ብለው የሄዱት ፊታውራሪ ከበደ ያዘውና ቀኛዝማች ደጀኔ ርገጤ ጎጀብ ወንዝ ላይ ድንገት በጣሊያን ወጥመድ ውስጥ ሲገቡ፥ እጃቸውን ከመስጠት በቀር ሌላ ማማረጫ ባይኖራቸውስ ቃፊር ለሆኑለት ሰራዊት አንዳች ያደጋ ምልክት ማሳየት አይችሉም ኖሮዋል? ከዚያ ቆይቶ የተከተለው ስደተኛ ህዝብና ጉዋዙ እንዴት ነው አንድ ወሬ ነጋሪ እንኩዋ ወደ ሁዋላ ሳይተው እወንዙ እንደ ደረሰ እዬተሻገረ እጁን የሰጠ? ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ከራስ ሰራዊት ብዙ የራባቸው የደከማቸውና ጥይት ያለቀባቸው አባሎች ተስፋ ቆርጠው ራስና መኩዋንንቱ ከመንገዱ አጠገብ ተሰብስበው በመምከር ላይ መሆናቸውን እያዩ፥ «ምን ይሉን » ሳይሉ በገሀድ መሳሪያቸን እያስረከቡ እጃቸውን ሲሰጡ ይታዩ ነበር! ይህስ ምን ይባላል? የሚያስገርም አደለም? ዛሬ ከብዙ አመታት በሁዋላ ለሚሰሙት የሚያስገርም ነው! በእለቱ እዚያ ቆመን እናይ ለነበርን ግን የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያስደነግጥና የሚያስለቅስ ስለ ነበረ አንዳችን የድካማችን ሁሉ መጨረሻ መሆኑ ተሰምቶን አለቀስን። በምክሩ ላይ ከመዋጋቱ እጅ መስጠቱ የተመረጠበት ምክንያትም ይህ ሁሉ ታይቶ መሆኑን እዚያ የነበሩ ሰዎች ነገሩኝ። እኒያ ሰዎች እንደ ነገሩኝ የሰራዊቱ እምራብና መድከም የጥይት ማለቅ ከሁሉም ይልቅ ያካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ማጣት ይህ ሁሉ ሰፊ ክርክር ከተደረገበት በሁዋላ እንዲህ ባለ ሁኔታ ሆነን ጦርነት መግጠሙ ሰው ከማስጨረስ በቀር ወደ ግባችን ስንዝር የማያራምድ ስለሆነ አንዳንድ ውለታዎች ተጠይቀው ጣሊያኖች የሚቀበሉ

ከሆነ እጅ መስጠቱ የሚሻል በመሆኑ ተወሰነ። «ተጠየቁ » ከተባሉት ውለታዎች የማስታውሳቸው የሚከተሉት ነበሩ።

፩ኛ፡- ለኢትዮጵያ ነፃነት ለመዋጋት ከኢጣሊያ የጦር ሰራዊት አምልጠው በዚያ ጊዜ ከራስ እምሩ ጦር ጋር የነበሩት ኤርትራውያን ከሌሎች የራስ ሰራዊት አባሎች የተለዬ ቅጣት እንዳያገኛቸው ሙሉ ምህረት እንዲደረግላቸው፤

፪ኛ፡- ወለጋ ውስጥ ቡናያ ላይ የጣሊያንን አይሮፕላን ባቃጠሉትና በውስጡ የነበሩትን ጣሊያኖች በገደሉት የሆለታ መኮንኖች ላይ ያን በማድረጋቸው የተለዬ ቅጣት እንዳይደረግባቸው፤

፫ኛ፡- ራስ እምሩን ተከትለው እስከዚያ ቀን ድረስ በኢጣሊያ ላይ ጦርነቱን ሲቀጥሉ በቆዩት ሁሉ ላይ ያን በማድረጋቸው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የተለየ ምንም አድርጎት እንዳይደረግባቸውና በዬሀገራቸው ገብተው እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር እንዲፈቀድላቸው » ከዚህ በላይ ያመለከትሁዋቸው አሁን የማስታውሳቸው አይነተኞች ጥያቄዎች ሲሆኑ የረሳሁዋቸው ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ።

ራስና መኰዋንንቱ በምክር ላይ እንዳሉ አንድ ከጣሊያን ሹማምንት የተላከ መላክተኛ እዬሮጠ መጥቶ ከራስ ጋር እንዲገናኝ ጠየቀ። ሰውዬው የያዘው መልእክት ጌራ ላይ የወለጋን የጣሊያንጦር ከሁዋላችን መድረሱን አስታውቆ ያ ከሁዋላ የመጣ ጦር፥ ባለበት እንዲቆም እንጂ ወደ ፊት እንዳይገፋ ለማድረግ የጣሊያንን ባንዲራ የያዙ መላክተኞች መላክ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ባንዲራውን የያዙት መላክተኞች በራስ ሰራዊት መሀከል ለማለፍ እንዲፈቀድላቸው ሹማምንቱ መጠየቃቸውን የሚያመለክት ነበር። ራስም በጉዳዩ ከመኰዋንንቱ ጋር አሳብ ከተለዋወጡ በሁዋላ መፍቀዳቸውን አስታውቀው አንድ የጣሊያንን ባንዲራ የያዘ ሰው በጥቂት ሰዎች ታጅቦ «ደረሰ » ወደ ተባለው ጦር ለመሄድ በሰራዊታችን መሀከል ሲያልፍ አዬን። እውነት - እንደ ተባለው - አዲስ ጦር ከሁዋላችን ደርሶ እንደሆነ ወይም የተከብንበት ዙሪያ መስመር የተዘጋና መውጫ የሌለን አስመስሎ አሳይቶ ራስ እጃቸውን ለመስጠት የሚጠይቁዋቸው ውለታዎች እንዳይበዙና አስቸጋሪዎች እንዳሆኑ

ተፅእኖ ለማድረግ የተፈጠረ ዘዴ እንደሆነ መቸም እኛ «መጣ » የተባለውን ጦር ስላላዬን እናውቅ!

የሆነ ሆኖ፥ ራስ እጃቸውን ለመስጠት ያቀረቡዋቸው ውለታዎች ለጣሊያን ሹማምንት ተላልፈው ሹማምንቱ በበኩላቸው በውለታዎቹ ውስጥ ከተጠየቁት ጥያቄዎች ላንዳንዶቹ መልስ መስጠት የሚችሉ ከነሱ በላይ ባለስልጣኖች እንጂ እነሱ ባለ መሆናቸው ቦንጋ ለዋናው አዛዥ ምናልባትም ላዲስ አበባ በቴሌግራም አስተላልፈው መልስ እንዳገኙ የሚያስታውቁ መሆናቸውን ገለፁ። ከዚያ ሁላችንም በያለንበት ሆነን ስንጠብቅ ውለን ከቀትር በሁዋላ አስር ወይም አስራ አንድ ሰአት ግድም ሹማምንቱ ወደ ራስ መጥተው ጥያቄዎቻቸው ሁሉ ባዲስ አበባ በኩል ለሙሶሊኒ ተላልፈው ሙሶሊኒ መቀበላቸውን ሲያስታውቁዋቸው ራስም፥ ያቀረቡዋቸውን ውለታዎች መሆናቸውን መንግስት የተቀበለ ከሆነ እጃቸውን ለመስጠት የወሰኑ መሆናቸውን አስታውቀው ሁሉም በዚያ አለቀ። የጦርነቱ የመንከራተቱ የነፃነቱ ባገራችን ጫካ ውስጥ በተስፋ የመቆየቱ ነገር እንኩዋ ለኛ ያነለት በዚያ አለቀ። ነገር ግን በተስፋ የመቆየቱ ነገር እንኩዋ ለኛ ያነለት በዚያ አለቀ። ነገር ግን ቀኑ መሽቶ ስለ ነበረ ከነመሳሪያችን በነበርንበት አድረን የመሳሪያ ርክክብ የተደረገና ወደ ቦንጋ የተጉዋዝን በማግስቱ ነበር። ታዲያ እዚያ ከመንገዱ ቀኝና ግራ ባለው ጫካ ተሰግስገን ስናድር «ጫካውን በሙሉ የጣሊያን ጦር ይዞታል » ተብሎ ተነግሮን የነበረ ቢሆንም የጣሊያንን ጦር እዚያ መኖር የሚያሳይ አንዳች ምልክት አላዬንም። ሁለተኛ ከጣሊያን ሰራዊት አምልጠው ከራስ እምሩ ጋር የነበሩት ኤርትራውያን «ሙሶሊኒ ምህርት አድርገውላቸዋል ተብሎ አደሩ። ከዚያም ከኢትዮጵያ ለመውጣት መቻላቸውን ሁዋላ ሰማሁ። ስለዚህ መጀመሪያ ድንገት ከጣሊያኖች ጋር ስንገናኝ ቀኛዝማች መጊድ «ከመንገዱ ግራና ቀኝ ያለው ጫካ በሙሉ በጣሊያን ጦር ስለተያዘ ተከበዋል » ብለው ለራስ የነገሩዋቸውን እነዚህ የተመለከቱት ሁለት ነገሮች ያስተባብሉዋቸዋል።

## ምዕራፍ ሃያ

# ቦንጋ

ክቡር ራስ እምሩ አብረዋቸው ከነበሩት መኰዋንንት ጋር ጎጀብ ወንዝ ላይ መክረው ያካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ካለማግኘትም ሌላ የስንቅና የትጥቅ እጥረት በሰራዊቱ ላይ ብርቱ የመንፈስና የአካል ድካም ያስከተለ መሆኑን በመገንዘብ እጃቸውን ለመስጠት መወሰናቸውን ባለፈው ምዕራፍ አመልክቻለሁ። ያን ውሳኔ ለማድረግ የተጠየቁትን ውለታዎች ጣሊያኖች መቀበላቸውን እስኪያስታውቁ ቀኑ ስለመሸ ሌሊቱን እዚያው ማደራቸውን በዚያ ምዕራፍ ተነግሮዋል።

በማግስቱ ወንዙን እየተሻገርን መሳሪያችንን ለጣሊያኖች ካስረከብን በሁዋላ አርበኝነታችን ቀርቶ ምርኮኞች ስለሆን፥ ብዙ ምርኮኞች ወደ ተሰበሰቡበት ወደ ቦንጋ ተወስደን። ቦንጋ ስንደርስ የማረኩን ሹማምንት ለበላያቸው፥ በዚያ ክፍል የጣሊያን ጦር ሰራዊት ዋና አዛዥ ለነበሩት ለኮሎኔል (ሁዋላ ጀነራል) ማልታ አስረከቡን።

ኮሎኔል ማልታ ባችር ጊዜ (ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 1929) ምእራብ ኢትዮጵያ የያዙበትን ፍጥነትና የጦርነትም የፖለቲካም ስልታቸውን ወይም እቅዳቸውን ተከታትሎ የተመለከተ ሁሉ ጠላት እንኳዋ ቢሆን እንዲያደንቃቸው ይገደዳል!

ፋሽስት ኢጣሊያ የኢትዮጵያን ነዋሪ ነፃነት ለማጥፋትና ህዝብዋን በቅኝ ግዛት ቀንበር ጠምዳ ለመጨቆን የተነሳችለትን የእብሪት አላማ ለማስፈፀም የቆሙ የዚያ ክፉ አላማ መሳሪያ በመሆናቸው ኢትዮጵያዊ እንደ መሆኔ ኮሎኔል ማልታን አጥብቄ እጠላቸዋለሁ። ነገር ግን እቅዳቸውን በጥንቃቄ ሰርተው ጊዜና የሰው ህይወት በከንቱ በማይባክንበት ትንሽ የማያቃውስባቸው መሪ በመሆናቸው ጠላት እቅዳቸውን ትንሽ የማያቃውስባቸው መሪ በመሆናቸው ጠላት ብሆንም በሙያቸው እንዳደንቃቸው እገደዳለሁ። የእቅድ

አሰራራቸውን ዘዴና ፍጥነታቸውን የተቻለውን ያክል አሳጥሬ በሚከተሉት መስመሮች ላንባቢዎች መግለስጽ እወዳለሁ።

እስከ ጥቅምት 1929 አጋማሽ ወይም እስከዚያ ወር መጨረሻ ግድም፤ ክቡር ራስ እምሩና እኛም ከሳቸው ጋር ጎሬ ስለ ነበርን ያን ጊዜ ጣሊያኖች ወደ ምእራብ ኢትዮጵያ አለመድረሳቸውን እናውቃለን። ስለዚህ ኮሎኔል ማልታ በምእራብ ኢትዮጵያ ዘመቻውን የጀመሩ በትቅምት 1929 መጨረሻ ግድም ነው ማለት ነው። እንግዲህ በዚያ በጥቅምት መጨረሻ ግድም ወደ ሰዬ (ወለጋ) ይዘምቱና በጦር በማስፈራራትም ይሁን በፖለቲካ በማግባባት የሰዬን ባላባቶችና ህዝቡን ያሳምናሉ። ከዚያ ሰዬ ከደጃዝማች ጆቴ ልጆች ወሰና የሚባሉትን ሾመው እዚያው ይተውና ሁለተኛውን ልጅ ደጃዝማች ዮሀንስ ጆቴን ይዘው ወደ ኢሉባቦር ይሻገራሉ። ኢሉባቦር ለጊዜው የኢትዮጵያ መንግስት እንደራሴ ሆነው ጎሬ የተቀመጡትን ቢትወደድ ወልደ ፃድቅን ከልጅ ልጃቸው ጋር ይይዛሉ። ከዚያ እነሱንም ይዘው ወደ ከፋ ይሻገሩና የከፋን ጥብቅ ገዥ ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴን ይይዛሉ። ከዚያ ክቡር ራስ እምሩ ወለጋና ጅማ ተይዘው ሲቆዩዋቸው ወደ ከፋ ቦንጋ የሚሄዱ መሆናቸውን እቅዳቸውን ጎጀብ ላይ ያጠምዱና ሲጠብቁ ይቆያሉ። ከዚያ ያ ጎጀብ ላይ የተጠመደ ወጥመድ አንድ ጥይት ሳይተኮስ የጎጃሙን ጠቅላይ ገዥ ክቡር ራስ እምሩን ብቻ ሳይሆን የጅማውን ገዥ ከንቲባ ጋሻው ጠናን ጭምር ይይዝላቸዋል። ከዚያ በሁዋላ ከደጃዝማች ሀብተ አምርያም በቀር የምእራብ ኢትዮጵያን ጠቅላይ ገዥዎች ሁሉ ምርኮኞቻቸውን አድረገው ባንድ ላይ ይሰበስቡና ቦንጋ ያስቀምጡዋቸዋል። ምእራብ ኢትዮጵያንም እንዲያ ባለ ጭምር ጊዜ ከሰሜንና ከመሀል ኢትዮጵያ ጋር ተጨምሮ የጣሊያን ቅኝ ግዛት እንዲሆን ለማድረግ ይችላሉ! የሚያስደንቅ ችሎታ ነው! ምናልባትም ኰሎኔል ማልታ በምእራብ ኢትዮጵያ ያሳዩት ችሎታቸው ይሆናል ወዲያው ከኰሎኔል ማልታ በምእራብ ኢትዮጵያ ያሳዩት ችሎታቸው ይሆናል ወዲያው ከኮሎኔልነት ወደ ጀነራልነት ማእርግ ለማደግ ያበቃቸው!

በምእራብ ኢትዮጵያ ጦራችን እንዲያ ባጭር ጊዜ ተፈትቶ ያ የኢትዮጵያ ክፍል በጣሊያኖች መያዙ የማይሻር የመንፈስ ስብራት ነበር ያደረሰብን። አንባቢዎች እንደሚያስታውሱት ክቡር ራስ እምሩ ተከዜ ሸለቆ

ውስጥ በሰፈርንበት እኔን ወደ ሱዳን ሊልኩኝ አስጠርተውኝ ስንነጋገር ጦራችንን በሽሬ ግንባር ድል ሳይሆን ለምን ወደ ሁዋላ እንደ መለሱት በጠየቅሁዋቸው ጊዜ «ረዥም ጊዜ ልንዋጋበት የምንችል ለኛ የሚመች ቦታ ይዘን ጦርነቱን ለመቀበል አስበን ነው » ብለው ጦርነቱን ለመቀጠል፥ ከሰሜን ኢትዮጵያ ምእራብ ኢትዮጵያ የሚሻልበትን ምክንያት ዘርዘር አድርገው ሲነገሩኝ በሰጡኝ ምክንያት እኔም አምኘበት ደስ ብሎኝ ነበር ወደ ተላኩበት የሄድሁ።

ራስ እንዳሉት ጦራችን ረዥም ጊዜ ጦርነቱን ለመቀጠል ከሰሜን ኢትዮጵያ የምእራቡ ክፍል አገራችን የሚስማማ እንደሚሆን ታምኖባቸው የነበሩት ምክንያቶች አጥጋቢ መሆናቸውን ለማስረዳት ሁለቱ ክፍሎች (ሰሜንና ምእራብ) በዚያ ጊዜ የነበሩትን ሁኔታ በማነፃፀር ልዩነታቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ባጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ።

፩ኛ፥ ሰሜን ኢትዮጵያ፡- ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር መነሳትዋ ከወልወል ግጭት ጀምሮ የታወቀ ቢሆንም የኢትዮጵያ መንግስት እምነቱን በአለም ማህበር ላይ ጥሎ ሳይሰናዳ ጣሊያኖች በምስራቅና በመሀል ትግራይ አዲግራትን መቀሌን፥ አድዋን አክሱምንና የዚያን አካባቢ ሁሉ አልፈው እስከ ተምቤን ደርሰው ነበር። በምእራብ ትግራይ በኩል እንዲያውም የትግራይን ግዛት በጠቅላላው ይዘው ተከዜ አፋፍ አጠገብ ዳባጉና ላይ መሽገው ነበር። ታዲያ በዚያ በያዙት የትግራይ ክፍል ሁሉ ምቹ ቦታዎች እየመረጡ ምሽጎቻቸውን መሽገው እርዶቻቸውን የመኪና መንገዶች ሰርተው ስለ ነበረ፥ ወታደርና ትጥቅም ስንቅም ሌላም ለጦርነት የሚያስፈልግ ነገር ሁሉ የማመላለስ ችግር ሊያገኛቸው ለጦርነት ታዝዞ ሊዋጋ ሲሄድ ባገሩ መሬት ቀድሞት ምሽጉን መሽጎና እርዱን አርዶ ከሚጠብቀው ጠላት ጋር ነበር የሚዋጋ። በሰሜን ኢሊያኖች የኢትዮጵያን ሰራዊት አስቀድመው ባሰናዱዋቸው ምሽጎችና እርዶች ተተግነው ብቻ ሳይሆን ቦምብና መርዝ እንደ እንደ ዝናም ከሰማይ እያወረዱ ጭምር ነበር የሚወጉት። አይም ሁሉ ሁኖ «በመጀመሪያው የተንቤን ጦርነትና በዳባጉና ጦርነት ኢትዮጵያውያን ጠላትን ሳይቀር ባስገረመ ጀግንነት ምሽግ እየጣሱ ገብተው ጣሊያኖችን በጨበጣ ውጊያ እያሸነፉ

ከምሽጋቸው አስወጥተው ድልን ተቀዳጅተው ነበር! እንዲሁም «በሰለክለካ » ጦርነት ኢትዮጵያውያን የመጨረሻ ድል አያግኙ እንጂ የጣሊያኖች ምሽግ ጥሰው ገብተው ከብርቱ የጨበጣ ውጊያ ቦሁዋላ ጣሊያኖችን ከምሽጋቸው አስወጥተው ለማባረር መቻላቸውን ራሴ የተመለከትሁ ያይን ምስክር ነኝ! እንዲያ ያለው የኢትዮጵያውያን ጀግንነት ጠላት አስቀድሞ ባገራችን ምሽጎችን ሳይመሽ ግና ጦሩ ሲጎዳበት አዲስ ጦር ለመተካት መሳሪያና ስንቅ ሲጎድልበት ለመሙላት መንገዶችን ሳይሰራ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያና የጣሊያን ሰራዊቶች በግልጥ ሜዳል ፊት ለፊት ገጥመው የሚዋጉበት ጦርነት ቢሆን ኖሮ ምናልባት ያ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት በሰሚአን ኢትዮጵያ ያድዋን ድል ለመድገም ሳያበቃን አይቀርም ነበር! ነገር ግን ጠላታችን አስቀድሞ ባገራችን ባለቤት ሆኖ እኛ ልናሰናዳው ይገባን የነበረውን መከላከያ አሰናድቶ እዚያ ላይ እንድንዋጋ ሳልስገደደን የኢትዮጵያውያን ጀግንነት «የእሳት እራት » ጀግንነት ሆኖ ቀረ!

፪ኛ፡- ምእራብ ኢትዮጵያ፡- የምእራብ ኢትዮጵያ ሁኔታ ከሰሜኑ ፈፅሞ የተለየል ነበር። ከሁሉ አስቀድሞ፤ ምእራብ ኢትዮጵያ እንደ ሰሜን ጣሊያኖች አስቀድመው በመረጡላቸው ቦታዎች ምሽጎቻቸውን ያልመሸጉበት ሰራዊታቸውንና ለሰራዊታቸው የሚያስፈልገውን ትጥቅና ስንቅ ከመነሻው እስከ ምሽጐቻቸው ለማመላለስ መንገዶች ያልሰሩበት ነበር። እንዲሁም ምእራብ ኢትዮጵያ ደናማ በመሆኑ የጣሊያን አይሮፐላኖች በሰሜን እንዳደረጉት ኢትዮጵያውያንን በግላጭ አግኝተው በቦምብና በመርዝ ለማጥቃት የሚችሉበት ነበር። ባንፃሩ ለኢትዮጵያውያን ከማናቸውም የጠላት ጥቃት ለመከላከልና ጠላትን ተሸሽጐ ለማጥቃት የሚያችል ምቹ ነበር። ስለዚህ ያ በሰሜን ኢትዮጵያ የታየው የኢትዮጵያውያን ቆራጥነትና ጀግንነት በምእራብ ኢትዮጵያም ቢኖር ኖሮ የምእራብ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ገዥዎችም «ማን በማን ውስጥ ሆኖ ማን የማንን ትእዛዝ ተቀብሎ ጦርነት ሊዋጋ! » እየተባባሉ እስበስ በመናናቅ ፈንታ እንዲያ ያለውን ምስኪን አስተሳሰብ ለመቁዋቁዋም ፈቃደኞች ቢሆኑ ኖሮ የምእራብ ኢትዮጵያ ጦርነት ባለቀበት ሁኔታ ባላለቀ ነበር! ኮሎኔል ማልታም ምንም ያክል የጦርነትና የፖለቲካ እቅድ መስራት አዋቂና የሰሩትን እቅድ በሚያስገርም ፍጥነት ወደ ፍፃሜ ለማድረስ ችሎታ ቢኖራቸው ከዚያ ሁሉ ችሎታቸው ጋር የምእራብ ኢትዮጵያን ጦርነት ሶስት ወራት ተካክሎ

ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ ባልተሳካላቸው ነበር! ነገር ግን የኢትዮጵያ ጠቅላይ አገረ ገዢዎች ታዝዘው እንጂ በስምምነት ተባብረው መስራት የለመዱ አልነበሩም። ወታደሩ ከትጥቅና ከስንቅ እጥረት ሌላ ያካባቢው ህዝብ ድጋፍ ስላልነበረው ተስፋ የቆረጠ ነበር። ህዝቡም የቅኝ ግዛት አስተዳደር ስለሚያከትለው የባርነት ኑሮም ሆነ በዚያ የባርነት ኑሮ ሊያኖር የመጣን ጠላት መቃወም የራስን ጥቅም መጠበቅ ስለ መሆኑ አስቀድሞ አንዳች ገለፃ ወይም ቅስቀሳ አልተደረገለትም ነበር። ስለዚህ በጠላት ገንዘብና መሳሪያ እየተባበለ፤ ጠላትን በመቃወም ፈንታ ለጠላት ረዳት ሆነ። በዚህ ሁሉ ምክንያት ለማውራት በሚያሳፍር አጭር ጊዜ ውስጥ ድል ሆነን፤ እጃችንን ብቻ ሳይሆን ምእራብ ኢትዮጵያን ጭምር ለጠላት ሰጠን!

ቦንጋ ከቡር ራስ እምሩ ከንቲባ ጋሻው ጠናና ከነሱ ጋር የነበሩት ታላላቅ መኩዋንንት እንዲሁም የሆለታ መኮንንኖችና ከፈረንጅ አገር ትምህርታቸውን ጨርሰውም ሳይጨርሱ አቋዋርጠውም ላገራቸው ሊዋጉ የመጡ ምሁራን ኰሎኔል ማልታ በነበሩበት ባገረ - ገዡ ግቢ ከቅጥር ውስጥ በድንኩዋን እንዲሰፍሩ ተደርጎ ነበር። ስለዚህ ጎልቶ አይታይ እንጂ፣ በነሱ ላይ ቁጥጥር መኖሩን ባንዳንድ ምልክት እናውቅ ነበር። በጠቅላላ ሰራዊቱ ግን ካገረ - ገዡ ግቢ ቅጥር ውጪ ተበታትኖ ስለ ነበረ የሰፈረ አንዳች ቁጥጥር የነበረበት አይመስልም። ኖሮ እንደ ሆነም ለኛ አይሰማንም ነበር። አቶ በትረ ፅድቅ ካሳና እኔ ከሰዎቻችን ጋር ከግቢው ቅጥር ውጪ ካንድ ወንድ አጠገብ ሰፍረን ከዚያ በፈለግን ጊዜ ራስንና እግቢው ውስጥ የሰፈሩትን ወዳጆቻችንን ልናይ ስንሄድ እንኩዋንስ ችግር ሊገጥመን «ለምን መጣችሁ » ተብለን ተጠይቀን አናውቅም። ሌሎችም ከግቢው ቅጥር ውጪ የሰፈሩት ሁሉ እንዲሁ እንደ ልብ ማግባትና መውጣት ከተማ ውስጥም መዘዋወር ይችሉ ነበር።

በምግብ ብኩል ከቅጥር ውጪ ከሰፈርነው እውስጥ የሰፈሩት ምርኮኞች በመጠኑም ቢሆን ይሻሉ ነበር። እግቢ በምንገባበት ጊዜ እንደ ተመለከትነው ዶክተር አለመወርቅ በየነ ጣሊያኖች ምግብ ከሚያከፋፍሉበት እንደ ዳቦ፥ በቆርቆሮ የታሸገ ምግብ ስኩዋርና ሻይ እንዲሁም አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች እያሸከመ አምጥቶ እዚያ ለሰፈሩት የኛ ሰዎች ሲያከፋፍል እናይ ነበር።

ዶክተር አለመወርቅ እዚያ ለሰፈሩት ምርኮኞች ተተሪ ሆኖ መመደቡን ያን ጊዜ ሰማሁ።

ከፈረንጅ አገር ከተመለሱት ምሁርና እና ከሆለታ መኮንኖች መሀከል ብዙ የሲጋራ ሱሰኞች ነበሩ። ታዲያ ዶክተር አለመወርቅ ያመጣው ሲጋራ በማይበቃበት ጊዜ፥ ሳጥኑ እየተከፈተ አንዳንድዋን ሲጋራ ሁለት ሰዎች የጋራ እንዲያጤስዋት ስትሰጣቸው «እኔ አንድ ጊዜ ስመጥ አንተ ሁለት ጊዜ መጠጥህ እኔ ባጭሩ ስስብ አንተ በረዥሙ ሳብህ » በመባባል በኒያ ሱሰኞች መሀከል የነበረው ፍጅት የሚያስቅም የሚያሳዝንም ነበር!

የቦንጋ ከተማ (ወይስ መንደር ልበለው?) ያን ጊዜ ከማናቸውም ከተማ ወይም አገር ጋር የሚያገናኝ የመኪና መንገድ ያልነበረው ከመሆኑ ሌላ ያይሮፕላን ማረፍያም አልነበረው። እዚያ ለነበረው የጣሊያን ስራዊት ምግብ ሆነ ሌላ ለእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ በአይሮፕላን ነበር የሚደርስ። ገብያ በማይውልባቸው ቀኖች አይሮፕላኖች ይመጡና ዝቅ ብለው ሊያወርዱ የፈለጉትን ሁሉ እገብያው ሜዳ ላይ በዣንጥላ (ፓራሹት) አውርደው ይሄዳሉ።

ስለዚህ የመኪና መንገድ እስኪከፈት ድረስ የምግብና የሌላ ለእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ እጥረት ስለ ነበረ፥ ከቅጥር ውጪ የነበረውን ምርኮኞች ከማራኪዎቻችን አንዳች የምናገኘው ነገር አልነበረም። ነገር ግን አስራ አምስት ቀናት ይሁን ሶስት፥ ሳምንት ያክል ቦንጋ፥ በቆየንበት ጊዜ ባለ መጋዘን መኪና ቀድሞ ጫካውን ሲጠርግ ቡልደዘር ተከትሎ መሬቱን እያስተካከለ ጊዜያዊ መንገድ ተከፈተና ስንቅም ሌላ ለሰራዊቱ የሚያስፈልግ ነገርም የጫኑ ካሚዮኖች ቦንጋ መግባት ጀመሩ። ብቻ ምግብ የጫኑ ካሚዮኖች መግባት እንደ ጀመሩ ቦንጋን ስለ ለቀቅን የምግቡ መድረስ የኛን ሁኔታ ምንም አልለወጠም።

ቦንጋን የለቀቅን ከፈረንጆች አዲስ አመት በሁዋላ ነበር። ላመት በአሉ መድፍ ሲተኮስ በትረ ፅድቅና እኔ፥ እነ ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው መጥተው በኮሎኔል ማልታ ላይ አደጋ የጣሉ መስሎን ደስታችን ቅጥ መጠኑን ያጣ ሆኖ ነበር።

ያን ጊዜ ራስ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች ገብረ ማርያምና ደጃዝማች በየነ መርእድ ከነየሰራዊታቸው እጃቸውን ሳይሰጡ፥ በሲዳሞ በባሌና በገምጎፋ በየግዛታቸው እንዳሉ ነበሩ። ታዲያ መነሻው ያልታወቀ ወሬ «ራስ ደስታ ደጃዝማች ገብረ ማርያምና ደጃዝማች በየነ፥ በአዲስ አበባ ላይ ሊዘምቱ ተነስተዋል፥ ጅማን ሊይዙ ተቃርበዋል ወደ ከፋ መጥተው ኮሎኔል ማልታን ሊዋጉዋቸው ነው » እየተባለ ይናፈስ ስለ ነበረ «ምኞት ባለበት አሰቱም ይመስላል እውነት » እንደሚባለው እንመኘው የነበረ ነገር ሆነና ከሶስቱ ጠቅላይ አገረ - ገዥዎች አንዱ ወይም ሶስቱ ባንድነት በኮሎኔል ማልታ ላይ አደጋ የጣሉ መሰለን። ነገር ትንሽ ቆይተን ተኩሱ ለበአሉ ክብር መሆኑን ስንሰማ፥ ደስ ያለንን ያክል የሀዘን ስሜት እንደ ገና ድል የመሆን ስሜት ተሰማን። ያነለት ለበአሉ ክብር ኮሎኔል ማልታ ለጣሊያኖች ብቻ ሳይሆን ከቅጥር ውስጥ ለሰፈሩት ኢትዮጵያውን ምርኮኞች ጭምር ግሩም የሆነ ግብዣ ማድረጋቸውን ሁዋላ ሰማን።

በአሉ እንዳለፈ ማራኪዎቻአችን ወዴት እንደሚወስዱን ሳናውቅ ክቡር ራስ እምሩና አብረናቸው የነበርን ምርኮኞች የጅማን መንገድ ይዘን ጉዞ ጀመርን። ክቡር ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴም አብረውን ነበሩ። የጎጀብን ወንዝ፥ በተማረክን ጊዜ በተሻገርንበት ሳይሆን በሺሺ ግንባር ተሻግረን እሜዳው ላይ አርፋ የቆየችን አይሮፕላን ክቡር ራስ እምሩንና ደጃዝማች ታዬን ይዛ ሄደች። ያን ጊዜ ራስና ደጃዝማች ወዴት እንደ ተወሰዱ ከጣሊያኖች በቀር ያወቀ ሰው አልነበረም። ሁዋላ ግን አዲስ አበባ አይሮፕላን ማረፊኢያ ወርደው አጭር ጊዜ ቆይተው፥ ከዚያ ከተማ እንኩዋ ሳይገቡ በቀጥታ ወደ ጣሊያን አገር መወሰዳቸውን ሰማን። የቀረውነው ምርኮኞች ጉዞዋችንን ቀጥለን - በስንተኛ ቀን እንደሆነ ረስቸዋለሁ - ጅማ አይሮፕላን ማረፊያው አጠገብ ሰፈርን። ከዚያ በማግስቱ ይመስለኛል ከምሁራኑና ከከመኩዋንንቱ መሀከል ጥቂት በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተወሰዱ። ከተከታዩ ቀን ከቀትር በሁዋላ ግድም በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ከተወሰዱት ምርኮኞች መሀከል አንዱ እኔ ነበርሁ።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

# አዲስ አበባ

አዲስ አበባ እንደ ደረስን ካይሮፕላን ማረፊያ በቀጥታ የ «ፖለቲካ ፅህፈት ቤት » ወደ ተባለው ቦታ ተወሰድን። ያ ቦታ ድሮ «ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት » ይባል የነበረው አሁን «አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ » የሚባለው ነው። እዚያ ‹ሲኞች ማርቻኖ› የተባሉ አማርኛ ግሩም አድርገው የሚያውቁ ጣሊያን የስማችንን ዝርዝር ከጅማ እስከ አዲስ አበባ ካደረስን ሰው ተቀብለው ሁላችንንም በተራ በየስም ከናባታችን እየጠሩ እድሜያችንን የተወለድንበትን አገርና እንዲያ እንዲያ ያለውን ለመታወቂያነት የሚያገለግል ነገር ሁሉ እየጠየቁ ይመዘግቡ ነበር። የኔ ተራ ደርሶ ሲጠሩኝ «አቤት » ብየ ከምርኮኞች ጉዋደኞቼ ተለይቼ እሳቸው ተቀምጠው በሚመዘግቡበት እስክደርስ ዝም ብለው በመገረም አይን ይመለከቱ ነበር። በድሜ ልጅ ከመሆኔም ሌላ የለበስሁት የካኪ ቁምጣ ኮትና ሱሪ ስለ ነበረ ይብሱን ልጅ ያስመስለኝ ነበር።

«ሀዲስ አለማየሁ ማለት አንተ ነህ? ግሩም ነው! ‹ቤት ሰው ከሌለበት ቁንጫ ይፈላበታል!› የሚሉት ተረት አሰት አይደለምኮ! ባገሩ ሰው ሲጠፋ ጊዜ አይደለም እንደናንተ ያላችሁ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ፈንታ ወደ ጦርነት ከዚያ አልፋችሁ ዲፕሎማቶች እየሆናችሁ ውል ለመፈራረም ወደ ውጭ መንግስታት የምትላኩ? ግሩም ነው! እሺ ታዲያስ የኛ ዲፕሎማት፤ የንግሊዝ መንግስት ምን ያክል የጦር ሰራዊትና ምን አይነት የጦር መሳሪያ ለራስ እምሩ ሊሰጥ አንተስ ስለ ራስ እምሩ ምን ልትሰጥ ተፈራርመህ መጣህ? » አሉ ሲኞር ማርቻኖ ንግግራቸውን ብቻ ሳይሆን ፈገግታቸውንና አስተያየታቸውን ጭምር ባሽሙር ቀለም አስጊጠው እፊታቸው እንደ ቆምሁ አይኔን እየተመለከቱ።

እስከያነለት ድረስ እንዲያ ያለ ጥሩ አማርኛ የሚናገር ፈረንጅ አጋጥሞኝ ስለማያውቅ ለጠየቁኝ ጥያቄ በመመለስ ፈንታ ሳይታወቀኝ አይኔን ብቻ ሳይሆን አፌን ጭምር በሰፊው ከፍቼ እመለከታቸው ኖሮዋል! በውነት ደንግጫለሁ! ከጥያቄያቸው ይልቅ አማርኛቸው ነበር ያስደነገጠኝ!

«ለጥያቄየ መልስለኝ እንጂ! የጠየቅሁህን አልሰማህም እንዴ! የንግሊዝ መንገስ ምን ያክል የጦር ሰራዊትና ምን አይነት የጦር መሳሪያ ለራስ እምሩ ርዳታ ሊሰጥና ራስ እምሩስ ምን ሊያደርጉ ተፈራርመህላቸው መጣህ? ብዬ ጠይቄህ ነበርኮ! » አሉኝ።

«የጠየቁኝን ሰምቻለሁ፤ የጦር ሰራዊትና የጦር መሳሪያ ውል ልፈራረም ወደ እንግሊዝ መንግስት አልተላክሁም » አልሁ።

«ምነው የራስ እምሩ ጦር ሽሬ ድል ከሆነ በሁዋላ፥ ወደ ሱዳን ተልከህ አልሄድህም? »

«መድሀኒትና ለወታደር ልብስም ድንኩዋንም የሚሆን ካኪ ከገብያ ልገዛ ሄደው እንጂ የጦር ሰራዊትና የጦር መሳሪያ ውል ከንግሊዝ መንግስት ጋር ለመፈራረም አልነበረም ወደ ሱዳን የሄድሁ » ስላቸው ፈገግ ብሎ የነበረ ፊታቸውን ኮስተር አድርገው ላጭር ጊዜ ዝም ብለው ሲመለከቱኝ ቆዩና «በል ደግ ነው » ብለው እድሜየን የተወለድሁበትን አገርና እንዲሁም ሌሎችን ጥያቄዎች እየጠየቁኝ ነግሬያቸው ከመዝገቡ በሁዋላ አሰናበቱኝ።

ሲኞር ማርቻኖ ምዝገባቸውን እስኪጨርሱ መሽቶ ስለ ነበረ ቀኛዝማች ‹መላኩ ታዬን› አስጠርተው ሁላችንንም ወደ ቤቱ ወስዶ አሳድሮ በማግስቱ ጥዋት እንዲመልስልን አስረከቡት። ቀኛዝማች መላኩ ታዬ የክቡር ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ ልጅ ነው። ሁለታችንም በልጅነታችን ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ስንማር እንተዋወቅ ነበር። ነገር ግን ምንም እንኩዋ የተለያዩንበት ጊዜ በጣም ረዢም ባይሆን «ምናልባት ረስቶኝ ይሆናል፤ ባይረሳኝም የጣሊያን ምርኮኛ ሆኘ ሲያየኝ የማያውቀኝ መስሎ መታየቱን ይመርጥ ይሆናል » ብየ

እንደማላውቀው ሁሉ፥ አየት አድርጌው ዝም አልሁ። እሱም እንደኔ ላንድ አፍታ አየት አድርጎኝ ዝም አለ።

ያነለት እቀኛዝማች መላኩ ቤት የተምራን ምርኮኞች ምናልባት ባስራ አምስትና በሀያ መሀከል እንሆን ይሆናል። ታዲያ ለዚያ ሁሉ ሰው የቀረበው መስተንግዶ፥ (መብሉና መጠጡ) ባይነቱም ሆነ በብዛቱ ባጭር ጊኤ የተሰናዳ አይመስልም፤ ግሩም ነበር! ከራት በሁዋላ - ምናልባት ሁላችንን ባንድ ላይ ለማስተኛት እንድንተኛ ወደየተሰናዱልን ክፍሎች እንደገባን ከቤቱ ልጆች አንዱ መጥቶ ቀኛዝማች መላኩ ሊያየኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ። ልጁን ተከትዬ ስሄድ ቀኛዝማች ከልፍኙ በራፍ ቆሞ ይጠብቀኝ ኖሮ ገና በሩቅ ሲያየኝ አብረን እንዳላመሸንሁሉ እየሮጠ መጣና አንገቴን አቅፎ እስኪጨንቀኝ ድረስ እያገላበጠ ሳመኝ። ከዚያ ወደ እልፍኙ ይዞኝ ገብቶ መጠጥ እንድጠጣ ቢለምነኝ፥ በራት ጊዜ ከጠጣሁት በላይ ብጨምር ጤና እንደማላገኝ ስላስረዳሁት እንዲሁ ተቀምጠን እንጫወት ጀመር።

«ታውቃለህ? እዚያ መስሪያ ቤት ካየሁህ ጀምሬ እንዲህ ብቻህን እስካገኝህ ምን ያክል ናፍቄ እንደ ላስረዳህ አልችልም! » አለኝ።

«እኔምኮ እዚያ በማላውቀው ሰው ሁሉ መሀከል አንተን ብቻ የማውቅህ በማግኘቴ ደስ ብሎኝ መጥቼ ልስምህ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን አሁን የምገኝበትን ሁኔታ ሳስብ፥ ‹ላንተ አይበጅ ይሆናል› ብየ ነው የተውሁት » አልሁት። ከዚያ እሱ ስለ ዘመቻውም ስለ አርበኝነቱም እኔ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከገቡ ጀምረው ስላደረጉት እየተጠያየቅን ብቻችንን ስናወራ ቆይተን ወደ የምኝታችን ከመሄዳችን በፊት በማግስቱ ላደርገው ስለሚገባኝ ምክር ስጠኝ።

«ነገ ጥዋት ወደ ፖለቲካ ፅህፈት ቤት መልሼ እንድ ወስዳችሁ ሲኞር ማርቻኖ አዝዘውኛል። ከዚያ በሁዋላ ምን እንደሚያደርጉዋችሁ ከነሱ በቀር ምቾም የሚያውቅ የለ። እስከ ዛሬ ድረስ እንኩዋ ጣሊያኖች - ምናልባት ሰው እንዳይሸሻቸው ሊሆን ይችላል - ፈቅደውም ሆነ ወይም በሀይል ተገደው በሚገቡት አርበኞች ላይ ክፉ ሲሰሩ አላየሁም። ነገር ግን ራስ እምሩንና የኔ አባት ወደ ጣሊያን አገር የወሰዱዋቸው በእስረኝነት እንደሆነ እስከ ዛሬ

ይከተሉት የነበረውን ፖለቲካ ሊለውጡ አስበው ሊሆን ይችላልና፥ ነገ በናንተ ላይ ስለሚያደርጉትም እርግጠኛ መሆን አይቻል! ስለዚህ ለማናቸውም ነገ ጥዋት እነሱ እጅ ከመግባትህ በፊት እስካሁን ደህና መሆንህንና ሌላም ለዘመዶችህ የምትልከውን መልእክት የሚያደርስልህ፥ የታመነ ሰው እንዳለህ ሰጥተህ ሌሎችን ይዤ ፖለቲካ ፅህፈት ቤት ግቢ ከመግባቴ በፊት ድረስብኝ » አለኝ።

«የታመነ ሰውስ አለኝ፤ ግን አንተን የሚያሰጋ አይሆንም? »

«ምኑ? »

«ቅድም እንዳልኸው ነገ የሚሆን እስኪታወቅ፥ ለጊዜው እስረኛ ነኝኮ! ታዲያ አሳድረህ እንድትመልስ የተሰጠሁህን እስረኛ መልቀቅህ ቢታወቅ አያሰጋህም? »

«ለምን ይታወቃል? አንተ አዋጅ እየተናገርህ አትሄድ! » አለ በቀልድ እንደ መሳቅ ብሎ።

«የተነገረ ነገር ምንም ቢሆን መታወቁ አይቀር! » አልሁት።

«ግዴለህም፤ በዚህ አትስጋ። ብቻ በሶስት ሰአት ስለ ሆነ ግቢኢ የምንገባ በጣም በጥዋት ሄደህ ጉዳይህን ፈፅመህ ለሶስት ሰአት አስር ደቂቃ ጉዳይ እንድትመለስና «አንበሳ በር » ይባል በነበረው የግቢው የምስራቅ በር እንድትጠብቀኝ » አለኝ። እከዚያ አንድ ልጅ ጠርቶ በጥዋት ስወጣ እንዳይከለክለኝ ዘብ ለሚጠብቀው ወታደር ነግሮኝል እንዲያድር እዘዘልኝና እዚያው እሱ እልፍኝ አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ የምተኛበት ተሰናድቶልኝ እዚያ አደርሁ።

ቀኛዝማች መላኩ ታዬ፥ አሳድሮ እንዲመልስ የተሰጠሁትን እስረኛ ያላንዳች ጠባቂ ጉዳየን ፈጽስሜ እንድመለስ መልቀቁ የጣለብኝን እምነት የማላጎድል መሆኔን ስላመነ ይሆን? ወይስ የጣለብኝን እምነት አጉድዬ ባመልጥም በኔ ምክንያት የመጣውን ሁሉ እስከ መቀበል ድረስ ይወደኝ ስለ ነበረ ይሆን? በማናቸው ምክንያት መሆኑን አላውቅም። ብቻ ያም ይሁን ይህ፥

ከዚያ በሁዋላ ባንገናኝም እድሜ ልኬን ሳስታውሰው የምኖር ውለታ ጥሎኝም ቀረ።

በጥዋት ተነስቼ ለዘብ ጠባቂው ወታደር ስሜን ነግሬ አባቴ ‹ቄስ ባድማ ያለው› ወደ ሚኖሩበት እንጦጦ ስዊድን ሚስዮን ትምርት ቤት ሄድሁ። ቄስ ባድማና በልተቤታቸው ወይዘሮ የሽመቤት ተገኝ፥ ልጆቻቸውም ሁሉ ከቤተሰቡ አባሎች አንዳንድ ይቆጥሩኝ ስለ ነበረ መዝመቴንና ከዘመዶቻቸው አለመመለሴን ሰምተው ኖሮ፥ ሲያዩኝ ደስታቸው እጅግ ታላቅ ሆነ። እመይቴ የሽመቤትና ልጃቸው ወይዘሮ አዲስ አለም ባድማ «እልል » ሲሉ እዚያ ግቢ ከሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ሰምተው ተሰበሰቡ። እቤት ገብተን ጎጃም ለዘመዶቼ እንዲተላለፍልኝ የፈለግሁትን መልእክት ቶሎ ቶሎ አሰናድቼ ላባቴ ቀኤስ ባድማ ሰጥቼ ቁርሴን በልቼ እርሳቸውም በኔ፥ ላይ የሚወስደውን ለማወቅ ስለ ፈለጉ አብረውን ወደ ፖለቲካ ፅህፈት ቤት ሄድን።

ከቀኛዝማች መላኩ ጋር በተቃጠርንበት አንበሳ በር ቆመን ስንጠብቅ ቀኛዝማች መላኩ በበቅሎው ተቀምጦ በብዙ እስረኞች ታጅቦ ደረሰና ይዞን ወደ ግቢ ገባ። እዚያ አንድ ባንድ እየተጠራን ወደ ሲኞር ማርቻኖ ፅህፈት ቤት ገብተን አዲስ አበባ የምንቆይበትን ቦታ እያስመዘገብን፥ ከኔ በቀር ሌሎች ሁሉ ያነሉት ወይም በማግስቱ የሚዋሱዋቸውን ሰዎች ይዘው ቀርበው እንዲያስፈርሙ ግዴታ እየገቡ መውጣታችውን ነገሩኝ። እኔ ግን አባቴ ቄስ ባድማ ቤት የምቆይ መሆኔን ካስመዘገብሁ በሁዋላ እሳቸው እዚያ ስለ ነበሩ በተፈለግሁ ጊዜ ሊያቀርቡኝ ዋስ ሆነው ፈረሙና ልንወጣ ስንል፤

«ስላንተ የመጨረሻ ሁኔታ የሚወሰነው እስኪነገርህ ድረስ በየቀኑ - ጥዋት ከሶስት እስከ ሰባት ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ - እየመጣህ ከዘብ ጠባቂው ጋር በምታገኘው ደብተር እንድትፈርም! » ብለው ሲኞር ማርቻኖ ለኔ ከነገሩኝ በሁዋላ «አንድ ቀን ሳይፈርም ቢቀር በሀላፊነት የሚጠየቁ እርስዎ መሆንዎን ማወቅ አለብዎ! » አሉ ወዳባቴ ቄስ ባድማ ዘወር ብለው። ሁዋላ ጠይቄ እንደ ተረዳሁት ከጅማ አብረን ከመጣን እሰረኞች መሀከል በየቀኑ እንዲፈርም የታዘዘ ከኔ በቀር አልነበረም።

አባቴ ቄስ ባድማና እኔ ከፖለቲካ ፅህፈት ቤት ወደሳቸው ቤት እንደ ተመለስን አቶ «ብርሃኑ ወንድምና » አቶ «መኰንን ቸኮል » የኔን ወሬ ሰምተው መጡ። ከሁለቱም ጋር ለከፍተኛ ትምርት ወደ «በይሩት » እስኪሄዱ ድረስ ከሚሲዮን ትምህርት ቤት እስከ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ድረስ አብረን ስንማር የኖርን፥ ጉዋደኞች ነበርን። ከበይሩት ሲመለሱ እኔ ጎጃም በስራ ላይ የነበርሁ በመሆኔ፥ ገና ያነለት መገናኘታችን ስለ ነበረ ከጦርነቱ በደህና ተመልሼ ሲያዩኝ በጣም ነበር ደስ ያላቸው።

ብርሃኑና መኮንን፥ ባንድነት ትንሽ የሻይ ቤት ከፍተው ቄስ ባድማ ከሚኖሩበት የሚሲዮን ትምርት ቤት ጎረቤት ስለ ነበረ የሚኖሩ የወደፊት እየጣየ እስኪጣል፥ ምግቤ ከነ ቄስ ባድማ ቤት ሆኖ ምኝታየ ከነሱ ጋር እንዲሆን በመሀከላችን ስምምነት ተደረገ። ከዚያ በየቀኑ ወደ ፖለቲካ ፅህፈት ቤት እየሄድሁ እየፈረምሁ፥ ካባቴ ቄስ ባድማና ከሁለቱ ጉዋደኞች ጋር አንድ ሳምንት ያልሞላ ጊዜ አዲስ አበባ እንደቆየሁ አንድ እሁድ አባቴ ቄስ ባድማ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ «የመጨረሻ ሁኔታየን ውሳኔ » የሚያመለክት ወሬ ይዘውልኝ መጡ።

«ጣሊያኖች ልጅ ይልማ ደሬሳንና አንተን ወደ ጣሊያን አገር ሊወስዱዋቸው መወሰናቸው ይወራል። ከግንሊዞች የተገኘ ወሬ ስለ ሆነ እርግጥ ነው » አሉኝ። በንግሊዝ ለጋሲዮንም በንግሊዝ ቆስላም አሰርጉዋሚዎችና የቅርብ ረዳቶች እየሆኑ ይሰሩ ከነበሩት ብዙ ጊዜ በሚሲዮን ትምርት ቤት የተማሩ ስለ ነበሩ፥ እንግሊዞች የሰሙትን ሲያካፍሉዋቸው እነሱም በበኩላቸው ለኢትዮጵያውያን የሚሲዮን መምህራን ያካፍላሉ። ስለዚህ ስለኛ የተወራውም ያን የተለመደ መንገድ ተከትሎ የመጣ ወሬ ሊሆን ይችላል።

«ለመሆኑ ከብዙ ባለስልጣኖችና የተማሩ ሰዎች መሀከል ሁለታችን ብቻ ተለይተን ወደ ጣሊያን አገር የምንወስድበት ምክንያትስ ታውቆ ይሆን? » አልሁ፤ ወሬው ስላስደነገጠኝ ትንሽ ዝም ብዬ ቆይቼ።

«ልጅ ይልማ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካይነተኞች ሹማምንት መሀከል የነበረ ከመሆኑ ሌላ ራስ እምሩ እጃቸውን ለመስጠት ከጣሊያኖች ጋር ንግግር ባደረጉ ጊዜ ዋና አማካሪያቸው የነበረ ስለሆነ፥ አንተ እንግሊዞች ርዳታ እንዲያደርጉላቸው ራስ እምሩ ልከውህ ወደ ሱዳን ሄደው ስለ ነበረ ነው ይባላል » አሉኝ።

«ስማ ሀዲስ » አሉ አባቴ ቄስ ባድማ ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ቆይተው ቀና አሉና። «ዛሬ ማታ ወደ ‹ውጊያ› ልውሰድህና ዘመዶችዋ በሚያውቀኡት አልባሌ መንገድ አባይን አሽግረው አገርህ ጎጃም እንዲያገቡህ እንድታደርግ ልንገራት። ከዚያ በሁዋላ ብትፈልግ ወደ ሱዳን ትሄዳለህ ያለዚያም ጫካ ውስጥ ካሉት አርበኞች ጋር ተጨምረህ እነሱ እንደ ሆኑት ትሆናለህ! » ‹ወይዘሮ ወጊዶ› የሚባሉት ሱሉልታ የሚኖሩ ለቄስ ባድማ ቤተሰብ የረዥም ጊዜ ወዳጅ ስለ ነበሩ የጠየቁዋቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉላቸው ያምኑ ነበር።

«እንኩዋንስ ጠፍቼ ‹አንድ ቀን ሳልፈርም ብቀር በሀላፊነት እንደሚጠየቁ› ለኔ ዋስ ሆነው ሲፈርሙ እኒያ የጣሊያኑ ሹም ያስጠነቀቁዎን ረሱት እንዴ » አልሁዋቸው።

«አልረሳሁትም። ታዲያ አንተ ብትጠፋ እኔን ምን የሚያደርጉኝ መሰለህ? ስላንተ ጣሊያን አገር ወስደው የሚያስሩኝ መሰለህ? »

«ስልጣን ሁሉ በጃቸው ነው፤ ከፈለጉ ዛሬ ለማድረግ የማይችሉት ነገር ምን አለ? እንኩዋንስ ጣሊያን አገር ወስዶ ማሰር ቢገድሉስ ማን ጠያቂ አለባቸው? »

«አይምሰልህ ምንም አያደርጉኝ! አየህ? የሚሲዮን ሰራተኛ ስለሆንሁ እዚህ ግቢ ውስጥ ገብተው እኔን አንድ ነገር ቢያደርጉኝ ሚሲዮናችንን ብቻ ሳይሆን የስዊድንን መንግስት ጭምር የሚያሳዝን ይሆናል። ስለዚህ፥ ዛሬ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛታቸው መሆንዋን ብዙ መንግስታት እንዲያውቁላቸው በሚፈልጉበት ጊዜ አንተ በመጥፋትህ ብቻ የስዊድንን መንግስት የሚያሳዝን

አንዳች ነገር የሚያደርጉ አይመስልህ! » አሉና አሁንም ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው፥

«ደግሞ ምንም አያደርጉ እንጂ ቢያደርጉስ እኔኮ ያገልግሎት ዘመኔን ወደ መጨረሻ አድርሼ ሞት መጥቶ እስኪወስደኝ በመጠባበቅ ላይ ያለሁ ሽማግሌ ነኝ! እናንተ ግን ያገልግሎት ዘመናችሁን ለመጀመር ገና በመሰናዳት ላይ ስለሆናችሁ ለሀገራችሁና ለወገናችሁ ተስፋዎች ናችሁና የናንተ ህይወት መጠበቅ ይገባል። ከንግዲህ ወዲያ ያለው የኛ ህይወት ዋጋም የለው። ስለዚህ ማታ እወስድህለሁና ተሰናዳ » አሉኝ አሳባቸውን የማልቀበል መሆኔን ወዲያው ልነገራቸ ብፈልግ ስሜቴ ስለ ታወከብኝና እንባየ ስለ ተናነቀኝ መናገር ባለ መቻሌ ዝም ብዬ ቆየሁ። ከዚያ ትንሽ ፀጥ ስል «እንዲህ ያለውን አሳብ አልቀበልምና ዳግመኛ እንዳያስነሱብኝ! » አልሁዋቸው።

«እንዴት? »

«የርስዎ ህይወት የብዙ ሰው ህይወት ነው እንጂ የርስዎ ብቻ አይደለምኮ! አያርገውና እርስዎ አንድ ነገር ቢሆኑ ብዙ ሰው መጠጊያ ያጣል! ስለኔም የሆነ እንደ ሆነ እንድኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ጣሊያን አገር ስለ ተወሰድሁ አልሞት! ስለዚህ በኔ ወደ ጣሊያን አገር መወሰድ አይጨነቁበት » ብየ በውሳኔየ ስለ ፀናሁና ቢቆጡኝም ቢያባብሉኝም አሳቤን የማልለውጥ ስለሆንሁ ተቆጥተው ትተውኝ ሄዱ።

በማግስቱ ይሁን በሳልስቱ - ቀኑን ረስቸዋለሁ - ልፈርም ወደ ፖለቲካ ፅህፈት ቤት በሄድሁበት ከዚያ በሚከተለው ቀን «በሶስት ሰአት የፖለቲካው ዋና ሹም «ማጆሬ ፓርላቨቸኒ » ሊያዩኝ ስለሚፈልጉ ቀደም ብዬ እዚያ እንድደርስ ተነገረኝ። በተቀጠርሁበት ቀንና ሰአት ፖለቲካ ፅህፈት ቤት ደርሼ ሹማምቱ ገና ስላልገቡ ቆሜ ስጠብቅ ልጅ ይልማ ደሬሳ መጣ። እሱንም እንደኔ፥ ማጆሬ ፓርላቪቸኒ እንዳስጠሩት ሲነግረኝ ለምን እንዳስጠሩኝ ያውቅ እንደሆነ ብጠይቀው እንኳዋንስ የሚያውቀው በግምት የሚጠረጥረው እንኳዋ አለመኖሩን ነገረኝ። ጣሊያኖች እሱንና እኔን ወዳገራቸው ሊወስዱን መወሰናቸውን - ከእንግሊዞች የተገኘ ወሬ ነው ብለው - አባቴ ቄስ ባድማ

ከሁለት ይሁን ከሶስት ቀን በፊት ነግረውኝ እንደ ነበረ ስነግረው ማመኑም አለማመኑም አስቸግሮት ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ፥

«ታዲያ አመንህ? » አለኝ።

«እስከ ዛሬ ጥርጥር ነበረኝ ዛሬ ግን አመንሁ » አልሁት።

«ለምን? »

«በቀድሞ አባቴ ቄስ ባድማ ሁለታችን ልንወሰድ መወሰኑን ነግረውኝ ዛሬ ሁለታችን ባንድ ላይ ስለ ተጠራን። »

«እውነት ነው፤ ይመስላል » አለ። ትንሽ ቆይተን ተጠራን።

ስንገባ «ማጆሬ ፓርላቪቺኒ » ከክፍላቸው መሀከል ቆመው ነበር። ለሁለታችንም የጅ ሰላምታ ከሰጡን በሁዋላ፥

«ይልማ ደሬሳ ማንኛችሁ ናችሁ? » አሉ፤ ፈገግ ብለው።

«እኔ ነኝ » አለ ልጅ ይልማ።

«በለንደን የኢኮኖሚ ትምርት ቤት የኢኮኖሚክ ሳይንስ ምሩቅ መሆንህን አውቃለሁ፤ አንተም ሀዲስ አለማየሁ መሆንህን አውቃለሁ። ኑ፥ ተቀመጡ፤ ወዳጆቼ » ብለው ከጠረጴዛቸው ፊት በነበሩ ሁለት ወንበሮች አስቀምጠውን ዞረው በወንበራቸው ተቀመጡ። እንግሊዝኛ ሲናገር የሰማቸው «እንግሊዛዊ አደሉም » ቢሉት ሊያምን አይችልም፤ እንደ ተማሩ እንግሊዛውያን ፈፅሞ የጠራ እንግሊዝኛ ነበር የሚናገሩ። ቡና ይሁን ሻይ አዝዘውልን ስንጠጣ ስለ ተጠራንበት ጉዳይ ከመንገድ የወጣ መጣጣርና ክፉ ስራችውን በጎ ለማስመሰል ይቀባቡት የነበረው የውሸት ቀለም ሁሉም ውሸት መሆኑን ይብስ አጉልቶ ያሳያቸው ነበር።

«ኢትዮጵያ » አሉ ማጆሬ ፓርላቪቸኒ፥ «ኢትዮጵያ የጥንታዊኢ ስልጣኔና ባህል ባለ ፀጋ የሆነች አገር ስለ ሆነች፥ እንደ ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ስላልሆነች ኢጣሊያ፣ እንደ ሌሎች የአውሮፓ ገዢዎች ህዝብዋን ለመግዛትና

ሀብትዋን ለመዝረፍ የመጣች አለመሆንዋን የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ እናንተ የተማራችሁት እንድታውቁልን እንፈልጋለን። የኢትዮጵያን ጥንታዊ ስልጣኔ ተባብረን አድሰን፥ ያልለማ ሀብትዋን ተባብረን አልምተን የጋራ ለመጠቀም ነው የምንፈልግ። ተባብሮ ለመስራት ደግሞ፥ የሁለቱን ወገኖች የጣሊያኖችንና የኢትዮጵያን መግባባትና መተማመን ያስፈልጋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ታላላቅና የተማሩ ሰዎች፥ ከታላቁ ንጉሳችንና ከመሳሪያችን ከሙሶሊኒ ጋር እየተገናኙ የጣሊያን መንግስት ኢትዮጵያን ለመጥቀም እንጂ ለመጉዳት ፍፁም የማይሻ መሆኑን ከነሱ ከንጉሱና ከሙሶሊኒ አፍ ሲሰሙ እንደሚያምኑ ስለ ታውቀ ነው፥ አሁን ራስ እምሩና ዳጃች ታዬ ተጋብዘው ወደ ጣሊያን አገር የሄዱ። ራስ እምሩና ደጃች ታዬ ከንጉሱና ከሙሶሊኒ ጋር ተገናኝተው የጣሊያን መንግስት አሳብ ከተገለፀላቸው በሁዋላ በጣሊያን አገር የተሰራውን ልዩ ልዩ ዘመናዊና ታላላቅ ስራ እየተዘዋወሩ አይተው ሲመለሱ ከነሱና እንደስነሱ በየጊዜው እየተጋበዙ የጣሊያንን ስራ ጎብኝተው ከሚመለሱት ኢትዮጵያውያን ጋር ተባብረን ኢትዮጵያን ባጭር ጊዜ ውስጥ ዘመናዊ አገር ልታደርጋት ነው የምንፈግል።

«ራስ እምሩና ደጃች ታዬ ጣሊኢያን አገር እንደ ደረሱ ይህ ሁሉ ተገልፆላቸው ከተማሩት ሰዎች መሀከል ከነሱ ጋር ንጉሱንና የመንግስቱን መሪ ሙሶሊኒን ተገናኝንተው በጣሊያን አገር የተሰሩትን የልማት ስራዎች ጎብኝተው ሲመለሱ እዚያ ባዩት አይነት ከኛ ጋር ተባብረው አገራቸውን ለማልማት ፍላጎትም ችሎታም ያላቸውን ሰዎች ስም እንዲሰጡ ተጠይቀው የናንተን የሁለታችሁን ስም ስለ ሰጡ ነው፥ እነሱ ወዳሉበት እንድትሄዱ አሁን የጠራናችሁ። በጣሊያን አገር ተወልደው ኖረው እስኪሞቱ ድረስ ከንጉሱና ከሙሶሊኒ ፊት ቀርበው ለመነጋገር የታደሉ ምን ያክል ጥቂት ይመስሉዋችሁዋል! እናንተ ግን ይኸው ሳትፈልጉ ተፈልጋችሁ ከታላቁ ንጉሳችንና ከታላቁ መሪያችን ከሙሶሊኒ ጋር ተገናኝታችሁ ልትነጋገሩ ነው! በውነት እድለኞች ናችሁ! ራስ እምሩና ደጃች ታዬ እናንተ እስክትደርሱላቸው እየጠበቁ ከንጉሱና ከሙሶሊኒ ጋር ገና አልተገናኙምና ቶሎ መሄድ አለባችሁ።

«ከምፅዋ በመርከብ ተሳፍራችሁ ወደ ጣሊያን አገር ስትሄዱም ጣሊያን አገር ስትደርሱም የሚያስፈልጋችሁ ገንዘብ ተሰናድቶ ይጠብቃችሁዋል። ግን

እስከ ምፅዋ ኪሳችሁ ባዳ እንዳይሆን ያክል፥ ትንሽ ገንዘብ ያስፈልጋችሁ ይሆናል » አሉ የፖለቲካው ዋና ሹም የፖለቲካ «ሀ. ሁ » የማያውቅ መሀይም በማያምነው ረዢም ስብከታቸው ካሰለቹን በሁዋላ።

«እግዚአብሄር ይስጥልን፤ ሁለታችንም የኪስ ገንዘብ አለን » አለ ልጅ ይልማ ምንም እንኩዋ የኔን አሳብ ባያውቅ ስለ ራሱም ስለ እኔም ሆኖ። እውነትም ሁዋላ እስበሳችን ስንነጋገር እንደ ተገላለፅነው፥ እኔ ትንሽ እሱ ከኔ የተሻለ ገንዘብ ነበረን። ስለዚህ ይልማ የፖለቲካውን ሹም «ገንዘብ አለን፤ የርስዎን የኪስ ገንዘብ አንፈልግም » ሲላቸው በጣም ነበር ደስ ያለኝ! ነገር ግን እሳቸው ጉርሻቸውን ላለመቀበል የፈለግንበት በኩራት መንፈስ መሆኑን አውቀው ይሁን ወይም ሳያውቁ እንድንቀበል አስገደዱን።

«የነበራችሁበትን ስለማውቅ ገንዘብ እንደሌላችሁም አውቃለሁ! ስለዚህ አስመራ ስትደርሱ የፈለጋችሁትን ያክል ገንዘብ እንዲሰጡዋችሁ ላገረ - ገዡ አሁን በስልክ እነገራቸዋለሁ፤ እስከዚያ ድረስ ኪሳችሁ ባዶ እንዳይሆን ይህን ተቀበሉኝ እባካችሁ ወዳጆቼ » ብለው አምስት መቶ ሊሬ የያዘ እጃቸውን ለይልማም ለኔም በየተራ ሲዘረጉ ለመናው አብቅቶ ትእዛዝ እንዳይመጣ ፈርተን ተቀበልንና ወደ ጣሊያን አገር የምነሳበት ቀን ተነግሮን ወጣን።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

# ካዲስ አበባ እስከ ፓንዛ

ልጅ ይልማ ደሬሳና እኔ በጥር 1929 ምርኮኞች ሁሉ ተለይተን በግዞት ወደ ጣሊያን አገር ልንወስድ መወሰኑ ሲሰማ ዘመዶቻችንና ወዳጆቻችን ብቻ ሳይሆኑ በሩቅ፥ ከሚያውቁን መሀከልም፥ ብዙዎች አዝነውልን ነበር። ትንሽ ቆይቶ በየካቲ 12 1929 ማርሻል ግራሲያኒን ለመግደል ሙከራ ከተደረገ

በሁዋላ የምርኮ ጉዋደኞቻችን ሁሉ በመብራት እየተፈለጉ ተለቅመው ማለቃቸው ሲታይ ግን የኛ ቀደም ብሎ በግዞት ከኢትዮጵያ መውጣት መዳኛችን ሆኖ በመገኘቱ እኛንም አዝነውልን የነበሩትን ሁሉም አስገረመን! ከክቡር ራስ እምሩና ከከንቲባ ጋሻው ጠና ጋር ከነበሩት መኩዋንንትም ከሆለታ መኮንኖችና ከፈርንጅ አገር ከተመለሱት ምሁራንም፥ ከጅማ አዲስ አበባ እንደ ገቡ ወደ ባላገር ሸሽተው ወይም ከዘመድ ቤት ተሸሽገው ካመለጡት አንዳንድ በቀር ሁሉም አለቁ! ልጅ ይልማና እኔ ፖንዛ ከደረስን በሁዋላ ነበር ማርሻል ግራሲያኒ አደጋ ተጥሉባቸው መቁሰላቸውን የሰማን።

በጥር 1929 እኩሌታ ግድም በጣም ጥዋት ጀንበር ከመውጣትዋ እንኩዋ በፊት በአይሮፕላን ካዲስ አበባ ተነስተን መስሪኢያ ቤት ተዘግቶ ከሰባት ሰአት በሁዋላ አስመራ ደረስን። (በዚያ ጊዜና ባሁን መሀከል አይሮፕላኖች የጨመሩት ፍጥነት የሚያስገርም መሆኑን ይህ ያሳያል!) አስመራ መስሪያ ቤት እስኪከፈት ወደ ጦር ሰራዊት ሰፈር ተወስደን እዚያ ሲጠብቀን እንዲቆይ የተረከበን ወታደር እስከ ዛሬ ድረስ ሊገባኝ ምክንያት ሲያስቸግረን የቆየውን አልረሳውም!

ከአይሮፕላን ማረፊያ እስከ ጦር ሰራዊት ሰፈር በካሚዮን የወሰደን የጣሊያን የጦር መኮንን ከካሚኢዮን አውርዶ ለወታደሩ በጣሊያንኛ የነገረውን ነግሮት ስለኛ ካዲስ አበባ ያመጣውን ወረቀትም ሰጥቶት ከሄደ በሁዋላ ያ ወታደር አንድ ትንሽ ቤት ከፍቶ እዚያ እንድንገባ በቁጣ አዘዘን። ቤቱ የሲሚንቶ ሽክላ የተነጠፈ ከመሆኑ በቀር የሌላ ምንጣፍ ወይም የወንበር ምልክት አይታይበትም፤ ፍፅም ባዶ ነበር!

«ተቀመጡ! » አለ ወታደሩ በቁታ።

«እዚህ እግራችንን አጥፈን ለመቀመጥ ስለሚኢያስቸግረን እባክህ ወንድሜ ውጪ እደረጃው ላይ እንቀመጥ » አለው ልጅ ይልማ።

«ተቀመጡ ብያለሁ፤ ውጪ አትወጡም! »

«እንግዲያው ውጪ መውጣታችን የሚያስፈራ ከሆነ በሩን ይዝጉብንና ባይሆን መቀመጣችን ቀርቶ እዚሁ እንቁም » አልሁ፤ አስታራቂ አሳብ ያገኘሁ መስሎኝ።

«ማነው እናንተን የሚፈራ! እኔ ነኝ እናንተንም የምፈራ? ተቀመጡ አሁን! » አለ ቁታው ይብሱኑ ግሎ ግሎ የጠመጃውን አፈሙዝ አስቀድሞ ወደኛ እየመታ። ያን ጊዜ ሰውዬው ክፉ ነገር ለማድረግ ምክንያት የሚፈልግ መሎ ስለ ታየን ምንም ሳንመልስ እዚኢያ ሲሚንቶ ወለል ላይ እግራችንን ዘርግተን ተቀመጥን። እሱም እየተሳደበ ቤቱን ዘግቶ ወጣና እደጅ ይንሸራሸር ጀመር። እንዲያ ሲንሸራሸር ይቆይና በቤቱ መስኮት አንገቱን አስገብቶ ሰድቦን ይሄዳል። ብዙ ጊዜ እየተመላለሰ ሲሰስቡን ከቆዩ በሁዋላ እንደ ገና በሩን ከፍቶ ገብቶ፥

«ንጉስ ሀይለ ስላሴ ተሸንፈው አገር ለቀው ሲሄዱ እናንተ የጣሊያንን መንግስት ልታሸንፉ ነው ሽፍቶች የሆናችሁ? እናንተ ርጉማን? » አለ፥ እግራችንን ዘርግተን እንደ ተቀመጥን ከፊታችን ቆሞ።

«ተነሱ! » አለ ቀጥሎ። ስንነሳ፥

«ውጡ! » አለ በሁዋላችን እንደ ሆነ የጠመንጃውን አፈሙዝ ወደኛ አድርጎ። ወጥተን እበረንዳው ላይ ቆመን ተከታዩን ትእዛዝ ስንጠብቅ፥

«ደረጃው ላይ ተቀመጡ! » አለ መጀመሪያ እንደ ለመነነው። እንዳዘዘን እደረጃው ላይ ስንቀመጥ እሱ ደረጃውን ወርዶ እታች ብቻውን በትግርኛ እየተናገረ ሲንሸራሸር ከቆየ በሁዋላ ወደኛ መጥቶ በፊታችን ቆመና ሌላ ሰው እንዳይሰማው የፈራ ይመልስ ጎንበስ ብሎ አፉን ወደኛ ቀረብ ድምፁን ዝቅ አድርጎ፥

«አንተ! » አለ። «አንተ! የናንተ ጌታ የናንተ ንጉስ ሀይለ ስላሴና እናንተ ርጉማን ሁሉ ብዙ ሽህ አመታት ነፃ ሆና የኖረችውን አገር ኢትዮጵያን የጣልያን ግዛት አደረጋችሁ፤ የኢጵያን ህዝብ የጣሊያን ባሪያ አደረጋችሁ። ኢትዮጵያን ነፃ እንደ ሆነች ቆይታ ስትሰለጥንና ስትበረታ እኛን ጭምር ረድታ አብረን ነፃ

ሆነን እንድንኖር ተስፋ ነበረን። አሁን ንጉሳችሁ ሀይለ ስላሴን እናንተ የኢትዮጵያን ነፃነትም የኛን ተስፋም ባንድ ላይ አጠፋችሁ! እዝግሄር ያጥፋችሁ! » አለ ቁጣው በፊቱ ላይ እንድ እሳት ሴንድ እየታየ። እንዲያ ጎንበስ ብሎ በዝቅተኛ ድምፅ ለኛ ሲናገር ምንም እንኳዋ ባቅራቢያው ሌላ ሰው ባይኖር የፈራው ነገር እንደ ነበረ ሁሉ በየቅፅበቱ ቀኝና ግራ እየተገላመጠ ያይ ነበር! ትንሽ ቆይቶ መስሪያ ቤት የሚከፈትበት ጊዜ ደርሶ አንድ ትንሽ ካሚዮን የሚነዳ ሰው መጥቶ ያው ሲነዘንዘን የዋለው ወታደው እጅቦ ወዳገረ - ገዡ ፅህፈት ቤት ወሰደን።

ሹማምንቱም ሌሎች ሰራተኞችም ወደየ ፅህፈት ቤታቸው የሚገቡ ባለ ጉዳዮች ተቀምጠው ተራ በሚጠብቁበት ክፍል አልፈው ስለ ነበረ እዚያ እንደ ተቀመጥን አንዳንድ ሹም አልፎ በሄደ ቁጥር፥

«ተነሱ፤ ባለጌ! » ይለናል ወታደሩ ባጠገባችን ቆሞ።

እዚያ ከተቀመጡት መኰዋንንት መሀከል አንድ የማውቃቸው የትግራይ ወይም የኤርትራ መኮንን ነበሩ። እኒያ መኮንን በሽሬ ግንባር እጦርነት ላይ በነበርንበት ጊዜ በራሳቸው ስም ይሁን ወይም ከሌላ ሰው ተልከው ክከቡር ራስ እምሩ ጋር ሊነጋገሩ መጥተው ጥቂት ቀናት ለብቻ እየተገናኙ ሲነጋገሩ ቆይተው እስኪሄዱ እንተያይ ነበር። ባልሳሳት ስማቸው ፊታውራሪ ወልደ ስላሴ ይመስለኛል። ፊታውራሪ ወልደ ስላሴ ያን ያስቸግረን የነበረውን ወታደር ጠርተው ምን እንደ ነገሩት አናውቅም፤ ወደኛ እያመለከቱ የነገሩትን ከነገሩት በሁዋላ «ተነሱ ተቀመጡ! » እያለ ማስቸገሩን ተወንና አርፈን ቆየን። ከዚያ እኛን ጉዳይ የሚመለከቱት ሹም ስላስጠሩን ወታደሩ ይዞን ገብቶ ካዲስ አበባ ያመጣን ሰው ከሰጠው ወረቀት ጋር አቀረበን።

ሹም ካዲስ አበባ የመጣውን ወረቀት ካዩ በሁዋላ ወደ ጣሊያን አገር የምትሄደዋ መርከብ፥ ያንለት ማታ ከምፅዋ ስለምትነሳ፥ ከመነሳትዋ በፊት ለመድረስ ቶሎ ለመሄድ እንዳለብን አዘዙ። ያ፥ ሲነዘንዘን የዋለው ወታደር እስከ ምፅዋም አጅቦ ወስዶ እዝያ ለሚያረከቡን ሰዎች እንዲያስረክብ ጠይቆ ነበር። ወታደሩ ሹሙን የጠየቀው በጣሊያንኛ ስለ ነበረ ምን እንደ ተናገረ እኔን አልገባኝም ነበር። ልጅ ይልማ ግን ከኔ የተሻለ ፈረንሳይኛ ያውቅ ስለ ነበረና!

ጣሊያንኛ ለፈረንሳይኛ ቅርብ በመሆኑ ሰውዬው የጠየቀው ከሞላ ጐደል ገብቶት ኖረዋል። ስለዚህ፥ ያ ሰው ሲያስቸግረን የዋለ መሆኑን ገልፆ፥ እከሰ ምፅዋ ሌላ ጠባቂ እንዲያደርጉልን ሹሙን በፈረንሳይኛ ስለ ጠየቃቸው ወታደሩን ተቆጥተው ከቢሮዋቸው አስወጥተው ትርፍ አጃቢ ሳያስፈል መሳሪያ ያለው ሰው በኦቶመቢል እንዲያደርሰን ስለ ተወሰነ ማእርጉ ምን እንደ ሆነ የማላስታውሰው የጣሊያን የወታደር ሹም እንዲወስደን ታዘዘ።

ካስመራ እስከ ምፅዋ የሄድንበት ኦቶመቢል በነጂውና ሁውላ በተቀመጥነው በኛ መሀከል ያለው ቦታ ጥይት ሊሰብረው በማይችል መስትዋት የተዘጋ ነበር። እንዲሁም በቀኝና በግራችን ያሉት መስኮቶች ጥይት ከማይሰብረው መስትዋት የተሰሩ ሆነው ስለ ተዘጉ አየር አናገኝም ነበር። ነጂው ብቻ በጎኑ ያለውን መስኮት ከፍቶ ለኛ አያስተርፍልንም እንጂ፥ ለራሱ አየር እንደ ልብ ያገኝ ስለዚህ ያ ነጂ መትረየሱን ባጠገቡ አስቀምጦ መርከብዋ የምነሳበት ጊዜ ሳይደርስ ምፅዋ ለመድረስ ሲደርስ ሙቀቱ የበረታ በሄደ መጠን ልጅ ይልማም እኔም ሰውነታችን ታውኮ ተቸገርን። ይልቁንም እኔ የቅልሽልሽ ስሜት ስለ ፀናብኝ መታገስ አቅቶኝ በኛና በነጂው መሀከል ያለውን መስተዋት አጥር መላልሼ ስመታ ነጂው ኦቶመቢሉን ከመንገዱ ዳር አቁሞ መትረየሱን ይዞ መጣና ከውጪ የተቆለፈውን የኦቶመቢል በር ከፍቶ ራስኑ ነቅነቅ እያደረገ በጣልያንኛ ተናገረ። እኔ ያን ጊዜ አንድ የጣሊያን ቃል አላውቅም ነበር። ነገር ግን የነጂው አነጋገር በራሱና በጁ ያሳያቸው ከነበሩት ምልክቶች ጋር «ምን ትፈልጋላችሁ? » የሚል ጥያቄ መሆኑን ገምቼ እኔም ባፌና በጄ የ«እውኪያ » ምልክት አሳየሁት። ያን ጊዜ ቶሎ በሩን በሰፊው ከፍቶልን ወደ ሁዋላ ፈንጠር ብሎ ቆሞ እንድንወጣ ምልክት ሰጠን። ወጠውን ንፁህ አየር እየተነፈስን ትንሽ እንደ ቆየን ደህና ሆነን ማቅለሽለሹንም ተወኝ። ግን በሱ ፈንታ ብርቱ ራብ ተሰማኝ። ያነለት ከነጋ ጀምሮ ልጅ ይልማም እኔም ምንም አልቀመስን፤ ባዶ ሆዳችንን ነበርን። ወዲያው ጥዋት እኔ ፊቴን ስታጠብ ከጐዋደኞቼ ከብርሃኑናን ከመኮንን አንዱ «ትንሽ አርፋችሁ እህል የምትቀምሱበት እድል ያጋጠማችሁ እንደሆነ «ሳንድዊች » እዚህ በሽንጣህ ኪስ አስቀምጠንላችሁዋል » ያለኝ ትዝ አለኝ።

«አልራበህም? እኔን በጣም ራበኝ! » አልሁት ልጅ ይልማን።

«ቢርበኝ ምን ላድርግ እችላለሁ እንጂ እኔንም ርቦኛል » አለ።

«ጥዋት ጉዋደኞቼ ሳንድዊች በሻንጣየ ውስጥ ያስቀምጡልን መሆናቸውን ነግረውኝ ነበር፤ እስቲ አውጥተን እንድንበላ ይፈቅድልን እንደሆነ ይህን ሰውየ እንጠይቀው » አልሁት።

«በምን ቁዋንቁዋ እንጠይቀዋለን? ፈረንሳይኛ ያውቅ ይሆን? » አለና በፈረንሳይ ሊያነጋግረው ቢሞክር ሰውየው ራስኑ ነቀነቀ። ከዚያ እኔ የሰው ዘር ሁሉ በሚግባባበት ቁዋንቁዋ በጥቅሻ ስልጠይቀው አሰብሁና ሻንጣየ በኦቶመቢሉ የእቃ መጫኛ ላይ ስለ ነበረ፥ ወደሱ እያመለከትሁ በእጄ የመጉረስ ባፌ የማላመት ምልክት ሳሳየው ሰውየው እየሳቀ ሰአቱን አይቶ አውርደን እንድንበላ ፈቀደልን።

ሻንጣውን አውርጄ ስከፍት ተከድኖ ለብቻው በሻንጣው ኪስ በተቀመጠ እቃ አራት ከጠጠበሰ ስጋና ከሰላጣ ተደባልቆ የተሰናዳ ሳንድዊች አገኘሁ። ከዚያ ይልማና እኔ አንዳንድ ይዘን ሁለቱን ከነቃው ለጣሊያኑ ስናቀርብለት መጀመሪያ እሱም አንዱን አንስቶ ሌላውን እኛ እንድንበላው በምልክት አሳይቶን ነበር። ነገር ግን እሱ እንዲበላልን መፈለጋችንን እኛም በምልክት ስናሳየው እሱንም እንደኛ ርቦት ኖሮ እኛ አንዳንዱን እሱ ሁለቱን ባንድ ጊዜ ጨረስን! ከዚያ በሁዋላ ጣሊያኑና እኛ ወዳጆች ሁነን ተማመንና አጠገባችን ከነበረች ትንሽ ወንዝ ውሀ እንድንጠጣ በምልክት ስንለምነው አፈምሙዙን ወደኛ አድርጎ በጁ ይዞት የቆየውን መትረየሱን በትከሻው አንግቶ አብረን ውሀ ጠጥተን ተመለስን። ከኦቶመቢሉ ውስጥ አስገብቶ ከቆለፈብን በሁዋላም አየር እንድናገኝ የመስኮቱን መስትዋት ካንድ ወገን ትንሽ ዝቅ አደረገልን። ከዚያ ምፅዋ ለመድረስ ምንም ያክል ጊዜ አልፈጀብንም፤ ቶሎ ደርሰን፤ ጣሊያን አገር ለሚረከበን ባለስልጣን ለሚያስተላልፉን የመርከቡ ሹማምንት ተሰጠን።

ከምፅዋ እስከ ናፖሊ (ጣሊያን አገር) የሄድንበት መርከብ በኢትዮጵያ ሲዋጉ የቆዩትን ወታደሮች ይዞ የሚመለስ ነበር። ቁጥራቸውን በትክክል ባላውቅም ወታደሮቹ ብዙ ነበሩ። ያ ሁሉ ወታደር የሚበላበትና የሚተኛበት

በቂ ቦታ ስላልነበረ ሁሉም መቂነኑን በየቁናው እየያዘ ባገኘው ክፍት ቦታ ተቀምጦ በልቶ ክፍት ቦታ በተገኘበትና በመከቡ ጣራ ላይ ነበር የሚተኛ። የመርከቡ የምኝታ ክፍሎችና የመብል አዳራሹ ለመኮንኖች ብቻ የተመደቡ ነበሩ። ልጅ ይልማና እኔ እንደ መኮንኖች የምንተኛበት አንድ የጋራ ክፍል ተሰጥቶን መብል ቤት ከመኮንኖች ጋር ተሰርቶልን ነበር የምንበላ። የወታደሮች ዋና አዛዥ አንድ ኮሎኔል ነበሩ። አዛዣቸውም «የሻምበል » ማእርግ የነበራቸው ቄስ ነበሩ።

ኮሎኔል እንደ ነገሩን ካንደኛው የአለም ጦርነት በሁዋላ ከአውስትርያ ተከፍላ ለኢጣልያ የተጨመረች «ቲሮል » የምትባል አገር ተወላጅ ነበሩ። ቄሱ ግን ቱባ ጣሊያን ነበሩ። ሁለቱም እንግሊዝ ደህና አድርገው ያውቁ ስለ ነበረ ብዙ ጊዜ ወደኛ ክፍል እየመጡ በየተራ መጠጥ አዝዘው አስመጥተው እየጠጣን ስንጫወት እናመሽ ነበር።

በጭዋታው መሀከል ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በጦርነት ይዛ ቅኝ ግዛትዋ የማድረግዋ ነገር ሲነሳ ቄሱ ተገቢ መሆኑን ኮሎኔል ተገቢ አለመሆኑን ለማስረዳት ሲጨዋጨዋሁ ተጣልተው የሚለያዩ ይመስል ነበር ግን አይጣሉም።

የቄሱ አስተይየት ከሞላ - ጎደል «ኢጣሊያ ምንም እንኩዋ በዘመናዊው የሳይንስና የቴክኖሎጂ እውቀት ከቀደሙት አገሮች አንድዋ ብትሆን በህዝብዋ ብዛት መጠን መሬትዋ በጣም ጠባብ በመሆኑ ህዝብዋን በቴክኖሎጂ እንደ ቀደሙት አገሮች ህዝብ በምቾት ልታኖር አልቻለችም። ባንፃሩ ኢትዮጵያ መሬትዋ ሰፊ ህዝብዋ ጥቂት ስለ ሆነ ወደ ፊትም ለብዙ መቶ አመታት ህዝብዋ በዝቶ የመሬት ችግር የሚያሳስባት አገር አይደለችም። አሁን ኢትዮጵያን የሚያሳስባት ሀብታም መሬትዋን በዘመናዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት እልምቶ የህዝብዋን ኑሮ ማሻሻል ነው። ስለዚህ ኢጣሊያ ሀብትዋን የቴክኖሎጂ እውቀትዋን ይዛ ኢትዮጵያ ገብታ የሀዋርያነት ስራዋን እየሰራች የኢትዮጵያን ህዝብ ብትጠቅምና ራስዋም ብትጠቀም ለሁለቱም ወገኖች ይበጃል እንጂ ለማንም አይከፋም። ይህ ካልሆነ ግን፥ ለጣሊያን መንግስት ያለው ማማረጫ አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም ያገሩ ሀብት ሊያኖር የሚችለውን ያክል ህዝብ

አስቀርቶ የቀረውን ማጥፋት! ይህ ደግሞ በሰውም በእግዚአብሔርም ህግ የተከለከለ ነው! » የሚል ነበር።

የኮሎኔል አስተያየት ደግሞ፡- እንዲሁ ከሞላ ጐደል - «ኢጣሊያ ብዙ ሀብት ያላትና፥ ኢትዮጵያ የሌላትን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቁ ብዙ የጦር ሰራዊት ያላት አገር መሆንዋ ኢትዮጵያን በጦርነት ይዛ ቅኝ ግዛትዋ ለማድረግ ሙብት አይሰጥዋትም። እነዚህ የተባሉት ምክንያቶች ሙብት የሚሰጡ የሚሰጡ ከሆነ፥ ከኢጣሊያ የተሻለ የጦር መሳሪያና የበዛ የጦር ሰራዊት ያላቸው አገሮችም ኢጣሊያን በጦር ሀይል ይዘው ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ሙብት ይኖራቸዋል ማለት ነው! በጠቅላላው ብርቱዎች ደካማዎችን ትልቆች ትንሾችን ለመግዛት ደካማው ከብርቱ ትንሹ ከትልቁ ጋር የሰው ማህበር መስርተው የሚኖሩበት መሆኑ ቀርቶ ደካማውን ብርቱው ትንሹን ትልቁ የሚበላሉበት ያራዊት ማህበር ይሁን ማለት ነው! እንዲሁም ‹ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛትዋ አድርጋ ከብዙ ህዝብዋ ከፍላ ልታሳርፍትበት ካቻለች፤ የቀራትን የቀረውን ጥፋት ብቻ ነው!› ያሉት እውነት አደለም፤ ሌላ ማማረጫ አለ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር ካጠፋችው ብዙ ሀብትዋ ትንሹን ክፍልና የቴክኖሎጂ እውቀትዋን ይዛ ገብታ የርሻ የንዱስትሪ የመገናኛና ሌሎችን የልማት ስራዎች ለመስራት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የመተባበርና የወዳጅነት ስምምነት ብታደርግ በሁለቱ ሕዝቦች መሀከል በጠላትነት ፈንታ ወዳጅነትን አትርፋ በቅኝ ገዥነት ከምታገኘው በይበልጥ ያላነሰ ጥቅም ታገኝ እንደ ነበር አይጠረጠርም! » የሚል ነበር።

ይህ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በጦርነት የመያዝዋ ነገር ሲነሳ ልጅ ይልማና እኔ የጭዋታው ተካፋዮች መሆናችን ቀርቶ ተመልካቾች በመሆን እንወስን ነበር። ኮሎኔሉና ቄሱ መጀመሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲከራከሩ ቆይተው ከሄዱ በሁዋላ፤

«እባክህ! እነዚህ ሰዎች የኢጣሊያን አሸናፊነትና የኢትዮጵያን ተሸናፊነት ካላጡት ቦታ እኛ ዘንድ መጥተው የሚያወሩ ይልቁንም ቄሱ ኢትዮጵያ የጣሊያን ቅኝ ግዛት ልትሆን እንደሚገባት እኛ ዘንድ መጥተው በድፍረት የሚሰብኩ ሆነ ብለው እኛን ለማናደድና ለማሳዘን ነው? ወይስ የሚያስዝን

ልብ እንደሌለን በድኖች ቆጥረውን ይሆን? » አልሁ ሳይታወቀኝ በልጅ ይልማ ላይ በቁጣ አይኔን አፍጥጬ።

«ታዲያ ይህን ቁጣህን ማድረግ በቁሱ ላይ ነበር እንጂ በኔ ላይ ነው? » አለ ሁኔታየን ሲያይ እየሳቀ። ከዚያ ትንሽ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆየና፤

«ምናልባት በጉዞዋችን ላይ ሁሉ፥ ዛሬ የተነጋገሩትን የመሰለ ነገር እየተነጋገሩ የኛን ስሜትና ሁኔታ ሲያጠኑ ቆይተው በመጨረሻ ለሚረከቡን ባለስልጣኖች ምን አይነት ሰዎች መሆናችንን ለማስረዳት ይሆናል። ወይም እንዲሁ ለሰው ስሜት የማያስቡ ግዴለሾች ቢሆኑ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ አሁን ባለበት ሁኔታ ከዚህ የከፋ ሊደርስብን ስለሚችል የሚደርሰውን ሁሉ ለመቀበል ተሰናድቶ መጠበቅ ይሻላል! » አለኝ። ግን ከምፅዋ እስከ ናፖሊ እስክንደርስ ድረስ፥ ከዚያ የከፋ ነገር አልገጠመንም፤ እንዲያውም እዚያ መርከብ ላይ የነበሩት ሁሉ እንደ እስረኞች ሳይሆን እንደ ክብር እንግዶች ይመለከቱን ስለ ነበረ እኛም እስረኞች መሆናችንን ልንረሳው ትንሽ ቀርቶን ነበር!

ናፖሊ እንደ ወረድን «የጣሊያን - ምስራቅ - አፍሪቃ ጉዳይ ፅህፈት ቤት » የሚባለው መስሪያ ቤት ሰራተኞች መጥተው ስለኛ ከተፃፈው መሸኛ ሰነድ ጋር በመርከብ ካመጡት ሹማምንት ተረከቡን። ከዚያ ወደ መስሪያ ቤታቸው ወስደው ካለቃቸው ጋር አገናኙን። ከዚያም ወደ መስሪያ ቤታቸው ካለቃቸው ጋር አገናኙን። በናፖሊ የጣሊያን ምስራቅ አፍሪካ ፅህፈት ቤት ዋና ሹም - ሻለቃ ወይም ኮሎኔል መሆናቸውን አስታውሳለሁ። እኒያ መኮንን ስንገባ ተነስተው የጅ ሰላምታ ሰጥተው ከጠረጴዛቸው ባሻገር በፊት ለፊታቸው ካስቀመጡት በሁዋላ ቡና አዝዘው እሳቸው ጭምር ስንጠጣ ጣሊያንኛ ወይም ሌላ ያውሮፓውያን ቋንቋ እናውቅ እንደ ሆነ ጠየቁን። እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛም በመጠኑ እንደምናውቅ ልጅ ይልማ ሲነገራቸው እሳቸው ካገራቸው ቋንቋ ሌላ እንግሊዝኛ ፈረንሣይኛና የስፓኝ ቋንቋ የሚያውቁ መሆናቸውን ነግረውን በንግሊዝኛ እንነጋገር ጀመር። እውነትም መኮንኑ የተማሩ ሰው ከመሆናቸው ሌላ እንደ ነገሩን ወደኛው አለም ወደ አፍሪቃ መጥተው ባያውቁም በአውሮፓ ውስጥ አንዳንድ አገሮችን ተዘዋውረው

የጎበኙ ስለ ነበሩ ሰፋ ያለ አስተያየት የነበራቸውና ጭዋ ነበሩ። አብረናቸው የቆየንበት ጊዜ ዘለግ ያለ ቢሆንም በዚያ ጊዜ ስለ ኢጣሊያና ስለ ኢትዮጵያ ጦርነት አንድ ቃል አልተናገሩም። ስንነጋገር የቆየን ስለ ጉዞዋችን ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ተወለድንበት አገር ትምርታችንን ወዴት እንደ ተማርን ምን ስራ እንደ ነበርንና እነሱን ስለመሳሰለው ያለፈ ኑሮዋችን እየጠየቁን ስንመልስ እንዲሁም በዚያ ሳቢያ በሚነሱ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ አስባ ስንለዋወጥ ነበር። ታዲያ፥ ምንም እንኳዋ እፅህፈት ቤታቸው በቆየንበት ጊዜ ልጅ ይልማና እኔ የተናገርነው ለጠየቁን በመመለስና ባንዳንድ ጉዳዮች ላይ አጫጭር አስተያየት በመስጠት የተወሰነ ቢሆንም ስለ ኢትዮጵያውያን መንግስታቸው ሲሰብከው የኖረው ፕሮፓጋንዳ እኛን ከሰውነት ደረጃ ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ ስለ ነበር እኒያው፥ ለጥያቄዎቻቸው የመለስናቸውን ባንዳንድ ጉዳዮች ላይ የሰጠናቸው አጫጭር አስተያዬቶች እንኳዋ ያስገረሙዋቸው፥ እንዲያውም ያስደነግጡዋቸው መሆናቸው ከፊታቸው ይታወቅ ነበር። መኮነኑ እፅህፈት ቤታቸው ስንገባ ጀምረው በጭዋነት የተቀበሉትን ቢሆንም ባነጋገሩን መጠን ልባቸው እያከበረን የሄደ መሆኑ ከሁኔታቸው ሁሉ ይታይ ነበር። ይኸውም ከገባን በሁዋላ ሊያስከብረን የሚገባ ልዩና ትልቅ ነገር ስናደርግ አይተው ወይም ስንናገር ሰምተው ሳይሆን እዚህ ላይ እንዳልሁት እኛን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት ሲሰብክ ሲሰሙት ከኖሩት ልዩ ሆነን ስላገኙን ይመስለኛል። ለምሳሌ ከተገረሙባቸ ትናንሽ ነገሮች አንዱ ትግራይ ውስጥ ‹አንቲጮ› የሚባለውን ቦታ እሳቸውና ረዳቶቻቸውን በርካታ (መልክአምድር) ላይ ፈልገው አጥተውት ኖሮ እኔ በዘመትሁበት በሽሬ ግንባር የነበረ በመሆኑ አውቀው ስለነበረና ስላሳየሁዋቸው ነበር! መቸም ከዚህ ያነሰ ነገር የለ፤ ግን መኮንኑን አስገረማቸው!

«አገራችነን ኢጣሊያ ከዛሬ በፊት ታውቁታላችሁ? ወይስ ገና አሁን ማየታችሁ ነው? » አሉ መኮንኑ ‹አንቲጮን› ከሁዋላቸው እግንቡ ላይ በተሰቀለው ካርታ አሳይቻቸው እንደ ተቀመጥሁ።

«ከዛሬ በፊት አናውቅም፤ አሁን ማየታችን ነው » አለ ልጅ ይልማ።

«ከዚህ የምትሄዱበት ቦታስ ተነግሮዋችሁዋል? »

«አልተነገረንም » አለ አሁንም ልጅ ይልማ።

«ፓንዛ የሚባል ደሴት ነው። አገሩ እንኳዋ እኔ አይቸው ባለውቅም በበጋ የከተማ ሰዎች ለእረፍት የሚሄዱበት ጥሩ ቦታ መሆኑን ሰምቻለሁ፤ ግን ወደዚያ ከመሄዳችሁ በፊት የጣሊያንን አገር ትንሽ ተዘዋውራችሁ ማየት ብትችሉ መልካም ነበር። ሌላው ቢቀር ሮምን እንኳዋ ብታዩ ኢጣሊያ እንዴት ያለች አገር እንደ ሆነች አንድ አሳብ ይኖራችሁ ነበር! አሉ፥ እንደ ማዘን ብለው።

«ግዴለም፤ አሁን ባይሆን ወደ ፊት እድል ይኖረን ይሆናል » አለ ልጅ ይልማ። ከዚያ መኮንኑ፥ አንድ የመቶ አለቃ በስልክ ጠርተው እዚያው ከፅህፈት ቤታቸው ውስጥ ገለል ብለው ሲነጋገሩ ቆይተው መጡና፥

«በዚህ ምክንያት የሚመጣ ችግር ቢኖር አላፊነቱን እኔ ለመቀበል ዝግጁ ስለሆንሁ፥ የመቶ አለቃ ዛሬ በማታው ባቡር ወደ ሮም ወስዶ፥ ቅዳሜና እሁድ ቱሪስቶች ከያገሩ እየመጡ የሚጐበኙዋቸውን ታሪካዊ ቦታዎች እያዞረ ካሳያችሁ በሁዋላ ሰኞ ማታ ተመልሳችሁ ማክሰኞ ወደ ፓንዛ ትሄዳላችሁ። የመቶ አለቃ ከኔ የተሻለ እንግሊዝኛ ያው ቃል፤ ለዚህ ነው እሱን የመረጥሁላችሁ » አሉ ፈገግ ብለው የመቶ አለቃውን ለኛ እያመለከቱ። ማውታውን በባቡር ወደ ሮም ተጉዋዝን።

የመቶ አለቃው፥ ሮምን ደህና አድርጎ የሚያውቅ ኖሮ፥ በደረጃው መሀከለኛ ቢሆንም ምቾት ባልጎደለው ሆቴል አሳርፎ ቅዳሜና እሁድ ሊታዩ የሚገባቸውን ታሪካዊና አዲሶችም ቢሆኑ ስመጥር የሆኑትን ቦታዎች እያዞረ አሳዬን። የናፖሊው አለቃው ስለኛ የነበራቸውን መልካም አስተያየት ተመልክቶ ይመስለኛል፤ የመቶ አለቃው በብርቱ ጥንቃቄና በትህትና ነበር ሲያስተናግደን የሰነበተ።

«ትናንት ምሳ በበላንበት ሆቴል አንዳንድ የዋንው መስሪያ ቤት (የቅኝ ግዛቶች ሚኒስቴር) ሰራተኛ አይተዋችሁ ከየት እንደ መጣችሁ ጠይቀውኝ ከኢትዮጵያ የመጣችሁ መሆናችሁን ነግሬያቸዋለሁ። ስለዚህ እዚህ መድረሳችሁ ከታወቀ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት ወስጃለሁ የከፍሉን አላፊ

አይታችሁ ብትሄዱ የሚገባ አይመስላችሁም? » አለ የሙቶ አለቃው በትህትና ሰኞ ጥዋ እቁርስ ላይ።

«የመስሪያ ቤቱን ስነ ስራት የሚያውቁ እርስዎ ስለሆኑ የርስዎን አሳብ እንቀበላለን » አለው ልጅ ይልማ።

ከቁርስ በሁዋላ ወደ ቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ሄደን፥ የምስራቅ - አፍሪቃ ክፍል ሹም ከሆኑት አንድ ሻለቃ ተገናኘን። ሻለቃው እንኩዋንስ ኢትዮጵያን፥ ኢጣሊያ ቀደም ብላ የያዘችውን ኤርትራያን ሶማሊያንም ስማቸውን ካልሆነ መልካቸውን የሚያውቁ አልነበሩም። ስለዚህ ቅኝ አገር ቆይተው የተመለሱት ሹማምንት እንደሚያደርጉት እንደ አሽከሮች ሳይሆን እንደ እንግዶች የጅ ሰላምታ እዬሰጡ አስቀምጠው ባንድ ኤርትራዊ አነጋጋሪነት ትንሽ ሲያነጋግሩን ከቆዩ በሁዋላ ወደ ሚኒስቴሩ ዋና ዲሪክተር ላኩን።

የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ሚኒስቴር (ዋና ዲሪክተር) የተባለው ሰው ከወጣትነቱና ገና ውፍረት ያልተጫነው ከመሆኑ በቀር መልኩና በጠቅላላ ሁኔታው «ሲኞር ሙሶሊኒን » በጣም ይመስል ነበር። ስሙን ምን ጊዜም አልረሳው፤ «ዶክቶር ሚቸሌ » ይባል ነበር። የሙቶ አለቃውንና ኤርትራውያን አነጋጋሪ ተከትለን ገብተን ያንገት ሰላምታ ስንጥስ ግንባሩ ቁዋጥሮ ዝም ብሎ ሲመለከትን ቆይቶ፥

«ሮም መቸ መጣችሁ? ለምን መጣችሁ? በላቸው » አለ፤ ግን ባሩን እንደ ቁዋጠረ ወደ አነጋጋሪው ዘወር ብሎ። ሮም የሄድን አርብ መሆኑንና የፓንዛ መርከብ የሚነሳበት ቀን እስኪደርስ ታሪካዊ ቦታዎችን ለማየት መሄዳችነን እንዲነግርልን ልጅ ይልማ በንግሊዝኛ ለሙቶ አለቃው ሲነገረው ዋናው ዲሪክተር በታም ተቆጥቶ፥

«እስረኞች ናችሁ እንጂ ቱሪስቶች አለመሆናችሁን ማወቅ አለባችሁ! ደግሞ በኛ ፊት ከጣሊያንኛ በቀር በማናቸውም የአውሮፓውያን ቁዋንቁዋ እንድትናገሩ አንፈልግም። ጣሊያንኛ እስከታውቁ ባነጋጋሪ አማካይነት ባገራቸው ቁዋንቁዋ መናገር ትችላላችሁ ባላቸው » አለው አነጋጋሪውን። ያረፍንበትን ጠይቆ ሆቴል መሆኑን የሙቶ አለቃው ሲነገረው እዚያ ከመስሪያ

ቤቱ አጠገብ ኤርትራውያን ሰራተኞች በሚኖሩበት በማሳረፍ ፈንታ ሆቴል በማሳረፉ እሱንም ተቆጣው። ከዚያ ያኑለት ወደ ናፖሊ በሚሄደው የመጀመሪያ ባቡር ወስዶ፥ ወዲያውኑ ወደ ፓንዛ እንድንሄድ እንዲያደርግ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶና እስከዚያ ድረስ ባስተናገዱን ሹማምንት ደግነት ምክንያት ልንረሳው ትንሽ ቀርቶን የነበረውን እስረኝነታችነነም አስታውሶ ወደ እስር ቤታችን አባረረን!

## ምዕራፍ ሃያ ሶስት

# ፓንዛ

ፓንዛ ከናፖሊ ብዙ ሳይርቅ በምእራብ መሀከለኛ - ባህር የሚገኝ አነስተኛ ደሴት ነው። በውስጡ የባህሩን ዙሪያ ጠረፉን ተከትለው፥ በዬራሳቸው ስም የሚጠሩ ጥቂት መንደሮች አሉበት። ከኒያ ታናሽ መንደሮች አንዱ «ፎርና » ይባላል። ክቡር ራስ እምሩ ሀይለ ስላሴና ክቡር ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ፥ መጀመሪያ ወደ ጣሊያን አገር እንደ ሄዱ ያረፉት «ፎርና » ነበር። ብዙ ህዝብ ያለበትና የመንግስት መስሪያ ቤቶችም በገብያው ያሉበት ግን በጠቅላላው የደሴቱን መጠሪያ ስም የያዘው «ፓንዛ » ነው። እዚያ ፓንዛ የመንግስቱ ተቃዋሚዎች የሆኑ ብዙ ግዞተኞች (ኮንፊናቲ) ይኖሩ ነበር። ያን ጊዜ እንደደማነው በኒያ ግዞተኞች መሀከል በጣሊያን አገር ስመ - ጥር የሆኑ ፈላስፋዎች ፕሮፌሰሮች ጋዜጠኞችና ባለ ልዩ ልዩ ሙያ የፖለቲካ ሰዎች ነበሩባቸው። ልጅ ይልማና እኔ ከመርከብ ፓንዛ እንደ ወረድን፥ ወደ አስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሄደን ከተመዘገብንና ካገረ - ገዡ (ኮሚሳሪዮ) ከተገናኘን በሁዋላ ራስ እምሩና ደጃዝማች ታዬ ወደ ነበሩበት ወደ ፎርና ተወሰድን።

ፎርና ራስ እምሩና ደጃዝማች ታዬ የነበሩት እኛም ከደረስን የገባንበት ያንድ ሴት ቤት ነበር። ሴትዮዋ ባለቤታቸው ሞተው ከሽማግሌ አባታቸውና ከሁለት ወጣት ወንዶች ልጆቻቸው ጋር ይኖሩ ነበር። ታዲያ እርስ በርሳቸው ከነቤተሰባቸው ከሚኖሩበት ሌላ ሁለት ትፍር ቤቶች ስለ ነበሩዋቸው እኒያን ትርፍ ቤቶች ለኛ መኖሪያ ለመንግስት አከራይተው በዚያ ላይ ምግባችንንና የፅዳትም ሌላም የሚያስፈልገንን አገልግሎት እሳቸው ችለው በየወሩ ሂሳባቸውን ከመንግስት ይቀበላሉ። ስለዚህ ፎርና አምት ወር ወይም ከዚያ ትንሽ በለጥ ያለ ጊዜ ስንቆይ በገንዘብ መልክ እየራሳችን ከነበረን ትናንሽ ጥሪት በቀር የምናገኘው ነገር አልነበረም እንጂ በምግብና በሚያስፈልገን አገልግሎት በኩል አንዳች ችግር አልነበረብንም።

አገረ - ገዡ «ኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሪ » እውነት መሆኑን አናውቅም እንጂ ፋሽስት አለመሆናቸው ይወራላቸው ነበር። የሆነ ሆኖ ለኛ በጣም ደግ ነበሩ። በተለይ ለክቡር ራስ እምሩ እጅግ ከፍ ያለ አክብሮትና አድንቆት ነበራቸው። ፈረንሳይኛ ያውቁ ስለ ነበረ ተገናኝተው በሚነጋገሩበት ጊዜ ሁሉ «ኤክስላንስ » ክቡርነትዎ ከማለት በቀር አንድ ቀን «ራስ እምሩ » ብለው በስማቸው ሲጠሩዋቸው ሰምቼ አላውቅም። ለልጅ ይልማም፥ - ለንደን ዩኒቬርሲቲ የኢኮኖሚክ ሳይንስ ምሩቅ መሆኑን ስላወቁ - አክብሮትም የተለዩ ፍቅርም ነበራቸው። ብዙ ጊዜ «የሱን ያክል ትምርት ያለው እዚህ በመሀከላችን አንድ የለም! » እያሉ በርከት ያሉ ሰዎች ባሉበት ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አንዳንድ ቀን ኮሚሳሪዮው በሾፌር የሚነዳ ኦቶመቢላቸውን ትተው በሞተር ቢስክሌት መጥተው ልጅ ይልማን አፈናጥጠው ወስደው አብረው ይውሉና ማታ ይመልሱታል። በጠቅላላው ኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሬ ለኛ ምን ያክል ደግ እንደ ነበሩና ከፍ ያለ አክብሮት እንደነበራቸው ምስክር ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው እሳቸው አገረ - ገዢ ሆነው ፖንዛ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ እኛን ስለሚመለከት ጉዳይ - ትእዛዝም ይሁን ሌላ - ሊነጋግሩን ሲፈልጉ ራሳቸው እኛ ወዳለንበት መጥተው አነጋግረውን ከመሄድ በቀር አንድ ቀን እንኩዋ ወደ ፅህፈት ቤታቸው ጠርተው የማያውቁ መሆናቸው ነው። ታዲያ እሳቸው ስለኛ የነበራቸውን አስተያየት በመመልከት የመስሪያ ቤቱ ሹማምንትና ሰራተኞችም የፀጥታ ክፍል ሰራተኞችና ካራቢኔሪዎችም (ፖሊሶችም) የደሴቱ ህዝብ ሳይቀር በደህና ይመለከቱን ስለ ነበረ በጠቅላላው በሀገራችን በኢትዮጵያና በህዝብዋ ለዘለቄታው በደረሰው መከራ ከማዘን በቀር በእለት ኑሮዋችን የሚያሳዝነን ነገር አልነበረም።

ራስና ደጃዝማች ይኖሩበት የነበረው ቤት ባለ ሁለት ክፍሎች ሆኖ፥ አንዱ ክፍል ሁላችንም ባንድ ላይ ተቀምጠን የምንጫወትበትና ወዲያውም መብል ቤታችን ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የሁለቱ (የራስና የደጃዝማች) ምኝታ ቤት ነበር። ሁለተኛው ቤትም፥ እንዲሁ ባለ ሁለት ክፍሎች ሆኖ፤ አንዱ ክፍል ልጅ ይልማና እኔ የምንተኛበት ሁለተኛው የሚጠብቁን ፖሊሶች (ካራቢኔሪዎች) የሚኖሩበት ነበር።

አንድ ማታ ራስ በልተን ሁላችንም ወደዬምኝታ ቤታችን ከሄድን በሁዋላ በራችን ስለተመታ ብንከፍት ያገረ - ገዢው ሾፌር እዚያ ቆሞ አንዳችነን ኮሚሳሪዮ ሊያነጋግሩን እንደሚፈልጉ ነገረን። እሳቸውም ከኦቶመቢላቸው ወጥተው እዝያው ባጠገቡ ቆመው ነበር። ልጅ ይልማና እኔ ገና በቀን ልብሳችን እንድላእን ስናወራ ስለ ነበረ በራችን የተመታ ሁለታችንም ቶሎ ወደ ኮሚሳሪዮው ሄደን ሰላምታ ስንሰጣቸው በምኝታ ጊዜ መጥተው በማስቸገራቸው ማዘዛቸውን ገልፀው ከመንግስቱ መሪ ከሲኞር ሙሶሊኒ የተላኩ ትልቅ ሰው ክቡር ራስ እምሩን ለማነጋገር እንደሚፈልጉ ነገሩን። ከሙሶሊኒ የተላኩት ሰው ከኦቶመቢሉ ውስጥ እንደ ተቀመጡ ነበሩ።

«መቸ? » እሳቸው ልጅ ይልማ።

«ነገ ጥዋት መመለስ ስላለባቸው አሁን ማነጋገር ነው የሚፈልጉ። »

«አጉል ጊዜ መጥተን በማስቸገራችን እኔም የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተርም እናዝናለን፤ ነገር ግን የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር የመጡ ለዚህ ጉዳይ ብቻ ስለሆነና ነገ በጥዋት ለመመለስ የሚቸኩሉበት ጉዳይ ስላላቸው አሁን ተገናኝተው ማነጋገር ይፈልጋሉ » አሉ አገረ - ገዡ። ከዚያ ልጅ ይልማና እኔ እያዘንም እዬፈራንም ሄደን በር ስንመታ ትንሽ ከቆዬን በሁዋላ ራስ በሌት ልብሳቸው ላይ የጥዋት ልብሳችውን ደርበው መጥተው በሩን ከፈቱና በዚያ ሰዓት በቀን ልብሳችን ሲያዩን፥

«ምነ ምን ሆናችሁ? » አሉ እንደ መደንገት ብለው። ሁዋላ እንደ ነገሩን የዘመድ ሞት መርዶ ይዘንባቸው የሄድን መስሎዋቸው ኖሮዋል።

«ደህና ነን። አገረ ገዡ፥ የቅኝ ግዛቶችን ዋና ዲሪክተር ይዘው መጥተው ክቡርነትዎን ለማነጋገር ከሙሶሊኒ ተልከው መጥተዋልና አሁን ንገሩልን ስላሉን ነው። አሁን ሁለቱም እውጭ ቆመዋል » አላቸው ልጅ ይልማ።

«ምነው አይነጋም? ወይስ እንዲህ ሌሊት እንቅልፍ መከልከሉም ከቅጣታችን አንዱ ክፍል ይሆን? » አሉ ራስ በስጨት ብለው።

«ወደ ምኝታ ቤት ክገቡ መቆዬትዎንና ሳይተኙ እንደማይቀሩ ስንነግራቸው ኮሚሳሪዮው በጣም ነው ያዘኑ። ስለዚህ መቸም ተነስተዋልና አነጋግረዋቸው ቢመለሱ የሚሻል አይመስልዎትም? » አለ ልጅ ይልማ ብስጭታቸውን ለማብረድ የሚናገራቸውን ቃላትም የሚናገርበትን ስልትም በጥንቃቄ እዬመረጠ።

«ድግ ነው፤ ልብሴን ለብሼ ልምጣ » ብለው ወደ ምኝታ ቤታቸው ሲገቡ እኛም ኮሚሳሪዮውና የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር ወዳሉበት ሄድን ያነለት ማታ ከሲኞር ሙሶሊኒ ወደ ክቡር ራስ እምሩ ተልኮ የመጣው የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር ባለፈው ምዕራፍ የማለከትሁትን አንባቢዎች እንደሚያስታውሱት ሮማን፥ በመንብናታችን ተቀጥቶ ወዲያውኑ ወጥተን ወደ ፓንዛ እንድንላክ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ ያባረረ «ዶክተር ሚቸሊ » የተባለው ወጣት ነው። ዶክቶር ሚቸሊ ሮማ ፅህፈት ቤቱ ተቀምጦ ካነጋገርን ፍፁም የተለዬ ሆን ታዬን። ኮሚሳሪዮው በዬስማችን ሲያስተዋውቁን፥ ከዚያ በፊት አይቶን እንደማያውቅ ሁሉ በፈገግታ የጅ ሰላምታ ሰጥቶ፥ ያገሩ አዬርና የኑሮው ሁኔታ ተስማምቶን እንደ ሆነ ትንሽ እንደ ጠያዬቀን ራስ ለብሰው ወደ ሙብል ቤት ሲመለሱ በመስኮት ስላዬን፥ መጀመሪያ ልጅ ይልማ ሄዶ፥ አነጋገሮዋቸው ተመለሰና ሁላችንም እንድንገባ ምልክት አሳዬን።

ከሙብል ቤቱ ውስጥ ራስ ከተቀመጡበት ሌላ አንድ ወንበር ብቻ ነበር። በጠቅላላው የነበሩን ወንበሮችም በቁጥራችን ልክ አራት ስለ ነበሩ ባንድ ተቀምጠን በምጫወትበትና በምንበላበት ጊዜ ወደ ሙብል ቤት እንወስዳቸዋለን፤ በምንተኛበት ጊዜ፥ ለልብሳችን ማስቀመጫ እንዲሆኑ ወደዬምኝታ ቤታችን እንወስዳቸዋለን፤ ስለዚህ ያንለት ማታ የልጅ ይልማና የኔ ወንበሮች እምኝታ ቤታችን ስለ ነበሩ እሙብል ቤት የነበሩ የራስና የደጃዝማች ወንበሮች ብቻ ነበሩ።

ክቡር ራስ ተነስተው ለኮሚሳሪዮው የጅ ሰማታ ከሰጡና፥ ከዚያም ኮሚሳሪዮው ከቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር ጋር ካስተዋወቁዋቸው በሁዋላ ተቀምጠው ኮሚሳሪዮውን እንዲቀመጡ ጋበዙዋቸው። ኮሚሳሪዮው በበኩላቸው እዚያ የነበረው ባዶ ወንበር አንድ ብቻ መሆኑን ሲያዩ የቅኝ

ግዛቶችን ዋና ዲሪክተር እንዲቀመጡ ጋብዞዋቸው። ዋናው ዲሪክተር ግን ኮሚሳሪውን አቁሞ እሱ መቀመጥ አለመፈለጉን ራሱን በመነቅነቅ ገልፀ። እኔ ሶስተኛ ወንበር ባለመኖሩ የተፈጠረውን ችግር የተገነዘብሁት የሁለቱን (የኮሚሳሪዮውንና የዋናውን ዲሪክተር) መገባበዝ ከተመለከትሁ በሁዋላ ነበር። ያን ጊዜ እንደ መደንገጥ አልሁና እኛ ምኝታ ቤት ወንበር ለማምጣት ልወጣ ስል፥ ራስ ተመልከተው፥

«ሀዲስ ወንበር ለማምጣት እንደሆነ የምትሄድ አያስፈልግም » ስላሉኝ መለስ አልሁ። ከዚያ እንዲያ ራስ ተቀምጠው ሁለቱ ሹማምንት ቆመው በዝምታ ትንሽ ተፋጥጠው ከቆዩ በሁዋላ፥

«ነገ በጣም ጥዋት ወደ ሮማ የምመልስበት ብርቱ ጉዳይ ስላስገደደኝም ምንም እንኩዋ የያዝሁዋቸው መልእክቶች ደስ እንደሚያሰኙዎ ባምን አጉል ጊዜ መጥቼ ከምኝታዎ እንዲቀሰቀሱ በማድረጌ አዝናለሁ። የመንግስታችን መሪ ክቡር ቤንቶ ሙሶሊኒ ሁለት መልክቶች እንነግርዎ ልከውኝ ነው የመጣሁ። አንደኛው መልእክት ቤት - ንብረትዎ ርስትዎና ማናቸውም የርስዎ የነበረው ሁሉ እንዲመለስልዎ ገናናው የጣሊያን መንግስት ስለ ፈቀደ እርስዎ ከዚህ ወደ ሀገርዎ እስኪመለሱ ድረስ ስለርስዎ ሆኖ የሚረከብልዎን ሰው በፅሁፍ እንዲያስታውቁ ነው። ሁለተኛው መልእክት » ብሎ የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር ሊቀጥል ሲል ራስ አቋዋርጠው ከተቀመጡበት ተነሱና፥

«እግዚአብሄር ይስጥልኝ፥ የኔ ቤት - ንብረት ርስትና ማናቸውም የኔ የነበረው ሁሉ የኢትዮጵያ ነፃነት ሲጠፋ አብሮ ጠፍቶዋል! አሁን ቤት - ንብረት ርስትና ማናቸውም የኔ የሆነ ነገር የለኝም! ሁሉንም የጣሊያን መንግስት ለወደደው ይስጠው? » ሲሉ የመራራ ንግግራቸው ተቃራኒ በሆነ ፈገግታ ፊታቸው ሁሉ በርቶ ሁላችንም በድንጋጤ ዝም ብለን እንመለከታቸው ጀመር። እንዲያ ዝም ብለውን ትንሽ ከቆዬን በሁዋላ የቅኝ ግዛቶች ዋና ዲሪክተር በቆመበት እንዳለ የቃል ሰላምታ ብቻ ሰጥቶ ዘወር አለ። ከዚያ ኮማሳሪዮውም የቃልና የጅ ሰላምታ ለራስም ለኛም ሰጥተው ዋናውን ዲሪክተር ተከትለው ወጡ።

የጣሊያን ሹማምንት ከሄዱ በሁዋላ ደጃዝማች ከተኙበት ተነስተው እኛ ወደ ነበርንበት መጥተው የሆነውን ሁሉ ስንነግራቸው እሳቸውም እንደኛ እንዲያውም ከኛ ጠንከር ባለ ቁዋንቁዋ በራስ ላይ ፈረዱ።

ክቡር ራስ እምሩና ክቡር ደጃዝማች ታዬ፥ በሁሉ ባይሆን በብዙ ነገር የተለያዩ እምነት የተለያዩ አስተሳሰብና ያሰራር ስልት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። ክቡር ደጃዝማች ታዬ፥ በድሮው የኢትዮጵያውያን እምነት የፀኑ በድሮው አስተሳሰብና ያሰራር ስልት የሚያምኑ ነበሩ። ክቡር ራስ እምሩ ምንም እንኩዋ ጥንታዊውን የኢትዮጵያውያን እምነትና አስተሳሰብም ያሰራር ስልትም ጭራሽ ዋጋ ባያሳጡ ለዘመናዊው እምነትና አስተሳሰብም ያሰራር ስልትም ክብደት የሚሰጡ ነበሩ። ታዲያ ሁለቱ ሲከራከሩ ልጅ ይልማና እኔ አብረናቸው ተቀምጠን መስማቱ ደስታን ብቻ ሳይሆን ትምርትን ጭምር ይሰጠን ነበር።

«አሁን ሁላችሁም በኔ የፈረዳችሁብኝ እኮ ወይ እኔ አሳቤን እንዲገባችሁ አድርጎ መግለፅ አልቻልሁ ይሆናል፤ ወይም እናንተ እንዲገባችሁ አልፈለጋችሁ ይሆናል እንጂ፥ አሳቤን ከተረዳችሁልኝ ልትፈርዱብኝ አትችሉም። እኔ ያልሁት «ይህ ቤት የኛ ቤት አደለም የጣሊኢያን መንግስት ሰርቶም ይሆን ተከራይቶ እኛን በእስረኝነት ያስቀመጠበት ቤቱ ነው። ስለዚህ ለኛ ሹማምንቱ ሲመጡ የሚቀመጡበትም በቂ ወንበር እንዲኖር ማድረግ የባለቤቱ የመንግስት ፈንታ ነው። እንጂ የኛ ፈንታ አይደለም። እኛ እስረኝነታችነን ትተን ለሹማምንት መቀመጫ ወንበር ልንበደር አንሄድም፤ ወይም ስላሰሩን ውለታቸውን ለመመለስ የተቀመጥንበትን ወንበር እኛ ተነስተን ለነሱ አንሰጥም » ነው፤ ይህ ደግሞ «እልከኛ አያሰኝም » አሉ ራስ።

«ስማኝ ራስ » አሉ ደጃዝማች። «ስማኝ፤ ይህ ሁሉ አሁን ለክርክር ያመጣኸው ነው። እኛ ወንበር ለመደበደር ባለመሄድህ ሳይሆን እቤታችን ያለው ወንበር እንዳይመጣ ከልክለህ ሊጎዱህም ሊጠቅሙህም የሚችሉትን ባለሥልጣኖች በማሳዘንህ ነው የፈረድንብህ። ደግሞ ከብርቱ ጠላት ጋር መከራከርና መፈካከር በጁ ሳይገቡ ነው እንጂ በጁ ከገቡ በሁዋላ እግዚአብሄር «በቃ » እስኪል ድረስ አመልን አሳምሮ የታዘዙትን ፈፅሞ ካልኖሩ በባሰ ችግር ላይ በባሰ ውርደት ላይ መውደቅን ያስከትላል። አሁን እግዚአብሔር ላንተ

ቆሞ «ተው! » ባይላቸው መንግስት የላካቸውን ሹማምንት «እኔ ተቀምጬ እናንተ ቆማችሁ መልእክቱን ንገሩኝ » ስትላቸው ተቆጥተውው ፖሊሳቸውን ከውጪ ጠርተው እጅህን ጎትቶ እንዲያነሳህና እነሱ ባንተ ወንበር ተቀምጠው፥ አንተ ቆመህ መልእክቱን እንድትሰማ ለማድረግ አይችሉም ኖሮዋል? ይህስ ያንተን ክብር የሚነካ አይሆንም ኖሮዋል? በኔ አስተያየት እንዲህ ያለው ሳያስፈልግ ራስን ላደጋ ማጋለጥ ነው። እንዲህ ያለው ባገራችን ‹ከተያዙ በሁዋላ መፈራገጥ ጀርባን ወይም ጎንን ለመምለጥ› እንደሚሉት ያለ ነው። »

«እጀን በፖሊስ አስጎትተው ማስነሳትና እነሱ በኔ ወንበር ተቀምጠው እኔ ቆሜ መልእክቱን እንድሰማ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን እንዲያ ማድረግ የማይገባ ግፍ መሆኑን ስለማምን በግድ ስሸነፍ አደርገዋለሁ እንጂ ወድጄ በፈቃዴ አላደርገውም። ‹ማድረግ የማትወደውን ነገር ጠላትህ አስገድዶህ ስታደርግ ክብርህ የሚነካህ አይሆንም ወይ?› ስላሉት እኔ አስተያየት ሰው ለሚያምንበት ነገር ወይም ለመብቱ ከብርቱ ጠላት ጋር ተከራክሮ ታግሎ ሲሸነፍ የሚያምንበትን ነገር ቢተውና መብቱን ቢያጣ አይዋረድም፤ ክብሩም አይነካም። የሚዋረድና ክብሩ የሚነካ ገና ለገና ጠላቴ ሀይለኛ ስለሆነ ሳያሸንፈኝ አይቀርም ብሎ ፈርቶ ሳይከራከር ሳይታገል የሚያምንበትን ነገር የትወና መብቱን ፈቅዶ የሰጠ እንደ ሆነ ነው » አሉ ራስ።

«በጠላት እጅ ሳይገቡ በጠላት እጅ እንዳይገቡ መታገልና መጋደልማ ያባት ነው። አሁን የምነጋገረው በጠላታችን እጅ ከገባን በሁዋላ በጠላታችን ስልጣን ስር ከዋልን በሁዋላ ስለተደረገውና ሊደረግ ስለሚገባው ነው። ለዚህ ነው አሁን ለክርክር ብለህ ያመጣኸው ነው ያልሁህ » ብለው ደጃዝማች ሲነሱ ሌሊቱ ተገባድዶ ስለነበረ ሁላችንም ተሰነባብተንና ወደዬምኝታ ቤታችን ሄድን። ባማግስቱ ኮሚሳሪዮ ሳልቮቶሬ ጥዋት የቅኝ ግዛቶችን ዋና ዲሪክተር ሸኝተው ከቀትር በሁዋላ ወደ አስራ አንድ ሰአት ግድም ወደኛ መጥተው ትናንቱን ማታ ስለደረሠው ቅር የሚያሰኝ ነገር ክቡር ራስን ይቅርታ ከለመኑ በሁዋላ ዋናው ዲሪክተር ሳይነግረን ወዝፎ የተወውን ከሙሶሊኒ የተላከ መልእክት ነገሩን።

መልእክቱ አንደኛ እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንኖርበት የነበረው ቤት ባለቤት ለቤት ኪራይ ለምግብ ለፅዳትና ለሌላ ለኛ ለሚሰጥ ማናቸውም አገልግሎት ሁሉ ሂሳባቸውን ለመግንስት ባለስልጣኖች እያቀረቡ ይከፈል በነአበረው ፈንታ ከተከታዩ ወር ጀምሮ ለክቡር ራስ እምሩና ለክቡር ደጃዝማች ታዬ፥ በወር አንዳንድ ሺህ ሊሬ እንዲከፈለንና ለቤት ኪራይ ለምግብ ለሰራተኛ ደመወዝና ለማናቸውም ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ወጪ ራሳችን ከዚያ በዬወሩ ከሚሰጠን ገንዘብ እንድንከፍል፤ ሁለተኛ በደህና ቦታ ላይ የገንዘብ አቅማችን በሚችለው ኪራይ ቤት እንደ ተገኘ ተከራይተን ከፎርና ወደ ዋናው ከተማ ወደ ፓንዛ እንድንዛወር መፈቀዱን የሚገልፅ ነበር። ወዲያው አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፓንዛ ከባህሩ ዳር ማለፊያ ቤት በደህና ዋጋ ስለተገኘልን ተከራይተን ምግብ የማሰናዳቱንና የፅዳቱን ስራ የምትሰራ አንድ ሰራተኛ ቀጥረን ወደዚያ ተዛወርን።

ፓንዛ ክቡር ደጃዝማች ታዬ፥ አንድ አመት ያክል የቀረነው ሶስታችን ሁለት ዓመት ካስር ወር ስንቆይ ኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሬ አገረ - ገዢ እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ አንዳች የምናማርረው ነገር አልገጠመንም፤ ኑሮዋችን በግዞተኞች ኑሮ አይን ሲታይ በውነቱ ደናህ ነበር። ልጅ ይልማና እኔ ወደ ግለኞች ቤት አንገባም እንጂ ቀን ከሆነ በደሴቱ ውስጥ በፈለግነው ጊዜ ወጥተን የፍለግነው ያክል ሽር ሽር ለማድረግ እንችል ነበር። ራስንና ደጃዝማችን ብቻ ሲወጡ አንድ «የካራብኔሪ » (የፖሊስ) ሹምና ሁለት ተራ ካራቢኔሪዎች ይከተሉዋቸው ነበር። ልጅ ይልማንና እኔን ግን ከነሱ ጋር መውጣት ስንፈልግ ካልሆነ ካራቢኔሪዎችም አይከተሉን። ፓንዛ፥ ካይነተኞች መዋኛዎች አንዱ ከኛ ቤት አጠገብ ያለው ስለሆነ በበጋ እዚያ፥ ሁላችንም ከውጭ ከሚመጣውና ከደሴቱ ህዝብ ጋር ስንዋኝ እንውል ነበር። የፈለግናቸውን መፃህፍት ከውጭ አገር አዝዘን አስገብተን ማንበብም እንችል ነበር። ራዲዮ ገዝተን እቤታችን ውስጥ የአለም ወሬ ያለተቆጣጣሪ መስማት እንችል ነበር። በጠቅላላው እስራታታችን «እዚያ ከነበሩት የጣሊያን ግዞተኞች የቀለለ ነበር« ለማለት ይቻላል።

ክቡር ደጃዝማች ታዬ፥ አንድ አመት ያክል ፓንዛ ከኛ ጋር ከቆዩ በሁዋላ «ምህረት ተደርጎልዎታል » ተብለው ወደ ሀገራቸው ከመመለሳቸው በፊት እዚያው በኢጣሊኢያ ውስጥ «አቨሊኖ » ወደ ሚባል አገር ሄዱ።

እንደሚወራው ወሬ - እውነት መሆኑ እንኩዋ አጠራጣሪኢ ነው - አቨሊኖ የጣሊያንን ጥንታዊና ዘመናዊ ስራዎች እየዞሩ ጎብኝተው ከሲኞር ሙሶሊኒና ከሌሎች የጣሊያን ታላላቅ ሹማምንት ጋር ተገናኝተው ተዋውቀው እንዲመለሱ የሚጋበዙ የኢትዮጵያ ታላላቅ መኩዋንንትና ወይዛዝር አርፈው ሚቆዩበት ቦታ ነበር።

ኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሪ፥ ከፓንዛ ገዢነታቸው ተሽረው በምትካቸው ሌላ ኮሚሳሪዮ ሲሾሙ የኛም የኑሮ ሁኔታ ከመልካም ወደ ክፉ ተለወጠ።

፩ኛ፡ - ጥዋት ከሶስት ሰአት በፊት ከቤታችን እንዳንወጣና ማታ ካስራ ሁለት ሰአት በሁዋላ ከቤታችን ውጪ እንዳንገኝ ታዘዝን።

፪ኛ፡ - በደሴቱ ውስጥ ለሽርሽር መሄድ የምንችልባቸው ቦታዎች ተወሰኑ።

፫ኛ፡ - ያገሩ ህዝብ በማይዋኝበት ጊዜ ለብቻችን ካልሆነ፥ ጣሊያኖች በሚዋኙበት ጊዜ እንዳንዋኝ ተከለከልን። ባጭሩ ሁኔታችን ከግዞተኝነት ለእስረኝነት የቀረበ ሆነ። ደግነቱ ኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሬ ተሽረው በቦታቸው አዲሱ ኮሚሳሪዮ ከተተኩ በሁዋላ ፓንዛ ብዙ ጊዜ አለመቆየታቸውን ነው። አዲሱ ኮሚሳሪዮ በተሾሙ በጥቂት ወራት ውስጥ «ሊፓሪ » ወደ ሚባል ሌላ ደሴት ተዛወርን።

## ምዕራፍ ሃያ አራት

# ሊፓሪ

ሊፓሪ በጣሊያን አገር «ሲሲሊያ » ከሚባለው ክፍል ሰሜን በምእራብ መሀከለኛ ባህር የሚገኝ ደሴት ነው። በሮማውያን ተረት፥ (ሌጅንድ) ሊፓሪ «የነፋሶች አምላክ የሚኖርበት መናገሻ ከተማው ነው » ይባል ነበር። በነፋሱ

ሀይለኛነትና ባዬሩ ጠባይ ቶል ቶሎ ተለዋዋጭነት ሊፓሪ ባጠገቡ ካሉት የደቡብ ጣሊያን ክፍሎች (ከሲሲሊያና ከካላብሪያ) የተለዬ መሆኑ እሙን ቢሆንም «በጣም ከፉ » የሚባል አይደለም።

ከቡር ራስ እምሩን ልጅ ይልማንና እኔን አንድ የፀጥታ ጥበቃ ሹም አምስት ያክል ጭፍሮቹ ከፓንዛ በመርከብ ወስደው ሊፓሪ ሲያወርዱን እዚያ አንድ የፀጥታ ጥበቃና የፖሊስ (የካራቢሬኔ) ሹማምንት ከጥቂት የዬድርጅታቸው አባሎች ጋር ሆነው ተቀበሉን። የሊፓሪ ከተማ ዙሪያውን በዳገት ተከበው ከዳገቱ ስር ባለ ሸለቆ ውስጥ ነው። ከምስራቅ ወገን ባለው ዳገት አናት ላይ፥ ትልልቅ ያረጁ ህንፃዎችና የህንፃ ፍራሾች ባንድነት በሸበት አሮጌ ግንብ ታጥረው ይታያሉ። በዚያ በሸበታም ግንብ በታጠረው ሰፊ ግቢ ውስጥ ቁጥራቸውን የማላስታውሰው ብዙ ዩጎስላቮች ይኖሩ ነበር።

እኒያ ሊፓሪ አሮጌ ግንብ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ዩጎስላቮች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1934 የዩጎስላቪያ ንጉስ የነበሩትን ንጉስ አሌክሳንድርን ያስገደለው ኡስታሸ የተባለው የዩጎስላቪያ አቢዮታዊ ድርጅት አባሎች መሆናቸውን ሰማን። ንጉስ አሌክሳንድር የፈረንሳይ መንግስት ጋብዞዋቸው ሄደው፥ ማርሴይ በሚባለው የወደብ ከተማ ሲወርዱ በጊዜው የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩት ሊዊስ ባርቱ ይቀበሉዋቸዋል። እዚያ፥ ሁለት (ንጉሡና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባርቱ) ጎን - ለጎን ሲሄዱ፥ የኡስታሸ አባሎች ባንድ ላይ ይገድሉዋቸውና ከሌሎች ያሳብም የግብርም አበሮቻቸው ጋር ሆነው ወደ ጣሊያን አገር ሸሽተው ይሄዳሉ። «በንጉስ አሌክሳንድር መገደ የጣሊያንና የሀንጋሪ መንግስቶች ነበሩበት እዬተባለ ይወራ ለነበረው ወሬ ምናልባት የኒያ ዩጎስላቮች ያንጊዜ ጣሊያን አገር ሊፓሪ ግንብ ውስጥ መኖር እንደ ምስክርነት ሊጠቀስ ይችል ይሆናል።

ያ፥ ዩጎስላቮች ይኖሩበት የነበረው ባሮጌ ግንብ የታጠረ ግቢ፥ ለኛም ሊፓሪ በምንቆይበት ጊዜ መኖሪያ እንዲሆን ተወስኖ ኖሮ በመርከብ ወሰዱና ከመርከብ ስንወርድ የተቀበሉን ሹማምንትና ጭፍሮቻቸው ይዘውን ወደዚያ ሄዱ። ግን፥ ግቢው አንድ ይሁን እንጂ ለኛ መኖሪያ እንዲሆን የተመደበልን ቤት ዩጎስላቮች የሚኖሩበትን አልፎ ለብቻው ፈንጠር ብሎ ካጥሩ ጥግ የተሰራ

ዘመናዊ መጠነኛ ቤት ነው። እዚያ ዋና ዋናዎቹ ሹማምንት ተሰብስበው ይጠብቁን ነበር። እነዙም የደሴቱ ዋና አስተዳዳሪ (ኮሚሳሪዮ) የፀጥታ ጥበቃ ሹምና አንድ የፖሊስ (የካራቤኔሬ) ኮሎኔል ነበሩ። ከመርከብ መውረጃው ለመኖሪያ እስከ ተመደበልን ቤት ድረስ ራቅ ያለ ቢሆንም በግራችን ነበር የሄድን። እዚያ እንደ ደረስን የተቀበሉን ሹማምንት እኛን ለሰላምታ ያክል እንኩዋ ሳያነጋግሩን ከወሰዱን የፀጥታ ጥበቃ ሰዎች ጋር ሲነጋገሩ ቆይተው የፖሊሱ ኮሎኔል ወደኛ መለስ አሉና፥ ሻንጣዎቻችነን እዬከፈትን እንድናሳይ አዘዙን።

«ከያዛችሁን ጀምሮ እስካሁን ድረስ እኛም፥ ሻንጣዎቻችንም በናንተ እጅ ነን። ፓንዛ ስንኖርም ከዚያ ተነስተን እዚህ እስክንደርስ ስም የጠባቂዎቻችሁ አይን ላንድ አፍታ አልተለዬንም፤ ታዲያ እንዲያው እኛን ለማስቸገር ካልሆነ፥ አሁን በሻንጣችን ውስጥ ‹ምን ይገኛል› ብላችሁ ነው ‹ክፈቱ ዝጉ› የምትሉን? » ሲሉ ራስ ባማርኛ ልጅ ይልማ በጣሊያንኛ ተረጎመላቸው።

«ቀዋሚ ስራታችን ነው እንጂ፥ እናንተን ለማስቸገር የምናደርገው አይደለም፤ ስለዚህ ሻንጣዎቻችሁ ሁሉ ከፍታችሁ ማሳዬት አለባችሁ? » አሉ ኮሎኔሉ ንግግራቸውንም ፊታቸውንም ከረር አድርገው።

«መክፈቻ የለኝም፤ ሁሉንም እዬሰበራችሁ እዩ በለው » አሉ ራስ በቁጣ።

«ሻንጣዎች ቢሰብሩኮ የምንጎዳ እኛ ነን! ታዲያ ብንከፍትላቸውና ቢያዩ አይሻልም? » አላቸው ልጅ ይልማ። እኔም የሱን አሳብ ደግፌ ነበር። ነገር ግን ራስ፥ እኛን ገላመጡና በኮሎኔሉ ላይ አይናቸውን አፍጥጠው «ሮምፐሬ ቪዴሬ! » (ሰብራችሁ እዩ!) አሉ፤ በደካማ ጣሊያንኛቸው። የጣሊያን ሹማምንት ግን ሻጣን ወደ መስበሩ በመሄድ ፈንታ ባንድ ላይ ሰብሰብ ብለው በዝቅተኛ ድምፅ ይመካከሩ ጀመር። በዚያ ፈንታ እኛም ራስን ለምነን፥ መክፈቻዎቻቸውን ለልጅ ይልማ እንዲሰጡ ለማድረግ ቻልን። ከዚያ ኮሎኔሉ መጀመሪያ ከራስ ሻንጣዎች አንዱ እንዲከፈት አዝዘው ተከፍቶላቸው ከፀጥታ ጥበቃ ሰዎች አንዱ፥ በሻንጣው ውስጥ ያለውን እቃ በጥንቃቄ ገለጥ፥ እያደረገ

ሲያይ፥ ከስር ባንድ የተሸፈነ ትንሽ ሳጥን ውስጥ የጣሊያን መንግስት የነገስታት ተወላጆች ለሆኑ ልኡላን የሚሸልመውን ኒሻን ስላገኙ፥

«ይህ ምንድነው? » ሻንጣ ፈታሹ ኒሻኑን ከሳጥኑ ውስጥ አውጥቶ እዚያ ለነበርነው ሁሉ እያሳዬ። ሹማምንቱ ያን ኒሻን ከብበው እያዩ እስበሳቸው ሲነጋገሩ ቆይተው፥

«መቸ ያገኙት ነው? » አሉ ኮሎኔሉ ራስ ሻንጣቸው ሲበረበር ፈንጠር ብለው ቆመው ወደ ምሚመለከቱበት ዘወር ብለው።

«ነፃ በነበርን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስትና የጣሊያን መንግስት፥ ለመሳፍንቶቻቸውና ለሚኒስትሮቻቸው ሽልማት ሲለዋወጡ ያገኘሁት ነበር » አሉ ራስ።

«ይህ፥ ከነገስታት ለተወለዱ መሳፍንት ብቻ የሚሰጥ እጅግ የተከበረ ሽልማት ስለሆነ በጥንቃቄ ሊጠብቁት ይገባል » ሲሉ ኮሎኔሉ፤

«እኔ አሁን፥ ይህን ኒሻን ከምንም አልቆጥረው! አሁን ይህ ኒሻን ለኔ፥ ከዚህ ከመሬቱ አሸዋ ምንም ልዩነት የለውም! ብትፈልጉ ውሰዱት! » አሉ ራስ፥ ኒሻኑን በመፀየፍ አይን እያዩ። ከዚያ በሁዋላ ያልተከፈቱት የራሽ ሻንጣዎች የልጅ ይልማና የኔ ሻንጣዎችም ሳይከፈቱ እዚያ እኛን ለመጠበቅ ከተመደቡት ፖሊሶች (ካራቢኔሪዎች) በቀር፥ የጣሊያን ሹማምንት ተከታዮቻቸውን ሁሉ ይዘው፥ የቃል ሰላምታ ብቻ ሰጥተውን ሄዱ።

እንዲህ በዬቦታው ካጋጠሙን የጣሊያን ሹማምንት አንዳንዶቹ ስልጣናቸውን ለማሳዬት ትንሽ ከመንገድ የወጣ ነገር ሲያደርጉ ካዩ ክቡር ራስ እምሩ፥ ለዚያ ለትንሹ ከመንገድ የወጣ ነገር ትልቅ ከመንገድ የወጣ ነገር ሳይመልሱ አሳልፈውት አያውቁም። ታዲያ፥ አድርጎታቸው ከባድ የእስረኝነት ኑሮዋቸውን ይብሱን እንዳያከብድባቸው ሰግተን ነገሩ ካለፈ በሁዋላ ያደረጉት ወይም የተናገሩት የማይገባ መሆኑን ስንነግራቸው ከኛ ጋር ይስማማሉ። ነገር ግን በትኩሱ ያሰቡትን ሳይናገሩ ወይም፥ ሳያደርጉ አይመለሱም። ብቻ የሚያስገርመው፥ ያ አይነት ጥጥር አቋዋማቸው ቀንበራቸውን በማከበድ ፈንታ ሲያቀልላቸው በጣሊያን ሹማምንት ሁሉ ፊት ሲያከብራቸው ይታይ ነበር።

ሊፓሪ በገባንበት ቀን ማግስት፥ የሚጠብቁን ካራቢኔሬዎች ሹም (አፑንታቶ) ልጅ ይልማንና እኔን «ተጠርታችሁዋል » ብሎ ወደ አገረ - ገዥው ፅህፈት ቤት ወሰደን። እዚያ ኮሚሳሪዮው ተቀብለው ትንሽ ካነጋገሩን በሁዋላ ስለ ማንነታችን ቅፅ እንድንሞላ ወደ ክፍሉ ሰራተኛ ላኩን። ያነለት በኔ የደረሰው ለክቡር ራስ እምሩና ለልጅ ይልማ የብዙ ቀን መሳቂያ ሆናቸው። ወደ ሀገራችን ተመልሰን አመታት ካለፉ በሁዋላ እንኩዋ ልጅ ይልማ በጭዋታ መሀከል በኔ ሊያስቅብኝ ሲፈልግ ከሚያወራቸው ወሬዎች አንዱ ያ «በኔ ደረሰ » ያልሁት ነበር። ታሪኩ ከሞላ ጎደል የሚከተለው ነው።

ፓንዛ እስክንደርስ ድረስ ስለያንዳንዳችን የተመዘገበው መታወቂያችን ስም ከናባታችን የተወለድንበት ክፍለ ሀገር እስከ ቀበሌው የተወለድንበት አመተ ምህረት የተፃፈበት ነበር እንጂ የናት ስም አልነበረበትም። ፓንዛ ስንገባ ግን የናቶቻችነንም ስም እንድናስመዘግብ ስለ ተጠዬቅን ልጅ ይልማ አስመዝግቦ እስኪጨርስ እኔ አንድ አሳብ መጥቶብኝ እሱን አውጥቼ አውርጄ ወዲያው አንድ ውሳኔ አደረግሁ። ‹አሁን ይህን ሁሉ የሚፅፉትኮ› አልሁ ባአቤ። ‹አሁን ይህን ሁሉ የሚፅፉት ምናልባት፥ መልካም እድል አጋጥሞን ከዚህ ማምለጥ ብንችል የወላጆቻችን ስም እስከሚኖሩበት ቦታ ስለሚያውቁ እነሱን ይዘው ለማሰቃየት ነው። ታዲያ ምን ይሻለኛል? ስም ከተማረክሁበት ቀን ጀምሮ በዬደረስሁበት ቦታ የተፃፈ ስለ ሆነ መቸስ እግዚአብሔር ይሁናቸው እንጂ አሁን ምንም ማድረእግ አልችል። እናቴን ግን አሁን የውሸት ስም ፈጥሬ ብሰጥ ላድናት እችላለሁ› አልሁና ወዲያው አገሬ ሳለሁ ከማውቃቸው ሴቶች መሀከል ስም መረጣ ጀመርሁ። ከዚያ በህይወት ያሉ ሴቶች ስም የሰጠሁ እንደ ሆነ እናቴን ለማዳን እነሱን አሳልፎ ለስቃይ መዳረግ የማይገባ መሆኑን ህሊናየ ጮሆ ስለ ነገረኝ የሞተች ሴት ስም ፍለጋ ሄድሁ። ወዲያው ልጅ ሳለሁ ከጎረቤታችን የጎዋደኛየ እናት ሞታ እዚያ መሰንበቻውን የነበረው ልቅሶ ትዝ አለኝና የስዋን ስም ለመስጠት ወስኜ፥ ከማስመዝገቤ በፊት ለልጅ ይልማ ስነግረው «አንተን ለማምለጥ ያብቃህ እንጂ እናትህን ፍለጋ የሚሄድ ሰው የለምና ይልቅ ዝም ብለህ የውነተኛ ስማቸውን ብታስመዘግብ ይሻልላ » አለኝ። ነገር ግን እኔም እሱም ምክንያታችነን ለማስረድት ጊዜ

ስላልነእብረን በውሳኔየ ፀንቼ ያን የውሸት ስም አስመዘግቤ ነበር። ከዚያ በሁዋላ ፓንዛ ሁለት አመት ካስር ወር በቆዬንበት ጊዜ ስለ ማንነታችን ቅፅ መሙላት አስፈላጊ ስልነበረ ችግርም አልነበር። ነገር ግን ወደ ሊፓሪ ስንዛወር፥ ቅፅ መሙላት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ስለዚህ መዝጋቢው በልጅ ይልማ ጀምሮ ልክ ፓንዛ የተጠዬቅናቸውን እዬጠዬቀ መጣና «የናት ስም? » ሲል ስሰማ ፓንዛ ለናቴ ፈጥሬ የሰጠሁዋትን የውሸት ስም ለማስታዎስ ብፈልግ ጠፋኝ። መዝጋቢው ልጅ ይልማን እየጠዬቀ መዝግቦ እስኪጨርስ ያን የውሸት ስም መስጠቴኢ እንኩዋ ትዝ አለልኝ አለ። ያን የጠፋ ስም እንዲወልድ አሳቤን ባስጨነቅሁት መጠን፥ እንኩዋንስ የጠፋውን ሊገኝ የያዘውም እዬተበተነበት መሰብሰብ አቃጠው። ደግነቱ መዝጋቢው የልጅ ይልማን ምዝገባ በመጨረስ ላይ እንዳለ ኮሚሳሪዮው አስጠርተውት ሄደ።

«ኧረ ጉድ ፈላልህ! » አልሁት ልጅ ይልማን፤ መዝጋቢው ተጠርቶ እንደ ወጣ።

«የምን ጉድ ነው የፈላው? »

«ፓንዛ ቅፅ ስናስሞላ ለናቴ የሰጠሁዋት የውሸት ስም ጠፋኝ? » ስለው ገርሞት ዝም ብሎ ቆይቶ፥

«እየውልህ ያነለት ‹እባክህ ዝም ብለህ የናትህን የውነተኛ ስም አስመግብ› ብዬ ስለነበር ‹አሻፈረኝ!› ብለህ አሁን ራስህን ብቻ ሳይሆን እኛን ጭምር የሚያዋርድ ነገር ልታደርስብን ነው! » አለኝ።

«እናንተን ጭምር የሚያዋርድ ምን ነገር አደረግሁ? »

«ፓንዛ ለናትህ ያስመዘገብኸው የውሸት ስም ከጠፋ እዚህስ የውሸት ስም ልታስመዘግብ አደል? ታዲያ እዚህ የምታስመዘግበው ፓንዛ ካስመዘገብኸው የተለዬ ሆኖ ሲገኝ ውሸታሞች ናቸው መባላችን ይቀራል? »

«እኔ ‹ስለዋሸሁ እናንተ የምትዋረዱበት ምክንያት አይታዬኝምና ይልቅ እሱን ትተህ መዝጋቢ ሳይመጣ ፓንዛ ስለዚህ ነገር ከተነጋገርነው የምታስታውሰው አለ እንደሆነ ይረዳኝ ይሆናልና ንገረኝ »

«እኔ፥ አንተ ከዚህ ማምለጥ አትችልም እንጂ ማምለጥ ከቻልህ፥ እናትህን ማንም አያገኛቸውና፥ የሞተች ሴት ስም ከማስመዝገብ የውነተኛ ስማቸውን ብታስመዘግብ ይሻላል› ብዬ መምከሬ እንጂ ሌላ የማስታውሰው የለኝም » ሲል፤

«አ - እቴቴ ያጤነሽ! » አልሁ እዬሳቅሁ። «እቴቴ ያጤነሽ » ስምዋን ለናቴኢ የሰጠሁት የሞተቹ የጉዋደኛዬ እናት ነበረች። ልጅ ይልማ «የሞተች ሴት ስም ከማስገብ የናትህን የውነተኛ ስም ብታስመዘግብ ይሻላል » ሲል የሞተች ሴት ስም ማስመዝገቤና የሞተችቱ ሴትም የጉዋደኛየ እናት «እቴቴ ያጤነሽ » መሆንዋን አስታወስሁ።

«እኔን የብዙ ቀን መሳቂያ አደረገኝ » ያልሁት ታሪክ ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ ያመለከትሁት ሆኖ ሳለ፥ ልጅ ይልማ ያነለት ከኮሚሳሪዮ ፅህፈት ቤት እንደ ተመለስን ለክቡር ራስ እምሩ ያወራውና ሁዋላም ለብዙ ሰው ያወራው የነበረ በኔ ለማሳቅ እንዲመቸው ታሪኩን ትንሽ ለውጥ እያደረገ ነበር።

«ሀዲስ » ይላል፤ ወሬው እውነት እንዲመስልለት አስቀድሞ እዬሳቀ። «ሀዲስ፥ ሊፓሪ ከሚሳሪዮ ፅህፈት ቤት መዝጋቢው «የናትህን ስም ንገረኝ » ቢለው ከመደንገጡ የተነሳ የናቱ ስም ጠፍቶት እኔ አስታዎስሁት! ታዲያ እላይ እንደ ተመለከተው እናቴን በኔ ምክንያት ሊደርስባት ከሚችል አደጋ ለመሰወር የፈጠርሁት የውሸት ስም ነበር እንጂ የጠፋኝ የውነተኛ ስምዋ አልነበረም። ብቻ እሱ የሚፈልገው በኔ ማሳቅን ስለ ነበረ አሰማምሮ ሲያወራ እንኩዋንስ ሌሎችን እኔንም ያስቀኝ ነበር!

እኛ ሊፓሪ ገብተን አጭር ጊዜ እንዳሳለፍን፥ ዩጎስላቮች ከዚያ ሄዱ። ወዳገራቸው ተመልሰው ወይም ወደ ሌላ ሀገር ሄደው እንደሆን ግን አናውቅም። ስለዚህ፥ እዚያ ባሮኜ ግንብ በታጠረ ሰፊ ግቢ ውስጥ እኛን ከኛ ራቅ ብለው ካጥሩ በር አጠገብ እየኖሩ ግቢውን የሚጠብቁ ሽማግሌ ከቤተሰባቸው ጋር ቀረን። አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ልጅ ይልማም «ምህረት ተደርጎልሀል » ተብሎ ወደ ሀገሩ ስለ ተመለሰ፥ ከእስረኞች፥ ክቡር ራስ እምሩና እኔ ብቻ ቀረን።

ከቡር ራስ እምሩና፥ እኔ ከሁለት አመት በላይ ሊፓሪ ስንቆይ እኔን ፓንዛ የጀመረኝ «የብሮንካይቲስ » በሽታ - ባዬሩ ጠባይ ተለዋዋጭነት ምክንያት - እዬጠነከረብኝ ከመሄዱ በቀር፥ ከሹማምንቱ ሆነ ከደሴቱ ህዝብ በኩል አንዳች ችግር ገጥሞን አያውቅም ነበር። በገንዘብ በኩል ሊፓሪ በማንከፍልበት የመንግስት ቤት እንኖር ስለ ነበረ እንዲያውም ከፓንዛ ይሻለን ነበር። እንዲሁም ፓንዛ በኮሚሳሪዮ ሳልቫቶሬ ቦታ የተተኩት አገረ - ገዥ ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ከቤታችን ውጪ እንዳገኘና ከተወሰነ ጊዜ በፊት ከቤታችን እንዳንወጣ በደሴቱ ውስጥ ከተወሰነ ቦታ አልፈን እንዳንሄድና ብቻችነን ካልሆነ ካገሩ ህዝብ ጋር እንዳንዋኝ ከልክለውን የነበረውን ሁሉ የሊፓሪው ኮሚሳሪዮ ፈቅደውልን ስለ ነበረ፥ የሊፓሪው የእስረኝነት ኑሮዋችን ፓንዛ ወደ መጨረሻው ጊዜ የነበረውን ያክል ከባድ አልነበረም።

የሊፓሪው ኮሚሳሪዮ፥ በተለይ እኔ በወጣትነት እድሜዬ በባእድ አገር የእስረኝነት ኑሮ መኖሬ አንሶ ደግሞ በዚያ ላይ ጤና አጥቼ የምሰቃይ በመሆኔ ያዝኑ እንደ ነበረ ከነገሩዋቸው ሰዎች ከመስማቴም ሌላ ባድራጎታቸው ይታይ ነበር። ለምሳሌ ሀኪም ቤት ሄጄ መታከሜን ከዘበኞች ወይም ከሌላ የሰሙ እንደ ሆነ ብዙ ጊዜ ለምርመራም ሆነ ለህክምናና ለመድሀኒት የከፈልሁትን ፋክቱር አየው - በገንዘብ ያልተቸገርሁ መሆኔን እዬነገርሁዋቸው - በግድ ይመልሱልኝ ነበር። እንዲሁም የምችል ብሆን ኖሮ ላቲን ለመማር ፍላጎት እንደ ነበረኝ ከነገርሁዋቸው ሰዎች ሰምተው ከደሴቱ ጳጳስ ጋር ተነጋግረው አንድ መነኩሴ በነፃ እንዲያስተምሩኝ አድርገውልኝ ያለ ጠባቂ ብቻየን ወደ ጳጳሱ ግቢ እዬሄድሁ እማር ነበር። በመጨረሻ በሽታየ እያደር እዬጠነከረብኝ መሄዱን ሲያይ የደሴቱ ዋና ሀኩም ወደ ሊፓሪ ከተዛወርሁ ጀምሮ የጤናየን ሁኔታ በተከታተለው መጠን በሽታየ እዬከፋ እንጂ እዬተሻሻለ የማይሄድ መሆኑን ሲያረጋግጥ ቢቻል ወደ ተወለድሁበት አገር እንድመለስ የማይቻል ከሆነ ግን ያዬሩ ጠባይ ቶል ቶሎ ወደማይለዋወጥበት የጣሊያን «የብስ » ክፍል እንድንዛወር የውነተኛ (ፕሮፌሽናል) አስተያየቱን እንዲሰጥ ስለነገሩት እሳቸው ያስመሩለትን መስመር ተከትሎ አስተያየት ሰጠ። ከዚያ የሀኪሙን «ሪፖርት » መሰረት አድርገው ወደ ተወለድሁበት አገር እንድመለስ ያ ባይቻል ግን ጣሊያን አገር ወደ «የብሱ » ክፍል እንድዛወር የበላይ

ባለስልጣኖች ጠይቀው ረዢም ጊዜ ሳይፈጅ «ካላብርያ » ወደ ሚባለው የጣሊያን የብስ ክፍል እንድዛወር መፈቀዱን የሚያበስር መልስ ደረሰን። የደረሰን መልስ ካንድ ወገን ፋታ ከማይሰጥ «የብሮንካይቲስ » በሽታየ የሚያሳርፈኝ ስለመሰለኝ ደስ ቢያሰኘኝ፥ ከሌላ ወገን፥ ራስን ብቻቸውን ትቻችወ እኔም አንድ ኢትዮጵያዊ በሌለበት ብቻየን ለመኖር የመሄዱ ሃሳብ ከብዶኝ በመሄድና ባለሁበት ከስቃይ ጋር በመቆዬት መሀከል መወሰን አቅቶኝ ተቸግሬ ነበር። ነገር ግን ሀኪሙና ኮሚሳሪዮው ብቻ ሳይሆን ራስ ጭምር ሊፓሪን ለቅቄ እንድሂድ አጥብቀው ስለመከሩኝ «ከላብሪያ » ውስጥ «ሎንጎብኮ » ወደሚባል ቦታ ሄድሁ።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት

# ሎንጎቡኮ

ሎንጎቡኮ በደቡብ ጣሊያን «ካላብርያ » በሚባለው ካንድ ከፍተኛ ተራራ ደረት ላይ የሚገኝ ትንሽ ከተማ ነው። «ከተማ » ከመባል እንኳዋ ምናልባት፥ «የጠገር መንደር » ቢባል ከእውነተኛ ሁኔታዎች ጋር በተስማማ! ከህዝቡ የሚበዛ በርሻና በከብት እርባታ የሚኖር ባላገር ከመሆኑ ሌላ ከጥቂት ትናንሽ ሱቆች በቀር፥ ከፍተኛ የንግድ ቤቶች ወይም ፋብሪካዎች አልነበሩበትም። የነበረው ትምህርት ቤት አንድ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ የሚማሩበት ያንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነበር። የጤና አገልግሎት የሚሰጠውም አንድ ክሊኒክ ብቻ ነበር። ከዚያ ከፍ ያለ ትምርትና ህክምና የሚፈልግ ሰው ቢኖር ተራራውን ወርዶ ሮሳኖ ወደ ተባለ ከተማ ወይም ራቅ ወዳሉ ሌሎች ከተሞች መሄድ ነበረበት። በጠቅላላው ሎንጎቡኮ በከንቲባዎችና በከተሞች ስራት ይተዳደር የነበረ ከመሆኑ በቀር «ከተማ » የሚያሰኝ ሌላ ምክንያት አልነበረውም።

ሎንጎቡኮ እስኪደርስ ድረስ እዚያ ወይም በሌላ የጣሊያን ክፍል የኢጣሊያን ክፍል የኢትዮጵያ እስረኞች መኖራቸውን አላውቅም ነበር። እርግጥ ከነክቡር (ሁዋላ ልኡል) ራስ እምሩ ጋር «ፓንዛ » ሳለን «ማርሻል ግራሲያኒን » ለመግደል ሙከራ ከተደረገ በሁዋላ «ሳርዴኒያ » ውስጥ «አሲናራ » በሚባል ደሴት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ታስረው እንደ ነበረ ሰምተናል። ታዲኢያ እኒያ ያሲናራ እስረኞንች ሁሉ ምህረት ተደርጎላቸው ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን ይጠብቁን የነበሩት የፀጥታ ክፍል ሰራተኞችና ፖሊሶች (ካራቢኔሬዎች) ነግረውን ነበር። ነገር ግን ግንጎቡኮ ስንደርስ አስራ አድስት ያክል እስረኞች አገኘሁ። እነሱም፡-

፩. ደጃዝማች (ሁዋላ ቢትወደድ) መንገሻ ውቤ ከሌሎች እስረኞች ተለይተው እዚያ ባጠገብ ለብቻ ይኖሩ የነበር።

፪. ባላምባራስ (ሁዋላ ፊታውራሪ) እማኙ ይመር፥

፫. ሙሴእ አብርሃም ከኢትዮጵያዊት ባልተቤታቸውና ካራት ወንዶች ልጆቻቸው ጋር።

፬. ልጅ (ሁዋላ ደጃዝማች) ግርማቸው ተክለ ሀዋርያት፥

፭. ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህ፥

፮. ልጅ (ሁዋላ ኮሎኔል?) ኮስሮፍ በጐሲያን፥

፯. ልጅ (መሀንዲስ) አበበ ገብረ ፃድቅ፥

፰. አቶ ሳሙኤል ገብረ የሱስ፥

፱. አቶ በርሄ ክፍሉም፤

፲. አቶ ብርሃነ ሀብተ ሚካኤል፤

፲፩. አቶ ግራዝማች ለገሰ ገብሬ ነበሩ ፡

እኒህ እስረኞንች መጀመሪያ - እዚህ ላይ እንደ ተመለከተው ማርሻል ግራሲያኒን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ምክንያትን «አሲናራ » በሚባለው ደሴት ታስረው ከነበሩት ብዙ ኢትዮጵያውያን ጋር ነበሩ። ሁዋላ፥ የሚበዙት በምህረት ወደ አገራቸው ሲመለሱ ከመሀከላቸው እነሱና ሌሎች ተመርጠው ሎንጎቡኮ እንዲቆዩ ተደረገ። ከነዚያ ደግሞ «ነጋድራስ ወዳጆ አሊ » እዚያው ሲሞቱ አሁንም በርከት ያሉት በምህረት ተመልሰው አስራ አድስቱ ቀሩ። እኒህ አስራ አድስቱ ተለይተው የቀሩበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ አልተገለፀላቸውም። «ከሁሉ ተለይተው ወደ ሁዋላ መቅረታቸው ከሁሉ የበለጠ አደገኞች በመሆናቸው ወደ ሀገራቸው የተመለሱ እንደ ሆነ በጣሊያን ባለሥልጣኖች ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ የተደረገ ነው » ሲባል ይሰማ ነበር፤ ሊመስልም ይችላል። ነገር ግን መጀመሪያ እስረኞች ወደዬስርቤቱ የተሰደዱበትም ሆነ ሁዋላ በምህረት የሚበዙት ሲመለሱ ጥቂቱ ተመርጠው ወደ ሁዋላ የቆዩበት ሁኔታ ሲታይ እንዲሁ በዘፈቀደ እውር የበቀል ጥምን ለማርካትና ቁጥር ለመሙላት እንጂ የተገደሉት ወይም የታሰሩት ሰዎች አደገኞች መሆኑ አለመሆናቸው በጥናት ተደርሶበት አለመሆኑ ግልፅ ነበር።

‹አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም› የተባሉ ወጣቶች የማርሻል ግራሲያኒን ህይወት ለማጥፋት በሰነዘሩት አደጋ ምክንያት ከክቡር (ሁዋላ ልኡል) ራስ እምሩ ጋር የነበሩት የሆለታ መኮንኖችና ወታደሮች ካለቃቸው ከኮሎኔል በላይ ሀይለ አብ ጋር እንዲሁም የራስ መኩዋንንትና አዲስ አበባ የነበሩት ምሁራንም መኩዋንንትም በዬተገኙበት በገፍ እዬተያዙ ተገድለው እንደ ጥራጊ ባድነት በሰፋፊ ጉድጉዋድ ከተጣሉ በሁዋላ የተረፉት እዬተሰበሰቡ በዬቦታው ታጐሩ። ከዚያ በተከተሉት ጥቂት ቀናት፥ ለይምሰል ያክል እንኩዋ «ምርመራ » የሚባል ነገር ሳይሞከር ከኒያ በዬቦታው ከታጐሩት እስረኞች ብዙዎች እንደ በግ እዬተጐተቱ እዬወጡ ሲታረዱ ሰነበቱ።በመጨረሻ ከመጉደል፥ የተረፉት በእስረኝነት ናኩራ ደናኔ አሲናራ፥.....ወዘተ ወደ ተባሉ ቦታዎች ተላኩ። አንዳንዶቹ ተይዘው ወደ እስር ቤት የተላኩበትን ሁኔታ ራሳቸው ሲያወሩ ከማስገረም አልፎ ያስቅ ነበር። ያቶ «በርሄ ክፍሎም » ታሪክ ትንሽ ረዘም ቢልም ለምሳሌነት መጥቀሱ በዚያ ጊዜ የተደረገውን ለማሳዬት ይረዳል።

አቶ በርሄ ክፍሉም እንዳወራን በትግራይ ክፍለ ሀገር ተወልዶ፥ አስመራ በሚሲዮን ትምህርት ቤት የጣሊያን ቋንቋዋ የተማረ ነበር። እዚያ (አስመራ) ነጋድራስ ወዳጆ አሊን ያገኝና አዲስ አበባ ወስደው የመንግስት ቤት ተቀእምጦ ስራ ሲፈልጉት ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ይይዙና የመንግስት ስራ የመያዙ ተስፋ ከንቱ ሆኖ ይቀራል። ከዚያ ጣሊያንኛ የሚያውቅ በመሆኑ ሁዋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተባለው የጃንሆይ ግቢ የብዙ ጣሊያን ሹማምንት ፅህፈት ቤት ሆኖ ስለ ነበረ እዚያ በተላላኪነት ተቀጥሮ ያገለግል ኖሮዋል። ግራሲያኒን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ምክንያት ያለቁት ኢትዮጵያውያን አልቀው ወደዬእስር ቤቱ እንዲላኩ የተመደቡት የስም ዝርዝር ወጥቶ ከሚጠባበቁት መሀከል ወደ አሲናር እንዲሄዱ የተወሰነባቸው «ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ » የተባሉ መኮንን ኖረዋል። እስረኞቹን ከያቅጣቸው የሚወስዱት ካሚዮኖች ቀርበው የስም፥ ዝርዝር የያዙት የአሊያን ሹማምንት እያንዳንዱን እስረኛ በስሙ እዬጠሩ በካሚዮን በሚጭኑበት ጊዜ፥ ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ ቢጠሩ ሌሊቱን ሾልከው አምልጠው ኖሮ «የውሀ ሽታ » ይሆናሉ! «ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ! » ቢባል በያቅጣጫው «አቤት » ባይ ይጠፋል። ከዚያ አንድ ታሊያን «ቆይ በርሄ ያለበትን እኔ አውቃለሁ » ብሎ እዬሮጠ ሄዶ፥ «ተላላኪ በርሄ ክፍሎምን » ይዞ ይመጣና «ያውልህ በርሄ! » ብሎ ለስም ዝርዝር ጠሪው ይሰጠዋል።

«አንተ ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ ነህ? » ይላል የስም ዝርዝር ጠሪው።

«ኧረ ፊታውራሪ በርሄ ተስፋይ አይደለሁም፤ እኔ በርሄ ክፍሎም ነኝ » ይላል በርሄ ክፍሎም።

«ፊታውራሪ ባትሆንም አባትህ ተስፋይ ባይሆንም አንተ ‹በርሄ› ከሆንህ ግዴለም ይበቃል፤ ሂድ ግባ፥ ጊዜየን አታጥፋብኝ! » ብሎ የስም ዝርዝር ጠሪው ጣሊያን እዬገፋ እካሚዮኑ ውስጥ ያስገባውና በርሄ ወደ ምፅዋ፥ ከዚያ ወደ አሲናራ ከተወሰዱት እሰረኞች ጋር ይወሰዳል! እስረኞች አሲናራ የቆዩትን ያክል ከቆዩ በሁዋላ ደግሞ ለብዙዎቹ ምህረት ተደርጎላቸው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ፥ በርሄ ተመርጠው ሎንጎቡኮ በእስረኝነት እንዲቆዩ ከተወሰነባቸው

ጋር እንዲቀር ይወሰንበታል! ስለዚህ «ተመርጠው ሎንጎቡኮ በእስረኝነት እንዲቆዩ ከተወሰነባቸው ጋር እንዲቀር ይወሰንበታል! ስለዚህ «ተመርጠው ወደ ሁዋላ የቀሩት ከሁሉ የከፋ አደገኞች ስለሆኑ ነው » ከተባለ ከነሱ አንዱ በርሄ ክፍሎም መሆኑ ነው! እንግዲህ የበርሄ፥ ክፍሎምን ረዢም ታሪክ ለማውራት ከመስመሪ ስለወጣሁ ያንባቢዎችን ይቅርታ እዬለመንሁና እንዳልካቸው ተስፋ እያደረግሁ ወደ ዋናው ታሪክ እመለሳለሁ።

ካስራ ስድስቱ እስረኞች ሙሴ አብራህም ከባልተቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር መንግስት በተከራዬው ቤት ለብቻቸው ይኖሩ ነበር። ሌሎች እስረኞች፥ ሁሉም ባንድ ምድር ቤትና ፎቅ ያለው ትልቅ ቤት ነበር የሚኖሩ። ያ ቤትም እንዲሁ መንግስት ከግለሰብ የተከራዬው ነበር። ቤቱ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ የቅርብ ጉዋደኞች ከሆኑት አንዳንድ ክፍል ለሁለት የያዙ ቢኖሩም የሚበዙት ለዬብቻቸው ክፍል ነበራቸው። ልጅ ግርማቸው ተክለ ማርያም ለዬብቻቸው ክፍል ከያዙት አንዱ ስለ ነበረ እኔ ከሱ ጋር እንድዳበል ተደረ። ከጥቂት ወራት በሁዋላ ግን ልጅ ግርማቸው ወደ ክቡር (ሁዋላ ልኡል) ራስ እምሩ እንዲሄድ ጠይቆ ስለ ተፈቀደለትና ስለ ሄደ ብቻዬን የክፍሉ ባለቤት ሆንሁ።

እኔ ሎንጎቡኮ ስደርስ እዚያ የነበሩ እስረኞች በወር የተወሰነ ገንዘብ እዬተሰጣቸው በዚያ ገንዘብ ምግባቸውን እያሰናዱ የሚመገቡ ራሳቸው ነበር። ለልብሳቸው ሆነ ወይም ለሌላ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳይ ሁሉ፥ ያንኑ በወር የሚያገኙትን እንዲበቃ ማድረግ የነሱ ፈንታ ነበር። ቀደም ብሎ ግን - እነሱ እንደነገሩኝ - «ሮማኖ » የተባለ ቤተሰብ የምግብ ማሰናጃ ትንሽ ሆቴል ስለ ነበረ እዚያ፥ እየተመገቡ ሂሳቡን መንግስት ይከፍል ኖሮዋል። እንዲሁም ለልብስ ለመድሃኒትና ለሌላ መንግስት አስፈላጊነቱን ላመነበት ጉዳይ ይከፍልላቸው ኖሮዋል። ታዲያ በዚያ ጊዜ እነሱ አስፈልጊያቸው በመሆኑ እንዲገዛላቸው የሚፈልጉት ነገር ለመንግስት ባለስልጣኖች አስፈላጊ ሆኖ ስለማይታያቸው ባለስልጣኖቹን ለማስረዳት ብርቱ ችግር የነበረ ከመሆኑ ሌላ ባለ ሆቴሉም ትርፉን ለማብዛት ለሚከፍለው ገንዘብ ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ ባለማቅረቡ ፅኑ ርሀብ እንደነበረባቸው ይናገሩ ነበር።

ሁዋላ፥ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረርዋ በፊት ብዙ አመታት ኢትዮጵያ የኖሩ፥ ኢጣሊያዊ ካቶሊክ መነኩሴ እስረኞችን ለመጎብኘት ወደ ሎንጎቡኮ ሄደው፥ በተለይ በምግብ በኩል መጎዳታቸውን ስለ ተረዱ መንግስት ለያንዳንዳቸው በዬወሩ የተወሰነ ገንዘብ እዬሰጣቸው በዚያ ምግባቸውን እንዲችሉ አስደረጉላቸው። እኔም ልጅ ግርማቸው ተክለ ሀዋርያት ወደ ከቡር ራስ እምሩ ከሄደ በሁዋላ የምኝታ ክፍሌ ለብቻየ ይሁን እንጂ የምግብ ጉዋደኝነቴን ካቶ ሳሙኤል ገብረ የሱስ ከልጅ አበበ ገብረ ፃድቅና ካቶ በርሄ ክፍሎም ጋር አድርጌ ምንም እንኩዋ ያ ጊዜ በጦርነቱ ምክንያት በጠቅላላው የጣሊያን ህዝብ ላይ ችግር እዬተባባሰ የሄደበት ጊዜ ቢሆን ያገኘነውን፥ እዬተረዳዳን ሰርተን እዬተመገብን ወደ ሀገራችን እስክንመለስ ድረስ የተለዬ ችግር ሳይይደርስብን ቆዬን።

የፓንዛና የሊፓሪ ነዋሪ ህዝብ፥ እዚያ የነበርነውን እስረኞች በደህና አይን ያየን እንደ ነበረ ሁሉ የሎንጎቡኮ ነዋሪ ህዝብም እዚያ ለነበሩት እስረኞች ማዘን ብቻ ሳይሆን ፍቅርም አክብሮትም ነበረው። ለዚህ ምክንያቶች ነበሩ። እነሱም፦

አንደኛ፥ ምንም እንኩዋ በሙሶሊኒ ጊዜ ለጣሊያን ህዝብ ቢያንስ ያንደኛ ደረጃን ትምህርት መጨረስ በህግ ግዴታ የነበረ በመሆኑ ከሎንጎቡኮ ህዝብ እስከ አራተኛ ክፍል በሚማሩበት ያንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብሮ ያልወጣ ባይኖር አብዛኛው ህዝብ ከትምርት ቤት ከወጣ በሁዋላ ወደ እርሻውና ወደ ከብት እርባታው ስለ ሚሄድ በጥቂት አመታት ውስጥ ያን ለማንበብና ለመፃፍ ያክል የተማረውን ትምርት ይረሳዋል። ስለዚህ ለማዘጋጃ ቤት ለፖሊስ ፅህፈት ቤት ወይም ለሌላ መስሪያ ቤት ማመልከቻ ማግባት ከሚፈልጉት የሎንጎቡኮ ነዋሪዎች መሀከል ለብዙዎች ማመልከቻቸውን ያለ ምንም ዋጋ የሚፅፉላቸው ኢትዮጵያውያን እስረኞች ነበሩ።

ሁለተኛ፥ ካንደኛ ደረጃ በላይ ትምህርታቸውን መቀልጠል ለሚፈልጉ የሎንጎቡኮ ወጣቶች መሸጋገሪያ ትምርት (ኢንተሚዲየሪ ኮርስ) የሚሰጥ ድርጅት ወይም ሰው ስላልነበረ ወጣቶቹን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ኮሌጅ ለመግባት የሚያበቃ የመሸጋገሪያ ትምህት ያለ ምንም ዋጋ የሚሰጥ «አበበ ገብረ ፃድቅ » ነበር። አበበ በመሀንዲስነት የፈረንሳይ

ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ ነበር። እንዲሁም ኮስሮፍ በጎሲያ (በትምርት ይሁን በልምድ አላውቅም) እንስሳትን ማከም ይችል ስለ ነበረ የሎንጎቡኮ ባላገሮች ከብቶቻቸው ሲታመሙባቸው ወደሱ እዬወሰዱ ያለ ዋጋ ያክምላቸው ነበር። ስለዚህ አበበንና ኮስሮፍን ሎንጎቡኮ በስማቸው የሚጠራቸ አልነበረም፤ ሁሉም አበበን «እንጀኜሬ » ኮስሮፍን «ዶቶሬ » ነበር የሚላቸው።

ስለዚህ የሎንጎቡኮ፥ ህዝብ እነዚህን በላይ ያመለከትሁዋቸውን የመሳሰሉትንም ሌሎችንም እንደ መልካም ጠባይና እንደ ጭዋነት ያሉ ነገሮች በኢትዮጵያውያን ላይ ሲያይ ኢትዮጵያውያን ፋሽስቶች ይሰብኩት እንደ ነበረው አውሬዎችና ፍፁም ደንቆሮዎች ሳይሆኑ፥ እንደ ሌላው ህዝብ ሁሉ ደግነትም እውቀትም ያላቸው ሰዎች የነበሩባቸው በመሆናቸው ይወዳቸውና ያከብራቸው ነበር። አንዳንድ የፋሽስትን ስራት አጥበው ይጠሉ የነበሩ አዋቂዎች ኢትዮጵያውያንን ከመውደዳቸው የተነሳ እንዲያውም፥ ላገራቸው ሰዎች ደፍረው የማይናገሩትን ምስጢር ለኛ ይነግሩን ነበር።

ከኒያ የፋሽት ጠላቶች መሀከል አንድ ቄስ ላቶ ሳሙኤል ገብረ የሱስና ለኔ የነገሩንን ለምሳሌ ያክል፥ ከሞላ ጎደል ከዚህ፥ እንደ ሚከተለው እፅፈዋለሁ።

«ሙሶሊኒ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የጣሊያን ህዝብ ከችግር ወጥቶ ስለማያውቅ ያን የውስጥ ችግር ለማስረሳት ባገር ፍቅርና እውን ሊሆን በማይችል ከንቱ የታላቅነት ህልም የህዝቡን መንፈስ መሸንገልን በስልጣን ላይ ለመቆዬት የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ አድርጎ የያዘ ነው። ስለዚህ ኢጣሊያን ካንድ ጦርነት ወደ ሌላ ጦርነት እዬመራ እያገባ የሀብትና የወጣት ድሀ አደረጋት! ዛሬ የቅኝ ግዛቶች ያሉዋችወ መንግስታት የማያዛልቅ መሆኑን ተረድተው የያዙዋቸውን ግዛቶች የሚለቁበትን ሁኔኢታ ሲያመቻቹ በሚታዩበት ጊዜ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ያን ያክል ህይወትና ሀብት እንዲጠፋ ያደረገበት ምክንያትና የኢትዮጵያ ጦርነት ከማለቁ «የጀነራል ፍራንኮን » የፋሽስት ስራት ለማበርታት ‹በስፔይን› ጦርነት ኢጣሊያ ጣልቃ እንድትገባ ማድረጉም የዚያ ዘዴው ክፍሎች ናቸው። የስፔይን ጦርነት ስያልቅ እንኩዋ ሙሶሊኒ በስልጣን እስካለ ድረስ ኢጣሊያ የወጣቶችዋን ህይወትና የተረፈ ትንሽ ሀብትዋን የምታጠፋበት ጦርነት መፍጠሩ አይቀርም »

እውነትም ቄሱ እንዳሉት፥ እንደ «ጎሪጎሪዮስ » አቆጣጠር በ1939 ሁለተኛው የአለም ጦርነት ከተነሳ በሁዋላ በ1940 ሙሶሊኒ ኢጣሊያ የአለም የጃፓን የጦር ባለ ቃልኪዳን መሆንዋን ባጅዋ አስታውቀ።

ቄሱም ሌሎችም ይሉት እንደ ነበረው የጣሊያን ህዝብ ችግር እዬተባባሰ የሄደ በተለይ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከወረረችበት ጊዜ ጀምሮ ነበር። በዚያ ጊዜ በሙሉ ኢጣሊያ የቃ እጥረትና የዋጋ ግሽበት ስለ ነበረ በገብያ የሚገኘውን ያክል መጠነኛ እቃ በውድ ዋጋ እዬገዙ የሚጠቀሙ ሀብት ያላቸው ነበሩ። የሚበዛው ህዝብ የሚኖርበትን የችግር ደረጃ በዬቤቱ ገብተን በባናይም ስራቱን የሚያቃወሙት ሰዎች ይናገሩት የነበረው እውነት መሆኑን በውጭ የሚታዬው ይመሰክር ነበር። ለምሳሌ ተራው ሰው ይቅርና በመንግስት ሰራተኞች መሀከል እንኩዋ መቀመጫውና ጉልበቱ የተጣፈ ሱሪ ወይም አንገቱና ክርኑ የተጠቃቀመ (የተደረተ) ኮት ለብሶ መሂድ የተለመደ የማስነውር ነገር ሆኖ ነበር። ወዳጆች ይሁኑ ወይም ጉዋደኞች በመንገድ ሲገናኙ ከሰላምታ ቀጥለው «ዛሬ ምን በላህ? አንተስ ምን በላህ? » ተባብለው ሲጠያየቁ መስማትም ልክ እንደ ሰላምታው የማይቀር፥ የተለመደ ነበር። ታዲያ ምንም እንኩዋ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ይዘው በቆዩበት ጊዜ ሁሉ እነሱ አገር በስረኝነት ስለ ነበርሁ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ይኖሩ እንደ ነበረ ባላይ የነሱ የምቾት ኑሮና የቃው በያይነቱ መትረፍረፍ የሚያስገርም እንደ ነበረ በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያ የነበሩት ሁሉ የሚናገሩት ነው። ቀደም ብለው በኤርትራ ይኖሩ የነበሩት ጣሊያኖችም እንዲሁ ከፍ ባለ ድሎት ይኖሩ እንደ ነበረ የሚያውቁ ሰዎች ይናገሩ ነበር። ታዲያ ባገራቸው የሚኖሩትን ጣሊያኖች ምቾትና የቃ መትረፍረፍ ስሰማ «ከቶ በሚገዙት ህዝብ አይን ምንም የማይጎላቸው ‹ምሉእ በኩለሄ› መስሎ ለመታየት ለፕሮፓጋንዳ የሚያደርጉት ይሆን? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ።

አንድ ቀን አቶ ሳሙኤል ገብረየሱስና እኔ ለሽርሽር በወጣንበት ካንድ ዛፍ ስር ተቀምጠን ስናወጋ የእስረኞች (የኛ) ጠባቂ የነበሩት «ሹምባሽ ገብረ ፃድቅ » መጥተው ባጠገባችን ከመቀመጣቸው አንድ ያረጀ ልብስ ለብሳ ባዶ እግርዋን የምትሂድ የጣሊያን ሴት ጀንያ - ሙሉ የጉቶ እንክትካች በራስዋ ተሸክማ፥ ባጠገባችን ከነበረው ጫካ ውስጥ ብቅ አለች። ያች መሀከል እድሜ

የነበራት ሴት እንደ ማቶት (የጋን፥ ወይም የንስራ ማስቀመጫ) ክብ ሆኖ በወፍራሙ የተጠቀለለ የጨርቅ መደላድል በራስዋ ላይ አስቀምጣ፥ በዚያ እምደላድል ላይ የጉቶ እንክትካች የሞላ ትልቅ ጆንያዋን አመቻችታ ተሸክማ በግራና ቀኝ እጆችዋ ወገብዋን ደገፍ አድርጋ ባዶ እግርዋን፥ ቀጥ ብላ ፈጠን እያለች ስትራመድ እንኩዋንስ ጆንያ ሙሉ የጉቶ እንክትካች የተሸከመች፥ አንድ ቁና እህል የያዘች አትመስልም ነበር። አቶ ሳሙኤልና እኔ፥ ያች ሴትዮ በሁለት እጆችዋ ወገብዋን ደግፋ እንዲያ በፍጥነት ስትሄድ፥ ጆንያው ከራስዋ ጋር የታሰረ ወይም በጅዋ የደገፈችው ይመስል ትንሽ እንኩዋ ንቅንቅ አለማለቱ አስገርሞን ስንነጋገር፥

«ወይ ግሩም አንታ! መቆዬትኮ መልካም ነው፤ ብዙ ነገር ያሳያል! » አሉ ሹምባሹ ሴትዬዋ ከኛ እስክትርቅም ዝም ብለው ሲመለከቱ ቆይተው። ሹምባሹን ያስገረማቸው ጉቶው ያለ ማሰሪያ ወይም ያለ ድጋፍ በሰው ራስ ላይ ተቀምጦ መሄዱ ሳይሆን አንድ የጣሊያን ሴት ጫማ ሳታደርግ ባዶ እግርዋን አሮጌ ልብስ ለብሳ ጆንያ ሙሉ ጉቶ በራስዋ ተሸክማ ስትሄድ ማየታቸው ነበር!

«መቆየት አደለም እዚህ አገር መጥቼ አሮጌ ልስብ የለበሰ አበሻ ሲያዩ የሚፀዩፉት የጣሊያን ሴቶች አሮጌ ልብስ ለብሰው ያለ ጫማ ያህያ ጭነት ተሸክመው ሲሄዱ እንዳይ ያደረገኝ? አሁን አገሬ ተመልሼ እዚህ ያዩሁትን ሁሉ እዚህ የጣሊያን ህዝብ የሚኖርበትን የኑሮ ሁኔታ ሁሉ ባወራ ማን ያምነኛል? ያገሬ ሰው ሁሉ ‹ውሸታ ወይም እድብ ነው› ኮ የሚለኝ! » አሉ።

በዚያ ጊዜ በጣልያን አገር ስለ ነበረው ችግር ሙሶሊኒንና የፋሽስትን ስራት ይጠሉ የነበሩ ሰዎች፥ ከዚህ የሚከተለውን ይነግሩን ነበር።

«መቸም ሙሶሊን ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የጣሊያን ህዝብ ከችግር ወጥቶ አያውቅ! ነገር ግን ችግሩን ይህን ያክል አከፍቶ የእለት ኑሮ ለመኖር የማይቻል ያደረገው አገር በማያፈራው ብቻ ተወስኖ መኖር (አውታርኪያ) የተባለው ትእዛዝ ከወጣና ብስራ ላይ ከዋለ በሁዋላ ነው። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ፥ የአለም መንግስታት ማህበር ወደ ኊልቱ አገሮች (ወደ ኢጣሊያና ወደ ኢትዮጵያ) የጦር መሳሪያ እንዳይገባ የእገዳ ውሳኔ አሳልፎ

ነበር። ነገር ግን ውሳኔው፥ የጦር መሳሪያን እንጂ እንኩዋንስ ለሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን እቃዎች የጦር መሳሪያ ለመስራት የሚያገለግሉትን ጥሬ እቃዎችም አልከለከለም። ብቻ ለሙሶሊኒ ያን ውሳኔ ምክንያት አድርጎ፥ አገር ውስጥ የማይገኙበትንና ቢገኙም በብቃት የማይገኙትን ለሰላማዊ፥ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ እቃዎች «በአውታርኪያ » ትእዛዝ መሰረት ከውጭ እንዳይገቡ እገዳ ለማድረግ ተመቸው። ታዲያ ካንድ በኩል ‹በጣሊያን አገር ብርቱ የእቃ እጥረትና የዋጋ ግሽበት እንዲፈጠር ያደረገው የአለም መንግስታት ማህበር ያሳለፈብን የእገዳ ውሳኔ› ነው እያለ የውሸት ፕሮፓጋንዳውን እየነዛ ከሌላ በኩል ለሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን እቃዎች ከውጭ ገዝቶ ለማስገባት ሊውል ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን እቃዎች ከውጭ ገዝቶ ለማስገባት ሊውል በሚገባው ገንዘብ ለጦር መሳሪያ የሚሆኑትን ጥሬ እቃዎች ብቻ እዬገዛ እያስገባ የጦር መሳሪያ ሀብት ከማምከን በቀር ሀብት ይወልድ ይመስል፥ ያው እሱን እዬሰራ በላይ በላዩ እየከመረ፥ ህዝቡን በብርቱ ችግር እንዲኖር አደረገው! »

በኢትዮጵያ «ያንድ ሰው ቤት ሲቃጠል በጎረቤቱ እጨለማ ውስጥ ላሉ ብርሃንን ራቁት ለሆኑ ሙቀትን ይሰጣል! » ይባላል። እንደዚያ ሁሉ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ተነስቶ ኢጣሊያ በ1940 እጦርነቱ ውስጥ መግባትዋ ሲታወጅ ምንም እንኩዋ ያ ጦርነት የብዙ ህዝብ ህይወትና ንብረት የሚያጠፋ መሆኑን እንጂ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ባናውቅ እኛ ነፃነታችንን ተገፈን ዙሪያው ጨለማ ሆኖብን እንኖር የነበርን ኢትዮጵያውያን እስረኞች «ምናልባት ኢጣሊያና የጦር ጉዋደኞችዋ ድል ሆነው ነፃነታችንን የምናገኝበት ጊዜ ይደርስ ይሆናል » ብለን ተስፋ የነፃነት ፍላጎታችንን ለመቀስቀስና ጊዜያዊ ደስታን ለመስጠት ያክል እንጂ ከዚያ የማያልፍ አልነበረም። ይሁን ለማለትም ምልክንያቶች ነበሩ፤

አንደኛ ያ ጊዜ ጀርመን በአውሮፓ ጃፓን በሩቅ ምስራቅ ብርቱ ተቃውሞ ሳይገጥማቸው ድል በድል እያከታተሉ የተቀዳጁበት ጊዜ ነበር። ሁለተኛ፥ በአውሮፓ አዶልፍ ሂትለርና ዮሴፍ ስታሊን መስኮብ ምስራቅ ፖላንድን የቦልቲክን አገሮችና ፊንላንድን ለመያዝ ጀርመን፥ መሀል አውሮፓን ለመያዝ በሚወስዱት እርምጃ አንዱ ሌላውን እንዳያሰናክል የምስጦር ውል ከተዋዋሉ

በሁዋላ ጀርመን ወዲያው ከስዊድን በቀር የሰሜንንና የመሀል አውሮፓን አገሮች የያዘበት ጊዜ ነበር። እንዲሁም ጀርመን ለርዳታ እፈረንሳይ አገር ገብቶ ይዋጋ የነበርውን የእግሊዝ ሰራዊት ድል አድርጎ ወደ አገሩ አባርሮ ያስወጣበትና የእንግሊዝ ራስዋ ፍታ ሳታገኝ በጀርመን ያዬር ሀይል በብርቱ ከመደብደብዋ የተነሳ የወደፊት ሁኔታዋ አጠራጣሪ የነበረበት ጊዜ ነበር። ሙሶሊኒም «ሲያመነታ ቆይቶ በመጨረሻ ኢጣሊያ የጀርመንና የጃፓን የጦር ባለቃልኪዳን ሆና እንድትገባ የወሰነ እኒያ ሁለቱ አገሮች (ጀርመን እና ጃፓን) ድል አድራጊዎች እንደሚሆኑ ርግጠኛ ስለሆነ የምርኮው ተካፋይ መሆን እንዳይቀርበት ከምርኮው ድርሻውን ለማግኘት ብሎ ነው » ይባል ስለ ነበረ ባጠቃላይ በዚያ ጊዜ የነበረው ሁኔታ «የአክሲስ መንግስታት » ይባሉ የነበሩትን (ጀርመን ጃፓን ኢጣሊያ) ድል የሚያደርጉ አስመስሎ የሚያሳይ ነበር። ስለዚህ ለኛ የነፃነት ተስፋችን ሞቶ ተቀብሮ በፍፁም ጨለማ ውስጥ እንኖር ለነበርን ኢትዮጵያውያን እስረኞች የኢጣሊያ እጦርነቱ ውስጥ መግባት ብቻ ያልታሰበ አዲስ ምዕራፍ ስለ ከፈተ ያ ሞቶ የነበረ ተስፋችን እንደ ገና ህይወት ያገኘ መስሎ ተሰምቶን ለጊዜው ደስ ቢለንም፥ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ደስታችን የሞቀና የደመቀ አልነበረም። ነገር ግን እያደር የጦርነቱን መልክ የለወጡ አዳዲስ ሁኔታዎች ስለ ደረሱ የኛም ተስፋ በዚያው መጠን ከቀድሞው እዬጠነከረ ይሄድ ጀመር።

በእንግሊዝ አገር ከጦርነቱ በፊትና በጦርነቱም ጊዜ፥ ጀርመን የእንግሊዝ የጦር ሰራዊት ድል አድርጎ ከፈረንሳይ አገር ሲይስወጣ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ኒቪል ቸምበርሊን ስልጣን ለቅቀው ሰርዊንስተር ቸርችል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ። ስለዚህ የቸርችል ጠቅላይ ሚኒስትር መሆንና ያሜሪካም የእንግሊዝ ተባባሪዎች የሆኑት መንግስታትም (ኮመንዌልዝ) እጦርነቱ ውስጥ መግባት የጦርነቱን መልክ ከለወጡት አይነተኞዎች ነበሩ። እንዲሁም «ጀነራል ቻርልስ ደጎል » ተሰደው እንግሊዝ አገር ከነበሩት «ነፃ ፈረንሳይ » ይባል ለነበረው ክፍልና ለፈረንሳይ የቅኝ ግዛት ህዝብ በሳቸው መሪነት ለነበረው ክፍልና ለፈረንሳይ የቅኝ ግዛት ህዝብ በሳቸው መሪነት ለነፃነቱ ትግል ታጥቆ እንዲነሳ ያደረጉት ጥሪ፥ በተለይ የፈረንሳይ ህዝብ ያገር ፍቅር ስሜት ቀስቅሶት ባጭር ጊዜ በቂ ሰራዊት በዙሪያቸው ለማስለፍ ችለው ነበር። ስለዚህ ያ

በጀነራል ደጎል ይመራ የነበረው የፈረንሳይ የጦር ሰራዊት በጠቅላላው ለነፃነቱ ጦርነት ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያደረገ መሆኑ በጊዜውም ከጦርነቱ በሁዋላም ይነገርለት ነበር።

«ሰር ዊንስተር ቸርችል » የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን ሲይዙ ያደረጉት ንግግር ጦርነቱ ወደ መጨረሻው የደረሰ መስሎዋቸው ከምርኮውም ከክብሩም ለመካፈል ሲሉ ጦርነት ለገቡት ለሙሶሊኒና በጣሊያን አገር የፋስሽትን ስራት ይደግፉ ለነበሩት ሁሉ እጅግ አሳሳቢና አስጊ የነበረ መሆኑ በግልፅ ይታይ ነበር። በንግግሩ ውስጥ ከሞላ ጎደል እንዲህ የሚል ነበረበት። «ጦርነቱ ምንም ያክል ረዥም ጊዜ ቢወድስ፥ ይህች አገራችን እንግሊዝም የምትያዝ ቢሆን እንኩዋ መንግስታችነን የእንግሊዝ ተባባሪዎች ከሆኑት አገሮች (ኮመንዌልዝ) ወደ አንዱ አዛውረን ትግላችነን እንቀጥላለን እንጂ የጦርነቱ ጊዜ ስለረዘመና አገራችን ስለ ተያዘች መጨረሻው አይሆንም። ለምንም ያክል የረዥም ጊዜ ጦርነት የሚብቃ ህዝብና የሚበቃ ሀብት ስላለን የጦርነቱ መጨረሻ «የአክሲስ » መንግስታት (ጀርመን ጃፓን ኢጣሊያ) ድል ሆነው የጦር ሀይላችን ሲደመሰስ ብቻ ነው! » ይህን የመሰለ ንግግር ለኛ፥ የጣመንን ያክል ወይም ከዚያ የበለጠ በችግር ላይ ለነበረው ለጣሊያን ህዝብ መራራ ነበር።

በተለይ ለኛ ለኢትዮጵያውያን እስረኞች ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችልና ያሜሪካው ፕሬዝደንት «ፍራንክሊን ዳላኖ ሮዝቬልት » አትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ በመርከብ ተገናኝተው ከተነጋገሩ በሁዋላ፥ ጦርነቱ ስለሚዋጉበት አላማ ያወጡት «አትላንቲክ ቻርተር » በተባለ ስም የታወቀ መግለጫ የነፃነት ተስፋችነን ከምንጊዜውም የበለጠ አጉልቶና አበርትቶ ደስታችነንም በዚያ መጠን አብዝቶት ነበር። የመግለጫው ፍሬ ነገር ሁለቱ ሀያላን መንግስታት (እንግሊዝና አሜሪካ) ተባባሪዎቻቸው ጭምር ጦርነቱን እስከ መጨረሻ የሚዋጉበት አላማ «የአክሲስ » መንግስታት (ጀርመን ጃፓን ኢጣሊያ) ድል አድርገው እኒያ ሶስት መንግስታት በሁለተኛው የአለም ጦርነት የያዙዋቸው አገሮች ሁሉ ሙሉ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ማድረግ እንጂ በኒያ ባጥቂዎች ቦታ

ተተከተው ቅኝ ግዛቶቻቸው ለማድረግ ፍፁም ሙላት የሌላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነበር።

ያን «የአትላንቲክ ቻርተን » መግለጫ ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ ራሳችነን ባካል ባይሆን በመንፈስ በግብር ባይሆን ባሳብ የአሜሪካ የእንግሊዝና የተባባሪዎቻቸው የጦር ባለ ቃልኪዳኖች አድርገን ቆጥረን በእስር ቢዒታችን እንዳለን የነፃነቱን ጦርነት አብረናቸው እንዋጋ ጀመር! ሲቀናቸው ደስታ ሳይቀናቸው ብስጭትና አዘን እንደነሱ እዬተፈራረቁብን የነፃነቱን ትል አብረናቸው እንታገል ጀመር!

ካንድ ወገን እንግሊዝ ተጠናክረው አሜሪካና የእንግሊዝ ተባባሪዎች (ኮመንዌልዝ) ተጨምረው የሚዋሉለትን አላማ ጥርት አድርገው ገልፀው ጦርነቱን ባዲስ መንፈስ መጀመራቸው ደስ ሲያሰኘን ከሌላ ወገን መስኮብ በጦርነቱ አለመግባቱ የሩቅ ተመልካች ሆኖ መቅረቱ ያናድደን ነበር። አሜሪካና እንግሊዝ ከተባባሪዎቻቸው ጋር፥ በአውሮፓ ጀርመንና ጣሊያንን ከፊት ሲወጉ መስኮብ ጀርመንን ከጀርባው የሚወጋው ቢሆኖ ኖሮ ድል አድራጊዎች መሆናችን የተረጋገጠ ከመሆኑ ሌላ የጦርነቱ መጨረሻም ይፋጠን እንደ ነበረ እናምን ነበር። ነገር ግን ከዚህ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው አዶልፍ ሂትለርና ዮሴፍ ስታሊን፥ መስኮብ ምስራቅ ፖላንድ የቦልቲክን አገሮችና ፊንላድን ለመያዝ ጀርመን መሀል አውሮፓን ለመያዝ ቀደም ብለው «መጥወኒ እመጥወከ » (አጉርሰኝ ላጉርስህ) ተባብለው የምስጢር ውል የተዋዋሉ በመሆናቸው ኮሚኒስት መስኮብ ሁለቱ ወገኖች ጠላቶቹ እስኪተላለቁ ያለዚያም እስኪዳከሙ ሲጠብቅ የሚቆይ መስሎ ታይቶን እንናደድ እናዝን ነበር።

አንድ ቀን አበበ ገብረ ፃድቅና እኔ ከፎቅ በረንዳችን ላይ እየተመላለስን ስናወራ፥ እታች ኮስሮፍ ከወደ አደባባዩ እዬሮጠ ወደኛ ሲመጣ፥ አይተን «ምን ሆኖዋል » ስንል እሱም ቀና ብሎ አዬንና፥ «ልጆች የምስራች! » አለ።

«ምስር ብላ! ምንድን ነው የምስራቹ? » አልሁ እኔ።

«ጀርመን መስኮብን ዩክሬንን ወረረ! »

«መቼ? »

«ትናንት »

አቤ - ት፥ ያ ጊዜ ደስታችን! «ያንዱ ቤት ሲቃጠል ለሌላው ብርሃንንና ሙቀትን ይሰጣል » እንደሚሉት አደል? ኮስሮፍ እኛ ዘንድ ሲደርስ ሁለታችንም እያቀፍን ስመነው፥ «በቃ፤ ድል አደረግን! ድል አደረግን! ያውም ነገ! » ተባብለን በደስታ እንዘል ጀመር። ብቻ ድሉ እንዳሰብነው የኛ መሆኑ እውን ቢሆንም የጦርነቱ መጨረሻ እንዳሰብነው «ነገ » ወይም ከነገ - ወዲያ አልሆነም፤ ረዢም ጊዜ ፈጀ። ጀርመን መስኮን የወረረበት እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር 1942 በጀነራል አይዘንሀወር ይመራ የነበረው ያሜሪካ የንግሊዝና የተባባሪዎቻቸው የጦር ሀይሎች የነበሩ ነፃ አውጪ ሰራዊት በሰሜን አፍሪካ ወርዶ ያለ ብርቱ ተቃውሞ ሰፊ ቦታ መያዙን ሰማን። ያነለት «እሰይ የድል በር ተከፈተ! » ብለን ደስታችን ቅጥ መጠን ያጣ ሆነ። ጀነራል አይዘንሀወር በአውሮፓ የጦር ግንባር የነፃ አውጪው ሰራዊት ጠቅላይ አዛዥ ነበሩ።

እኛም አብዛኛው የሎንጎቡኮ ህዝብም ራዲዮ ስላልነበረን ወሬውን መስማት የምንችል በከተማው ዋና አደባባይ የራዲዮ ማጉያ ስለ ነበረ ከቀኑ በሰባት ሰአት እዚያ የተሰበሰብን ነበር። ታዲያ እዚያ በጣሊያን ራዲዮ ሲነገር እንሰማው የነበረ ሁሉ የውሸት ፕሮፓጋንዳ ነበር። ጀርመን ጃፓንና ጣሊያን በየጦር ግንባሩ ይደረግ በነበረው ግጥሚያ የደረሰባቸው ጉዳት አይነገርም ነበር፤ አንዳንድ ጊዜ የሚነገረው ይህን ያክልም ከጉዳት ቁጥር የማይገባ ፈፅሞ «ጉዳት » ሊባል የማይችል ነበር። ያን ጊዜ የጣሊያን ራዲዮ እያጋነነ ይናገር የነበረ በዬጦር ግንባሩ ከመጠን ያለፈ ጉዳት የሚደርሰው ባሜሪካኖች በንግሊዞችና በተባባሪዎቻቸው ላይ መሆኑን ነበር። ካሜሪካ ከንግሊዝና ከተባባሪዎቻቸው በዬቀኑና በዬጦር ግንባሩ የሚወድቀው አይሮፕላን የሚደመሰሰው ታንክና የሚገድለው ወይም እስከ አለቆቹ የሚማረከው ወታደር የጣሊያን ራዲዮ እንደሚያወራው ቢሆን ኖሮ ሰራዊታቸውና መሳሪያቸው አልቀው በጥቂት ወራት እየጦርነቱ ፍፃሜ የሚህን ይመስል ነበር! ነገር ግን ጦርነቱ ይበልጥ እዬተፋፋመ ይቀጥል ነበር። ስለዚህ የጣሊያን

ራዲዮ፥ የጀርመንና የጣሊያን ሰራዊቶች የበረቱ፤ ያሜሪካ የንግሊዝና የተባባሪዎቻቸው ሰራዊቶች ወታደርና መሳሪያ አልቆባቸው የደከሙ አስመስሎ ያወራ የነበረው ምኞት እንጂ እውነት አለ መሆኑን አውቀን ወሬ በምንሰማበት አደባባይ እንደቆምን እኛ እስረኞች እስበሳችን እየተጠቃቀስን ያሹሙር ፈገግታ እንለዋወጥ ነበር። ታዲያ ለካስ ያን ሁኔታችንን ሁሉ ይመለከቱ ከነበሩት መሀከል አንዳንዶቹ እየሄዱ ለባለስልጣኖች ይነግሩብን ኖሮ ወደ አደባባይ እየሄድን ወሬ እንዳንሰማ ተከለከለን። እኛም አድራጎታችን የማይገባ መሆኑን ተረድተን፥ በሱ ተቆጥተውና ያገር ፍቅር ገፋፍቶዋቸው ለባለስልጣኖች የነገሩብንም የራዲዮን ወሬ ወደሚሰማበት አደባባይ እንዳንሄድ የወሰኑብን ባለስልጣኖችም ጥፋት እንዳልነበረባቸው ጥፋት የራሳችን እንደ ነበረ አምነን «እንዲያውም ሲያንሰን ነው! » ብለን ውሳኔውን በጥሞና ተቀብለን በወሬ ጊዜ እንኳዋንስ ወደ አደባባይ ልንሄድ ከቤት መውጣቱንም ተወን። ይሁን እንጂ ሙሶሊኒንና የፋሽስት ስራት ይጠሉ ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶቹ ካደባባይ ሲመለስ ወደኛ እየመጡ የሰሙትን ይነግሩን ስለ ነበረ ወደ አደባባይ እንዳንሄድ በመከልከላችን በየቀኑ በራዲዮ ይነገር የነበረው ወሬ ከሞላ ጎደል አያመልጠንም ነበር።

መቸም የውሸጥ ፕሮፓጋንዳ አልፎ አልፎ ባንዳንድ ተጨባጭ እውነት ካልተደገፈ ፕሮፓጋንዳ በሚነዛው ሰውም ሆነ መንግስት ትዝብትንና ንቀትን ማስከተሉ የማይቀር ነው። በጣሊያን መንግስት የደረሰውም ይህ ነበር። ጦርነቱ በሰሜን አፍሪካ እስከ ግብፅ ወሰን ሲደርስና በተለይ የነፃ አውጪው ሰራዊት ያዬር ሀይል የመሬት ውጊያ በሚደረግበት በሰሜን አፍሪካ ብቻ ሳይወስን ከዚያ አልፎ የጣሊያንን አገርም ጀርመኖች የያዙትን ምእራብ አውሮፓንም መደብደብ ሲጀምር እኛ በነበርንበት ክፍል እንደ ተመለከትነው፣ የጣሊያን ህዝብ መንግስቱ በራዲዮ ስለሚነዛው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ትዝብቱንና ንቀቱን በስውር ሳይሆን በግልፅ ማሰማት ጀመረ።

በኢትዮጵያ «ማሰሪያውን ቆርጦ የወጣ በቅሎ ሙብረር ታፍኖ የኖረ ሰው መናገር ከጀመረ በፊት አደጋ ቢኖር አይታዬውም! » እንደሚባለው የጣሊያን ህዝብ አፍኖት ይኖር የነበረው የፋሽስት ብርቱ ክድን ደከም ያለ ስለ መስለው እስከዚያ ጊዜ ድረስ በመንግስቱ ላይ መናገር ይቅርና መስማት እንኳዋ ይፈራ

የነበረው ነቀፋና ዘለፋ እስበሱ ሳይፈራራ በድፍረት መነጋገር የተለመደ ሆነ። በጦር ጉዋደኝነት ጣሊያን አገር የነበሩትን የጀርመን ወታደሮችም እንደ ጦር ጉዋደኞች ሳይሆኑ አገሩን ሊይዙበት እንደ መጡ የጠላት ወራሪ ወታደሮች ቆጥሮዋቸው በጥላቻ አይን የመለከታቸው ጀመር። ይህ ሁሉ በኢጣሊያን አገር ከዚያ በፊት ከነበረ ሁኔታ ፈፅሞ የተለየ ትልቅ ለውጥ ሆኖ ታይቶን፥ ቀኑ መቼ እንደሚሆን ባናውቅም ሙሶሊኒ የሚወድቅበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አምነን፥ ከሙሶሊኒ በሁዋላ በጣሊያን አገር የሚደረገው ለውጥ «በሬቮሉሽን ይሆን ወይስ በሰላም? » በሚለው ጥያቄ ላይ እስበሳችን እንከራከር ጀመር።

የጄነራል አይዘንሀወር ነፃ አውጪ ሰራዊት ሞሮኮን ቱኒስያንና አልጀሪያን አልፎ ሊቢያ መድረሱ እንደ ታወቀ ከዚያ ደቡቡ የጣሊያን ክፍል ሩቅ ስላል ሆነ «በቅርቡ ወደዚያ ክፍል ሳይሻገር አይቀርም? » እየተባለ ይወራ ጀመር። ወዲያው በዚያ ጊዜ ይወራ በነበረው ወሬ ምክንያት ይሁን ወይም በአጋጣሚ ክቡር ራስ እምሩና ልጅ ግርማቸው ተክለ ሀዋርያት ከሲሲሊ ሰሜን ሊፓሪ በሚባለው ደሴት ከነበሩት እኛ ወደ ምንኖርበት ወደ ሎንጎቡኮ እንዲዛወሩ ተደረገ። ነገር ግን ሎንጎቡኮ ከኛ ጋር ሳይሆን መንግስት የተለዩ ቤት ተከራይቶ ነበር ያስቀመጣቸው። ቢሆንም እንዳንገናኝ ስላልተከለልን እየተገናኘን በጠቅላላው ስለ ጦርነቱም በተለይ ስለ ሀገራችንም ለመወያየት ተመቸን።

ነፃ አውጪው ሰራዊት መጀመሪያ ሰሜን አፍሪካ ሲወርድ የገጠመው ተቃውሞ «እጅግ ብርቱ » የሚባል አልነበረም። ነገር ግን ጀርመናዊው ፊልድ ማርሻል ሮሜላ የጀርመንና የጣሊያን ሰራዊቶች ባንድነት አጠናክሮ እዬመራ የመከላከያ ጦርነት በመዋጋት ሳይወሰን የማጥቃት ጦርነትም መዋጋት ከጀመረ በሁዋላ ጦርነቱ በጣም ጠንክሮ እዚያው ሰሜን አፍሪካ ላይ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ሲመላለስ ዘጠኝ ወራት ያክል ቆዬ። ሮሜላ፥ የሚያስገርም ችሎታ የነበረው የጦር አዛዥ መሆኑን ጠላቶቹ ሁሉ ተስማምተው በአድንቆት ይመሰክሩለት ነበር። ከዚያ ጀነራል አይዘንሀወር ሰራዊት በማየሉ በሀምሌ ወር 1943 ከሰሜን አፍሪካ ተራምዶ በደቡብ ኢጣሊያ ሲሲሊ የተባለውን ክፍል መውረር ጀመረ። ከሌሎች የኢጣሊያ ክፍሎችም ብዙ ከተሞችን ባዬርና በጠረፍ ያሉትን በመርከብ መደብድቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ይሄድ ጀመር።

ያን ጊዜ ችግርና ጦርነት ተደራበው ያመረሩት የጣሊያን ህዝብ «ሰላም እንፈልጋለን፤ ከጦርነቱ እንውጣ! » እያለ እስከዚያ ድረስ ያደርገው እንደ ነበረ በማጉረምረም ሳይሆን ድምፁን ከፍ አድርጎ በየቦታው ማሰማት ጀመረ።

የሲሲሊ ጦርነት ብዙ አልቆየም። በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ደሴቱ በሙሉ በነፃ አውጪው ሰራዊት ተያዘ። ከዚያም ነፃ አውጪው ሰራዊት «የመሲናን የባህር ሰላጤ » ተሻግሮ ካላብርያንና ሌሎችን የደቡብ ኢጥሊያ ክፍሎች ለመውረር በመሰናዳት ላይ እንዳለ የኢጣሊያ ንጉስ ቪቶሪዮ አማኑኤል ሙሶሊኒ ስልጣኑ ለማርሻል ፔትሮ ባዶሊዮ እንዲያስረክቡ ማዘዛቸው በይፋ ተገለፀ። ስለዚህ በዚያው በሀምሌ ወር 1934 ሙሶሊኒ ስልጣኑን ለባዶሊ ለቅቆ፥ «ፓንዛ » በሚባል ደሴት በግዞት እንዲቆይ መደረጉን ሰማን። «ፓንዛ » ሙሶሊኒና የፋሽስትን ስራት ይቃወሙ የነበሩ ብዙ የፖለቲካ ሰዎች ፈላስፎችና ፀሀፊዎ በዞት ይኖሩበት የነበረ ቦታ ከመሆኑ ሌላ፥ አንባቢዎች በሌላ ምዕራፍ ያመለከትሁትን እንደሚያስታውሱት ክቡር ራስ እምሩ ክቡር ደጃዝማች ታዬ ልጅ ይልማ ደሬሳና እኔም መጀመሪያ በእረኝነት ወደ ጣሊያን አገር እንድሄድ እዚያው ፓንዛ ነበር የቆይነው። ስለዚህ የሙሶሊኒን በግዞት ወደ ፓንዛ መወሰድ ስንሰማ «ታሪክ አሽሙር ነው! » የሚባለውን ዘይቤ አስታውሰን ተገረምን።

«ማርሻል ባዶሊዮ ከሙሶሊኒ ስልጣን እንዲረከቡ የተደረገበት ዋና ምክንያት ህዝቡ ሰላም ስለ ፈለገ በተቻለ መጠን የኢጣሊያ ክብርም ጥቅምም የማይጎዳበት የእርቅ ስምምነት ከድል አድራጊዎች መንግስታት ጋር ለመነጋገር እንዲመች ነው » ሲባል ይሰማ ነበር። ነገር ግን ያ ሳይሆን ቀርቶ ባዶሊዮ ስልጣን በያዙ ባርባ ቀናት ውስጥ መስከረም 3 1934 ኢጣሊያ ድል መሆንዋን ተቀብላ ያለምንም ውለታ (ኮንዲሽን) እጅዋን ሰጠች። ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ነፃ የሆነች እንዲያውም ኢጣሊያ ድል ሆና እጅዋን ከመስጠትዋ በፊት በ1940 – 41 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933) ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ነፃነት ከኢጣሊያ ድል መሆን ጋር የተያያዘ መሆኑን እናምን ስለ ነበረ ያገራችን ነፃነት እውን መሆን ተቀብለን እስበሳችን «የምስራች! » እየተባባልን። ኢጣሊያ ድል ሆና እጅዋን መስጠትዋን በሰማ ጊዜ ነበር።

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

# ነፃነት

ኢጣሊያ እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር በመስከረም መጀመሪያ 1943 ላይ ድል መሆንዋን ተቀብላ እጅዋን ብትሰጥም በጣሊያን አገር ጦርነቱ አልቆመም፥ ይቀጥል ነበር። በዚያ ጊዜ ነፃ አውጪው ሰራዊት የያዘው ከደቡብ ኢጣሊያ ጥቂቱን ክፍል ብቻ ስለ ነበረና የሚበዛው የጣሊያን ክፍል ገና በጀርመን ሰራዊቱ እንደ ተያዘ ስለ ነበረ በዚያ የጀርመን ሰራዊት በያዘው ክፍል ብርቱ ጦርነት ይካሄድ ነበር። ዋናው ከተማ ሮም እንኳዋ በነፃ አውጪው ሰራዊት የተያዘ ኢጣሊያ እጅዋን ከሰጠች በሁዋላ ዘጠኝ ወራት ያክል ቆይቶ፥ በሰኔ ወር መጀመሪያ 1944 ነበር። ከዚያ በሁዋላም ቢሆን፥ በሰሜኑ የኢጣሊያ ክፍል በነፃ አውጪው ሰራዊትና በጀርመን ሰራዊት መሀከል ብርቱ ጦርነት እንደ ተካሄደ ነበር። እንዲያውም ነፃ አውጪው ሰራዊት በሰሜን ኢጣሊያ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ምእራብ አውሮፓን ወርሮ ጀርመን የያዛቸውን አገሮች ለማስለቀቅ አይነተኛውን የማጥቃት ጦርነት የጀመረ በዚያው በሰኔ ወር 1944 ነበር። ያሜሪካ የንግሊዝና የተባባሪዎቻቸው ሰራዊት ከምእራብ የመስኮብ ሰራዊት ከምስራቅ ሀይላቸውን አስተባብረው ጀርመንን መውጋት የጀመሩም በዚያ ጊዜ ነበር።

መቾም የምእራቡ ክፍል ነፃ አውጪ ሰራዊት መሰናዶውን፥ በንግሊዝ ሀገር ካጠናቀቀ በሁዋላ በስኔ መጀመሪያ 1944 ወራሪ ሰራዊቱን በፈረንሳይ አገር ለማወድ ያሰለፈው የመርከብና ያዬር ሀይል «ከዚያ በፊት በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅ » ይባላል። ከታች የጠላትን መከላከያ እየደመሰሰ ወታደሩን በፈረንሳይ መሬት ያወረደው መረከብ ብዛት ከ4000 በላይ ሲሆን እመሬት የወረደውን ወታደር ከጠላት አደጋ ለመጠበቅና ለመከላከል የፈረንሳይን ጠፈር እንደ ጉም የሸፈነው ያይሮፕላን ብዛት ከ3000

በላይ እንደ ነበረ ይናገራል። ከዚያ በሁዋላ ጦርነቱ በየቦታው ሁሉ ነፃ አውጪው ሰራዊት የማጥቃት ጀርመን የመከላከል ጦርነት የሚዋጉበት ሆነ።

ሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዴት እንደ ተነሳና እንደ ተፈፀመ በያንዳንዱ የጦርነት ቦታ ተፋላሚ ሀይሎች ምን ምን ያክል ሰራዊት አሰልፈው በምን አይነት መሳሪያ እንደ ተዋጉና በየቦታውስ ማን አሸናፊ ማን ተሸናፊ እንደ ሆነ በመጨረሻም ጦርነቱን ያነሱት ዲክቴተሮች ፍፃሜያቸው ምን እንደ ሆነ ይህን ሁሉ ለመረዳት የሁለተኛውን አለም ጦርነት ዝርዝር ታሪክ ማንበብ ያስፈልጋል። ነገር ግን እኔ ከዚህ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ከኢትዮጵያና ከኛ ከኢትዮጵያውያን እስረኞች ጋር የተዛመደውን ክፍል ብቻ ለማመልከት ያክል እንጂ በጠቅላላው የጦርነቱን ታሪክ ለመፃፍ አሳቡም አስፈላጊው ጠለቅ ያለ ጥናትም ስለሌለኝ እሱን ለታሪክ ፀሀፊዎች ትቼ እኛን እስረኞችን ወደሚከተለው ክፍል እመለሳለሁ።

አንድ ቀን እስረኞች በርከት በለን ከፎቅ በረንዳችን ላይ ተቀምጠን ስናወራ ቴዎድሮስ ወርቅነህ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ወደኛ ሲመጣ አየን። ወታደሮች የለበሱት መለዮ የጣሊያን አለመሆኑን ብናውቅም፥ የምን አገር መሆኑን ልናውቅ ሳላልቻልን «የምን ወታደሮች ይሆኑ? » እየተባባልን እስበሳችን ስንጠያየቅ እኛ ባለንበት ደረሱና ቴዎድሮስ አስተዋወቀን። የ ‹ካናዳ› ወታደሮች ነበሩ።

በመልእክት ላይ የነበሩ ጉዋደኞቻቸው ከኛ፥ በላይ በገደላማው ቦታ መኪና ተሰናክሎባቸው ከላካቸው የጦር ሰፈር ርዳታ እንደሚደርስላቸው በራዲዮ አመልክተው ኖሮ፥ እነሱን ለመርዳት የሚሄዱ ወታደሮች ነበሩ። ሎንጎቡኮ ሲደርሱ ቁርስ ቀምሰው ለማለፍ «ሮማና ሆቴል » ገብተው የፈለጉትን ለሆቴሉ አስተናጋጆች ለመንገር እነሱ ጣሊያንኛ የሆቴሉ አስተናጋጆች እንግሊዝኛ ባለማወቃቸው የመግባባት ችግር ስለ ተፈጠረ፥ ባጋጣሚ ቴዎድሮስ እዚያ ተገኝቶ በሱ አስተርጉዋሚነት የፈለጉት ቀርበላቸው እየተመገቡ ከቴዎድሮስ ጋር ሲጫወቱ ስለሱም ስለነሱም ማነንት በሰፊው ተነጋግረው ይተዋወቃሉ። ቴዎድሮስ እንግሊዞች ባፄ ቴዎድሮስ ላይ በዘመቱ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ - እጃቸውን ለጠላት ከመስጠት ራሳቸውን መግደል

መርጠው በገዛ መሳሪያቸው ህይወታቸውን ሲያሳልፉ አባቱን ሀኪም ወርቅነህን በሕፃንነታቸው ወስደው እያስተማሩ ካሳደጉዋቸው በሁዋላ ሀኪም ወርቅነህ ከእንግሊዛዊት እናት የወለዱት ስለ ነበረ በእንግሊዝኛ አነጋገሩት በመልኩም ልክ እንግሊዞችን ነበር የሚመስል።

ቁርሳቸውን እንደ ጨረሱ የካናድያኑ ሹም (የሙቶ አለቃ ነበር) ሶስት ወታደሮች አስከትሎ የቀሩትን ከመኪናዎቻቸው ጋር እዚያው ትትወ ከቴዎድሮስ ጋር እኛን ለማየት መጡ። ወዲያው፥ ወንበሮችን ከየክፍሉ ሰባስበን አስቀመጥናቸውና ስለኛም ስለነሱም መነጋገር ጀመርን። ቡና እንዲጠጡ ብንለምናቸው በችግር ላይ ለነበሩ ጉዋደኞቻቸው ለመድረስ መቸኮላቸውን ምክንያት አድርገው ግብዛችንን አልተቀበሉም። ቢሆንም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወርራ ከያዘችበት ከ1936 (በጎርጎርዮስ አቆጣጠር) ጀምሮ ከሰባት አመት በላይ በእስረኝነት ጣሊያን አገር የኖርን መሆናችንንና ኢጣሊያ ከሀገራችን ከወጣች በሁዋላም በሁለቱ አገሮች (በኢጣሊያና በኢትዮጵያ) መሀከል ግንኙነት ባለ መኖሩ በእስረኝነታችን እንዳለን መሆናችንን ስንነግራቸው በትእግስት ለማዳመት ያክል ጊዜ ሰጡን። ከዚያ እነሱ አባሎች የሆኑበት የነፃ አውጪው ሰራዊት ዋና መምሪያ «ባሪ » በሚባለው የወደብ ከተማ በመሆኑ ለርዳታ ከሚሄዱበት ቦታ እንደ ተመለሱ እኛ ስለምንገኝበት ሁኔታ የተረዱትን ለሰራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ ነግረው ባንድ ሳምንት ውስጥ ነፃ የሚያወታን ባለስልጣን እንደሚላክልን የሙቶ አለቃው የተጋረጠ ተስፋ ሰጠውን ሄዱ።

እድሜውን ሙሉ ታውሮ የኖረ ሰው «ነገ ትበራለህ » ቢሉት «ዛሬን እንዴት አድሬ? » አለ እንደሚባለው እኛም ከሰባት አመታት በላይ በእስረኝነት ኖረን «ባንድ ሳምንት ውስጥ ነፃ ትሆናላችሁ » ሲሉን ሳምንቱን በጣም ረዢም ቢጎቱት የማይደርስ መስሎ ታየን። ሁውላ ያ ሳምንት እንደ ምንም እያዘገመ ደረሰ ነፃ የሚያወጣን ባለስልጣን ግን አብሮ አልደረሰንም። ያን ጊዜ እንዴት ተሰቀቅን «ምነው እኒያን ካናዳውያን ባላገኘንና የነፃነትን ወሬ ባላሰሙን ኖሮ! » እያልን ማልካም ወሬ ያሰሙንን ሰውፐች ወቀስን! ታዲያ ካንድ ወገን ያ ስንመኘው የነበረው ነፃነት «ያዝነው ጊዜንና ያመለጠን መስሎን

ስናዝን ከሌላ ወገን ሰውና ሁኔታው ጊዜንና ጊዜ የሚወልዳቸውን አዳዲስ ሁኔታዎች ተከትለው የሚለዋወጡ መሆናቸውን ስንገረም እየተመለከትን ሰነበትን!

ኢጣሊያ ድል ሆና፥ እጅዋን ከሰጠች በሁዋላ በጣሊያን አገር ላስራ አንድ ወራት ያክል መንግስት አልነበረም። ሰሜኑ ክፍል የጀርመንና የነፃ አውጪው ሰራዊቶች የሚዋጉበት ደቡብ ክፍል በነፃ አውጪው ሰራዊት ቁጥጥር ስር ነበሩ። ስለዚህ የነፃ አውጪው ሰራዊት አካል የሆኑት ካናዳውያን ጉዞዋቸውን አቋዋርጠው ወደኛ መጥተው አነጋግርውን መሄዳቸው በሎንጎቡኮ ህዝብ መሀከል ሲታወቅ በእረኝነት በኖርንበት አገር እንደ እስረኞች መታየታችን ቀርቶ የነፃ አውጪው ሰራዊት ወገኖች ሆነን ታየን! ስለዚህ ወዳጅነታችንን የሚፈልገው ሰው በዝቶ ሰነበተ። ከህዝቡ መሀከል እንኩዋ - እስከምናውቀው ድረስ - እኛን በመልካም በክፉ አይን የሚያየን ፊቱንም ብዙም እንዳልነበረ እናምናለን። ከሹማምንቱ መሀከል ግን እንዳንቸገር ሊረዱን የሚሞክሩም ትናንሽ ምክንያቶችን እየተቆጣጠሩ ያስቸግሩን የነበሩም ነበሩዋቸው። ታዲያ እንዳንቸገር ያስቸግሩን የነበሩት ከበላይ የተሰጣቸው ትእዛዝ ወይም መመሪኢያ አስገድዶዋቸው የሰሩት አንዳንድ ስራ አሳዝኖን ሆነ «ይቅር » እንድንልና የነፃ አውጪው ሰራዊት ሹማምንት ቢመጡ በመልካም እንጂ በክፉ እንዳአስተዋውቃቸው ሲያስተባብሉን ሰነበቱ።

የካናዳ ወታደሮች ከሙቶ አለቃቸው ጋር አነጋግረውን ከሄዱ በሁዋላ በሶስተኛው ሳምንት ኢጋማሽ ግድም እስረኞች ሁሉ ከክቡር ራስ እምሩና ከልጅ ግርማቸው በቀር ወደ ከንቲባው መስሪያ ቤት ተጠርተን ስንደርስ አደባባዩን ብዙ ወታደሮችና ካሚዮኖች ሞልተውት አገኘን። እኒያ ወታደሮችና ካሚዮኖች ነፃ አውጪው ሰራዊት እኛን ነፃ ለማውጣት ከ«ባሪ » የላከቸው ነበሩ። እኛ ከመድረሳችን በፊት የወታደሮቹ አዛዥ እንግሊዛዊው ሻለቃ ክቡር ራስ እምሩ ወደ ነበሩበት ቤት ሄደው እሳቸውንም ልጅ ግርማቸውንም አነጋግረው መመለሳቸውን ሁዋላ ሰማን። ደጃዝማች (ሁዋላ ቢትወደድ) መንገሻ ውቤም እኛ ከነበርንበት ትንሽ ራቅ ባለ ቦታ ስለ ነበሩ፥ እዚያ አልነበሩም። ወደ ከንቲባው ፅህፈት ቤት ስንገባ እንግሊዛዊው ሻለቃ ዋናውን ቦታ ይዘው

በዙሪያቸው ከንቲባውና ሌሎች የዚያ አገር ሹማምንት ተቀምጠው ነበር። ሻለቃ ተነስተው ለሁላችንም የጅ ሰላምታ ሰጥተውን እስኪቀመጡ ድረስ፥ ከንቲባውም የዚያ አገር የፀጥታውና የፖሊሱ ሹማምንትም እኛን ለማስከበር ሳይሆን እንግሊዛዊውን መኮንን ለማጀብ አብረዋቸው ተነስተው ቆመው ቆዩ።

ከዚያ የንግሊዙ ሻለቃ እዚያ አገር በእስረኝነት ስንኖር በምግብ በልብስ በህክምና እጦትና በሌላ በማናቸውም ነገር የደረሰብን በደል ቢኖር እንድንናገር ጠየቁን። እኛም ከመግባታችን በፊት የምንጠይቀው ጥያቄ ቢኖር በሁላችን ስም ባላምባራስ እማኙ ይመር በቴዎድሮስ ወርቅነህ አስተርጉዋሚነት እንዲመለሱ ተስማምተን ስለ ነበረ፥ እሳቸው መልስ ሰጡ።

ባላምባራስ በሰጡት መልስ «እስረኞች እንደ መሆናችን ከቤት ወጥተውን የምንገባበት ጊዜና የምደርስበት ቦታ የተወሰኑ ከመሆናቸውና እንዲሁም በእስረኞች ሊደርሱ ከሚችሉ እንዳንድ ነገሮች በቀር የደረሰብን ልዩ በደል የለም። ለምግብ ለልብስ ለመድህኒትና በጠቅላላው ለሚያስፈልገን ሁሉ በየወሩ እንዲከፈለን ከተመደበው ገንዘብ ያለፈው ወር እስከ ዛሬ ባይከፈለንም ወደ ፊት እንደሚከፈለን ተስፋ ስለ ተሰጠን ችግር አልደረሰብን፤ እግዚአብሔር ይስጥል« ሲሉ እንደሚያበቁት ወቀሳው እንዳይመር በምስጋና አጣፍጠው ሻለቃውና ከንቲባው ሳቁ። ከንቲባው እንግሊዝኛ ማወቃቸውን ገና ያነለት ነበር ሁላችንም የተረዳን።

«እውነት ነው ገንዘብ ይላክልን ከነበረበት ቦታ ባንዳንድ ችግር ምክንያት ሳይላክልን ቆይቶ ስለ ነበረ ያለፈው ወር ከሚመጣው ወር ጋር ተጨምሮ የሚከፈል መሆኑን ነግረናቸው ነበር። አሁንም በሁለት ቀናት ውስጥ የሁለቱ ወራት ባንድ ላይ እንዲከፈላቸው እናደርጋለን » አሉ ከንቲባው።

«እንግዲህ የሁለቱ ወራት ገንዘባችሁ በሁለት ቀናት ውስጥ የሚከፈላችሁ መሆኑን ይሄው አሁን ከከንቲባው ስምታችሁዋል፤ ሌላም የጎደላችሁ ነገር መኖሩን አልነገራችሁን። ስለዚህ እዚህ የምትፈፅሙት ጉዳይ እንዳላችሁ ፈፅሙና ጉዋዛችሁን አሰናድታችሁ እንዳበቃችሁ ወደ «ባሪ » እንወስዳችሁዋለን፤ ከዚያም ወደ ሀገራችሁ ትሄዳላችሁ፤ እንኩዋን ከእስረኝነት ነፃ ለመሆን አበቃችሁ! » ብለው ሻለቃው እንደ ገና ተነስተው ለሁላችንም የጅ

ሰላምታ ሲሰጡን አብረዋቸው ተቀምጠው የነበሩት የጣሊያን ሹማምንትም ተነስተው «እንኳዋን ደስ ያላችሁ! » እያሉ የጅ ሰላምታ ሰጡንና እያመሰገን ተሰናብተን ወጣን። ከዚያ ጀምሮ ካሳሪዎቻችን ወደ ነፃ አውጭዎቻችን እጅ ተላለፍን። እስረኞች ሆነን በጣሊያን አገር ከሰባት አመታት በላይ ከኖርን በሁዋላ ነፃ ሆን!

የሎንጎቡኮ ከንቲባ፥ በንግሊዛዊው ሻለቃ ፊት በሰጡት ቃል መሰረት በሁለት ቀናት ውስጥ የሁለት ወራት ገንዘባችንን እንደ ሰጡት በየሱቁ የነበረንን «ዱቤ » ከፋፈልን ከእንዳችንም ነፃ ሆነን። ከዚያ የምንይዘውን እቃ (ልብስና መፃህፍት) እያሰናዳን ሶስት ቀናት ያክል ሎንጎቡኮ ስንቆይ ከእቃ ማሰናዳቱ በተረፈ ጊዜ ባካባቢያችን አይተናቸው የማናውቀውን የሚያማምሩ ተራራዎችና ጫካዎች ከንግሊዝ ወታደሮች ጋር ሆነን እንደ አገር ጉብኝዎች እየዞርን ስናይ ሰነበትን። ከዚያም እቃችንን በካሚዮኖች አስጭነን፥ በጠላት አገርም ወዳጆች ስለ ማይጠፉ ከወዳጆቻችን ጋር ተሰነባብተን ተነሳን። ደጃዝማች መንገሻ ወቤ አቶ በህርነ ሀብተ ሚካኤልና ጠባቂያችን የነበሩት ሹምባሽ ገብረ ፃድቅ ለጊዜው እዚያው ቆዩ። ሌሎች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥቅምት ወር መጨረሻ 1936 አካባቢ ክቡር ራስ እምሩ ከእግንሊዛዊው መኮንን ጋር በኦቶመቢል የቀረ ነው ሁላችንም ከእቃችን ጋር በካሚዮኖች ተሳፍረን ከሎንጎቡኮ በዚያ ክፍል የነፃ አውጪው ሰራዊት ዋና ሰፈር ወደ ነበረው ወደ «ባሪ » ተጉዋዝን። ሹምባሽ ገብረ ፃድቅ ሎንጉቦኮ የቀሩበት ምክንያት ድሮውንም እዚያ የነበሩ እስረኞችን የጣሊያን መንግስት ስላዘዛቸው እንጂ ራሳቸው እስረኛ ስላልነበሩ ነው። ደጃዝማች መንገሻ ውቤና አቶ ብርሃነ ሀብተ ሚካኤል ከኛ ተለይተው ሎንጎቡኮ የቆዩበትን ትክክለኛ ምክንያት ግን እኔ አላወቅሁትም።

ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ ከተያዘች በሁዋላ እንደ ገና ነፃ መሆንዋና እኛም በኢትዮጵያ ነፃነት ምክንያት ከኛ በፊት ጠላቶቻችን ምህረት እያደረጉላቸው አገራቸው እንደ ገቡት ጉዋደኞቻችን ሳይሆን እነሱ (ጠላቶቻችን) ድል ተመትተው በሙሉ ነፃነት ወደ አገራችን ለመግባት በመሰናዳት ላይ መሆናችን እንደ ታምር ሆኖ ነበር የታየን! መቸም ታምር

ማለት ያስተሳስብን ስነ ስራት ተከትሎ ይሆናል የተባለው ሳይሆን ሲቀር «አይሆንም » የተባለው ሆኖ ሲገኝ ነው። የኢትዮጵያን የኛ ነፃት መሆንም አያስተሳስብን ስነ ስራት ተከትሎ ለተመለከተው «ሊሆን ይችላል » የማይባ ነበር።

በየጦር ግንባሩ ተሰልፎ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ድል ተመትቶ ጠፍቶ እንደ ቀደሙት ነገስታት የክፍላተ ሀገሩን ህዝብ አስተባብረው እየመሩ ጠላትን መቁዋቁዋም ይችሉ የነበሩት ንጉሰ ነገስቱ አገራቸውን ትተው ተሰደው በየጫካው ተበታትነው ይገኙ ከነበሩት አርበኞች በቀር፥ በብሄራዊ ደረጃ የተደራጀ አንዳች ሀይል ባልነበረበት ፋሽስት ኢጣሊያ ትዮጵያን ከያዘች በሁዋላ እስዋን (ኢጣሊያ) አስወጥቶ ኢትዮጵያን እንደ ገና ነፃ የሚያደርግ ሀይል ይገኛል ማለ ከማንም አሳብ የራቀ ነበር። ለኛ ለእስረኞችም ቢሆን ሁለተኛው የአለም ጦርነት ከመነሳቱ በፊት ተስፋችን ከስረኝነት ወጥተን፥ ወደ ሀገራችን ተመልሰን ቢቻል ወደ ሌላ አገር ማምለጥ፥ ካልተቻለ እዚያው ፋሽስት ኢጣሊኢያ የጫነችብንን የባርነት ቀንበር ከወገኖቻችን ጋር ተሸክሞ ለመኖር ካልሆነ በቀር ነፃነት የምንመኘው ምኞት ወይም የምናልመው ህልም እንጂ «እናገኘው ይሆናል » ብለን ተስፋ የምናደርገው አልነበረም። እንገር ግን እኛ ሳናስበው ሁለተኛው የአለም ጦርነት ተነስቶ ኢጣሊያ በመጨረሻ ሄዳ ድል ከተመቱት መንግስታት ወገን ተሰልፋ ስለ ተገኘች ቅኝ ግዛቶችዋን እንድትለቅ በመንገድዋ ኢትዮጵያ ነፃ ሆነች! እኛም ህልማችን እውን ሆኖ ነፃ ሆነ! «ደስታ ቀሊል » ያባቶች ብሂል ነው! መልካም ትልቅ ነገር ሁሉ ሲጠፋ የሚከብደውን ያክል ሲገኝ ደስታው ብዙ ጊዜ አብሮ የማይቆይ ቀላል ይሆናል። «ደስታ ቀሊል!! »

እኛ በእረኝነት እንዳለን ሌሎች ጉዋደኞቻችን በየጊዜው «የጣሊያ መንግስት ምህረት አድርጎላችሁዋል » እየተባለ ወደ ሀገራቸው በገቡ ቁጥር ተለይተን በመቅረታችን እናዝን ነበር። ነገር ግን ሁለተኛው የአለም ጦርነት ተነስቶ፥ የአሜሪካን የንግሊዝ መንግስታት ከተባባሪዎቻቸው ጋር ጦርነቱን የሚዋጉበትን አላማ «አትላንቲ ቻርተር » በተባለው ማስታወቂያ ካስታወቁ በሁዋላ አሳባችንን ለወጥን። በዚያ ማስታወቂያ የሚዋጉበት አላማ «የአክሲስ

» መንግስታት (ጀርመን ጃፓን ኢጣሊያ) በጦርነት የያዙዋቸውን አገሮች ሁሉ ነስጻ እንዲወጡ ማድረግ መሆኑን ከገለፀበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ብየ እንዳመለከትሁት እኛም ራሳችንን የነሱ (የነፃ አውጪዎች) ባለ ቃልኪዳኖች አድድርገን ቆጥረን በአካል ባይሆን በንመፈስ በግብር ባይሆን በአሳብ ጦርነቱን አብረናቸው እንዋጋ ነበር! ስለዚህ ጠላቶቻችን ድል ተመትተው ከእስረኝነታችን ነፃ ስንወጣ «እንኩዋንም እስረኞች እንደሆን ቆየን! እንኩዋንም በጠላቶቻችን ምህረት ሳይሆን እነሱ ድል ተመትተው በኛ አሸናፊነት ነፃ ወጣን! » ብለን ደስታችን እጥፍ ድርብ ሆነ! እውነትስ ነፃነትን የቀማ ጠላት ወድዶ ሳይሆን ተገድዶ ራርቶ ሳይሆን ድል ተመትቶ የቀማውን ነፃነት ሲመልስ ደስታን እጥፍ ድርብ የሚያደርግ አደለም? ነፃነት የቀማ ጠላት ባሸናፊነቱ ኮርቶ በንቀት ቁልቁል እያዬ «ምህረት እድርጌላችሁዋለሁ! » ከሚል ድል ተመትቶ ተንበርክኮ ሽቅብ እያዬ የደስታ ሁሉ ቁንጭላላት የሚያደርግ ነው! ይህን የምልም በበቀል መንፈስ አለመሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ሁልጊዜም ቢሆን ከበደለኛ ቅጣት እንጂ ምህረት አደለም የሚፈልገው! የበደል መካሱ እንጂ ዳረጎት ማጉረሱ የተበደሉትን ክብር አይመስልም! ተበድለው ተደብድበው እንኩዋ ዳረጎት ሲያደርጉባቸው ደስ የሚላቸው ውሾች እንጂ ሰዎች አይደሉም! ስለዚህ ሰዎች እንደ መሆናችን ጠላቶቻችን ራርተው በችሮታ ሳይሆን ድል ተመትተው በግዴታ በጌትነታቸው ዳረጎት ከሚያጎርሱን ተገደው ነፃነታችንን በመመለስ እንደ አቻዎች ሲክሱን ይህ ሁሉ ሲሆን ነፃነታችንን በመመለስ እንደ አቻዎች ሲክሱን ይህ ሁሉ ሲሆን ማየቱ ተገፍፈን የነበረው የሰውነት ክብራችን ተቀምጠን የነበረው ነፃነታችን ለመመለሱ ማረጋገጫ በመሆኑ የፋሽስቶች ድል መሆንና በዚያ ምክንያት «ያለውድ በግድ ያደርጉት የነበረው ሁሉ ደስታችንን የደስታ ቁንጭላላት አደረገው! » ያልሁ በዚህ መንፈሴ እንጂ በበቀል መንፈስ አደለም።

ከሎንጎቡኮ ተነስተን ባሪ እንደ ደረሰን እዚያ የክፍሉ ነፃ አውጪ ሰራዊት አዛዥና መኰዋንንታቸው ባንድ ትልቅ ሆቴል ድል የተመታችዋ የጣሊያን የጦር መኰዋንንት ባጠገቡ በሌላ ሆቴል እንደ ሚኖሩ ሰማን። የጣሊያን የጦር መኰዋንንት ቡናና ሌላ መጠጥ በሚጠጣበት አደራሽ ለመግባት

ቢፈቀድላቸውም የነፃ አውጪው ሰራዊት የጦር መኰዋንንት በሚኖሩበት ሆቴል ለመኖር ያልተፈቀደላቸው መሆኑንም ሰማን። ለኛ ግን የነፃ አውጪው ሰራዊት መኰዋንንት በነበሩበት ሆቴል ቦታ ተሰጥቶን እዚያ አረፍን። አመሻሹ ላይ አራት ወይም አምስት የምንሆን ኢትዮጵያውያን ቡና ለመጠጣት ወደ አዳራሹ ወርደን ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን። ከኛ ትንሽ ፈቀቅ ብሎ በነበረ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ልዩ ልዩ መጠጥ እየጠጡ የሚጫወቱ ሰዎችም ነበሩ። አሳላፊው መጥቶ ቡና እስክናዝዝ በመጠበቅ ላይ እንዳለ እኒያ ሰዎች እኛን እየተመለከቱ ሲነጋገሩ ቆዩና ከመሀከላቸው አንድ ትልቅ የጦር መኮንን ከተቀመጡበት ድንገት ብድግ ብለው እኛን እየተገላመጡ እያዩ እንደሚሸሽ ሰው ፈጠን ፈጠን ብለው ወጡ።

መኮንኑ የሸሹበትና እኛን እየገላመጡ፥ ያዩበት የነበረው ሁኔታ የተመልካችን አይን የሚጠራ ስለ ነበረ ሁላችንም ወደሳቸው ማየት ስንጀምር «ጀነራል ናዚ! ጀኔራል ናዚ! » አሉ ከመሀከላችን ጀኔራል ናዚ ናዚን አዲስ አበባ ያወቋቸው የነበሩት እየተቀባበሉ። ጀኔራል ናዚ፥ የጣሊያን እንደራሴ፥ ምክትል ወይም ዋና ባለስልጣን ሆነው ኢትዮጵያ በሰሩበት ጊዜ የፖለቲካም በጦርም ያመራር ችሎታቸው በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፥ ከሌሎች ፋሽስቶች የተሻለ ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸው ሰው ነበሩ። ታዲያ ያነለት «ያባረሩዋቸው ይመስል ያን ያክል የሸሹ ምናልባት እንዲያ እክፍ ብለው ይታይና ይከበሩ በነበሩበት አገር ሰዎች በኢትዮጵያውያን ፊት ምርኮኛ ሆነው መታየቱ አሳፍሮዋቸው ይሆናል! » ብለን ገምተን ከመሀከላችን አንዳንዶቹ ሲያዝኑላቸው ሌሎች «እንኩዋን እግዚአብሔር ይህን ለማየት አበቃን! » እያሉ ደስታቸውን ገለፁ። ወዲያው ደስታቸውን ከገለፁት አንዱ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ነገሩን።

«ላይኞቹ ሲወርዱ ታችኞች ሲወጡ፥
የሚጫወቱበት ቦታ እየተለወቱ፥
ይህ ነው ላስተዋለው የዚህ አለም ነገር፤
ቦታውን ሳይለውጥ በላይ እንደ ሆነ ዘላለም የሚኖር

ከቶ ምንም የለ፥ ከፈጣሪው በቀር »

ባሪ በቆየንባቸው ጥቂት ቀናት ቴዎድሮስ ወርቅነህ እንግሊዝኛ ጣሊያንኛ አዋቂ በመሆኑ እንግሊዞችን እየረዳ ጣሊያን አገር ለመቆየት ፈቃደኛ እንደ ሆነ ተጠይቆ ስለ ፈቀደ ከኛ ተለይቶ ከእንግሊዞች ጋር እንዲቆይ ተደረገ። ሁዋላ ግን ከስንት ወራት በሁዋላ መሆኑን አላስታውስም እንጂ እሱም ሎንጎቡኮ የቀሩትንም እንደኛ አገራቸው ገቡ።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ሐዲስ ዓለማየሁ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት በደብረማርቆስ አውራጃ ከየኔታ ዓለማየሁ ሰለሞን እና ከወ/ሮ ደስታ ዓለሙ ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም. የተወለዱ ሲሆን፥ ለቤተሰባቸው ብቸኛ ልጅ ናቸው።

ሀዲስ እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ በቤተሰባቸው አጠገብ እና በአባታቸው ሀገር ደብረ ኤልያስ ሄደው ከባህላዊ የግዕዝ ት/ቤት ዜማ ተምረዋል፥ቅኔ ተቀኝተዋል።

በ1918 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ የመጡት ሀዲስ፥በዚያው አመት በተፈሪ መኮንን ት/ቤት ዘመናዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ በአዲስ አበባ በመምህርነት በጎጃም በጉምሩክ ሥራ ባለሙያነት ሠርተዋለል።

በኢጣሊያ ወረራ ወቅት 1929-1933 ዓ.ም. ከልዑል ራስ አምኃ ኃ/ስላሴ ጦር ጋር በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው በምእራብ ኢትዮድያ በጣሊያን ተማርከው፥ ወደ ኢጣሊያ በግዞት ከቆዩ በኋላ በ1936 ዓ.ም. ወደ ሀገራቸው በነፃነት ተመልሰዋል።

ከነፃነት በኋላ ዘመናዊት ኢትዮድያን ለማደራጀት በተደረገው ትግል በማስታወቂያ ሚኒስቴር 1936፥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር - በኢየሩሳሌም 1937-1939 እና በተ.መ. ድ 1939-1946፥ በእንግሊዝ 1948፥ እንደገና በተ.መ. ድ 1949-1953 ሀገራቸውን በአምባሳደርነት ያገለገሉ ሲሆን በዚሁ "ወርቃማ" የሥራ ዘመናቸው በመዲናችን አዲስ አበባ- የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ECA እንዲመሰረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደጉ ክቡር ኢትዮድያዊ ናቸው።

ከ1953 ዓ.ም. የታኅሣሡ መፈንቅለ መነግስት ሙከራ በኋላ እስከ 1961 ዓ.ም. ድረስ በሚኒስትርነት ማእረግ በሚኒስትሮች ም/ቤት የመማክርት ጉባኤ አባል፥ ከ1961 - እስከ 1966 ድረስ በሀገሪቱ ፓርላማ የህግ መወሰኛ ም/ቤት አባል ከ1966 ጎጃም ሕዝብ በመረጣቸው መሰረት የብሄራዊ ሸንጎ አባል 1966-1968 ሆነው ያገለገሉ ሀዲስ ዓለማየሁ "ኢትዮድያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?" 1966 በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ሀገራቸው ያላቸውን የመልካም አስተዳደር ራእይ ተመልክቶ ደርግ የሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር ሆነው እንዲሰሩ ጠይቋቸው አለመቀበላቸው ተነግሯል።

ሀዲስ አለማየሁ በ1929 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ካዘጋጁዋት "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ" በኩር የተውኔት ድርሰታቸው ፋቡላ አንስቶ "ተረትተረት የመሰረት" 1948 "ፍቅር እስከመቃብር" 1958፥ ወንጀለኛው ዳኛ 1974፥ "የልምዣት" 1980 በተሰኙት የረዥም ልቦለድ ሥራዎቻቸው ያልታተሙ ድርሰቶችም አሏቸው የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሥነጽሑፍ በአያሌው የታደጉ "የቀለም ሰው" ናቸው።

ሀዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" በተሰኘው የአማርኛ ረዥም ልቦለድ ሥራቸው "ለኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ አዲስ ምእራፍ ከፋች!" የሚል ሞገስ ያገኙ ሲሆን፥ በዚሁ ኪናዊ ሥራቸውም ፋሽስት ኢጣሊያ ከወጣ በኋላ ብዚዎቹ ኢትዮጵያውያን ደራስያን ያላተኮሩበትን የፊውዳል ኢትዮጵያን ገፅታ በተለየ ትኩረት በስፋትና በጥልቀት በመዳሰስ ኪናዊ በሆነ የቋንቋ ኃይልና ውበት የገለጹ፥ በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ ያመፁ እንደ ጉዱ ካሣ፥ በዛብህ፥ ሰብለወንጌል፥ አበጀን የመሳሰሉ ሕይዋን ገፀባሕርያት በመሳል - በለውጥ የትግል መንፈስ ላይ ለነበረው አዲስ ትውልድ ሀዲስ ራዕያቸውን በጥበብ አጋርተዋል።

በአጻጻፍ ብልሃቱ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ አዲስ ፈር በቀደደው የ"ፍቅር እስከ መቃብር" ድርሰታቸው በሁለት የውጭ ቋንቋዎች ተተርጉሟል "አዲስ ዓለም አሳየን!" የሚል ሞገስ ያገኙት ሀዲስ ዓለማየሁ በ1960 ዓ.ም የቀ.ኃ.ሥ. ሽልማት ክብር በሥነጽሁፍ ነሐሴ 27 ቀን 1991 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ጽሑፍ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል።

"ትዝታ" 1985 በሚለው ግለ ታሪካቸው ሰብዕናቸውን የተረኩልን ታረክ ፀሐፊ፥ አርበኛ መምህር፥ አምባሳደር፥ ሚኒስትርና የሥነ ጽሑፍ ጠቢብ ሃዲስ ዓለማየሁ "የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ አባት!" የሚል የሀያስያንና የሕዝብ ሞገስ አግኝተው ኅዳር 28 ቀን 1996 ዓ.ም. በ94 ዓመታቸው አረፉ።

## <u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ፍቅር እስከመቃብር **(ልብወለድ)**
2. ትዝታ**(ታሪክ)**
3. ወንጀለኛው ዳኛ **(ልብወለድ)**
4. የሕልም እዣት **(ልብወለድ)**
5. ተረት ተረት የመሰረት **(ወግ)**

6. የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም **(ትምህርት)**
7. ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ **(ተውኔት)**
8. ኢትዮጵያ ምን ዐይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል? **(ታሪክ)**

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY